ሰቈቃወ ኤርምያስ

መግቢያ

1. ዳራ

ሰቈቃወ ኤርምያስ ዐምስት የልቅሶ ግጥሞች የያዘ ሲሆን፣ ከሦስተኛው ግጥም በቀር ሌሎቹ ሁሉ መነሻቸው ከለዳውያን በ578 ዓ/ክ በኢየሩሳሌም ላይ ያደረሱት ውድመትና ያስከተለው ጥፋት ናቸው። የኢየሩሳሌም መፈራረስ በመጽሐፉ በግልጽ ፍንትው ተደርጎ በመግለጹ፣ ጸሓፊው የዐይን ምስክር መሆኑን ይጠቁመናል። ጸሓፊው በሌሎች የይሁዳ ክፍሎች ስለ ደረሰው ጕዳት የሚያውቅ ቢሆንም፣ አትኩሮቱ ግን ኢየሩሳሌም ላይ ነበር።

2. ጸሓፊ

በዕብራይስጥ የመጽሐፉ ጸሓፊ አልተነገረም (ሰፕቱጀንት፡- የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም በመክፈቻ ጥቅሱ ጸሓፊው ኤርምያስ እንደ ሆነ ይገልጻል)። ጸሓፊው ኤርምያስ ለመሆኑና ላለመሆኑ የሚቀርቡ የመከራከሪያ ነጥቦች በእኩል አሳማኝነት ተሰንዝረዋል። ስለዚህም መንፈስ ቅዱስ የጸሓፊውን ስም በመሰወር ያኖረውን ማኅተም ማክበር ይገባናል። ኤርምያስ እንደጻፈው የሚቀርበው መከራከሪያ ባመዛኙ መነሻው በግጥሞቹ ከተንጸባረቀው ስሜት ጋር የሚዛመድ ነው። ከኤርምያስ ጋር ነገረ መለኮታዊ ተመሳሳይነት አላቸው ቢባልም እንኳ፣ ይህ ምስክል የኤርምያስን ትምህርትና በጠቅላላውም የዐበይት ነቢያቱን ትምህርት ከሚቀበል ማንኛውም ሰው የሚጠበቅ ነው።

3. የተጻፈበት ጊዜ

ዐምስቱ የልቅሶ ግጥሞች ከ586-538 ዓ/ክ ባለው ጊዜ መጻፋቸውን የሚጠራጠሩ አታኞች ስላለመኖራቸው በርግጠኝነት መናገር ይቻላል። እንዲያውም በግጥሞቹ ብሔራዊ ተስፋ ያለመንጸባረቁ ከ562 ዓ/ክ በፊት እንደ ተጠናቀቀ ያመለክታል፤ ምክንያቱም በዚህ ዓመት የዮአኪን ከእስር መፈታት (2ነገ25፥27-30)፣ ኤርምያስ የተናገራቸው የተስፋ ቃላት እንደሚፈጸሙ የሚያበስር ነበር። በምዕራፍ 3 ላይ፣ ይህ ተስፋ ለምድሪቷ ሳይሆን ለግለሰብ ሲገለጽ ይታያል፤ ይሁን እንጂ ጥቃት ያደረሱት ምድሮች ራሳቸው በጽዮን ላይ የወረደው ፍርድ እንደማይቀርላቸው ከሚናገሩ ክፍሎች በቀር ይህ ነው የሚባል ብሔራዊ ተስፋ ሲንጸባረቅ አይታይም።

4. ዐላማ

በዐምስተኛው ወር ሰባተኛ ቀን የቤተመቅደሱ መፈራረስ (2ነገ 25፥8-9) በዓመታዊ ጾም ይዘከር እንደ ነበር በዘካ 7፥3፡ 5፤8፥19 እናነባለን። (በሁለተኛው ዓመተ ምሕረት የዝክሩ ቀን ከሰባተኛ ወደ ዘጠነኛ ቀን ተዛውሮ ከዚያ ወዲህ አይሁድ መቅደሱ የፈረሰባቸውን ሁለት ጊዜያትና እንደዚሁም በ135 ዓ.ም. የተካሄደውን የባር ኮችባ የዐመፅ ሙከራ መቀጨት ከመጀመሪያውኑ በተገቢው ሁኔታ ጾምን በማወጅ በመቅደሱ ፍርስራሾች መካከል ይከበር እንደ ነበር ርግጠኛ መሆን ይቻላል።) (ይህንን እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች ወደመቅደሱ ሄደው የሚገባውን ሥርዓት መፈጸማቸው ዋነኛ ዓላማ እንደ ነበር ከሚነግረን ከኤር 41፥5 ጋር ያነጻጽሩ)። ገና ከትውልዱ ጅማሬ አንሥቶ፣ ሰቈቃወ ኤርምያስ በዐምስተኛው ወር ዘጠነኛ ቀን ይነበብ ነበር፤ ስለዚህም ገና ከጅምሩ ለዚህ ዐላማ የታቀደ እንደ ሆነ መገመቱ የሚያስዜድ ይመስላል።

ይሁን እንጂ ሰቈቃወ ኤርምያስ የተጻፈበት የወዲያው (ወቅታዊ) ዐላማ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ለመካተቱ በቂ ማብራሪያ አይሰጠንም፤ ምክንያቱም ሌላው ቢቀር ለክርስቲያን አንባቢ ከታሪካዊ ወይም ከጥንት ማስታወሻነት የዘለለ ፋይዳ ያለው አይመስልም። መጽሐፍ ቅዱስ ልብን የሚሰብር ሐዘንን ጨምሮ የሰው ልጅ ውጣ ውረዶችንና አጋጣሚዎችን ሁሉ ያካተተ መጽሐፍ ነው። የዚህ ዐይነቱ ሐዘን በግለሰብ ላይ (ለምሳሌ፣ በኢዮብ) ወይም በጥቅሉ በአገሪቱ ላይ ሊመጣ ይችላል። ሰዎች በዚህ ጭንቅና ምጥ ውስጥ በሚያልፉበት ጊዜ፣ ሌላው ይቅርና የመጽሐፍ ቅዱስ አጽናኝ ቃላት እንኳ ቀንበሩን የማያለዝበውንና የብርሃን ጮራ የማይፈነጥቁበት ጊዜ አለ። ኤርምያስ የባቢሎናውያን ግዛት እንደማይቀጥልና የጊዜ ልክ እንዳለው (ኤር 25፥11-12) እና የብሔራዊ መታደስ ዘመን ተስፋ መኖሩን ቢያመለክትም (ምዕ 30-31)፣ በሕይወት የተረፉት ልባቸው በመዛሉ እኒህ የተስፋ ቃላት እምብዛም አላስደሰታቸውም። በወንጌልም ዘመን እንኳ ይህ ዐይነቱ ነገር ዐልፎ ዐልፎ ይከሠታል፤ ይህ የሚገጥማቸው ሰዎች እነዚህን የልቅሶ ግጥሞች ሲያነቡ፣ ዳግመኛ የፀሓይ ብርሃን ባለበት ዳርቻ ከመድረሳቸው አስቀድሞ በዚህ ዐይነቱ ውድቀት ጨለማ ለማለፍ የመጀመሪያዎቹ እንዳልሆኑ ይገነዘባሉ። የጨለማውን ዘመን ተሻግረው ሲያልፉት፣ እንባቸውን በመጽሐፉ መዝገብ ያኖረ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ (መዝ 56፥8)።

በአሁኑ ዘመን ይህን መጽሐፍ የሚያነቡ ሰዎች፣ በመጽሐፉ የተገለጸው ሰቈቃ መሪርነት ሊያስገርማቸውና አይሁድ ናቡከደነፆር በምድራቸው ላይ የዋለውን ግፍ እስካሁን መዘከራቸው እንቆቅልሽ ሊሆንባቸው ይችላል። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ የውድመቱና የጥፋቱ ልክ ምን ያህል እንደ ሆነ ለማሰብ ይቸግረናል።

አሮጌዪቱ የዳዊት ከተማ የምትገኘው ከአሁኑ የከተማ ቅጥሮች ውጪ ነው። በከፊል ለዚህ ምክንያቱ ሮማውያን ያደረሱት ውድመት ውጤቶች ናቸው። ከለዳውያን የኢያቡሳውያንንና የዳዊትን ቅጥሮችና ግንቦች ፈጽመው በማፈራረሳቸው ዕድሳት የሚታሰብ አልነበረም፤ ነህምያ ቅጥሩን መልሶ ሲሠራ ዐቀበቱ ላይ ከፍ አድርጎ ሠርቶት ስለ ነበር የቀድሞው የከተማዪቱ ክልል እንዲቀንስ ምክንያት ሆነ። ሕዝቡ ከምርኮ ሲመለሱ ሙሉ በሙሉ እንደ ዐዲስ መጀመር ነበረባቸው። በዚህ መልኩ ስናየው፣ ሰቈቃወ ኤርምያስ አይሁድ ላይመለስ የተሰደቸውን የቀድሞ ዘመን ክብር እያሰቡ ሐዘን የሚቀመጡበት ሙሾ ነው።

5. ሥነ ጽሑፋዊ ዘይቤ

ምዕራፍ 5 ሃያ ሁለት ጥቅሶችን ያካተተ የተለመደ የዕብራይስጥ ግጥም ነው። ያልተመጣጠኑ (3+2) ቀለሞችን ያካተተ ረዥም ስንኝ ሲኖረው፣ የዕብራይስጥ ግጥም ዋና ገጽታ የሆነው አቻዊነት ብዙም አይታይበትም። ይህ ግጥም በርግጠኝነት የሞቱትን ለማወደስ በቃል የሚወረድ ሙሾ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል ነው። በምዕራፍ 1-4 ከስንኞቹ በርካቶቹ የዚህ ዐይነት መልክ ሲኖራቸው፣ የተለየ አካሄድ የሚከተሉት ስንኞች ብዙ በመሆናቸው፣ እንዲሁ ደንብ በማክበር ብቻ ጥቅም ላይ እንደማይውል ያመለክተናል።

በተጨማሪም፣ እነዚህ ምዕራፎች የተዋቀሩት በሆህያት ቅደም ተከተል መሠረት ነው። ምዕራፍ 1 እና 2 እያንዳንዳቸው ሃያ ሁለት ጥቅሶች ሲኖሯቸው፣ እያንዳንዱ ጥቅስ ሦስት ስንኞች አሉት፤ እያንዳንዱ ጥቅስ የሚጀምረው ከሃያ ሁለቱ የዕብራይስጥ ሆህያት (በቅደም ተከተላቸው) ለአንዱ ነው። ምዕራፍ 4 ተመሳሳይ አካሄድ ቢኖረውም፣ አንድ ጥቅስ ሁለት ስንኞች ብቻ አሉት። ምዕራፍ 3 ስድሳ ስድስት ጥቅሶች ሲኖሩት ለእያንዳንዱ ሦስት ጥቅሶች ስላሉት፣ መዝሙር 119ን ያስታውሰናል (ምንም እንኳ እነዚህኞቹ እያንዳንዳቸው ስምንት ጥቅሶች ያሉአቸው ቢሆኑም)። ሌላው ለየት የሚያደርገው ገጽታው በምዕራፍ 2-4፣ ከተለመደው የዕብራይስጥ ሆህያት ቅደም ተከተል በተቃራኒ፣ ‘ፌ’ (pe) ከ ‘ዔ’ (ayin) በፊት መሰለፉ ነው።

የዚህ ዐይነት የሆህያት መዋቅር ጥቅም ላይ ለመዋሉ በርካታ ማብራሪያዎች ተሰንዝረዋል። በመዝሙር 119 ጥቅሶቹን ለማስታወስ ባለው ዐጋዥነት ሲሆን እዚህ ላይ ግን ዐላማው

ይህ ነው ማለት የሚቻል አይመስልም። ከቀረቡት መላምቶች አንዱ፣ የዚህ ዐይነት ሥነ ጽሑፋዊ ዘይቤ መሪር ሐዘን ላይ ልዝም ለማኖር የሚረዳ መሆኑ ነው። ሌላው መላምት ደግሞ ሆህያት በተርታ ጥቅም ላይ መዋላቸው የተገለጸውን ሐዘን ምሉእነት (ከህ እስከ ፐ መሆን) ማመላከታቸው ነው።

6. ነገረ መለኮታዊ ፋይዳዎች

በእስራኤል የወረደው መዓት ብሔራዊና ግላዊ እርከኖች ነበሩት፡- ኤርምያስ ሁለቱ ተነጥለው መታየት እንዳለባቸው ያሳያል፤ የኢየሩሳሌምንና የዳዊትን መንግሥት ውድቀት ቢጠባበቅና ይህ በበደላቸው እንደ ደረሰባቸው ቢገልጽም፣ እርሱ ጻድቅ ሰው ሆኖ እያለ በተለምዶ ከሚታመነው በተለየ ለኃጥኣን የመጣው ለምን እንዳልቀረለት ሊገባው አልቻለም። ስለ ጻድቅ ሰው መከራ የሚያወሣው ታዋቂው መጽሐፈ ኢዮብ ነው። ሰቈቃወ ኤርምያስ በድፍን ምድሪቱ ላይ የመጣ መከራን ያንጸባርቃል።

ጸሓፊው የይሁዳን ኀጢአት አጠይሞ ለመናገር አልሞከረም፣ ስለሆነም በጥፋቷ ክብደት መደንገጡ ግልጽ ነው። ይህ ሁሉ ፍዳ የተከሠተው በራሱ በእግዚአብሔር እንጂ በጠላቶቹ እንዳይደለ ደኅና አድርጎ ተገንዝቧል። ይሁዳ የጠላቶቿ መዘባበቻ እንድትሆን ያደረገው ራሱ እግዚአብሔር ነበር (2፥17)። ስለዚህም ልቅሶዎቹ ከጸሎት ጋር የተዋሐዱ ናቸው፤ ጸሎትም ተስፋ ትርጉም አልባ በሚመስልበት ሁኔታ ተስፋን ያበሥራል።

ይህ ሁሉ የሚያመለክተን ምንም ያህል ለማወቅ ብንሞክር፣ ውሱን በመሆናችን ልንረዳቸው የማንችላቸው ጥልቅ የእግዚአብሔር ሥራዎች መኖራቸውን ነው። እግዚአብሔር በቃሉና በግብሩ በአዝልቆት ፍርዱንና የቃል ኪዳን ፍቅሩን ይገልጽልናል፤ ይሁን እንጂ ከእኛ ግንዛቤ በእጅጉ የሚልቀው ጥበቡ ፊት እጅ በመንሣት፣ ልባችንን እንድናስገዛ የሚጠይቀንን የተመክሮ ውሱንነት መቀበል ይኖርብናል። የዚህን የላቀ አብነት በመስቀሉና በማር 15፥34 በሚገኘው የኢየሱስ የጣር ጩኸት እናያለን (ከመዝ 22፥1 ጋር ያነጻ)። ለዚህም ነው ቀለው የሚቀርቡልን የሥርዐት ንድፈ ሐሳቦች ሁሉ አጥጋቢነት የሚጐድላቸው፤ የጐልጐታው መከራ ከሰው አእምሮ እጅግ ከፍ የሚሉ ጥልቅ ምስጢራትን ያዘለ ነውና። የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ፈቃድ ከፍትሕ አደራረጉና ከቃል ኪዳን ፍቅሩ ጋር ሙሉ በሙሉ ስምሙ እንደ ሆነ በክብር የምንገነዘበው፣ ነጻ ፈቃድና የቅድመ ውሳኔ ትምህርት ታርቀው ስናይ ብቻ ነው።

ትንተና

፩. የኢየሩሳሌም ውድመት ጕስቍልና (1፥1-22)

ይህ ልቅሶ ከምዕራፍ 2፣ 4 እና 5 በኋላ የሚከተል ነው (ምዕራፍ 3 የተጻፈበት ጊዜ የሚታወቅ አይመስልም)። ጸሓፊው የከተማዪቱ ጥፋትና መፈታት የተፈጸመበት ፍጹም ጭካኔ እንደ ቀድሞው አያስደነግጠውም፤ ሆኖም በሰከነ ልቡና የተከሠተውን ለማጤን ፋታ አግኝቷል። ኢየሩሳሌምን በዚህ ጊዜ የበለጠ ለሐዘን የዳረጋት ያለፈችበት መከራ ሳይሆን እንዳልሆኑ ሆኖ መቅረቱ ነበር። ልቅሶው በባለቅኔውና በከተማዪቱ መካከል የሚደረግ ውይይት ተደርጐ ሊተረጐም ይችላል፤ ይሁን እንጂ ከዚህ ይልቅ ሐዘኑን የሚቀሰቅሰው የገጣሚው አሣብ እንደ ሆነ ማሰቡ ይመረጣል፤ ገጣሚው ባሏ የሞተባት ይህቺ ከተማ አቤቱታዋን ወደ እግዚአብሔር እንዲሁም ጥፋቷንና ባድማ ሆና መቅረቷን ለሚመለከቱ ባዕዳን እንዳቀረበች አሳይቶናል።

1. የገጣሚው አሣሣል (1፥1-11ለ)

1 ገጣሚው በመጀመሪያ የይሁዳ መዲናና መታያ የሆነችውን ኢየሩሳሌምን በመመልከት፣ አሁን ያለችበትን ሁኔታ ከነበረችበት ሁኔታ ጋር ያነጻጽራል። በዳዊትና በሰሎሞን ታላቅ የግዛት ዘመን እንኳ፣ የእስራኤል ግዛቶች ግብፅ፣ አሦርና ባቢሎን በታላቅነታቸው ከደረሱበት ክብር ጋር የሚወዳደሩ አልነበሩም፤ በሕንጻዎችና በብልጥግና (ምናልባት በሰሎሞን የንግሥና ዘመን ካልሆነ በቀር) እንዲሁም በሕዝብ ብዛት ኢየሩሳሌም ከመካከለኛ ምሥራቅ ታላላቅ ከተሞች ጋር የሚተካከል ክብር አልነበራትም። ይሁን እንጂ፣ እዚህ ላይ የባለቅኔውን ቋንቋ ብሔረተኝነት ወይም ስሜታዊ አድርገን መውሰድ የለብንም። የእግዚአብሔር ምድር የሆነችው እስራኤልና የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ማደሪያ የሆነችው ኢየሩሳሌም፣ የጌታ ሁለንተናዊ ንግሥና በምድር ሁሉ ላይ የሚሰፍንባቸው ቦታዎች እንደ ሆኑ ተስፋ ያደርጋሉ። ስለዚህም ባለቅኔው እየገለጸ ያለው በእግዚአብሔር ዐላማዎች ያላትን ዕቅድ ነው። ከተማዪቱ የፍርስራሽ ቍልል፣ ምድሪቱ ደግሞ የባዕድ ተገዢ በሆኑበት ሁኔታ እንደ ምን ተስፋን ማሰብ ይቻላል?

2 ኢየሩሳሌም በጕስቍልናዋ ሌሊት፣ በደረሰባት መከራ ምክንያት ብቻ ሳይሆን ወዳጆቿና ባልንጀሮቿ ስለ ክፂት ጭምር አምርራ ስታለቅስ ትታያለች። እነዚህን ቃላት (ከኤር 4፥30፤ 30፥14 ጋር ያነጻ) ግሩም በሆነ መንገድ የሚያብራሩልን ሕዝ 23 እና ሆሴ 8፥9-10 ናቸው። እዚህ ላይ የተመለከተው ሐሳብ ዙፋኑ የተደላደለ መሠረት ላይ ከቆመ፣ እስራኤል ልታመልጠው የማትችል ምርጫ እንደሚጠብቃት ነው፤ አንድም የመጡባትን የውጪ ወራሪዎች ለመመከት በእግዚአብሔር ላይ መታመን፣ አንድም ታላቅም ይሁኑ ታናሽ ዐጋዥ የሚሆኗትን ሀገሮች መጠጋት (ከ1ነገ 15፥16 ጋር ያነጻ)። የዚህ ዐይነቱ ጥምረት መመሥረት የክሕደት ኀጢአት እንደ ሆነ ነቢያቱ ቢያስጠነቅቁም (ከሆሴ 5፥13፤ 8፥8፡ 11፥14፥3 ጋር ያነጻ) የሰሚኑና የደቡብ መሪዎች የነቢያቱን ቃል ጆሮ ዳባ ልበስ ብለውታል። ይሁዳ እንደዚህ ያሉ ወዳጆችን መታመን የተሰበረ ሸምበቆን መደገፍ እንደ ሆነ ቀደም ብላ ተምራለች (ሕዝ 29፥6-7)።

3 ባለቅኔው ትኵረቱን ከኢየሩሳሌም አንሥቶ፣ በምርኮ ተግዘው ስለ ሄዱትና ከተማቸው ባድማ ሆና ስለ ቀረችው ስለ ይሁዳ ሕዝብ ያወሣል። ይህ ማለት የደረሱት ችግሮችና ግዞቱ ሙሉ በሙሉ ውጤታማ ነበሩ ማለት አይደለም። "በሕዝቦች መካከል ተቀመጠች" የሚለው አባባል በ4፥20፣ በንጉሣዊው ግዛት ሥር በብሔራዊ ህልውና ስለ መኖር ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል፤ ስለዚህም በሕዝቦች መካከል መቀመጥ ምርኮን የሚያመለክት ላይሆን ይችላል። ይሁዳ የምታርፍበት ስፍራ ማጣቷ፣ በንጉሣዊው ግዛት ሥር ሰላምን ማረጋገጥ አለመቻሏን ይጠቁማል።

4 በዓል አክባሪዎች እንኳ ወደ ቤተ መቅደስ መምጣት አቁመዋል። ዕዝራ 3፥2-6 እንደሚያመለክተው፣ የቤተ መቅደሱ ሕንፃ ባይኖር እንኳ መሥዋዕት ማቅረብ ይቻላል፤ ኤር 41፥5 እንደሚጠቍመው ቤተ መቅደሱ ከወደመም በኋላ በዓል አክባሪዎች ወደ ስፍራው ይመጡ ነበር። አሁን ግን ይህም የቀረ ይመስላል፤ ይህ ሁኔታ ይህ የልቅሶ ክፍል ከሌሎች በኋላ የተጻፈ እንደ ሆነ ያሳያል። ካህናቷ የተባሉት ከምርኮ አምልጠው፣ ከቅዱስ ስፍራ በቅርበት የሚኖሩት ትሩፋን ካህናት ናቸው። ከመቅደሱ የአምልኮ ሥርዐት ጋር ያለው ግንኙነት ግልጽ ባይሆንም (መዝ 68፥25) ፣ ደናግሏ ከካህናቱ ጋር በአንድ ላይ መቅረባቸው በኤርምያስ 31፥13-14 እና በኢዩኤል 1፥8-9ም የምናገኘው ሐሳብ ነው።

5 ይህ ሁሉ አስቀድሞ በቃል ኪዳኑ የተተነበየ ነው (ከዘዳ 28፥44 ጋር ያነጻ)፤ ስለዚህም ይህ የደረሰባት ከኀጢአቶች ብዛት የተነሣ በራሱ በጌታ እንደ ሆነ በግልጽና በይፋ ይናዘዛል። ወደ ግዞት መሄድ፣ እስራኤላውያን ቃል ኪዳኑን ቢያፈርሱ ከሚከተሏቸው ቅጣቶች አንዱ ነበር (ከዘዳ 28፥36፡ 63-68 ጋር ያነጻ)። ልጆቹ የወላጆቻቸውን ኀጢአት ጦስ መቀበላቸው በሐዘኗ ላይ ሌላ ሐዘን ነበር።

6 ጽዮን ግርማ ሞገስ ተለይቷታል። መሳፍንቶቹ በዐዳኝ እንደሚሳደዱ የተራቡ ዋልያዎች መንጋውን ትተው ሸሽተዋል። ኢየሩሳሌም ሁለት ጊዜ ያለውጊያ ተሸንፋለች (2ነገ 24፥1፡ 17፤ ዳን 1፥2)፤ መጨረሻ ላይም ሴዴቅያስና መኳንንቱ የተወረረችውን ከተማ ትተው ሕይወታቸውን ለማትረፍ ይሸሻሉ (2ነገ 25፥4)።

7 ኢየሩሳሌም እዚህ ላይ የነዋሪዋ መከራ ተካፋይ ሆና ቀርባለች። የተጨነቀችባቸውንና የተንከራተተችባቸውን ቀናት ታስባለች፤ ይህም በመከራ የተጨነቀችበትና ሕዝቧም አስገባሪዎች እንዳሻቸው የሚያደርጓቸው ተገዢዎች የሆኑበትን ቀናት ማለት ነው። ይህ ልቅሶ ከተማዪቱ ከፈራረሰች ከተወሰነ

ጊዜ በኋላ ለመጻፉ ማስረጃ ነው። ከሁሉ የባሰው፣ ውድቀቷ ለጠላቶቿ መሣቂያ እንድትሆን ማድረጉ ነበር። ብዙ ጊዜ፣ ሣቅ ከንቀት ጋር የተዛመደ ነው (ከዘፍ 17፥17፤ 18፥21፤ ከኢዮ 8፥21፤ ከመዝ 126፥2 ጋር ያነጻ)። የኢየሩሳሌም ባለጋሮች በሣቅ ያላገጡባት፣ እስራኤል ራሷን በእግዚአብሔር የተመረጠች ምድር እንደ ሆነች መቊጠሯ የሚፈጥርባቸው ቅናት ለመሆኑ አያጠራጥርም።

8-9 ኢየሩሳሌም፣ ያለንፍረት ዕርቃኗን ከተጋለጠችና በቀሚሷ የሚታየው የወር አበባ ምልክት ከማያሸማቅቃት የተዋረደች ዝሙት ዐዳሪ ጋር ተመሳስላለች። ዝሙት ዐዳሪነት ተደጋግሞ የእስራኤልን ጣዖት አምላኪነትና የበዓል አምልኮ በመግለጽ ጥቅም ላይ በመዋሉ፣ እዚሁም ላይ በውስጠ ታዋቂነት መጠቀሙ ግልጽ ነው። የእስራኤል ውድቀት ፍጹም መሆን በመጨረሻ ወደ ልቧ እንድትመለስ ያደርጋል። የደረሰባት መዓት እንዲቀለበስ መለመን የሚያስችል አብነት እንደ ሌላት ታውቃለች፣ ይሁን እንጂ የጠላት ድፍረታዊ ድል ሽለላ መለኮታዊ ቅጣትን ግድ የሚል ነበር (ከኢሳ 10፥12 ጋር ያነጻ)። ጠላት "ድል አድርጎአልና" የሚለው የቃል በቃል ትርጕሙ ልክ ቢሆንም፣ ትክክለኛውን ፍቺ አያመለክትም። እዚህ ላይ አጽንዖት የተሰጠው ለድሉ ሳይሆን በድፍረት ለመሸለሉ ነው።

10 ከሁሉ የከፋው ነገር ኢየሩሳሌም ትልቅ ዋጋ ሰጥታ ያከበረችውን ማጣቷ ነበር። በኋለኛው ዘመን የሚንጸባረቁት ስሜቶች ኢየሩሳሌምን በምድራዊ ክብርና ውበት ድባብ የሚስቡ ናቸው፤ ሆኖም ኋላም እንደ ነበረው የቀደመው ዘመን ትልቁ ክብሯ ቤተ መቅደሱ ነበር፤ ያም ቢሆን ትልቁ ክብሩ መቀደሱ ነበር። ድል አድራጊዎቹ ግን ይህን ክብሯን አርክሰዋል የሎጥ ዘር የሆኑትና በዚህም ምክንያት ከእስራኤል ጋር የሩቅ ዝምድና ያላቸው አሞናውያንና ሞዓባውያን እንኳ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ እንዳይገቡ ከተከለከሉ (ዘዳ 23፥3) ይልቁንም ጨርሶ የማይዛመዷቸው ከለዳውያንማ ምንኛ የተናቁ ይሆኑ!

11ሀ-ሰ የባለቅኔው የልቅሶ ምሬት ያለልክ እያየለ ይመጣል። ኢየሩሳሌም ከተቀበለችው ሰቈቃ አንጻር "ህልውና ለማቈየት የከበረ ሀብታቸውን በምግብ ይለውጣሉ" የሚለው አባባል ያን ያህል ክብደት ያለው አይመስልም። በተጨማሪም፣ ከለዳውያን ከተማዪቱን በመዝረፍ አራቊተዋት ነበርና፣ የከበረ ሀብት ቀርቶ ነበር ብሎ ማመን ያዳግታል። ቴዎዶሬት የተባለው ጸሓፊ (450 ዓቅክ) የአባባሉ ትክክለኛ ፍቺ፣ ራሳቸውን በሕይወት ለማቈየት የሚወጿቸውን ልጆች ለወጡ ማለት እንደ ሆነ አመልክቷል። እዚህ ላይ አንድምታው ልጆቻቸውን በሉ ማለትም (ከ2፥20፤ 4፥10 ጋር በዘዳ 28፥53-7 ያነጻ፤ ከ2ነገ 6፥28-29 ጋር ያነጻ) ይሁን ለባርነት ሽጡአቸው እምብዛም ለውጥ የሚያመጣ አይመስልም። ምናልባት ሁለቱም ትርጕሞች ሊያስኬዱ ይችላሉ።

2. የከተማዪቱ ተማጽኖ (1፥11ሐ-16)

11ሐ እዚህ ላይ ግጥሙ እንደሚያመለክተን፣ ኢየሩሳሌም በባለቅኔው ቃላት ሐዘኗ በመቀስቀሱ የተማጽኖ ጥሪና ጸሎት ታቀርባለች። ጸሎቱ በግጥሙ መካከል ላይ የቀረበ በመሆኑ ቦታውን የጠበቀ ነው። እግዚአብሔር እንዲራራላት ተስፋ የምታደርገው በመናቋ ሳይሆን፣ በሌሎች የተቃለለችበት ሁኔታ ልክ በማጣቱ ነው።

12 ኢየሩሳሌም ወደ እግዚአብሔር ከተጣራች በኋላ፣ ባድማ ሆና በቀረችው ይሁዳ አጠገብ የሚያልፉ መንገደኞች ሆነው ለቀረቡት አገሮችም የጩኸቱን ስሙ አቤቱታ ታቀርባለች። "የጽኑ ቊጣው ቀን"፣ የጌታ ቀን ነው፤ በማርቆስ 13 እና በትይዩ ንባባቱ የኢየሩሳሌም ውድቀት ከዘመን ፍጻሜ መከራ ጋር እንደሚዛመድ ሁሉ፣ በዚህም ስፍራ ተዛምዶ እናያለን (ከኤር 4፥23-28 ጋር ያነጻ)።

13-14 ከከፍታ ስፍራ የተላከው እሳት የእግዚአብሔርን የሚነድ ቊጣ ሥዕል በማጠናከር የሚቀጥል ሲሆን በሰውነት ላይ ብርቱና የሚያነፍር ሥቃይ በማድረስ ለሞት የሚዳርግ ነው። በከተማዪቱ ላይ መረብን ዘርግቶ ማምለጫ በማሳጣት ለውድቀት ያበቃት እግዚአብሔር ራሱ እንጂ፣ ጠላቶቿ አይደሉም (ከሕዝ 12፥3፤ 17፥20 ጋር ያነጻ)። የዚህም ውጤት በገዳይ በሽታ የተከሠተ የውድመትና የመፍረስ ምሳሌ መሆን ነበር። "በዐንገቴም ላይ ተጭነዋል" ማለቷ የመጡባትን ጠላቶች መቋቋም እንደ ተሳናት ያመለክታል። ኢየሩሳሌምን ያህል በጠንካራ ምሽጎች የተከለለች ከተማ፣ ለአንድ ዓመት ከመንፈቅ ብቻ መከበቧ አስገራሚ በሆነ ሁኔታ ዐጭር ጊዜ ነበር (2ነገ25፥1-2፤ ከ17፥5-6 ጋር ያነጻ)።

15-16 በምድሪቱ የቀረው ቀቢጸ ተስፋ ብቻ ነበር። እዚህም ላይ መዓቱ በጠነከረ ቋንቋ ይገለጻል፤ "ሰራዊት" ተብሎ የተተረጐመውን የዕብራይስጥ ቃል ኢየሩሳሌም ሳትሆን ጠላቶቹ የታደሙበትን የደስታ "የመከር በዓል" እንደ ሆነ አድርገን መረዳት ይኖርብናል። የመከራው ጽዋ እጅግ የመረረ በመሆኑ ኢየሩሳሌም "እግዚአብሔርን" የምትጠራው "ያህዌ"፤ ከቃል ኪዳን ጕድኝት ጋር (ከዘፀ 3፥14 ጋር ያነጻ) ግን እግዚአብሔር (አዶናይ) በሚለው ስሙ ነው። ስለዚህም ባለቅኔው በውስጤ ያሉትን ተዋጊዎች ሁሉ፣ "እግዚአብሔር ተቃወመ" በማለት እንደገለባ እንደቈጠራቸው ይናገራል፤ ጕልማሶችን ለማድቀቅ "የመከር በዓልን በላዬ ላይ ጠራ" ሲል በማበራየት ብቻ እንዳልተወሰነ ይገልጻል። ድንግሊቱን የይሁዳ ሴት ልጅ፣ "እግዚአብሔር በወይን መጭመቂያ ውስጥ ረገጣት" ማለቱም ታዳሚዎቹ እየጠሙ የሚደሰቱበትን የወይን ጠጅ ለማቅረብ ነው። ኢየሩሳሌም በተሰበረ ልብ የምታለቅሰው "ጠላት" በመርታቱ ነው። ሽንፈት መራራ ቢሆንም፣ ድል ነሺዎቹ የእግዚአብሔር ጠላቶች ሲሆኑ ደግሞ ይበልጥ የሚያንገፈግፍ ይሆናል።

3. የገጣሚው ልቅሶ (1፥17)

17 ገጣሚው ለኢየሩሳሌም የመጨረሻ ኑዛዜ የሚያዘጋጀን፣ "ጽዮን እጆቿን" በጸሎት ብትዘረጋም፣ የሚያጽናናት አለማግኘ ቷን በመናገር ነው። ለዚህም ምክንያቱ ጥፋቷ በጌታ በራሱ የታዘዘ በመሆኑ ነበር። ኢየሩሳሌም በእርሱ ስትተው በሁሉም ዘንድ የተናቀች ርኩስ (የመርገም ጨርቅ) ነገር ሆና ተቈጠረች።

4. የከተማዪቱ ኑዛዜ (1፥18-22)

18-22 ገጣሚው በሚናገርበት ወቅት፣ ኢየሩሳሌም ዳግመኛ ያለችበትን ሁኔታ ለማስላስል ጊዜ ታገኛለች። ወዲያውኑም ይህ ሁሉ ፍዳ የመጣባት በገዛ ራሷ ዐመፃ እንደ ሆነ ትናዘዛለች። የኢየሩሳሌም አንዱ ተስፋዋ ምንም እንኳ ለራሷ መታደስን ባያመጣላትም፣ በጠላቶቿ ላይ ተመሳሳይ ዕጣ የሚገለጥ መሆኑ ነው። እነርሱ ላይ የሚመጣው መከራ በእርሷ ከመጣው እንደማይተናነስ እንዲያውም "ወዳጆቼን ዘራኋቸው፤ እነርሱ ግን ከዱኝ" በማለት የበለጠ ቅጣት እንደሚቀበሉ ታስታውሳቸዋለች። በዚህ መጽሐፍ ኢየሩሳሌም የቀራት አንድ ተስፋና መጽናኛት ጠላቶቹን የሚጠብቃቸው ያው ዕጣ መሆኑ ብቻ በራሱ ጸሓፊው ኤርምያስ ላለመሆኑ ለርግጠኝነት በጣም የቀረበ መከራከሪያ ነው፤ ምነው ቢባል ኤርምያስ ከሰባው ዓመት በኋላ በከለዳውያን እጅ እንደሚወድቁ ብቻ ሳይሆን፣ ኢየሩሳሌም እንደምትታደስም ጭምር መተንበዩ ነው (ኤር 25፥12)። የኢየሩሳሌም ውድቀት እግዚአብሔርን በሚፈሩት ላይ ሳይቀር የፈጠረው ፍጹም የሆነ ድንጋጤ ከዚህ ቀቢጸ ተስፋ የበለጠ ምስክርነት ሊኖረው አይችልም። በተጨማሪም የኤርምያስን ብቸኝነት፣ ከዮአኪን ምርኮ በኋላ በብዙዎች ልብ ተስፋ ማቈጥቈጡ (ኤር 28፥1-4፤ 29፥8-9) እና የሴዴቅያስ ዐመፅ እብደት መሆኑን ያብራራልናል።

፪. ጌታ ሕዝቡ ላይ መቈጣቱ (2፥1-22)

በመጀመሪያው ልቅሶ የሚስተዋሉት ገጽታዎች መተው፣ ባድማ መቅረትና ኀፍረት ናቸው፤ እዚህ ላይ አትኩሮት የተሰጠው ገጽታ ጥፋት ነው። ይህ ውድመት የደረሰው በአራተኛው ወር በተከሠተው የከተማዪቱ መያዝና (2ነገ 25፥3-4) እንደ ገና ከአንድ ወር በኋላ የናቡከደነፆርን በቀል ለመፈጸም ናቡዘረዳን ከመጣ በኋላ (2ነገ 25፥8-12) ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፤ የሚኾች አስከሬኖች ቀባሪ አጥተው በየመንገዱ ተጥለው ነበርና ነው። ለዚህም ነው የመጀመሪያው ልቅሶ፣ የመጨረሻው ሆኖ ሳለ መጀመሪያ ላይ የተቀመጠው። በመጀመሪያ ላይ በምድሪቷና በሰዎቹ ላይ የደረሰው ጥፋት አስደንጋጭ ስሜት ይፈጥራል፤ ውሎ ሲያድርም ይህ ሁኔታ ያስከተለው ኀፍረት የባሰ የከፋ ሆኖ ይታያል።

1. የሕዝቡና የመቅደሱ መጣል (2፥1-9)

1 ገጣሚው የጥፋቱ ማዕበል ከዐናቱ በላይ ሲያልፍ ያያል። ከተሸሸገበት ተነሥቶ በዙሪያው የደረሰውን ውድመት ሲመለከት፣ ይህ የሉዓላዊው ጌታ ሥራ መሆኑን በእምነት ድምፅ ያውጃል። የኢየሩሳሌም ፀሓይ ተሰወረች፤ የእስራኤል ክብር (ቤተ መቅደሱ) ከከፍታ (ከሰማይ) ተወርውሮ ተጣለ ፤ የተናቀም ሆነ። የእግሩ መቀመጫ የሚለው ሐረግ ታቦቱን የሚያመለክት አይመስልም፤ ምክንያቱም ኤር 3፥16 ከመቅደሱ መውደም በፊት የተጻፈ በመሆኑ መቅደሱ ከዚያ ጊዜ ቀድሞ ለመጥፋቱ ማስረጃ ነው።

2-3 ይሁዳ ሁሉ ወደመች፤ መንግሥቱም የቅድስና ክብሩ ተገፈፈ። የቅጣት እጁን በመዘርጋት ("የእስራኤልን ቀንድ ሁሉ ሰበረ") እና ራሱን በማግለል ("ቀኝ እጁን ወደኋላ መለሰ")፣ ጌታ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለጥፋት አሳልፎ ሰጣቸው።

4-5 እግዚአብሔር እዚህ ላይ የተሣለው ከሩቅ የሚገድል ቀስትና የጨበጣ ውጊያ ሰይፍ እንደ ታጠቀና ("በጽዮን ሴት ልጅ ድንኳን ላይ ለዐይን ደስ የሚያሰኙት ሁሉ") መጨረሻው ላይ የቀረውን ሁሉ በእሳቱ የሚያቃጥል ብርቱ የጠላት ተዋጊ ሆኖ ነው። በሕዝቡ ላይ እንደ ጠላት ሆነ።

6-7 እንደ ጠላት፣ ጌታ መሰብሰቢያ ስፍራውን (መቅደሱን) አፈረሰ። እዚህ ላይ ንጉሡና ካህኑ በአንድነት ተጣምረዋል፤ የነገሥታቱ ታሪክ በግልጽ እንደሚያሳየው ንጉሡ ምንም እንኳ በበርካታ የክህነት ሥራዎች መሳተፍ ባይፈቀድለትም የቤተ መቅደሱ አምልኮ የበላይ ተቈጣጣሪ ነበር። የቤተ መንግሥቶቿ ቅጥሮች ማለት የተመሸጉ መኖሪያዎች ናቸው። ከነገሥታቱ ቀጥሎ፣ ቤተ መቅደሱ ንጉሣዊ ቤተ መንግሥትና የንጉሡ ሕንጻዎች የተካተቱበት ትልቅ ተቋም አካል ነበር። የጠላቶች የድል ጩኸት ከደስታ ክብረ በዓላት ጩኸት ጋር ሲነጻጸር እንመለከታለን (ከመዝ 66፥1፣ 81፥1፤ 95፥1 እና ከሌሎችም ጋር ያነጻ)።

8-9 ልቅሶው ከቤተ መንግሥቱ ተነሥቶ ወዲያውኑ ወደ ከተማዪቱ፣ ወደ ንጉሡና (ያለጥርጥር ዮአኪንን ያመለክታል) በግዞት ወዳሉ ሹማምቱ ተዛመተ። "ሕጉ ከእንግዲህ አይኖርም፤ ነቢያቶቿም ከእንግዲህ ከእግዚአብሔር ራእይ አያገኙም" የሚለው ክፍል በአንድ ላይ ተጣምሮ መታየት ይኖርበታል። በሕጉ ክህነታዊ ፍቺም ይሁን በነቢያዊ ራእይ፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ቀድሞው ለሕዝቡ መታወቁ ቀርቷል።

2. የሕዝቡ ሰቈቃ (2፥10-17)

10 ልቅሶው ከቀደመው መሪር ትውስታ ወደ አሁኑ የበለጠ መሪር እውነታ ይሸጋገራል። "ሽማግሌዎች" እና "ወጣት ሴቶች" እዚህ ላይ መጠቀሣቸው ምናልባት በሕይወት የተረፉትን ሁሉ ለማመልከት ታስቦ ይሆናል። ራስ ላይ ትቢያ ነስንሶና ማቅ ለብሶ ምድር ላይ በዝምታ መቀመጥና ዐንገትን ማቀርቀር ብርቱ ሐዘንን የሚገልጹ አባባሎች ናቸው።

11-12 ገጣሚው ዐብሮ ማዘኑን በሚያመለክት ቋንቋ ከሕዝቡ ጋር ልቅሶ ይቀመጣል። የከተማዪቱ ውድቀትና ባዶአቸውን ቀርተው ከጥቃት ሲመክቱላት የተገደሉት ሰዎች ለረኃቡ እልባት አልሰጡም። ከተማዪቱ በጠላት ወታደሮች ቊጥጥር በነበረችባቸው የመጀመሪያ ቀናት ከአቀራቢያ ባሉት ከተሞች ምግብ መቃረም የሚፈቀድ አይመስልም። "እንጀራና የወይን ጠጅ" ነፍስን ለማቈየት የሚረዳ የዕለት ጉርስና ቢጋኝ የማይጠላ ምቾትን የሚያመለክት ይመስላል።

13 ሰቈቃ በጣም እየበረታ በመምጣቱ ቃላት እንኳ ዐቅም ያጣሉ። ምናልባት እዚህ ላይ መጥቀስ የተፈለገው የባሕሩን ጥልቀት ያህል ሳይሆን፣ የከተማዪቱ ውድመት በማዕበል የሚናወጥ ባሕርን የሚያስታውስ መሆኑን ነው።

14 ይህን ጥቅስ ግሩም አድርገው የሚያብራሩት ኤር 23፥18-22 እና ሕዝ 13፥10-16 ናቸው። በርካታ ሰባኪዎች ስለ ቤተ ክርስቲያን ቅድስና አጥብቀው የሚያስቡ ከመሆናቸው የተነሣ ጉድለቷን እንደሚገባ መመልከት እንደሚሳናቸው ሁሉ፣ በእስራኤልም ዘንድ እንዲሁ ነበር።



ዛሬ ኢየሩሳሌምን የሚጐበኙ ሰዎች ኤርምያስ የከተማዪቱን መጻኢ ዕጣ በማሰብ ያለቀሰበትን ዋሻ መመልከት ይችላሉ። የሕዝቡን ልብ ማርከው የነበሩ ነቢያት ሥልጣንና ተሰሚነታቸው ከስም መጨረሻም ላይ ፍጹም ተቀባይነት ያጡት የባቢሎን ምርኮ በሕዝቡ ዘንድ በፈጠረው ድንጋጤ ሳቢያ ነበር።

15-17 እያንዳንዱ የአረማውያን ከተማ ወይም ከተሞች የራሱ የሆነ ጣዖትና ጣዖታት በነበረው ጥንት ዘመን የእኔ ይበልጥ መቀናቀን ቢኖርም የተወሰነ መቻቻል ነበር። ይሁን እንጂ፣ እስራኤል እውነተኛው አምላክ የእነርሱ ብቻ፣ ሕዝቡም እነርሱ፣ ኢየሩሳሌምም መዲናው እንደሆነች ማወጃቸው አሕዛብን ቅናት ያሳድርባቸው ስለ ነበር በውድቀታቸው በጣም ተደስተዋል። "እግዚአብሔር ያሰበውን . . . ከረኸርም ጊዜ በፊት የተናገረውን፣ ቃሉን ፈጸመ" የሚለው ቃል ዘሌ 26፥14-46 እና ዘዳ 28፥15-68 የመሳሳሉ ክፍሎችን የሚያመለክት ይመስላል።

3. የጸሎት ጥሪ (2፥18-19ሐ)

18-19ሀ ቀቢጸ ተስፋ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲሹ ያደርጋል፤ ስለዚህም ባለቅኔው ጽዮንን በጸሎት እጇን እንድትዘረጋ ጥሪ ያቀርብላታል። እዚህ ላይ የመጀመሪያው ሐረግ "የጽዮን ሴት ልጅ ቅጥር ሆይ፤ ከልብሽ ጩኺ" ተብሎ ቢተረጐምም የበለጠ ትክክለኛ ይሆናል። አባባሉ እንግዳ ቢመስልም፣ ጥፋቱ የደረሰበት ሁሉ፣ የከተማዪቱን ፍርስራሾች ጨምሮ፣ በዚህ የጭንቅ ጸሎት ልባቸውን እንዲያፈሱ የቀረበ ጥሪ ነው።

19ሐ ይህ ስንኝ ከዚህ ቀደም የተገለጸውንና ልቅሶው የሚገልጸው በከበባው ወቅት የተከሠተውን መከራ ሳይሆን፣ ከከበባው በኋላ ያለውን ሁኔታ ነው የሚለውን አተረጓጐም የሚያረጋግጥ ነው።

4. የተሰጠው ምላሽ (2፥20-22)

20-22 እዚህ ላይ ለማቅረብ፣ ባለቅኔው ቅኔውን የሚቀኘው በሕይወት ለተረፉት ወይም አብነት መሆን የሚችል ጸሎት ወይም የጸሎቱ ቅኔያዊ አገላለጽ መሆኑ አይደለም ቁም ነገሩ። ጸሎቱ ጠሊቅና መሪር ዋይታን በጭንቅ ይተርካል። ቊጥር 20ሀ የቃል ኪዳን ግንኙነት መኖሩን ያስታውሰናል። የቤተ መቅደሱን ሊገሰስ የማይችል ክብርና ቅድስና ነቢያቱ በአጽንዖት የሚያስተምሩት ነገር ነበርና (ከኤር 7፥4 ጋር ያነጻ)፣ በመጨረሻው ሰዓት በዚህ ስፍራ በአንድነት መሰብሰባቸው የሚጠበቅ ነገር ነበር። 'የተቀደሰ ጉባኤ' እና 'የበዓል ቀን' ለሚሉት ሐረጋት በ1፥15 ላይ የተሰጠውን ሐተታ ይመልከቱ።

፫. የእስራኤል የምሬት ቃል (3፥1-66)

ይህ ልቅሶ በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ የሚገኝ ቢሆን ኖሮ፣ ከኢየሩሳሌም ውድቀት ጋር ቊጥጥ ያለ ተያያዥነት ይኖረዋል ብሎ ማሰብ ያዳግት ነበር፤ ለዚህ ምክንያቱ የተነገረበት ቋንቋ ውድቀቷንና ታላቅ ጭንቋን ከሚያመለክት ሁኔታ ጋር ይህ ነው የሚባል ተዛማጅነት የሌለው መሆኑ ነው። ትውፊታዊው (ዘልማዳዊው) አመለካከት የኤርምያስን የራሱን የግል ሐዘን እንደሚገልጽ ይነግረናል።

1. በግል የደረሰበት መከራ (3፥1-20)

1 በብሉይ ኪዳን ዘይቤ፣ “ማየት” አንድን ነገር በዐይን ከመመልከትና ከማጤን ያለፈ ትርጉም አለው። ከቍጥር 18 ውጪ ከ1-21 ባሉት ቍጥሮች የእግዚአብሔር ስም አለመጠቀሱ፣ - ባለቅኔው ያደረበትን የመተውና የመነጠል ስሜት በአጽንዖት ያሳያል። “የቍጣው በትር” የሚለውን ሐረግ ለመረዳት ኢዮብ 9፥34፤ 21፥9፤ መዝ 89፥32 እና ኢሳ 10፥5ን ይመለከቷል።

2-3 “አስወጣኝ” ተብሎ የተተረጐመው የዕብራይስጥ ቃል እንስሳትን ማባረርን አስመልክቶ ጥቅም ላይ የሚውል እንጂ ከቶም ቢሆን የእግዚአብሔርን የጸጋ ምሪት አያመለክትም። የሚያስወጣው በቍጣው በትር ነው። “በርግጥ ቀኑን ሙሉ በመደጋገም፣ እጁን በላዬ ላይ መለሰ” ሲል ስለ ደረሰበት መራር መከራ በምሬት እየገለጸ ነው።

4 “አስረጀ” ተብሎ የተተረጐመው የዕብራይስጥ ቃል የሚያመለክተው አሮጌ ማድረግን ሳይሆን የአርጅናንና የድካምን ውጤት ማሳደር ወይም ማልፋትን ነው። “ዐጥንቶቼንም ሰባበረ” ሲል፣ የትኩሳት (ነዲድን) ሥቃይን የሚያመለክት ሲሆን በትርጉም ከኢሳ 38፥13 ጋር ስምሙ ነው።

5-9 “ምሬት” የሚለው ቃል የመጨረሻ መራቁትና የተስፋ መሟጠጥን ይገልጻል። ጨለማ ሲኦልን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ከሚውሉ የተለመዱ ዘይቤዎች አንዱ ነው። “ከሞቱ ብዙ ጊዜ እንደ ሆናቸው” የሚለው ሐረግ እነርሱም ጨርሶ መረሳታቸውን ያመለክታል። “የእስር ሰንሰለቴ” የሚለው አባባል፣ ባለቅኔው ርዳታ ፍለጋ ቢጣራ፣ የማይሰማበት ቅጥር ውስጥ እንደ ተዘጋበት ይጠቀሙማል። ባለቅኔው አንዳች ማጥ ውስጥ ገብቶ የተጠመደ ይመስላል። ቅጥሮቹ “በተጠረቡ ድንጋዮች” በጥንካሬ በመታጠራቸው በመካከል ባሉ ክፍተቶች በኩል ወደ ውስጥ ለመመልከት አይቻልም፤ የጐንዮሽ መንገዶች ደግሞ ወደ የትም የሚያደርሱ አይሆኑም፤ ወይም ማምለጥን የማይቻል ያደርጉታል።

10-12 ይባስ ብሎ፣ የባለቅኔው መንገድ በአደጋ ተከቧል (ድብና አንበሳ ለሚለው አሞ 5፥9 እና ሆሴ 13፥8ን ይመ)። ሕይወቱን ለመንጠቅ አድብተው የሚጠብቁ ጠላቶቹንና የእግዚአብሔርን በአሳሳች መንገድ መምራት ማምለጥ ቢችልም እንኳ፣ አጥቂዎቹ ሳይሆኑ ራሱ እግዚአብሔር እንደ አሳዳጅ ቀስቱን ይዞ ይጠብቀዋል።

13-15 “ፍላፃዎችን ከሰገባው አውጥቶ፣ ልቤን ወጋው ሲል” የቀስተኛውን ክንድ ጥንካሬ ያመለክታል። ልብ ለተለዋጭ ዘይቤው ትርጉም ተገቢ ተስታካካይ ቢሆንም፣ እዚህ ላይ የታሰበ የሚመስለውን ኩላሊት የሚለውን ቃል በቃል ገላጭ አልተጠቀመም። ኤርምያስ በሕዝቡ ዘንድ የሚገጠሙ ዘፈኖች መዘባበቻ ሊሆኑ መቻላቸው መገንዘብ እምብዛም አያደግትም። በተለምዶ (መራራ ሥር) ተብሎ የሚታወቀው “ሐሞት” ለአንዳንድ መጦጦች መራራ ቃና ለመስጠት ጥቅም ላይ የሚውሉ የተወሰኑ ዕፀዋትን ያመለክታል።

16-18 “ጥርሴን በድንጋይ ሰበረ፤ በትቢያ ውስጥ ረጋገጠኝ” የሚለው አባባል መሬት ላይ ተጥሎ በጭካኔ ፊቱ የሚደበደብ ሰውን ያመለክታል። “ነፍሴ ሰላምን ዐጣች” እና “ደስታ ምን እንደ ሆነ ረሳሁ” በሚሉት አቻዊ ጥምረቶች፣ ሰላም ተብሎ የተተረጐመው የዕብራይስጥ ቃል ‘ሻሎም’ ‘ስኬት’ ወይም ‘ብልጽግና’ የሚለውን ትርጉም ማዘሉ ጥርጥር የለውም። “ክብሬ ሄዶአል” ሲልም የክብር መለየትን ያመለክታል። ለነቢዩም ይሁን ለእስራኤል በጌታ ተስፋ ማድረግ ክብራቸው ነበር፤ ክብራቸው ተለይቷቸው ሲሄድ በዙሪያቸው ካሉት አረማውያን እኩል ሆኑ። ባለቅኔው እዚህ ላይ የእግዚአብሔርን ስም የጠቀሰው የከበበውን መከራ ድባብ ለመግፈፍ ነው።

19-20 ባለቅኔው የጭንቀቱንና የመንከራተቱን፣ ምሬትንና ሐሞትን ዐስባለሁ ይላል። ጸሓፊው ወደ ጌታ ከመጮሁ በፊት በቅድሚያ የእግዚአብሔርን የምሕረት ባሕርይ (በቍጥር 22-32) ማሰብ ይኖርበታል።

2. መጽናናትና የጸጋ ተስፋ (3፥2-39)

21-24 እዚህ ላይ ጸሓፊው የሚያበሥረው፣ “ተስፋ” ያለበትን መከራና ችግር እንደሌለ ከመቍጠር ወይም ከማቃለል የተገኘ አይደለም። ይልቁንም፣ ሰው ልቡን ወደ እግዚአብሔር ዘወር ሲያደርግ፣ የእነዚህ ነገሮች መልክ ይለወጣል። በቍጥር 22 የሚገኘው ወሳኙ ቃል “ታላቅ ፍቅር” ሲሆን፣ ይህም ርኅራኄን የሚያመለክተውን የቃል ኪዳን ፍቅርና የጌታን ታማኝነት ይገልጻል። እስራኤልን ወደ ህልውና ያመጣት ይህ የቃል ኪዳን ፍቅር እንደ መሆኑ፣ ጌታ የራሱ ፍጥረት ለሆነው ሕዝብ ያለው የፍቅር ርኅራኄ ማለቂያ የለውም። የአንድ ዐዲስ ቀን መጨመር በራሱ የእግዚአብሔር ምሕረት ያለመቋረጥ ምልክት ነው። ሕዝቡ የሞት አመልካች በሆነው በጨለማ በሰላም ማለፍ ችሏል። ስለዚህም ጥቅሱ፣ “የታላቅ ፍቅር” አቻዊ ትርጉም በሆነው በ“ታማኝነት” ይደመደማል። ባለቅኔው ዕድል ፈንታው እግዚአብሔር ስለ ሆነ የዚህ ዓለም መልካም ነገሮችና ተድላዎች ተካፋይ አይደለም ማለት ይቻላል (ከመዝ 16፥5፤ 73፥26፤ 119፥57፤ 142፥5 ጋር ያነጻ)።

25-27 በዕብራይስጡ እነዚህ ሦስት ትርጉሞች የሚጀምሩት “መልካም” በሚለው ቃል ነው። የዚህ ቃል ቀዳሚ ትርጉም የእግዚአብሔርን ፈቃድና ዐላማ የሚገልጽ ማለት ነው። እዚህ ላይ እምነት ራሷን በጸጥተኛ ተስፋና ራስ ማስገዛትን በመማር፣ የእግዚአብሔርን ጊዜና ፈቃድ ስትቀበል ይታያል።

28-30 እነዚህ ጥቅሶች የቍጥር 25-27 መርሖች በተለይም ቀንበር የመሸከም መርሕ እንደ ምን በግብር እንደሚገለጡ ያትታሉ። የእግዚአብሔር የአገልግሎት ቀንበር አንድን ሰው ከተለመደው ሕይወት አውጥቶ የተገፋ ያደርገዋል (ከኢዮ 2፥8 ጋር ያነጻ)። ዝምታ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መቀበልና ለሌሎች ሰዎች ስሞታ ከማቅረብ የመቈጠብ አንድምታ አለው። ከዚህ ጋር በቍጥር 29 ላይ በምሥራቃዊው ራስን የማዋረድ ዘይቤ የተገለጸው ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር የመገዛት ሥዕል ይታያል። በተጨማሪም ይህ የመገዛት ቀንበር የማገልገል ምልክት እንደ መሆኑ፣ እንደ አገልጋይ ለመቈጠር ፈቃደኛ ወደ መሆን ይመራል። እዚህ ላይ የተቀመጡት መርሖች፣ ያለጥርጥር ለነቢይነት የተጠራ ሰውንና እግዚአብሔር የግል ንብረቱ ያላቸውን ሕዝቡን በእኩል የሚመለከቱ ናቸው (ዘፀ 19፥5-6)።

31-33 እነዚህ ጥቅሶች ቀንበር መሸከምን ቀላል የሚያደርጉ ምክንያቶችን ይሰጡናል። እግዚአብሔር ቢጥልም፣ ለጊዜው ነው። ቢያስጨንቅም፣ ርኅራኄና የቃል ኪዳን ፍቅሩን ዳግመኛ ይዘረጋል፤ በሥቃይና በቅጣት የሚያስጨንቀውም እንዲያው በዘፈቀደ አይደለም።

34-36 የእግዚአብሔር የምሕረትና የፍቅር ባሕርይ ከሰው ኢሰብኣዊነት ሦስት አመልካች ገጽታዎች ጋር በተነጻጻሪነት ቀርቧል። አንድ ሰው እስረኛ በመሆኑ ብቻ ግፍ ሲዋልበት ይታያል። ፍትህ እየተጓደለ ነው። እግዚአብሔር የሰማይ አምላክ በመሆኑ፣ ሁሉን የሚያይ መሆኑን ለማጽናት “ልዑል” ተብሎ ተጠርቷል፤ በመሆኑም ፍትሕን መንፈግ ሆነ ብሎ ፈቃዱን መቃወም ነው። ሰዎች እግዚአብሔር ከላይ የማይመለከት ይመስል የሌሎችን መብት ሆነ ብለው ይጨቍናሉ።

37-39 ይህ የልቅሶ ክፍል የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንድንቀበል ግድ የሚለንን ሁሉን ቻይ ኀያልነቱን ያጸናል። መልካምም ይሁን ጥፋት እርሱ ያመጣው በመሆኑ (ከኢሳ 45፥7 ጋር ያነጻ)፣ ሰዎች ለኀጢአታቸው መከራን ሲቀበሉ ከሚያማርሩ ይልቅ ሌላ ቀን በሕይወታቸው እስከ ተጨመረ ድረስ፣ ነገሮች እንደሚለወጡ ተስፋ ቢያደርጉ ይሻላል።

3. የንስሓ ጥሪ (3፥40-51)

ይህ ክፍል ሁለት አንጓዎች አሉት። ከቍጥር 40-47 ጸሎቱን የሚያደርሱት ሕዝቡ ናቸው። ከቍጥር 48-51 ደግሞ ባለቅኔው ጸሎቱን በእንባው ያሳርጋል።

40-41 ሕዝቡ የሚያሰሙት እሮሮ (ከቍጥር 39 ጋር ያነጻ) አግባብነት የጐደለው እንደ ሆነ ዐውቀው መንገዳቸውን ማለትም ያደረጉትን መመርመር እንዳለባቸው ይገነዘባሉ። በተለምዶ

ለጸሎት እንደሚያደርጉት እጃቸውን ብቻ ሳይሆን፣ መላውን ሁለንተናቸውን (“ልባችንን”) ወደ እግዚአብሔር ለማንሣት ይወስናሉ፤ ጕዳዩ ሥርዐት የመፈጸም አፋዊ ነገር ብቻ እንዳልሆነ ልብ ይሏል።

42-43 እዚህ ላይ በ“እኛ” እና “በአንተ” መካከል ንጽጽር እናያለን፤ የእስራኤል ዐመፃና አለመታዘዝ በአንድ ጕን፣ ይቅር ለማለት የእግዚአብሔር በጀ አለማለት በሌላ ጕን ተነጻጽረው ቀርበዋል፤ አንድምታው እርሱ ጻድቅ መሆኑ ነው። ተማጽኖው ይቀጥላል፣ “ራስህን በቍጣ ከደንህ”፤ ስለዚህም ያለምሕረት እንዳሳደዳቸውና እንደ ፈጃቸው እንመለከታለን።

44-46 እግዚአብሔር ከሰዎች እይታ ራሱን በደመናና በጨለማ መሰወሩ በብሉይ ኪዳን የተለመደ ነው (ከዘፀ 20፥21፤ 40፥34-35፤ ከዘሌ 16፥2፤ ከ1ነገ8፥10፡ 12 እና ከሌሎችም ጋር ያነጻ)። ይሁን እንጂ ይህ ግርዶሽ ጸሎት እንዳያልፍና የሚከለክል ተደርጎ ሊታሰብ አንመለከትም። በቀጣዩ ክፍል ሕዝቡ ራሳቸውን እንደ ጕድፍና ዋጋ ቢስ አድርገው በመቅረብ ይናዘዛሉ። እግዚአብሔር ካደረገባቸው የተነሣ፣ ጠላቶቻቸው በይፋ ናቋቸው (ከ2፥16፤ ከመዝ 35፥21 ጋር ያነጻ)። ይሁዳ ለክብሯ መሟገት የማትችል ሆነች፤ ይህን ሊያደርግላት የሚችል ወዳጅም አልነበራትም።

47-48 “እንቅፋት” ተብሎ የተተረጎመው ቃል ምናልባት የዐዳኝ ወጥመድ ማለት ይሆናል (ከኢሳ 24፥17-18፤ ከኤር 48፥43-44)። የሕዝቡ ንስሓ ኤርምያስን ሥቃያቸውን ከሁሉ የበለጠም የራሱን ያስታውሰዋል (ከኤር 9፥1፤ 14፥17 ጋር ያነጻ)።

49-51 ኤርምያስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምላሽን እስኪያገኝ ድረስ እንባ ማፍሰሱንና፣ ለእስራኤል መማለዱን ይቀጥላል። ቍጥር 51 በዕብራይስጡ ቃል በቃል፣ “በከተማዬ ባሉት ሴቶች የተነሣ ዐይኔ ነፍሴን አስጨነቃት” የሚል ሲሆን፣ በግልበጣ ስሕተት “መከራ” መባል የነበረበት ማየትን እንዲያመለክት ሆኗል። ትክክለኛው ትርጕም እንዲህ ይሆናል፤ “እግዚአብሔር ከሰማይ እስኪያይና በከተማዬ ባሉት ሴቶች ምክንያት የደረሰብኝን መከራ እስኪመለከት ድረስ”።

4. የተሰፋ ማቈጥቈጥ (3፥52-57)

52-57 ገጣሚው በሕዝቡ ዕጣ ፈንታ የደረሰበት የነፍስ ሰቀቀን የራሱንም እንዲያስታውስ ያደርገዋል። እንደ ወፍ መታደንን በተመለከተ በመዝ 11፥1-2፤ 124፥7፤ 140፥5 ይመ። በዚህ አባባል ትርጕም ኤርምያስ 18፥18 ምሳሌ ይሆነናል። “ሕይወቴን በጉድጓድ ውስጥ ሊያጠፉ ሞከሩ” ማለቱ ያለጥርጥር በኤር 38፥6 የሰፈረውን ክሥተት የሚጠቍም ነው። “ውሃ ሞልቶ በዐናቴ ላይ ፈሰሰ፣ ጭንቀትን የሚያመለክት የተለመደ ምሳሌ ነው (ከኢዮ 27፥20፤ ከመዝ 42፥7፤ 66፥12፤ 69፥12፤ 88፥7፤ 124፥4 እና ከሌሎችም ጋር ያነጻ)። የውሃ ኩሬ በተለምዶው አፉ በድንጋይ ይከደናል። በቍጥር 56 የሚገኙትን ቃላት ትክክለኛ ትርጕም መወሰን ቀላል አይመስልም። “ከመስማት ጆሮህን አትክልክል” ማለቱ ጸሎቱን (“ርዳታም ፈልጌ ስጮህ”) የሚያመለክት ይመስላል።

5. የበቀል ጥሪ

58-66 እነዚህ ጥቅሶች እንዳሉ በቀጥተኛ ትርጕማቸው ቀርበዋል። እግዚአብሔር በቀደሙት ጊዜያት ኤርምያስን በጥበቃው መከለሉ ለወደፊቱም ዋስትና ይሆነዋል። ነቢዩ የዚህ ዐይነት ርግማን ከአፉ ማውጣትን እንደ ተሻገረና በኢየሩሳሌም ጥፋት እግዚአብሔር ጠላቶችን ሲቀጣ እንደ ተመለከተ ልናስብ እንችላለን። ይሁን እንጂ ኤርምያስ ለሕዝቡ ሲል ሁሉን ነገር፣ ከቤተ ሰብ ሕይወትና ልጆች የሚገኘውን ደስታ ሳይቀር እንደ ተወ መርሳት የለብንም (ኤር 16፥1-4)። በተጨማሪም እግዚአብሔር የዐዲሱን ቃል ኪዳን መታደስ ጨምሮ ስለ እስራኤል ተሐድሶ ደማቅ ተስፋ ቢሰጠውም፣ እግዚአብሔር ከመቃብር ባሻገር ስላለው ሕይወት የጨረፍታ ምልክት እንኳ እንደ ተሰጠው የሚጠቍም ነገር የለም። ታዲያ እስከ ግብፅ ድረስ የተከተለው መገፋትና የውለታ ቢስነት ሸክም ምንኛ ጀርባውን የሚያጐብጠው ይሆን!

፬. የትላንቷና የዛሬዋ ጽዮን (4፥1-22)

ይህ ልቅሶ ምዕራፍ 2 ከተጻፈበት ጊዜ ብዙም ሳይቈይ የተጻፈ እንደ ሆነ መገመት እንችላለን። የመጀመሪያው ድንጋጤ የፈጠረው ውጤት አሁን በመደብዘዙ፣ ባለቅኔው የተከሠተውን ነገር በሰከነ ሁኔታ በመቃኘት ለምዕራፍ 27 ድጋፍ ይሰጣል።

1. የቀረበው ንጽጽር (4፥1-11)

1-2 ወርቅ የማይዝግ በመሆኑና ሁለተኛው መሥመር የፈራረሰውን መቅደስ የሚያመለክት በመሆኑ፣ እዚህ ላይ የተሣለው ሥዕል በወርቅ የተለበጡት ዐምዶቹ እና የወርቅ ሰሐኖች በአሳራ በመሸፈናቸው እንደ ተራ ነገር ሆነው ውድነታቸው መረሳቱ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ በሕይወት የተረፉት ታሳሪዎች የቀድሞ ክብራቸው አሁን ተለይቷቸዋል።

3-5 “ቀበሮ” ግልገሎቿን በመንከባከብና በማጥባት እምብዛም የማትታወቅ አጥቢ ናት። ሰጕንም ዕንቍላሎቿን ችላ በማለት በምሳሌ የምትጠቀስ ወፍ ናት (ኢዮብ 39፥13-18)፤ ሕዝቤ ልጆቻቸውን በመርሳታቸው እንደነዚህ እንስሳት ሆነዋል። ገንዘብ ትርጕም አልባ ሆኗል፤ ባለጠጋ ሴቶችም ረዳት ቢፈልጉ ስለማያገኙ በቈሻሻ መካከል ምግብ መቃረም ግድ ሆነባቸው።

6-9 እዚህ ላይ በሰዶም ላይ ከደረሰው ይበልጣል ስለ ተባለለት የይሁዳ ቅጣት ወይም ዐመፃ (ከሕዝ 16፥44-52 ጋር ያነጻ) ርግጠኛ መሆን የሚቻል አይመስልም። የሆነው ሆኖ ብዙ ለውጥ የሚያመጣ አይመስልም፤ ምክንያቱም የዐመፃውና የሚደርሰው ቅጣት ልክ ቍርኝት ስላለው ነው። ‘ናዚር’ የሚለው ቃል ናዝራዊ ተብሎ የሚተረጐም ቢሆንም፣ በዘፍ 49፥26 እና በዘዳ 33፥16 ላይ ከቀሩት የዘመን ተጋሪዎች በደረጃና በብቃት ከፍ ያለ ሰውን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል።

እዚህ ላይ ትርጕሙ ይህ በመሆኑ፣ መሳፍንቶች ተብሎ መተርጐሙ ተገቢ ነው። በክፍሉ የተገለጹት ሰዎች ሰውነታቸውንና የውጪ ሁኔታቸውን የሚንከባከቡ፣ የሚያሳምሩም ናቸው። እነዚህ በአንድ ወቅት መልከ መልካም የነበሩ መሳፍንቶች ዛሬ ውርደት ዕጣቸው ሆኑ። ሞት ተናፋቂ እስኪሆኑ ድረስ መከራቸው የከፋ ሆኗል።

10-11 ረኃብ ሰዎችን ኢሰብኣዊ ነገሮችን እንዲያደርጉ ይገፋፋቸዋል (ከ2ኛ ነገ6፥25-29 ጋር ያነጻ)። ይህ ሁሉ በሕዝቡ ላይ የመጣባቸው እግዚአብሔርን በማስቈጣታቸው ነው።

2. የካህናቱና የነቢያቱ ኀጢአት (4፥12-16)

12 እዚህ ላይ ጕልሕ ሆኖ የሚታይ ግነት (ኩሸት) አለ። ለማመልከት የተፈለገው፣ ኢየሩሳሌም በሰናክሬም ዘመን የእግዚአብሔርን ትድግና ማየቷ ለሕዝቡ የሚያስገነዝበው፣ ከተማዪቱ የእግዚአብሔር እጅ እስካረፈባት ድረስ ለጥቃት የማትበገር መሆኗን ነው።

13 እግዚአብሔር ከለላውን ያነሣው ካህናቱና ነቢያቱ እጃቸው በደም ስለ ተበከለ ነው። እዚህ ላይ የተጠቈመው የትንቢታዊ ሥነ ምግባር መሠረታዊ ሐሳቦች አንዱ ጕዳይ ነው። ሕዝ 22፥1-22 እንደሚያሳየን፣ ደም ማፍሰስ ነፍስ በማጥፋት ወይም በግድያ ብቻ የተወሰነ አይደለም፤ የኀብረተ ሰብን ሥርዐት የሚያናጋ ወይም ሰዎችን ከምድራቸው ወይም ከኑሮ መሠረታቸው የሚያፈናቅል ግብር ሁሉ ሕይወታቸውን በዐጭር የሚያስቀር በመሆኑ ከደም ማፍሰስ ጋር የሚተካከል ተደርጎ ይቈጠራል። ካህኑና ነቢዩ ለዚህ አምንታዊና አሉታዊ ድርሻን ያበረክታሉ፤ አምንታዊው እንደዚህ ዐይነቱን ግብር ማጽደቅና ይሁንታ መስጠት ሲሆን፣ አሉታዊው ደግሞ ወገኖቻቸው በሆኑ እስራኤላውያን ላይ በደል የሚፈጽሙትን ሰዎች አለመኮነን ነው።

14-16 እነዚህ ጥቅሶች የቍጥር 13 ቀጥተኛ ቅጥያዎች፣ ማለትም እጃቸው በደም የረከሰ ካህናትና ነቢያት የሚቀበሉትን ፍርድ የሚያመለክቱ እንደ ሆኑ አድርጎ ማሰብ የተለመደ ነው። በዚህ ምልክታ እኒህ ሰዎች የቃየን ምልክት የታተመባቸው፣ ግብራቸው በመርከሱ ሰው ሁሉ እንደ ለምፃም የሚሸሻቸውና በሄዱበት ሁሉ የተተፋ ናቸው። ይሁን እንጂ ኤር 29፥15-23 እና የመጀመሪያዎቹ የሕዝቅኤል ምዕራፎች፣ ከኢዮአኪን ጋር በምርኮ የተጋዙት ሰዎች ዕጣ ይህ መሆኑን አያመለክቱም፤

ባለቅኔው ከኢየሩሳሌም ውድቀት በኋላ በሕይወት ስለ ተረፉት መጨረሻ በተመለከተ ዕውቀት ሊኖረው አይችልም። ምናልባት ገለጻው በባዕድ ምድር ተበታትነው ስለ ቀሩትና አሳዛኝ ዕጣ ስለ ገጠማቸው ትሩፋን በጠቅላላው የሚያመለክት ይሆናል። በቍጥር 16 ላይ ሽማግሌዎች እንጂ ነቢያት አለመጠቀሳቸው እንደዚህ ዐይነቱን ንባብ የሚያጠናክር ይመስላል። ይሁዳ ሙሉ ለሙሉ ማለት ይቻላል አሉኝ የምትላቸውን ባለማዕረግ ሰዎች አጥታለች።

3. ዐውል ተስፋዎች (4፥17-20)

17-20 የምርኮኞቹ መታወር በምድሪቱ ትሩፋን ላይ ከደረሰው መታወር ጋር ብቻ ነበር የሚስተካከለው። ተስፋ ሳይኖር ተስፋ እንዳለ በተላላነት በማሰብ እስከ መጨረሻው ቅጽበት ድረስ የግብፅን ርዳታ ፍለጋ ደጅ ከመጥናት አሳቋረጡም (ኤር 37፥3-10)። ባለቅኔው "እኛ" በሚለው ተውላጠ ስም መጠቀሙ እርሱም የዚህ ከንቱ ተስፋ ተካፋይ መሆኑን ያመለክታል። ይህ አባባልና ሴዲቅያስ የተገለጸበት ሁኔታ የመጽሐፉ ጸሓፊ ኤርምያስ ነው ከሚለው አባባል ጋር ፈጽሞ የሚጣጣም አይደለም (ቍ. 19ን በተመለከተ፣ ዘሌ 26፥8፤ ዘዳ 32፥20፤ ኢሳ 30፥16-17ን ይመ)። ሴዲቅያስ ለማምለጥ ያደረገው የመጨረሻና የጭንቅ ሙከራ በቍጥር 19-20 እንደ ተጠቈመ መገመት ይቻላል። ይሁዳ ለዕብደትና ለመታወር የተዳረገችው በመቅደሱ ብቻ ሳይሆን፣ የዳዊት ሥርወ መንግሥት ፈጽሞ የማይገሰስ እንደ ሆነ በማመኗ ነበር። ለዚህም ነው ኤርምያስ ስለ መሲሓዊው ተስፋ ምንም ያልተናገረው። "የሕይወታችን እስትንፋስ" እና "በጥላው ሥር" የሚሉት ሐረጋት ከጥንት የመካከለኛው ምሥራቅ የችሎት ቋንቋ የተወሰዱ ናቸው።

4. የጥፋት መቀልበስ (4፥21-22)

21-22 ከንቱ ተስፋዎች እንደ ጉም ሲበኑ፣ የሚመረውን እውነታ መጋፈጥ ግድ ሆነባቸው። የይሁዳ ጠላቶችን ሁሉ የምትወክለውን ኤዶምን (ከኢሳ 34፣ ከሕዝ 35 ጋር ያነጻ) ባለቅኔው፣ "እስከ ጊዜው ድረስ ደስ ይበልሽ፤ አንቺም ከፍርድ አታመልጪምና" እያላት ነው። ዕርቃናቸውን መቅረታቸው ኀፍረትንና የኀጢአታቸውን መጋለጥ፣ በተጨማሪም ባርነትን የሚያመለክት ነው (ከኢሳ 47፥2-3 ጋር ያነጻ)። ጽዮን እዚህ ላይ የቀረበላት መጽናናት የሚገባትን ቅጣት ሁሉ በመቀበሏ (ከኢሳ 40፥2 ጋር ያነጻ)፣ ከእንግዲህ የስደት ዘመን የማይኖር መሆኑን የሚያመለክት ነው።

፭. ጌታን መማጸን (5፥1-22)

የሆህያት ምኅባርና የልቅሶ ቀለም (ምት) በዚህ ክፍል አለመኖራቸው ይህ ልቅሶ በሌላ ሰው እጅ የተጻፈ መሆኑን የሚጠቁም ይመስላል። በከበባው ወቅት የተከሠቱ ሁነቶች ቢጠቀሙም፣ ይህ ልቅሶ ባመዛኙ ከጥፋቱ በኋላ ስላለው ጊዜ የሚተርክ በመሆኑ የተወሰነ ጊዜ እንዳለፈ ያመለክታል።

1. የጌታ ሕዝብ መከራ መቀበል (5፥1-18)

1-3 በመጽሐፍ ቅዱስ ያለፈውን መዘከር ሁልጊዜ ድርጊትን ያስከትላል፤ ስለዚህም እግዚአብሔር እንዲሠራ ጥሪ ይቀርብለታል። በተለምዶ ውርስ ተብሎ የተተረጐመው ቃል በማንኛውም ዐይነት መንገድ የተገኘን ንብረት ያመለክታል። ባለቅኔው በሚኖርበት ኅብረተ ሰብ ወላጅ አልባ ልጆችና የደረሱ ወንዶች ልጆች የሌሉአቸው ባልቴቶች የሚቆምላቸው ተማጓች ከሌላቸው እንደ ምስኪኖች ይቈጠሩ ነበር። ይህ እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ እንዲሟገት በውስጠ ታዋቂነት የቀረበ ተማጽኖ ነው።

4 ከ2ነገ24፥14፤ 25፥12 እና ኤር 39፥10 እንደምንረዳው፣ በይሁዳ የቀሩት ብዙዎቹ ሥራቸው ማሳና የወይን አትክልት መንከባከብ የሆነ በጣም ድኻ ሰዎች ናቸው። እግዚአብሔር ሙከራውን ሻረበት እንጂ ባዕዳን ዜጎችን በምድሪቱ ማስፈር የናቡከደነፆር ሐሳብ ነበር። ስለዚህ ይህ ጥቅስ ትሩፋን በሕይወት መኖር ይችሉ ዘንድ፣ በሕዝቡ ላይ መጣል የነበረበትን ከባድ ግብር ሳያመለክት አይቀርም።

5 በዚህም ጥቅስ ተመሳሳይ ሐሳብ ተንጸባርቋል። ብዙ ሰዎች እንደ ባሮች ቢወሰዱም፣ ጸሓፊው እዚህ ላይ የሚያመለክተው ባሪያ አሳዳሪዎችን አይደለም፤ ወደፊት እንዲገሠግሡ የሚያደርጋቸው በሕይወት የመቈየት ፍላጎት ነው፤ እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው ማሳደድ እንደሚያሳርፋቸው የሰጣቸውን የተስፋ ቃል ትተዋል (ከዘዳ 12፥10፤ 25፥19፤ ከ2ሳሙ 7፥1፡11) ጋር ያነጻ)።

6-7 ኋላ ቂሮስ እንዳደረገው፣ ናቡከደነፆር የአሦር ሥልጣን ገሸር ሆኖ መቀጠሉ እውነት ቢሆንም (ከዕዝ 6፥22 ጋር ያነጻ)፣ እዚህ ላይ "የአሦርና" ትርጉም ይህ አይመስልም። ባለቅኔው የሚያመለክተው አባቶቻችን የሠሩትን ኀጢአት ነው። መልሱ እስራኤል የተፈጥሮ የወላድነት ጣዖታትንና በአሲሪን ማምለኳ በተገለጸበት በሆሴዕ 2፥5፡8 ላይ ተመልክቷል። በእስራኤላውያን ዘንድ ጌታ ከአማልክት እንደ አንዱ ብቻ ሆኖ ተቈጠረ፤ ስለዚህም ከግብፅና ከአሦርያ ጋር ግንባር መፍጠር ፈለጉ (ሆሴ 5፥13፤ 7፥11፤ 12፥1)። በእነርሱ ጦስ ልጆቻቸው ብድራቱን ተቀበሉ፤ ልክ ሰማርያ ከአንድ ምእት ዓመት ከመንፈቅ በፊት እንደ ሆነባት ሁሉ።

8-10 ሕዝቡ እንደ ቀድሞው በራሳቸው ንጉሥና ሹማምት መገዛታቸው ቀረና በባቢሎን አለቆች አገዛዝ ሥር ማደር ጀመሩ፤ እነዚህ አለቆች ብዙዎቹ ዝቅተኛ ማዕረግ ያላቸውና 'የንጉሡ ባሮች' ተብለው በመጠራታቸው የሚመኩ ሰዎች ናቸው። እንደ ወደዱ ለሚፈጽሙት የግፍ ተግባር ይግባኝ የሚባልበት ችሎት አልነበረም። ይህ ሁኔታ የዕለት ጉርስን ለማግኘት በሕይወትና በአካል መወራረድና ለአደጋ መጋለጥ ድረስ በሚደርሰው ውጣ ውረድ ተመልክቷል፤ ቈዳቸው እንደ ምድጃ ጠቍሮ ተቃጥሏል፤ ይህም በረኃብ መጠበስን ያመለክታል።

11-13 ሕዝቡ የተቀበሉት ግፍ ቀደም ሲል ከለዳውያን ከተማዪቱን ሲይዟት የተቀበሉት መከራ ቀጣይ ክፍል ነበር። "መሳፍንት በእነርሱ እጅ ተሰቀሉ" ሲል ባለጠነቹ ሀብታቸውን የት እንደ ደበቁ እንዲናገሩ የደረሰባቸውን ግርፋትና ሥቃይ ያመለክታል። ይህ ትርጉም ስለ ሽማግሌዎች በሚናገረው ሁለተኛ መሥመር ተብራርቷል፤ አለመከበራቸውም ሆነ ተብሎ የደረሰባቸውን ኀፍረት በግልጽ ያመለክታል።

ስለዚህም እዚህ ላይ የተመለከተው፣ የሚቾችን አስከሬን በመስቀልና በመውጋት ማዋረድ ነው። ናቡከደነፆር አጥፊዎች ብሎ የቈጠራቸውን የሚያሠቃይ ሰው ባለመሆኑ (ኤር 52፥10-11፡ 24-27) የተወጉት ወይም የተሰቀሉት በሕይወት ሳሉ ነው ለማለት አያስደፍርም። ጉልማሶች ወፍጮ እንዲፈጩ በመገደዳቸው ለወትሮው ወታደሮች መሆን ሲችሉ፣ አሁን የሴት ሥራ ይሠሩ ጀመር። "ወንዶች ልጆች በዕንጨት ሸክም ተንገዳገዱ" ሲልም እንደ ጢሰኞች መቈጠራቸውን ያሳያል።

14-18 ለሽማግሌዎችና ለጉልማሶች ሕይወት ምስቅልቅል ሆነች፤ በቀደመው ኀጢአታቸው ሳቢያም ደስታ ሁሉ ራቃቸው። የእግዚአብሔር ቍጣ የመጨረሻው መገለጫ የቤተ መቅደሱ ተራራ የአውሬዎች መፈንጫ መሆኑ ነው። በመካከል ረዘም ያለ ጊዜ እንዳለፈ አልተገለጸም። የቤተ መቅደሱ ተራራ አሁንም የተቀደሰ መሬት ነው (ከኤር 41፥5 ጋር ያነጻ)፤ በዚህ የተቀደሰ ተራራ መሥዋዕት ማቅረብ ስለ መቀጠል አለመቀጠሉ በርግጠኝነት መናገር የሚቻል አይመስልም፤ ሆኖም መሥዋዕት ቢቀርብም እንኳ (ስለዚህ ጉዳይ በሰቈቃወ ኤርምያስ የተነገረ ነገር የለም)፣ በልዩ ቀናት በዓላት ላይ ብቻ ነው የሚሆነው። በሌላ ጊዜ ትሩፋኑ ካህናት እንኳ ሳይቀሩ መበደላቸውንና መርከሳቸውን ያውቁ ነበርና ወደ መቅደሱ አቅራቢያ መድረስም አልፈለጉም። ዛሬም ሳይቀር ወግ አክባሪና ርቱዓን አይሁድ ወደ ቤተ መቅደሱ አይገቡም። የምዕራቡ (የዋይታው) ግንብ ከተቀደሰው ስፍራ ውጪ ይገኛል። ቀበሮዎች የግንብ ፍርስራሾችን ሲያገኙ ወዲያውኑ ይሰፍሩባቸዋል።

2. የጌታ ዘላለማዊ ኀይል (5፥19-22)

19-20 "ዙፋን" የሚታይ የንጉሣዊ ሥልጣን ምልክት ነው። ባለቅኔው ልቅሶውን ሲጀምር ወዳቀረበው አቤቱታ ይመለሳል። "የደረሰውን ዐስብ" (ቍ. 1) በ"መርሳት"፣ "እይ ተመልከት"፣ በ"እስከ መቼ ትተወናለህ" ይተካል።

21 ባለቅኔው፣ እውነተኛ ንስሓን እግዚአብሔር ራሱ የሚጠነሰሰው እንደ ሆነ በቅጽበት ይገነዘባል (ከኤር 31፥18፡ 33-

34፤ ከሕዝ 36፥26-27 ጋር ያነጻ)። ይህ የዐዲስ ኪዳን ዳግም የመወለድ አስተምህሮ ትንቢታዊ አመልካች ነው። ይሁን እንጂ፣ ይህን እውነት በወቅቱ ብዙዎች አልተገነዘቡትም ነበር። የአይሁድ እምነት ንስሓ ላይ ትልቅ አጽንዖት ቢሰጥም፣ ሰው በራሱ አነሣሽነት የሚያደርገው እንደ ሆነ ተደርጎ ይታሰባል።

22 "ካልጣልኸን" "ካልተቈጣኸን" የሚሉት ቃላት በቀደሙት ጥቅሶች አሉታዊ ፍቺ እንድንጠብቅ ይመሩናል። ምናልባት የተሻለው ትርጉም፣ "ፈጽመህ ከጣልኸን፣ በኛ ላይ እጅግ ተቈጥተህ ሳይሆን አይቀርም" የሚል ይሆናል። ምናልባት ውጤቱ ቢለዝብም እንኳ፣ ሰቈቃወ ኤርምያስ ምኩራብ ውስጥ ሲነበብ በዚህ ዐይነት ጸሊም ፍጻሜ እንዳይቋጭ በማለት መጨረሻው ላይ ቍጥር 21 በድጋሚ ይነበባል።

ኤርምያስ ከሌሎች ወገኖች የበለጠ መከራ ለምን እንደ ደረሰበት መገንዘብ የሚሳነንን ያህል፣ ልቡን በእግዚአብሔር ፊት እንዲህ ማፍሰስ የሚችል ሰው ለምን ተገቢ መጽናናትን ሳይቀበል ቀረ የሚለው ጥያቄ ለብዙዎች እንግዳ ሆኖባቸዋል። በዚህ መጽሐፍ፣ ኤርምያስና ሕዝቅኤል የገለጹት የመመለስና የመታደስ የፋመ ተስፋ እንኳ አልተንጸባረቀም። በጣት ከሚቈጠሩት በቀር የእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔርን መገለጥ ለመረዳት በመቸገራቸው፣ እስራኤልን ለመሲሕዋና ለዓለሙ አዳኝ ምጽአት ሊያዘጋጃት የሚችል በግብፅ ውስጥ ከነበረችበት እስራት ጋር የሚተካከል ልምምድና ዐዲስ ፀአት ያስፈልጉ ነበር።

ትንቢተ ሕዝቅኤል

መግቢያ

1. ታሪካዊ ዳራ

የእስራኤል የጣዖት አምልኮ አስጸያፊ ክፋት ዐሥሩ የሰሜን ነገዶች በ722 ዓቅክ በአሦራውያን ተማርከው እንዲወሰዱ አደረገ። በዚያን ጊዜ የደቡቡ የይሁዳ መንግሥት እንደ ኢሳይያስ ባሉ ጻድቅ ሰዎች የአገልግሎት ተጽዕኖ የተነሣ ተረፈ። ስለሆነም ይሁዳ በወጣቱ በንጉሥ ሕዝቅያስ አመራር መነቃቃትንና መንፈሳዊ ተሐድሶን ተለማመደች። ሕዝቅያስ ከእስራኤል ውድቀት መንፈሳዊ ትምህርትን ከመማሩም በላይ በነቢዩ በኢሳይያስ አገልግሎት ተበረታትቶ ነበር (2ነገ 18-19)። ይሁን እንጂ ሕዝቅያስ በእግዚአብሔር ላይ የነበረው እምነትና ለሙሴ ኪዳን የነበረው ቅንዐት ልጁ ምናሴና የልጅ ልጁ አሞን የጌታን መንገድ በተቃውሞ ጊዜ ተረሱ። ለንምሳ ዐምስት ዓመት (2ነገ 21፥1-18) ሕዝቡን ለማናቸውም ዐይነት የጣዖት አምልኮና ክፋት አሳልፈው ሰጡት። ይህ ሕዝቡን ወዳልተፈለገ አቅጣጫ ዘወር ከማድረጉ በላይ የእግዚአብሔርን ሕግ እንዲንቁ አደረጋቸው፤ የኋላ ኋላም እስከ መኖሩ ረሱት።

የንጉሡ የአሞን ጻድቅ ልጅ የነበረው ኢዮስያስ ለይሁዳ ዐዲስ ተስፋን አመጣ፤ ይሁን እንጂ ተሐድሶው የመጣው እጅግ ዘግይቶ ነበር። ቤተ መቅደሱን እያደሰው ሳለ የሙሴ የሕጉ መጽሐፍ ቅጂ ተገኘ (2ነገ 22)። በሚያነበውም ጊዜ ኢዮስያስ ሙሉ በሙሉ ለታዘዝ ተነሣሥቶ ነበር (2ነገ 23)። ቤተ መቅደሱን አነጻ፤ በይፋም ምናሴና አሞን ያረከሱትን ምድር አነጻ። ነገር ግን ይህ ተሐድሶ በሕዝቡ ዘንድ ላይ ላዩን ብቻ የተፈጸመ ነበር። ረኛርም ዘመን ያስቁጠረው የምናሴ ጣዖት አምልኮ ልባቸውን እጅግ ስላረከሰው፤ እውነተኛው ንስሓ እጅግ አነስተኛ ነበር (ከኤር 3፥10 ጋር ያነጻ)። የሙሴ ኪዳን ሕዝቡ ያለማቋረጥ የኪዳኑን ግዴታዎች የማያሟሉ ከሆነ፤ የእስራኤል ሕዝብ ተማርከው እንደሚወሰዱና በአሕዛብም መካከል እንደሚበተኑ ተናግሮአል (ዘሌ 26፤ ዘዳ 28-29)። ያ ርግማን አሁን እውን ሆኖአል። የእስራኤልን ክፋት ሊያስወግድ የሚችል አንድ ነገር ይህ ብቻ ነበር፤ ወደ አምላካቸው ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉ የሚያደርጋቸውም ይኸው ነው።

በዚህ ጊዜ በዓለም ዐቀፋዊው ሁኔታ ዐዲስ የሥልጣን ትግል ነበር። ጥንታዊውን ቅርብ ምሥራቅ ከሁለት መቶ ኀምሳ ዓመታት በላይ ስትገዛ የነበረችው ኀያል መንግሥት አሦር ልትወድቅ የተዳረሰችበትና ዐዲሱ የባቢሎናውያን መንግሥት ደግሞ በናቡፓላሳር አመራር እየተነሣሣ ያለበት ወቅት ነበር። በ612 ዓቅክ ባቢሎናውያን አሦራውያን አሸነፉአቸው፤ የአሦራውያን ዋና ከተማ ነነዌም ወደቀች። የቀረው የአሦር ሰራዊት በዳግማዊ አሹሩባሊት መሪነት ወደ ምዕራብ ወደ ሀራን አፈገፈገ፤ ይኸውም ከበስተ ጀርባው ግብፃውያንን በማሳለፍ የመከላከያ ኀይላቸውን ለማጠናከር ታስቦ የተደረገ ነበር።

በ609 ዓቅክ የግብፅ ፈርዖን ኒካው አሦራውያንን ለመርዳት ታላቅ ሰራዊት ይዞ ተነሣ። በመጊዶ የተሓድሶው የይሁዳ ንጉሥ ኢዮስያስ፣ የኒካውን እንቅስቃሴ ለመግታት ሞከረ፤ ነገር ግን ተከትሎ በመጣው ጦርነት መካከል ተገደለ። ኒካው ወደ ሀራን በመገሥገሥ ሀራንን የራሱ ለማድረግ እየሞከረ የነበረውን አሹርባሊትን ለመርዳት ተጣደፈ፤ ነገር ግን የባቢሎናውያን ብርታት ወሳኝ የሆነውን ድል ለማግኘት አላስቻላቸውም።

ኒካው አሦራውያንን በሀራን መርዳት ባይችልም እንኳ፣ ፖለስቲናንና ሶርያን ለማስተባበር ችሎ ነበር። የይሁዳ ሕዝብ ዐዲስ ንጉሥ በማድረግ አንግሠውት የነበሩትንና ባቢሎናውያንን ይደግፍ የነበረውን የኢዮስያስን ልጅ ኢዮአካዝን ከዙፋን በማውረድ፣ ግብፃውያንን ይደግፍ የነበረውን የኢዮስያስን ታላቅ ልጅ ኢዮአቄምን እንደራሴው በማድረግ በይሁዳ ላይ አነገሠው። ይህ ዓለም ዐቀፋዊ ነውጥ በነበረበት ጊዜ፣ ነቢዩ ኤርምያስ የይሁዳ ሕዝብ በግብፅ ሳይታለሉ ለባቢሎናውያን እንዲገዙ አስጠንቅቆአቸው ነበር። ይሁን እንጂ ፈጽሞ አልስሙትም።

በ605 ዓቅክ የባቢሎናውያን ዐልጋ ወራሽ የሆነው ናቡከደነፆር በታሪክ ውስጥ እጅግ ወሳኝ በሆነው ጦርነት በኤፍራጥስ ወንዝ በከርከሚሽ በተባበረው በአሦርና በግብፅ ሰራዊት ላይ ከፍተኛ ጥቃት አደረሰ። በዚህ በናቡከደነፆር አስደናቂ ድል ዳግመኛ ላያንሠራሩና ዓለም ዐቀፋዊ ዕውቅና ላያገኙ ሁለት የጥንታዊው መካከለኛ ምሥራቅ ኀያላን መንግሥታት ወደቁ። ባቢሎናውያን በድል አድራጊነት ወደ ደቡብ እየገሠገሡ ሳለ፣ ይሁዳን ወረሩ፤ ከይሁዳም የተወሰኑ መሳፍንትን ማርከው አጋዙ (2ነገ 24፥1፤ 2ዜና 36፥6፤ ዳን 1፥1-3፡6)። ይህ በመጨረሻ ሁሉንም እስራኤላዊ ያዳረሰ ባቢሎናውያን የይሁዳን ምርኮ የጀመሩበት ወቅት ነው።

ኢዮአቄም ለባቢሎናውያን ያደረ ቸልተኛ መሪ ሲሆን፣ ሕዝቡን በስግብግብነት የመራ፣ የሙሴን ኪዳንና የአባቱንም ተሓድሶ የናቀ ሰው ነበር (ኤር 22፥13-17)። ለሦስት ዓመት ያህል ያለፈቃዱ ለናቡከደነፆር ከተገዛ በኋላ፣ ኢዮአቄም የኤርምያስን ማስጠንቀቂያ አልተቀበለም፤ ግብፅንም በመደገፍ በባቢሎን ላይ ዐመፀ (2ነገ 24፥1)። በ601 ዓቅክ በግብፅ የጦር ግንባር በባቢሎናውያንና በግብፅ መካከል የነበረው ጦርነትና ያለመሸናነፋቸው በመጠኑም ቢሆን ኢዮአቄምን አበረታታው። ዐመፅ ማካሄዱ ስሕተት ነበር፤ ምክንያቱም ናቡከደነፆር ሰራዊቱን እንደ ገና በማደራጀት በእርሱ ላይ በዐመፅ በተነሡት መንግሥታትና ግብር አንክፍልም ባሉት ላይ በበቀል ዘምቶ ነበር።

በታኅሣሥ በ598 ዓቅክ ባቢሎናውያን ይሁዳን መውጋት በጀመሩበት ወር ኢዮአቄም ሞተ። ዮአኪን የተባለው የዐሥራ ስምንት ዓመት ልጁ ዙፋኑን ቢወርስም እንኳ (2ነገ 24፥8)፣ ከሦስት ወር በኋላ የኢየሩሳሌምን ከተማ ለናቡከደነፆር ከማስረከብ በቀር ሌላ ነገር ማድረግ አልቻለም። ዮአኪንን፣ እናቱን፣ ሚስቶቹን፣ መኳንንቱንና፣ የምድሪቱንም ዋና ዋና ሰዎች እንዲሁም (2ነገ 24፥12-16) ሕዝቅኤልን (ካህን፣ ሕዝ 1፥1-3) ጨምሮ እነዚህ ሁሉ ተማርከው ወደ ባቢሎን ተወሰዱ። የዮአኪን አጎት ሴዴቅያስ በይሁዳ ላይ እንደራሴ እንዲሆን ናቡከደነፆር ሾመው። በግዞት ላይ ቢሆንም እንኳ በባቢሎን በቁፋሮ የተገኙት የአስተዳደር መዛግብት እንደሚያመለክቱት፣ በባቢሎን ዘንድ፣ የይሁዳ ንጉሥ እንደ ሆነ የሚታወቀው አሁንም ዮአኪን ነበረ።

የናቡከደነፆር ኀይል በቅርቡ እንደሚሰበርና ምርኮኞችም በድል አድራጊነት እንደሚመለሱ የሐሰት ነቢያት በተናገሩት መልእክት በመደገፍ፣ የዳግማዊ ፈርዖን ሰሜቲክ (594-588 ዓቅክ) እና የአፕሪስ (588-568 ዓቅክ) ኀይል የተጠናከረ መስሎ በመታየቱ በመታመል፣ ወላዋይ በነበረው በዘካርያስ ሐሳብ ላይ በመደገፍና ብሔራዊ ነጻነት ይመለሳል በሚለው ተስፋ ላይ በመጣበቅ ንጉሡ እንደ ገና በናቡከደነፆር ላይ እንዲያምፅ ተገፋፉ። የባቢሎን ምላሽ ፈጣን ነበረ። በ588 ዓቅክ መጀመሪያ ላይ የባቢሎን ሰራዊት ኢየሩሳሌምን ከበበ (2ነገ 25፥1፤ ኤር 32፥1-2)፤ ይህም የሆነው ቀደም ብሎ የይሁዳን ተራራማ አገር የተመሸጉ ከተሞች ከደመሰሰ በኋላ ነበር (ይህም በለኪሶ ደብዳቤ ላይ በግልጽ ተቀምጦአል)። በ586 ዓቅክ ማብቂያ ላይ ኢየሩሳሌም ተደመሰሰች፤ ሴዴቅያስም ተይዞ ወንዶች ልጆቹን እያያቸው እንዲገደሉ ከተደረገ በኋላ ዐይኑ እንዲጠፋ ሆነ፤ አያሌ የኢየሩሳሌም ነዋሪዎችም በባቢሎናውያን ተገደሉ፤ ሌሎቹም ወደ ባቢሎን ተግዘው ተወሰዱ (2ነገ 25፥2-21፤ ኤር 52፥5-27)። ይሁዳም ወደቀች።

ዓለም ዐቀፋዊ ነውጥና አለመረጋጋት በነበረበት በዚህ ዘመን፣ በይሁዳም ኢግብረባዊ ሁኔታና ክሕደት በአንድ ላይ በነበረበት በዚህ ወቅት ሕዝቅኤል ያገለግል ነበር። ኢዮስያስ

ተሐድሶን ባመጣበት ዘመን ያደገውና አሁን ደግሞ በ597 ዓቅክ ዮአኪን በተጋዘበት ዘመን እርሱም ዐብሮ በምርኮ የተወሰደው ሕዝቅኤል በግዞት ላሉት አይሁድ የእግዚአብሔርን ፍርድና የመጨረሻውን ባርኮት ዐወጀላቸው።

ቀጥሎ ያለው ቢጋር በይሁዳ፣ በግብፅና በባቢሎን ነገሥታት መካከል የነበረውን የትውልድና የጊዜን ግንኙነት በግልጽ ያሳየናል፦

1. የይሁዳ ነገሥታት

   ኢዮስያስ (640-609 ዓቅክ)

   ኢዮአካዝ (የኢዮስያስ ሁለተኛ ወንድ ልጅ - 609 ዓቅክ)

   ኢዮአቄም (የኢዮስያስ የመጀመሪያ ወንድ ልጅ - 609 - 597 ዓቅክ)

   ዮአኪን (የኢዮአቄም ወንድ ልጅ 597 ዓቅክ)

   ሴዴቅያስ (የኢዮስያስ የመጨረሻ ወንድ ልጅ እንደራሴ 597-586 ዓቅክ)

   ኢየሩሳሌም ተደመሰሰች (586 ዓቅክ)

2. የግብፅ ነገሥታት

   ቀዳማዊ ሳሜቲክ (664-609 ዓቅክ)

   ኒካዑ (609 - 594 ዓቅክ)

   ዳግማዊ ሳሜቲክ (594 - 588 ዓቅክ)

   አፕሪስ (ሐፍራ) (588 - 568 ዓቅክ)

3. የዐዲሲቱ ባቢሎን ነገሥታት

   ናቦፓላሳር (626 - 605 ዓቅክ)

   ናቡከደነፆር (605 - 562 ዓቅክ)

2. ጸሓፊውና የተጻፈበት ዘመን

ሕዝቅኤል ሙሉውን መጽሐፍ መጻፉን በተመለከተ የሃያኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛው ኢጋማሽ ከመግባቱ በፊት ብርቱ ጥያቄ ቀርቦበት አያውቅም ነበር። ስለ መጽሐፉ አሐዳዊነት በቅርቡ ተቃውሞዎች የተሰነዘሩት የሰላ ሥነ ጽሑፋዊ ትንታኔን መሠረት በማድረግ ነበር። የሕዝቅኤል ራእይ እርሱ በባቢሎን ሳለ በኢየሩሳሌም ያሉትን ሁኔቶች እንዲያይ ቢያስችለውም እንኳ፣ ይዘትን ከመለወጥና ስልታዊ፣ መልክአ ምድራዊና ታሪክ ነክ ተቃውሞዎችን ከማዘጋጀት ይልቅ፣ ትውፊታዊ የሆነውን አሐዳዊነት በመቀበል ረገድ ያለው የሕዝቅኤል መጽሐፍ ችግር አነስተኛ ነው። አቀራረቡና ይዘቱ ቋሚ ነው። አንዳንዶች መጽሐፉ የተጻፈው በፖለስቲና አካባቢ እንደ ሆነ ያስባሉ።

ሕዝቅኤል እንዳደረገው በብሉይ ኪዳን ጥቂት መጻሕፍት በትውልድና በጊዜ ላይ ትልቅ ትኩረት አድርገዋል። በምዕራፍ አንድ ውስጥ ያሉት የመጀመሪያዎቹ ሦስት ቁጥሮች የትውልድንና የጊዜን አቀማመጥ ለማሳየት፣ ዮአኪን በ597 ዓቅክ ተማርኮ የሄደበትን ጊዜ በመጥቀስ መጽሐፉ የተጻፈበትን ጊዜ ገልጠዋል። የመጀመሪያው ትንቢታዊ መልእክት የመጣበት ጊዜ "ንጉሡ ዮአኪን በተማረከ በዐምስተኛው ዓመት" (1፥2 ይኸውም 593 ዓቅክ) በሚል ሲገለጽ፣ የመጨረሻው መልእክት (29፥17-30፥19) "በሃያ ሰባተኛው ዓመት" (571 ዓቅክ) በሚል ተገልጾአል። መጽሐፉ ዐሥራ ሦስት ትውልድንና ጊዜን የሚያመለክቱ ማስታወሻዎችን ይዞአል። በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ላይ የሚመጣውን ፍርድና የፍርዱንም መሠረታዊ ምክንያት የሚገልጹት ከምዕራፍ 1-24 ያሉት ክፍሎች የሚያመለክቱት ጊዜ ከ593-589 ዓቅክ ነው (1፥1-3፤ 8፥1፤ 20፥1፤ 24፥1)። ስለ ባዕድ አገሮች ከምዕራፍ 25-32 የተነገሩት ትንቢቶች የሚያመለክቱት ጊዜ ከ587-585 ዓቅክ (26፥1፤ 29፥1፤ 30፥20፤ 31፥1፤ 32፥1:17) ያለውን ሲሆን፣ ይህም ከ29፥17-30፥19 በቀር ማለት ነው። በምዕራፍ 33-48 ላይ ያሉት የበረከትና የተስፋ መልእክቶች የተላለፉት ከ585-573 ዓቅክ (33፥21፤ 40፥1) ባሉት ጊዜያት ነው።

3. የተጻፈበት ቦታና የተጻፈላቸው ሰዎች (ተደራሲያኑ)

በሕዝቅኤል 1፥1-3 እና 3፥15 ላይ በግልጽ ሕዝቅኤል ያገለገበት ቦታ ባቢሎን በተለይም በኮቦር ወንዝና በጥንታዊቷ ኒፑር አጠገብ ባለችው በቴል አቢብ ነበር። ብዙዎች ይህን "ወንዝ" የኤፍራጥስን ወንዝ ሁለት ጫፎች የሚያገናኘው በስተ ደቡብ ምሥራቅ ያለው ክብ የሚሠራው ቦይ ነው ይላሉ።

በባቢሎን በምርኮ የነበሩት አይሁድ ሁኔታ ይህን ያህል አስከፊ አልነበረም። በአንድ በተወሰነ ቴል አቢብ በተባለ ስፍራ እንዲቀመጡ ቢደረጉም እንኳ፣ በአገሪቱ ውስጥ በነጻነት እንዲንቀሳቀሱና የንግድ ልውውጥም እንዲያደርጉ አጋጣሚው ነበራቸው። እንደ ባሮች ሳይሆን፣ እንደ ቅኝ ተገዢዎች ነበር የሚቈጠሩት።

የሕዝቅኤል መልእክት በመሠረቱ ለእነዚሁ ምርኮኞች ነበር። ኢየሩሳሌምንና ይሁዳን ወደ መጨረሻው መፈራረስ እንዲያመሩ ያደረጓቸውን ርኩሰቶች አወገዘ። ምርኮኞቹ ሕዝቅኤል ባቀረባቸው ትንቢታዊ መልእክቶች ላይ ጥያቄ አቅርበዋል፤ እርሱም በጥንቃቄ መልሶላቸዋል። ራሱን እንደ ጉበኛ በማድረግ በይሁዳ ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶአል፤ ደግሞም በእስራኤል ምድር በመጨረሻ ተመልሰው የሚኖሩ መሆናቸውን የሚያሳዩ የተስፋ ቃሎችን ነግሮአቸዋል። በአንዳንዶቹ የሕዝቅኤል ራእዮች (ምዕ 8 እና 11) ወደ ኢየሩሳሌም የተወሰደ ቢሆንም፣ መልእክቶቹ በፖለስቲና ለሚኖሩ አይሁድ ሲባል በቀጥታ አልተሰጡም ነበር። በባቢሎንና በኢየሩሳሌም መካከል ያለው ርቀት እነዚህ መልእክቶች ወደ ኢየሩሳሌም እንዲያተኩሩ ባያደርግም፤ አንዳንዶቹ የሕዝቅኤል ሐሳቦች ተጣርተው ዞረው ዞረው የሚያመክቱት ፖለስቲናን ነው። በሕዝቅኤል ዘመን የነበረው ኤርምያስም በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ለቀሩት አይሁድ ተመሳሳይ የሆነ የማስጠንቀቂያና የፍርድ መልእክት አስተላልፎአል።

4. የተጻፈበት ሁኔታና ዐላማው

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ሲፈጥር ሕጋቸው በመሆን ለጌታ እንዲኖሩ መኖር እንደሚገባቸው የሚነግራቸውን የሙሴን ኪዳን (ዘፀ 20 - ዘኍ 9፤ ዘዳገም) ለሕዝቡ ሰጠ። ሕጉ የተሰጣቸው ለዕብራውያን ሸክም እንዲሆንባቸው አልነበረም፤ ይባረኩ ዘንድ (ዘዳ 5፥28-33) ለጥቅማቸው የተሰጠ ነበር እንጂ (ዘዳ 10፥12-13)።

ይሁን እንጂ የእስራኤል ታሪክ በጉልሕ የሚታወቀው እስራኤላውያን ለዚህ ኪዳን ባለመታዘዛቸው ነበር። ብዙውን ጊዜ ሕዝቡ በዙሪያቸው የነበሩትን ሕዘቦች አማልክት ይከተሉ ነበር። ከላይ የተጠቀሰው ታሪካዊ ንድፍ እንደሚያመለክተው፣ የእስራኤልና የይሁዳ መንግሥታት ርኩሰታቸውን እያደር ጨመሩ፤ በመጨረሻም የተሰጣቸውን ሕግ ረሱ። በሥርዐቱና በትእዛዛቱ ከተገለጠው ከጌታ መንገድ ሕዝቡ ቢወጡ፣ እነርሱን ወደ እርሱ ይመለስቸው ዘንድ፣ በመበታተን እንደሚቀጣቸው ኪዳኑ ራሱ አስጠንቅቆአል።

ሕዝቅኤል በእርሱ ዘመን ለነበሩት ሰዎች የእግዚአብሔርን ታማኝነት፣ ቅድስናና ክብር በመግለጥ ነገራቸው። የእስራኤል አምላክ ብቻውን እውነተኛ አምላክ እንደ ሆነ ሰዎች ሁሉ ያውቁ ዘንድ አምላካቸው ፍርድን፣ መንጻትንና የመጨረሻ በረከትን ያመጣል። እግዚአብሔር የእስራኤል ምርኮኞች ከነጢአተኛ መንገዳቸው ዘወር እንዲሉና ወደ እርሱ እንዲመለሱ አጥብቆ ይሻል። ስለዚህ የእርሱ ፍርድ እነርሱ ርኩሰታቸውን እንዲመለከቱና እርሱም ለኪዳኑ ያለውን ታማኝነት እንዲረዱ ለማድረግ የሚጠቀምበት የፍቅር መሣሪያው ነው። በርግጥ እርሱ በሕዝቡ ላይ ለመፍርድና ሕዝቡን ለመባረክ የገባውን የተስፋ ቃል ለመፈጸም ታማኝ ነው። የኢየሩሳሌም ከተማ መደምሰስ በኪዳኑ ውስጥ እንደ ተገለጠው (ከዘሌ 26 እና ከዘዳ 28-30 ጋር ያነጻ) እግዚአብሔር ለቅዱስ ባሕርይ ያለውን ታማኝነት ያሳያል። በሌላ በኩል ሕዝቡን ሊመራ እውነተኛው እረኛ፣ መሲሑ አንድ ቀን እንደሚመጣ ተስፋ ሰጥቶአል። በጊዜው የነበሩት መሪዎቻቸው ቢበዘብዙአቸውና ከጌታም መንገድ ቢያርቁአቸውም እንኳ፣ ወደፊት ጻድቅ በሆነ መሪ ሕዝቡ ወደ ተስፋዪቱ ምድር ይመለሳሉ (ዘፍ 12፥7)። በዚያ ቀን ሁሉም የጌታ ኪዳኖች ለሕዝቡ ይፈጸማሉ (ሕዝ 37፥24-28)።

ሕዝቅኤል የእስራኤል ጉበኛ እንደመሆኑ መጠን ሊመጣ ስላለው ፍርድ ሕዝቡን በማስጠንቀቅ፣ በእግዚአብሔር ፊት በግል በኀላፊነት፣ በአገር ደረጃም በተጠያቂነት እንደሚያስቆም በአጽንዖት ተናግሮአል። እያንዳንዱ እስራኤላዊ በግሉ ወደ እግዚአብሔር መመለስ ነበረበት። እንደዚሁም መላው ሕዝብ በመጨረሻ ወደ እርሱ መመለስ ይኖርበታል።

5. ነገረ መለኮታዊ ፋይዳዎች

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባሉት ትንቢታውያን ገጾች ውስጥ ዐምስት ጕልተው የወጡ ነገረ መለኮታውያን ሐሳቦች ተሠራጭተው ይገኛሉ፡- (1) የእግዚአብሔር ባሕርይ፣ (2) የእግዚአብሔር ፍርድ ዐላማና ባሕርይ፣ (3) የግል ኀላፊነት፣ (4) የእስራኤል ሥነ ምግባራዊ፣ ሃይማኖታዊና ግብረ ገባዊ ታሪክ እና (5) የእስራኤል እንደ ገና የመቋቋም ባሕርይና የሺሁ ዘመን አምልኮ።

(1) በአብዛኛው ጠንከር ብለው በአጽንዖት የተገለጹት የእግዚአብሔር ባሕርያት ከኪዳኑ ተስፋ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናቸው። ጻድቅና ቅዱስ የሆነው እግዚአብሔር ለሕዝቡ መልካም ይሆንላቸው ዘንድ ጽድቅ የሞላበትን የሕይወት መንገድ አበጅቶላቸው ነበር። ኪዳኑ የሚጠይቀውን ማናቸውንም ነገር በመከተል ቢፈጽሙ፣ በማናቸውም መንፈሳዊና ሥጋዊ መንገድ ይባረካሉ (ዘሌ 26፥3-13፤ ዘዳ 28፥1-14)። በእግዚአብሔር ጽድቅ ሥርዐቶች ላይ ቢያምፁና ባይታዘዙአቸው፣ እግዚአብሔር ቅዱስ፣ ፍትሓዊና ጻድቅ ስለ ሆነ ሕዝቡን ይቀጣል፤ በረከቱንም ይከለክላቸዋል (ዘሌ 26፥14-39፤ ዘዳ 28፥15-68)። ለእነዚህ የተስፋ ቃሎች እግዚአብሔር ያለውን ታማኝነት ሕዝቅኤል አጉልቶ አሳይቶአል። ሕጉን በመጣሳቸው እግዚአብሔር በእስራኤልና በይሁዳ ላይ ፈርዶአል፤ ይሁን እንጂ እርሱ ሕዝቡን በታማኝነት በበረከት ምድር መልሶ ያቋቁማል፤ የአብርሃም፣ የዳዊት የዐዲሱ ኪዳን የሆኑትን መሲሓውያን በረከቶችንም ያወርሳቸዋል (ዘሌ 26፥40-45፤ ዘዳ 30 ይመ፤ ከዘፍ 12፥1-3፤ ከ2ሳሙ 7፥12-17፤ ከኤር 31፥31-34 ጋር ያነጻ)።

(2) የእግዚአብሔር ባሕርይ አሳማኝ በሆነ መንገድ ፍርዱን ያንጸባርቃል። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ወደደ፤ ዓለምንም በእነርሱ በኩል ሊባርክ የራሱ ሕዝብ አድርጎ መረጣቸው (ዘፍ 12፥2-3፤ ዘፀ 19፥4-6፤ ዘዳ 7፥6-11)። ከእርሱ የጽድቅ መንገድ ሲርቁበት፣ ክፋታቸውን ዐውቀው ወደ እርሱ ዘወር እንዲሉ እግዚአብሔር ፍርድን አመጣባቸው። የእግዚአብሔር የፍርድ ዐላማ እስራኤልም ሆኑ አሕዛብ በዚህ መጽሐፍ ላይ ስድሳ ዐምስት ጊዜ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ እንዲያውቁ በማለት በተደጋጋሚ በተገለጸው ሐረግ መሠረት እርሱን እንዲያውቁ መሆኑን ሕዝቅኤል ያለማቋረጥ ዐውጆአል። ፍርድ መምጣቱ ለእስራኤል ጥቅም ነበር፤ ምክንያቱም ውጤቱ ወደ እርሱ እንዲመለሱና እርሱ ብቻ እውነተኛ አምላክ መሆኑ እንዲያውቁ ስለሚያደርግ ነው።

(3) እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር በአብዛኛው የተነጋገረ ቢሆንም፣ ሕዝቅኤል የመልእክቱን ሚዛን በመጠበቅ ከግል ኀላፊነት ጋር በማያያዝ በአጽንዖት ገልጾታል (ከዘዳ 24፥16፤ 29፥17-21 ጋር ያነጻ)። አንድ ሰው በብዙኃኑ ጽድቅ ወይም በሌላው ሰው መንፈሳዊነት ከእግዚአብሔር ርግማን ማምለጥ አልቻለም ነበር። እያንዳንዱ ሰው በእግዚአብሔር ፊት በግሉ ተጠያቂ ነበር። እያንዳንዱ ሰው በእርሱ ፊት በጽድቅ ይኖር ዘንድ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ሕጎች መታዘዝ ይኖርበታል። እያንዳንዱ ሰው ስለ ፈጸመው ርኩሰትና አለመታዘዝ በግሉ ተጠያቂ ነው። ስለዚህ ሕዝቅኤል ምርኮኞቹ በሙሴ ኪዳን መሠረት (ምዕራፍ 18፤23) ከክፉ መንገዶቻቸው ተመልሰው በጽድቅ እንዲኖሩ አጥብቆ መከራቸው።

(4) በዚህ ትንቢት ውስጥ ከተነገረው ከእግዚአብሔር ፍርድ ጋር የእስራኤልን ሥነ ምግባራዊ፣ ግብረ ገባዊና ሃይማኖታዊ ታሪክ በማስታወስ ሕዝቅኤል የእግዚአብሔር ጻድቅ ፍትሓዊነት እንከን የሌለበት መሆኑን አመልክቶአል። ይህም በግልጽ የታየው እስራኤል መንፈሳዊ አመንዝራ በመሆን ባሳየችው ነገር ነው፤ ይኸውም በእግዚአብሔር ተወድዳና ከእርሱም ጋር ተጋብታ ሳለ በመላው ታሪክዋ ውስጥ የሌሎች አሕዛብ አማልክትን በመከተል ራሷን አመንዝራ በማድረጓ ነው። ይህ የጣዖት አምልኮና ያለመታመን ሁኔታ በግብፅ ከተወለደችበት ጊዜ ጀምሮ ሲታይ የነበረ ባሕርይዋ ነው።

(5) እስራኤል ባለማቋረጥ በጣዖት አምልኮዋ ብትቀጥልም እግዚአብሔር በነቢዩ በኩል የተስፋ መልእክትን ሰጥቶአታል። በመጨረሻው ዘመን እስራኤል በፍልስጥኤም ምድር መልሳ እንደምትቋቋም ከተነገሩት ፍጹም ዝርዝሮች ውስጥ በአንዱ በተስፋ መልእክቶች ውስጥ ተሰጥቶአል (33፥21-39፥29)፤ ይኸውም በተስፋዪቱ ምድር ውስጥ የእስራኤል መልሶ መቋቋም እውን የሚሆንበትን መሠረት፣ ሁኔታና ውጤቶችን በግልጽ የሚናገረው ክፍል ነው። ልክ እንደዚሁ ከ40 -48 ምዕራፎች ባለው ክፍል በሺሁ ዘመን የሚኖረው የአምልኮ ሥርዐት ምን እንደሚመስል ሙሉ በሙሉ በዝርዝር ተገልጾአል። ስለ ሥነ ፍጻሜ የሚያጠና ማንም እነዚህን የትንቢተ ሕዝቅኤል መጽሐፍ ክፍሎች በሚገባ ማወቅ ይኖርበታል።

ትንተና

፩. የሕዝቅኤል ተልእኮ (1፥1-3፥27)

ሀ. የእግዚአብሔር ክብር ራእይ (1፥1-28)

1. የራእዩ መቼት (1፥1-3)

1-3 በአሦራውያንና በባቢሎናውያን ዘመን የተከሠተው የሚስጴጦምያ ሕልም-ራእይ መቼት አራት ክፍሎችን ያካተተ ነው፤ እነርሱም የታየበት ዘመን፣ የታየበት ቦታ፣ ተቀባዩ ሰውና ሁኔታዎች ናቸው። ሕዝቅኤል እነዚህን አራት ገጽታዎች በራእዩ ውስጥ አካትቶአል።

የዚህ ራእይ ጊዜ በሁለት የተለያዩ መንገዶች ተገልጾአል፤ እነርሱም "በሠላሳኛው ዓመት፣ በአራተኛው ወር፣ በዐምስተኛው ቀን" የሚልና "ንጉሡ ዮአኪን በተማረከ በዐምስተኛው ዓመት፣ በዐምስተኛው ወር" በሚል የተገለጹ ናቸው። "ሠላሳኛው ዓመት" የሚለው ምናልባት ከሕዝቅኤል ዕድሜ ጋር የተያያዘ ሳይሆን አይቀርም። ያለፉ የግል ማስታወሻዎች በሚነገሩበት ጊዜ በሰው ዕድሜ መሠረት ማቅረብ ያልተለመደ አሠራር አልነበረም (ከዘፍ 8፥13 ጋር ያነጻ)። በተጨማሪም ሕዝቅኤል ካህን ሲሆን፣ አንድ ሰው ወደ ክህነት አገልግሎቱም የሚገባው በሠላሳ ዓመት ዕድሜው ነበር (ዘኍ 4፥3:23:30:39:43፤ 1ዜና 23፥3)። ስለዚህ ሕዝቅኤል ይህንን ራእይና ተልእኮ በግልጽ የተቀበለው የክህነት አገልግሎቱን በጀመረበት በመጀመሪያው ዓመት ነበር።

የሕዝቅኤል ሠላሳ ዓመት ንጉሡ ዮአኪን ከተማረከበት ከዐምስተኛው ዓመት ጋር የተያያዘ ነው። በቁ 1 ላይ በግልጽ ከሰፈረው አረፍተ ነገር መረዳት እንደሚቻለው ወር የሚለው (ይኸውም አራተኛ ወር) መሆኑ ግልጽ ነው። ዮአኪን ወደ ባቢሎን የተጋዘበት ጊዜ 597 ዓቅክ ስለ ሆነ፣ ሕዝቅኤል ተልእኮውን የተቀበለበት ጊዜ 593 ዓቅክ መሆን አለበት። ዮአኪን የተጋዘበት ዘመን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለተጠቀሱት ቀናት በሙሉ መነሻ መሠረት ነው።

ሕዝቅኤል ይህን ራእይ የተቀበለው "በባቢሎን ምድር በኮበር ወንዝ አጠገብ" ነበር። የኮበር ወንዝ ከባቢሎን ከተማ ወደ ደቡብ ምሥራቅ የሚፈስ ጀልባዎች የሚመላለሱበት ወንዝ ነው።

ሕዝቅኤል ራእዩን እንደ ተቀበለ በግልጽ ተነግሮአል። እርሱም ካህንና ቡዝ የተባለ ሰው ልጅ ነበር። ስለ ቡዝ የተነገረ ምንም ነገር ባይኖርም የሕዝቅኤል አባት እንደ መሆኑ እርሱም ካህን ሳይሆን አይቀርም። ሕዝቅኤል ካህን መሆኑ መነገሩ ወሳኝ ጕዳይ ነው። የዚህን መጽሐፍ ሙሉ መልእክት የሚሸፍኑትን ሁለቱን ማለት የሙሴን ኪዳንና በቤተ መቅደሱ ውስጥ የክህነት አገልግሎትን በሚገባ ያወቀ ሰው መሆን አለበት። ሕዝቅኤል በቤተ መቅደስ ውስጥ የእግዚአብሔርን ክብርና የቤተ መቅደሱን አገልግሎት ለመግለጽ ችሎ ነበር። ነቢዩ የተናገረው የጌታ ፍርድ መነሻ የሆነውን ይኸውም ሕዝቡ በግልጽ በተቀመጡት በሕጉ ትእዛዞች ላይ ያደረጉትን ዐመፅ በትክክል ለመመዘንም ተዘጋጅቶ ነበር። ከዚህም በላይ ይህ የክህነት መሠረት ሙሉውን ትንቢት የሚደመድመውን የሺህ ዘመን ቤተ መቅደስ ራእይ ለመረዳት ሕዝቅኤልን አስችሎታል።

በተከታታይ ለሚቀርበው ራእይ በዚህ መግቢያ ላይ የሚታዩት ብቸኛ ሁኔታዎች "የእግዚአብሔር ቃል ወደ ሕዝቅኤል መጣ" እና "የእግዚአብሔር እጅ በእርሱ ላይ ነበረች" የሚሉ ሐረጎች ነበሩ። እነዚህ ሐረጎች የሚከሠቱት ሕዝቅኤል የእግዚአብሔርን ራእይ ሊቀበል ወይም ሊናገር ሲል ነው (3፥22፤ 8፥1፤ 33፥22፤ 37፥1፤ 40፥1)። "የእግዚአብሔር እጅ በእርሱ ላይ ነበረች" ሲል፣ የሚያመለክተው በተጠቀሰው ሰው (3፥14) ምትክ የእግዚአብሔርን ብርቱነት ለመግለጽ ሲሆን፣ "ሕዝቅኤል" ("እግዚአብሔር ያበረታል ማለት ነው") በሚለው ስም ውስጥ ያለ ሐሳብ ነው። የቀረውን የትንቢት ክፍል መረዳት ይችል ዘንድ እግዚአብሔር ሕዝቅኤል ራእዩን መቀበል እንዲችል አስፈላጊ የሆኑትን መሠረታዊ ነገሮች በመስጠት እያዘጋጀው ነበር። የዚህን መጽሐፍ ትርጓሜ ለማወቅ "የእግዚአብሔርን ራእይ አየሁ" የሚለውን ሐረግ ልብ ማለት ይገባል፤ ይህ ቀጥሎ ያለውን የራእይ ባሕርይ ወዲያውኑ ይገልጻልና።

፪. የራእዩ ገለጻ (1፥4-28)

ሀ. ሕያዋን ፍጡራን (1፥4-14)

በነቢያቱ የተልእኮ አካሄድ ላይ አጠቃላይ የሆነ ሂደት ይታያል። የመጀመሪያው ከመለኮት ጋር ፊት ለፊት የመጋጠም ሁኔታ ነው፤ ይኸውም በመቀጠል ለሚመጣው ተልእኮ መሠረት የሚጥለውና መንገድ የሚያበጀው የመግቢያ ቃል ነው። ከዚያም ተልእኮው ራሱ ነቢዩ የተጠራበትን ሥራና የሥራውን አስፈላጊነት ያመለክተዋል። ሦስተኛው ነቢዩ የሚያቀርባቸው ተቃውሞዎች የቀረቡበት ነው፤ ከዚያም የጥሪው ትረካ በእግዚአብሔር ዋስትና መስጠት ይጠቃለላል፤ ይህም ዋስትና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ እንዲሁም እግዚአብሔር ከነቢዩ ጋር መሆኑን ዋስትናን የሚሰጥበት ነው። አራቱም መሠረታውያን ነገሮች በሕዝቅኤል ተልእኮ ውስጥ ይገኛሉ።

በእስራኤል ሕዝብ ላይ ፍርድን የሚያመጣውን አምላክ ያውቅ ዘንድ እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል በዚህ የከበረ ራእይ የተገለጠለት፣ የእርሱን ግርማዊነት፣ ቅድስና እና ድንቅ አድራጊነቱን እያሳየ በማስገረም ነበር። ሕዝቅኤል የእግዚአብሔርን ቅድስና ሲመለከት በፍርሀት ተሞላ። በራሱ ዘመን ለነበሩ ሰዎች የእግዚአብሔርን ፍርድ በመናገር ሕዝቅኤል አስቸጋሪ የሆነውን አገልግሎቱን በሚፈጽምበት በዚህ ጊዜ፣ ከአእምሮው የማይጠፋው በግጻዌ መለኮት መገለጥ የማያቋርጥ ማጽናናት በመሆን አገለገለው። በዚህ ስፍራ ከበሰተ ጀርባው ከተመለከተው አስፈሪ ከሆነው የእግዚአብሔር ቅድስና አንጻር፣ ሕዝቅኤል የእስራኤልን ርኩሰት ተመለከተ፤ እግዚአብሔር ኀጢአተኛ በሆነው ሕዝቡ ላይ ሊፈርድ ለምን እንደ ተነሣሣም ተረዳ። የይሁዳ ሕዝብ የተማረከው አምላካቸው ደካማ ስለ ሆነ ነው በማለት አሕዛብ እግዚአብሔርን ሲንቁ፣ ሕዝቅኤል ግን የእርሱ አምላክ ከባቢሎናውያን አማልክት እንደሚበልጥ ያውቅ ነበር። እግዚአብሔር በዚያን ወቅት ሕዝቡን መቅጣት ተገቢ መሆኑን ቢመርጥም፣ እስራኤልን በተስፋዱቱ ምድር መልሶ በሚያቋቁምበት ጊዜ በአሕዛብ ሁሉ ላይ ድል አድራጊ ይሆናል።

ይህ የከበረና ቃል ኪዳኑን የሚጠብቀው አምላክ በመጀመሪያ ራሱን ለእስራኤል በሲና ተራራ ተመሳሳይ በሆነ አስፈሪ ራእይ የተገለጠው እግዚአብሔር ነው (ዘፀ 19)። እንደ ገናም የመገናኛው ድንኳን በሚመረቅበት ጊዜ በቅድስተ ቅዱስን ውስጥ በክብሩ በማደሪያው ታየ (ዘፀ 24፥15-18፤ 29፥42-46፤ 40፥34-38)። ይህ ግጻዌ መለኮት የእስራኤልን ልጆች በምድረ በዳ መራቸው (ዘኍ 9፥15-23፤ 14፥10፤ 16፥19፤ 20፥6)፤ የሰሎሞንን ቤተ መቅደስ በክብሩ ሞላው (1ነገ 8፥10-11፤ 2ዜና 5፥14)፤ ኢሳይያስም ተልእኮውን በተቀበለ ጊዜ ተገለጠ (ኢሳ 6፥3)። አንዳንዶች የእግዚአብሔር ክብር መገለጥ በተመሳሳይ መንገድ ባለመሆኑ የሚደናገጡ ቢሆኑም፣ የእግዚአብሔርን ወሰን የለሽነት ለተረዳ ለማንም ሰው፣ እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ የመገለጡ ጉዳይ ሊሆን የሚችል ነው። ይሁን እንጂ ሕዝቅኤል ካህንና የእግዚአብሔር ቃል ተማሪ እንደመሆኑ መጠን ባለማቋረጥ የእግዚአብሔር ክብር እንደዚህ በመገለጡ፣ ነቢዩ ወዲያውኑ የእግዚአብሔር ክብር ራእይ መሆኑን ለመረዳት አልተቸገረም (ቍ 28)።

4-14 ይህ ራእይ የጀመረው "እኔም አየሁ፤ ስመለከትም" በሚለው በተለመደው የራእይ መግቢያ አካሄድ ነው። ሕዝቅኤል ድንገት ያየው ከሰሜን የሚመጣ የሚያስፈራ የማዕበል ኀይል ያለበትን ዐውሎ ነፋስ የሚመስል ነው፤ ይኸውም ጥቁር ደመና በታላቅ ብርሃን የተከበበ መብረቅ ነው። በዚህ ዐውሎ ነፋስ ውስጥ እርሱ የሚገልጻቸው ሕያዋን ፍጡራንን የሚመስሉ አራት ፍጥረታትን አየ (ከራእ 4 ጋር ያነጻ)። እነዚህ ፍጥረታት ሰው ቢመስሉም እያንዳንዳቸው አራት አራት ፊትና አራት አራት ክንፍ ነበራቸው። በእያንዳንዳቸው ፊት ያለው የሰው ፊት ጐልቶ የሚታይ ሲሆን፣ በቀኝ በኩል ያለው የአንበሳ ፊት፣ በግራ በኩልም የበሬ ፊት (ወይም የኪሩብ ፊት ከ10፥14:22 ጋር ያነጻ)፣ በጀርባ በኩልም የነበረው የንስር ፊት ነበረ።

ክንፎቹ በአንድ ላይ የተያያዙ ነበሩ (ቍ 9:23)፤ እያንዳንዳቸው ሰውነታቸውን በሁለቱ ክንፎቻቸው ሲሸፍኑ፣ በሁለቱ ክንፎቻቸው ለመንቀሳቀስ ወደ ላይ ይዘረጉ፣ የእያንዳንዱም ክንፍ የሌላውን ክንፍ ይነካ ነበር (ቍ 11:23)። ክንፎቻቸው ሲንቀሳቀሱ ድምፃቸው እንደሚጮርፍ ውሃ ጩኸት፣ እንደ ከባድ ነጐድጓዳማ ዝናም ወይም እንደ ታላቅ ሰራዊት ውካታ ማለትም ልክ "ሁሉን ቻይ እንደ ሆነው አምላክ" ድምፅ ነበረ። በአራቱ ጐኖቻቸው ባሉት ክንፎቻቸው ሥር የሰውን የሚመስሉ እጆች ነበሩአቸው፤ ቀጥ ያሉ እግሮችና እንደ ጥጃ ያለ እግር ነበሯቸው።

የእነዚህ ሕያዋን ፍጥረታት ፈጣን እንቅስቃሴ እንደ መብረቅ ብልጭታ ነበረ። ወደ ፊት ሲሄዱ የሚንቀሳቀሱበት አቅጣጫ የሰው ፊት የሚመስለው ባለበት በኩል ነው። ሲንቀሳቀሱ ወደ ኋላ ዘወር አይሉም። እነዚህ ፍጥረታት "መንፈስ" (ቍ 12) ወደሚሄድበት ሁሉ ይሄዱ ነበር፤ ይህ መንፈስ በዚህ በእግዚአብሔር ክብር ዐውድ ውስጥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው።

ደማቅ ብርሃን ከሚታይበት ከዚህ አጠቃላይ ገጽታ በተጨማሪ፣ እነዚህ ፍጥረታት በመካከላቸው መብረቅ የሚወጣበት የከሰል ፍምና የተቀጣጠለ ችቦ የሚመስል መልክ ነበራቸው። እነዚህ ሕያዋን ፍጥረታት በ10፥15:20 ኪሩቤል በመባል ተጠርተዋል። በርግጥ ሕዝቅኤል በቤተ መቅደስ ውስጥ ከነበረው ሥልጠና የተነሣ ኪሩቤልን ከእነዚህ ፍጥረታት ጋር ካላቸው ተመሳሳይ ብዙ ገጽታ ጋር (ዘፀ 25-26፤ 36-37፤ 1ነገ6፤ 2ዜና 3) እንዲሁም ከመስጴጦምያ ባህል አንጻር ኪሩቤል በቤተ መቅደስ ውስጥ እንደ ጠበቂ መናፍስት ስለሚያገለግሉበት ሁኔታ ያውቃል። ኪሩቤል አብዛኛውን ጊዜ በብሉይ ኪዳን ከእግዚአብሔር ክብር ጋር የተያያዙ ናቸው፤ ይሁን እንጂ የተለየ አገልግሎታቸው በየትኛውም ስፍራ በግልጽ አልቀረበም።

ለ. መንኰራኵሮቹና እንቅስቃሴአቸው (1፥15-21)

15-18 አራት ፊቶች ባሉት በእያንዳንዱ ፍጡር አጠገብ አንዳንድ ከፍ ያለ አስፈሪ መንኰራኵር በአጠቃላይ መልኩ እንደ "ቢረሌ" የሚያንጸባርቅና የእያንዳንዱም መንኰራኵር ክብ ጠርዝ ዙሪያውን በዐይኖች የተሞላ ነበር (ከራእ 4፥6 ጋር ያነጻ)።

19-21 እነዚህ መንኰራኵሮች ሲንቀሳቀሱ፣ አንዱ መንኰራኵር በሌላው መንኰራኵር ተሰክቶ የተሠራ ይመስል ነበር። መንኰራኵሮቹ ከሕያዋን ፍጡራኑ ጋር ተቀናጅተው ይነቀሳቀሱ ነበር፤ ከምድር ወደ ላይ ከፍ ከፍ ማለት ቢሆን ወይም ቀጥ ብሎ መቆም ቢሆን፣ በየትኛውም አቅጣጫ ዐብረው ይንቀሳቀሳሉ። ማንኛውም እንቅስቃሴ በ"መንፈስ" ምሪት ቍጥጥር የሚደረግ ነበረ። በምዕራፍ 3 እና በምዕራፍ 10 ላይ መንኰራኵሮቹ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ስለማያሰሙት የህምህምታ ድምፅ በዝርዝር ይበልጥ ተገልጸአል (3፥12-13፤ 10፥5:13)።

ሐ. ጠፈር የሚመስለው ነገር (1፥22-28)

22-28 ከሕያዋን ፍጡራኑ ራስ በላይ የሚያስፈራና እንደ በረዶ የሚያንጸባርቅ ጠፈር የሚመስል ነገር ከላይ ተንጣልሎ ነበር (ከራእ 4፥6 ጋር ያነጻ)። ከራሳቸው በላይ ካለው ጠፈር ከፍ ብሎ በከበረ ላፒስ ላዙሊ የተሠራ (ሰንፔር በቍ. 26 ላይ ያለውን የዐመት ማስታወሻ ይመ) የሚመስል ዙፋን ነበረ፤

በዙፋኑም ላይ የሰው መልክ የሚመስል ነበር (ከዘፀ 24፥10፤ ከራእ 4፥2 ጋር ያነጻ)። ይህ ሰው የቀስተ ደመናን ጻዳል በመሰለ ነገር በእሳት የተከበበ መልክ ነበረው (ከ8፥2 ከዳን 10፥6፤ ከራእ 4፥3፡5 ጋር ያነጻ)።

የሙሉው ምዕራፍ ዋና ሐረግ፣ "ይህም የእግዚአብሔር ክብር መልክ አምሳያ ነበረ" የሚለው የመጨረሻው ጥቅስ ነው። ይህ መግለጫ በቀጥታ ይበልጡኑ የሚገናኘው በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠው የሰው መልክ የሚመስል ካለው ጋር ነው፤ ነገር ግን ዘፀ 19፤ 1ነገ 6፤ ኢሳ 6፤ ዳን 10 እና ራእ 4 የሚያረጋግጡት በአጠቃላይ ራእዩ የእግዚአብሔር ክብር መገለጫ እንደ ሆነ ነው (ከቊ 1 ጋር ያነጻ)። እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል የእርሱን ውብና ማራኪ ማንነት የገለጠለት ለአገልግሎቱ ሊያዘጋጀው ነው። በመጽሐፉ ውስጥ በአጠቃላይ በዚሁ ገጽታ በተከታታይ ለሕዝቅኤል የተገለጠለት የሁሉን ቻይ እግዚአብሔር አገልጋይ መሆኑን በማሳወቅ ሊያበረታታው ነው። በርግጥ አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ክብር ሲያይ ምንም ማድረግ አይችልም፤ ነገር ግን ሕዝቅኤል እንዳደረገው በሁሉን ቻይ እግዚአብሔር ፊት በአምልኮ በግንባሩ ይደፋል።

ይህ የእግዚአብሔር ክብር መገለጫ፤ ሕዝቅኤል ለሚናገረው የፍርድ ቃል አጠቃላይ ዳራ ነው። ከጻድቅ ባሕርዩ የተነሣ የሙሴን ኪዳን የሰጠው ክቡርና ቅዱስ የሆነው አምላክ (ዘፀ 19) ያን ኪዳን አለመታዘዝ መታገሥ ባለመቻሉ፣ ቅዱስ ባሕርዩ በማይታገሠው ኀጢአት ላይ መፍረድ አለበት። ስለዚህ እግዚአብሔር ፍርድን በኢየሩሳሌም ላይ ሲያመጣ፣ ክብሩ በቤተ መቅደስ ካለው ማደሪያው መነሣት ይኖርበታል (10፥1-20፤ 11፥22-23)። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ሕዝብ መንጻት ከተፈጸመ በኋላ የእግዚአብሔር ክብር ሲመለስ ሕዝቅኤል አየ (ከምዕ 43 ጋር ያነጻ)። ስለዚህ በመጽሐፉ ውስጥ የዐላማ ወጥነትን በማሳየት የእግዚአብሔር ክብር መገለጥ በትንቢቱ ውስጥ በአጠቃላይ የሚታይ ዋና ፍሬ ሐሳብ ነው።

ለ. ለሕዝቅኤል የመጣለት የእግዚአብሔር ጥሪ (2፥1-3፥27)

1. የሕዝቅኤል አገልግሎት ተቀባዮች (2፥1-5)

1-2 የእግዚአብሔር ድምፅ ከግጻዌ መለኮት ወደ ሕዝቅኤል የተላለፈው "የሰው ልጅ" በሚለው አድራሻ ነው። በቀረው የመጽሐፉ ክፍል ውስጥ ይህ የሕዝቅኤል የተለመደ መጠሪያው በመሆን ሲያገለግል ይታያል (ከ90 ጊዜ በላይ ውሎ ይገኛል)፤ ይህ አገላለጽ በዳን 7፥13፤ 8፥17 ላይ ካልሆነ በቀር በሌላው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ላይ አይገኝም። ይህ ስያሜ በኃያሉና በአስፈሪው እግዚአብሔር ፊት የተዋረደውን የሰውን ወገን ተሰባሪነትና ደካማነት ያሳያል። በዚህ ማዕረግ ሕዝቅኤል የሚረዳው የእግዚአብሔርን መልእክት ለመቀበል የሚያስችለውና መልእክቱንም የሚያስተላልፈው በእግዚአብሔር ኀይልና ሥልጣን መሆኑን በማወቅ ሳያቋርጥ ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር መንፈስ እንዲደገፍ ነው፤ ይኸውም "ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል በላቸው" የሚለው ነው። ይህ ተመሳሳይ ስም ማለትም "የሰው ልጅ" የሚለው በወንጌሎች ላይ ለክርስቶስ ተሰጥቶ ነበር (ሉቃ 19፥10)፤ የተሰጠውም እርሱ ከሰው ልጆች ጋር ያለውን ግንኙነትና በፈቃደኝነት በእግዚአብሔር መንፈስ ላይ ያለውን መደገፍ በአጽንዖት ለመግለጽ ነው (በዳን 7፥13-14፤ በማር 8፥31 ላይ ያለውን ማብ ይመ)።

3-4 የሕዝቅኤል ጥሪ ትረካ በተለይም ስለ ተልእኮው የሚናገረው ክፍል በአብዛኛው ምዕ 2-3 የሚያጠቃልል ነው። እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እጅግ ከባድ ለሆነ ሥራ ተልእኮ ሊሰጠው ነው። በእርሱ፣ በሕጉ እንዲሁም መልእክተኞቹ በሆኑት ነቢያት ላይ እንዳመፁ እግዚአብሔር ራሱ በተናገረላቸው በምርኮ ወዳሉት ወደ ራሱ ሕዝብ ሊሄድ ነው። ይህ ሕዝብ በመላው በታሪኩ ውስጥ በሙሴ ኪዳን ላይ በማመፁ የታወቀ ስለ ሆነ፣ ይህ ዐዲስ ክሥተት አይደለም። እግዚአብሔር የመረጠው ሕዝብ "የማያምን" እና "እብሪተኛ" ነው (ቃል በቃል "ልበ ደንዳና" እና "ፊቱን ያጠነከረ")፤ ይኸውም እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን መንገዶች ለመቃወም የሚደረግ ብርቱ ጽናትን የሚገልጽ ነው። በርግጥም ለይሁዳ የቅርብ ዐመፅ ዋና ምክንያት የሆነው የሕዝቡን ልብ ያረከሰው የምናሴ ርኩሰት ነበር።

5 የሕዝቅኤል መልእክት በአድማጮቹ ምላሽ ላይ የተመሠረተ አይደለም። ሕዝቡ እርሱ ለሚናገረው ቃል ጆሮዎቻቸውን ቢዘጉም እንኳ፣ በራሱ ሳይሆን በእግዚአብሔር ሥልጣን መናገር ነበረበት። ይህ ሲሆን ብቻ ነው ሕዝቡ ነቢይ በመካከላቸው መኖሩን የሚያውቁት።

2. በአገልግሎቱ ውስጥ ሕዝቅኤል የተቀበለው መጽናናት (2፥6-7)

6-7 ሕዝቅኤል በተጠራበት አስቸጋሪ በሆነው የአገልግሎት ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር ያደፋፍረዋል። ተቃውሞው የቱንም ያህል አስፈሪ ማለትም እንደ እሾኽ ቢወጋውም ወይም እንደ ጊንጥ ቢነድፈውም ሕዝቅኤል መፍራት፣ መበሳጨትና ተስፋ መቁረጥ የለበትም። አድማጮቹ ማስጠንቀቂያ የሚያስፈልጋቸው ዐመፀኞች ስለ ሆኑ፣ በእንጻፋ እርሱ የእግዚአብሔርን መልእክት ለማወጅ ታማኝ መሆን ይኖርበታል። ይህ እውነት ጠማማና ርኩስ በሆነ ትውልድ መካከል የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ለመስበክ ለተጠሩ አሁንም የመጽናናት ምንጭ ይሆናል።

3. የሕዝቅኤል አገልግሎት ባሕርይ (2፥8-3፥11)

2፥8-3፥3 ሕዝቅኤል የእግዚአብሔር አፍ ሆኖ ከመሄዱ በፊት የእግዚአብሔርን መልእክት መስማት፣ ማስተዋልና ከሕይወቱ ጋር ማዛመድ እንደሚኖርበት እግዚአብሔር በአጽንዖት ይነግረዋል። ሕዝቅኤል ቃሉን ለመስማት እምቢ እንዳሉት የእስራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር ላይ ሳያምፅ እርሱን መስማት ይኖርበታል (2፥8ሀ)።

ሕዝቅኤል አገልግሎቱን ከመጀመሩ በፊት የእግዚአብሔርን መልእክት ፈጽሞ መቀበሉን በምሳሌ ለማሳየት የተሰጠውን ጥቅልል መጽሐፍ አፉን ከፍቶ መብላት ነበረበት። የሚናገረው መልእክት ባሕርይ በጥቅልሉ መጽሐፍ ላይ ተጽፎ ነበረ፤ የተጻፈውም የሰቈቃ፣ የልቅሶና የዋይታ ቃል ነበር። በርግጥ ይህ መልእክት አገልግሎትን ለመጀመር የሚያስችል የደስታ መልእክት አልነበረም። ነገር ግን አገልግሎቱ አስቸጋሪና ደስ የማያሰኝ ቢመስልም፣ እግዚአብሔር ቃሉን እንደ ማር የሚጣፍጥ ያደርገዋል።

4-9 ተቀባዮቹ ለሕዝቅኤል መልእክት የሚሰጡት ምላሽ የአገልግሎቱን ባሕርይ ወይም ሁኔታ ለማዛ አይችልም። ከእግዚአብሔር ስለ ተለዩ ሕዝቡ የመለኮትን መልእክተኛ ተቃወሙ። እስራኤል ትዕቢተኛ ብትሆንም፣ በባዕድ ቋንቋ ለባዕድ ሕዝብ መናገር ቢቀልም፣ ሕዝቅኤል ብርቱ መሆን ነበረበት፤ በፍርሀትና ተስፋ በመቍረጥም ምላሽ መስጠት አልነበረበትም። ከእስራኤል ሕዝብ ይልቅ ብርቱ እንዲሆን በማድረግ ማለትም እንደ ባልጩት ጠንካራና የተሳለ በማድረግ እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን ሙሉ በሙሉ ለሥራው አዘጋጀው። እግዚአብሔር ሁልጊዜ መልእክተኞቹን በአስፈላጊው ነገር ሁሉ



በማስታጠቅ እያዘጋጀ ዋስትናን ይሰጣቸዋል።

እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል ይበላው ዘንድ ጥቅልል መጽሐፍን ሰጠው፤ ከዚያም ለእስራኤል ቤት የእግዚአብሔርን መልእክት ሄዶ እንዲናገር አዘዘው።

10-11 "ከመሄዱ" እና "ከመናገሩ" በፊት (ሕዝ 3፥1) የእግዚአብሔር ቃል የሕዝቅኤል ሕይወት አካል መሆን አለበት

(ከኤር 1፥9 ጋር ያነጻ)። ስለዚህ በአገልግሎቱ ሁሉ በቀጣይነት ለእርሱ ትልቅ ትኩረት በመስጠት ነቢዩ የእግዚአብሔርን መልእክት ማሰላሰል ይኖርበታል። ሊሰሙት ለማይፈልጉ ተደራሲያን እንኳ በእግዚአብሔር ሥልጣን በታደጋጋሚ መናገር የሚችለው እንዲህ ሲያደርግ ብቻ ነበር።

4. የራእዩ ማጠቃለያ (3፥12-15)

12-13 ራእዩ ሕዝቅኤልን በመንፈስ ከፍ በማድረግና እርሱም የእግዚአብሔርን ክብር መገለጥ በሚገባ መመስከሩን የሚያረጋግጥ የመጨረሻ ቡራኬን በማሰማት ይጠናቀቃል። ሕዝቅኤል የተንቀሳቀሰበት ሁኔታ በምትሐት፣ በቃል ድግምት ወይም አካልን በሚያንቀሳቅስ ልዩ ሥነ አእምሮአዊ ዕውቀት አልነበረም። ይልቁን እርሱ የተጓዘበት ሁኔታ በራእይና በመንፈስ ቅዱስ ኀይል የሆነ ነው።

14-15 እነዚህ ጥቅሶች ሕዝቅኤል የተሰጠውን ተልእኮ የተቃወመበትን ሁኔታ እንደ ገና የሚያሳዩ ናቸው (የተለመደው ነቢያዊ ጥሪ ትረካ ሦስተኛ ክፍል ነው በ1፥1-14 ላይ ያለውን ማብ ይመ)። ሕዝቅኤል በእግዚአብሔር መንፈስ በቴል አቢብ ወደሚኖሩት ምርኮኞች እንደ መጣ፣ ደስ ስላልተሰኘበት የአገልግሎት ጥሪ በማውጣትና በማውረድ በውስጡ ትግል ላይ ነበረ። ለማይቀበል ተደራሲ ደስ የማያሰኝ መልእክትን በማስተላለፉ እጅግ ዐዝኖና ተበሳጭቶ ነበር።

ሕዝቅኤል ይህን ራእይ ካየ በኋላ በውስጡ ያለውን ሐሳብና ስሜት ለማውጣትና ለማውረድ ሰባት ቀን ፈጀበት። ባየው አስደናቂና አስፈሪ ራእይ ፈርቶ በተቀመጠበት ስፍራ ይቁጣጠረው ዘንድ የእግዚአብሔር እጅ በላዩ ላይ ነበር። የሕዝቅኤል ሁኔታና ሰባቱ ቀናት ለምርኮኞቹ ትምህርት ሰጪ ነበሩ፤ ለሞተ ሰው ሰባት ቀን ሙሉ ሐዘን ይደረግ ነበርና (ዘፍ 50፥10፤ ዘኍ 19፥11፤ ኢዮ 2፥13)፤ እንዲሁም ካህን ይቀደስ ዘንድ ሰባት ቀን ያስፈልግ ነበር (ዘሌ 8፥33)። ሕዝቅኤል በሦሳኛው ዓመቱ ለክህነት አገልግሎት ተቀደሰ፤ የይሁዳንም የሐዘን ወዮታ እንዲሰብክ ተልእኮ ተሰጠው።

5. ሕዝቅኤል፦ የእስራኤል ጉበኛ (3፥16-21)

16-17 የሕዝቅኤል መሠረታዊ ነቢያዊ ሚና ለእስራኤል ቤት ጉበኛ መሆን ነበር (ከምዕ 18፤ 33 ጋር ያነጻ)። በብሉይ ኪዳን ዘመን ጉበኛ በከተማ ቅጥር ላይ እንደ ዘበኛ በመቆም በከተማዪቱ ላይ ከውስጥም ሆነ ከውጪ የሚመጣውን ጥቃት መመልከት ነው። በአካባቢው የወራሪን ኀይል አመጣጥ ሊመለከት ወይም እሳትንና ዐመፅን የመሳሰሉ በከተማዪቱ ውስጥ የሚታዩ አደጋዎችን ሲያይ ወዲያውኑ ሕዝቡን ለማስጠንቀቅ አስቸኳይ የማስጠንቀቂያ ድምፅ ያሰማል (2ሳሙ 18፥24-27፤ 2ነገ 9፥17-20)።

18-21 ሕዝቅኤል እግዚአብሔርን ሰምቶ በአካባቢው ስለሚመጣው ፍርድ የይሁዳን ሕዝብ ማስጠንቀቅ ነበረበት። ማስጠንቀቂያውም በሙሴ ኪዳን ላይ የተመሠረተ ነበር (ዘፀ 20-ዘኍ 9፤ ዘዳግም)፤ ይህም ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ላላቸው ሕይወትን በላቀ መንገድ እንዴት መኖር እንደሚገባ የሚያሳይ ነው። የኪዳኑ የጽድቅ ግዴታዎች ለሕዝቡ መልካም በማሰብ በፍቅር የተሰጡ ሲሆኑ (ዘዳ 5፥28-33፤ 6፥25፤ 10፥12-13)፣ በእነርሱ ላይ በብዛት እንዲፈሱ እግዚአብሔር ወዳዘጋጀላቸው በረከቶች ሁሉ እንዲገቡ የሚያስችሏቸው ናቸው (ዘሌ 26፥1-13፤ ዘዳ 16፥20፤ 28፥1-14፤ ሚል 3፥10-12)። እነዚህን ሥርዐቶች ባያከብሩ፣ ከእግዚአብሔርም የኑሮ መንገድ ዘወር ቢሉ፣ ለበጎ እንዲሆንላቸው እግዚአብሔር ወዳዘጋጀላቸው የጽድቅ ሕይወት ዘወር ይሉ ዘንድ እግዚአብሔር በፍቅር ሕዝቡን እንደሚቀጣ ቃል ገብቶአል (ዘሌ 26፥14-39፤ ዘዳ 28፥15-68)። ስለዚህ ሕዝቅኤል የማያመልጡት የእግዚአብሔር ቅጣት እንደሚመጣ ለእስራኤል ማስጠንቀቂያ መስጠት ነበረበት።

ሕዝቅኤል እንደ ጉበኛ የሚሰጠው አገልግሎት (ከኢሳ 56፥10፤ ከኤር 6፥17፤ ከሆሴ 9፥8 ጋር ያነጻ) የሚያዋርድ ወይም የሚጐዳ አልነበረም፤ ነገር ግን የሚያርምና የሚጠቅም ነበረ። ከርኩሰታቸው የማይመለሱ ከሆነ ያለ ጽድቅ እንደሚሞቱ ክፉዎችን ማስጠንቀቅ ነበረበት። ልክ እንደዚሁ ሕዝቅኤል ጻድቃንን ከጽድቅ መንገዳቸው ዘወር እንዳይሉ መክሮአቸዋል፤ ይኸውም ለሙሴ ሕግ ታማኞች እንዲሆኑና የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንዲያከብሩ ነው፤ ከዚህ ውጪ ቢሆኑ ግን በርግጥ ይሞታሉ። እነዚህ ማስጠንቀቂያዎች በቀጥታ የታለሙት ለግለሰቦች ነው።

አንድ ጻድቅ ሰው ከጽድቅ ዘወር ብሎ ክፉን ቢያደርግ፣ እግዚአብሔር "በፊቱ መሰናክልን ያስቀምጣል።" ያ ሰው ከእግዚአብሔር መንገድ ዘወር ብሎ ክፉውን ነገር አድርጓል፤ ስለዚህ ይህ መሰናክል እግዚአብሔር ሆነ ብሎ አንድ ሰው ኀጢአት ውስጥ እንዲወድቅ አላስቀመጠበትም። ነገር ግን በዚህ ሰው መንገድ ፊት መሰናክል የተቀመጠው እንዴት ምላሽ መስጠት እንደሚችል አይቶ እንዲወስን ነው። ቢወድቅ ግን አካላዊ ሞትን ይሞታል።

አንድ ጉበኛ በከተማ ላይ የሚመጣውን አደጋ አይቶ ነዋሪዎቹን ባያስጠነቀቅ ለሚከተለው ጥፋት ተጠያቂ ይሆናል። ስለዚህ ሕዝቅኤል ሕዝቡ ባለመታዘዛቸው የሚመጣባቸውን የእግዚአብሔርን ርግማን ሳይነግራቸውና ሳያስጠነቅቃቸው ቢቀር እግዚአብሔር በኀላፊነት እርሱን እንደሚቀጣው አስጠንቅቆታል፤ ስለሚሞቱት ሞት ሕዝቅኤል ተጠያቂ ይሆናል፤ እርሱ ራሱም ስለ ቸልተኛነቱ ይሞታል። የእግዚአብሔርን ቃል ለመናገር የተጠሩ ታማኝ እንዲሆኑ የሚያሳስብ እንዲህ ያለ ከባድ ኀላፊነት ተጥሎባቸዋል።

በዚህ ዐውድ ውስጥ "ሕይወት" እና "ሞት" መታየት ያለበት አካላዊ ሆኖ እንጂ ዘላለማዊ ሆኖ መታየት የለበትም። በሙሴ ኪዳን ውስጥ ስለ ሕይወትና ስለ ሞት የተጠቀሰው ሐሳብ በመሠረቱ አካላዊ ነው። ያ ኪዳን የተሰጠው በእምነት ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖር ወደሚገባው ግንኙነት አስቀድመው የገቡትን ለመምራት ነበር። ዕብራውያን እነዚህን ትእዛዛት በመጠበቅ በጽድቅና በነጻነት መኖር ይችላሉ (ዘሌ 18፥5፤ ዘዳ 16፥20)። ነገር ግን ባይታዘዙ በዐጭር ዕድሜ የሚያስቀር አካላዊ ሞት የማይቀር ውጤት ይሆናል (ዘዳ 30፥15-20)። እዚህ ላይ አጽንዖት የተደረገው የጽድቅን ሕይወት በመኖር ላይ ነው። በበዓላቱና በመሥዋዕቱ ሥርዐት የድነት ሥራው በምሳሌ በተገለጸው በመሲሑ እንዲያምኑ ይህ ኪዳን ሕዝቡን አመልክቶአል (ከዕብ 9፥6-10፥18 ጋር ያነጻ)፤ ነገር ግን የሕጉን ትእዛዛት መፈጸም ከቶ ድነትን አላስገኘም። በቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ዘላለማዊ ድነት የሚገኘው በሚፈጸም በማናቸውም የሥራ ዐይነት ሳይሆን ምንጊዜም በእምነት ነው።

6. የሕዝቅኤል ድዳ መሆን (3፥22-27)

22-23 የሕዝቅኤል ተልእኮ በእግዚአብሔር ክብር ሁለተኛ የውልብታ እይታ ተጠቃልሎአል። በምዕራፍ 1 ራእይ ላይ እንደ ሆነው ሕዝቅኤል የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመቀበል የእግዚአብሔር ክብር ወደ ተገለጠለት ወደ ረባዳው ስፍራ ሄደ።

24-27 ሕዝቅኤል በእግዚአብሔር ፊት በእውነተኛ ትሕትናና አክብሮት በግምባሩ ሲደፋ፣ ለምርኮኞች የሚያስተላልፈውን መልእክት እንዲቀበል የእግዚአብሔር መንፈስ አዘጋጀው (ከ4፥1-7፥27 ጋር ያነጻ)። ሕዝቅኤል በቀጥታ ወደ ቤቱ ተመልሶ በሩን ዘግቶ እንዲቀመጥ ተነግሮት ነበር። ምርኮኞቹ በገመድ ያስሩታል። ከዚያም እግዚአብሔር አፉን ካልከፈተለት በቀር ሕዝቡን እንዳይገሥጽ ጌታ ሕዝቅኤልን ድዳ ያደርገዋል። እግዚአብሔር ይህን ሲያደርግ፣ የሕዝቡ ምላሽ ምንም ይሁን ምን ሕዝቅኤል በእግዚአብሔር ሥልጣን ብቻ ይናገራል። "የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ "የሚለው ሐረግ (የክርስቶስ የተለመደ አባባል) መልእክቱን ለመቀበል የግል ኀላፊነት ያለ መሆኑን በአጽንዖት ይገልጻል።

የሕዝቅኤል ድዳነት ኢየሩሳሌም እስከምትወድቅበት ጊዜ ድረስ (በ1፥1-3 የተጠቀሰውን ዘመን በ33፥21-22 ካለው ጋር ያነጻ) በግምት ሰባት ዓመት ተኩል ያህል ይቈያል። ይሁን እንጂ በመካከሉ ባሉት ጊዜያት አያሌ የቃል መልእክቶችን ያስተላልፋል (ከ11፥25፤ 14፥1፤ 20፥1 ጋር ያነጻ)። ስለዚህ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ድዳ የመሆን ዕንሰ ሐሳብ፣ ሙሉ በሙሉ አፍን ዘግቶ የመኖር ጕዳይ አልነበረም። ነገር ግን ከተለመደው የነቢያት የቃል አገልግሎት ጋር ሲነጻጸር በሕዝቡ ፊት በጉባኤ ከመናገር ሕዝቅኤል ታቅቦ ነበር። ነቢያት የጊዜውን ሁኔታ በተመለከቱ ቍጥር ምንጊዜም ቢሆን በሕዝባቸው መካከል በመዘዋወር የእግዚአብሔርን መልእክት ይናገሩ ነበር። ነገር ግን ሕዝቅኤል የእግዚአብሔርን መልእክት

በምሳሌ ለመግለጥ ካልሆነ በቀር (ከ4፥1-5፥17 ጋር ያነጻ) በቤቱ እንዲቀመጥ ተደርጎ ነበር። መልእክትን እንዲያስተላልፍ እግዚአብሔር አፉን እስኪከፍትለት ጸጥ ማለት ነበረበት። ከዚያም እግዚአብሔር እንዲናገር እስከ ወሰነለት እስከሚቀጥለው ጊዜ አፉን ይዘጋል። ሕዝቅኤል ወደ ሕዝቡ ከመሄዱ ይልቅ ሕዝቡ ወደ እርሱ ይመጣል። እነዚህ ዐመፀኛ ሕዝቦች በመጀመሪያ የሕዝቅኤልን መልእክት ባይቀበሉም እንኳ፣ በጊዜው የነበረው የዓለም ሁኔታ የመለኮታዊውን መልእክት እውነተኛነት ሲያረጋግጥ፣ ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን መልእክት ከሕዝቅኤል በድብቅ መፈለግ ጀመሩ።

፪. የይሁዳ ኢግብረ ገባዊነትና ያስከተለባት ፍርድ (4፥1-24፥27)

ፍርድ እንደሚመጣ የይሁዳን ሕዝብ ለማስጠንቀቅና የማይቀረው ቅጣት የሚመጣበትን ምክንያት ለማስረዳት ከምዕራፍ 4-24 ያሉት ክፍሎች አያሌ የቃል መልእክቶችንና ትእምርታውያን ድርጊቶችን አጣምረው የያዙ ናቸው። ከምዕራፍ 4-7 ባለው ክፍል ሕዝቅኤል የሚመጣውን የኢየሩሳሌምን መከበብና (ምዕ 4) በመቀጠልም ሕዝቡ በምርኮ የሚበተኑ መሆናቸውን (ምዕ 5) በትውና አሳይቶአል። ትወናውን ያጠቃለለውም ይህ የማይቀረው ቅጣት የጣዖት አምልኮን ፈጽሞ እንደሚያጠፋ በማወጅ ነው። በሰው ጥረት ከምርኮ ማምለጥ አይቻልም (ምዕ 6-7)። በጣዖት አምልኮ አረማዊ ሥርዐት ውስጥ በዚያ ወቅት ይሁዳ ካደረገችው ተሳትፎ የተነሣ የደረሰባትን ርኵሰት በንጽጽር ለማሳየት የእግዚአብሔር ክብር በተደጋጋሚ ለሕዝቅኤል ተገለጠለት (ምዕ 8)። እግዚአብሔር በሙሴ ሕግ መሠረት በእስራኤል ላይ መዓቱን ያፈሰሰ ዘንድ የእግዚአብሔር ክብር በተከታይ ኢየሩሳሌምንና ይሁዳን ትቶ ሄደ (ምዕ 9-11)። ምርኮኞቹ ይህን ተቃወሙ፤ ሕዝቅኤል ግን ለቅሬታቸው በሚገባ መልስ ሰጠው (ምዕ 12-19)። ለእግዚአብሔር ለአምላካቸው ታማኝ ባለመሆንና በመንፈሳዊ ምንዝርነት የታወቀው፣ በብልሹ አመራርም የተገለጠው ታሪካቸው (ምዕ 20-23) የፈረደባቸው መሆኑን እንዲገነዘቡ ተደርገው ነበር። ምዕራፍ 24 የኢየሩሳሌምን ውድቀት በመግለጽ ይጠቃለላል።

፪ሀ. የጉበኛው የመጀመሪያ ማስጠንቀቂያ (4፥1-7፥27)

1. የኢየሩሳሌም መከብብ የተገለጸበት የአንድ ሰው ትወና (4፥1-5፥17)

(ሀ) የሸክላ ጡብና የብረት ምጣድ (4፥1-17)

1-3 በቅርቡ ስለሚሆነው የኢየሩሳሌም መከበብና ተከትሎ ስለሚመጣው ምርኮ ለማስጠንቀቅ ይችል ዘንድ ሕዝቅኤል የሚጠቀምበትን ዘዴ እግዚአብሔር አሳየው። ሕዝቅኤል ዲዳ ቢሆንም እንኳ ማስጠንቀቂያውን በትወና እንዲያሳይ እግዚአብሔር አዘዘው፤ ምናልባትም ይህን ያደረገው ከቤቱ ውጪ ነበር (ከ3፥24-25 ጋር ያነጻ)። ምርኮኞቹ በተለየ መንገድ ሕዝቅኤል ለሰባት ቀን ያህል የተቀደሰበትን ሁኔታ ተመለከቱ (3፥15-16)። ከዚህ በኋላ ምን ዐይነት አስደናቂ ነገር እንደሚያደርግ በትኵረት ይከታተሉ ጀመር። ሕዝቅኤል በምሳሌ እየፈጸማቸው ያሉ ነገሮች ተደራሲ ያስፈልጋቸው ነበር።

ሕዝቅኤል የሸክላ ጡብ ወስዶ የኢየሩሳሌምን ከተማ ካርታ ሠራበት። ከዚያም በወታደር እንደ ተከበበች፣ ምሽግ እንደ ተሠራባት፣ ዐፈር እንደ ተደለደለባት የቅጥር መደርመሻ ግንዶች በዙሪያዋ እንደ ተቀመጡባትና የጦር ሰፈር እንደ ተቀበቀበባት በማስመሰል ከበባት። በእርሱና በከተማዪቱ መካከል የብረት ምጣድ በማስቀመጥ በኢየሩሳሌም ላይ ትንቢት በመናገር ሕዝቅኤል ይህን የመሰለ የጦርነት ትወና ለ430 ቀናት ያህል በቀጭጠኝነት ፈጸመ (ቍ. 6-7)። ይህ ሁሉ ስለሚመጣው ከበባ "ለእስራኤል ቤት ምልክት ይሆናል።"

የብረት ምጣዱ ካህናት የተወሰኑ መሥዋዕቶችን በሚያቀርቡበት ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል ነበር (ዘሌ 2፥5፤ 6፥21፤ 7፥9)። በሕዝቅኤልና በሸክላ ጡብ ላይ በተሠራችው ከተማ መካከል እንዲቀመጥ ተደርጎ ነበር። "የብረት ምጣዱ" እንደ "ብረት ቅጥር" በመካከል የሚቆም ነው። እንደ ተለመደው ቅጥር የሚያገለግለው ለመካላከያነት ነው። በአገልግሎቱ ላይ ተቃውሞ እንደሚነሣበት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን አስጠንቅቆታል (ከ2፥6 ጋር ያነጻ)። ምስያው ሕዝቅኤል ሲተውን ሳለ የሚያገኘውን ጥበቃ ወይም ባቢሎናውያን በኢየሩሳሌም ዙሪያ የገነቡትን የወረራ ግድግዳ አጉልቶ ያሳያል።

4-8 ኢየሩሳሌም እንዴት እንደምትከበብ በትወና ካሳየ በኋላ የእግዚአብሔር ሕዝብ ስለ ኀጢአታቸው የሚቀጡበትን የጊዜ ርዝማኔ በትወና እንዲያሳይ አሁንም ሕዝቅኤል ታዘዘ። በመጀመሪያ ፊቱን ወደ ሰሜን አደረገ (ይህም በትእምርት እስራኤልን ለማሳየት ነው)፤ በግራ ጐኑ ለ390 ቀናት በመተኛት እስራኤል በኀጢአቷ ምክንያት የምትቀጣበትን ጊዜ በማሳየት ቅጣቷን ተሸከመ። እነዚህ 390 ቀናት "ሲፈጸሙ"፣ ሕዝቅኤል በቀኝ ጐኑ ለአርባ ቀናት ፊቱን ወደ ደቡብ በማድረግ (በትእምርትነት ወደ ይሁዳ በማድረግ) የይሁዳን ርኵሰት ቅጣት በመሸከም "እንደ ገና ይተኛል"። የእያንዳንዱን አገር ከበባ በቅደም ተከተል ለማየት የቅጣቱ ጊዜ እስከሚፈጸም በተመደበለት የጐን ማረፊያ እንዲተኛ ሆኖ ይታሰራል። በእያንዳንዱ ቀን ባለው ሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ሕዝቅኤል በጐኑ መተኛት አላስፈለገውም። በምዕራፍ 4 የቀረው ክፍል የተወሰነለትን የምግብ ዐይነት የያዘ ሲሆን በምዕራፍ 8 ላይ በቀኝ ጐኑ በተኛባቸው በመጨረሻዎቹ ቀናት ከምርኮኞቹ ሽማግሌዎች ጋር በቤቱ ተቀምጦ ነበር። ከእያንዳንዱ ቀን የተወሰነው ክፍል ትእምርቱን (ምልክቱን) ለማሟላት በቂ ነበር።

የዚህ ክፍል መሠረታዊ ትርጉም ግልጽ ቢሆንም፣ ቍጥሮቹ ግን አያሌ ገለጻዎች እንዲኑሡ አድርገዋል። አንዳንድ ነገሮች ግልጽ ናቸው፦ እያንዳንዱ ቀን አንድ ዓመትን ይወክላል (ቍ. 5-6 ይመ፤ ከዘኍ 14፥34 ጋር ያነጻ)፤ ዓመታቶቹ ደግሞ ሕዝቡ ኀጢአት የሠሩበትን ወቅት የሚወክሉ ናቸው። ቍጥሮቹ በ390 እና በ40 ዓመታት በሁለትና በተከታታይ የጊዜ ክፍተት የተለዩ ሆነው ቃል በቃል የሚታዩ የጊዜ ወቅቶች ሆነው መታየት አለባቸው። የጊዜ ቅደም ተከተልን ለመወሰን ሕዝቅኤል መነሻ ያደረገው ዮአኪን የተጋዘበትን 597 ዓቅክ ነው። ስለዚህ ይህ እነዚህ ጥቅሶች የሚናገሩት የጊዜ ወቅት የተጀመረበትን ሊያመለክት ይችላል። 430ዎቹ ዓመታት የሚያለክቱት የታወቀው ንጉሣቸው ዮአኪን ተማርኮ ከሄደበት ማለትም የእስራኤልንና የይሁዳን ልጆች ድል በማድረግ የቀጣቸው የውጪ ኀይላት ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ በ167 ዓቅክ ተነሣ እስከ ተባለው የመቃብያን ዐመፅ ድረስ ያለውን ነው። በመቃብያን ዘመን አይሁድ እንደ ገና የይሁዳን ግዛት ተቈጣጠሩ። ይህ ሊሆን የሚችል መፍትሒ ቢሆንም፣ ስለ ቍጥሮቹ ያለው ሐሳብ ይኸው ብቻ ነው ማለት ግን አንችልም።

9-17 በ390 ቀናት ሕዝቅኤል በጐኑ ተኝቶ ኢየሩሳሌም እንደምትከበብ ሲያሳይ፣ እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን የተወሰነ የምግብ ዐይነት ብቻ እንዲመገብ አዘዘው፣ ስለዚህ ከተለያዩ እህሎች ተደባልቆ የተጋገረ እንጀራ መብላት ነበረበት። ከዓመት በላይ በየቀኑ በሁለት እፍኝ ውሃና ግማሽ በሚመዝን ፓውንድ እንጀራ ብቻ እንዲወሰን ሆነ። ይህ አነስተኛ የአመጋገብ ሁኔታ ኢየሩሳሌም በምትከበብበት ጊዜ ሊደርስ የሚችለውን ረኃብ እውንነት የሚያመለክት ነው። እግዚአብሔር የኢየሩሳሌምን የምግብ ምንጭ ያደርቃል (ይኸውም በዘሌ 26፥16፡20፡26፡29 ላይ ተስፋ እንደ ተናገረው)። ለእንጀራ የሚሆን የማንኛውም ዐይነት እህል እጥረትና የውሃ አቅርቦት ፈጽሞ የሌለበት ሁኔታ ይፈጠራል። የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ይደናገጣሉ፤ እርስ በርሳቸውም በፍርሀት ይተያያሉ (ከዘሌ 26፥19፡35፤ ከ2ነገ 25፥3፤ ከኤር 34፥17-22 ጋር ያነጻ)።

ከዚህ እጅግ ዝቅተኛ ከሆነው ምግብ በተጨማሪ፣ ሕዝቅኤል ድርጎውን በረከሰ ማገዶ ያውም በሰው ዐይነ ምድር እንዲያበስል ተደርጎ ነበር (ከዘዳ 23፥12-14 ጋር ያነጻ)። የተደባለቀ እህል መብላት ተቀባይነት ያለው ቢሆንም፣ የሰው ዐይነ ምድርን እንደ ማገዶ መጠቀም ግን እጅግ መርከስ ነው፤ የረከሰ ምግብ መብላት በሙሴ ኪዳን የተከለከለ ነበርና (ዘሌ 22፥8፤ ዘዳ 12፥15-19፤ 14፥21)። ታማኝ ካህን የሆነው ሕዝቅኤል እስካሁን የረከሰ ምግብ በልቶ የማያውቅ ስለ ነበር ይህን የረከሰ ምግብ እንዳይበላ አጥብቆ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ። እግዚአብሔርም በቸርነቱ ምግቡን በሰው ዐይነ ምድር

ሳይሆን፣ በተለመደው ማገዶ በከብት ኩበት እንዲያበስል ፈቀደለት። በረከሰ መንገድ ምግብን የማዘጋጀት ሁኔታ፣ ከምርኮው በመቀጠል የማይቀረውን የኢየሩሳሌምን መከበብና መውደቅ ገለጸ። ምርኮኞቹ እንዲጠፋፉ ተወሰነበትን የባዕድ ምድር ርኩስ ምግብ ይበላሉ።

ሕዝቅኤልን ይህን ሁሉ እንዲያደርግ እግዚአብሔር ቢያዝዘውም እንኳ ሕጉን እየለወጠ አልነበረም። ምርኮው የቱን ያህል የከፋ እንደ ሆነ አጉልቶ ለማሳየት ሲል፣ ሕዝቅኤል የረከሰ ምግብ የመብላትን መርሕ ለጊዜው ችላ እንዲል አደረገ። እግዚአብሔር ይህን እውነት መረዳት በሚቻልበት መንገድ ለማስረዳት በትውና መልክ የቀረበን ምሳሌ ተጠቀመ፤ የረከሰን ምግብ መብላት የተፈቀደ ነገር እንደ ሆነ ተደርጎም እዚህ ላይ መታየት የለበትም። የረከሰን ምግብ በመብላት ከሚመጣው ጉዳት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን በሉዓላዊ ኀይሉ ጠበቀው።

ለ. ጠጕርን መከፋፈል (5፥1-4)

1 ሕዝቅኤል በምዕራፍ 4 ላይ የጀመረውን ትወና ጢሙንና ጠጕሩን በመላጨት፣ የተቈረጠውንም ጠጕር በመመዘንና ሦስት ቦታ እኩል በእኩል በመከፋፈል ፈጸመው። ይህ የመጨረሻው ድርጊት የሚያመለክተውም መርከስን ነው። ጠጕርንና ጢምን መላጨት ሰዎች ሲሞቱባቸው ስለ ነዘኑ ጣዖት አምላኪዎች የሚፈጽሙት ሥርዐት ነው (27፥31 ይመ፤ ከኢሳ 22፥12፤ ከኤር 16፥16፤ ከአሞ 8፥10 ጋር ያነጻ)፤ ይህንንም ሕጉ ይከለክላል (ዘዳ 14፥1)፤ ዝቅ የማለትና የመዋረድም ምልክት ነው (7፥18 ይመ፤ ከ2ሳሙ 10፥4 ጋር ያነጻ)። አንድ እስራኤላዊ ካህን የራሱን ጠጕር ቢላጭ ይረክሳል፤ ከዚያም በኋላ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ አይሆንም (ዘሌ 21፥5)። ለረከሱትና ከእንግዲህም ለእግዚአብሔር ቅዱሳን ላልሆኑት ለይሁዳ ሕዝብ ለውርደታቸው ትእምርት ይሆናቸው ዘንድ ሕዝቅኤል ራሱን አረከሰ፤ አዋረደም። ሊደረግ የሚገባው የቀረ ነገር አልነበረም፤ ነገር ግን እንደ ሕዝብ ስለሚሞቱ የቀረው ማልቀስ ብቻ ነው።

2-4 ጠጕሩ የሚያመለክተው የኢየሩሳሌምን ነዋሪዎች ነው።ከከበባው በኋላ ኢየሩሳሌም በሞትቃጠልበት ጊዜ፣ ከሕዝቡ ሚሶው ይቃጠላል (2ነገ 25፥9)። ከዚህ ሕዝብ መካከል የተወሰኑት በከበባው ጊዜ በረኃብና በጭንቀት አስቀድመው ሞተዋል (ቍ 12ሀ)። ሁለተኛው ሚሶ ኢየሩሳሌም በምትወድቅበት ጊዜ በሰይፍ ይሞታል። (ቍ 12ለ፤ 2ነገ 25፥18-21ሀ፤ 2ዜና 36፥17)። የመጨረሻው ሚሶ በስደት ውስጥ ለነፋስ ይበተናሉ (ቍ 12ሐ፤ 2ነገ 25፥11፡ 21ለ)። ከዚህ ከመጨረሻው ክፍል የተወሰኑት ግማሾቹ ኢየሩሳሌምን ትተው በሚወጡበት ጊዜ በእሳት እንዲቃጠሉ ሲፈረድባቸው፣ ሌሎቹ ደግሞ በምርኮ ውስጥ በሰይፍ ይሞታሉ። ከዚህ ከመጨረሻው ሚሶ ከኢየሩሳሌም ነዋሪዎች መካከል እግዚአብሔር ትሩፋንን ያስመልጣል፤ ይኸውም ሕዝቅኤል ከጠጕሮቹ ጥቂት ወስዶ በመጐናጸፊያው ጫፍ ላይ የቋጠራቸው ምሳሌ ናቸው።

ሐ. የትእምርቶቹ አስፈላጊነት (5፥5-17)

5 ስለ ከበባውና ስለሚመጣው ፍርድ እግዚአብሔር ለተቀባዮቹ "ኢየሩሳሌም ይህች ናት" በሚለው አረፍተ ነገር በአጽንዖት ነገራቸው። ወዲያውኑ ሰው በ4፥1 ላይ በሸክላ ጡብ የተሠራውን የከተማ ካርታ ልብ ይላል። ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ፍቅር ትኩረት ነበረች። ይሁን እንጂ እነዚህ ትእምርታዊ ድርጊቶች ሁሉ በእርሷ ላይ የሚፈጸመውን ይገልጣሉ።

6-7 የፍርድ ንግግር ይኸውም በኢየሩሳሌም ላይ የተቈጠረው ክስና በእርሷ ላይ የተሰማው ፍርድ የአንድን ሰው ተውኔት አጠናከረ። መሠረታዊ የሆነው ክስ ይህች የተባረከችው ከተማ ኢየሩሳሌም በትእዛዙ ላይ በማመፅ መንገዱን ባለመቀበልና በሙሴ ኪዳን መሠረት ሕይወትን ለመምራት ባለመቻል ለእግዚአብሔር በረከት ምላሽ ሰጠች። እጅግ ከመርከሷ የተነሣ በዙሪያዋ ያሉ አገሮች እንኳ የሚያከብሩትን የተለመደ ሕግ መጠበቅ አልቻለችም። ወደፊት በሚመጣው ከበባ አንዳንድ የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ሰውን ወደ መብላት ይወርዳሉ (ቍ 10ሀ ይመ፤ ከዘሌ 26፥29፤ ከዘዳ 28፥53፤ ከ2ነገ 6፥28-29፤ ከኤር 19፥9፤ ከሰቆኤር 4፥10 ጋር ያነጻ)። እጅግ አስጸያፊ በሆነ የጣዖት አምልኮ ቅዱሱን ማደሪያውን አርክሰዋል (ቍ 11ሀ፤ ምዕ 8)።

8-17 እግዚአብሔር በሙሴ ሕግ መሠረት በአሕዛብ ፊት በኢየሩሳሌም ላይ ፍርድን ያመጣባታል። እንዲህ ዐይነት ፍርድ እንደ ገና ከቶ አያመጣም። ያለ ርኅራኄ ፍርዱን ለማውረድ ሲል ራሱን ከማደሪያው ያስወጣል (ከ10፥4፤ 11፥22-23 ጋር ያነጻ)። ከኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ሚሶዎቹ በከተማዪቱ ውስጥ በበሽታና በረኃብ ይሞታሉ፤ ሚሶዎቹ ደግሞ በሰይፍ ይሞታሉ፤ የቀሩትም በየአቅጣጫው በአሕዛብ መካከል ይበተናሉ። በኢየሩሳሌም ላይ የሚወርደው ፍርድ (ከዘሌ 26፥21-26 ጋር ያነጻ) ረኃብን፣ የዱር አራዊትን፣ ቸነፈርንና ደም መፋሰስን በሙሉ ያካተተ ነው። እግዚአብሔር ካደረገባት የተነሣ አሕዛብ እንዲያላግጡባት የይሁዳ ምድር ባድማ ትሆናለች። በዚሁ ተመሳሳይ ጊዜ እነዚሁ አሕዛብ፣ እግዚአብሔር በራሱ ሕዝብ ላይ እንኳ ባመጣው ፍርድና መዓት በፍርሀትና በሽብር ይመታሉ። እነርሱም እስራኤልን ቢራገሙ (ከዘፍ 12፥3 ጋር ያነጻ) እግዚአብሔር የሚያመጣባቸው ፍርድ የቱን ያህል ከባድ እንደ ሆነ እንዲረዱ በይሁዳ ላይ የመጣው ፍርድ ለአሕዛብ ማስጠንቀቂያ ይሆን ዘንድ አገልግሎአል። ከዚህ ፍርድ የተነሣ የእግዚአብሔር ፍትሕ የተሟላ ትርጕም ያገኛል፤ የኢየሩሳሌም ሕዝብም እግዚአብሔር ተገቢውን መዓት እንዳወረደባቸው ያውቃሉ። ቅጣቱ የታወቀ ነው፤ እግዚአብሔር ተናግሮአልና!

2. በይሁዳ ምድር ላይ የሚመጣው ፍርድ (6፥1-7፥27)

ሀ. የጣዖት አምልኮ መሠዊያዎች መፈራረስ (6፥1-14)

1-7 እግዚአብሔር የሕዝቅኤልን ድዳነት በማስቀረት ፍርድን በይሁዳ ተራሮች፣ ኰረብቶች፣ ገደላገደሎችና ሸለቆዎች ላይ እንዲናገር አደረገው። ሕዝቅኤል በእነዚህ አራት የምድሪቱ መልክአ ምድራዊ ገጽታዎች ላይ ፊቱን አዞረ፤ ይህን ያደረገውም ጣዖት አምላኪዎች በአብዛኛው የጣዖት አምልኮ መቅደሶቻቸውን የሚሠሩት በእነዚሁ ሰፍራዎች በመሆኑ ነው (ከ2ነገ 23፥10 ጋር ያነጻ)። የከነዓናውያን ሃይማኖት ጠማማ በሆነ በወሲብ ሁኔታ፣ በጦርነት፣ ሙታንን በማምለክ፣ እንዲሁም እባብን በማምለክ፣ በጣዖት አምልኮም ላይ አጽንዖት በማድረግ፣ ለአምልኮው ኰረብታዎችንና የዛፍ ጥሻዎችን ይመርጣል። የይሁዳ ንጉሥ የነበረው ምናሴ (695-642 ዓቅክ) እነዚህ ሁሉ የጣዖት አምልኮ ልምምዶች በምድሪቱ ላይ እንዲስፋፉ አድርጎአል።

ከዚህ በመቀጠል እግዚአብሔር ሕዝቡ በሚከተሉአቸው በጣዖት አምልኮ መቅደሶችና እነርሱም በሚፈጽሙአቸው የጣዖት አምልኮ ልምምዶች ላይ ፍርድን አወረደባቸው። ሕዝቡ እየተጋፈጡት ያሉትን ፈተና ለማስወገድም "ኰረብቶቻቸውን" "መሠዊያዎቻቸውን"፣ "የዕጣን መሠዊያዎቻቸውን" እና "ጣዖቶቻቸውን" ሁሉ ያወድማል። እነዚህን የጣዖት አምልኮ መቅደሶችንም ለማርከስ ዐጥንቶቻቸውን በመሠዊያዎቻቸው ዙሪያ ይበትናል። "ዐጥንቶቻቸሁንም እበትናለሁ" የሚለው ሐረግ ርኩሰትና ውርደት የተቀላቀለበት ፍርድ እንደሚመጣ የተገለጸበት ነው (ከመዝ 53፥5፤ 141፥7 ጋር ያነጻ)። እነዚህ ዐጥንቶች በተዘረዘሩት የጣዖት አምልኮ ልምምዶች የተዘፈቁ የእስራኤላውያን ዐጥንቶች ናቸው (ከ2ነገ 23፥20፤ ከኤር 8፥1-2 ጋር ያነጻ)። እግዚአብሔር በዘሌ 26፥30 ላይ ለተገለጸው የተስፋ ቃል ታማኝ ነው፤ አንዳች ነገር የእርሱን ሕጋዊ ቦታ እንዲወስድ አይፈቅድም። በዚህ ቅጣት አማካይነት እግዚአብሔር ብቻውን አምላክ እንደ ሆነ የይሁዳ ሕዝብ ያውቃል።

8-10 ምን ጊዜም ቢሆን እግዚአብሔር ፍርድን ሲናገር ማምለጫ መንገዱንም እንዲሁ አንድ ላይ ያመለክታል፤ ይኸውም ወደ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ዘወር ማለትና መንገዶቹን መከተል ነው (ከኤር 18፥7-10 ጋር ያነጻ)። ስለዚህ በሕዝቅኤል ሕጋዊ ፍርድ ውስጥ ከምርኮኞቹ አንዳንዶቹ በፊት የሄዱበትን መንገድ ርኩሰት እንዲሚያዩና በእርሱም እንደሚያፍሩ የእግዚአብሔር ማረጋገጫ ነበር። እግዚአብሔርን ያስባሉ፤ በጽድቅ እንዲኖሩ አለበለዚያ በቅጣት ተሠቃይተው እንደሚመለሱ ባስተማራቸው ጊዜ በከንቱ እንዳልተናገራቸውም

ልብ ይላሉ። እነዚህ ትሩፋን ለእግዚአብሔር ቅጣት ምላሽ ይሰጣሉ፤ እግዚአብሔርንም ካሳዘነው መንፈሳዊ ምንዝርና ንስሓ በመግባት ይመለሳሉ። አምላካቸው በእውነት እግዚአብሔር እንደ ሆነ ያውቃሉ። የእግዚአብሔር ቅጣት አጠቃላይ ዐላማ ሕዝቡን ወደ ራሱ መመለስ ነው።

11-14 እግዚአብሔር ወደማይቀረው ዋና የፍርድ ሐሳቡ በመመለስ፣ እየመጣ ካለው ፍርድ የተነሣ ሕዝቅኤል ደስታን እንዲገልጽ ያዘዋል። በእጅ ማጨብጨብና በእግር መራትን መርገጥ በደስታ ማመስገንን ወይም ስለ ኀጢአትና ስለ ፍርድ መሣለቅንና ማላገጥን ሊያመለክት ይችላል (21፥14-17፤ 22፥13፤ 25፥6፤ ከሰቆ. ኤር 2፥15፤ ከናሆ 3፥19 ጋር ያነጻ)። በአጠቃላይ የጣዖት አምልኮ መቅደሶችና ልምምዶቻቸው ከምድራቱ በመወገዳቸው እግዚአብሔር ደስ መሰኘቱን ሕዝቅኤል በልዩ ሁኔታ ገልጾአል። ምድራቱ በአጠቃላይ በደ.ክ.ላታ አቅጣጫ እንዳለው ምድረ በዳ ወና ትሆናለች። ማንኛውም ሰው በፍርዱ ይነካል፤ በሩቅ ያሉት በበሽታ፣ በቅርብ ያሉት በሰይፍ፣ የተረፉት በኢየሩሳሌም በውስጥና በውጭ ያሉት የተረፉት በራብ ያልቃሉ። የእግዚአብሔር የፍርድ ዐላማ አድማጮቹ ስለ እግዚአብሔር ተመክሮአዊ ዕውቀት ይኖራቸው ዘንድ መሆኑን (ቍ. 7:10:13፤14) እንዲያሳስባቸው እግዚአብሔር አራት ጊዜ ሙሉ ለሕዝቅኤል ነገረው። ይህ የመጽሐፉ ኀይለ ቃል ሕያው ላልሆኑ ጣዖታት ታዝዞ ከመጥፋት ይልቅ ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ጋር የቅርብ ግንኙነት እንዲያደርግ የሚጣራ ነው።

በማንኛውም ትውልድ ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን ፍርድና ቅጣት ዐላማ በወጉ መረዳት አይችሉም። የእግዚብሔር ዋና ፍላጎት ሕዝቡን ወደ ራሱ ለማምጣት ወይም ለመመለስ ነው። የሰው ዘር በራሱ ፈቃድ ወደ እግዚአብሔር መመለስን ባይመርጥ፣ እግዚአብሔር በምሕረቱ ቅጣትና ፍርድን በመጠቀም ምን ጊዜም ቢሆን በቃሉ ለተናገረው ታማኝ መሆኑን በማሳየት እርሱ ብቻ እውነተኛ አምላክ መሆኑን ሕዝቡ እንዲያውቁ ያደርጋል።

ለ. የርግማኑ ተፈጻሚነትና አጠቃላይነት (7፥1-13)

1-4 በይሁዳ ሁሉ ላይ በሚመጣው አይቀሬና አጠቃላይ ፍርድ ላይ አጽንዖት የሚያደርጉ፣ በግጥምም መልክ የቀረቡ አራት ዐጫጭር፣ ብርቱ ነቢያዊ ንግግሮችን እግዚአብሔር አሁን ለሕዝቅኤል ሁለተኛ መልእክት ይሰጣል። አያሌ አረፍተ ነገሮች እንዲሁም ተደጋጋሚ የሆኑ ቃላትና ሐረጎች የመልእክቱን ጥንካሬ ይገልጻሉ። "ፍጻሜ"! የሚለው ቃል በተደጋጋሚ መገለጹ ፍርዱ የመጨረሻ መሆኑን በእጅጉ ያመለክታል። ፍርድ መጥቶአል! አይቀሬነት በጉልሕ የተመለከተው "መጥቶአል" የሚለው ግስና፣ "አሁንም" የሚለው ቃል በመደጋገማቸው ሲሆን፣ "ጊዜ፣" "በዚያ ጊዜ፣" "መጥቶአል" የሚሉት ቃሎችም በመደጋገማቸው ነው።

የመጀመሪያው ትንቢታዊ ንግግር (ቍ. 1-4) የፍርዱን ስፋት ያመለክታል፤ ይኸውም "በአራቱም የምድራቱ ማእዘን" በሚል የተገለጸው ሲሆን፣ የፍርዱን መሠረት እንዲሁም የፍርዱን ምክንያት ሁለት ዋና ዋና ሐሳቦች በዐጭሩ ያቀርባሉ። በይሁዳ ላይ የሚፈረደው ከሄደችበት የክፋት መንገድ አኳያ ነው። ርኩሰቷ በላይዋ ላይ ይመጣል። ምርኮው ሲያደርጉት የነበረው ተመሳሳይ ጸያፍ ተግባር የዕለት ተዕለት ክሥተት ወደ ሆነባቸው አገሮች የይሁዳን ሰዎች ያመጣቸዋል። ከዚህ ሁኔታ የሚጠበቀው እነዚህን የረከሱ ሥርዐቶች እንዲጠሉአቸው ያደርጋቸዋል የሚል ነው። ከዚህም በላይ እግዚአብሔር ማናቸውንም በርኅራኄ ዐይን አያይም። አንዳቸውንም አያስተርፋቸውም። ትዕግሥቱና ርኅራኄው ቅጣቱን ቢያዘገየውም እንዲህ ዐይነቱ መዘግየት ግን ብዙ አይቈይም። በርግጥ የእግዚአብሔር ፍርድ ፍቅሩን ይገልጻል፤ ዐላማው ይሁዳ እግዚአብሔር እርሱ አምላክ እንደ ሆነ እንድታውቅ ነውና።

5-9 ሁለተኛው ንግር ስለ ፍርዱ አስደንጋጭነትና ድንገተኛነት እንዲሁም ስለ ፈራጁ ማንነት በአጽንዖት ይናገራል። ምድራቱን የሚሞላው ሽብር "መዓት" እና "ፍጻሜ መጥቶአል" በሚሉት ቃላት በአጽንዖት ሲነገር፣ በተጨማሪም በሚመጣው ፍርድ የሽብር ድምፅ የሚሰማበት እንጂ በመከር ወራት እንደሚሰማው ዐይነት የደስታ ድምፅ እንዳይደለም ተነግሮአል (ከኢሳ 16፥10፤ ከኤር 25፥30 ጋር ያነጻ)። የፍርዱ ድንገተኛነት (ምዕ 12-19) "ፍጻሜ መጥቶአል"፣ "በአንቺ ላይ ተነሣሥቶአል" እንዲሁም "መዓት ይመጣል፣" "ጊዜው ደርሶአል፣" "ቀን ቀርቦአል" በሚሉ ሐረጎች ተንጸባርቆአል። ከቍ 3-4 ለተገለጸው ፍርድ ቍ. 8-9 መሠረት ይሰጣሉ። መልእክቱ የሚጠቃለለው ምርኮቹቹን በማስገረም እግዚአብሔርን በዐዲስ ስም በማስተዋወቅ ነው፤ ይኸውም "የሚቀሥፍ እግዚአብሔር" የሚለው ሲሆን፣ አሁን በይሁዳ ላይ ፍርድን ያደርጋል ማለት ነው።

10-11 ሦስተኛው ንግር ትኩረት የሚያደርገው በፍርዱ አይቀሬነት፣ አጠቃላይነትና ዝግጁነት ላይ ነው። የፍርዱ የወጋገን ቀን በፍጥነት ደረሰ፤ በድንገት "አቈጠቈጠ"፤ እንዲሁም "አበበ"። "በትሩ" የፍርድ መሣሪያ የሆነው ናቡከደነፆር ወይም የእስራኤል ነገሥታት ያሳዩት ንቀት ሲሆን ይችላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ "በትር ማቈጥቈጥ" የተጠቀሰ ምንባብ የምናገኘው በዘኁ ምዕ 17 ውስጥ ብቻ ነው፤ ይኸውም እንዲህ ዐይነቱ በትር የእግዚአብሔር ምርጫ እንደ ሆነ የሚያመለክት ነው። ነገር ግን በይሁዳ ላይ ስለ መጣው ፍርድ በዚህ ስፍራ ስለ ተገለጸ፣ "በትር" የሚለውን ቃል ልንረዳው የሚገባን በእግዚአብሔር ተመርጦ ጥቅም ላይ ሊውል የተዘጋጀ የፍርድ መሣሪያ እንደ ሆነ ነው። በማቈጥቈጥ ላይ ያለው በትር ፅንሰ ሐሳብ ከመጀመሪያው የግጥም ስንኝና (ይኸውም የፍርዱን አይቀሬነት በማመልከት ሲሆን)፣ ቀጥሎ ካለው ስንኝ (ይሁዳን ለመቅጣት እግዚአብሔር የሚጠቀምበትን የበትር ዐይነት በመግለጽ ሲሆን ይህም የ"ትዕቢት" በትር ነው) ጋር ጉድኝት አለው። ስለዚህ ይህ በትር የፍርድ መሣሪያ በመሆን ናቡከደነፆር ከገለጸው ጋር ይስማማል። በምድራቱ ጠቃሚ ነገር ነው የሚባለው ሁሉ እስከማይተርፍ ድረስ እግዚአብሔር ይህን መሣሪያ ይጠቀማል።

12-13 የመጨረሻው ንግር የፍርዱን ቋሚነትና በፍጥነት መከናወን በአጽንዖት ያመለክታል። ፍጥነቱ በጉልሕ የተመለከተው እጅግ ድንገተኛ መሆኑ የሚመጣው ቅጣት ፈጣን ከመሆኑ የተነሣ አንድ ሰው የሸጠውን መልስ ለማግኘት ባለመቻሉ ነው። ይህ ምሳሌ የተሰጠው ከሰባት ዓመቱ ሕግ (ዘዳ 15፥1-2) ወይም የኢዮቤልዩን ዓመት (ዘሌ 25፥13-16) በማሰብ ሳይሆን አይቀርም። በዚያ ሕግ መሠረት አንድ ሰው ዕዳውን ለመክፈል መሬት ቢሸጥ፣ ያ መሬት ቀድሞ በወጣው ማለትም በሰባተኛው ዓመት ወይም በኢዮቤልዩ ዓመት ይመለስለታል ማለት ነው። አንድ ሰው በዚሁ የስምምነት ሕግ መሠረት መሬትን ቢሸጥ፣ ከሰባት ዓመት በኋላ ሻጩ ወይም ገዥ በይሁዳ ምድር ስለማይኖር፣ ሻጩ ይመለስልኛል ብሎ ተስፋ እንደሚያደርግ ሕዝቅኤል አስተዋለ። ገዥ መሬቱን ለሻጩ መቼውንም የማይመልስ በመሆኑ ሊደሰት ቢችልም ጊዜው ግን ለማንኛቸውም የደስታ ጊዜ አይሆንም። ፍርዱ ሲመጣ ሁለቱም የንብረቱ ባለቤት አይሆኑም። የንብረቱ ባለቤት የምትሆነው ባቢሎን ናት!

የፍርዱ ራእይ እውን ነው! እግዚአብሔር ፈጽሞ አይመልሰውም! ማንኛውም በበደሉ በመኖር መቀጠል አይችልም፤ ርኩሰት ሁሉ ይፈረድበታልና!

ሐ. ለርግማኑ ያለው ምላሽ (7፥14-27)

14-18 የዚህ ምዕራፍ የመጨረሻው ግማሽ በግልጽ የሚያመለክተው ለዚህ ፈጣንና ከባድ ፍርድ የይሁዳ ሰዎች የሰጡትን ምላሽ ነው። ሥጋቸውን በማስደሰት የደረሰባቸው ግብረ ገባዊ ውድቀት፣ ረኃብና በሽታ አብዛኛውን ሕዝብ ስለ ጨረሰው መለከት ለጦርነት ሲነፋ ለውጊያ ሊሰባሰቡ አልቻሉም። ስለዚህ ባቢሎናውያን ለከበባ ወደ ኢየሩሳሌም ይቀርባሉ (ከዘሌ 26፥7 ጋር ያነጻ)።

በሽታና ራብ በኢየሩሳሌም ያሉትን ይጨርሳሉ፤ ሰይፍም ከቅጥሩ ውጭ የሚሠሩትን ድንገት ይይዛቸዋል። ከመጀመሪያው ወረራ ለማምለጥ የቻለ ዕድለኛ ወደ ተራሮች ይሸሻል። በዚያም በፍርሀት በመንቀጥቀጥ፣ በድካምና በውርደት ውድቀታቸውን ባመጣው ኀጢአት ያፍራሉ፤ ይዋረዳሉም። በሐዘን ማቅ ይለብሳሉ። በውርደትም ራሳቸውን ይላጫሉ፤ እንደ ርግብም ያለቅሳሉ።

19 በ586 ዓቅክ ኢየሩሳሌምንና ይሁዳን ከሚያጠፋው ከተገለጠው የእግዚአብሔር አስፈሪ ቍጣ እስራኤላውያንን

ማንም ሊያድናቸው አይችልም። አብዛኛዎቹ ነዋሪዎቿ እስካሁን የኖሩት ለብልጥግና ስለ ሆነ ሥሳዊ ጥቅም አእምሮአቸውን ሙሉ በሙሉ ተቈጣጥሮአል። ይሁን እንጂ እነዚህ ብልጥግናዎች በፍርድ ጊዜ ምንም ማለት አይደሉም። ጣዖት አምልኮ፣ ርኩሰትና ሥሳዊ ፍላጎት ብዙውን ነገራቸውን ስለ ዘረፋቸው፣ ለፍርድ ተዳርገዋል። ገንዘብ እንደ ርኩስ ወሲባዊ ነገር ይጣላል።

20-22 ይሁዳ መቅደሷን አርክሳለች፤ "በውብ ዕንቊቸው" የተባለው ኢየሩሳሌምንና መቅደሷን የሚመለከት ሲሆን፣ "የከበረውን ቦታዬን" የሚለው ደግሞ ይህንኑ ሙሉ በሙሉ ከኢየሩሳሌም ውድቀት ጋር ካያያዝነው መቅደሱን የሚያመለክት ይሆናል (24፥21፡25 ይመ)። ሕዝቡ ከቤተ መቅደሱ ውስጥ ጌጣ ጌጦችንና የከበሩ ዕቃዎችን በመዝረፍና የጣዖታትን ምስል በእነርሱ በማበጀት የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ አርክሰዋል። አሁን በአንጻሩ ባዕዳን የከበረ ሀብቱን በመዝረፍ ቤተ መቅደሱን እንዲያረክሱ እግዚአብሔር ፈቅዶላቸዋል። ለባቢሎናውያን አሁን ማንኛውም ነገር ለብዝበዛ ይሆንላቸዋል።

23-24 ምርኮኞችን አስሮ ወደ ባቢሎን ለማጋዝ ሰንሰለት ተዘጋጅቶ ነበር። ይህ ለፈጸሙት ከባድ ወንጀል የሚገባቸው ዋጋ ነበር። የይሁዳ ሰዎች ሲወጡ፣ ከአሕዛብ መካከል እጅግ ክፉዎች የሆኑ ባዕዳን ይገባሉ፤ ምድሪቱን ይይዛሉ፤ የተቀደሰውንም ስፍራ ሁሉ ያረክሳሉ። ምድሪቱ በአጠቃላይ በባቢሎናውያን አገዛዝ ሥር ትሆናለች።

25-27 ለአንዳንዶቹ የመጨረሻው ምላሽ ርዳታን መፈለግ ነበር። ሕዝቡ የትድግናን ራእያዊ መገለጥ ተስፋ በማድረግ ወደ ነቢይ ይሮጣሉ፤ ከሕጉ የሚረዳ መልእክት ለማግኘት ደግሞ ወደ ካህን ይመጣሉ፤ በዚህ ጭንቅ ጊዜ የሚረዳ ምክርን ለማግኘ ትም ወደ ሽማግሌዎች ይሄዳሉ። ማንኛቸውም ግን ርዳታን ሊሰጡአቸው አይችሉም። ምንም ዐይነት ምላሽ ከቶውንም የላቸውም! መሪዎች ሕዝቡን በእግዚአብሔር መንገድ ለመምራት የተሰጣቸውን ኀላፊነት ሊወጡ አልቻሉም። ጊዜው አልቋል! የጥፋት ፍርድ መጥቶአል! ቀደም ብሎ ባለው ጊዜ ሕዝቡ ሰላምን ፈልገው ቢሆን ኖሮ፣ በተገኘ ነበር፤ አሁን ግን ፈጽሞ ሰላም የለም። ነገሥታትና መሳፍንት ይሸበራሉ፤ ያለቅሳሉ። እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ የፈረደው ማወቅና መከተል በነበረባቸው በሙሴ ሕግ ይህም በራሷ በእስራኤል መመዘኛዎች ነው። ሊያድናቸው የሚችል ብቸኛ ምክንያት እግዚአብሔር እርሱ እውነተኛ አምላክ እንደ ሆነ መማርና የእርሱንም ሕግ ሊታዘዙት እንደሚገባቸው ማወቅ ነው።

ፀሎ- የእግዚአብሔር ክብር የወጣበት ራእይ (8፥1-11፥25)

1. የእስራኤል ቤት ጣዖት አምልኮ (8፥1-18)

ሀ. ቅናት የሚያነሣሣው የጣዖት ምስል (8፥1-6)

1-6 ቊ 1 ከምዕራፍ 8-11 ያለውን አንድ ራእይ በዝርዝር ያቀርባል። ቀኑ "በስድስተኛው ዓመት፣ በስድስተኛው ወር፣ በዐምስተኛው ቀን " ነው፤ (ይኸውም ነሐሴ/ መስከረም) 592 ዓቅክ ነው። ራእይን የተቀበለው ሕዝቅኤል ነው። የተቀበለውም የይሁዳ ሽማግሌዎች በፊቱ ተቀምጠው ሳለ በቤቱ ተቀምጦ እያለ ነበር። የእግዚአብሔር እጅ በሕዝቅኤል ላይ መጣች ወደ ራእይም ውስጥ ይዛ አስገባችው። በ1፥1-3 እና በ8፥1 ያለውን የጊዜ ቅደም ተከተል ስንመረምር የኢየሩሳሌምን መከበብ በትእምርታዊ ሁኔታ በመግለጽ፣ ካየበት ከዐሥራ አራት ወር በኋላ ይህን እንዳየ እንረዳለን። አሁንም የይሁዳን ኀጢአት በመሸከም በየቀኑ በቀኝ ጐኑ እየተኛ ነበር (ከ4፥6 ጋር ያነጻ)። ሽማግሌዎቹ ምን ዐዲስ ነገር ይመጣል በሚል እየተደነቁ ትእምርታዊ ድርጊቱን ሳይከታተሉ አልቀሩም። ይህ በይሁዳ ላይ የሚመጣው ፍርድ ለእርሱ በተገለጠ ጊዜ ሕዝቅኤል በቀኝ ጐኑ መተኛቱ ተገቢ ነበር።

ከርቀትና ከጊዜ አንጻር ይህ ሁኔታ ሲመረመር እነዚህ ሽማግሌዎች ከይሁዳ ወደ ባቢሎን ከሕዝቅኤል ምክር ፍለጋ የመጡ በጊዜው የነበሩ የይሁዳ ሽማግሌዎች አልነበሩም። በተጨማሪም በዚህ ራእይ ላይ የታዩት የእነዚህ የይሁዳ ሽማግሌዎች አሳዛኝ ባሕርይ ለእውነተኛ መንፈሳዊ ጕዳይ ይህን አስቸጋሪ ጕዞ ወደ ባቢሎን ያደረጉ አያስመስላቸውም። ይልቁንስ በሕዝቅኤል ፊት ተቀምጠው የነበሩት ሽማግሌዎች ዳንኤል (605 ዓቅክ) እና ዮአኪን (597 ዓቅክ) ተማርከው ወደ ባቢሎን በተጋዙበት ጊዜ የይሁዳ ምርኮኞች መሪዎች ነበሩ።

የራእዩ ዋነኛ ሐሳብ በኢየሩሳሌም ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ምክንያቱ ምን እንደ ሆነ ማሳወቅ ነበር። የፖለቲካ መሪዎች፣ ነቢያትና ካህናት ይሁዳን በተቀደሱ መንገዶቿ እንዲመሩአት ይጠበቅባቸው ነበር። በዚህ ራእይ ሕዝቅኤል የተመለከተው በመቅደሱ ውስጥ ባለው በእግዚአብሔር ክብርና በአገሪቱ መሪዎች ሕይወት የሚታየውን ከፍተኛ የግብረ ገብና የመንፈሳዊ ውድቀት ንጽጽር ነው። የመሪዎቹ ሕይወት የተበከለ መሆኑ እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም ላይ ላመጣው ፍርድ ምክንያት ነው። በምዕራፍ 8 ላይ በቤተ መቅደሱ ግቢ ውስጥ የይሁዳ መሪዎች የፈጸሙት እጅግ አስጸያፊ የሆነው ጣዖት አምልኮ ተገልጦአል። በምዕራፍ 9-11 ቅዱሱ እግዚአብሔር በምዕራፍ 8 ላይ በተገለጠው አስጸያፊ ርኩሰት ላይ የሰጠውን ፍርድ እንመለከታለን። ቀስ በቀስ የእግዚአብሔር ክብር ከኢየሩሳሌምና ከይሁዳ ተወሰደ። የተሾሙ ሰዎች በዚህ የረከሰ የጣዖት አምልኮና በተከታዮቻቸው ላይ ይህን አስፈሪ ፍርድ እንዲያፈሱ ተጠርተዋል። የይሁዳ መሪዎች በ11፥14-21 ላይ በተለይ ተወግዘዋል፤ ነገር ግን ስለ ኀጢአተኛ መንገዳቸው ንስሓ የገቡ ታማኞቹ ትሩፋን ጥበቃ እንደሚያገኙ (9፥4) እንዲሁም በመጨረሻ መልሰው እንደሚቋቋሙና ነጻ እንደሚሆኑ ተረጋግጦላቸዋል (11፥14-21)።

ከቊ 1-6 ሕዝቅኤል ያየው ራእይ የሚጀምረው በምዕ 1-3 በኮቦር ወንዝ ካየው የእግዚአብሔር ክብር መገለጥ ጋር ተመሳሳይ ነው። በምዕራፍ 8 ላይ በሚገኘው ራእይ፣ በምዕራፍ 1 ላይ እንደ ተገለጸው ራእይ መልክ ያለው የሰው አምሳል (ከ1፥27 ጋር ያነጻ) ሕዝቅኤልን በራስ ጠጕሩ ይዞ በራእይ ውስጥ ወደ ኢየሩሳሌም በመንፈስ ወሰደው። እንዲህ ዐይነቱ የከበረ አካል በቤተ መቅደሱ ውስጥ ከተካሄደው እጅግ ከረከሰው ሃይማኖታዊ ሥርዐት ጋር በንጽጽር ቆመ።

ሕዝቅኤል በውስጠኛው አደባባይ በሰሜን በር ላይ በእግሩ ቆሞ ራሱን አገኘው፤ ይህ በር መሥዋዕት የሚቀርብበት መሠዊያ በበሩ ውስጥ ስላለ "የመሠዊያ በር" ተብሎ ይጠራል (ከዘሌ 1፥11 ጋር ያነጻ)። ሕዝቅኤል የቆመው በራሱ በውስጠኛ ው አደባባይ ሳይሆን፣ በውጪው አደባባይ ሆኖ በበሩ መግቢያ ላይ ነበረ። በስተ ሰሜን ወደ ውጪው አደባባይ ሲመለከት፣ "ቅናት የሚያነሣ"ውን "ጣዖት አየ።" ይህ ጣዖት የእግዚአብሔርን ቅናት አነሣሣ፤ ምክንያቱም በሙሴ ሕግ እግዚአብሔር እርሱ ብቻ አምላክ እንደ ሆነ (ዘፀ 20፥1-3)፤ ጣዖት አምልኮ ሁሉ የተከለከለ (ዘዳ 4፥16፤ 32፥16፡21) እንደ ሆነ ተናግሮአልና። ስለዚህ የጣዖቱ አገላለጽ ግልጽ አይደለም፤ ስለሆነም እንዲህ ነው ብሎ መናገር አይቻልም። ምናልባት ምናሴ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ያቆመው (2ነገ 21፥7፤ 2ዜና 33፥7) በኋላም የተወገደው (2ዜና 33፥15) አሁን እንደ ገና የተሠራውን የክነዓናውያን የልምላሜ አምላክ የምትባለው የሴት ጣዖት ምስል የአስታሮት ጣዖት ምስል ሊሆን ይችላል። ይህ ምስል በእስራኤላውያን ታሪክ ውስጥ በሕዝቡ ላይ ተጽዕኖ እንደ ነበረው የሚታወቅ ነው፤ ንጉሡ ኢዮስያስ በተሐድሶው ጊዜ አስወግዶት ነበርና (2ነገ 23፥6)። ነቢዩ ኤርምያስ ለሰማይ ንግሥት የሚደረገውን አምልኮ ያወገዘበት ሁኔታ ከዚህ ምስል ጋር ግንኙነት ሊኖረው ይችላል (ኤር 7፥18፤ 44፥17-30)።

"ከዚህም የባሰ አስጸያፊ ነገር ታያለህ" የሚለው አረፍተ ነገር በዐጭሩ የቅናት ጣዖትን ሁኔታ ያጠቃልላል። ይህ ማጠቃለያ በሂደት እየባሰ የሄደውን የይሁዳን ጣዖት አምልኮ አስከፊነት በአጽንዖት ያመለክታል።

ለ. የሽማግሌዎቹ ጣዖት አምልኮ (8፥7-13)

7-9 ሕዝቅኤል ወደ ሰሜኑ በር መግቢያ እንዲመጣ ተደረገ። በዚያም በግንቡ ውስጥ ቀዳዳን አየ፤ ግንቡን ነድሎ ወደ ውስጥ በመግባትም የእስራኤል ሽማግሌዎች በውስጠኛው አደባባይ በስውር ምን እየሠሩ እንደ ነበር እንዲያስተው ተነገረው። እነዚህ ሰባ ሽማግሌዎች ሙሴ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመምራት እንዲያግዙት በሾማቸው ሰባ ሽማግሌዎች አሺኗም ላይ በመመሥረት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ሹመታቸውን

በዚሁ ላይ መሠረት ያደረጉ የሕዝቡ መሪዎች ሳይሆኑ አይቀሩም (ዘፀ 24፥1:9፤ ዘኍ 11፥16-25)::

10-11 የሳፋን ልጅ ያእዛንያ (ምናልባትም የንጉሡ የኢዮስያስ ጸሓፊ ልጅ ሳይሆን አይቀርም፤ 2ነገ 22፥8-14፤ 2ዜና 34፥15-21፤ ኤር 26፥24፤ 29፥3 ወዘተ ይመ)፤ በግንቡ ላይ ለተቀረጹት የእንስሳት ዐይነት ሁሉ፣ በደረታቸው ለሚሳቡ ፍጡራን ሁሉና ለርኩሳን አራዊት ዐይነት ሁሉ ዕጣን ሲታጠን ሽማግለዎቹን ሁሉ ይመራ ነበር:: ምናልባት ርኩሳን አራዊት የተባሉት በዘሌ 11 ላይ የተገለጡት የረከሱ እንስሳት የተባሉት ሊሆኑ ይችላሉ::

12-13 እነዚህ የይሁዳ መሪዎች እያንዳንዳቸው በየጓዳቸው ውስጥ በጨለማ ለየጣዖቶቻቸው አስጸያፊ አምልኮ ያካሂዱ ነበር:: የእነዚህን የየግል ጓዳዎች ሁኔታ መግለጽ ያስቸግራል:: እነዚህ ጓዳዎች በውስጠኛውና በውጪው አደባባይ ግድግዳ በተሰይ የተሠሩ ይሁኑ ወይም በእያንዳንዱ ሽማግሌ ቤት ውስጥ ያሉ ጓዳዎች ይሁኑ አይታወቅም፤ እያንዳንዱም ሽማግሌ ይህን አስጸያፊ አምልኮ በግሉ ወይም በሕዝብ ፊት ያድርገው በግልጽ አልተመለከተም:: እንዲህ ዐይነት ጓዳዎች በሰሎሞን ቤተ መቅደስ በውስጠኛው አደባባይ ስለ መኖራቸው የታወቀ ባይሆንም በዐውደ ንባቡ መሠረት ቀደም ብሎ የተገለጸው ሐሳብ ይመረጣል::

እነዚህ ሽማግሌዎች ድርጊታቸውን ተገቢ ያደረጉት እግዚአብሔር እንደማያያቸው በመናገር ወይም ፈጽሞ እንደሌለ በማሰብ ነው:: በ605 ዓቅክ እና በ597 ዓቅክ በተፈጸመው ምርኮ ጉልሕ ሆኖ እንደ ታየው እርሱ ምድሪቱን ትቶአታል:: የእግዚአብሔርን መኖር፣ "እግዚአብሔር በዚያ አለ" የሚለውን ቀጥተኛ ስሙን በመቃወም ካዱ:: እግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ መገኘቱንና ሁሉን ማወቁን በመቃወም፣ "የዘላለም አምላክን ክብር ምዉት በሆነው ሰው፣ በወፎች፣ በእንስሳትና በምድር ላይ በሚሳቡ ፍጥረታት መልክ መስለው ለወጡ" (ሮሜ 1፥23) እንደሚል ቃሉ፣ ምርጫቸውን በጣዖታትና በምስል ላይ አደረጉ:: ሽማግሌዎቹ እግዚአብሔር ምድሪቱን ትቶአል በማለት እግዚአብሔር ለአብርሃም ለገባው ኪዳን ታማኝነቱን፣ ለመረጣቸው ሕዝቡ ያለውን ፍቅርና ፈጽሞ አለመለወጡን ካዱ:: በዚህ ዐይነቱ አስተሳሰባቸው የፈለጉትን ነገር ለማድረግ ለራሳቸው ፈቃድ ሰጡ:: እግዚአብሔር ካልኖረ፣ ማንም ስለ እርሱ የሚያስብ አይኖርም::

ሐ. ተመዝ የተባለው የሴቶች አምልኮ (8፥14-15)

14-15 የውስጠኛውን አደባባይና የሽማግሌዎቹን ርኩሰት ካየ በኋላ ሕዝቅኤል ወደ ውስጠኛው አደባባይ ሰሜን በር መግቢያ ዘወር አለ፤ በዚያም ሴቶች ተመዝ የተባለውን ጥንታዊውን የአካድያንን አምላክ እንዲሁም የአሸታር ባልና ወንድም የሆነውን ሲያመልኩ ተመለከተ:: የተመዝን ስም በኋላ ላይ ከአዶኒስና ከአፍሮዳይት ስም ጋር ተያይዞ እናገኘዋለን፤ እርሱም የልምላሜና የዝናም አምላክ ሲሆን ከሐዳድና ከበኣል ጋር ተመሳሳይ ነው:: በወቅታዊው አምልኮአዊ ዑደት አትክልቱ በጠወለገበት ቀደም ብሎ በጋው እንደ ገባ ሞተ:: አሸታር በምታለቅስበት ጊዜ ይነሣል፤ ይህም የሚታወቀው ቊጥቋጦው መብቀል ሲጀምርና ምድሪቱ መለምለም ስትጀምር ነው:: እንዲህ ዐይነቱ ተሐድሶ የሚበረታታውና የሚከበረው ወሲባዊ የሆነ ኢግብረ ገባዊነት በሚታይባቸው የልምላሜ በዓላት ነው::

የዚህ ራእይ ጊዜ ተመዝ የተባለው ይህ ጣዖት በምተበት ጊዜ ማለትም በነሐሴ/መስከረም ወር ነው:: ይህ ራእይ በታየበት በዚህ ጊዜ የፖለስቲና ምድር በበጋው ፀሓይ በደረቀበት ጊዜ እንዲሁም በተመዝ ሞት ሴቶቹ ባለቀሱበት ጊዜ ነው:: እነርሱም ምናልባት ተመዝ እንዲነሣ በማልቀስ የአሸታርን ሥርዐት ሳይከተሉ አልቀረም:: ይሁን እንጂ ከዚህም የባሰ አስጸያፊ ነገር ሕዝቅኤል ገና ያያል (ከቊ 6፥13 ጋር ያነጻ)::

መ. ለፀሓይ የሚደረግ አምልኮ (8፥16-18)

16 ሕዝቅኤል በቤተ መቅደሱ ውስጠኛ አደባባይ ዘወር ሲል ሃያ ዐምስት ሰዎች ጀርባቸውን ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሰጥተው ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ አድርገው ለፀሓይ ሲሰግዱ ተመለከተ:: የእነዚህ ሰዎች ማንነት አልታወቀም:: ምናልባት ከተጠቀሱት ሰባ ሽማግሌዎች መካከል ሳይሆኑ አይቀሩም:: ነገር ግን ከሰባዎቹ የተወሰኑት እንዲህ ለፀሓይ መስገዳቸው የሚገርም ነው:: ከዚህም በላይ ይህ ስፍራ የውስጠኛው አደባባይ መሆኑና ወደዚያም አደባባይ መግባት የሚፈቀድላቸው ካህናት በመሆናቸው (2ዜና 4፥9፤ ኢዩል 2፥17) እነዚህም ካህናት ሳይሆኑ አይቀሩም (ርግጠኛ ለመሆን ሰባዎቹ የእስራኤል ሽማግሌዎች የጣዖት አምልኮአቸውን በውስጠኛው አደባባይ ተግባራዊ ሲያደርጉም እንኳ ታይተዋል):: ተለይቶ የተመለከተው ሰባ ቊጥርና (ቊ 11) ሃያ ዐምስት የተጠቀሱት ምናልባት ሁለቱን ቡድን መለየት ይቻል ዘንድ ለመርዳት ነው:: ስለዚህ እነዚህ ሃያ ዐምስት ሰዎች ካህናት ሳይሆኑ አይቀሩም:: ይህ ከሆነ ሃያ ዐምስት የሚለው ቊጥር የሚያመለክተው ለሃያ አራቱ ካህናትና በተጨማሪም ለአንዱ ሊቀ ካህናት ለእያንዳንዱ አንዳንድ የውክልና ሥራ ነበረ ለማለት ነው (ከ1ዜና 23 ጋር ያነጻ):: ማንነታቸው ምንም ይሁን ምን ለፀሓይ የሚደረግ አምልኮ በሙሴ ሕግ በጥብቅ የተከለከለ ነው (ዘዳ 4፥19)፤ ሕዝቅያስና ኢዮስያስም ይህን የጣዖት አምልኮ ልምምድ በዘመነ መንግሥታቸው ከይሁዳ ማስወገድ ነበረባቸው (2ነገ 23፥5:11፤ 2ዜና 29፥6-7)::

17-18 የይሁዳ መሪዎች ክፋት ዐመፅ በምድሪቱ ላይ እንዲነግሥ ያደረገ መሆኑን በመግለጽ እነዚህ ቊጥሮች በዚህ ምዕራፍ ላይ የሚገኘውን የከፋ የጣዖት አምልኮ ያጠቃልላሉ:: ይህ ሁሉ እግዚአብሔርን በተደጋጋሚ ለቊጣ አነሣሥቶአል:: ከዚህም በላይ፣ "ቅርንጫፉን ወደ አፍንጫቸው አቅርበዋል::" የዚህ ሐረግ ትርጉም ችግር አለው:: የቃሉ መደበኛ ትርጉም "ቀንበጥ" የሚል ነው:: ምናልባት ይህን ትንሽ ቅርንጫፍ ወይም ቀንበጥ በአፍንጫ ማሽተት የፀሓይ አምልኮ የተለመደ ሥርዐት ሊሆን ይችላል፤ ይህም ሐሳብ ከዐውዱ ጋር የሚስማማ ነው:: ጉዳዩ ምንም ይሁን ይህ ድርጊት እግዚአብሔርን የሚያሳዝነው መሆኑ ዐውዱ ያመለክታል::

እነዚህ ሁሉ አስጸያፊ የጣዖት አምልኮ ሥርዐቶች የቅዱሱን የእግዚአብሔርን ቊጣ አምጥተዋል:: ስለሆነም ያለርኅራኄ ይፈርዳል ማለት ነው:: ሕዝቡ ከፍ ባለ ድምፅ ቢጮኹም እንኳ፣ ምሕረት እንዲመጣላቸው የሚያስሙትን ጩኸት ፈጽሞ አይሰማም:: ፍርድ መምጣቱ አይቀርም! የራእዩ ቀሪ ክፍልም በመቀጠል ይህንኑ ሐሳብ በአጽንዖት ይናገራል::

2. በኢየሩሳሌም ላይ የወረደ ፍርድና የእግዚአብሔር ክብር መሄድ (9፥1-11፥23)

ሀ. የጽሕፈት ዕቃ ማኅደር ያነገበ ሰው (9፥1-4)

1-2 ሕዝቅኤል በቤተ መቅደሱ ውስጠኛ አደባባይ ቆም የሚደረገውንም አስጸያፊ ርኩሰት ተመልክቶ ተደናግጦ ሳለ፤ እግዚአብሔር ከተማዪቱን የሚቀጡትን ሰዎች መምጣት ተናገረ:: ሕዝቅኤል "በሰሜን አቅጣጫ ካለው ከላይኛው በር" ማለትም ከውስጠኛው አደባባይ ሰሜን በር አቅጣጫ ሲመጡ አየ (ከ2ነገ 15፥35፤ ከ2ዜና 27፥3፤ ከኤር 20፥2፤ 36፥10 ጋር ያነጻ):: እያንዳንዱ ቀጪ አጥፊ የሆነ የጦር መሣሪያ በእጁ ይዞአል:: ሁሉም በአንድነት ተሰብስበው በነሐስ መሠዊያው አጠገብ ቆሙ:: ከእነርሱም ጋር ቀጭን በፍታ የለበሰ፣ በጕኑም የጽሕፈት ዕቃ ማኅደር ያነገበ ሰው ነበረ::

በሕዝቅኤል 8፥18 እግዚአብሔር ፍርድን በኢየሩሳሌም ላይ ያወጀበትን በራእዩ ውስጥ ሽግግርን ያቀርባል:: በእነዚህ ሰባት ሰዎች ፍርዱን ይፈጽማል፤ እነዚህም ከተማዪቱን ሊቀጡ የመጡ ስድስት ሰዎችና ቀጭን የበፍታ ልብስ የለበሰው ሰው ናቸው:: እግዚአብሔር የእስራኤል እውነተኛና ባለመብት አምላክ እንደ መሆኑ መጠን፣ ቅዱስና ጻድቅ የሆነው አምላክ የጣዖት አምልኮ ተገቢ ስፍራውን እንዲወስድበት አይፈቅድም:: በግጻዌ መስኮት ክብርና የጽሕፈት ዕቃ ማኅደር ያነገበው ሰው በለበሰው ቀጭን የበፍታ ልብስ በኩል የታየው ቅድስና የፍርዱ መሠረት ነው:: ቀጭን የበፍታ ልብስ አብዛኛውን ጊዜ የእግዚአብሔር መልእክተኞች ይለብሱታል (ከዳን 10፥5፤ ከራእ 15፥6 ጋር ያነጻ)፤ ለክህነት አገልግሎትም የሚለበስ መለያ ልብስ ነው (ዘፀ 28፥42)፤ ስለዚህ የበፍታ ልብስ የእግዚአብሔርን ንጽሕናና ቅድስና ያመለክታል:: በሌላ በኩል ፍርድ የሚካሄደው በነሐሱ መሠዊያ አጠገብ በቆሙት በእነዚህ ሰዎች እንደ ሆነ በአጽንዖት ተነግሮአል፤ መሠዊያው

መሥዋዕታዊ ፍርድ የሚሰጥበት እንደመሆኑ፣ ሰዎቹ የተሰጣቸውን ኀላፊነት ለመፈጸም በዚያ ተዘጋጅተው ቆመዋል።

3 የከበረው እግዚአብሔር ከነበረበት ከኪሩብ በላይ ተነሥቶ ወደ ቤተ መቅደሱ በር ሲሄድ፣ እነዚህ ሰዎች ይህን ፍርድ እንዲፈጽሙለት ኀላፊነቱን ሊሰጣቸው ተዘጋጅቶ ነበር። በራእዩ ውስጥ በ8፥2 ባለው ሰው ላይ የታየው የእግዚአብሔር ክብር ከኪሩቤል የዙፋን ሠረገላ ተለይቶ ከቅድስተ ቅዱሳኑ (ከ8፥4 ጋር ያነጻ) ወደ ቤተ መቅደሱ በር ሳይንቀሳቀስ አልቀረም። ከዚያም እግዚአብሔር ከሕዝቡ ተለይቶ ለፍርድ የተዘጋጀበት ሁኔታ ጀመረ ማለት ነው። ፍርድ አይቀሬ ሆኖ እያለ የእግዚአብሔር ክብር በቅድስተ ቅዱሳኑ በቃል ኪዳን ታቦቱ ላይ ወይም በእግዚአብሔር ፍርድ ሀልዎት ፊት ፈጽሞ ሊገኝ አይችልም። ስለዚህ እግዚአብሔር ግልጽ በሆነ መንገድ በሕዝቡ ላይ ሊፈርድ መዘጋጀቱን ለማሳየት፣ የፍርድ አፈጻጸሙን ለሰዎቹ በኀላፊነት ይሰጣቸው ዘንድ ክብሩን ከቅድስተ ቅዱሳኑ ወደ ቤተ መቅደሱ በር እንዲሄድ አደረገው።

4 እግዚአብሔር ቀጭን የበፍታ ልብስ የለበሰውንና የጽሕፈት ዕቃ ማኅደር ያነገበውን ሰው በኢየሩሳሌም ከተማ በመዘዋወር ስለ ከተማዪቱ ኀጢአት እውነተኛ ኀዘንና ጸጸት በነበራቸው ሰዎች ግምባር ላይ ምልክት እንዲያደርግ አዘዘው፤ እነዚህ ሲያዝኑና ሲያለቅሱ የነበሩ ሰዎች በኢየሩሳሌም ከተማ የሙሴን ሕግ የሚላረሩ የአሕዛብ መንገዶችን ያዩና ሕጉ በከተማዪቱ ውስጥ በትክክል እንዲፈጸም የሚሹ ናቸው። ይህ ሰው በግምባሮቻቸው ላይ ምልክት የሚያደርገው ምልክቱ በቅርብ ሊመጣ ካለው ፍርድ እንዲጠብቃቸው ነው (ከራእ 7፥3፤ 9፥4፤ 14፥1 ጋር ያነጻ)። እነዚህ ሰዎች በልባቸው ውስጥ የጽድቅ ሐሳብ አለ።

ለ. ከተማዪቱን እንዲቀጡ የታዘዙት የወሰዱት የፍርድ ርምጃ (9፥5-8)

5-7 እግዚአብሔር ስድስቱን ሰዎች በከተማዪቱ ውስጥ በመዘዋወር ላይ የነበረውን የጽሕፈት ዕቃ ማኅደር ያነገበውን ሰው እየተከተሉ ጸታና ዕድሜ ሳይለዩ ምልክቱ በግምባሮቻቸው ላይ ባልተደረገላቸው ሰዎች ላይ ፍርዱን እንዲፈጽሙ አዘዛቸው። እነዚህም ሰዎች በውስጠኛው አደባባይ በድብቅ በግንቡ ላይ ተቀርጸው ለነበሩት እንስሳት ሲሰግዱ በነበሩት ሰባ ሽማግሌዎች ፍርዱን ጀመሩ። ፍርዱ መንፈሳዊ አመራር ሊመጣበት ከሚገባው ማእከል ከቤተ መቅደሱ ተጀመረ (ከ1ጴጥ 4፥17 ጋር ያነጻ)። ይሁን እንጂ የይሁዳ አመራር የተበላሸ ነበር። ስለዚህ የቤተ መቅደሱ አደባባይ የአሕዛብን አማልክት ባመለኩ በእነዚህ ሰዎች ደም ይረክሳል (ከዘኁ 19፥11፤ ከ2ነገ 23፥16 ጋር ያነጻ)።

8 ሕዝቅኤል በውስጠኛው አደባባይ ከፍርዱ እንደ ተረፈ ራሱን ብቻ ሲመለከት፣ ብዙ ሕዝብ በእነዚህ ሰዎች እንደ ተገደለ በማስተዋሉ እጅግ ደነገጠ። ጨካኝ መስሎ ቢታይም፣ ልቡ ለእግዚአብሔርና ለሕዝቡ ላለው ፍቅር እጅግ ተናወጠ። የይሁዳን ትሩፋን በሙሉ እንዳያጠፋቸው እግዚአብሔርን ተማጠነው። ከእስራኤል ነገዶች የቀረው ነገድ የይሁዳ ነበር፤ ከዚሁም ነገድ አንዳንዶቹ አስቀድሞ በምርኮ ወደ ባቢሎን ሄደዋል (605 ዓቅክ እና 597 ዓቅክ)። የአሁኑ ፍርድ በእነዚህ ስድስት ሰዎች እንደ ተገለጸው የተረፈውን የይሁዳ ነገድ ፈጽሞ የሚያጠፋ ይመስላል።

ሐ. የእግዚአብሔር ፍርድ ትክክለኛነት (9፥9-11)

9-10 ሕዝቅኤል ለጠየቀው ጥያቄ የእግዚአብሔር ምላሽ የይሁዳ በደል እጅግ የከፋ እንደ ነበር እርሱን ማስታወስ ነው። ሕዝቡ እግዚአብሔር እኛን ስለ ተወን እኛ የምናደርገውን አያይም ብለው በማሰብ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ረስተዋልና ዐመፅና መንፈሳዊ ጥመት ምድሪቱን ሞልቶአታል። የእግዚአብሔርን ሁሉን ዐዋቂነት፣ በሁሉ ስፍራ መገኘትና ታማኝነት ካዱ። እግዚአብሔር አልተወም፤ ይሁዳን አሁን ስለ በደልዋ እየፈረዳበት ነውና፤ ማንንም አያስተርፍም። የሕዝቡን ርኩሰት ያውቃል፤ ለዚያ የሚገባቸውን ይሰጣቸዋልና።

11 የይሁዳ ሕዝብ በሙሉ ከእግዚአብሔር እንዳልራቀ ለሕዝቅኤል መበረታቻ ይሆነው ዘንድ የጽሕፈት ዕቃ ማኅደር ያነገበው ሰው፣ "እንዳዘዝኸው ፈጽሜአለሁ" የሚል መልስ ሰጠ። በሌላ አነጋገር በጻድቃኑ ግምባር ላይ ሁሉ ምልክት ተደርጎ አብቅቶአል ማለት ነው።

መ. በኢየሩሳሌም ላይ የተበተነው የእሳት ፍም (10፥1-7)

1-2 እግዚአብሔር በፍታ የለበሰውን ሰው ከኪሩቤል ራስ በላይ ካለው ጠፈር ከፍ ብሎ የሰንፔር ዙፋን ከሚመስለው (ከምዕራፍ 1 ጋር ያነጻ) ከተማዪቱን ንጹሕ ያደርጋት ዘንድ (ከኢሳ 6 ጋር ያነጻ) የእሳት ፍም ወስዶ እንዲበትን አዘዘው።

4-5 ይህ መግቢያ መቼቱን የሚያብራራ ነው። የኪሩቤል ዙፋን ሠረገላ ከቤተ መቅደሱ በስተ ደቡብ በውስጠኛው አደባባይ ነበረ። የቤተ መቅደሱ አደባባይ በስድስቱ ሰዎች ነጽቶ ነበረ፤ የእግዚአብሔርም ክብር ወደ ቤተ መቅደሱ በር ሄደ። ከዚያም ቤተ መቅደሱንና አደባባዩን ሁሉ ሞላው።

6-7 የበፍታ ልብስ የለበሰው ሰው ከኪሩቤል የእሳት ፍም እንዲወስድ የታዘዘውን የእግዚአብሔር ትእዛዝ በታማኝነት ፈጸመ። በዚህ ስፍራ ኪሩብ የተባለው የ"ኪሩብ" ፊት ያለው ሕያው ፍጡር ሳይሆን አይቀርም። እርሱም የእሳቱን ፍም የበፍታ ልብስ ለለበሰው ሰው ሰጠው።

ሠ. ኪሩቤልና ኢካቦድ (10፥8-22)

8-17 20-22 በዚህ ምንባብ በምዕራፍ 1 ላይ ሕያዋን ፍጡራን ሲባሉ የነበሩት "ኪሩቤል" ተብለው ተጠርተዋል። በሕዝቅኤል መጽሐፍ ውስጥ እንደ ዐዲስ ቢቀርቡም ኪሩቤል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሌላ ስፍራ ተጠቅሰዋል። በጥንታዊዋ ቅርብ ምሥራቅ የአንበሳ ወይም የበሬ አካል እንዲሁም የሰው ራስ ያለውና ባለ ክንፍ ስፊኒክስ "ኪሩብ" በመባል ብዙ ጊዜ ይታወቅ ነበር። በኪዳኑ ታቦት ላይ ሆነው እነርሱም አምልኮ ቢፈጽሙም (ዘፀ 25፥18-20) የብሉይ ኪዳን ኪሩቤል በመሠረቱ የሚታወቁት ጠባቂና ከለላ በመሆን ነው (ከዘፍ 3፥24 ጋር ያነጻ)። ምናልባት እንደ ዙፋን ሠረገላ (ከ1ሳሙ 4፥4፤ ከ2ሳሙ 6፥2፤ ከ2ነገ 19፥15፤ ከ1ዜና 13፥6፤ 1ዜና 28፥18፤ ከመዝ 18፥10፤ 80፥1፤ 99፥1 ጋር ያነጻ) የእግዚአብሔር ክብር ጠባቂና ዘብ ነበሩ።

18-19 በዚህ ራእይም ሆነ በሕዝቅኤል መጽሐፍ ውስጥ ዋነኛው ፍሬ ሐሳብ የእግዚአብሔር ክብር ትቶ መሄድና ተመልሶ መምጣት ነው። በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ርኩሰት ስላለ ቤተ መቅደሱን ትቶ ሄደ፤ ነገር ግን ምድሪቱን ፈጽሞ ካነጻ በኋላ በመጨረሻው ጊዜ ይመለሳል (ከ43፥1-9 ጋር ያነጻ)። የእግዚአብሔር ክብር ቀስ በቀስ ትቶ መሄዱን የጀመረው በ9፥3 እና በ10፥4 ላይ ነው፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ክብር ቅድስተ ቅዱሳንን ትቶ ወደ ቤተ መቅደሱ በር ሲሄድ ነው። የእግዚአብሔር ክብር ከቤተ መቅደሱ በር ተነሥቶ በኪሩቤል የዙፋን ሠረገላ ላይ ተቀመጠ። ክብሩና ኪሩቤል በአንድነት ከቤተ መቅደሱ ወደ ምሥራቅ በር አመሩ፤ ከዚያም በመጨረሻ ለቅቀው ሄዱ (ከ11፥22-23 ጋር ያነጻ)። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያመለክተው (ዘዳ 31፥17፤ ሆሴ 9፥12) እንዲህ ዐይነቱ መለየት የሚከሠተው ሕዝቡ ከእግዚአብሔር መንገድ ዘወር ሲሉ መሆኑን ነው። በ1ኛ ሳሙኤል 4 ላይ ተመሳሳይ የሆነ የእግዚአብሔር ክብር መልቀቅ በፍርድ ጊዜ በካህኑ ዔሊ የልጅ ልጅ ስም "ኢካቦድ" (1ሳሙ 4፥21) ማለትም "ክብር የለም" በሚለው ይታወሳል። አሁንም ቢሆን በሕዝቅኤል ዘመን እግዚአብሔር በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ላይ "ኢካቦድ" በሚል።

ረ. ፍርድ በኢየሩሳሌም መሪዎች ላይ (11፥1-3)

1 ሕዝቅኤል የእግዚአብሔር ክብር በቤተ መቅደሱ ሕንጻ ወደ ምሥራቅ በር እየመራ መሆኑን ሲመለከት፣ መንፈስ ወደዚያ በር እርሱኑ አመጣው። በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል የሕዝቡ አመራር የሚፈጽመውን ክፋት አሳየው። ሃያ ዐምስት ሰዎች በአንድነት ተሰብስበው በሕዝቡ መሪዎች በአዙር ልጅ በያእዝንያንና በበናያስ ልጅ በፈላጥያን ይመሩ ነበር (እነዚህ ሃያ ዐምስት የፖለቲካ መሪዎች በ8፥16 ላይ ካሉት ሃያ ዐምስት ፀሓይ አምላኪዎች የተለዩ ነበሩ)።

2-3 እነዚህ መሪዎች ለሕዝቡ ሐሰተኞና መጥፎ ምክር ሰጥተዋል። የኢየረሳሌምንና የይሁዳን ነዋሪዎች በማታለል፣ ነቢያት በተከታታይ የሚመጣውን የባቢሎናውያንን ጥፋት በተመለከተ የሰጡትን ማስጠንቀቂያ በማጣመም ቤቶችን እንዲሠሩ በማደፋፈር በዚህ ጊዜ ክፉ ዕቅድ አውጥተው ነበር። እነዚህ መሪዎች ምንም አደጋ አይመጣም በሚል ኑሮ የተመቻቸውና ደንታቢሶች ነበሩ። የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች በኢየሩሳሌም ቅጥር ውስጥ በሙሉ ዋስትና ይኖራሉ በማለት “ይህች ከተማ ድስት ናት፤ እኛም ሥጋዎች ነን” የሚለውን ምሳሌ ያውጁ ነበር። ድስት በላዩ ላይ ያለውን ሥጋ እንደሚጠብቅ ሁሉ ድስቲቱ ኢየሩሳሌም ሥጋ ለሆኑት ኗሪዎቿ ዋስትናን (ጥበቃን) ትሰጣለች። እንደ ሕዝቅኤል ያሉ ነቢያት በጊዜው ያልተለመደ መልእክት የሚናገሩ የሳቱ ሰዎች በመባል ይፈረጁ ነበር።

4-6 ሕዝቅኤል በእነዚህ ሃያ ዐምስት ሰዎች ላይ የፍርድ ንግርን ተነበየ። ክሱ በቁ. 5-6 የተገለጸ ሲሆን፣ ፍርዱ ደግሞ በቁ. 7-12 ላይ ተገልጾአል። ለእነዚህ መሪዎች ያሳሰባቸው የፈጸሙት ድርጊት ከእግዚአብሔር የተሰወረ አለመሆኑ ነው። እግዚአብሔር ያስቡት የነበረውን፣ የተናገሩትንና ያደረጉትን በትክክል ያውቃል። የነቢያትን ማስጠንቀቂያ እንደ ተቃወሙ፣ የሕጉን የጽድቅ መሠረት በጣዖት አምልኮ እንደ ለወጡ እንዲሁም ተንኰል በተሞላው ዕቅዳቸው የኢየሩሳሌምን ነዋሪዎች እንደ ገደሉ ያውቃል።

7-12 ሕዝቡ በቁ. 3 ላይ በምሳሌያዊ አነጋገር እንደ ገለጹት ፍርዱም በተመሳሳይ ምስያ ተገልጾ ነበር። የኢየሩሳሌም ድስት እነዚህ ክፉ መሪዎች ያረዱአቸውን ጻድቃንን ብቻ ትጠብቃለች። እነዚህ ብልሹ መሪዎችና ተከታዮቻቸው ከኢየሩሳሌም ድስት ይወጣሉ፤ በባዕዳንም አስፈሪ ሰይፍ ይመታሉ። በምድሪቱ ባጠቃላይ ያሉትን የይሁዳን ሰዎች በማረድ ባቢሎን ይህን ፍርድ ትፈጽማለች (ከ2ነገ 25፥18-21 ጋር ያነጻ)። ኢየሩሳሌም በ586 ዓ.ክ በናቡከደነፆር እጅ ስትወድቅ፣ የይሁዳ መሪዎችና ሕዝባቸው እግዚአብሔር በእውነት አምላክ እንደ ሆነ ያውቃሉ። በእርሱ ሕግ መሠረት ባልኖሩት ላይ ያወጀውን የጽድቅ ፍርድ በታማኝነት እንደሚፈጽም ያስተውላሉ። እስራኤል ብትታዘዝ ኖሮ በሕይወት በኖረች ነበር (ዘሌ 18፥5)። ነገር ግን በዙሪያዋ እንደሚኖሩት አሕዛብ የጣዖት አምልኮን መንገድ መረጠች፤ ስለሆነም የሕጉን በረከት ከመቀበል ይልቅ መርገሙን ተቀበለች።



አንዳንዶች ምንም ዐይነት ስንጥቅ የማይታይባቸው ትልልቅ ማብሰያ ድስቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስፍራዎች በአርኪዎሎጂስቶች ሲቈፈሩ ብዙ ጊዜ ተገኝተዋል።

13 ሕዝቅኤል ይህን መልእክት ለመሪዎች እየተናገረ ሳለ ፈላጥያ ሞተ። ፈላጥያ የሕዝቅኤልን ትንቢት ሰምቶ አልሞተም፤ ነገር ግን የፈላጥያ ሞት ወሬ ሕዝቅኤል እውነተኛ ነቢይ መሆኑን አረጋገጠ። ይህ የትንቢቱ አስደንጋጭ ውጤት ሕዝቅኤል እግዚአብሔርን እንደ ገና እንዲፈራና እግዚአብሔርም የእስራኤልን ትሩፋን ሁሉ እንደሚያጠፋ እንዲያስብ አደረገው።

ሰ. የትሩፋኑ የወደፊት ዕጣ ፈንታ (11፥14-21)

14-15 ሕዝቅኤል ለይሁዳ ትሩፋን የነበረው ታላቅ ጭንቀት በእግዚአብሔር ዘንድ አልተዘነጋም። እግዚአብሔር በመልእክቱ እርሱንና ትሩፋኑን፣ ዘመዶቹን ሆነ ብሎ በምርኮ እንደሚጠብቃቸው በመንገር አበረታታው። የይሁዳ ዜጋዎች ምርኮኞቹን ከሕዝቡ መካከል የረከሱና ኀጢአተኞች አድርገው ይቈጥሩ ነበር። በምርኮ እንዲጋዙ በማድረግ እግዚአብሔር አልፈረደባቸውምን? የይሁዳ ሰዎች ምርኮኞቹ በተቻለ መጠን ከእስራኤል ምድር ርቀው እንዲሄዱ ያበረታቱአቸው ነበር፤ ያንን ስፍራ ለኀጢአተኞቹ ምርኮኞች ሳይሆን አሁንም በይሁዳ ላሉት ሰጥቶአቸው ነበርና።

16-20 በአንጻሩ እግዚአብሔር አሁን ለተጋዙት ትሩፋን እንክብካቤ እንደሚያደርግ ይናገራል፤ ምርኮኞቹንም ሰብስቦ ወደ ተስፋዱቱ ምድር እንደሚመልስ ተስፋ በመስጠት እንክብካቤውን ያሳያቸዋል። ወደፊት ስለሚፈጽመው መልሶ መቋቋም በሕዝቅኤል መጽሐፍ ላይ በመጀመሪያ የምናየው እዚህ ላይ ነው። አብዛኛዎቹ ነቢያት መልሶ መቋቋም ለጻድቃን ቀጣይ ተስፋ እንደ ሆነ ተናግረዋል። በሙሴ ሕግ መሠረት ነቢያት ሁሉ ለይሁዳ ስለ ኀጢአት የሚሰጧት ፍርድን ነው። በረከት በሙሴ ሕግ የታወጀ ቢሆንም እንኳ (ዘሌ 26፥40-45፤ ዘዳ 30፥1-10) በምድሪቱ ላይ መልሶ የመቋቋም ተስፋ መሠረት የተደረገው ለአብርሃም (ዘፍ 12፥1-3)፣ ለዳዊት (2ሳሙ. 7፥12-16) እና ለኤርምያስ (ኤር 31፥31-34) በተሰጠው ዘላለማዊ ኪዳን ነው።

በምርኮው ዘመን እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሁልጊዜ አመች የሚሆን ማደሪያ መቅደስ ይሆናል፤ በየትም ቢበተኑም የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ይሰጣቸዋል። ይህ ዛፊም ለሚያምኑት በምንም ዐይነት ሁኔታ ውስጥ ቢገኙም የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ የሚያደርግላቸው ምን ጊዜም የሚገኘው ያው እግዚአብሔር ነው። ከዚያም እግዚአብሔር የእስራኤልን ትሩፋን ከቀጣ በኋላ (1) ዳግም ይሰበስባቸዋል (2) በእስራኤል ምድር ላይ መልሶ ያቋቁማቸዋል፣ (3) ምድሪቱን ከርኩሰትዋ ያነጻታል፤ እናም (4) ከእነርሱም ጋር ዐዲሱን ኪዳን ይፈጽማል።

በኤር 31፥31-34 የተሰጠው ዐዲሱ ኪዳን የሚያመጣው የተለወጠን ልብና ዐዲስን መንፈስ ነው። ይህ ዐዲሱ መንፈስ እንደሚወርድ በነቢያት የተነገረው መንፈስ ቅዱስ ሲሆን (ዘዳ 30፥6፤ ኤር 31፥33፤ ኢዩል 2፥28-29)፣ በይበልጥ በሕዝ 36፥26-27 ባለው ተብራርቶ በሐሥ 2 ላይ የመጀመሪያው ምልክት ተፈጽሞአል። ዐዲሱ ልብና መንፈስ በእግዚአብሔርና በመንገዶቹ ላይ ጠንክሮ የነበረውን አሮጌውን የእስራኤል ድንጋይ ልብ አስወጥቶ (ዘካ 7፥12) የሚገባ ነው። ሕዝቡ በሙሴ ሕግ መሠረት እግዚአብሔርን በመፍራት መኖር እንዲችሉ የሚያደርጋቸውን ኀይል ያገኛሉ። በመጨረሻም በሙሴ ሕግ መሠረት ሊኖር የሚገባው ሕይወት ምሳሌ ይሆናሉ፤ ይኸውም እነርሱ የእግዚአብሔር ሕዝብ፣ እርሱም የእነርሱ አምላክ ይሆናል ማለት ነው።

ስለ ኀጢአት አንድ ጊዜ በመሞቱ የዐዲስ ኪዳን መካከለኛ የሆነው ክርስቶስ (ዕብ 8፥6) አማኞች የመንፈስ ቅዱስን መለኮታዊ ችሎታ ተቀብለው እንዲኖሩ አስችሎአቸዋል፤ ከዚህም የተነሣ እነርሱም በእግዚአብሔር የጽድቅ መለኪያ መሠረት መኖር ይችላሉ። ይህም ከሞት በተነሣው በመሲሑ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እምነታቸውን ለሚያደርጉ ሁሉ የተሰጠ ነው።

21 ይሁን እንጂ ንስሓ የማይገቡትና እርሱንም የማይከተሉት በኀላፊነት እንደሚጠየቁና እደሚፈርድባቸው እግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ ሰጥቶአቸዋል።

ሸ. የእግዚአብሔር ክብር ከኢየሩሳሌም ለቅቆ መሄዱ (11፥22-25)

22-25 ወደፊት የይሁዳ ትሩፋን መልሰው እንደሚቋቋሙ በመንገር፣ እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን ካበረታታው በኋላ፣ ክብሩ

ከኢየሩሳሌም ለቅቆ ወደ ምሥራቅ ወደ ደብረዘይት ተራራ ሄደ። ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔር ሀልዎት (በ43፥1-4 እስኪመለስ ድረስ) ከእስራኤል ተወሰደ። ፍርድ አሁን የማይቀር ሆነ! ሕዝቅኤል በራእይ ወደ ባቢሎን ተመለሰ፤ ራእዩም ቆመ። ከዚያም በትእምርት ከበባውን ሲመለከቱና በራእይ መወሰዱንም ሲያዩ ወደ ነበሩት ወደ ምርኮኞቹ ተመልሶ ራእይን በአጠቃላይ ይነግራቸው ጀመር።

፪ሐ. ምርኮኞቹ ለነበራቸው የእንመለሳለን ከንቱ ተስፋ እግዚአብሔር የሰጠው ምላሽ (12፥1-19፥14)

1. አሳዛኙ የምርኮ ሁኔታ (12፥1-20)

ሀ. መግቢያ (12፥1-2)

1-2 የመግቢያው ሐረግ ዐዳዲስ መልእክቶች እንደሚጀምሩ የሚያስክት ነው። ሁልጊዜ ሕዝቅኤል ለዐዳዲስ ራእዮችም ሆነ ንግሮች ግልጽ የሆኑ ወቅቶችን ያመለክታል። ምንም ዐይነት ዐዲስ የጊዜ ቅደም ተከተል ባይሰጥም፣ ከምዕራፍ 12-19 ያሉት ንግግሮችም በዋነኛ ሐሳባቸው ካለፈው ራእይ ጋር የተቀራረቡ ቢሆንም፣ እነዚህ መልእክቶች የተነገሩት ሕዝቅኤል ከምዕራፍ 8-11 ያለውን ራእይ ከብራራ በኋላ ነው።

ሕዝቅኤል የሚኖረው "በዐመፀኛ ሕዝብ መካከል መሆኑን እግዚአብሔር ወዲያውኑ አሳሰበው። ሕዝቅኤል ስለዚሁ ሁኔታ በመጀመሪያ ተልእኮውን በተቀበለ ጊዜ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ነበር (2፥3-8)፤ አሁን ግን ያን እውነታ ተመክሮው ያደርጋል። ምርኮኞቹ ከዓመት በላይ ትእምርታዊ ድርጊቱን ሲያዩና የፍርድ ንግሮቹን ሲሰሙ ነበር። በተቻለው ሁሉ ፍርድ እንደሚመጣ፣ የፍርዱን ከባድነትና የሚመጣበትን ምክንያት ሲነግራቸው ነበር (ምዕ 4-11)። ሽማግሌዎቹ ጆሮም ሆነ ዐይን ቢኖራቸውም አንድም መልእክቶቹን አልሰሙም፤ አሊያም ከምዕራፍ 8-11 ያሳያቸውን ምልክቶች አላዩም (ከኢሳ 6፥9-10፤ ከኤር 5፥21 ጋር ያነጻ)። ሕዝቅኤል ለዚህ ዐመፅ መናገር ነበረበት።

ምርኮኞቹ የሕዝቅኤል ማስጠንቀቂያዎች የሚያስከትሉትን ከባድ ውጤቶች ልብ አላሉም ነበር። አሁንም ከጊዜው በፊት ወደ ፖለስቲና እንደሚመለሱ ተስፋ ያደርጉ ነበር፤ ኢየሩሳሌምና ይሁዳ በቀጣይነት መጠበቃቸው። የዋስትና ምልክት እንደ ሆነ ዐሰቡ። መቼም ኢየሩሳሌም ዘላለማዊት ከተማ ናት። ከምዕራፍ 12-19 ባሉት በሕዝቅኤል ማስጠንቀቂያዎች ላይ እንዳደረጉት ሁሉ ስለ ተስፋቸውና ስለ ዋስትናቸው አያሌ ምክንያቶችን አቅርበዋል።

በመጀመሪያ ነገር፣ ሕዝቅኤል እንደ ተናገረው ፍርድ የሚመጣ ከሆነ (ምዕራፍ 12)፣ በእነርሱ የሕይወት ዘመን አይመጣም። ሁለተኛ ነገር፣ ሕዝቅኤል ከብዙዎቹ ነቢያት አንዱ ብቻ ነው። አያሌ ወንድና ሴት ነቢያት ተስፋንና መልካም ጊዜ የሚመጣበትን ምክንያት ተናግረዋል። ታዲያ ሕዝቡ ሕዝቅኤልን ለምን ይሰሙታል (ምዕራፍ 13) ሦስተኛ፣ ለሚመጣው ፍርድ በመጨረሻ ተጠያቂ መሆን ያለባቸው መሪዎች ናቸው፤ ፍርድ የሚመጣ ከሆነ፣ በእነርሱ ላይ እንጂ በምርኮኞች ላይ አይሆንም (ምዕ 14)። አራተኛ፣ እውነተኛ የፍርድ አዳጋ የሚከሠት ከሆነ፣ በእግዚአብሔር ፊት እንዲማልድላቸው ጻድቅ ሰው ብቻ መፈለግ አለባቸው፤ ከዚያም ከፍርድ ያመልጣሉ (ምዕ 14)። ዐምስተኛ፣ እግዚአብሔር ራሱ በመረጠው ሕዝብ ላይ ይፈርዳል ብሎ እንዴት ሕዝቅኤል ሊያምን ይችላል? ይህን ፈጽሞ አያደርገውም (ምዕ 15-16)። ስድስተኛ፣ ስለ አባቶች ኀጢአት በማንም ላይ መፍረድ ለእግዚአብሔር የሚገባ አይደለም። ሕዝቡ ያሰቡት ሕዝቅኤል ተቃራኒውን እንደሚናገር ነው (ምዕ 17)። ሰባተኛ፣ በርግጥ ፍርድ የሚመጣ ከሆነ፣ ለማስቆም የሚያደርጉት ምንም ዐይነት ነገር አይኖርም፤ ስለ አባቶቻቸው ኀጢአት ዋጋ እንዲከፍሉ ሆነዋልና። ንስሓ ቢገቡም እንኳ ምንም ለውጥ አይመጣም (ምዕ 18)። ስምንተኛ፣ በጊዜው የነበረው የይሁዳ ገዥ ሴዴቅያስ ሊታመን ይገባዋል። የባቢሎንን ቀንበር ከላያቸው ላይ ያነሣል (ምዕ 19)።

ሕዝቅኤል በትዕግሥት፣ በዘዴና በብርቱ ሐሳብ የምርኮኞቹን የዋህ አመለካከት ለመጋፈጥ እንዲሁም እርሱ ለሰጣቸው የፍርድ ማስጠንቀቂያ ለሚያቀርቡት መነሻ ምንጭ የሚገባ መልስ ለመስጠት ሞከረ። ሕዝቅኤል አሳማኝ ሐሳቦቹን አቅርቦ ከፈጸመ በኋላ ምንም ዐይነት ምክንያት ሳይዳሰስ አልቀረም።

በሕዝቅኤል ትንቢት ሂደት ውስጥ መሠረታዊ የሆነ አካሄድን መመልከት ይቻላል፤ እያንዳንዱ ራእይ ተከታይ መልእክት ያለው ሲሆን፣ መልእክቱም በራእይ ውስጥ ያለውን ሐሳብ እያሰፋ የሚያዳብር ነው። ለምሳሌ፣ ሕዝቅኤል ተልእኮውን የተቀበለበትን ራእይ (ምዕራፍ 1-3) በኢየሩሳሌም ላይ ስለሚመጣው ፍርድ የተነገረው መልእክት ተከትሎት ነበር። በቤተ መቅደስ ውስጥ የኢየሩሳሌም ሃይማኖታዊ ርኩሰት ራእይና በምዕ 8-11 ላይ የሚገኘው ፍርድ የአገሪቱ ኀጢአት እምብርት በመሆን የይሁዳን መሪዎች ሁሉ (ነገሥታት፣ ነቢያትና ካህናት) ኀጢአት በሚያዳብረው በምዕ 12-19 ላይ አሁን ተብራርቶአል። እነዚህም ምዕራፎች አጽንዖት የሚያደርጉት ብልሹ በሆነው አመራርና በሚመጣው ፍርድ ምክንያቶች ላይ ነው።

ለ. በምርኮ የመወሰድ ሥዕል (12፥3-16)

3-7 ሕዝቅኤል በትእምርት የሚያሳየው ድርጊት ያለጥርጥር በጉጉት ሊመለከቱ የሚችሉ ሰዎችን ስቦአል። የሕዝቅኤልን የቀደሙ መልእክቶች ፋይዳ ምርኮኞቹ ይህን ያህል ልብ ባይሉም፣ አሁንም እግዚአብሔር በቸርነቱ ማስጠንቀቂያውን ወደ እነርሱ ለማቅረብ ፈለገ። ምናልባት በዚህ ጊዜ ልብ ሊሉ ይችሉ ይሆናል። እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን ሁሉም ሊያየው የሚችለውን ትዕይንት እንዲያሳይ በተደጋጋሚ ያደፋፍረው ነበር። ሕዝቅኤል ለእነርሱ "ምልክት" ይሆናቸዋል።

ስለዚህ ሕዝቅኤል ለሚያየው ሰው ሁሉ የተለመደ የሆነውን ነገር እንዲተውን ተነግሮት ነበር፤ ይኸውም በምርኮ የመሰደድን ሂደት ነው። በቀን አንድ ስደተኛ ይዞ ለመሰደድ የሚችለውን አነስተኛ ጓዝ ጠቀለለና ሁሉም ሰው ሊያየው ወደሚችለው ቦታ ይዞ መጣ። በምሽትም በቤቱ ውስጥ ያለውን የሸክላ ግንብ ነደለው። በቀዳዳው ውስጥ በመሸከክ ሕዝቅኤል ጓዙን ተሸክሞ ወጣ። በሚቀጥለው ቀን ፊቱን ሸፍኖ ሕዝቡ ሁሉ እያዩት ወደ ሌላ ስፍራ ሄደ። የሕዝቅኤል ድርጊት "ምልክት" ሲሆን፣ እግዚአብሔር ተጨማሪ ምርኮኞችን ወደ ባቢሎን እንደሚያመጣ ያመለክታል።

8-16 ምርኮኞቹ ሁሉ እነርሱ ራሳቸው በምርኮ ውስጥ የታቀፉ በመሆናቸው (በ605 ዓቅክ ወይም በ597 ዓቅክ)፣ የሕዝቅኤልን በምርኮ የመጋዝ ሥዕል በግልጽ መረዳት ነበረባቸው። ሕዝቡ፣ "ይህ የምታደርገው ምንድን ነው?" ብለው ስለ ጠየቁት ብዙዎቹ ተውኔቱ እንዳልገባቸው እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን አሳውቆት ነበር። ስለዚህ ሕዝቅኤል ማንም ሰው ትርጉሙን እንዳያጣ አድርጎ ትወናውን በሚገባ ገለጸ።

በ586 ዓቅክ ትሩፋኑ ከኢየሩሳሌም ተማርከው እንደሚጋዙ ሕዝቅኤል ትንቢት ተናግሮ ነበር፤ ይህም በተለይ በጊዜው የይሁዳ መሪ ከነበረው ከሴዴቅያስ ጋር በተለይ ተያይዞ ነው። አሁን ያሉት ነዋሪዎች በቅርብ ቀን ለሚያልፉበት ግዞት እርሱ ምልክት መሆኑን ሕዝቅኤል በኢየሩሳሌም ለምርኮኞቹ ነገራቸው። ከባቢሎን ወደ ተስፋዱቱ ምድር እንደሚመለሱ ትዕይንቱ እያሳየን ይሆናል የሚለውን ተስፋቸውን የሕዝቅኤል መልእክት ከንቱ ሳያደርግባቸው አልቀረም።

ሴዴቅያስ "መስፍን" ተብሎ የተጠራው ሕጋዊ ንጉሥ ባለመሆኑ ነበር። ያ መብት በባቢሎን በምርኮ የተወሰደው የዮአኪን ነበር። ሴዴቅያስ ዓዙን በምሽት ይጠቀልላል (2ነገ 25፥4፤ ኤር 39፥4፤ 52፥7)፤ ከኢየሩሳሌም በስተ ደቡብ ምሥራቅ ባለው በንጉሡ የአትክልት ስፍራ በር በችግር ያመልጣል፤ ወደ ዮርዳኖስ ይሸሻል፤ ይሁን እንጂ ታድኖ እንደሚያዝ እንስሳ በናቡከደነፆር ሰራዊት በዚያ በሸሸበት አገር እያለ ይያዛል። ድል አድርጊ ጠላቶቹን በመረብ የሚይዝበት ምሳሌ በመካከለኛው ምሥራቅ አዕዋፍን ወይም አራዊትን ከሚያድን ዐዳኝ ሁኔታ የተወሰደ ነው። የሴዴቅያስ ወታደሮች ይበታተናሉ፤ እርሱም በሪብላ በናቡከደነፆር ፊት ይቀርባል። የእርሱም ዐይኖች እንዲወጡ ከመደረጉና ዕውር ከመሆኑ በፊት ዐይኑ እያየ በዚያ ወንዶች ልጆቹና መሳፍንቱ ይታረዳሉ። ምርኮኛ ሆኖ እያለ በዚያው ቢሞትም ሴዴቅያስ የባቢሎንን ምድር ፈጽሞ አያይም (ከ2ነገ 25፥5:7፤ ከኤር 39፥6-7፤ 52፥8:10-11 ጋር ያነጻ)። ሕዝቅኤል በትዕይንቱ ፊቱን መሸፈኑ ሴዴቅያስ ከከተማዪቱ ሸሽቶ ለማምለጥ ሲል ራሱን ለመደበቅ

የሚፈልግበትን ሳያመለክት አልቀረም። “ምድሪቱንም እንዳያይ ፊቱን ይሸፍናል” የሚለው ሐረግ ሴዴቅያስ ዐይኑ ወጥቶ በምርኮ ከተጋዘበት ሁኔታ ጋር የሚገናኝ ነው።

ከዚህም በላይ እግዚአብሔር የምርኮውን ዐላማ ግልጽ ለማድረግ ፈልጎአል። እግዚአብሔር የሚመለሱት የእስራኤል ታማኝ፣ አፍቃሪና ኃያል አምላክ እንደ ሆነ ምርኮኞቹ ያዩ ዘንድ ግዞቶቹ ታቅደው ነበር። እግዚአብሔር ባዕዳን ሕዝቦች የይሁዳን መበተን በዐጉል መልክ እንዳይገነዘቡት ሲል፣ ምርኮኞቹን የራሳቸው ርኩሰት መጋዘን እንዳመጣቸው እንዲመለክሩ አደረገ። በዚህ መንገድ አሕዛብ እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ እንዲሁም ለሕዝቡ ጥንቃቄ የሚያደርግ አምላክ እንደ ሆነ ይረዳሉ። የተሸነፈ አገር የተሸነፈበት ምክንያት ጎይል የሌላቸውን አማልክት ስላገለገለ ይሆናል፤ አለበለዚያም ስለ ሕዝባቸው ግድ የሌላቸውን አማልክት ስለ ተከተለ ይሆናል የሚለውን የተሳሳተ የጥንት ቅርብ ምሥራቅ አመለካከት ይህ ሁኔታ ያስተካክላል። እንዲህ ዐይነቱን አስተሳሰብ ለማስቀረት ተማርከው የተሰደዱት በራሳቸው በደል ምክንያት እንጂ በእግዚአብሔር ስሕተት እንዳልሆነ የሚያስረዱ የአይሁድ ትሩፋንን እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ይልካል። ከዚያም ምናልባት አሕዛብም እውነተኛው አምላክ እግዚአብሔር ብቻ እንደ ሆነ ያውቁ ይሆናል።

ሐ. የፍርሀት ተውኔት (12፥17-20)

17-20 በሌላ ዐጭር ድርጊት ላይ ሕዝቅኤል በሚበላበትና በሚጠጣበት ጊዜ መደንገጥና መፍራት ነበረበት። ይህም ከተሞቻቸው ሁሉ በሚደመሰሱበትና ፍርስራሽ ሆነው በሚቀሩበት ጊዜ የኢየሩሳሌምና የይሁዳ ከተሞች ሁሉ የሚያጋጥማቸውን ፍርሀትና ሽብር ያሳያል። በላይዋ ላይ ከተፈጸመው ዐመፅ የተነሣ ምድሪቱ ትራቈታለች። በሌሎች ላይ የፈጸሙት ዐመፅ በራሳቸው ላይ ይደርሳል። ስለሆነም የይሁዳ ሰዎች እግዚአብሔር እውነተኛና ለተስፋ ቃሎቹም ታማኝ እንደ ሆነ ያውቃሉ። በበረከት ጊዜ ሊማሩአቸው ያልፈለጓቸውን ነገሮች፣ እግዚአብሔር በፍርድ ሽብር ውስጥ ያስተምራቸዋል። ነገር ግን ፍርዱ አሁንም የፍቅሩ መግለጫ ነው፤ ለእነርሱ ባይጠነቀቅላቸው ኖሮ ባልቀጣቸውም ነበርና።

2. የእግዚአብሔር ታማኝነት፦ የአሁኑ ፍርድ (12፥21-28)

21-25 ሕዝቅኤል የእርሱን መልእክት በተመለከተ ምርኮኞች ላቀረቡት ጥያቄ መልስ ሰጠ። የአይሁድ ምርኮኞች ግዴለሽነት የእርሱን ትእምርታውያን ድርጊቶችና ንግሮች ልብ እንዳይሉ ማስተዋላቸውን አዳክሞታል (12፥2)። የሕዝቅኤል ትንቢቶች ፋይዳ እንዳላቸው (እንደሚፈጸሙ) አላሰቡም። በጊዜው የነበረውን አባባል በመጠቀም ምርኮኞቹ ቀደም ብለው የነበሩት የፍርድ ትንቢቶች ሁሉ ማለትም በኢሳይያስ፣ በሚክያስና በሌሎቹ ነቢያት የተነገሩት ሲፈጸሙ ስላልታየ እውነተኛ ትንቢቶች አልነበሩም የሚል እምነት ነበራቸው። ታዲያ አሁን በምን ምክንያት የሕዝቅኤል ትንቢት እውነት ነው የሚል እምነት ሊኖራቸው ይችላል? አመለካከታቸው በእግዚአብሔር ምሕረት፣ ትዕግሥትና ሁሉን ቻይነት ላይ የተመሠረተ ነበር። ይህ የእግዚአብሔርን አለመለወጥና በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ እንደ ተገለጠው የቃሉን ታማኝነት አለማመንን ያሳያል። ከጸጋው ብዛት የተነሣ ብቻ ነበር እግዚአብሔር እስራኤልን ፈጥኖ በፍጥረት ያልቀጣት። እስራኤል ሐሳቧን ለውጣ ወደ እርሱ ትመለስ ዘንድ በትዕግሥት ተጠባብቆአል። በዚህ ፈንታ ፍርድ አይቀሬ ሆኖ እያለ ሕዝቡ ምንም አይደርስብንም በሚል ቅዠት ከመንገዱ እየራቁ ሄዱ።

ፍርድ የማይቀር ጉዳይ ስለ ሆነ እግዚአብሔር የምርኮኞቹ ምሳሌ ከእንግዲህ እንደማይሰማ ተናገረ። በእንጻሩ እግዚአብሔር፣ “ራእይ ሁሉ የሚፈጸምበት ጊዜ ቀርቦአል” የሚል ዐዲስ አባባልን ይፈጥራል። በሕጉና በነቢያት አማካይነት እግዚአብሔር የተናገራቸው ፍርዶች ሁሉ በቅርቡ ይፈጸማሉ። ሐሰተኛ ነቢያት ባለማቋረጥ ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ ሕዝቡን የሚያበረታቱባቸው ሐሰተኛ ራእዮችና አሳሳች ሟርቶች በኢየሩሳሌም ላይ ከሚመጣው ፍርድ የተነሣ በድንገት ይቋረጣሉ።

26-28 አንዳንዶች ፍርድ እንደሚመጣ ሕዝቅኤል የሰጠውን ማስጠንቀቂያ ቢያምኑም ራቅ ባለው በወደፊቱ እንጂ በእነርሱ ዘመን እንደማይፈጸም አመኑ። እግዚአብሔር ለይሁዳ ያለው መልስ ዐጭርና ግልጽ ነው፤ ይኸውም ፍርድ ከእንግዲህ አይዘገይም! እግዚአብሔር የተናገረውን ይፈጽማል፤ በፍጥነትም ያደርገዋል የሚለው ነው።

3. በነበሩት ሐሰተኛ ነቢያት ውግዘት (13፥1-23)

ሀ. በወንድ ነቢያት ላይ የወረደ ፍርድ (13፥1-16)

1-7 በ12፥21-28 ፍርድ በቅርቡ አይፈጸምም በሚል ምርኮኞች በሐሰተኛ ዋስትና ላይ ተመሥርተው የሚያስቡትን ሕዝቅኤል ተቃውሞአል። በዚህ ሐሳብ ላይ ከአያሌ ሐሰተኛ ነቢያት በመጣ ራእይና ሟርት መበረታቻን አግኝተዋል። አሁን ሕዝቅኤል በእነዚህ ነቢያት ላይ የእግዚአብሔርን ውግዘት ያስተላልፋል። ፍርድ (ወዮታ) በነቢያት ሞኝ መንገድ ላይ ሊወርድ ስለ ሆነ ነቢያቱ ልባቸውን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰሙ ይነግራቸው ዘንድ እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን አዘዘው።

የፍርዱ ትእዛዝ ከመውጣቱ በፊት፣ እግዚአብሔር (ቍ. 8-16) ይህ ፍርድ በእነርሱ ላይ እንዲመጣ ያደረጉትን ነቢያት ባሕርይ በግልጽ ዘርዝሮአል። ነቢያቱ በዐጭሩ “ሞኞች” ተብለው ተጠርተዋል። ይህ ቃል ሰፋ ያለ ትርጉም ሲኖረው ከብልኀ ሰው ባሕርይ ተቃራኒ የሆነውን ማንኛውንም መንፈሳዊና ግብረ ገባዊ ድንዛዜ የሚያቅፍ ነው። ሕዝቅኤል ለሞኝነታቸው ምክንያት አድርጎ በዝርዝር ያቀረበው በራሳቸው ልብ መተማመናቸውንና የእግዚአብሔርን መገለጥ ለማግኘት አለመሻታቸውን ነው።

ነቢያቱ የራሳቸውን ፍላጎት ተከተሉ፤ ለሕዝቡ መጨነቅን ችላ በማለት የልባቸውን ጠማማነት እንደ እግዚአብሔር መገለጥ ቈጠሩት። ፈጽሞ ምንም ዐይነት ነገር ስላላዩ ራእዮቻቸው ሐሰትንና ማጭበርበርን የተሞሉ ነበሩ። ከእግዚአብሔር መልእክትን ለማግኘት የጣዖት አምልኮ ልምምድ የሆነውን ሟርት ይጠቀሙ ነበር፤ ይኸውም የከዋክብትን እንቅስቃሴ መመልከትን፣ የእንስሳትን የውስጥ አካሎች መመርመርንና፣ ዕጣ መጣልን የመሳሰሉ ነገሮችን የሚመለከት ነው። ይህ የሆነውም በነቢያዊው የመለኮት ሥልጣን ቀመር ይኸውም “እግዚአብሔር እንዲህ ይላል” በሚለው የማጭበርበሪያ ሐሳብ በማታለል በመግቢያ ላይ እንዲያስቀምጡ በማድረግ ነው። ሆኖም እግዚአብሔር አልተናገረም ወይም እነርሱን አልላካቸውም። ይናገሩ የነበሩት ከቶ ያልመጣውን የማረጋገጫ ቃል ተስፋ በማድረግ ጠማማ ከሆነው ልባቸው ብቻ ነበር። እግዚአብሔር በእነርሱ ያልተናገረ መሆኑን በአጽንዖት ገልጾአል።

እነዚህ ነቢያት የተከተሉት የራሳቸውን መንፈስ እንጂ የእግዚአብሔርን መንፈስ አልነበረም። ሥጋዊ የሆነው የመንፈሳቸው ምኞት “በፍርስራሽ መካከል እንደሚኖሩ ቀበሮዎች” ያለ ባሕርይ እንዲኖራቸው አድርጓቸዋል። ቀበሮዎች ለራሳቸው ዋሻዎችን በመሻት በፍርስራሽ መካከል መራወጥን ይወዳሉ። ስለ ፍርስራሹ ይህን ያህል አይጨነቁም። በተመሳሳይ ሁኔታ እነዚህ ነቢያት ስለ ይሁዳ ሕዝብ ብዙ አይጨነቁም፤ ነገር ግን ለራሳቸው ምቹ የሚሆነውን ቦታ ይፈልጋሉ። ሕዝቡንና ምድሪቱን ያጠፋውን የራሳቸውን የሐሰት ትንቢት ጨዋታ ተጫወቱ። ስለዚህ ሕዝቡን ስለሚመጣው አስቸጋሪ ጊዜ ወይም ስለሚኖሩበት አስጨናቂ ጊዜ ሳያዘጋጁ ቀሩ። ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር እስካልተመለሱ ድረስ ይሁዳ ፍርድንና ምርኮን መጋፈጧ የማይቀር ነው።

ነቢያቱ ጣልቃ በመግባት የሙሴን ሕግ በመጣስ “የተሰነጠቀውን ቅጥር” መጠገን ነበረባቸው። የተሰነጠቀውን ለመጠገንና ሕዝቡን ከፍርድ ለመጠበቅ የኪዳኑን እውነት አስመልክቶ ሕዝቡን መምከር ነበረባቸው። ነገር ግን ኀላፊነታቸውን በቸልታ ሳይወጡ ቀሩ። የእግዚአብሔርን ሕዝብ ስብራት ለመጠገን (22፥30) የተገኘ አንድም ሰው አልነበረም። ከሁሉም በላይ “በእግዚአብሔር ቀን” ከሚመጣው ጦርነት ማደሪያው ራሱን በቅድስና መቋቋም እንዲችል አላዘጋጁትም፤ ይህ “የእግዚአብሔር ቀን” የተባለው ወደፊት በክርስቶስ ዳግም ምጽአት የሚመጣውን ፍርድ የሚያመለክት ሳይሆን፣ በቅርቡ በናቡከደነፆር ወረራና ከበባ በውስጥዋ ካለው ቤተ መቅደስ ጋር

በምትወድቀዋ ኢየሩሳሌም ላይ የሚመጣውን የፍርድ ቀን ነው። በቤተ መቅደሱ ውስጥ የከፋ ኀጢአት የሞላባቸው ርኩሰቶች እንዲገቡ ፈቃድ የተገኘው በከፊል እነዚህ ነቢያት የሙሴን ሕግ ትእዛዛትና ሥርዐቶች በማስተማር ለሕዝቡ እውነትንና ማስጠንቀቂያን ስላልተናገሩ ነው።

8-16 ፍርድ በአካባቢው እየታየ “ሰላም ነው” በማለት የሚጮኹ ሐሰተኛ ነቢያት በይሁዳ ሕዝብ ላይ “ጉበኛ” መሆን አይችሉም። እነዚህ ነቢያት ባዶ ቃል ተናግረዋል፤ ውሸትንም አይተዋል። የእግዚአብሔር ፍርድ ቀላልና ግልጽ ነው፤ ይኸውም “በእናንተ ላይ ተነሥቻለሁ” የሚል ነው። ሕዝቅኤል የፍርዱን ምክንያቶች በተደጋጋሚ ገልጾአል።

እነዚህ ሐሰተኛ ነቢያት ሕዝቡን ስላሳቱ ከሕዝቡ የተቈረጡ ይሆናሉ፤ በእስራኤል መግቦትም ውስጥ ዕድል ፈንታ አይኖራቸውም። ነቢያት እንደመሆናቸው መጠን በሕዝቡ መካከል ከፍተኛ ሥልጣንና የተሰሚነት ስፍራ ነበራቸው፤ ነገር ግን ከእንግዲህ በእግዚአብሔር ሕዝብ ጉባኤ ተካፋይ አይሆኑም (ከኤር 23፥22 ጋር ያነጻ)። በዚህም ምትክ ሰሞቻቸው ከእስራኤል ዜግነት መዝገብ ላይ ይሰረዛሉ። ከባቢሎን ምርኮ በኋላ መልሶ መቋቋም ሲሆን (539 ዓክክ) ወደ እስራኤል ምድር ተመልሰው አይገቡም። ይህ ፍርድ ነቢያት ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱና እርሱ ያለና እርሱ ብቻ እውነተኛ አምላክ እንደ ሆነ እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል። እንድምታው አሁንም ንስሓ ለመግባትና ለዘላለማዊ ድነት ወደ መሲሑ ለመምጣት ዕድሉ ያላቸው መሆኑ ነው።

በነቢያት ላይ የሚመጣው ፍርድ የተሰገጸው “ኖራ በመለሰን” በሚያደርጉት ትብብር ነው። እነዚህ ነቢያት የሰላምንና የብልጥግናን ጊዜ ይተነብዩ ስለ ነበር፣ ቤት መሥራትን ማደፋፈራቸው ከመሥመር መውጣት አልነበረም። ከዚህም የተነሣ የሰዎችን ግድግዳ ኖራ በመለሰንና በየቤቱ ያሉትን ትናንሽ ክፍሎች በማስጌጥና በመርዳት ይዘዋወሩ ነበር። ይህ “ዐርፈህ ተቀመጥ” የሚለው ፍልስፍና ማረጋገጫ ነው። ይሁን እንጂ እነዚህ ቅጥሮችና በኖራ የተለሰነው ጌጣቸው ከእርሱ ቍጣ ዝናብና በረዶ እንዲሁም ከኀይለኛው የመዓቱ ነፋስ በታች እንደሚወድቅ እግዚአብሔር ተናግሮአል። ቅጥሮቹ ሲፈራርሱ፣ ነቢያቱም በፍርስራሹ ውስጥ ያልቃሉ። ከዚያም ማንም ሰው ቤትን በኖራ ልስን ስለ ማስጌጥ አያስብም። እግዚአብሔር፣ “ቅጥሩና ቅጥሩን የለሰኑት የሉም” የሚል ዐዲስ ምሳሌ ያበጃል።

ለ. በሴት ነቢያት ላይ የወረደ ፍርድ (13፥17-23)

17-19 እግዚአብሔር እንደ ገና ሕዝቅኤልን ልክ እንደ ሐሰተኛ ነቢያት ከልባቸው አውጥተው ትንቢት በሚናገሩት ሴት ነቢያት ላይ እንዲናገር አዘዘው። እነዚህ ሴቶች በሟርትና በጥንቈላ ሥራ ውስጥ ነበሩ። የጥንቈላ አሠራራቸው በጥንታዊቷ ቅርብ ምሥራቅ በተለይም በባቢሎንና በግብፅ የተለመደ ነበር። ይሁን እንጂ በሙሴ ሕግ መሠረት ጥንቈላ የተከለከለ ነበር (ዘሌ 19፥26)። የእነዚህ የሴት ነቢያት ልምምድ የሕዝቡን ነፍስ ለማሰርና ለማጥመድ በሚጠነቀሉበት ጊዜ ለእጃቸው አንዳ ሁሉ አሸንክታብ በማሰፋትና የራስ መሸፈኛ በማበጀት ጥንቈላውን ማካሄድ ነበር። እነዚህ ሴቶች ጻድቁን እንዲሞት፣ ኀጢአተኛውን በሕይወት እንዲኖር አድርገዋል።

ገብስና ቍራሽ እንጀራ የጥንቈላ መሣሪያዎች ነበሩ። በሒታውያን ልምምድና በኋለኛው የሶርያውያን የሃይማኖት ሥርዐት ጥንቈላ በሚካሄድበት ጊዜ የገብስ እንጀራ የጣዖት አምልኮው የመሥዋዕት አቀራረብ ሃይማኖታዊ ሥርዐት ክፍል ወይም የሚጠነቈልበት ሰው የሚሞትም ሆነ የሚድን መሆኑን ለመለየት የሚጠቀመበት ዕቃ እንደ ሆነ ይታወቃል። ስለዚህ እነዚህ ሴት ነቢያት የማይሆን ነገር በማድረግ እግዚአብሔርን አርክሰዋል። የእግዚአብሔር ሴት ነቢያት በመምሰል ቢቀርቡም እነዚህን የጥንቈላ ልምምዶች በማድረግ የእግዚአብሔርን ስም አረከሱ።

እነዚህ ሴቶች የነበራቸው በጥንቈላቸው ሰውን የመግደል ኀይል ብቻ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርንም ሕዝብ ያታልሉ ነበር። የይሁዳ ሰዎች እነዚህን ውሸቶች በመስማታቸው ብዙዎች የማያስፈልግ ሞት ሞቱ። ከፍተኛው የሕይወትና የሞት ሥልጣን በእነዚህ ሴት ነቢያት እጅ ወደቀ ለማለት ሳይሆን፣ የመጨረሻው ሥልጣን የሚያርፈው በኃያሉ እግዚአብሔር እጅ ላይ ብቻ ነው።

20-23 እግዚአብሔር የእነዚህን ሴት ነቢያት አሸንክታብ ከክንዶቻቸው ላይ ቀድዶ እንደሚያነሣና የፊታቸውንም መሸፈኛ እንደሚቀዳድድ፣ ሕዝቡንም የሚያስሩበትንና የሚያጠምዱበትን ወጥመድ እንደሚበጣጥስ እንዲሁም የይሁዳን ጻድቃን ከወጥመዳቸው እንደሚያስመልጥ ሕዝቅኤል ተናገረ። እንደ ገናም እግዚአብሔር የዚህን ቅጣት ምክንያት አረጋግጦአል። እነዚህ ሴት ጠንቋዮች ወደ ጥንቈላ ወጥመዳቸውና ተጽዕኖአቸው ለመሳብ እንዲያስችላቸው የጻድቃንን ልብ በማሳዘን ማጭበርበርና ዐመፅ የሞላትን መንገድ ተጠቅመዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ ክፉዎች የእግዚአብሔርን መንገድ እንዳይከተሉ አበረታተዋል። ስለዚህ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከረከሰ እጆቻቸው በማስመለጥ የሐሰት ራእያቸውንና የጥንቈላ ሟርታቸውን እንዲቆም ያደርጋል። እርሱ ይህን ሲያደርግ እነዚህ ሴት ነቢያት እግዚአብሔር ምንጊዜም በስፍራው ላይ ያለ ታማኝና የማይለወጥ ጌታ እንደ ሆነ ያውቃሉ።

4. በመሪዎች ላይ የሐሰተኛ ነቢያት ተጽዕኖ (14፥1-11)

1-2 ከምርኮው አንዳንድ የይሁዳ ሽማግሌዎች ወደ ሕዝቅኤል መጥተው በፊቱ ተቀመጡ። እነዚህ “ኀላፊነት የተሰማቸው” ሽማግሌዎች ነቢያትን ያወገዘበትን ምክንያት ግልጽ አድርጎ እንዲነግራቸውና ለእነርሱም የእግዚአብሔር መንገድ ምን እንደ ሆነ እንዲያሳውቃቸው ወደ እርሱ መጡ። ሕይወታቸውና አስተሳሰባቸው የሚያሳየው እነዚያን ሐሰተኛ ወንድና ሴት ነቢያትን እንደ ተከተሉ ነው።

3 እነዚህ መሪዎች በአፍአዊ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመጠየቅ እውነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋይ ወደ ሆነው ወደ ሕዝቅኤል መጡ። ይሁን እንጂ በሌላ በኩል የሕይወታቸው እውነተኛ አማልክት በማድረግ በልባቸው ዙፋን ላይ ውስጥ ውስጡን ጣዖታትን ያከብሩ ነበር። አቀራረባቸው ተለዋዋጭ ለሁለት ጌቶች የተገዛ ዐይነት ነው። ለጣዖት አምልኮ ያላቸው ጥልቅ ምኞት ሽማግሌዎቻቸው በኀጢአት ጉድጓድ ውስጥ እንዲወድቁ አድርጎአል። በእግዚአብሔር ላይ የሚገልጡት ውጫዊ ዐመፅ፣ የጣዖት አምልኮ ሃይማኖታዊ ሥርዐታቸውና የሙሴን ሕግ ለማክበር አለመፈለጋቸው፣ እነዚህን ሐሰተኛ አማልክት ውስጥ ውስጡን እንደሚያመልኩ አሳይቶአል። ስለዚህ በልባቸው ውስጥ የጣዖት ምስልን ላቆሙት እውነተኛ አቅጣጫ ሊሰጥ አይችልም።

4-11 እግዚአብሔር መልሱን ሰፋ በማድረግ ይህን ጣምራ መገዛት የሚፈጽምን ማንኛውንም እስራኤላዊ እንዲጨምር አድርጓል፤ “ማንኛውም እስራኤላዊ” እና “የእስራኤል . . .” ቤት የሚሉት ሐረጎች ይህን ግብዝነት አጋልጠዋል። ሽማግሌዎቹ አመራራቸውን የተከተለውን ሕዝብ ሁሉ ወክለዋል።

የእግዚአብሔር መልስ በሦስት ገጽታ የተከፈለ ነበር፦ ሁለቱ እጅ ሽማግሌዎቹንና ሕዝቡን በስፋት የሚይዝ ሲሆን፣ አንዱ እጅ ሐሰተኛ ነቢያትን በተመለከተ የቀረበ ነው። እግዚአብሔር በመጀመሪያ የተናገረው ሽማግሌዎቹን በልባቸው ላሉት አያሌ ጣዖታት አሳልፎ እንደሚሰጣቸው ነው። እስራኤል ስለ ኀጢአቷ ንስሓ ትገባ ዘንድ ለጣዖት አምልኮ ተጨማሪ ርካታ አሳልፎ መስጠት እንደ ሆነ እግዚአብሔር ያውቃል። ሕዝቡ የጣዖት አምልኮ ባዶነትና ምንዝርና እንዲያቅለሸልሻቸው ይደረጋሉ። ለእነዚህ የጣዖት አምልኮ ዘማዊ ልምምዶች ባላቸው ፍላጎት የተነሣ ከእርሱ የራቁትን ለመመለስ እግዚአብሔር ፈለገ። የእርሱን የንስሓ ጥሪ ሰምተው እንዲመለሱ ስለ ኀጢአታቸው ሊወቅሣቸው ፈለገ።

የእግዚአብሔር ዐላማ ኀጢአተኞችን ስለ ኀጢአታቸው መውቀሥ ብቻ ሳይሆን፣ ወደ መሲሑም እንዲመጡለት ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር እነዚህን ሁለት ልብ ያላቸውን መሪዎችና ተከታዮቻቸውን ከጣዖቶቻቸውና ለእርሱም አስጸያፊ ከሆኑ ነገሮቻቸው ተመልሰው ንስሓ እንዲገቡ በፍቅር መከራቸው። ለጣዖት በልብ ከመገዛት ይልቅ ለእግዚአብሔር በልብ መገዛት እጅግ አስፈላጊ ነው።

የእግዚአብሔር ሁለተኛው መልስ አቅጣጫ የእርሱን የንስሓ ጥሪ ለመቀበል ፈቃደኞች ወዳልሆኑት ነው። ለዚህ መልስ ባይሰጡ፣ እግዚአብሔር ራሱ ለዚህ ባዶ ጥያቄአቸው በቃል ሳይሆን በተግባር መልስ ይሰጣቸዋል። የሙሴን ሕግ "የእርግማን" ደንቦች በመፈጸምም፣ እግዚአብሔር ፊቱን በእነዚህ ሕዝብ ላይ ያዞራል፤ ከእስራኤላዊነት ዜግነትም ይሰርዛቸዋል (ከ13፥9፤ ከዘሌ 20፥3፡ 5-6 ጋር ያነጻ)፤ የቃል ኪዳን ፍርዱን በመፈጸም ረገድ ያለውን ታማኝነቱን በማሳየትም ለሕዝቦች ሁሉ "ማላገጫና መዘባበቻ" ያደርጋቸዋል (ዘዳ 28፥37)። ከዚያም እርሱ እውነተኛ፣ ምንጊዜም ያለና የሚኖር የእስራኤል አምላክ መሆኑን ያውቃሉ።

ከዚያም እግዚአብሔር በመጨረሻ በሐሰተኛ ራእያቸውና በጥንቁላ ሟርታቸው ሽማግሌዎቹንና ሕዝቡን ወዳሳቱት ሐሰተኛ ነቢያት ዘወር አለ። እነዚህ ሐሰተኛ ነቢያት በምንም መንገድ ይሁን እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል ከሰጠው ውጭ ሌላ ትንቢት ሊናገሩ የቻሉት እግዚአብሔር ስለ ፈቀደላቸው ነው። እግዚአብሔር የሐሰት ነቢያትን ሳይቀር በመጨረሻ ሁሉንም ነገር ይቈጣጠራል። ለተለዋዋጭ ጠያቂዎች እግዚአብሔር የእጃቸውን የሚሰጠውን ቅጣት፣ እነዚህ ነቢያትም ተመሳሳይ ቅጣት ይቀባላሉ፤ የእያንዳንዳቸው ኀጢአት ተመሳሳይ የሆነው ያው የጣዖት አምልኮ ነውና ጣዖት የሚያመልኩትን ወደ ራሱ ይመልሳቸው ዘንድ እግዚአብሔር በአዝልቆት ቀጥቶአቸዋል። ልክ እንደዚሁ በእነዚህ ነቢያት ላይ የወረደው ይህ ፍርድ የተሰጠበት ምክንያት፣ እስራኤላውያን ከአምላካቸው ርቀው ከእንግዲህ እንዳይባዝኑና ራሳቸውንም እንዳያረክሱ፣ ነገር ግን ሕዝቡ እንዲሆኑለት ምንግዜም ወደሚፈልገው ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱና ከእርሱ ጋር ግንኙነት እንዲያደርጉ ነው። ይህ ግንኙነት የተገለጠው፤ "እነርሱ ሕዝቤ ይሆናሉ፤ እኔም አምላካቸው እሆናለሁ" (ከዘፀ 19፥5-6፤ ከዘሌ 26፥12፤ ከኤር 7፥23 ወዘተ ጋር ያነጻ) ከሚለው የኪዳኑ ዋና ቃል ነው። እግዚአብሔር ሐሰተኛ ነቢያትንና መሪዎችን ያስወግዳል፤ ይኸውም በሙሴ ኪዳን በተገለጠው መሠረት ሕዝቡ በእውነት መንገዱን የሚከተሉ እንዲሆኑ ነው።

5. በግል ከመጸደቅ ውጭ ትድግና የለም (14፥12-23)

12-14 ሽማግሌዎቹ የሕዝቅኤልን የንስሓ ጥሪ እየሰሙ ሳሉ (ቍ. 1-11)፣ አንዳንዶቹ በኢየሩሳሌም ላይ የሚመጣው ፍርድ አንድ የታወቀ ጻድቅ ሰው ወይም ሰዎች በከተማዪቱ ቢኖሩ አቅጣጫውን ይቀይር ይሆን የሚል አስተሳሰብ ነበራቸው (ከዘፍ 18 ጋር ያነጻ)። ሕዝቅኤል የመለሰላቸው፣ በእነርሱ ዘመን የነበረው በባቢሎን ከተማ ናቡከደነፆርን እያገለገለ ያለው ዳንኤል እንኳ ኖኅንና ኢዮብን ከመሰሉ ሰዎች ጋር ቢተባበር አገሪቱን ሊያድናት እንደማይችል ነው። እግዚአብሔር ሽማግሌዎቹን ያሳሰባቸው ለእርሱ ታማኝ ያልሆነና ፊቱን ወደ ሌሎች አማልክት ዘወር ያደረገ ማንኛውም አገር እንደሚቀጣ ነው፤ እግዚአብሔር በኪዳኑ ላሉት ርግማኖችና በረከቶች ታማኝ በመሆን ጸንቶ ይኖራልና (ዘሌ 26፥22-26)። እያንዳንዱ ግለሰብና እያንዳንዱ አገር በእግዚአብሔር ፊት በየራሱ በጎላፊነት ይጠየቃልና።

15-20 ሕዝቅኤል ሐሳቡን በተለመዱት በአራቱ የፍርድ መሣሪያዎች ይገልጻል፤ እነርሱም የዱር አራዊት፣ ሰይፍ፣ ቸነፈርና ራብ ናቸው። ከእነዚህ ፍርዶች አንዱ በምድሪቱ ላይ ቢመጣ፣ የኖኅ፣ የዳንኤል ወይም የኢዮብ የግል ጽድቅ ሌላውን ሰው ከፍርድ መታደጉ ቀርቶ ከቤተ ሰባቸው አንዱን እንኳ ማዳን አይችልም። እነዚህ ሦስት ጻድቅ ሰዎች እያንዳንዳቸው በግላቸው ካጋጠማቸው አደጋ ድነዋል፤ ነገር ግን እያንዳንዳቸው በየዘመናቸው በዚህ ረገድ የሚያደርጉት ለውጥ አልነበረም።

21-23 የይሁዳ የጊዜው ሁኔታ ከሌላው የተለየ አልነበረም። እግዚአብሔር አራቱን አስከፊ ፍርዶቹን በኢየሩሳሌም ላይ ይሰድዳል። በምርኮኞቹ ፊት የእርሱን ፍትሕ ለማረጋገጥ፣ እግዚአብሔር ንስሓ ያልገቡ ጥቂት ዕብራውያንን በማስቀረት ወደ ባቢሎን በምርኮ ይሰድዳቸዋል። ይህ በርግጥ የእግዚአብሔር ጸጋ መግለጫ ነው። እነዚህ ጻድቃን ያልሆኑ ሰዎች ለምርኮ ወደ ባቢሎን ሲሄዱ፣ በዚያ ያሉት ምርኮኞች ያደረጉትን ያስታውሳሉ፤ የይሁዳ ሰዎችም የቱን ያህል ክፉ እንደ ነበሩ ያስተውላሉ። በዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም ላይ ባመጣው ፍርድ ፍጹም ጻድቅ እንደ ሆነ በመረዳት ይጽናናሉ። ምርኮኞቹ የምድር ሁሉ ፈራጅ የሆነው ያደረገው ትክክል እንደ ሆነ ሲያዩ (ዘፍ 18፥25)፣ በኢየሩሳሌም ላይ በደረሰው ሐዘናቸው ይጽናናሉ።

6. ኢየሩሳሌም የማትረባዋ የወይን ግንድ (15፥1-8)

1-5 ይህ ምሳሌ ምርኮኞቹ ስለ እግዚአብሔር ታማኝነት የጠየቁትን ጥያቄ የሚመለከት ነው። እነርሱ የእርሱ ምርጥ ሕዝብ፣ የተመረጡ የወይን ግንድ እንደ ሆኑ ነው እንጂ የሚያምኑት የእግዚአብሔር ፍርድ ሕዝቅኤል እንደ ተናገረው ይሁዳን ያጠፋል ብለው አያስቡም ነበር። ስለሆነም ምሳሌው የሚያሳየው የወይን ግንድ ፍሬ ከማፍራት ውጭ ከንቱና የማይረባ እንደ ሆነ ነው። ግንዱ እጅግ ለስላሳ፣ ደካማና ለሕንጻ መሥሪያ የማይሆን ነው። በግድግዳ ላይ ዕቃ ወይም ልብስ የሚንጠለጠልበት ኩላብ እንኳ ከእርሱ መሥራት አይቻልም። የወይን ግንድ በተፈጥሮው ይህን ያህል የማይጠቅም ከሆነ፣ እሳት ካቃጠለውና ከለበለበው በኋላማ ይጠቅማል ተብሎ አይታሰብም።

6-8 በምሳሌው የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች በወይን ግንድ ተመስለዋል። የወይን ግንዱ ፍሬ በማፍራት ብቻ ጠቃሚ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ይሁዳና ኢየሩሳሌምም ፍሬ ማፍራት አለባቸው። ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ ከመታመናቸው በቀር (ከዳዊት ዘመን ጋር ያነጻ) አገሪቱ በወታደራዊ ኀይልም ሆነ በብልጽግና ረገድ እንደ ሌሎቹ አገሮች (ዛፎች) አልነበረችም። በታሪክ ዘመን ሁሉ በዚህ ረገድ ፍሬያማ ሆና ባታውቅም እግዚአብሔር እስራኤልን የመረጠው ለሌሎች አገሮች በረከት እንድትሆን ነው (ዘፍ 12፥1-3)። እስራኤል እንዳልተገረዘው የወይን ግንድ ፍሬያማ አልነበረችም፤ አሁን በባቢሎን ወረራና ምርኮ የእግዚአብሔር ፍርድ እሳት ካለፈባት በኋላ ጠቃሚነቷ ጨርሶ ጠፍቷል። ፍሬ አፍሪ በመሆን ረገድ (ለአሕዛብ በረከት በመሆን) የማትረባ የወይን ግንድ ሆናለች። ልትጠቅም የምትችለው ለማገዶነት ብቻ ነው። እግዚአብሔር እሳት ወደ ሆነው ቅጣቱ ይመልሳታል። የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች በእሳት ይበላሉ፤ ምድሪቱም ባድማ ሆና ትቀራለች።

የዚህ አሰፈሪ ፍርድ ምክንያት እንደ ገና በግልጽ ቀርቦአል፤ ይኸውም ይሁዳ ለእግዚአብሔርና ለሕጉ ታማኝ ያልነበረች መሆኗ ነው። ለዓለም ሕዝብ በረከት ለመሆን አልቻሉም። የእግዚአብሔርን ሕግ ባለመታዘዝ ኀጢአትን ሠሩ። ከጣዖት አምልኮአቸው የተነሣ የማይረቡና የማይጠቅሙ ነበሩ። በእግዚአብሔር ምሕረት አሁንም ምርኮኞቹ ለእግዚአብሔር ጠቃሚና ፍሬያማ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ይህም ሊሆን የሚችለው ለእርሱ ታማኞች ከሆኑ ብቻ ነው። ወደ ራሱ ለመመለስ እግዚአብሔር ይህን መፈራረስ በኢየሩሳሌም በሚኖሩት ላይ አመጣ። በዚህ ፍርድ አማካይነት ምርኮኞቹ እግዚአብሔር ምንጊዜም ሕያው አምላካቸው መሆኑን ያውቃሉ። ስለዚህ ምርታማ ካለመሆን ይልቅ ፍሬያማ ይሆኑለት ዘንድ እግዚአብሔር የመረጣቸውን ሕዝቡን ቀጣቸው (ከዮሐ 15፥1-16 ጋር ያነጻ)።

7. የኢየሩሳሌም ታሪክ የዘማዊት ሴት ታሪክ ዐይነት መሆኑ (16፥1-63)

ሀ. የኢየሩሳሌም መወለድ (16፥1-5)

1-2 ምርኮኞቹ ስለ ወይን ግንዱ በተነገረው ምሳሌ አልተረቱም (ምዕ 15)። በርግጥ የእስራኤል የወይን ግንድ ባለፈው ዘመን ጥቂት ስሕተቶችን አድርጋ እንደ ነበር አምነዋል፤ ይሁን እንጂ ሕዝቅኤል እንደ ተናገረው ዐይነት ፍርድ የሚገባት አይደለችም ብለው ያስቡ ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን፣ "ለኢየሩሳሌም አስጸያፊ ተግባርን ፊት ለፊት ንገራት" አለው። ሕዝቅኤል የእስራኤል ዋና ከተማና የአገሪቱ ምልክት የሆነችውን የኢየሩሳሌምን ታሪክ ወደ ኋላ መለስ ብሎ በመተረክ እስራኤል የቱን ያህል የተበላሸ ታሪክ እንደ ነበራት ያሳያል። ልክ እንደዚሁ የዚህ ምሳሌ መሰጠት ዐላማ በኢየሩሳሌም ላይ ለመጣው ፍርድ ምክንያት የሆነውን አስከፊና አስጸያፊ ነገር ለምርኮኞቹ መሪዎች ለማሳየት ነው። የኢየሩሳሌም ርኩሰት አገሪቱን ሁሉ መሸፈኑና የሚደርስባትም ፍርድ ይሁዳን ሁሉ እንደሚያካትት ግልጽ ነው።

3 ኢየሩሳሌም በከነዓን ምድር ከአሞራውያንና ከኬጢያውያን የተፀነሰች ነበረች። ከተማዪቱም የተቈረቈረችው በዕብራውያን ሳይሆን፣ አረማውያን በሆኑ የከነዓን ሰዎች ነበር። የኢየሩሳሌም አባት አሞራዊ፣ እናትዋም ኬጢያዊት መሆኗ መገለጡ ከተማዪቱ እንዴት እንደ ተመሠረተች ለማሳየት ነው። በኢያሱ መሪነት እስራኤላውያን ወደ ምድሪቱ በገቡ ጊዜ፣ ኢየሩሳሌም የኢያቡሳውያን ከተማ ነበረች (ኢያ 15፥8፡63)፤ በገባዖን ደግሞ በዕብራውያን ላይ ተባብረው ከተነሡት የአሞራውያን ወገን መካከልም ነበረች (ኢያ 5፥1)።

4-5 ኢየሩሳሌም በተወለደበት ቀን እንደ ተተወ ሕጻን ተይዛ ነበረች። በቅርብ ምሥራቅ አገሮች ዐዲስ የተወለደን ሕጻን ማጠብ፣ ጕዳት ከሚያደርሱ ሕዋሳት ለመጠበቅ ሕፃኑን በጨው ማሸትና በጨርቅ መጠቅለል እንዲሁም እትብቱ ከተቈረጠ በኋላ እነዚህን በአርባኛው ቀን ሁለት ጊዜ መለወጥ የታወቀ ልምድ ነበር። በምስያ ረገድ ሲታይም ገና ከጅምሩ እንዲህ ዐይነቱ የተለመደ እንክብካቤ ለኢየሩሳሌም አልተደረገም ነበር። የከነዓን ሰዎች እንክብካቤ ስላልተደረገለት ወይም፤ ዕብራውያን የኢያቢስን ከተማ ማሸነፍ ስላልቻሉ (ኢያ 15፥63) በመውደቅ ላይ የነበረች ከተማ ነበረች። በርግጥ ይህችን ከተማ በመሰፍንት ዘመን ሁሉ እንዳልተፈለገ ልጅ ሜዳ ላይ ጥለዋት ነበር፤ ይህ በጥንት ቅርብ ምሥራቅ ያልተፈለገ ልጅ የሚወገድበት በስፋት የተለመደ አካሄድ ነበር።

ለ. እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ማፍቀሩና በኋላም የጋብቻ ቃል ኪዳን ማድረጉ (16፥6-14)

6 እግዚአብሔር የኢየሩሳሌምን ወራዳ ሁኔታ በመመልከት፣ ከኢያቡሳውያንና ካለባት ችግር ሁሉ ነጻ ለማውጣት በእስራኤል ላይ ዐዲስ የተቀባውን ንጉሥ ዳዊትን ላከላት (2ሳሙ 5፥6-10)። እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ሲመሠርት የወደፊት ዕጣ ፈንታዋን ወስኖ ነበር፤ እንደምትኖርም አጽንዖት አደረገ።

7 ነጻ ከወጣች በኋላ ኢየሩሳሌም ወዳጅዋ ከሆነው ከእግዚአብሔር በረከቶችንና ጥቅሞችን ተቀበለች። በመስክ ላይ እንደሚገኝ ተክልም ሕዝቧን ለመጨመር ተስፋ ሰጠ። ከእርሱ ቸር እንክብካቤ የተነሣ ኢየሩሳሌም እንደ ከተማ ወደ ሙሉ ብስለት አደገች። ለጋብቻ ዕድሜ ብትደርስም "ዕርቃን"ዋን ነበረች።

8-14 እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ተመለከተ፤ መጕናጸፊያውንም በላይዋ ላይ በመዘርጋት የጋብቻ ቃል ኪዳን ገባላት (ከሩት 3፥9 *ጋር ያነጻ*)። ከኢየሩሳሌም *ጋር* የጋብቻ ቃል ኪዳን አደረገ (ከመዝ 132፥13-17 *ጋር ያነጻ*)። ዳዊት የቃል ኪዳኑን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም ባመጣ ጊዜና የኢያቡሳዊውን የኦርናን ዐውድማ ለቤተ መቅደሱ ሕንጻ ሥራ ዝግጅት በገዛ ጊዜ (2ሳሙ 6፤ 24)፣ እርሱ የሚኖርባት የእግዚአብሔር ከተማ ሆነች። ሙሽራ ለሙሽራዪቱ እንደሚያደርገው እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም የጋብቻ ስጦታዎችን ሰጣት፤ እነዚህም ስጦታዎች ጌጣጌጦች፣ መታጠቢያዎች፣ ቅባቶች፣ ውድ ልብሶች፣ ዕንቊች፣ አክሊልና ምርጥ ምግቦች ነበሩ። ከሚገባ በላይ ውብ እንድትሆን ተደረገች፤ እንዲሁም በዳዊትና በሰሎሞን ዘመናተ መንግሥታት ወደ ንጉሥ መንበርነት አደገች። በጥንታዊ ቅርብ ምሥራቅ በዚያ ዘመን ዝናዋና ውበትዋ የገነነ ዋና ከተማ ሆነች (1ነገ 10፤ ሰቈ 2፥15)።

ሐ. ከሌሎች ምድሮችና አማልክት ጋር የተፈጸመ የኢየሩሳሌም ምንዝርና (16፥15-34)

15 እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን በውበትና በዝና እንደ ሙሽራው አክሊል ደፍቶላት ብዙ ሳይቈይ፣ ይህን ሁሉ በሰጣት በእርሱ ከመመካት ይልቅ በውበትዋ መመካት ጀመረች። ከማንኛውም አገር *ጋር* መንፈሳዊ ምንዝርናን ፈጸመች። ሰሎሞን ከብዙ አገሮች *ጋር* የሰምምነት ውል በማድረግ፣ ከእግዚአብሔር የእምነት መንገድ በተቃራኒ እስራኤልን መራ (ከዘዳ 17፥1-20፤ ከ1ነገ 11፥1-13 *ጋር ያነጻ*)። ዓለም ዐቀፋዊ ስምምነቶችን በጋብቻ ማኅተም ማተም የተለመደ ነበር። የሰሎሞን አያሌ ባዕዳን ሚስቶች እርሱ በእግዚአብሔር ከመታመን ይልቅ በእነዚህ ስምምነቶች ላይ የሚታመን ለመሆኑ ማረጋገጫ ሆኑ (አረጋገጡ)። ይህም የሚስቶቹን ባዕዳን አማልክት እንዲያመልክ አደረገው። በውጫዊና በቀኖሳዊ ነገሮች ላይ አጽንዖት ማድረግ መጣ። እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ሰጥቶአት የነበረው የተለየ ስጦታ የውድቀቷ ምክንያት ሆነ፤ ከሰጪው ይልቅ ስጦታውን እጅግ ወድዳ ነበርና።

16-22 በሰሎሞን አገዛዝ ሥር ከነበረው ዐመፅ፣ ኢየሩሳሌም በእስራኤል ዋና ከተማነቷ ሕዝቡን ወደ ብልሹ መንገድ ቀስ በቀስ መራች። የእግዚአብሔር ስጦታዎች በተፈጥሮአቸው ክፉት ባይኖርባቸውም፣ ኢየሩሳሌም ከእግዚአብሔር ይልቅ ስጦታዎችን አገባች። ለጣዖት አምልኮ ኰረብታ ላይ የተሠሩ መስገጃዎችን አበጀች፤ በልብሶችዋ በማስጌጥም በእግዚአብሔር ላይ አመነዘረችባቸው (2ነገ 23፥7)። የወንድ ጣዖት ምስሎችን ከአበሩ ዕንቆች በማበጀት ውብ የሆኑ ልብሶቿን አለበሰቻቸው። እነርሱን በዕጣን፣ በፈሳሽ ቁርባኖችና በሌሎች ቁርባኖች በማምለክም አመነዘረችባቸው።

ከሁሉም የከፋው ነገር ኢየሩሳሌም ለእነዚህ ጣዖታት ልጆችዋን *መሥዋዕት* አድርጋ ማቅረብዋ ነው (ከ2ነገ 16፥3፤ 21፥6፤ 23፥10፤ ከኤር 32፥35 *ጋር ያነጻ*)። በአረማውያን ሕዝቦች መካከል በሚደረገው ማንኛውም አስጸያፊ ሃይማኖታዊ ድርጊት ውስጥ ገባች። ምንም ነገር ባልነበራትና ምንም ነገር በማይገባት በወጣትነትዋ ዘመን እግዚአብሔር ያደረገላትን ረሳች። ወደ ንግሥናና ወደ ውበት ከፍ ከፍ በማድረግ እጅግ ከተናቀ ሁኔታ ያወጣትን አምላክዋን ዘነጋች።

23-25 ኢየሩሳሌም በራስዋ ወደ እነዚህ አስጸያፊ የጣዖት አምልኮ ልምምዶች ውስጥ መግባትዋ በቂ ነበር፤ ነገር ግን እነዚህን አረማውያን ልምምዶች ሌሎች እንዲያደርጉአቸው ተግታ የምታደፋፍር ሆና ተገኘች። ኢየሩሳሌም በየመንገዱ በሚገኙ ኰርብታዎችና ጉብታዎች ላይ ሁሉ አስጸያፊ አምልኮ የሚካሄድባቸውን የጣዖት መስገጃዎች ሠራች። ማንኛውም የሐሰት ሃይማኖት ሥርዐት ወደ እርስዋ እንዲመጣና የቅይጥ መንፈሳዊ ምንዝርናዋ የጠበቀ አካል እንዲሆን በማድረግ እንደ አመንዝራ ራሷን አዋርዳ አቀረበች። እንዲህ ዐይነቱን ነገር በማድረግ እግዚአብሔር የሰጣትን ውበት አረከሰች። ስለዚህ ኢየሩሳሌም በዘማዊነታ ልቡን ስለ ሰበረችው እግዚአብሔር ወዮታን በእርስዋ ላይ ማወጅ ጀመረ።

26-29 ኢየሩሳሌም ከግብፅም *ጋር* ማመንዘር ጀመረች። የእስራኤል መንግሥት አንድ መንግሥት በነበረበት ጊዜ ግብፅ ከእስራኤል *ጋር* ለማመንዘር ትፈልግ ነበር። እንደ ሆሴዕና እንደ ኢሳይያስ ያሉ ነቢያት እንዲህ ዐይነቱን መንፈሳዊና ፖለቲካዊ ምንዝርና ቢያወግዙም ቀዳማዊ አዮርብዓምና ሌሎቹ ከግብፅ *ጋር* አመነዘሩ (2ነገ 17፥4፤ 18፥21፤ ኢሳ 30፥7፤ 36፥2)። ኢየሩሳሌም ከአምላኳ ይልቅ ስለ ደኅንነትዋ ከባዕዳን መንግሥታት *ጋር* ባለው የፖለቲካ ስምምነት ላይ ታመነች። ስለዚህ እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ለፍልስጥኤማውያን አሳልፎ ሰጣት፣ ስትቁጣጠረው ከነበረው ግዛትም የተወሰነውን እንድታጣ አደረጋት (ከ2ዜና 21፥16-17፤ 28፥18፤ ከኢሳ 1፥7-8 *ጋር ያነጻ*)። እንዲህ ዐይነቱ ሁኔታ ኢየሩሳሌም ስላለፈው ኀጢአተኛ መንገድዋ ዘወር ብላ እንድትመለከት ምክንያት ሊሆናት ሲገባ፣ እርስዋ ግን ከአሶርና ከባቢሎን *ጋር* ፖለቲካዊ "ግንኙነት" በማድረግ ሽርሙጥናዋን በይፋ ቀጠለች።

30-34 እግዚአብሔር በእርሱ ቦታ ጠበቃዎችን አቁሞ፣ ደካማነታቸውን በማውገዝ ወደ ኢየሩሳሌም ጮኸ። ከእግዚአብሔር *ጋር* በነበራት ግንኙነት ባሳየቸው የልብ ደካማነት ምክንያት አመንዝራ ሚስት እንደምትሆነው ዐይነት ከባልዋ ከእግዚአብሔር *ጋር* ከመሆን ይልቅ ከሌሎች አገሮች *ጋር* "ግንኙነት" የምትፈጥርበትን መንገድ አብዝታ ፈለገች። በተለመደው አሠራር መሠረት ስጦታን በመቀበል ፈንታ ወይም አመንዝራ በመሆኗ ስለ አገልግሎቷ በመክፈል ፈንታ፣ ኢየሩሳሌም እነዚህን ባዕዳን (አገሮች) አባበለች። ከእርስዋ *ጋር* የቀረበ ግንኙነት እንዲያደርጉ በማግባባት ጉቦ ወይም ክፍያ ሰጣቻቸው (ከሆሴ 8፥9 *ጋር ያነጻ*)። ስለ ሁኔታዋ እግዚአብሔር እንደሚከተለው በማጠቃለል ተናግሮአል፤ ኢየሩሳሌም የማይታመን ልብ ያላት ዐመፀኛና የማትታዘዝ ናት፤ ምንም ዐይነት ምክንያት የላትም!

መ. ኢየሩሳሌም፦ የተፈረደባት ዘመት ዐዳሪ (16፥35-43)

35-41 ፍርድ በኢየሩሳሌም ላይ ታውጆአል። ያለ ገደብ ከአረማውያንና ከረከሱ ጣዖቶቻቸው ጋር መንፈሳዊ ምንዝርና ውስጥ ገብታ ተገኝታለች። እግዚአብሔር አሁን እነዚህን አገሮች መሣሪያ በማድረግ እርሷን ለመቅጣት ይጠቀምባቸዋል። ኢየሩሳሌም በምንዝርና የወደደቻቸውን አገሮችና የጠላቻቸውን ሁሉ ብልጽግናዋንና በረከቷን አሟጥጠው ባዶ እንዲያደርጓት እግዚአብሔር ይጠቀምባቸዋል፤ ስለሆነም ኢየሩሳሌምና ይሁዳ ያለ እግዚአብሔር በረከት የቱን ያህል ባድማና ራቁታቸውን እንደሚሆኑ አሕዛብ ሁሉ ያያሉ። እነዚህ ባዕዳን አገሮች ይፈርዱባታል፤ ለምንዝርናና ልጅን ለአሳት አሳልፎ በመስጠት ላይ በሙሴ ሕግ በተሰጠው ቅጣት መሠረትም ቅጣት እንድትቀበል ያደርጓታል፤ ይኸውም ሞት ነው (ዘፀ 21፥12፤ ዘሌ 20፥10)። እየዘበቱ የጣዖት ማምለኪያ ስፍራዎችዋን ይደመስሳሉ (ከሆሴ 2፥12፤ ከናሆ 3፥5 ጋር ያነጻ)፤ ልብስዋንም ቀድደው በመውሰድ ሁሉም እንዲያዩዋት ዕርቃንዋንና ባዶዋን ያስቀሯታል። ከዚያም ትከሰሳለች፤ በድንጋይ ትወገራለች፤ በሰይፍም ትቈራረጣለች። በጣዖት አምልኮ ምክንያት ሕጉን በመጣስዋ እነዚህ አሕዛብ የእግዚአብሔርን ፍርድ ሲፈጽሙ ቤቶቿ እንዳለ ይቃጠላሉ (ዘዳ 13፥12-18)።

42-43 ይህ ቅጣት የኢየሩሳሌም አስጸያፊ የጣዖት አምልኮ በቆመበት በ586 ዓክክ በናቡከደነፆር መሪነት የባቢሎናውያን ወረራ ሲካሄድ በመጨረሻ ላይ ተፈጸመ። በዚህ ጊዜ የተቃጠለ ፍርስራሽ ሆና ቀረች። የተረፈው ሕዝብዋ ምርኮኛ ሆኖ ወደ ባቢሎን ተወሰደ። በዚያም እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ፍርድ የታቀደበትን ትምህርት በመማር፣ ከጣዖት አምልኮ ወደ አንድ አምላክ አምልኮ ተመለሱ። በዚያን ጊዜ ፈታሒነቱ በመርካቱ፣ በኢየሩሳሌም ላይ የነበረው የእግዚአብሔር ቍጣ ቆመ። ይኸውም እግዚአብሔር ይህን ቅጣት በእርሷ ላይ ያመጣው ኢየሩሳሌም ዳግም ታስታውሰው ዘንድ ነው። ምንም እንኳ እኛ እግዚአብሔርን ብንረሳ፣ ፍቅሩ የራሱ የሆኑትን ከመርሳት ያግደዋል። እግዚአብሔር እንደ ኪዳኑ ለግል ግንኙነት ያለውን ዐደራ በትኩረት ይከታተለዋል።

ሠ. የኢየሩሳሌም ጠማማነት (16፥44-58)

44-48 በኢየሩሳሌም፣ በሰዶምና በሰማርያ መካከል ንጽጽር ለማድረግ ሕዝቅኤል ከዚህ ላይ ምሳሌውን በመጠኑ ይለውጣል። እነዚህ ሦስት ከተሞች በሦስት እኅትማማቾች ተመስለዋል፤ ሁሉም የኬጢያዊት እናታቸውና የአሞራዊ አባታቸው ዘር ናቸው። ኬጢያዊቷ እናታቸው ባሏንና ልጆቿን የተጸየፈችበት ሁኔታ በግልጽ አልቀረበም። ምናልባት እርስዋም እግዚአብሔርን በመተው ልጆቿን ለጣዖት መሥዋዕት ይሆኑ ዘንድ አሳልፋ ሳትሰጥ አልቀረችም። ይሁን እንጂ ምስለሙሽ ትኩረት የተደረገበት የከነዓን ምድር ባሕርይ የሆነውን አስጸያፊ ኀጢአት ለመግለጥ ነው፤ ከነዓን የምትታወቀው ከማንኛውም ዐይነት የጣዖት አምልኮና ሃይማኖታዊ ጥመት የተደባለቀ ሃይማኖትን በመከተል ነውና።

እነዚህን ሦስት ከተሞች በተመለከተ የቀረበው የተለመደ ምሳሌ "እናቷን አይተህ ልጅቷን" የሚለው ዐይነት ነው። ኢየሩሳሌም፣ ሰዶምና ሰማርያ ያደጉት በከነዓን ምድር በነበረው ጠማማ ሃይማኖታዊ ሥርዐት ውስጥ ነው፤ አሁን ደግሞ የወላጆቻቸውን ርኩሰት ባሕርይ ወርሰዋል። ይሁን እንጂ ከእነዚህ ሁሉ በመንፈሳዊ ርኩሰትና ክፋት ቀዳሚ እኅት ሆና የተገኘችው ኢየሩሳሌም ናት። በስተ ሰሜን ያለችው ሰማርያ በብርታትና በወታደራዊ ኀይል የላቀች በመሆን የኢየሩሳሌም ታላቅ እኅት ብትሆንም፣ ደግሞም በስተ ደቡብ ያለችው ሰዶም በክብርና በኀይል ትንሽ በመሆን የኢየሩሳሌም (ዘፍ 10፥19) ትንሽ እኅት ብትሆንም፣ ኢየሩሳሌም በእግዚአብሔር ላይ ክፉ በማድረግና በማመፅ ከሁለቱም እጅግ የከፋች ነበረች። ሁለቱም እኅቶችዋ እጅግ የከፋ ኀጢአት በማድረግ የታወቁ ቢሆኑም፣ ኢየሩሳሌም ከሁለቱም እጅግ የከፋች ምግባረ ብልሹ ነበረች።

49-50 የሰዶም ዋነኛ ኀጢአት ትዕቢትና ጥጋብ ሲሆን፣ ይህም የመጣው እግዚአብሔር ከሰጣት እጅግ የተትረፈረፈ ብልጥግና ነው (ዘፍ 13፥10)፤ ይህም ከንቱ መተማመንን፣ ደንታ ቢስነትንና ንቀትን፣ ድኾችንና ችግረኞችን ችላ ማለትን አምጥቶአል። እንዲህ ዐይነቱ እጅግ የተትረፈረፈ ብልጥግና ከሚገባ በላይ ወሲባዊ ነውረኝነትን አስከትሎአል (ዘፍ 13፥13፤ 18፥20፤ 19፥4-5)። ሰዶም በራስዋ ክፉ ብትሆንም እንደ ኢየሩሳሌም ክፋትን ለማድረግ ገና አልጀመረችም። እግዚአብሔር ሰዶምን በፍርድ ስላስወገደ፣ በርግጥ ኢየሩሳሌም የበለጠ ቅጣት ይጠብቃታል ማለት ነው (ሰቆ 4፥6 ይመ፤ ከማቴ 11፥23 ጋር ያነጻ)።

51-52 በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር ከማድረጓ የተነሣ ተማርካ ከተወሰደችው የሰሜኑ መንግሥት ክፉ ከተማ ከነበረችው ከሰማርያ ይልቅ፣ ኢየሩሳሌም ሁለት ዕጥፍ ኀጢአትን ሠርታለች (1ነገ 12፥25-33፤ 15፥30፤ 16፥20፡26፡31-34)። የኢየሩሳሌም ርኩሰት እጅግ የከፋ በመሆኑ ከእርስዋ ይልቅ በንጽጽር ሰዶምና ሰማርያ ከክፋታቸው ጋር ጻድቃን መስለው እንዲታዩ አደረገች።

53-58 ፍርድ በኢየሩሳሌም ላይ ይመጣል። ከምግባረ ብልሹነትዋ የተነሣ በአሕዛብ መካከል መሣለቂያ በሆነችው በሰዶም ላይ ክፋዋ ኢየሩሳሌም እንደ ተኩራራች፣ ኢየሩሳሌምም በራስዋ ጊዜ በኤዶምና በፍልስጥኤም ፊት መሣለቂያ ትሆናለች። አሕዛብ ይንቋታል። ለኢየሩሳሌም ብቸኛ ተስፋም እግዚአብሔር ወደፊት ከምርኮ መልሶ እንደሚያቋቁማት የሰጣት የተስፋ ቃል ነበር። እግዚአብሔር መልሶ የሚያቋቁመው ኢየሩሳሌምን ብቻ ሳይሆን፣ የከነዓንን ምድር መልሶ በሚያቋቁምበት ጊዜ ሰዶምንና ሰማርያንም ጭምር ነው (ከምዕ 36 ጋር ያነጻ)። ያ መልሶ የማቋቋም ሁኔታ ኢየሩሳሌምን ዝቅ ዝቅ ያደርጋታል፤ ስለ ክፋትዋም ሁሉ ያዋርዳታል።

ረ. መልሶ መቋቋም፦ የፍቅር ተስፋ (16፥59-63)

59 እግዚአብሔር ይህን ምስለሙሽ የሚያጠቃልለው እርሱ ለተስፋ ቃሉ ያለውን የማይለወጥ ታማኝነት በማረጋገጥ ነው። ለእርሱ ሊኖራቸው የሚገባውን ታማኝነት ስላጓደሉና ከእርሱ ጋር ያላቸውን ቃል ኪዳን ስላፈረሱ በሙሴ ሕግ ላይ ተስፋ ሆኖ በተሰጠው መሠረት ኢየሩሳሌምን (እናም እስራኤልን) ይቀጣል። በመንፈሳዊ ምንዝርናቸው የተጣሰው ሕግ የሙሴ ኪዳን ነው፤ ይህም እስራኤል በመሐላ ከእግዚአብሔር ጋር የገባቸው ብቸኛ ኪዳን ነው (ዘፀ 24፥7-8፤ ዘዳ 29፥10-21)። ነገር ግን ይሁዳ ኢየሩሳሌም ልክ በዘዳግም 29 እንደ ተጻፈው ያንን ኪዳን አፈረሰች። ስለዚህ እግዚአብሔር በታማኝነት የዚያን ኪዳን ተገቢ ፍርድ ማለትም ርግማኖቹን ሁሉ ያፈስባቸዋል ማለት ነው።

"መሐላ" የሚለው ቃል ርግማን ማለት ሲሆን፣ በአጠቃላይ በብሉይ ኪዳን በሁለቱም መንገዶች ጥቅም ላይ ውሎ እናገኘዋለን። እግዚአብሔር ይህን ቃል ሆነ ብሎ የተጠቀመው በዘፀአት 24 እና በዘዳግም 29 ላይ የተጠቀሰውን መሐላ ኢየሩሳሌም የናቀችበትን ሁኔታ ለማሳየትና የሚመጣባትንም ርግማን ችላ ያለችበትን ሐሳብ ሁለቱንም ለማስተላለፍ ነው።

60 ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም ላይ ያወረደውን ፍርድ ከፈጸመ በኋላ፣ በልጅነትዋ ጊዜ ከአገሪቷ ጋር የገባውን ዘላለማዊ ኪዳን በማስታወስ የፍቅር ታማኝነቱን ይቀጥላል። በሙሴ ሕግ (ዘሌ 26፥40-45) በእስራኤል ላይ የወደፊቱንና የመጨረሻውን ፍርድ ካደረገ በኋላ፣ ከአብርሃም ጋር የገባው ቃል ኪዳን ማለትም የከነዓንን ምድር ለእስራኤል የዘላለም ርስት አድርጎ እንደሚሰጥ የገባውን (ከዘፍ 17፥7-8፤ ከዘሌ 26፥42 ጋር ያነጻ) እንደሚያስብ እግዚአብሔር ቃል ገብቶአል። ይህ ዘላለማዊ ኪዳን ሲሆን፣ እግዚአብሔር ከምሕረቱና ከፍቅሩ የተነሣ የሰጠውን ተስፋ እንደሚያስብ ተናግሮአል። የሰው ልጅ ታማኝ አለመሆን የእግዚአብሔርን ታማኝነት አይለውጠውም (ከ2ጢሞ 2፥13 ጋር ያነጻ)።

61-63 እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባውን ኪዳን ሲያስብ፣ ኢየሩሳሌምንና ይሁዳን በከነዓን ምድር መልሶ ሲያቋቁም፣ ኢየሩሳሌም ተማርካ እንድትወሰድ ያደረጓት ክፉዎቹ መንገዶችዋ እንደ ሆኑ በማስብ ታፍራለች። ወደ ፊት በሚመጣው መንግሥት (ከምዕ 48 ጋር ያነጻ) ኢየሩሳሌም በክበረ ስፍራ ላይ እንደ ገና ትመሠረታለች። ከሰዶም ወይም ከሰማርያ እጅግ የከፋች በመሆንዋ እጅግ ከባድ ፍርድ የምትቀበል ብትሆንም፣ እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ እነርሱን

“ሴቶች ልጆችዋ” አድርጎ በመስጠት (20፥43፤36፥31) በእነርሱ ላይ እጅግ ከፍ ከፍ ያደርጋታል። ስለዚህ እነዚህ ከተሞች እንደ እኅቶች (ከተማ/አገር) ከእንግዲህ አይታሰቡም፣ ነገር ግን በኢየሩሳሌም ሕጋዊ አስተዳደር ሥር የሆኑ ወጣ ያሉ ከተሞች ያሏቸው ከተሞች ይሆናሉ (ከቊ. 46፤ ከመሳ 1፥27 ጋር ያነጻ)። ሰዶምና ሰማርያ የኢየሩሳሌም ሴቶች ልጆች ሆነው መመለሳቸውና በእግዚአብሔር መሰጠታቸው በሙሴ ሕግ መሠረት የሚደረግ አይደለም፤ ይሁን እንጂ ይህ የሚሆነው ከእግዚአብሔር ቸርነት የተነሣ ነው።

ይህ የመልሶ መቋቋም ሁኔታ እግዚአብሔር ምንጊዜም ያለ፣ ምንጊዜም ታማኝ፣ በራሱ ተነሣሽነት ባለፈው ዘመን የመረጣትና ወደፊትም የሚያጽናናት አምላኳ እንደ ሆነ ኢየሩሳሌም እንድታውቅ ይደርጋታል። እንግዲህ ኢየሩሳሌምና ይሁዳ ያለፈውን ኀጢአታቸውን ከቶ እንደ ገና አያስታውሱትም፤ እግዚአብሔር ኀጢአታቸውን ሁሉ ያስተሰርይላቸዋል፤ በደላቸውንም ሁሉ ይረሳላቸዋል። በርግጥ ይህ ፍጻሜ ያገኘው ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሞተው ሞት ነው።

8. የሁለቱ ንስሮች እንቆቅልሽና ተምሳሊት (17፥1-24)

1-10 ምርኮኞቹ ሕዝቅኤል በምስስሎሽ ኢየሩሳሌም ለእግዚአብሔር በመንፈሳዊ ረገድ ታማኝ ያልሆነችበትን ረጅም ታሪክ ሲነግራቸው እያዳመጡ ሳሉ፣ አንዳንዶቹ በሕዝባቸው ባለፈ ኀጢአት ሁሉ ለምን እንደሚፈርድባቸው መጠየቅ ጀመሩ። ነገር ግን የሚፈረድባቸው በራሳቸው ዘመን በእግዚአብሔር ላይ ስላልታመኑ እንደ ሆነ ሕዝቅኤል ይመልስላቸዋል፤ አለመታመናቸውን የገለጡትም ስለ ደኅንነታቸው በግብፅ ላይ የመደገፍ ዝንባሌ በማሳየታቸውና መሪያቸው የነበረው ሴዴቅያስ ባሳየው ምግባረ ብልሹነት እንደ ሆነም ይገልጽላቸዋል።

ሕዝቅኤል ይህን መልእክት ለማስተላለፍ እንቆቅልሽን ይጠቀማል። በእንቆቅልሹ ውስጥ ሁለቱ ነገሥታት እግዚአብሔርና ሴዴቅያስ ናቸው። የዚህ እንቆቅልሽ ታሪካዊ ዳራ የሚገኘው በ2ነገ 24፥6-20፤ በ2ዜና 36፥8-16 እና በኤር 37፤ 52፥1-7 ላይ ነው። የይሁዳ ነገሥታት የነቢያትን ማስጠንቀቂያና የእግዚአብሔር ቅጣት መሣሪያ ለሆኑት ለባቢሎናውያን መገዛትን አሻፈረኝ በማለት ተሰዋዋጮች ነበሩ። ይልቁን ነገሥታቱ የደኅንነትና የርዳታ ዋስትናን ከግብፅ ለማግኘት ጥረት አደረጉ። ይህ ጉዳይ የዚህ ምዕራፍ ዋና ሐሳብ ነው።

እንቆቅልሹ በሁለት ክፍል ቀርቦአል። ከቊ. 1-6 ያለው ክፍል እጅግ የከበረና በኀብረ ቀለማት ያሸበረቀን ንስር የሚገልጽ ነው። ይህ ወፍ ወደ ሊባኖስ በመብረር (የከነዓን ምድር፤ ከኢያ 1፥4፤ ከ2ነገ 14፥9 ጋር ያነጻ) የዝግባን ጫፍና ከጫፉም የላይኛውን ቀንበጥ (ለጋ ቀንበጦችን) ወስዶ ወደ ነጋዴዎች ምድር አመጣቸው (ባቢሎን፣ ከ16፥29 ጋር ያነጻ)። ከዚያም ንስሩ ከከነዓን ምድር ጥቂት ዘር ወስዶ ለምለም ዐፈር ባለበት ምድር ተክለው (ከዘዳ 8፥7፤ 11፥11 ጋር ያነጻ)። ዘሩም በበቀለ ጊዜ ዐጭርና ወደ ጐን የተንሰራፋ የወይን ተክል ሆነ፤ ዕንቡጦቹና ቅርንጫፎቹም ወደ ንስሩ አዩ።

የእንቆቅልሹ ሁለተኛ ክፍል (ቊ. 7-10) ሌላ ታላቅ ንስርን የሚያመለክት ነው፤ ይህኛው እንደ መጀመሪያው የከበረ አይደለም፤ ነገር ግን የበቀለውን የወይን ተክል ቅርንጫፎችና ሥሮች ወደ ራሱ ዘወር በማድረግ እንዲያድጉ አድርጎአቸዋል። ይህ የወይን ተክል በመልካም መሬት ቢበቅልና ብዙ ፍሬ ቢያፈራም ሊያድግ አልቻለም፤ ሥሩም ተነቀለ፤ በምሥራቅ ነፋስ ተመትቶም ፍሬው ደረቀ። ማንም እንደ ገና ሊመልሰው አልቻለም።

11-14 ለትርጕሙ ቊ. 11-12ᵘ ማዳመጥ እንዲደረግ ጥሪ ያቀርባሉ፤ ቊ. 12ለ-18 ክሱን ይሰጣሉ፤ ቊ. 19-21 ደግሞ “ስለዚህ” በሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ጣልቃ መግባት ያውጃሉ። እያንዳንዱ ንስር በአንድ በኩል እግዚአብሔር በይሁዳ ላይ የቅጣት መዓቱን ለማውረድ መሣሪያ አድርጎ የተጠቀመበትን ድል አድራጊ ንጉሥ የሚወክል ነው። የመጀመሪያው ንስር የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ሲሆን፣ ንጉሥ ዮአኪንን (የዝግባው ቀንበጥ) እና የእርሱን ወጣት ልዑላን እንዲሁም መሳፍንቱን (የላይኛው ቀንበጥ) ወስዶ ወደ ነጋዴዎች ምድር (ከ1ነገ 10፥27፤ ከ2ነገ 24፥10-12፤ ከኤር 22፥15:23 ጋር ያነጻ) ወደ ባቢሎን ማረካቸው። ዝግባው መሲሓዊ መልእክትን የያዘ ነው (ከኢሳ 10፥33-11፥1 ጋር ያነጻ)። የዳዊትን ዘር የሚወክል ሲሆን፣ በመሲሑ ማለትም በኢየሱስ ክርስቶስ ይደመደማል።

ዮአኪን ከዳዊት ዘር የሆነ ንጉሥ ነበር። “ቤተ ሰብ” የተባለው የመንግሥት ዘር ሲሆን፣ ናቡከደነፆር ወስዶ በከነዓን ምድር የተከለው ነው። የመንግሥት ዘር የሆነው ሴዴቅያስ (ወይም ማታንያን ከ2ነገ 24፥17፤ ከኤር 37፥1 ጋር ያነጻ) የዮአኪን አጎት ሲሆን፣ ናቡከደነፆር ከእርሱ ጋር የሚያስተሳስር ኪዳንን በመፈጸም ሴዴቅያስን በቀሩት የይሁዳ ትሩፋን ላይ መሪ አድርጎ ሾመው። ዮአኪን በዚህ ጊዜ በምርኮ በባቢሎን ቢሆንም ሕጋዊው ንጉሥ እርሱ ነበር። ሴዴቅያስና በምድሪቱ ከእርሱ ጋር የቀሩት ዕብራውያን ፍሬ የሚያፈራ የወይን ተክል እንዲሆኑ ነበር፤ ነገር ግን በምዕራፍ 15 ላይ እንደ ተገለጸው የወይኑ ተክል ከንቱና ጥቅም የሌለው ሆኑ። ዐጭርና ወደ ጐን የተንሰራፋ ነበር፤ ምክንያቱም ናቡከደነፆር ራሱን ከፍ ከፍ እንዲያደርግ አልፈቀደለትም።

15-21 ሁለተኛው ንስር የሚወክለው የግብፅን ንጉሥ ሲሆን፣ ሴዴቅያስ ከናቡከደነፆር ጋር የገባውን ኪዳን አፍርሶ (ከ2ዜና 36፥13 ጋር ያነጻ) በ588 ዓክክ በናቡከደነፆር ላይ ባመፀ ጊዜ፣ ወታደራዊ ድጋፍን ያገኝ ዘንድ መልእክት የላከበት ንጉሥ ነው። ይህ በግብፅ የመታመን ሁኔታ በኢሳይያስና (ኢሳ 30፥1-2) በኤርምያስ (ኤር 37፥1) ከፍተኛ ተቃውሞ አጋጥሞት ነበር። እግዚአብሔር ይህ የወይን ተክል (ሴዴቅያስና ትንሹ የይሁዳ መንግሥት) ይሳካለት ይሆን? የሚል መልስ ዐዘል ጥያቄ አቅርቦአል። በአጽንዖት የተገለጸው ምላሽ አይሳካለትም! የሚል ነው። ናቡከደነፆር ይሁዳን በሚያጠቃበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ፍርድ ይቀበላሉ፤ ምክንያቱም ሴዴቅያስ ከእርሱ ጋር የገባውን ኪዳን በመናቅና በማፍረስ ወደ ግብፅ ዘወር ብሏልና (2ዜና 36፥13 ይመ፤ ከሕዝ 5፥7 ጋር ያነጻ)።

ሴዴቅያስ ከናቡከደነፆር ጋር ለገባው ኪዳን ባለመታዘዙና (በእግዚአብሔር ስም በመማል፣ ከ2ዜና 36፥13 ጋር ያነጻ) ከእግዚአብሔር ጋር የገባውንም ኪዳን በማፍረሱ፣ ባላከበረው በሙሴ ኪዳን ላይ በተሰጠው ፍርድ መሠረት ፍርድን ይቀበላል። እግዚአብሔር መረብ ይዘረጋል ከባቢሎን ሰራዊት ጋር ሆኖም ይይዘዋል፤ በምርኮም ወደ ባቢሎን ያመጣዋል። ኢየሩሳሌም በናቡከደነፆር ስትከበብ ግብፅ ምንም አትረዳም፤ የሴዴቅያስ ሰራዊት በሰይፍ ይገደላልና፤ ቀሪው ሕዝብ በመላዩቱ ምድር ይበተናል፣ ሴዴቅያስም በመጨረሻ በባቢሎን ምድር ይሞታል (ከ12፥13-14 ጋር ያነጻ)። ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ምሕረት መገለጫ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ብቻ እውነተኛ አምላክ እንደ ሆነ ሴዴቅያስ ያውቅ ዘንድ፣ በእነዚህ ፍርዶችም የተናገረ መሆኑን ይኸው ንጉሥ ያውቅ ዘንድ እግዚአብሔር ፍትሓዊነቱን በታማኝነት እየፈጸመ ነበርና። ይህን ፍትሕ በመስጠቱ እግዚአብሔር ታማኝነቱን አሳይቶአልና። ስለዚህ ሴዴቅያስ እግዚአብሔር ብቻውን እውነተኛ የሆነው አምላክና እነዚህን ፍርዶች ተናግሮ ያደረገውን ያውቅ ይሆናል።

22-24 ይህ የዝክረ ታሪክ ሐሳብ የድነትን ንግር ይሰጠናል። እግዚአብሔር ፍርድን ሲያውጅ ብዙውን ጊዜ ተስፋንም ይፋ ያደርጋል። ይሁዳ ተተክላና ፍሬያማ ሆና ለመጽናት አልቻለችም። ይሁን እንጂ ወደፊት እግዚአብሔር በቅጣት ይሁዳን ካጠራ በኋላ “ከረጅሙ ዝግባ ጫፍ ቀንበጡን” ወስዶ ቀንጥሶ “ከሁሉ ከፍ ባለው ተራራ ላይ” ይተክለዋል። ይህ መቀንጠስ ናቡከደነፆር በቊ. 4፡ 12 ላይ ዝግባውን በመቊረጥ ካደረገው የመጀመሪያ መቊረጥ ጋር የተያያዘ አይደለም፤ ምክንያቱም ኤር 22፥28-30 የኢኮንያን (የኮንያ) ቀጥተኛ ዘር በዳዊት ዙፋን ላይ በመሆን እንደማይቀጥል ተናግሮአል። ይልቁን የዳዊት ሐረግ የሚቀጥለው በሌሎች ትውልዶች በኩል ነው። ሆኖም ይህ ዐዲስ መቁረጥ አውን የሚሆነው ከመሲሑ ዘር ከ“ዝግባ”ው ነው። ቀንበጥ ነበር፤ ይህም መሲሓዊ እንድምታ ያለው ቀንበጥ ነው (ኢሳ 11፥1፤ ኤር 23፥5-6፤ 33፥14-16፤ ዘካ 3፥8፤ 6፥12-13)። ይህም በመሲሑ መንግሥት እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ንጉሥ አድርጎ የሚሾመው መሲሑ ነው።

ከፍ ያለው በጣም ረጅሙ ተራራ የጽዮንን ተራራና ቤተ መቅደሱን ሊያመለክት ይችላል (ከ20፥40፤ ከመዝ 2፥6፤ ከሚክ 4፥1 ጋር ያነጻ)። ይህ መሲሓዊ መንግሥት ልክ እንደ ዝግባ ዛፍ ታላቅና ፍሬያማ ይሆናል። ወፎች ሁሉ በቅርጫፎቹ ላይ ጎጆአቸውን ይሠራሉ፤ ይህም የዓለምን ሕዝቦች የሚያመለክት ተምሳሊት ሳይሆን አይቀርም (ከዳን 4፥17:32:34-37፤ ከማቴ 13፥31-32 ጋር ያነጻ)። ለመሲሑና ለእርሱ አገዛዝ ይንበረከካሉ።

9. ጽድቅን በተመለከተ የእያንዳንዱ ግለሰብ ኀላፊነት (18፥1-31)

ሀ. ምሳሌ የመርሕ ተቃራኒ ነው (18፥1-4)

1-4 በ16፥44 ላይ ሕዝቅኤል፣ እስራኤል በአካባቢዋ ያለውን የአረማውያን ባሕርይ ለራሷ ገንዘብ አድርጋ የወሰደች መሆኗን ለማሳየት ምሳሌ አቅርቦአል። የሕዝቅኤል አድማጮች ያንን ምሳሌ በሚገባ አልተረዱትም። ስለ አባቶቻችን ርኵሰት እየተፈረደብን ነው የሚል ምክንያት ሰጡ። የዚህ የዐውርቱ ትእዛዛት መርሕ በአባቶች ኀጢአት ልጆች ሊጐዱ እንደሚችሉ ያስተምራል ነው (ዘፀ 20፥5፤ ዘዳ 5፥9)። ወላጆች ለልጆቻቸው ምሳሌ ናቸው። በሚያሳዝን ሁኔታ ልጆች ወላጆቻቸው የሚፈጽሙትን ኀጢአት አዘውትረው ይፈጽማሉ። ልክ እንደዚሁ ለእንደነዚህ ዐይነት ድርጊቶቻቸው ተተካካይ ቅጣት መቀበል አለባቸው። እያንዳንዱ ልጅ በግሉ ተጠያቂ ነው። ልጅ "የኀጢአት ቅጣት ውርስ" የሚለውን ይህን ሂደት በማንኛውም ጊዜ ሊያሳጥር ይችላል፤ ነገር ግን እርሱ ወይም እርሷ ንስሓ በመግባት ተገቢ የሆነውን ማድረግ ይኖርባቸዋል።

የምርኮኞቹ አለመረዳት፣ "አባቶች ጐምዛዛ የወይን ፍሬ በሉ፤ የልጆችንም ጥርስ አጠረሰ" በሚለው የጊዜው ተምሳሊታዊ አነጋገር ተገልጸአል፤ ይኸውም አባት የሚያደርገው በልጅ ላይ ተጽዕኖ አለው ማለት ነው። ሕዝቡ ጽድቅና ክፋት በውርስ የተገኙ ናቸው ብለው አምነዋል፤ ስለዚህ የግል አካሄድ የሚለወጥበት ምክንያት አልነበረም።

ለዚህ ዐዲስ ምሳሌ የእግዚአብሔር ምላሽ የውርስ መርሕ ወዲያውኑ እደሚቆም ነው፤ በጽድቅና ጽድቅ ካልሆነ ነገር ጋር በተሳሳተ መንገድ እንዲገናዘብ ተደርጎአልና። እያንዳንዱ ሰው የሚኖረው ወይም የሚሞተው በእርሱ ወይም በእርሷ የግል ድርጊት መሠረት ነው። እግዚአብሔር በአጽንዖት "እነሆ ነፍስ ሁሉ የእኔ ናት" በማለት ተናግሮአል። የሰው ሁሉ ፈጣሪ እርሱ ስለ ሆነ፤ ሁሉም በፊቱ እኩል ናቸው። በእርሱ መንገድ ለመሄድ ወይም ላለመሄድ ሁሉም በነጻነት የየራሳቸውን ውሳኔ ማድረግ ይችላሉ። የግል ኀላፊነት መርሕ ምንጊዜም ቢሆን እውነት ነው (ከዘፍ 2፥17፤ 4፥7፤ ከዘዳ 24፥16፤ ከ2ነገ 14፥6 ወዘተ ጋር ያነጻ)። ልጅ የግድ አባቱን መምሰል የለበትም።

መሠረታዊ የሆነው መርሕ በቁ 4 ማጠቃለያ ላይ ቀርቦአል፤ "ኀጢአት የምትሠራ ነፍስ እርሷ ትሞታለች"። ሕይወትና ሞት በዚህ ዐውድ ውስጥ አካላዊ እንጅ ዘላለማዊ አይደሉም። አንድ ሰው በመሲሑ በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚገባው ወይም የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን እንዳደረጉት በመስቀሉ ላይ እርሱ የሠራውን ሥራ በእምነት ወደ ፊት በመመልከት ወይም የዐዲስ ኪዳን ቅዱሳን ዛሬ እኛ እንደምናደርገው በእምነት ወደ ኋላ በመመልከት ነው። ዘላለማዊ ድነት እውን የሚሆነው በእምነት ብቻ ነው (ከዘፍ 15፥6፤ ሮሜ 4፥5፤ ኤር 2፥8-9 ጋር ያነጻ)። የሙሴ ሕግ መመሪያ የተሰጠው እስራኤልን ከግብፅ በተቤዣት፣ ሕጉንም በገለጠው በእግዚአብሔር ላይ ተጨባጭና ተግባራዊ የሆነ እምነት ለነበረው የእምነት ግንኙነትም ከአምላክ ጋር ለነበረው ሕዝብ ነው። በእርሱ ማመን የደም መሥዋዕት ሥርዐትንና ለትእዛዛቱም መታዘዝን የያዘ ነው። ሕዝቡ እነዚህን ትእዛዛት ቢያከብሩ፣ ጽድቃቸውን ያሳያሉ፣ የእግዚአብሔርን በረከት በመቀበልም በሕይወት ይኖራሉ። ነገር ግን በሕጉ ውስጥ በተገለጠው በእግዚአብሔር መንገድ መሠረት መኖር ከልቻሉ፣ በመሲሑ ያመኑ እንኳ አካላዊ ሞትን እንደሚሞቱ የሙሴ ሕግ አመልክቶአል። (ከዘዳ 28፥58-66፤ 30፥15-20 ጋር ያነጻ)። ይሁን እንጂ በመሥዋዕቶቹ እንደ ተገለጸው በመሲሑ ካላመኑ ዘላለማዊ ሞትን ይሞታሉ።

ለ. የመርሑ ሦስት መግለጫዎች (18፥5-18)

5-9 የግል ኀላፊነትን የሚጠይቀው መርሕ ከእግዚአብሔር ጋር የታመነ ግንኙነት ያለው ጻድቅ ሰው በአካልና በዘላለማዊ ረገድ በሕይወት እንደሚኖር ያመለክታል። ይሁን እንጂ በመጀመሪያ እግዚአብሔር በሙሴ ሕግ መሠረት ጽድቅን መግለጽ ይኖርበታል። ዐምስት ሕጋዊ ዘርፎች የጽድቅ ድርጊት የሆነውን ከርኵሰት ሥራዎች ለይተው አስቀምጠዋል። በመጀመሪያ፣ ጻድቅ ሰው በከፍተኛ ተራሮች ላይ በተሠሩት በአረማውያን መቅደሶች ውስጥ ከሚሠዉት የጣዖት አምልኮ መብሎች እንዲሁም በሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት ተስፋፍቶ ከሚገኘው የጣዖት አምልኮ ራሱን ማግለል አለበት (ከዘዳ 12፥21 ጋር ያነጻ)። ሁለተኛ፣ እንዲህ ዐይነቱ ሰው የባልንጀራውን ሚስት ከማባለግ ወይም ሴትን በወር አበባዋ ጊዜ ከመገናኘት መጠበቅ አለበት (ዘፀ 20፥14፤ ዘሌ 15፥24፤ 18፥19፤ 20፥10:18፤ ዘዳ 22፥22)። ሦስተኛ፣ ሰዎችን በጉልበት ሥራና በጭቈና አያስጨንቅም፤ ነገር ግን የድኻውን ሰው ዕዳ በመሠረዝ ያጽናናዋል (ዘፀ 22፥26-27፤ ዘዳ 24፥6፤ አሞ 2፥8)። ባለጠጎች ድኾችን ይጨቍናሉ፤ በተለይም ወላጅ የሌላቸውን ልጆች፣ መበለቶችንና መጻተኞችን ለብዝበዛ ዘይሖአቸው በቀላሉ ይጠቀሙባቸዋል። አራተኛ፣ ጻድቅ ሰው አይሰርቅም (ዘፀ 20፥15፤ ዘሌ 19፥13)፤ ነገር ግን የተቸገሩትን ያበላል፤ ያለብሳል (ዘዳ 15፥11፤ 24፥19-22፤ ኢሳ 58፥7)።

በመጨረሻም ከአስራኤላውያን ወገኞች ምንም ዐይነት ወለድ ባለመፈለግ (ዘፀ 22፥25፤ ዘዳ 23፥19-20፤ መዝ 15፥5፤ ኢሳ 24፥2) ጻድቅ የሆነ ሰው ፍትሕን ብቻ ይፈጽማል (ዘሌ 19፥15-16: 35-36፤ ዘዳ 25፥13-16። በንግድ ግንኙነት ከፍተኛ ወለድ ከባዕዳን መቀበል የተለመደ ነው፤ ነገር ግን ድኻ ከሆነው ዕብራዊ ወገን በአራጣ አበድሮ ከፍተኛ ወለድ መቀበልና ከቸርነት ይልቅ ትርፍን ማግኘት፣ የፍቅርንና ለኪዳኑ ሕዝብ ሊታሰብ የሚገባውን የቸርነት መርሕ የሚቃረን ነው። ቍ 9 ጻድቅ ሰውን እንደሚከተለው ይገልጸዋል፤ በሙሴ ሕግ መሠረት የሚኖር ጻድቅ ሰው ነው፤ እግዚአብሔር እንዳቀደውም የበረከትን ሕይወት አሁንም ለዘላለምም ደስ እያለው ይኖራል (ከዘሌ 18፥1-5፤ ከዘዳ 11፤ 26፥16-19፤ 30፥15-20 ጋር ያነጻ)። በነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ያሉት ዝርዝር ሐሳቦች አንድ ሰው ለሌሎች ያለው አስተሰሳብና ድርጊት እርሱ ወይም እርሷ በእግዚአብሔር ስላላቸው እምነትና አስተሳሰብ የሚያመለክቱ ጠቋሚዎች እንደ ሆኑ ይገልጻሉ።

10-13 ሁለተኛው ምሳሌ የሚያመለክተው የጻድቅ ሰው ልጅ ስለ ሆነው ጻድቅ ያልሆነ ልጅ ነው። ይህ ልጅ ጻድቅ ያለመሆኑንና እምነት የሌለው መሆኑን የሚገልጸው የአባቱ ተቃራኒ የሆነ አኗኗር በመኖር ነው። አባትየው በጽድቅ ምንም ዐይነት ነገር ቢያደርግ፣ ልጁ አያደርገውም፤ አባትየው ከጽድቅ የተነሣ የሚቈጠብበትን ማንኛውንም ነገር ርኩሰ ልጅ ይፈጽመዋል። ሰውን ይገድላል። ቍ 18 በዐጭሩ የሚገልጸው ክፉ ሥራው መጨቈን፣ መዝረፍና ስሕተትን መፈጸም እንደ ሆነ ነው። በሕጉ መሠረት የጽድቅን መመሪያዎች ተከትሎ መኖር ባለመቻሉ በዚህም ሆነ በዚያኛው ዓለም ፈጽሞ በሕይወት አይኖርም። እንዲህ ዐይነቱ ሰው በርግጥ የተገለጸው በምናሴ ሕይወት ነው።

14-18 ሦስተኛው መግለጫ የሚያመለክተው ጻድቅ ያልሆነ ሰው የግድ ጻድቅ ያልሆነ ልጅ ይኖረዋል ማለት እንዳልሆነ ነው። አንድ የልጅ ልጅ አያቱ እንዳደረገው በመሲ ሕግ መሠረት በጽድቅ ቢኖርና የአባቱንም የረከሰ ሥራ ላለመከተል ቢወስን፣ ከአባቱ የርኵሰት ሥራ የተነሣ አይሞትም፤ ነገር ግን በርግጥ በሕይወት ይኖራል። አባቱ ግን የሚሞተው ራሱ ከሠራው ኀጢአት የተነሣ ነው።

ሐ. የመርሑ ዝርዝር መግለጫ (18፥19-32)

19-24 የግለሰብን ኀላፊነት በተመለከተ የተጠቀሱትን መርሖች ከቍ 1-4 ባሉት በማቅረብና ከቍ 5-18 ባለው ደግሞ አጉልቶ በማሳየት፣ ሕዝቅኤል ከዚያ በኋላ የመርሖቹን ዝርዝር መግለጫ አብራርቶአል። ንግግሩ የተጀመረው ምርኮኞቹ የሚከተለውን መልስ ዐዘል ጥያቄ ባቀረቡ ጊዜ ነው፦ "ልጅ ስለ አባቱ ኀጢአት ለምን አይቀጣም?" እግዚአብሔር እነዚህን

ጥያቄዎች የመለሰው ተከታታይና መለስተኛ የሆኑ መርሖችን በመስጠት ነው።

በመጀመሪያ፣ ማንም ሰው ጻድቅ ያልሆነ ሰው ልጅ ቢሆንም እንኳ በጽድቅ ከኖረ በአካል በሕይወት ይኖራል፤ በመጨረሻም ለዘላለም ይኖራል። ሁለተኛ፣ ጻድቅ ያልሆነ ኀጢአተኛ ለኑሮ አስፈላጊ የሆነውን የእግዚአብሔርን የጽድቅ መንገድ ባይታዘዝ፣ በአካል ይሞታል፤ በመጨረሻም ለዘላለም ይሞታል። ሦስተኛ፣ ልጅ የአባቱን የኀጢአት ቅጣት አይሸከምም፤ ወይም አባት የልጁን የኀጢአት ቅጣት አይሸከምም፤ አራተኛ፣ ጻድቃን ክጽድቃቸው የተነሣ ይኖራሉ (ከዘሌ 18፥5 ጋር ያነጻ)፤ ነገር ግን ክፉዎች ከኀጢአታቸው የተነሣ ይሞታሉ (ዘዳ 30፥17-18)። ዐምስተኛ፣ ክፉ ሰው ኀጢአት ከተሞላው ዐመፁ ቢመለስ፣ ጽድቅ ያለባቸውን ትእዛዛት ቢፈጽምና በመሲሑ ቢያምን በአካል በሕይወት ይኖራል፤ በመጨረሻም ለዘላለም መኖር ይችላል። የእንደነዚህ ዐይነት ሰዎች ያለፈ ኀጢአት ፈጽሞ አይታሰብም፤ ይኸውም አሁን ከሚኖሩት ጻድቅ ድርጊት የተነሣ ነው። እንዲህ ዐይነቱን ኀጢአተኛ ሰው ባለፈው እንዳይሞት የጠበቀው የእግዚአብሔር አስደናቂ ጸጋ ብቻ ነው። ስድስተኛ፣ ክፉ ሰው በመሞቱ እግዚአብሔር ደስ አይሰኝም። ከዚህ ይልቁን ክፉ ሰው ወደ እርሱ ተመልሶ በመታዘዝ ቢኖር እጅግ ደስ ይሰኛል። በኀጢአት የተሞላው የሰው ዘር ፍርድ እግዚአብሔርን ደስ እንደሚያሰኘው ብዙውን ጊዜ ይመለከታል። ምንም ነገር ከእግዚአብሔር ፍላጎት የራቀ አይደለም፤ ባይሆን ኖሮ አንድያ ልጁን ልኮ ለዓለም ሁሉ ኀጢአት በመስቀል ላይ እንዲፈረድበት ባላደረገ ነበር።

በመጨረሻ፣ በመሲሑ ያመኑ ጻድቃን ከኀጢአት ነጻ እንደ ሆኑ እንዲያስቡ የሚያደርግ ጊዜ ወይም ቦታ እንደሌለ ነው፤ በእግዚአብሔር የጽድቅ መንገድ ከመኖር ወደ ኀጢአት ዘወር ቢሉ እነርሱም ለዘላለም ባይሆንም እንኳ የሥጋ ሞትን ይሞታሉ። ለእግዚአብሔር ታማኞች ካለመሆናቸው የተነሣና ጽድቅ ከሌለበት ድርጊታቸው የተነሣ እነርሱም ይሞታሉ። እግዚአብሔር ኀጢአትን አያበረታታም፤ ወይም የእርሱን ጻድቅ ትእዛዛት እንዳይታዘዙ ለማንም ፈቃድ አይሰጥም።

25-29 ሕዝቅኤል እንደ ገና የምርኮኞቹን ሐሳብ የሚገልጸውን ሌላ መልስ ዐዘል ጥያቄ እንደሚከተለው አቀረበ፦ ይኸውም፣ "የጌታ መንገድ ቀና አይደለችም" የሚለው ነው። እግዚአብሔር ቀናና ጻድቅ ያልሆኑ የእስራኤል መንገዶች እንጂ የእርሱ እንዳልሆኑ መለሰ። ጻድቅ የሆነውንና ጻድቅ ያልሆነውን ነገር በተመለከተ ትክክል ባልሆነ መንገድ የውርስን መርሕ ከዚህ ጕዳይ ጋር ማገናዘብ ፈለጉ። መርሑ በድጋሚ ሲገለጽ ጻድቃን ጻድቃን የሆኑት በሙሴ ሕግ መሠረት ጽድቅንና ፍትሕን ስላደረጉ ብቻ ነው፤ ክፉዎችም ጻድቃን ያልሆኑት ጽድቅን ከሚጠይቀው ከሕጉ ዘወር ስላሉ ነው። የእግዚአብሔር ጸጋ ከሕጉ ጋር ከመስማማቱ የተነሣ፣ ክፋዎች ከክፉ ድርጊታቸው ተመልሰው የሙሴን ሕግ የጽድቅ ሥርዐቶች በመከተል ምንጊዜም ጻድቃን እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ልክ እንደዚሁ ጻድቃን በእግዚአብሔር ቅዱስ መንገድ መራመድ ካልቻሉ ሥጋዊ ሞትን ይሞታሉ። ጽድቅ ወይም ርኩሰት አይወረስም። ለአንድ ግለሰብ ጽድቅ የሚቁጠረው በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ በተገለጠው መሠረት የእግዚአብሔርን የጽድቅ ሥራ ሲፈጽም ወይም ስትፈጽም ነው። ልክ እንደዚሁ ጻድቅ አለመሆን የሚቁጠረውም አንድ ሰው በእግዚአብሔር የጽድቅ መንገድ መራመድ ሳይችል ሲቀር ነው። ውሳኔው የግል እንጂ የውርስ ጕዳይ አይደለም።

30-32 እግዚአብሔር ይህን መልእክት የሚያጠቃልለው ሕዝቡ በየግላቸው ስለ ኀጢአታቸው ንስሓ እንዲገቡ በማሳሰብና በመለመን ነው። መኖር ከፈለጉ ይህ ብርቱ ጥሪ ነው። በሕዝቅኤል ዘመን የእስራኤል ሕዝብ ንስሓ እንዲገቡ በር ተከፍቶላቸው ነበር። አንድ ሰው በኀጢአቱ ምክንያት ሲሞት እግዚአብሔር ደስ አይሰኝም። ስለዚህ እግዚአብሔር "ወደ እኔ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ!" በማለት ጥሪ ያቀርባል።

10. ለእስራኤል ልዑላን የቀረበ የሐዘን እንጕርጕሮ (19፥1-14)

1-9 በሕዝቅኤል መልእክት ተቀባዮች የቀረበው የመጨረሻ ጥያቄ የሚያተኵረው፣ በጊዜው የነበሩት የይሁዳ መሪዎች ሕዝቡን ወደ ቀደመው ሁኔታ ለመመለስ የሚችሉና የታመኑ በመሆናቸው ላይ ነው። ሕዝቅኤል ለዚህ ምላሽ የሚሰጠው የይሁዳን ልዑላን በተመለከተ የሐዘን እንጕርጕሮ በማቅረብ ነው። በጊዜው የነበሩት መሪዎች ማንም ሰው እምነት የሚጥልባቸው አልነበሩም። በምዕራፍ 18 ላይ የተጠቀሰው ርኩስ ሰው ምሳሌዎች ነበሩ። እነዚህ መሪዎች ይሁዳ ላለችበት ለዚህ ሁኔታ ተጠያቂዎች ነበሩ። ሁሉም ይሞታሉ፤ ምንም ዐይነት እውነተኛ መሪ በይሁዳ አይቀርም።

የሕዝቅኤል ሙሾ በመጀመሪያ ማእከል ያደረገው የእናት አንበሳንና የግልገሎቿን ምሳሌ ነው። አብዛኛውን ጊዜ አንበሳ በምሳሌ ሲቀርብ፣ ንጉሣዊ መንግሥትን የሚያመለክት ነው፤ በተለይም የዳዊትን ሥርወ መንግሥት ይመለከታል (ከዘፍ 49፥9 ጋር ያነጻ)። በዐውዱ መሠረት በዚህ ስፍራ በሴት አንበሳ የተመሰለችው እስራኤል ናት። ግልገሎቿ የተሰጡትን የእስራኤልን ነገሥታት የሚያመለክቱ ሲሆኑ፣ ከታሪካዊና ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ዐውድ አንጻር በኋላ የተነሡትን የይሁዳ መሪዎች የሚወክሉ ናቸው።

የመጀመሪያው ግልገል ከአባቱ ከኢዮስያስ ሞት በኋላ በይሁዳ ሕዝብ በዙፋን ላይ የተቀመጠው ኢዮአካስ ነበር (2ነገ 23፥31)። ኢዮአካስ እንደ ግልገል አንበሳ የሰውን ዘር በመንጠቅና በመብላት እንዲሁም ክፉ ነገርን በእግዚአብሔር ፊት ማድረግ ተማረ (2ነገ 23፥32)። በእርሱ የሦስት ወር ዘመነ መንግሥት በዓለም የታወቀ ዐመፀኛ ነበር፤ በዚህም ሳቢያ ልክ እንደ ታደነ አንበሳ በ609 ዓክክ ተያዘ፤ ታስሮ ወደ ግብፅ ተወሰደ በመጨረሻ በዚያ ሞተ (2ነገ 23፥33-34፤ 2ዜና 36፥1-4፤ ኤር 22፥10-12)።

ሁለተኛው ግልገል የኢዮአቄም ልጅ ዮአኪን ነው (ከ2ነገ 24፥8-17፤ ከ2ዜና 36፥8-10 ጋር ያነጻ)። ኢዮአቄም ራሱ ታልፎአል። የይሁዳ ተስፋ የመነመነው የግብፅ መንግሥት ድጋፍ በነበረው በኢዮአቄም መንግሥት አመራር ነው። አገሪቱ መውደቅ ጀመረች። ተስፋቸው እንደ ገና መለምለም የጀመረው ወጣቱ የዐሥራ ስምንት ዓመት ልዑል ዮአኪን በነገሠ ጊዜ ነበር። ይሁን እንጂ የእርሱም ዘመነ መንግሥት ይህን ያህል ከአባቱ ዘመን የተለየ አልነበረም፤ ዮአኪንም የሰውን ዘር መግደል ተምሮ ነበርና።

ዮአኪን ከተሞችን በመደምሰስ ምድሪቱን ባድማ አደረጋት። አንበሳ ከሚያድኑ አሕዛብ ማምለጥ አልቻለም፤ እነርሱም "መረባቸውን" ዘርግተውበት ወደ ናቡከደነፆር በ597 ዓክክ "ቀፎ ውስጥ ከተው" አመጡት። በኋላ ከእስር ተፈታ (2ነገ 25፥27-30፤ 2ዜና 36፥9-11)፤ ጽምፀም በይሁዳ "ዳግመኛ" አልተሰማም።

10-14 ምሳሌው አሁን ወደ "ወይን ተክል" ተለወጠ። ይህ ምሳሌ አብዛኛውን ጊዜ አሁንም የእስራኤልን ሕዝብ በአጠቃላይ የሚወክል ነው (15፥1-6፤ 17፥1-10 ይመ፤ ከመዝ 80፥8-16፤ ከኢሳ 5፥1-7፤ 27፥2-6 ጋር ያነጻ)። ምሳሌው በሕዝቅኤል ምናልባት እዚህ ላይ የተለወጠው ኢዮአካስና ዮአኪን ሕጋዊ ነገሥታት እንደ ነበሩት ሴዴቅያስ የይሁዳ ሕጋዊ ንጉሥ ባለመሆኑ ሊሆን ይችላል።

የወይን ተክሉ የሚያመለክተው ታሪካዊ የሆነውን የእስራኤልን ሕዝብ ነው። በከነዓን ምድር ብዙ ውሃ ባለበት አጠገብ ተተክሎ ነበር (ዘዳ 8፥7-8)፤ አንድ ወጥ የሆነ መንግሥት በነበረበት ጊዜ አድጎ ብዙ ፍሬ በማፍራት ለበትረ መንግሥት ወይም ለነገሥታት የሚሆኑ አያሌ ቅርንጫፎች ነበሩት። ይሁን እንጂ ይህ የወይን ተክል በመጨረሻ ተነቅሎ ወደ ምድር ተጣለ፤ የተጋለጡት ሥሮቹም በምሥራቅ ነፋስ (ባቢሎን፤ ከ17፥6-10፡15 ጋር ያነጻ) ተመትተው ደረቁ። የወይን ተክሉ ወይም ሕዝቡ ወደ በረሓ ተወሰዶ ተተከለ፤ ማለትም ወደ ምርኮ ተጋዘ። "ከዋና ቅርንጫፎቿ ከአንዱ እሳት ወጣ" የተባለው በጊዜው የነበረው የይሁዳ መሪ ሴዴቅያስ በይሁዳ ላይ ያመጣው ጥፋት ነው። በይሁዳ ላይ ለደረሰው ሁኔታ በከፊል ተጠያቂው ሴዴቅያስ ነው። ሕዝቅኤል ላለፈው የምርኮኞቹ ጥያቄ በሴዴቅያስ መታመን ሞኝነት እንደ ሆነ በመግለጽ መልሶአል፤ ለመጣው ፍርድ ሴዴቅያስ በከፊል ተጠያቂ ነበርና። በርግጥ በይሁዳ በአጠቃላይ "ለበትረ መንግሥት" የሚሆን አንድም ጠንካራ ቅርንጫፍ አልነበረም፤ በ586 ዓክክ ተማርኮ የሚወሰደው ሴዴቅያስ እንኳ አልነበረም። ምንም ተስፋ የለም! ፍርድ እየመጣ ነው!

መ. የእስራኤል አመራር ብቃት ማነስ (20፥1-23፥49)

1. የእስራኤል ዐመፅ ታሪክና የእግዚአብሔር ጸጋ (20፥1-44)

ሀ. በግብፅ ውስጥ የተነሣ ዐመፅ (20፥1-9)

1 የዘመን ቅደም ተከተሉ ማስታወሻ (ሐምሌ/ነሐሴ 591 ዓቅክ) የመጽሐፉን ዐዲስ ክፍል አጀማመርና ዐዲስ ተከታታይ መልእክቶችን የሚያመለክት ነው። ሕዝቅኤል ከእግዚአብሔር የተቀበላቸውን ያለፉትን ራእዮች ከተናገረ ዐሥራ አንድ ወራት ዐለፈ (ከ8፥1 ጋር ያነጻ)። ይሁን እንጂ በዚህ ጊዜ በባቢሎን የነበሩት የአይሁድ መሪዎች በትንቢቶቹ ላይ ለነበራቸው ክርክር ሕዝቅኤል የሰጠውን መልስ ልብ ብለዋል። በግልጽ እንደሚታየው ይሁዳ አሁን ካለችበት ሁኔታ ትድግናን ታገኛለች የሚል አሁንም መጠነኛ የሆነ ተስፋ አላቸው።

ግብፅ በሱዳን ውስጥ ያገኘችው ድል ወራ በቱል አቢብ ትሩፋን ወደ ነበሩት የይሁዳ ሰዎች ደርሶአል። ዳግማዊ ሳሜቲክ ፓለስቲናን ድል አድርጎ እንደሚይዛትም ጭምጭታ ተሰምቶአል። የምርኮኞቹ ተስፋ ምናልባት ይበልጥ ከፍ ያለው ግብፅ ከናቡከደነፆር ነጻ የምታወጣን አዳኛችን ትሆናለች ብለው በማሰባቸው ነው። ሴዴቅያስም እንዲሁ በሞኝነት ይህን ሕልም የተጋራው በባቢሎን አገዛዝ ላይ በማመፅ እምነቱን በግብፅ ብርታት ላይ በ591 ዓቅክ እና በ589 ዓቅክ መካከል ባደረገ ጊዜ ነው። ፈርዖን ወዲያውኑ ታምሞ ስለ ነበር የግብፅም ወታደራዊ ኀይል ይህን ያህል ባልነበረበት በዚያ ጊዜ እንዲህ ዐይነቱን እንቅስቃሴ ለማድረግ ጊዜው አልነበረም።

ከምዕራፍ 20-23 ባሉት የሕዝቅኤል መልእክቶች ውስጥ ላልተነገረው የሽማግሌዎቹ ጥያቄ እግዚአብሔር የሰጠው መልስ ቀርቦአል። እግዚአብሔር እንዲህ ዐይነቱን የሞኝነት ጥያቄ አይሰማም። የእስራኤል ታሪክ በእግዚአብሔር ላይ የተደረገን ያልተቋረጠ ዐመፅ የሚያመለክት ነው። እንዲህ ዐይነት ዐመፅ በእርሱ ላይ ቢያደርጉም እንኳ እግዚአብሔር በብዙ ትዕግሥት ለሕዝቡ የማያልቀውን ጸጋውን ገለጠ። ሕዝቡ ራሱን ለፍርድ የሚያዘጋጅበት ጊዜ መጣ፤ እግዚአብሔር ፈጥኖ ናቡከደነፆርን በኢየሩሳሌም ላይ በማምጣት ከተሞችዋን እንዲያወድምና አያሌ ምርኮኞችን ወደ ባቢሎን እንዲወስድ ያደርገዋልና (20፥45-21፥32)። የይሁዳ ክፋት በተለይም የመሪዎቿ ጽዋ ሞልቶ ነበር (ምዕ 22-23)።

2-6 እግዚአብሔር ለእስራኤል ሽማግሌዎች ጥያቄ በዐጭሩ መልስ ሰጠ፤ ምናልባትም ሴዴቅያስ ወደ ግብፅ ፊቱን በማዞሩ ምክንያት የመጣውን ውጤት በተመለከተ ሊሆን ይችላል፤ (1) ለእንዲህ ዐይነቱ ጥያቄ ምንም መልስ ሊሰጣቸው አልፈለገም፤ (2) መልስ መስጠት ያልፈለገው ከይሁዳ ርኩሰት የተነሣ ነው፤ (3) የይሁዳ ሕዝብ ስለ ፈጸመው በደል ይፈረድበታል። እነዚህ ሐሳቦች በስፋት የሚገልጹት ሕዝቅኤል እስራኤል በእግዚአብሔር ላይ ያመፀችበትን ታሪክ ሲያወሣና እግዚአብሔርም ለዚህ ክፉ ሕዝቡ ያሳየውን የማይነጥፍ ትዕግሥቱንና ጸጋውን ሲገልጥ ነው።

የእስራኤል ታሪክ በሕዝብነት የጀመረው በግብፅ አገር እግዚአብሔር በመረጣት ጊዜ ነበር። ራሱን ለእስራኤል በማሳወቅ፣ አምላክዋ እንደሚሆን ማለላት (ዘዳ 7፥6-11)። ለአብርሃም ቃል ወደ ገባለት፣ ፍሬያማና የከበረ ምድር ወደ ሆነው ስፍራ ሕዝቡን ሊያመጣ መሐላ አደረገ (ዘፍ 12፥7፤ ዘፀ 3፥8፡13-18፤ 6፥1-8፤ ኤር 3፥19፤ ዳን 8፥9፤ 11፥16፡42፡45)። ሕዝቡን ወደ እውንነት ለማምጣት ሦስት ነገሮች አስፈላጊ ነበሩ፤ (1) ሕዝብ (2) መንግሥት እና (3) አገር። የእስራኤል ሕዝብ ወደ መሆን የመጡት በግብፅ ነበር፤ መንግሥትን የተቀበሉት በሲና ተራራ ሲሆን፣ አገራቸውን ርስት አድርገው የያዙት ኢያሱ ከነዓንን ድል ባደረገ ጊዜ ነበር (በ33፥21-48፥35 ላለው መግቢያ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመ)።

7-9 ሕዝቅኤል የያዕቆብ ትውልዶች የተራዘመ የቅጣት ዘመንን በግብፅ ያሳለፉት አስጸያፊ በሆኑት በግብፃውያን ጣዖታት ስለ ረከሱ እንደ ነበር ተናገረ። የእግዚአብሔር ርኅራኄ የሞላበት ፍቅር ለእስራኤል የታየው የተለየ ጥሪና ቃል ስላላት ብቻ ሳይሆን፣ እርሱ ብቻ አምላኳ ይሆን ዘንድ የእርሷን የጣዖት አማልክት ለማስወገድ ከሰጣት ማስጠንቀቂያም አንጻር ነው (ከ23፥3፡8 ጋር ያነጻ)። እግዚአብሔር ሕዝቡ የተሳሳተ የአምልኮ አካሄድን እንዲከተሉ አይፈልግም።

ይሁን እንጂ የእስራኤል ታሪክ በቀጠለ ቍጥር፣ እርሷም የእግዚአብሔርን የምሕረት ማስጠንቀቂያዎች አልፎበቀችም። የግብፅ ጣዖታትን ሳታቋርጥ በማምለክ ይበልጥ በእግዚአብሔር ላይ ዐመፀች። ስለዚህ እግዚአብሔር በግብፅ ለ430 ዓመታት በባርነት በቈየችበት ጊዜ ሁሉ መዓቱን ሊያፈስባት ወሰነ። ነገር ግን የባርነቱ ጊዜ ሲያበቃ፣ እግዚአብሔር በምሕረቱ ሕዝቡን ከግብፅ አወጣ (ከዘፍ 15፥13-16 ጋር ያነጻ)፤ ይህን ያደረገውም ስሙ በአሕዛብ መካከል እንዳይሰደብ ነው። የእግዚአብሔር ስም ማንነቱን ሁሉ ያካተተ ነው። በግብፅ አገር የነበረው ባርነት ችሎታ እንደሌለው ያሳያል ተብሎ እንዲተረጐም አልፈለገም። እስራኤል በአሕዛብ መካከል የእግዚአብሔርን ስም መቀደስ ባትችልም፣ ራሱ እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ በማውጣት ስሙን ያስከብራል። ከዚያም አሕዛብ ሁሉ እርሱ እግዚአብሔር እውነተኛ፤ ታማኝና ኃያል የእስራኤል አምላክ እንደ ሆነ ያውቃሉ (ዘፀ 7፥5፤ መዝ 106፥8-12)።

ለ. በምድረ በዳ የተገለጠ ዐመፅ (20፥10-26)

10-12 ሕዝቅኤል ከእስራኤል የተበላሸ ጅማሬ፣ እግዚአብሔር በታላቅ ኀይሉ ከግብፅ ወዳወጣው ትውልድ ዘወር አለ (ዘፀ 12-15)። የእግዚአብሔር ቸርነትና ጸጋ የተገለጠው ሕዝቡን ከግብፅ በማውጣቱና ኪዳኑን በመስጠቱ ነበር። ይህ ኪዳን አንድ ሰው በላቀ ደረጃ እንዲኖር የሚያስችሉትን ፈሪሀ እግዚአብሔር ያለባቸውን መርሖች ያብራራል። ስለዚህ እስራኤል ሁሉ እነዚህን የሕጉን ትእዛዛት በሙሉ በዕለት ተዕለት ኑሮአቸው ሊጠብቁአቸው ይገባል (ዘሌ 18፥5፤ ዘዳ 10፥12-13)።

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕገ መንግሥት አካሄድ በዓለም ዐቀፋዊ ገናና እና ተገዢ መንግሥት በሁለተኛው ሺህ ዓቅክ በሚደረግ ስምምነት ዐይነት ገለጠው፤ ይኸውም ትልቁ ንጉሥ፣ አነስተኛ ዐቅም ካለው ጋር በረከትና ጥበቃ ለማድረግ ከዚያ ተገዢ ጋር የሚገባው ኪዳን ዐይነት ነው። በበኩሉ ተገዢው ሕዝብ በትልቁ ንጉሥ የሚሰጠውን ሕግ ሁሉ መከተል ይኖርበታል። እግዚአብሔር ታላቁ ንጉሥ ነው፤ እስራኤልም ተገዢው ሆነለች። እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ተገዢነት በማውጣት ቸርነቱን ገልጦላታል። እስራኤል በበኩሏ እግዚአብሔር በሙሴ ኪዳን በሰጣት የጽድቅ ሕግ መሠረት በመኖር ለዓለም የእግዚአብሔር ምስክር መሆን ነበረባት። ትልቁ ንጉሥ በሕጉ ፖሊሲ መካከል ላይ "ማኅተሙን" ወይም ምልክቱን በማስቀመጥ ይህን ኪዳን ያትማል። እግዚአብሔር በሰንበት ምልክት ላይ ራሱን እንደ ፈጣሪ አቅርቦአል (ዘፀ 20፥8-11፤ 31፥13፡17)። ሳምንታዊውን ሰንበት በማክበር እግዚአብሔር በቸርነቱ እስራኤል ለዓለም በረከት እንደ ሆነች ያሳስባታል፤ እንዲሁም ፈጣሪን ከማምለክ ፍጡርን ማምለክን ለተከተሉ ለጣዖት አምላኪዎች ምስክር ትሆናለች (ነህ 9፥14፤ ሮሜ 1፥25)።

13-17 "ሰው ቢጠብቀው በሕይወት የሚኖርበትን" የሚለው ሐረግ (ከዘሌ 18፥5 ጋር ያነጻ) ድነት በሥራ እንደ ሆነ አያመለክትም። የእግዚአብሔርን ሕግ መታዘዝ የሚገልጸው እስራኤል በእግዚአብሔር ላይ ያላትን እምነት ነው፤ አለመታዘዝም የእስራኤልን አለማመን ያሳያል። እግዚአብሔር ከቸርነቱ የተነሣ ቢባርከውም ይህ የእስራኤላውያን ትውልድ የሙሴን ኪዳን ትእዛዛት በመቃወምና ሰንበትን በማርከስ በአምላካቸው በእግዚአብሔር ላይ በምድረ በዳ ዓመፀ (ከዘኍ 11-14 ጋር ያነጻ)። ስለዚህ እግዚአብሔር እስራኤልን ሊያጠፋ ዐስቦ ነበር (ዘኍ 14፥11-12)፤ ይሁን እንጂ አላደረገውም፤ ምክንያቱም እርሱ ሕዝቡን ቢያጠፋ ስሙ በአሕዛብ ፊት ይረክሳል። አሕዛብ እግዚአብሔር አንዱ እስራኤልን ከግብፅ ካወጣ በኋላ በምድረ በዳ ሊጠብቃቸው አልቻለም ብለው ያስባሉ። እግዚአብሔር ያተርፋቸው ዘንድ ሙሴ ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ ማለደ (ዘኍ 14፥13-19፤ ዘዳ 1፥26-40)። በዚያ ፈንታ እግዚአብሔር ያንን ትውልድ ወደ ተስፋዪቱ ምድር እንደማያስገባ ተናገረ፤ በጣዖት አምልኮ ከተሞላው ልባቸው የተነሣ የእርሱን መንገድ ተቃውመዋልና (ከዘኍ 14፥32 ጋር ያነጻ)። እግዚአብሔር በቸርነቱ ሕዝቡን ከጥፋት ያዳነው ከቅዱስ ስሙ የተነሣ ብቻ ነው።

18-26 ዕድሜአቸው ሃያና ከዚያ በታች የሆኑ የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ወደ ከነዓን ምድር የመግባት ተስፋ ነበራቸው። እግዚአብሔር ይህን ዐዲስ ትውልድ የአባቶቹን የጣዖት አምልኮና የዐመፅ መንገድ እንዳይከተል ማስጠንቀቂያ ሰጠው። ይሁን እንጂ በአባቶቻቸው ዘመን እንደ ሆነው በሕጉ መሠረት ባለመኖርና ሰንበትን በማርከስ ይህም ትውልድ በእግዚአብሔር ላይ ዐመፀ። እንደ ገናም እግዚአብሔር ሕዝቡን ሊያጠፋ ዐስቦ ነበር። ይሁን እንጂ እንደ በፊቱ ስሙ በአሕዛብ መካከል እንዳይረክስ የእግዚአብሔር ቅድስና ፍርዱን እንዳያደርግ እጁን ሰበሰበ (ከዘኍ 16፥21-22፤ 25፥1-9 ጋር ያነጻ)። በዚያ ፈንታ እግዚአብሔር ሕዝቡን በአሕዛብ መካከል እንደሚበትን (ዘሌ 26፥33፤ ዘዳ 28፥64፤ መዝ 106፥26-27)፣ ሊኖሩባቸው ለማይችሉባቸው ሥርዐቶች አሳልፎ እንደሚሰጣቸውና መሥዋዕታቸውን እንደሚጸየፍ ማለ። ከዚያም የተተዉ እንደ ሆኑ በማድረግ እግዚአብሔር ብቻ አምላካቸው መሆኑን እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል። እግዚአብሔር እስራኤልን "መልካም ላልሆነ ሥርዐት" አሳልፎ ይሰጣል ማለት እስራኤል ጥፋትንና ሞትን በሚያመጡ የዓለም ሥርዐቶች መሠረት መኖርን ትመርጣለች ማለት ነው። ቊ. 26 ላይ የተገለጠው "መሥዋዕት" የሚያመለክተው ሃይማኖታዊ መሥዋዕቶችን ነው (ከዘፀ 28፥38፤ ከዘሌ 23፥38 ጋር ያነጻ)። በዚህ ስፍራ በግልጽ ልዩ መሥዋዕቶች የተባሉት ለጣዖት አማልክታቸው በእሳት አሳልፈው የሚሰጡት የበኵር ልጅን መሥዋዕት ነው (ዘፀ 13፥12፤ ዘሌ 18፥21፤ ዘዳ 18፥10)። ይህ ልምምድ በተለይ ሞሎክ የተባለው ጣዖት በሚመለክበት ጊዜ የሚደረግ የተለመደ መሥዋዕት ነው (2ነገ 21፥6፤ 2ዜና 28፥3)።

ሐ. ድል ባደረጉና በምድሪቱ በተቀመጡ ጊዜ የተደረገ ዐመፅ (20፥27-29)

27-29 እግዚአብሔር የእስራኤልን የመጀመሪያ ትውልድ ኀጢአት ክሕደትና ታማኝ አለመሆን በሚል ገልጾታል (ዘኍ 15፥30-31)። አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ሲያቃልል ያ ሰው እግዚአብሔር ተሳድቧል ወይም ተጻርፏል ይባላል። እስራኤላውያን ከአባቶቻቸው ስሕተት አልተማሩም። ወደ ከነዓን የገባው የዕብራውያን ትውልድ ያየውን የከነዓናውያን አረማዊ የሃይማኖት ሥርዐት መፈጸም ጀመረ።

መ. በሕዝቅኤል ዘመን የነበረው የይሁዳ ዐመፅ (20፥30-44)

30-31 እግዚአብሔር አሁንም በድንገት የቸርነቱን የአካሄድ ዐይነት እንደሚከተለው ገለጸ፤ የእስራኤል ዐመፅ፣ የእርሱ ፍርድ፣ የጊዜውን ሁኔታ ለመታገሥ የሚገልጠውን ምሕረት። የምርኮኞቹና የይሁዳ ተወካዮች እንደ መሆናቸው መጠን በጊዜው ያሉትን ሽማግሌዎች እግዚአብሔር በሚከተለው ጥያቄ አፋጠጣቸው፤ "አባቶቻችሁ እንዳደረጉት ራሳችሁን ታረክሳላችሁን?" በጊዜው የነበረችው እስራኤል አባቶችዋ እንደ ሆኑት ዐመፀኛ ነበረች። ስለዚህ እግዚአብሔር የሕዝቡ ጥያቄ ወደሆነው የቅርብ ጉዳይ ዘወር አለ። በመንገዶቹ የማይሄዱትን ግን ፈቃድህን ለማወቅ እንፈልጋለን የሚሉትን እንደማይሰማ በአጽንዖት ገለጸ።

32-37 እርሱ ስለሚወዳቸው እስራኤል እንደ ሌሎች ጣዖት አምላኪ አሕዛብ ለመሆን የነበራቸውን ፍላጎት እግዚአብሔር ተቃወመ። ይህን በማድረግም በእስራኤል የወደፊት ታሪክ ውስጥ የፍርድና የጸጋ ዐዳትን አካሄደ። በፍርዱ አሁን በእርሷ ላይ ገዥ እርሱ ነው፤ ይሁን እንጂ ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ይሁዳን መልሶ ያቋቁማታል። ነገር ግን እስራኤላውያን በግብፅ በነበሩበት ወቅት እግዚአብሔር እንዳደረገው ሁሉ እርሱ በእስራኤል ላይ የሚፈርድበትና ወደ "አሕዛብ ምድረ በዳ" የሚያመጣበት የእስራኤል ሁለተኛ መበተን ይኖራል።

ሆኖም የእግዚአብሔር ምሕረት ፍርዱን ተከትሎ ሲመጣ፣ እስራኤልን የተለየ ርስቱ ወዳረገበት ወደ ኪዳኑ በመጨረሻ ያመጣቸዋል። አንድ በግ ከአረኛው በትር ሥር ሲያልፍ፣ ያ በግ የአረኛው መሆኑን ያመለክታል። "አረኛ" የሚለው ቃል ንጉሥ የሚጠራበት ጥንታዊ የሆነ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። በትር ደግሞ ፍርድንና ቅጣትን የሚያመለክት ትርጉም (ፍካሬ) ሊኖረው ይችላል (መዝ 89፥32፤ ሶሔር 3፥1)።

38 ኪዳኑ የተገለጸው እግዚአብሔርን በማወቅ ከሚመነጨው መንጻት አንጻር ነው። ይህ የዐዲሱ ኪዳን የተስፋ ቃል ማእከላዊ ሐሳብ ነው (36፥25-38፤ ኤር 31፥31-34)። በዐዲሱ ኪዳን አማካይነት በመጨረሻ እስራኤል የነጻ መንጋ ይሆናሉ። የማንጻቱ ሂደት ኀጢአተኞችን ከእስራኤል አጥርቶ ያወጣል፤ ስለሆነም እነዚህ ኀጢአተኞች እግዚአብሔር በመጨረሻ ሕዝቡን በምድሪቱ መልሶ ሲያቋቁም ወደ በረከት ምድር ፈጽሞ አይመለሱም (ከዳን 12፥10፤ ከኤር 31፥34 ጋር ያነጻ)።

39-44 የእስራኤል የዐመፅ ታሪክ ዐጭር ገለጻ በሕዝቅኤል ዘመን ለነበሩት መልእክትን በመስጠት ይጠቃለላል። እነርሱ በተደጋጋሚ እርሱን ስላልሰሙት እግዚአብሔር ለጣዖቶቻቸው አሳልፎ ሰጥቶአቸዋል። እግዚአብሔር እንደ ገና በመጨረሻው ጊዜ ለእስራኤል የሚገልጠውን የመጨረሻ ጸጋ በማሳሰብ ያበረታታቸዋል። እስራኤል አንድ ጊዜ በመጨረሻው ፍርድ ከነጻች በኋላ እንደ ገና የእርሱን ቅዱስ ስም በአሕዛብ መካከል እንደማታረክስ እግዚአብሔር ሊያረጋግጥ ይፈልጋል። እግዚአብሔር ይህንን የሚፈጽመው በቅዱሱ ተራራው ላይ ያመልኩት ዘንድ በዚያ ዘመን የነበሩትን እስራኤላውያን ሁሉ መልሶ በማምጣት ነው። በዚያም እነርሱንም ሆነ የሚያቀርቡትን መሥዋዕታዊ አምልኮ ይቀበላል። እስራኤላውያን ስላለፈው ኀጢአታቸው ያዘነና የተዋረደ ልብ ይኖራቸዋል። በሺሁ ዘመን ሁሉ የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ፈሰሰላቸው ያዩ ዘንድ ይመጣሉ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ቅዱስ ስሙ እንዲረክስ አይፈቅድም። እግዚአብሔር ያለማቋረጥ ለእነርሱ ያደርግላቸው የነበረው ከጸጋው የተነሣ እንጂ የሚገባቸው ሆኖ አይደለም።

2. በዘመኑ በነበሩት በይሁዳ መሪዎች ላይ የተገለጠ ፍርድ (20፥45-21፥32)

ሀ. የደቡቡ ደን መቃጠል (20፥45-21፥7)

45-49 የእስራኤልን የዐመፅ ታሪክ ከቃኘ በኋላ በሕዝቅኤልም ዘመን ሕዝቡ ፍርድ የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ፣ እግዚአብሔር በይሁዳ ላይ ሊያመጣ ስላለው ፍርድ ተናገረ፤ የፍርዱንም ዐይነት ገለጸ። በባቢሎን አማካይነት ስለሚመጣው ፍርድ አራት መልእክቶች በዝርዝር ቀርበዋል (ከቊ. 45፤ 21፥1:8:18 ጋር ያነጻ)። የመጀመሪያው መልእክት ተምሳሌቱንና በግልጽ የቀረበውን ትርጉም ይዞአል (21፥1-7)። ተምሳሌቱ በደቡብ ደን ላይ የተነሣውን የደን ቃጠሎ ይገልጻል፤ (የይሁዳ የደብቡ መንግሥት ሲሆን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ደን የለበሰ ክልል ነበር) እሳቱ የለመለመውንና የደረቀውን ዛፍ ሁሉ ምንም ሳያስቀር እንደሚበላ ይገልጻል። ይህን የማይጠፋ እሳት እግዚአብሔር እንደ ለኰሰው ሰው ሁሉ ያያል።

ቊ. 49 የሚያመለክተው በተምሳሌቱና በትርጉሙ መካከል ያለውን ሽግግር ነው። የሕዝቅኤል አድማጮች ተሰላችተዋል። ሕዝቅኤል የቀድሞ ምሳሌ ተናጋሪ አሁንም እንደ ገና ሌላ ምሳሌ ቢናገርም ማንኛቸውም አልተረዱትም። ስለዚህ እግዚአብሔር ራሱ ትርጓሜውን ይሰጣቸዋል።

21፥1-5 የተምሳሌቱ ትርጓሜ በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ በግልጽ ቀርቦአል። ሕዝቅኤል "ፊትህን ወደ ደቡብ አዙር" (20፥46) በሚል ታዞአል፤ ይኸውም ወደ ኢየሩሳሌም፣ ወደ ቤተ መቅደሱና ወደ እስራኤል ምድር ሁሉ ማለትም ወደ ይሁዳ ማለት ነው። በተምሳሌቱ የተጠቀሰው እሳት (20፥47) የፍርድ ሰይፍን የሚያመለክት ሲሆን፣ የናቡከደነጾርንና የሰራዊቱን ሰይፍ ማለት ነው (ከቊ. 18-27 ጋር ያነጻ)። የለመለመውና የደረቀው ዛፍ በትእምርት የሚያመለክቱት ጻድቁንና ክፉውን ነው። የእግዚአብሔር ፍርድ ሁሉንም የሚያጠቃልል ይሆናል። እግዚአብሔር ፍርዱን በኀጢአተኞች ላይ በሚያፈስስበት ጊዜ፣ ጉዳቱ ከሰሜን እስከ ደቡብ ያለውን ምድሪቱን በሙሉ የሚያጠቃልል ይሆናል። እያንዳንዱ ሰው በእግዚአብሔር የቊጣ ሰይፍ ይነካል። ጻድቃንም ሆኑ ክፉዎች ሁለቱም የምድሪቱን ጥፋት ተመክሮአቸው ያደርጋሉ። እያንዳንዱም ሰው ፍርዱን ያመጣው እግዚአብሔር እንደ ሆነ ያውቃል።

6-7 በይሁዳ ላይ የሚመጣው የእግዚአብሔር ፍርድ ጉዳቱ እጅግ አስከፊ ይሆናል። ሕዝቡ ዐቅም ያጣል። ሕዝቅኤል ይህንን የሕዝቡን ጥልቅ ስሜት ለመግለጽ በተሰበረ ልብና

በመረረ ሐዘን በማቃሰት ይገልጻል። በዚህ ማቃሰት ምክንያት ምን እንደ ሆነ ምርኮኞቹ ሲጠይቁት፣ የእግዚአብሔር ፍርድ በሚመጣበት ጊዜ እነርሱ የሚያልፉበትን የጭንቀት ስሜት ለማሳየት የተጠቀመበት ምልክት እንደ ሆነ ያስረዳቸዋል። በዚያ ጊዜ ልባቸው ይቀልጣል፤ መንፈሳቸው ይዝላል፤ እጃቸውና ጕልበታቸው እንደ ውሃ ፈስሶ ይደክማል።

ለ. የሰይፍ ዕርድ (21÷8-17)

8-13 ሕዝቅኤል ስለ ተሳለ፤ ስለ ተወለወለ፣ በመብረቅ ፍጥነት እየተበረቀረቀ ሊያርድ ዝግጁ ስለ ሆነ ሰይፍ ቀረርቶና ሽለላን የመሰለ ዘፈን እንዲዘፍን ታዘዘ። ሰይፉ በዚህ ስፍራ የተገለጸው በዐራጁ እጅ ማለትም በናቡከደነፆር እጅ እንዳለ ነው (ቊ. 18-23)።

ስለዚህ ሕዝቅኤል የባቢሎናውያን የፍርድ ሰይፍ በእግዚአብሔር ሕዝብ በተለይም በመሪዎቿ በይሁዳ ላይ ስለ ሆነ ማልቀስና መጮኽ ነበረበት። ሕዝቅኤል ደረቱን ወይም ጭኑን መምታት ነበረበት፤ ይህም በዚህ ልብን በሚሰብር ፍርድ ስብራት፣ ሐዘንና ጭንቀት የሚገለጽበት አካላዊ ምልክት ነው (ከኤር 31÷19 ጋር ያነጻ)። የይሁዳ ሕዝብ ተፈትኖአል፤ ችግር ያለበት ሆኖም ተገኝቶአል። ሕዝቡ ፈተናውን ማለፍ ስላልቻለ፤ ተገቢው ጥያቄ ይሁዳም ሆነች መሪዋ (ማለትም በትረ መንግሥትዋ ከቊ. 10 ጋር ያነጻ) ወደፊት በሕይወት መኖር ስለ መቻላቸው ወይም አለመቻላቸው ነው። የእግዚአብሔር ፍርድ የመጨረሻ ይሆን?

ይሁዳና ምርኮኞቹ በይሁዳ ነገድ በኩል የመሲሑ ዘር መንግሥትን ይይዛል በሚል የተሰፋ ቃል አሁን ተስፋ በማድረግ ይደሰቱ ነበር። በዘፍ 49÷10 "ልጁ" እና "በትረ መንግሥት" የሚሉት የተሰፋ ቃሉን ለመግለጽ አገልግሎት ላይ ውለዋል። የዘፍ 49÷9-10 መሲሓዊ ጕልሕ ሐሳብና በ2ሳሙ 7 ላይ የተሰጠው የዳዊት ኪዳን የተስፋ ቃል ሁለቱም ለይሁዳ ተስፋ ታሳቅ መሠረት ናቸው። ሕዝቡ የእግዚአብሔር መሲሓዊ ተስፋ (ማለትም የልጁ በትረ መንግሥት) የሚለው እነርሱን እንደ ሕዝብ ለዘላለም እንደሚጠብቃቸው በጣም ርግጠኞች ነበሩ። የሕዝቅኤልን የፍርድ ዐዋጅ መፍራት አላስፈለጋቸውም። ነገር ግን በዳዊት ኪዳንና (2ሳሙ 7÷14) በሙሴ ሕግ በሚገኘው የእርግማን ፍርድ ውስጥ (ዘዳ 28-29) ማለትም በሁለቱም ያለውን የቅጣት ትእዛዝ ፈጽሞ ረስተዋል።

በጊዜው ላለው ይሁዳ በዘፍ 49 (ከቊ. 27 ጋር ያነጻ) ላይ ባለው የተስፋ ቃል መሠረት በቅርብ የሚፈጸም ተስፋ የለም፤ ያጠራቸው ዘንድ እግዚአብሔር በይሁዳና በጊዜው መሪ ላይ ፍትሕን ለመስጠት፣ ታማኝ ነውና። ነገር ግን የመጨረሻው 'የይሁዳ በትረ መንግሥት'፣ መሲሑ ፈጽሞ አይጠፋም (ከቊ. 13 ጋር ያነጻ)። በቅርቡ በሚፈጸምባት ፍርድ መካከል ይሁዳ የሚኖራት ተስፋ ይኸው ብቻ ነው። በመጨረሻ ይሁዳ ስትጠራ፣ በትረ መንግሥትዋ ማለትም መሲሑ ሕዝቡን ይገዛል (ከቊ. 27 ጋር ያነጻ)።

14-17 ሕዝቅኤል የእግዚአብሔር ፍርድ ተገቢ መሆኑን እጁን በማጨብጨብ ቢያረጋግጥም፣ የእግዚአብሔር መዓት ባመጣው ውርደትና ንቀት በማዘንና በመቈጨት ነው። በዚህ ድርጊት ሕዝቅኤል በይሁዳ ኀጢአት ላይ እግዚአብሔር ያለውን የፍትሕ አስተሳሰብ አጉልቶ አሳየ፤ የሰይፉንም የላቀ ውጤታማነት አበረታታ። የፍርዱን ብርታት ለመግለጽ ሁለት ሦስት ጊዜ ደጋግሞ በመምታት አሳይቶአል፤ ከተለመደው በላይ ሦስት ዕጥፍ ውጤታማ ሆነ። ሰይፉ ሕዝቡን በሙሉ የሚያጠቃልል ነው፤ የብዙዎቹ ልብ ቀለጠ፤ ብዙዎቹም በመብረቅ ፍጥነት በመጣው ወረራ በየበሮቻቸው ወደቁ። በመጨረሻም ሰይፉ በእግዚአብሔር እጅ ላይ እንዳለ ዐይነት ሆነ። ፍርዱ ሁሉን ሰው የሚያጠቃልል ነበር።

ቀረርቶው ወይም ቅኔው ከፍተኛው ደረጃ ላይ ደረሰ። የሰይፉ ጥፋት አገሪቱን በአጠቃላይ ከቀኝ (ወይም ደቡብ) ወደ ግራ (ወይም ሰሜን) ያለውን ሁሉ አዳረሰ። እዚህ ላይ ያለው የቃሉ አገላለጽ የሰይፉን ስለት ወደ ፊትና ወደ ኋላ በማመልከት ከሰሜን እስከ ደቡብ ድረስ ያለውን ግዛት በአጠቃላይ የነካውን የፍርድ ሰይፍ ለመግለጽ የገባ አባባል ነው። እግዚአብሔር የፍርዱን ማረጋገጫ የሰጠው በእጅ ጭብጨባ ነው። ነገር ግን ፍርዱ በሚፈጸምበት ጊዜ መዓቱ እንደሚቆምም ተናግሮአል።

ሐ. በባቢሎን አማካይነት የሚመጣው አይቀሬ ፍርድ (21÷18-27)

18-21 ትንቢታዊው "የሰይፍ ቀረርቶ" አሁን በትእምርታዊ ድርጊት ጕልበት አግኝቶአል፤ ተጠናክሮአልም። ሕዝቅኤል አሁን ከባቢሎን ወደ ከነዓን አቅጣጫ የሚያመራ መንገድ የተግለበትን ካርታ ምናልባት በዐፈር ወይም በሸክላ ላይ ሠራ። መንገዱ የሚገነጠልበት ቦታ ላይ ምልክት ሠራ፤ አንዱ የምልክት አቅጣጫ ወደ አሞናውያን ከተማ ወደ ራባት- አሞን ሲሆን፣ ሌላው የምልክት አቅጣጫ ወደ ኢየሩሳሌም የሚወርድ ነበር። የተለመደው የመንገድ መገንጠያ ደማስቆ ነበረች። የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር የትኛውን ከተማ አስቀድሞ መውረር እንዳለበት ለማወቅ ማንኛውንም ዐይነት የጥንቈላና የሚርት ዘዴ እየተጠቀመ በመንገዱ መገንጠያ ላይ ቆሞ ይታያል። ያለጥርጥር በ589 ዓክክ ይሁዳና አሞን በባቢሎን ላይ ያደረጉት የተባበረ ሤራ ለባቢሎናውያን ሰራዊት መምጣት ምክንያት ሳይሆን አይቀርም።

የሰው ወይም የቦታ ስሞች የተጻፉባቸውን ቀስቶች በመወዝወዝ ዕጣ መጣል የተለመደ ድርጊት ነበረ። እያንዳንዱ ቀስት ስም ይጻፍበታል፤ ቀስቶቹ በአፎት ውስጥ ይቀመጣሉ፤ አፎቱ ይወዘወዛል፤ ሲወዘወዝ ቀድሞ የሚወድቀው ቀስት የአማልክቱ ውሳኔ እንደ ሆነ ይታመናል። የቤት የጣዖት ምስሎች ከዘር ውርስ ጋር በቅርበት የተገናኙ ናቸው፤ ምናልባትም ምሪት ይሰጣሉ ተብለው ስለሚገመቱ እነርሱም ለምሪት እንደ አማልክት ምክር ሳይጠየቁ አልቀረም። ጉበት የሕይወት ወይም የነፍስ መቀመጫ ሆኖ የሚታሰብ ሲሆን ከተመረመረ በኋላ በሚታየው ቀለሙ ወይም ምልክቱ አማካይነት ምሪቱ ይወሰናል። ናቡከደነፆር ሦስቱን የጥንቈላ መንገዶች ተጠቅሞ ያገኘው ውጤት ተመሳሳይ ሆነ። እግዚአብሔር በምንም ዐይነት መንገድ ጥንቈላን ባያበረታታም ሉዓላዊ አምላክ እንደ መሆኑ ሁሉንም ነገር ይቈጣጠራል። ፈቃዱን ሊፈጽም እነዚህን የጥንቈላ ልምምዶች ተቈጣጥሮአል (ከኤር 27÷6 ጋር ያነጻ)።

22-23 ተመሳሳይ ሆኖ የተገኘው የጥንቈላው ውሳኔ ወደ ኢየሩሳሌም የሚወስደውን መንገድ መከተልና ከተማዪቱንም መክበብ ነበር (ከ4÷2 ጋር ያነጻ)። የይሁዳ ነዋሪዎች ምላሻቸው ያለማመን ነበር። ይህ ጥንቈላ ሐሰት እንደ ሆነ በማሰብ ከናቡከደነፆር ጋር በገቡት ኪዳናዊ ስምምነት ላይ ወይም ከእግዚአብሔር ጋር በገቡት በሙሴ ኪዳን ላይ ታመኑ። "ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን ለገቡት" የሚለው ሐረግ ከባቢሎን ጋር የገቡትን የስምምነት መሐላ የሚያመለክት ነው፤ በዐውዱ መሠረት ስምምነቱን ያደረጉት ሁለቱ ወገኖች ባቢሎንና ይሁዳ ናቸው። ይሁዳ ባፈረሰችው በዚህ ውል ላይ መሠረት የሌለው እምነት አሳደረች። ይህ ምንም ዐይነት ዋስትና ሊሆን አልቻለም። በሌላ በኩል ናቡከደነፆር የእግዚአብሔር ፍርድ መሣሪያ ሆኖ አገሪቱን ሲደመስስ ይሁዳን ስለ በደሏ እንድትጸጸት ያደርጋታል ማለት ነው።

24-27 ይህ መልእክት የተጠቃለለው በሕጋዊ ፍርድ ነበር። የይሁዳ ኀጢአት ስለ ተጋለጠ ኢየሩሳሌም ትያዛለች፤ ሴዴቅያስ የተባለው የይሁዳ ክፉ መሰፍንም በዚህ የመጨረሻው የቅጣት ጊዜ ፍጻሜው ይሆናል (በ586 ዓክክ)። የክህነትና የንጉሥነት አገልግሎት ከይሁዳ መወገዱን ለመግለጽ በሊቀ ካህናቱ የራስ ጥምጥም መውለቅና (ዘፀ 28÷4: 37:39፤ 29÷6 ወዘተ) በዘውድ መጣል በምሳሌነት ቀርቦአል። "የሚገባው ባለ መብት እስከሚመጣ ድረስ" እነዚህ ዳግም አይለበሱም፤ ይህም በዘፍ 49÷10 ላይ ያለውን የንጉሥ - ካህን መሲሕ (ከዕብ 5-7 ጋር ያነጻ) ግልጽ አመልካች ነው። ሕዝቅኤል ይህን መሲሓዊ ድምፀት ያለውን መልእክት ሲናገር ያ ንጉሣዊ አገልግሎት (እና ክህነት) በፍርድ ጊዜ እንደሚወገድ፣ ነገር ግን በዘፍ 49÷10 መሠረት በመጨረሻ በመሲሑ መምጣት እንደሚመለስ በማመልከት ነው። የእግዚአብሔር ፍርድ ፍጹም ከመሆኑ የተነሣ በማኅበራዊ ጕዳይ ረገድ ሁሉም ነገር የተገለባበጠ ይሆናል። "ባድማ" የሚለው ቃል ሦስት ጊዜ በተደጋጋሚ መቅረቡ የእግዚአብሔርን ፍርድና በባቢሎናውያን የሚፈጽመውን ማፈራረስ በአጽንዖት ለመግለጽ ነው።

መ. በአሞን ላይ ሊፈጸም የነበረው ፍርድ መተላለፉ (21፥28-32)

28-32 በመንገድ መገንጠያ ላይ ናቡከደነፆር ሊዔድበት የሚገባው ሌላው መንገድ ወደ አሞን የሚወስደው መንገድ ነው (ከቍ. 20 ጋር ያነጻ)። ይሁዳ በባቢሎናውያን ፊት በመውደቋ አሞን የሚሳደብና የሚሣለቅ ቢሆንም፣ ሕዝቅኤል ተመሳሳይ የሆነ ሙሾ ለአሞንም ያወርዳል። አሞናውያን ባዶ ራእይንና የሐሰት ሟርትን ተመልክተዋል፡ ይህም በይሁዳ ላይ እንዲወድቁ የሚያደርጋቸው ነበር፤ ይሁን እንጂ ስለ በደላቸው በሚቀጡበት ቀን ቀናቸው በደረሰ፣ "መታረድ በሚገባቸው ክፉዎች ዐንገት ላይ" ይሆናል።

አሞን ለይሁዳ ጦር በመጥራት ይሁዳን ብታሸብርም፣ እግዚአብሔር ግን በእርስዋ ላይ የተመዘዘው ሰይፍ ወደ ሰገባው እንዲመለስ አደረገ። ለምን ይህ እንደ ሆነ አናውቅም። እግዚአብሔር አሞናውያንን በገዛ ምድራቸው በሰይፍ እንዲያልቁ ይፈርድባቸዋል፤ በቍጣው እሳት ጥፋትን በላያቸው ላይ ያፈስስባቸዋል፤ በጥፋት ለሠለጠኑ ሰዎች አሳልፎ በመስጠትም እንዲቦጫጭቁአቸው ያደርጋል። ባቢሎን አስቀድማ ኢየሩሳሌምን መውጋት ስለ መረጠች በአሞን ላይ የተነገረው ይህ ፍርድ አልተረሳም። በባቢሎን፣ በኩል በቅርብ ቀን ከሚፈጸመው ፍርድ ጋር የተዛመደ ቢመስልም ይህ ፍርድ መቼ እንደሚፈጸም በርግጥ አይታወቅም። አሞን ከእንግዲህ የምትታወስ አትሆንም!

3. የፍርዱ ምክንያት፣ የይሁዳ ጣዖት አምላኪ መሪዎች (22፥1-31)

ሀ. የሙሴን ሕግ ሆነ ብሎ ያለመታዘዝ ሁኔታ (22፥1-16)

1-2 የእስራኤል የነጢአት ታሪክ ቅጣትን የሚያስከትል ቢሆንም፣ ቅጣቱን ያነሣሣው በዘመኑ የነበረችው እስራኤልና የመሪዎቿ አስጸያፊ ርኩሰት ነበር። ሕዝቡ ይህን እውነት መረዳት ሳይችሉ በመቅረታቸው፣ ይህንን እንደ ገና ግልጽ ለማድረግ ሦስት የፍርድ መልእክቶችን እንዲያስተላልፍ እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን አዘዘው። የመጀመሪያው መልእክት በዝርዝር ያቀረበው ሕዝቡ በዋና ከተማዪቱ በኢየሩሳሌም በመሪዎቿ አማካይነት የሙሴን ሕግ የተላለፉበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው። ሁለተኛው በአጽንዖት የሚናገረው የተቀጣጠለው የእግዚአብሔር ፍርድ የሕዝቡን ርኩሰት እንደሚያጋልጥ ነው። ሦስተኛው መልእክት በትኩረት የሚያሳየው ማንኛውም የይሁዳ ነብረተ ሰብ በተለይም የአመራር አካሏ የእግዚአብሔርን መንገዶች ለመከተል አለመቻሉን ነው።

ሕዝቅኤል በዚህ ስፍራ እንደ ዐቃቤ ሕግ በመሆን "ደም በምታፈሰስው በዚች ከተማ ላይ አትፈርድባትምን?" በማለት ለሚፈረድባት ፍርድ ምክንያት የሆናትን ነጢአቷን በሙሉ እንድታስተውል ያደርጋል። የኢየሩሳሌም ዋና ባሕርይ ሆኖ የተገኘው ላጠፋችው ሕይወት ጸጸት ሳይሰማት መቅረቷ ነበር። ይህ ጠማማነት የመጣውም የእግዚአብሔርን ሕግ ካለመታዘዝዋ የተነሣ ነበር።

3-5 ክሱ የተመሠረተው በሁለት ተከፍሎ ነበር፡- የኢየሩሳሌም የጥፋት ርኩሰት (ቍ. 3-5) እና የይሁዳ መሪዎች የጥፋት ርኩሰት (ቍ. 6-12)። ኢየሩሳሌም ነፍስ ግድያን በተለያየ መንገድ ፈጽማለች፤ እነዚህ ደግሞ በዝርዝር የተገለጹት በመሪዎቹ ርኩሰት ገለጻ ላይ ነው (ቍ. 6-12፤ ከ18፥15-17 ጋር ያነጻ)። ነገር ግን የዚህ ደም መፍሰስ ዋና ምክንያት በከተማዪቱ ውስጥ የነበረው ጣዖት አምልኮ ነው። ከነበራት መለኮታዊ ጥሪ በተቃራኒ ነዋሪዎቿ ከተማዪቱን በጣዖታት ሞሉ፤ ይህም በበኩሉ አረከሳት (ዘፀ 20፥3-7)። የጣዖት አምልኮ ሃይማኖታዊ ሥርዐት ሰውን መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብንና ክፉ መንገዶችን ስለማያውቅ፣ የጣዖት አምልኮ ተጽዕኖ የእግዚአብሔር ፍርድ ፈጥኖ እንዲመጣ የሚያደርግን፣ ልዩነት የሌለበትን ነፍስ ግድያን አበረታታ። ኢየሩሳሌም በአካባቢው ላሉ አገሮች መሣለቂያ ትሆናለች። እነርሱም በእርሷ ላይ በደረሰው አሳዛኝ ሁኔታና ወራዳ ነገር ይሥቃሉ።

6 የኢየሩሳሌም ነጢአት ዋና ምክንያት ክፉ መሪዎቿ ሲሆኑ፣ በተለይም በቅርብ የነበሩት ነገሥታት (ምናሴና ኢዮአቄም) እንዲሁም መስፍኗ (ሴዴቅያስ) ናቸው። እያንዳንዱ መሪ ሥልጣኑን አላግባብ በመጠቀም ደም አፍስሶአል (ከ2ነገ 21፥16፤ 24፥4 ጋር ያነጻ) እያንዳንዱ ሥልጣኑ እስከ ፈቀደለት ድረስ ተጉዞአል። እያንዳንዱም በሙሴ ሕግ ላይ በግልጽ የተከለከለውን ሁሉ ጥሶአል (ዘፀ 20፥13)።

7-12 መሪዎቹ የወላጆችን ተገቢ ስፍራና ሥልጣን ግምት አልሰጡትም፤ ስለሆነም የቤተ ሰብን ሕይወት አጠፉ (ከዘፀ 20፥12፤ ከዘሌ 19፥3 ጋር ያነጻ)። በማኅበራዊ ኑሮ ረገድ እነዚህ መሪዎች ረዳት የሌላቸውን ሰዎች በዘበዙ (ከዘፀ 22፥21-24፤ 23፥9፤ ከዘሌ 19፥33፤ ከዘዳ 24፥17 ጋር ያነጻ)። መሪዎቹ ለሚመሩት ሕዝብ ያሳዩት የነበረ ግዴለሽነት ለእግዚአብሔር ቅዱስ ነገሮች ያሳዩት ከነበረ ግዴለሽነት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው። ሰንበትን ናቁ፤ ብሎም የሙሴን ኪዳንና ታላቁን አምላካቸውን ካዱ (ከዘፀ 20፥8፤ ከዘሌ 19፥3 ጋር ያነጻ)።

በተቃራኒው መሪዎቹ አረማውያን በሆኑ የሃይማኖት ሥርዐቶች ውስጥ ገቡ (ከዘዳ 12፥1-2፤ 16፥21-22 ጋር ያነጻ)። "ወሬ የሚያቀብሉ" የተባሉ ሰዎች ወሬ እንዲያመጡላቸው በማድረግ እነዚህ መሪዎች የታቀዱ የግድያ ተግባራትን ፈጸሙ (ከዘሌ 19፥16፤ ከ1ነገ 21፤ ከኤር 6፥28፤ 9፥3 ጋር ያነጻ)። እነዚሁ መሪዎች በወሲባዊ ኀጢአት ውስጥ ተዘፈቁ (ከዘሌ 18፥6-23፤ 20፥10-21 ጋር ያነጻ)። አላገባብ ጥቅምን በማሳደድ ራሳቸውን አበለጸጉ (ከዘፀ 23፥8፤ ከዘዳ 24፥6፡ 10-12፤ 23፥19-20፤ 27፥25 ጋር ያነጻ)። ነገር ግን ዋናው ምክንያት "እኔንም ረስተሻል፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር" የሚለው ነው።

13-16 ሕዝቅኤል ይህን የፍርድ ንግግር የሚያጠቃልለው ኢየሩሳሌም ያለ አግባብ ባገኘችው ጥቅምና በውስጧም ባፈሰሰችው ደም እግዚአብሔር በንቀት በሚሰጣት ፍርድ ነው። እግዚአብሔር እጁን የሚያጨበጭበው ንቀት በተሞላበት ሁኔታ ነው። ከዚህም በላይ ኢየሩሳሌም በፍርድ ጊዜ መቆም መቻል አለመቻሏን ሳይቀር ጠየቀ። ልቧና እጆቿ የእግዚአብሔርን ቅጣት መቋቋም ይችሉ ይሆን? ፍርዱ ሦስት ዕጥፍ ይሆናል፤ ይኸውም በአሕዛብ መካከል መበተን፣ የኢየሩሳሌምን ርኩሰት ማንጻትና በባቢሎናውያን አማካይነት በአሕዛብ ፊት የኢየሩሳሌም መዋረድ ነው። ይሁን እንጂ በፍርድ ሂደት ውስጥ የእግዚአብሔር ዋና ዐላማ ሕዝቡ እርሱ ብቻ ጌታ እውነተኛ አምላክ እንደ ሆነ ያውቁ ዘንድ ነው።

ለ. የፍርድ የማጥራት ኀይል (22፥17-22)

17-22 ምስያ ብረትን የማቅለጥ ሂደት በዚህ በሁለተኛው የፍርድ ንግግር ላይ ማእከላዊ ስፍራን ይዞ ይገኛል። እስራኤል ቀደም ብሎ ከነበረ ብረትን የማቅለጥ ሂደት የተነሣ ዋጋ የሌለው ጉድፍ ሆናለች። አሁንም እንደ ገና በኢየሩሳሌም የእሳት ማንደጃ በእግዚአብሔር ቍጣ እሳት ነድዳ ትቀልጣለች። ይህ የእግዚአብሔር የቍጣ እሳት በቁመ. የሚፈጸመው ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምን በማቃጠል ሲደመስሷትና ሲዘርፏት በሚፈጸመው ሁኔታ ነው። በዚህ አስፈሪ መከራ ውስጥ እግዚአብሔር እርሱ ራሱና ትክክለኛው ፍርዱ እንዲታወቅ ፈልጎአል።

ሐ. ጻድቃን መሪዎች አለመገኘታቸው (22፥23-31)

23-29 የይሁዳ ምድር ያልነጻች ከመሆኗ የተነሣ በፍርድ ቀን ("በቍጣ ቀን" "ዝናብ" አታገኝም። የይሁዳ ሕዝብ ያልጠራ ሕዝብ ነበር፤ ዋናው ምክንያትም ሕዝቡ በተለይም መሪ ሆነው ለበረከት የተሾሙት ኀላፊነታቸውን ሳይወጡ ቀርተዋል። "መሳፍንቷ" (ነቢያት፣ የዐመት ማስታወሻ ይመ) በግላቸው ለመበልጸግ ከመፈለጋቸው የተነሣ በሕዝቡ ላይ አሚረዋል። ሕዝቡንም ወደማይሆን ሁኔታ (በጦርነት፣ በዐመፅ ወዘተ) በመምራት ለብዙዎች እልቂት ምክንያት ሆኑ፣ በምድሪቱም የመበለቦቶች ቍጥር እንዲበዛ አደረጉ። እነዚህ መሪዎች ሰዎችን እንደሚቦጫጭቅ አንበሳ ቦጫጭቀው በሉ።

"ካህኗቷ" የእግዚአብሔርን ቅዱስ ሕግ በመበከል በኪዳኑ ላይ ዐመፁ። በቅዱሱና በረከሰው ወይም ንጹሕ በሆነውና ባልሆነው መካከል ያለውን ልዩነት ለማሳየት ወይም

ለማስተማር አልቻሉም። ሰንበትን ከማክበር ዘወር በማለት በጣዖት አምልኮ ሃይማኖታዊ ሥርዐታቸው እግዚአብሔርን አረከሱ።



የምድሪቱ የፖለቲካ ባለሥልጣኖች (“መኳንንት”) የግል ጥቅማቸውን ለማካበት ግዳይ እንደሚቦጫጭቅ ተኩላ ሕዝቡን ለማጥፋት ዐመፅ ፈጸሙ። በሐሰት ራእያቸውና በውሸት ሟርቶቻቸው ነቢያት የራሳቸውን የረከሰ ፍላጎት ለማሟላት ሲሉ ይህን ሁሉ ድርጊት ልክ አስመስለው አቀረቡ፤ ከእግዚአብሔር ሥልጣን እንዳላቸው በማስመሰልም ሕዝቡን ወደ ስሕተት መሩ።


በመጨረሻም ሕዝቡ ይህን የተበላሸ አመራር በመከተላቸውና እርስ በርሳቸውም ስለ ተጨካከኑ እግዚአብሔር አውግዞአቸዋል። በመካከላቸውም ቅሚያና ዝርፊያ በመፈጸም፣ ፍትሕንም በማጉደል ድኻውን፣ ችግረኛውንና መጻተኛውን መጨቈን በብዛት ታይቶባቸዋል። እያንዳንዱም ሰው ለራሱ የመሰለውን ለራሱ ጥቅም ሲል ማንኛውንም ነገር ያደርግ ነበር (ከመሳ 21፥25 ጋር ያነጻ)።

30-31 በመንፈሳዊ መሪነትና በምልጃ ከሚመጣው ፍርድ ለሕዝቡ በመከላከል የሚቆም አንድ ሰው እግዚአብሔር ፈልጎ ማግኘት አልቻለም ነበር። በራሱ ዘመን ሙሴ ለሕዝቡ ለመማለድ፣ እንደ መሪም የእግዚአብሔርን መንገድ ለሕዝቡ ለማስተማር ሕጉ በተጣሰ ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ነበር። ነገር ግን አሁን ፊት ለፊት የሚቆም፣ ይሁዳንም በሙሴ ሕግ በተጻፈው ትእዛዝ መሠረት ወደ ንስሓና ወደ እግዚአብሔር መንገድ የሚመራ ሰው እግዚአብሔር ሊያገኝ አልቻለም። ስለ ሕዝቡ የሚማልድ አንድም መሪ አልነበረም። ሁሉም ብልሹዎች ነበሩ! ስለዚህ እግዚአብሔር ይህን የመጨረሻ መልእክት በፍርድ ቃል ደምድሞታል። ሕዝቡን በቀጣው እሳት ያጠፋቸዋል። ለሚመጣው ፍርድ ሁሉም በጎላፊነት ይጠየቃሉ!

4. የእስራኤልን ፖሊቲካዊ ምንዝርና በተመለከተ የቀረበ ዐጭር ምስያ (23፥1-49)

ሀ. የእስራኤልን አሳፋሪ የወጣትነት ዘመን (23፥1-4)

1-4 ሕዝቅኤል ንግግሩን የሚያጠቃልለው የእስራኤልን የመሪነት ድክመት በማሳየት ነው። ይኸውም የእስራኤል ብልሹ መሪዎች ሕዝቡን ወደ ምን ዐይነት ፖለቲካዊ ምንዝርና እንደ መሩት የሚያሳይ ዐጠር ያለ ምስያ በማቅረብ ነው። ምስያውን በአጠቃላይ አያሌ ልዩ ልዩ ንግግሮችን የያዘ ነው። ሰማርያንና ኢየሩሳሌምን በተመለከተ አንድ የተወሰነ ንግር ከማስተላለፉ በፊት ሕዝቅኤል በዐጭሩ የእነዚህን ሁለት እኅት-ማማቾች የቤተ ሰብ መነሻ ታሪክ ይናገራል። እነዚህም “ከአንድ እናት የተወለዱ ሁለት ሴቶች ልጆች ነበሩ።” ይህም ከግብፅ ጀምሮ እስከ ሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ድረስ ያለውን የአንድን ሕዝብ የአንድነት መንግሥት በትኩረት የሚያሳይ ነው። ሁለቱም በወጣትነታቸው ዘመን በግብፅ በነበሩበት ጊዜ የዝሙት ዐዳሪነትን ሥራ ጀመሩት (ከ16፥26፤ 20፥7-8፤ ከዘኍ 25፥3-9 ጋር ያነጻ)። እግዚአብሔር የርኩሰትንና የኀጢአትን አስጸያፊነትና ክፋት በግልጽ፣ በትክክልም በዝርዝር ይናገራል እንጂ በመሸፋፈን ፈጽሞ አይከላከልም።



የብረት ዐፈር ከምድር ተቈፍሮ ከወጣ በኋላ በብረት ማቅለጫ ብረቱ ቀልጦ እንዲወጣ እሳት ይለቀቅበታል። በስተ ግራ ያለው ሥዕል ብረት አቅላጭ ቲምና በተባለችው የፍልስጥኤም ከተማ የሚሠራውን ሥራ ያሳያል። እላይ ያለው ፎቶግራፍ በቦታው ላይ ጥንታዊው የብረት ማቅለጥ ሥራ እንዴት እንደ ነበረ ለጐብኚዎች ለማስረዳት የተዘጋጀ ሥዕል ነው።

የሁለቱ እኅት-ማማቾች ስም ተጠቅሶአል። ታላቂቷ ሰማርያ ስትሆን፣ ታላቅ የተባለችበትም ምክንያት ከሌሎች አሕዛብ ጋር የርኩሰት ግንኙነትን በመጀመሪያ በማድረጓና በቅድሚያ ቅጣቷን በመቀበሏ ነው። ሰማርያም “ኦሖላ” ተብላ ተጠርታለች፤ ትርጓሜውም “የእርስዋ ድንኳን” ማለት ነው። የአረማውያንን የጣዖት አምልኮ መቅደስ ድንኳኖችን የመትከል ዝንባሌ ከማሳየቷ በቀር የዚህ ስያሜ አስፈላጊነት በግልጽ የሚታወቅ አይደለም። ታናሽ የሆነችው ኢየሩሳሌም “ኦሖሊባ” ተብላ ተጠርታለች፤ ትርጓሜውም “ድንኳኔ በእርስዋ ውስጥ ነው” ማለት ነው። ምናልባት ይህ ስም በኢየሩሳሌም ከተማ ውስጥ ያደረውን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ (“ድንኳን” ወይም “ማደሪያ”) የሚያመለክት ሊሆን ይችላል (ከ2ሳሙ 6፥17፤ ከ1ነገ 8፥4 ወዘተ ጋር ያነጻ)። ሁለቱም ከተሞች በተለይም የእርሱ ሕዝቦች በመሆን የእግዚአብሔር ርስቶች ናቸው። የዚህ ርስት ትርጓሜ “ጋብቻን” ወይም “ወላጅነትን” የሚመለከት ስለ መሆኑ በክፍሉ ውስጥ በግልጽ አልተመለከተም። ሁለቱም ከተሞች ልጆችን ወልደዋል። እነዚህ ልጆች ነዋሪዎቻቸው ወይም ትናንሽ ከተሞቻቸው ሳይሆኑ አይቀሩም።

ለ. የሰማርያ ዝሙት ዐዳሪነት (23፥5-10)

5-8 በአሕዛብ ብርታት በመታመኗ፣ የእነርሱን ጥገኝነትም በመፈለጓ፣ ለእግዚአብሔርም ታማኝ ባለመሆኗ በመጀመሪያ የተገሠጻችው ታላቂቱ ናት። የሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት ዋና ከተማ የሆነችው ሰማርያ ስትሆን፣ “በዝሙት” ለ“አሦራውያን ሁሉ አሳልፋ ሰጠች”። እርሷም የአሦርን ገዢዎች፣ መኳንንትና የጦር አዛዦች በማባበል ከእርሷ ጋር ግንኙነት እንዲያደርጉ ለመነች፤ እነርሱም በፈቃደኛነት ከእርሷ ጋር ግንኙነት መሠረቱ (ከ2ነገ 15፥19-20፤ 17፥3-4 ወዘተ ጋር ያነጻ)። እስራኤል ለአሦር ተገዢ የሆነችው በፖለቲካ ግንኙነት ረገድ ብቻ ሳይሆን፣ ራሷን በማርከስ የአሦርን ጣዖታትና አማልክትንም በመከተል ረገድ ነው። ይህ መንፈሳዊና ፖለቲካዊ ምንዝርና የአገሪቱ ባሕርይ የሆነው እስራኤል በግብፅ ከነበረችበት ጊዜ ጀምሮ ነው። በወጣትነቷ የተማረችው፣ እጅግ ከባድ የሆነ ባሕርይን ስለ ፈጠረ፣ እያደር ፈጽሞ ሊስተካከል ከማይችል ደረጃ ላይ ደረሰ።

9-10 ስለዚህ እግዚአብሔር የፍርድ ውሳኔውን ሰጠ። ሰማርያን ለወዳጆቿ ለአሦራውያን አሳልፎ ይሰጣታል፤ እነርሱም

ነዋሪዎቿን ማርከው በመውሰድ ወይም በሰይፍ በመግደል ምድሪቱን ዕርቃኗን ያስቀራሉ። ይህ የተፈጸመው በ722 ዓቅክ ሲሆን፣ ለእስራኤል የነጢአት ምንዝርና ምክንያት የሆነችው አሦር፣ በእስራኤል ላይ ለመጣው ፍርድ መሣሪያ በሆነችበት ጊዜ ነበር። የሰማርያ ምንዝርና እጅግ የከፋ ከመሆኑ የተነሣ ስሟም የባለጌ ሴት መተረቻ ስም ሆኖ ቀረ።

ሐ. የኢየሩሳሌም ዝሙት ዐዳሪነት (23፥11-35)

11-21 እግዚአብሔር በሰማርያ ታናሽ እኅት በኢየሩሳሌም ላይ ግሣጹውን ለመሰንዘር ዘወር አለ። ኢየሩሳሌም የደቡብ መንግሥት የይሁዳ ዋና ከተማ ብትሆንም፤ እንዲሁም የሰማርያ ምንዝርና በ722 ዓቅክ በአሦራውያን እጅ እንድትወድቅ እንዳደረጋት ብታይም፣ ሰማርያ ካጋጠማት ነገር ምንም ዐይነት ትምህርት ልትወስድ አልቻለችም። ከዚያ ይልቅ ኢየሩሳሌም ከሰማርያ ይበልጥ በከፋና በተበላሸ ምንዝርና ውስጥ ተዘፍቃ ተገኘች። ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር አገልጋይ ሆና ለአሕዛብ ድነትን በማምጣት ተልእኮዋን ከመወጣት ይልቅ፣ ልክ እንደ ዝሙት ዐዳሪ አሕዛብን ለራስዋ ጥቅም በብልኀት ተጠቀመችባቸው።

ልክ እንደ ሰማርያ የኢየሩሳሌም የመጀመሪያ ዋና "ውሽማ" አሦር ነበረች (ከቊ 5፤ ከ2ነገ 16፥8፤ ከኢሳ 7፥7-9 ጋር ያነጻ)። ከዚያም ይሁዳ ዝሙት ዐዳሪነትዋን ወደ ባቢሎን አስፋፋች። የባቢሎናውያንን ምስል በቅጥር ላይ በማየት ለባቢሎናውያን ገዢዎች ከልክ ያለፈ ፍቅር ነበራት (ከኤር 22፥21 ጋር ያነጻ)። ምናልባት ይህ አንዳንድ የይሁዳ መልእክተኞች ወደ ባቢሎን ሄደው በቅጥሮቿ ላይ የተመለከረውን የታላቅ ኀይሏን ሥዕል በመመልከት የሰጡት ግንዛቤ ሊሆን ይችላል። ይሁዳም መልእክተኞችን ወደ ባቢሎን በመስደድ ከእርሷ ጋር ግንኙነት እንድታደርግ አግባብታለች፤ ባቢሎንም ይህንኑ ዐይነት ግንኙነት ከኢየሩሳሌም ጋር ግንኙነት በማድረግ ስምምነቷን ገልጻለች (ከ2ነገ 23፥32:37 ጋር ያነጻ)። ይሁዳ በእንዲህ ዐይነቱ የፖለቲካ ግንኙነት ረክሰች። በእግዚአብሔር ፍጹም ጥበቃ ከመታመን ይልቅ በዓለም መንግሥታት ተማመነች። ይሁን እንጂ ኢየሩሳሌም ስሕተቷን በከፈል የተረዳችው የባቢሎን ተገዢ ከሆነች በኋላ ነው። ከተዋረደች በኋላ ባቢሎናውያንን ጠላች። ነገር ግን ጊዜው ዐለፈ! እግዚአብሔርም በኢየሩሳሌም እንዳፈረባት ተናገረ፤ ይህም እውን የሆነው በ586 ዓቅክ በናቡከደነፆር እጅ ከወደቀች በኋላ ነው።

ኢየሩሳሌም ትምህርት እንዳልተማረች ሁሉ ከባቢሎን ዘወር በማለት ከግብፅ ርዳታን ለማግኘት ፊቷን አዞረች (ከኤር 2፥18፤ 6፥8፤ 37፥5-7፤ ከሰቈ 1፥17 ጋር ያነጻ)። ፍጹም ጥበቃ የሚገኘው ከእግዚአብሔር ብቻ መሆኑን አሁንም ኢየሩሳሌም አልተማረችም። ግብፅ ከይሁዳ ጋር "ግንኙነት" ለማድረግ በእጅጉ ትፈልግ ነበር፤ ፈርዖኖች በእስያ ውስጥ ጣልቃ ለመግባት እያቀዱ ነበርና። በግብፅ በኩል ያለው እንዲህ ዐይነቱ ፍላጎት በአሀዮችና በፈረሶች የዝሙት ፍላጎት ተገልጾአል፤ በኢየሩሳሌም በኩል ያለው ሴሰኛነት ደግሞ ከግብፅ ጋር በነበራት የወጣትነት ዘመን የምንዝርና ትዝታ እንደ ሆነ ተገልጾአል።

22-27 ኢየሩሳሌምን ከአሕዛብ ጋር ከልክ በላይ በምትፈጽመው ዝሙት እግዚአብሔር ከገሠጻት በኋላ በአራት ዐጫጭር ንግግሮች የፍርድ ውሳኔውን ሰጥቶአል። የመጀመሪያው ንግግር አድንዖት የሚያደርገው በእርሷ ላይ ፍርድን ለመፈጸም "ውሽሞቿን" (የኢየሩሳሌምን) እንደሚጠቀም ነው። በዚያ ጊዜ ኢየሩሳሌም የጠላቾቹ ባቢሎናውያን በእግዚአብሔር ተልከው በወታደራዊ ኀይል በኢየሩሳሌም ላይ በፍርድ ይወጣሉ። ባቢሎን በሥልጣኗ ሥር ያሉትን አገሮች ሁሉ በማስተባበር እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም ላይ ያለውን ቅንዓት በማነሣሣት በጥላቻ በኢየሩሳሌም ላይ ትዘምታለች።

"ከለዳውያን" የሚለው ቃል ቀደም ብሎ ሲያመለክት የነበረው ከፋርስ ባሕረ ሰላጤ በስተ ሰሜን አቅራቢያ የሚኖረውን ሕዝብ ነበረ። ይሁን እንጂ ቃሉ ከዐዲሱ የባቢሎን መንግሥት እያደገ መምጣት ጋር በአጠቃላዩ በባቢሎን መንግሥት ሥልጣን ሥር የሚኖረውን ሕዝብ ሁሉ የሚያመለክት ሆነ።

ለኢየሩሳሌም የተሰጠው ፍርድ በጥንቱ የቅርብ ምሥራቅ ለአንድ አመንዝራ በሚሰጠው የፍርድ አገላለጽ ተጠቅሶ እናገኛለን፤ ይኸውም "አፍንጫሽንና ጆሮሽን ይቈርጣሉ" የሚለው አገላለጽ ነው። ይህም በይሁዳ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወደ ባቢሎን መማረክና መጋዝ በትእምርት ተገልጸአል (ከ2ነገ 24፥10-16፤ 25፥11፤ ከዳን 1፥1 ጋር ያነጻ)። የቀረው የኢየሩሳሌም ነዋሪ በሰይፍና በእሳት ይሞታል (ከ2ነገ 25፥18-21 ጋር ያነጻ)። ባቢሎን የኢየሩሳሌምን ልብሶች ሁሉ በመግፈፍ እንደ ሴተኛ ዐዳሪ ታዋርዳታለች። የኢየሩሳሌም ልብሶች ምርጥ የሆኑ ጌጣ ጌጦቿ ሲሆኑ፣ በአብዛኛው ሀብቷንና ንብረቷን ሳያመለክት አይቀርም (ከቊ 46 ጋር ያነጻ)። ባቢሎናውያን በጭካኔ በኢየሩሳሌም ላይ የሚያካሂዱት ፍርድና ምርኮ ኢየሩሳሌም ከግብፅ ጋር ለምታደርገው ዘማዊ ግንኙነት ማብቃት መንገድ ይሆናል። ይሁዳ ግብፅን ትረሳለች፤ ከእርሷም እንደ ገና ርዳታ የምትፈልግ አትሆንም። ይህ ሁኔታ በ586 ዓቅክ ከሆነው ከባቢሎናውያን ምርኮ በኋላ እንደ ጸና ቀርቶአል።

28-31 ባቢሎን በኢየሩሳሌም ላይ የምትፈጽመው ፍርድ የኢየሩሳሌም የከፋ ዘማዊ መንገድ የቱን ያህል ከባድ እንደ ነበረ ለማሳየት በአሕዛብ ሁሉ ፊት ይገለጣል። የኢየሩሳሌም ባድማነት ይሁዳ እንዲህ ዐይነቱን ቅጣት ለመቀበል የሚያበቃ ሁኔታ እንደ ነበራት አሕዛብ ሁሉ እንዲያስተውሉት ያደርጋል። ኢየሩሳሌም ለደኅንነቷ በእግዚአብሔር ከመታመንና በመንገዶቹ ለእርሱ ታማኝ ሆና ከመኖር ይልቅ ከአሕዛብና ከአማልክታቸው ጋር ፖለቲካዊና መንፈሳዊ ምንዝርናን ፈጸመች (ከዘፀ 20፥1-7፤ ከዘዳ 17፥14-20 ጋር ያነጻ)። ኢየሩሳሌም የሰማርያን ምሳሌነት በመከተል በእርሷ የምንዝርና መንገድ በመሄድ በመጸናቷ ሰማርያ የተቀበለችውን የቅጣት ጽዋ የምትካፈል ትሆናለች።

32-34 ጽዋ የሚለው ቃል አብዛኛውን ጊዜ በነቢያት አገልግሎት ላይ የዋለው የእግዚአብሔርን ቊጣ ለመግለጽ ነበር። ይህ "የጽዋ ቅኔ" ልክ እንደ "ሰይፉ ቅኔ" (21፥8-17) ትኩረት የሚያደርገው በፍርድ ዋና ሐሳብ ላይ ነው። የኢየሩሳሌም የፍርድ ጽዋ ስድብንና ነቀፌታን ያካትታል። በስካርና በሐዘን ትሞላለች፤ በሽብርና በመፈራረስም ትፈጸማለች። ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔርን ፍርድ ሙሉ በሙሉ አንጠፍጥፋና የሸክላውን ጽዋ ጨልጣ ጠጥታ እስክትሰባብረው ድረስ ትጠጣዋለች፤ በከፍተኛ ሐዘኗ ጡቶቿን ትቈራርጣለች። የቅጣቷ አስፈሪነትም እጅግ የሚሰቀጥጥ ነው።

35 የእነዚህ የአራቱ የፍርድ ንግሮች የመጨረሻ መልእክት ምናልባት ከሁሉም ይልቅ ዋናው ፍሬ ሐሳብ ያለበት ሳይሆን አይቀርም። በኢየሩሳሌም ላይ በመምጣት ላይ ያለው ፍርድ ዋና ምክንያት እርሷ እግዚአብሔርን መርሳቷ ነበር። ሕዝብ (ወይም ግለሰብ) እግዚአብሔርን ወደ ኋላ ገሸሽ ሲያደርግ፤ ወደ ተጣመመና ወደ ውርደት መንገድ ከመግባት በቀር ሊከተለው የሚገባ ሌላ መንገድ አይኖርም።

መ. በዝሙት ዐዳሪነት ላይ የተሰጠ ፍርድ (23፥36-49)

36-39 ቀጥሎ ባሉት መልእክቶች ሁለቱ ከተሞች ለየብቻቸው የሚታዩ ቢሆኑም፣ አሁን ሁለቱ እኅትማማቾች በአንድ ላይ ቀርበዋል። ሕዝቅኤል በሁለቱም ሴቶች ላይ እንዲፈርድ ማለትም ፍርድ ፊት እንዲያቆማቸውና አስጸያፊ ተግባራቸውን እንዲያጋልጥ ተበረታትቶአል። እግዚአብሔርን ከማምለክ ይልቅ ጣዖታትን በማምለክ መንፈሳዊ ምንዝርናን ፈጽመዋል (ከዘፀ 22፥20፤ 23፥13፤ ከዘዳ 4፥15-24፤ 12፥24-32 ጋር ያነጻ)። የዚህ አምልኮ አንዱ ክፍል ሕፃናትን መሥዋዕት ማድረግን ማለትም ለእሳት አሳልፎ በመስጠት መግደልን ይጨምራል (ከዘፀ 20፥13፤ ከዘሌ 18፥21፤ 20፥1-5 ጋር ያነጻ)። የጣዖት አምልኮና ሕፃናትን ለእሳት አሳልፎ መስጠት በአንድነት በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ በመደረጋቸው መቅደሱ ረክሶ ነበር (ከዘፀ 20፥24-26 ጋር ያነጻ)። እነዚህ እጅግ የከፉ ኀጢአቶች የሚደረጉት በሰንበት ነበር፤ ስለሆነም ሰንበትን ያቀለሉ ናቸው (ከዘፀ 20፥8-11፤ ከዘሌ 19፥3:30 ጋር ያነጻ)። በተጨማሪም ነቢያት ሁለቱ መንግሥታት በተከፈሉበት ዘመን አብዛኛውን ጊዜ ሰንበት ተረስቶ እንደ ነበር ተናግረዋል።

ሰማርያም እንዲሁ መቅደሱን በማርከሷ ተወግዛለች። ምናልባት መቅደሱን ያረከሰችው በተገቢው የአምልኮ ጊዜ የሚጠበቅባትን ነገር ተገንታ ባለማድረጓና የአሕዛብን የጣዖት አምልኮ ቤተ መቅደሶች ለራሷ ስለ ገነባች ሊሆን ይችላል።

40-42 እነዚህ ሁለት “ከተሞች” የተወገዙት የዋስትና ትብብር ለማድረግ ሲሉ ከባዕዳን ሕዝቦች ጋር ግንኙነትን በመሻት ስላሳዩት የአመንዝራ ፖለቲካዊ ፍላጎት ነበር (ከዘዳ 17፥14-20 ጋር ያነጻ)። ሁለቱ ከተሞች ባዕዳን አገሮችን ያታለሉት አንዲት ሴተኛ ዐዳሪ በጌጣጌጥና በልብሶች ውሽሞችዋን እንደምታታልል የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ዕጣንና ዘይት ለእነርሱ በማቅረብም ጭምር ነበር። ማናቸውም ዐይነት ባለጌ ሰዎች ለዚህ የዝሙት ፍላጎት መልስ ሰጥተዋል፤ የበረሓ ሰካራሞች እንኳ ሳይቀሩ ማለትም ይህ መግለጫ የሚመለከታቸው ዐረባውያን፣ ሞዓባውያን፣ ኤዶማውያን ወይም ሳባውያን መጥተዋል። እነዚህ የይሁዳ ውሽሞች የአመንዝራን ዋጋ ማለትም አንባር፣ አክሊል ወዘተ ሰጥተዋል።

43-47 የእግዚአብሔር ፍርድ “በአመንዝራነት ሰውነቷ ስላለቀው” በሚል ሐረግ ተጠቃልሎአል። ኢየሩሳሌምና ወይም ሰማርያ በዚህ አባባል መገለጻቸው እጅግ የሚያሳዝን ነው። ኢየሩሳሌምና ሰማርያ ለዚህ “ግንኙነት” የሳቧቸው አገሮች አሁን በእነዚህ ከተሞች ላይ ይፈርዳሉ። በዐውዱ መሠረት በኢየሩሳሌምና በሰማርያ ላይ የሚፈርዱ አገሮች (አሦርና ባቢሎን መሆናቸው ነው) “ጻድቃን ” ተብለው ተጠርተዋል። ይኸውም በሰማርያና በኢየሩሳሌም ላይ ሲፈርዱ በጽድቅ ይፈርዳሉ ማለት ነው (በኢሳ 41 ከተጠቀሰው ከቂሮስ ጋር ያነጻ)።

በሙሴ ሕግ መሠረት አመንዝራና ነፍስ ገዳይ ሊቀበሉት የሚገባ ፍርድ በሰማርያና በኢየሩሌም ላይ አሦርና ባቢሎን ይፈርዳሉ፤ ይኸውም አብዛኛውን ጊዜ በድንጋይ ተወግሮ መሞት ነው (ከዘፀ 21፥2፤ ከዘሌ 20፥10፤ ከዘዳ 22፥22 ጋር ያነጻ)። “እጎተማማኞች” ይወረወራሉ፤ ይዘረፋሉ፤ በድንጋይ ይወገራሉ፤ እንዲሁም በሰይፍ ይቈራረጣሉ፤ ልጆቻቸው ይገደላሉ፤ ቤቶቻቸውም ይቃጠላሉ።

48-49 በዚህ ፍርድ ውስጥ የእግዚአብሔር ዐላማ በአራት አኳያ ተገልጸአል፤ (1) እንዲህ ዐይነቱ ቅጣት በተሰፋዱቱ ምድር ያለውን ክፋት እንዲያበቃ ያደርጋል፤ (2) ይህ ፍርድ እንዲህ ዐይነቱን የረከሰን ነገር መከተል የሚያስከትለውን ፍሬቢስነት ሌሎች አገሮች (“ሴቶች”) እንዲማሩበት ያደርጋል፤ (3) ይሁን እንጂ እነዚህ ከተሞችና የየግላቸው አገሮች በዚህ ጣዖት አምልኮ ለፈጸሙት ኀጢአት ይህ ቅጣት እንዲፈጸምባቸው አስፈላጊ ነበር፤ (4) እስራኤልንና ይሁዳን እርሱን ወደ ማወቅ ወደ ትክክለኛውና ወደ ተገቢው መንገድ ለመምራት እግዚአብሔር ይህን ቅጣት መፈጸም ነበረበት።

ሠ. በኢየሩሌም ላይ የተፈጸመው ፍርድ (24፥1-27)

እስከዚህ ድረስ ሕዝቅኤል በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚመጣ በተለያየ መንገድ ተናግሮአል። አይቀሬ በሆነው ፍርድ ላይ ለቀረበው ለእያንዳንዱ ክርክር በሥርዐት መልስ ሰጥቶአል። ያ ቅጣት ከመፈጸሙ በቀር የቀረ ነገር አልነበረም (ምዕ 24)። ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምን መክበብ መጀመራቸው በዝርዝር ተገልጸአል። ከዚያም ይሁዳ በተፈረደበት ጊዜ ባዋረዷትና ባላገጡባት አሕዛብ ላይ ሕዝቅኤል ትንቢት ይናገራል (25፥1-33፥20)። እነዚህ ባዕዳን ሕዝቦች በይሁዳ ላይ ስለ ገለጡት ክፉ አስተሳሰብና ድርጊት ይፈረድባቸዋል። ይሁን እንጂ ይሁዳ ወደፊት መልሳ እንደምትቋቋምና እንደምትባረክ ተስፋ ተሰጥቶታል።

1. የድስቱ ምሳሌ (24፥1-14)

1-2 ቀኑ ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን መክበብ የጀመረበት ቀን ነው፤ ይኸውም ታኅሣሥ ጥር 589/588 ዓ.ክ.ነበር። በመለኮታዊው መገለጥ የተናገረው ትንቢት ፍጻሜ መጀመሩን አስተውሏል፤ ይህም አስቀድሞ የመጨረሻዎቹን ዝርዝር ትንቢቶች በተናገረ ሁለት ዓመት ከዐምስት ወር ነው (ከ20፥1 ጋር ያነጻ)። ይህ የጊዜ መግለጫ የተመለከተው ዮአኪን ተማርኮ የሄደበትን ዓመት መሠረት በማድረግ ነው፤ ይህም ሴዴቅያስ የገዛበትን ዓመት መሠረት ካደረገው ከ2ነገ 25፥1 እና ከኤር 39፥1፤ 52፥4 ተመሳሳይ መግለጫ ጋር የተዛመደ ነው። ሴዴቅያስ የነገሠበት ዓመትና ዮአኪን ተማርኮ የሄደበት ዓመት ተመሳሳዮች ነበሩ።

ሕዝቅኤል ይህን ቀን ለይቶ በመመዝገብ በቋሚነት እንዲያስታውሰው እግዚአብሔር አዘዘው። ይህም ምርኮኞቹ በመካከላቸው ነቢይ እንደ ነበረ እንዲያውቁ የትንቢቱን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ነው። ይህ ቀን የሚታሰብ ቀን ሆኖ በእስራኤል ታሪክ በየዓመቱ በጾም ይታወሳል (ከዘካ 8፥19 ጋር ያነጻ)።

ከምዕራፍ 24-25 ያለው ክፍል በ24፥1 ላይ በተሰጠው ቀን ሦስት መልእክቶችን የያዘ ነው። የመጀመሪዎቹ ሁለቱ (በምዕራፍ 24 ውስጥ ያሉት) የኢየሩሳሌምን ከበባ ጅማሬ የሚያሳዩ ናቸው። ከቍ 3-4 ያለው ክፍል የከበባውን ሁኔታ በምሳሌ በማሳየት ትርጉሙን ይገልጣል። የእግዚአብሔር ፍርድ ባሕርያት እንደ ገና ታድሰው ቀርበዋል። ሁለተኛው መልእክት በአጽንዖት የሚያሳየው ምርኮኞቹና የይሁዳ ሰዎች ለከበባው የሚሰጡትን ምላሽ ነው (ቍ 15-27)። ሕዝቅኤል ከሚስቱ ሞት በኋላ ስሜቱን እንዲገዛ ትእዛዝ ተሰጥቶታል፤ ይህም ኢየሩሳሌም ከወደመች በኋላ ሕዝቡ ማልቀስ እንደሌለባቸው ለማሳየት ነው። ያም ሆነ ይህ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ በተከታታይ በማርከሳቸው ጽኑ ፍርድ እንደሚመጣባቸው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸው ነበር፤ የመጣውም እንደ ድንገት አልነበረም። በመጨረሻም ሕዝቅኤል የይሁዳ ጐረቤቶች የሚያደርሱባት ሰድብም በቸልታ እንደማይታለፍ ሕዝቅኤል ተናግሮአል። እግዚአብሔር በእነዚህ አሕዛብ ላይና በራሷም በይሁዳ ላይ የሚያመጣው ፍርድ ፍጹም ፍርድ መሆኑ ለይሁዳ ተነግሮአታል።

3-8 በማብሰያው ድስት ተምሳሌት ሕዝቅኤል የተናገረው ለ“ዐመፀኛ ቤት” ለእስራኤል ሕዝብ ነበር። ለተምሳሌቱ ትርጓሜ መፍቻ ሐሳብ የተሰጠው “የባቢሎን ንጉሥ ኢየሩሳሌምን በዚህ ቀን ከቦአታልና” (ቍ 2) በሚለው ጥቅስ ነው። እንግዲህ ተምሳሌቱ የተሰጠው ከዚህ የኢየሩሳሌም ከበባ አንጻር ነው።

ሕዝቅኤል እንደ ገና በዚህ ስፍራ መልእክቱን “በማብሰያው ብረት ድስት ዝማሬ” በትኩረት ገለጠ (ከ21፥8-17፤ 23፥32-34 ጋር ያነጻ)። ተምሳሌቱ የሚገልጸው አንድ ብረት ድስት በሚንቀለቀል ዐጥንት ላይ መጣዱን ነው። ውሃ ብረት ድስቱ ላይ ተጨመረ፤ ከዚያም ምርጥ የሆነ ሙዳ ሥጋ በደንብ ተቀቀለ።

ሁለት ትርጓሜን የሚያመለክቱ ንግግሮች ከተምሳሌቱ በኋላ ቀጥለው ቀርበዋል፤ እያንዳንዱም ንግግር ተምሳሌቱን በመፍታትና በማብራራት ፍርዱን ያስተጋባል። የመጀመሪያው የፍርድ ንግግር (ቍ 6-8) ብረት ድስቱ ማን እንደ ሆነ በመግለጥ ኢየሩሳሌም አሁን ለሚደርስባት ፍርድ ምክንያቱ ምን እንደ ሆነ አጥብቆ ይናገራል። “ድስቱ” የሚወክለው ኢየሩሳሌምን ሲሆን፣ ከተማዪቱም “ደም ያፈሰሰችው ከተማ ተብላለች። ምርጥ ሥጋ የተባሉት ማለትም የምርጥ መንጋው አካላት እንደዚህኛው በሌላ ስፍራ በግልጽ አልተጠቀሱም። ዐወዱ የከበባውን ፍርድ በመግለጹ ድስቱ ኢየሩሳሌምን የሚያመለክት ቢሆንም፤ መንጋ የሚለው ቃል በሕዝቅኤል በሌላ ስፍራም በመጠቀሱ ሙሉ በሙሉ የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው (ከምዕ 34 ጋር ያነጻ)። ስለሆነም ሙዳ ሙዳ ሥጋ በሚል የተገለጡት በናቡከደነፆር ከበባ የፍርድ እሳት የሚቀቀሉት የኢየሩሳሌም ኗሪዎች ናቸው። ተምሳሌቱ የኢየሩሳሌምን ከበባ የሚገልጸው በእግዚአብሔር ቍጣ ድስት ውስጥ ሕዝቧ የሚቀቀልበትን ሁኔታ በማሳየት ነው።

ይህ የመጀመሪያውን ትርጓሜ የሚያመለክት ንግግር በድስቱ ላይ የተጋገረውን ዝገት በማሳየት ዐዲስ ትርጓሜን ይጨምራል። ቍ 7 እና 8 የሚያመለክቱት እነዚህ “ዝገቶች” “የደም አፍሳሿን ከተማ” ከፍተኛ ደምን የማፍሰስ ሁኔታ ነው፤ ይህ ደምን የማፍሰስ ሁኔታም በዐፈር ያልተሸፈነን በገላጣ ዐለት ላይ የፈሰሰን ደም የሚያመለክት ነው። ኢየሩሳሌም በሙሴ ሕግ መሠረት (ዘሌ 17፥13) የሚገባውን ማለትም የፈሰሰውን ደም ለመሸፈን (ለማስተሰረይ) ያደረገችው ምንም አልነበረም። ያልተሸፈነ ወይም ስርየት ያልተደረገለት ደም የእግዚአብሔርን ቍጣ ያነሣሣል (ከዘፍ 4፥10፤ ከኢሳ 26፥21 ጋር ያነጻ)። የኢየሩሳሌምን ደም በገላጣ ዐለት ላይ ማፍሰሱን እግዚአብሔር ይናገራል፤ ቍጣው በእርሷ ላይ ይፈስ ዘንድም ደሟ እንዲሸፈን አይፈቅድም።

ሌላው ዐዲስ ገጽታ ሥጋው ከተቀቀለ በኋላ ያለምንም አድልዎ ሁሉም ከድስቱ ተገልብጦ መጣሉን ነው። “የመለያ ዕጣው” ሐሳብ፣ “ዕጣ” በማንም ሰው ወይም ሥጋ ላይ እንደማይጣልና እያንዳንዱም ያለምንም ምርጫ ለምርኮ ዐልፎ እንደሚጣል የሚያሳይ ነው። ከሰው አመለካከት አንጻር እንዲህ ዐይነቱ ነገር ጊዜያዊና እንደ አጋጣሚ የሚሆን ቢመስልም፣ እግዚአብሔር ግን በሉዓላዊነቱ የሚያደርገውን ሁሉ ይቈጣጠራል።

9-14 ሁለተኛው የፍርድ ንግግር በመቀጠል ኢየሩሳሌም በፍርድ እንደምትጠራ በአጽንዖት በመናገር ትርጕሙን በስፋት ይገልጣል። እጅግ ብርቱ ከሆነው ከእሳቱ ኀይል የተነሣ፣ ሥጋው የሚቀቀለው ዐጥንቶቹ እስኪቀሩና እስኪያርሩ ድረስ ነው። እሳቱ በኀይል የመንደዱ ሁኔታ ሲፈጸም ማለትም ከበባው ሲጠቃለል ግፉ እንዲወገድ ያደርጋል፤ ማለትም ሕዝቡ ወደ ምርኮ ይጋዛል፤ ከዚያም በእሳቱ ላይ የተጣደው ባዶው ድስት እስኪሞቅና እስኪግል ድረስ በእሳቱ ላይ ይተዋል፤ የዝገቱም ክምር ማለትም እጅግ የከፋው ደም መፋሰስ እንዲቀልጥና በእሳቱ እንዲበላ ይተዋል። እግዚአብሔር ቅድስቲቷን ከተማውን ማለትም ኢየሩሳሌምን ያነጻል። ቀደም ባለው ጊዜ አንጽቷታል (በ605 ዓቅክ እና በ597 ዓቅክ ላይ በተፈጸመው ምርኮ)፤ ይሁን እንጂ ሙሉ በሙሉ አልነጻችም ነበር። እጅግ የከፋ በሆነው ደም ማፋሰስ ደግሞ ጕድፋና ዝጋ ነበር። ነገር ግን የእግዚአብሔር የፍርድ እሳት አሁን ፍጹም የሆነን ሥራ ያከናውናል፤ ስለዚህም ኢየሩሳሌም ትነጻለች፤ ይሁን እንጂ ይህ ሙሉ በሙሉ የሚፈጸመው እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም ላይ የጠራውን ፍርድ እስከሚያቆምበት ጊዜ ነው። የሕዝቅኤል ትንቢት ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚነት የሚያገኘው፣ በእስራኤል ላይ የተጠራው ቊጣ የሚያቆመውና እርሷም ሙሉ በሙሉ የነጻች የምትሆነው በመጨረሻው ዘመን እግዚአብሔር እስራኤልን በከነዓን ምድር መልሶ የማቋቋም ሥራውን ሲጀምር ነው (ከ36፥22-23 ጋር ያነጻ)።

ይህ መልእክት በርግጥ የሚፈጸም መልእክት ነው። እግዚአብሔር ተናግሮአል፤ እርሱም የተናገረውን ይፈጽማል። እርሱ ጻድቅ ስለ ሆነ፣ የጽድቅ ፍርዱን ሳያሳይ አይቀርም። በርኅራኄ ማንንም አያስተርፍም ወይም ስለ ማንም አያዝንም፤ ኢየሩሳሌም ስለ ሠራችው ክፉ ሥራ የሚገባትን መቀበል ይኖርባታልና።

2. ለምርኮኞቹ የተሰጡ ምልክቶች (24፥15-27)

ሀ. የሕዝቅኤል ሚስት መሞት (24፥15-24)

15-17 እግዚአብሔር በዐጭር ጊዜ ሚስቱን “በአንድ ሞት” እንደሚነጥቀው ለሕዝቅኤል አሳውቆታል፤ “በአንድ ሞት” የሚለው ሐረግ መቅሠፍትን ወይም በሽታን የሚያመለክት ነው (ከዘፀ 9፥14 ጋር ያነጻ)። ይህ አስቀድሞ የተነገረው የሕዝቅኤል ሚስት ሞት “የዐይንህ ማረፊያ” በሚለው ሐረግ በአጽንዖት ተገልጦአል።

በጥንታዊው ቅርብ ምሥራቅ የቀብር ሥርዐት፣ ሐዘንተኛው ሰው በአብዛኛው ልብሱን በመቅደድና ማቅ በመልበስ ሐዘኑን ይገልጻል (2ሳሙ 3፥31)። ጫማውንም ያወልቃል፤ ጥምጥሙንም ከራሱ ያወርዳል (2ሳሙ 15፥30፤ ሚክ 1፥8)፤ ጠጉሩን በመላጨትም ትቢያ በራሱ ላይ ይነሰንሳል (1ሳሙ 4፥12)። ከጢሙ በታች ያለውን የፊቱን ክፍል በሆነ መሸፈኛ ይሸፍነዋል (2ሳሙ 15፥30፤ 19፥4)። ሐዘንተኛው በራሱ ወይም በመላ ሰውነቱ ትቢያ ላይ ይንከባለልና እዚያው ይተኛል ወይም በዐመድ ክምር መካከል ይቀመጣል (ኢሳ 58፥5፤ ሚክ 1፥10)። ቀኑን ሙሉ ይጸማል (2ሳሙ 1፥12፤ 3፥35)፤ ከዚያ በኋላም ወዳጆቹ የዕዝን እንጀራ ያመጡለታል (ኤር 16፥7)። የቀብር ልቅሶ በቤተ ሰብ፣ በዘመዶችና በቅጥረኛ አስለቃሾች ይፈጸማል (2ሳሙ 1፥17፣ 11፥26፤ ሚክ 1፥8)።

በቊ 16ለ - 17 እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን በሚስቱ ሞት ምክንያት የተለመደውን የልቅሶ ሥርዐት እንዳያካሂድ አዞታል። እንዲያውም ለማልቀስም ሆነ እንባውን እንኳ ለማፍሰስ አልተፈቀደለትም። የተፈቀደለት ድምፁን ዝቅ አድርጎ እንዲያንራጉር ብቻ ነበር። በተለይም ሕዝቅኤል በነበረበት ዘመን እንዲህ ዐይነቱ የሐዘን መግለጫ የተለመደ አልነበረም። ካህናት ከቤተ ሰባቸው አንዱ ቢሞት እንዲያለቅሱ ይፈቀድላቸዋል (ዘሌ 21፥1-3)፤ ለሕዝቅኤል ግን ይህ መብት አልተሰጠውም ነበር።

18-19 ሕዝቅኤል ይህን መልእክት ለሕዝቡ የተናገረው ምናልባት በማለዳ ሳይሆን አይቀርም፤ ምሽቱ ላይ ሚስቱ ሞተች። በሕይወቱ ከፈጸማቸው እጅግ ከባድ ነገሮች ይህ ያለ ጥርጥር አንዱ ቢሆንም፣ ሕዝቅኤል የሚስቱን ሞት በተመለከተ በታማኝነት በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሠረት ተቀበለ። ይህን ከባድ ትእዛዝ ሊፈጽም የቻለው እግዚአብሔር በሰጠው ብርታት ብቻ ነበር። ሞትን በተመለከተ እርሱ የሰጠው ያልተለመደ ምላሽ በፍጥነት የሕዝቡን ሐሳብ ማረከለት፤ ሕዝቡም ይህን ያደረገው ለምን እንደ ሆነ ወዲያውኑ ጠየቁት። የሕዝቅኤል ሙሉ ሕይወት ለምርኮኞቹ ምስክር ነበር።

20-24 የምርኮኞቹ የዐይናቸው “ደስታ” ኢየሩሳሌም ባለው ቤተ መቅደስ (ከቊ 25 ጋር ያነጻ) ላይ በትምክሕት (ጊዜና 36፥19፤ ሰቈ 1፥10-11) እና በልዩ አምሮት ውስጥ መግባት ነበር። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱን ያረክሰዋል፤ ኢየሩሳሌምም በባቢሎናውያን በምትያዝበት ጊዜም የይሁዳን ልጆች ለሰይፍ ይዳርጋል። ሕዝቅኤል ለእነርሱ ምልክት መሆን ነበረበት። ሕዝቅኤል ሚስቱ በሞተች ጊዜ ምላሽ እንደ ሰጠ፣ እነርሱም ኢየሩሳሌም ስትወድምና ልጆቻቸው ሲሞቱ በተመሳሳይ ሁኔታ ምላሽ መስጠት ነበረባቸው። የሕዝቅኤል የዐይኑ ማረፊያ (ሚስቱ) እንደ ተወሰደች፣ የእነርሱም የዐይን ማረፊያ የሆኑት (ቤተ መቅደሱና ልጆቻቸው) ይወሰዱ። የኢየሩሳሌም ውድቀት በነቢያት ተነግሮ ስለ ነበር ማልቀስ አልነበረባቸውም። ፍርድ የሚጠብቁት ጉዳይ መሆን ነበረበት።

ለ. የሕዝቅኤል ዲዳነት መወገዱ (24፥25-27)

25-27 የኢየሩሳሌም መያዝ ሙሉ በሙሉ እውን በሚሆንበት ጊዜ የሕዝቅኤል ዲዳነት እንደሚያበቃ እግዚአብሔር ተናግሮአል (ከ3፥25-27 ጋር ያነጻ)። ኢየሩሳሌም በወደቀችበት ቀን አንድ ያመለጠ ሰው የኢየሩሳሌምን መፈራረስ ወደ ባቢሎን ሄዶ ለሕዝቅኤል ይነግረዋል። ያ ያመለጠ ሰው ባቢሎን በሚደርስበት ቀን የሕዝቅኤል አፍ ይከፈታል፤ ከዚያም በሕዝቡ መካከል በመመላለስ ወደፊት ስለሚኖረው የተስፋን መልእክት የማወጅ ነጻነት ይኖረዋል። እንደ ገናም በእግዚአብሔር ፊት በመቆም ለሕዝቡ ይማልዳል። ይህ የፍጻሜ መልእክት በ33፥21-22 ባለው ክፍል ተዘርዝሮአል (ከ2ነገ 25፥8 ጋር ያነጻ)፤ ይኸውም ስለ እስራኤል ተስፋ ሕዝቅኤል ታላቁን መልእክት ባስተላለፈበት ምሽት ነው (33፥31-39፥29)። ዲዳነቱ መወገዱ ሕዝቅኤል ለምርኮኞቹ የትንቢት ስጦታ እንደ ነበረው የሚያመለክት ሌላ ማረጋገጫ ነው። በነቢያቱ አማካይነት የተነገረው የእግዚአብሔር መልእክት መፈጸሙን በሚያዩበት ጊዜ ምርኮኞቹ እግዚአብሔር የእስራኤል አምላክ መሆኑን ያውቃሉ።

፫. በአሕዛብ ላይ የተነገረ ፍርድ (25፥1-33፥20)

ሀ. በይሁዳ የቅርብ ጕረቤቶች ላይ የተነገረ ፍርድ (25፥1-17)

1. በአሞን ላይ የተነገረ ፍርድ (25፥1-7)

1-7 በ25፥1-33፥20 ነቢዩ ለአሕዛብ መንግሥታት እንዲነገር ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ንግር ሁሉ በዋና ዋና ሐሳብ ከፋፍሎ አስቀምጦአል (ከኢሳ 13-23፤ ከኤር 46-51 ጋር ያነጻ)። መልእክቶቹ የቀረቡት በተለያየ ጊዜ ቢሆንም በርእሰ ጕዳይ ረገድ በነጠላ አሐድ የቀረቡ፣ በዚህ መጽሐፍ ላይም ፋይዳ ባለው ሁኔታ የተቀመጡ ናቸው። ባለፉት ሃያ ሦስት ምዕራፎች ላይ ሕዝቅኤል ለይሁዳ ስለ ፍርድ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶአል። ምዕራፍ ሃያ አራት እነዚህ ማስጠንቀቂያዎች ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሰው ስለ ይሁዳ አስቀድሞ የተነገረው ቅጣት እንደ ጀምረ ይገልጻል። ይሁዳና ኢየሩሳሌም መውደቃቸውን ተከትሎ ሕዝቅኤል እስራኤልን በተወሰነ መልክ ወደ አወገዟት በዕዳን አገሮች ይመለሳል (ከ25፥1-33፥20 ጋር ያነጻ፤ እንዲሁም ከዘፍ 12፥3 ጋር ያነጻ)። በባዕዳን አገሮች ላይ እነዚህን ንግሮች ከዚህ ላይ በመጨመር ሕዝቅኤል ወሳኝና ድጋፍ ሰጪ በሆኑ የተስፋ ቃሎች መጽሐፉን ይደመድማል። የተሐድሶን ተልእኮ በ33፥1-20 ላይ በመቀበል፣ ሕዝቅኤል ትንቢቱን እስራኤል በደኅና ወደ

ተስፋዩቱ ምድር እንደምትመለስና መልሳም እንደምትቋቋም ተስፋ በሚሰጡ መልእክቶች አጠቃልሎታል (33፥21-48፥35)።

ምዕራፍ 25 ዐዳዲስ ተከታታይ መልእክቶችን አይጀምርም። በይሁዳ የቅርብ ጐረቤቶች ላይ የተነገሩት አራቱ ዐጫጭር ንግሮች፣ በ24፥1 ላይ የተጀመረውንና ዘመን የተቈጠረለትን የሕዝቅኤልን የፍርድ መልእክት ይቀጥላሉ። በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉ መልእክቶች በይሁዳ ላይ ፍርድን ያውጃሉ፤ ከዚያም በይሁዳ መውደቅ ደስ የተሰኙትን እንዲሁም ትርፍንና ጥቅምን ተስፋ ያደረጉትን በዙሪያ ያሉትን ሕዝቦች ለማውገዝ ዘወር ይላሉ። እግዚአብሔር በእነዚህ ሕዝቦች ላይ ፍርድን ያውጃል፤ አለዚያ ፈንዳቂ አንጓጮቻቸው በዚያው ይቀጥላሉ፤ ምርኮኞቹም እግዚአብሔር ለገባው የተስፋ ቃል ታማኝ ስለ መሆኑ ይጠራጠራሉ።

በእነዚህ መንግሥታት ላይ የታወጀውን ፍርድ ቀደም ብሎ ኤርምያስ ብዙ ጊዜ ተንብዮት ነበር (ኤር 9፥25-26፤ 25፥1-26፤ 27፥1-11፤ 48፥1-49፥22)። ናቡከደነፆርና የባቢሎናውያን ሰራዊት በእነዚህ መንግሥታትም ሆነ በይሁዳ ላይ የእግዚአብሔር የፍርድ መሣሪያ ይሆናሉ። እነርሱም ለሰባ ዓመታት በምርኮ በባቢሎን ይኖራሉ (ኤር 25፥11)። በቀደመው ዘመን እስራኤልን የሚረግሙ የተረገሙ እንደሚሆኑ እግዚአብሔር ተናግሮአል (ዘፍ 12፥3)። አሁን ያንን "ርግማን" በእነዚህ አሕዛብ ላይ ያመጣል። ጌታ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ለዘላለም እስኪነግሥ ድረስ ፍርድ እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽት ይቀጥላል (ከኢሳ 11፥14፤ ከዳን 11፥41፤ ከኢዩል 3፥1-4 ጋር ያነጻ)። ስለዚህ የእግዚአብሔር የፍርድ እይታ በቅርቡ በባቢሎናውያን ከሚፈጸመው እስከ መጨረሻው ዘመን ድረስ ይዘልቃል።

ሕዝቅኤል በአሞን ልጆች ላይ ትንቢት መናገር ነበረበት፤ ይኸውም የራሳቸውን አማልክት መልእክት ከመስማት ይልቅ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰሙ በማሳሰብ ነው። በአሞን ላይ የተነገረው ፍርድ በዐጭሩም ቢሆን በ21፥20፡28-32 ላይ ተነግሮአል፤ ይሁን እንጂ ከዚያ ላይ በሕዝቅኤል ክርክር ውስጥ እንደ ተመለከተው ቀደም ያለው የኢየሩሳሌም ቅጣት እስኪፈጸም ድረስ የአሞን ፍርድ ለሌላ ጊዜ ተላልፎ ነበር። በአሞን ላይ የተሰነዘረው ክስና ፍርድ በቍ. 3-5 እና 6-7 ባለው ክፍል ላይ ተገልጸዋል። አሞን የተወቀሠችው ጠላታና ተፎካካሪዋ በሆነችው በይሁዳ ላይ በደረሰው ክፉ ነገር ደስታዋን በመግለጿ ነው፤ ይኸውም "እሰይ" በሚለው ቃል የተገለጸው ነው። ቤተ መቅደሱ ሲረክስ (ከ24፥21 ጋር ያነጻ)፣ የይሁዳ ምድር ባድማ ሲሆን፣ የይሁዳ ሕዝብ በባቢሎናውያን ተማርኮ ሲሄድ አሞናውያን በእጆቻቸው በማጨብጨብና በእግሮቻቸው ዝለለው በመጨፈር ደስታቸውን ገልጸዋል።

እግዚአብሔር የአሞናውያንን ርስት ምድራቸውን ለሚበዘብዙ፣ ሰፍረውም የምድሪቱን ፍሬ ለሚበሉ "ለምሥራቅ ሕዝብ" አሳልፎ ይሰጣል። የምድሪቱ ባድማነት በትእምርት የሚገለጸው ዋና ከተማቸውን ረባትን የግመሎች መሰማሪያ፣ ምድራቸውንም የመንጎች ማጐሪያ (ማረፊያ) በማድረግ ነው። "የምሥራቅ ሕዝብ" የተባሉት በዚህ ስፍራ ማንነታቸው አልተገለጸም፤ ነገር ግን በቅርቡ ያለው ዐውድ፣ ትይዩ የሆኑት ምንባቦችና ጥንታዊው ታሪክ ባቢሎንን እንደሚያመለክት ሁሉም ይስማማሉ። ሕዝቅኤል የእግዚአብሔርን ቀጣይ የፍርድ ዐላማ በማስመልከት ያወጀው ዐዋጅ፣ በአሞን ላይ የሚመጣውን ፍርድ ባወጀ ጊዜም አልተለወጠም። ይህ ቅጣት እርሱ እግዚአብሔር፣ የእስራኤል አምላክና እርሱ ብቻ እውነተኛ አምላክ መሆኑን አሞናውያን ያውቁ ዘንድ እንዲያደርግ እግዚአብሔር ፈለገ።

2. በሞዓብ ላይ የተነገረ ፍርድ (25፥8-11)

8-11 ለዓለም የበረከት መሣሪያ ትሆን ዘንድ ይሁዳ በእግዚአብሔር መመረጧን በማንቋሸሽ፣ ሞዓብ የእስራኤልን ሕዝብ ረግማለች። ይሁዳ በባቢሎን አገዛዝ ሥር በመውደቋ ሞዓብ እንደ ሌሎች አሕዛብ አድርጋ ቈጥራታለች። ይሁዳ በእንዲህ ዐይነት ሁኔታ በመሸነፏም ሞዓብና ሌሎች አሕዛብም የይሁዳ አምላክ ደካማ እንደ ሆነ ዐስበዋል። ስለሆነም በዚህ አምላክ በተለየ መንገድ ይሁዳ መጠራቷም እንደ ቀልድ ተቈጠረ። ይሁዳ በተለየ መንገድ ከመጠራቷ አንጻር በእርሷ ላይ በደረሰው ሽንፈት ሞዓብ እጅግ ሥቃለች (ኤር 48፥27፤ ሶፎ 2፥8-9)። በብሉይ ኪዳን በሌላ ስፍራ "ሴይር" ተብላ የምትታወቀው ኤዶም (ከዘፍ 32፥3፤ 36፥30፤ ከሕዝ 35 ጋር ያነጻ)፣ በይሁዳ ላይ የደረሰውን ይህን ንቀት ከሞአብ ጋር ትጋራለች። በኤዶም ላይ ተጨማሪ ሙሉ ክስ ቀጥሎ ባለው የፍርድ ንግግር ይቀርባል።

በሞዓብ ላይ የተበየነው ፍርድ እስራኤልን የሚረግሙ እንደሚረገሙ የሚገልጸውን የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል የሚያሳይ ነው (ከዘፍ 12፥3 ጋር ያነጻ)። እግዚአብሔር የሞዓብን ስሜን ምዕራብ ክፍል ማለትም ከዮርዳኖስ ሸለቆ በላይ ያለውን ተራራማ ስፍራ "የምሥራቅ ሕዝብ" እንዲወርረው ያደርጋል (ባቢሎናውያን በሞዓብ ላይ ጥቃት ያደረሱትም በ583/582 ዓክክ ላይ ነው)። ጥቃቱ የሚጀምረው በሞዓብ ምድር አናት ላይ፣ ከስሜን ወደ ደቡብ በተሠመረው መሥመር በቤት የሺሞጽ ከተሞች መካከል (በዮርዳኖስ ሸለቆ ውስጥ)፣ በበዓልሜዎን (ዐምስት ማይል ያህል ከማዴባ በስተ ደቡብ ምዕራብ)፣ እና በቂርያታይም (ስፍራው በውል አይታወቅም)፣ "ክብር" በሆነው ምድር (እጅግ ለም በሆነው) ላይ ነው። የሞዓብ ሕዝብ ከአሞን ልጆች ጋር በአንድነት "ለምሥራቅ ሕዝብ" ርስት ሆነው ይሰጣሉ፤ ይህም በአንድ ጊዜ ተመሳሳይ ወረራ መካሄዱን ያመለክታል። ሞዓብ ለምርኮ ዐልፎ በመሰጠት ባድማ ትሆናለች (ኤር 48፥7-9)። እስከ መጨረሻው ዘመን ሞዓብም ሆነች አሞን በአሕዛብ ዘንድ ከእንግዲህ መታሰቢያ አይኖራቸውም። ይህ ፍርድ በናቡከደነፆር ተጀምሮ ጌታ ዳግም በሚመጣበት ዘመን ይጠናቀቃል። እግዚአብሔር ስለ ፍርዱ የሰጠው ቋሚ ዐላማ እንደ ገና በዚህ ስፍራ ተደግሞአል፤ ይኸውም ቅጣቱ እርሱ እግዚአብሔር፣ እርሱ ብቻ እውነተኛ አምላክ መሆኑን ሞዓብ እንድታውቅ ነው።

3. በኤዶም ላይ የተነገረ ፍርድ (25፥12-14)

12-14 በኤዶም ላይ የተሰነዘረው ወቀሣ ትኵረት ያደረገው በይሁዳ ላይ ባላት የማያቋርጥ የቂም በቀል አስተሳሰብ ላይ ነው፤ ይህ አስተሳሰብ የጀመረው በያዕቆብ (በእስራኤል) እና በዔሳው ግጭት ነበር (ኤዶም ዘፍ 25፥30፤ 27፥41-46፤ 32፥4)። ኤዶም እስራኤልንና ይሁዳን ለመያዝ ስለ ፈለገች (35፥10)፤ ይሁዳን ለማዋረድ ከአሞንና ከሞዓብ ጋር ተባበረች (ከቍ. 8፤ 36፥5፤ መዝ 137፥1፡ 7-9 ጋር ያነጻ)። በይሁዳም ላይ አሳዛኝ ድርጊቶችን ፈጸመች። ኤዶም መንትያ ወንድም ስለ ሆነ፤ ይህ ባሕርዩ ይቅርታ የሚያሰጥ አልነበረም! ይሁን እንጂ እስራኤል ይህን ወገናዊነቱን አክብሮ ቢጠብቅም ኤዶም ከቁም ነገር አልቈጠረውም።

ስለዚህ እግዚአብሔር ፍርዱን በኤዶም ላይ አወረደ፤ ይህም ፍርድ ከ35፥1-36፥15 በስፋት ተገልጦአል። እግዚአብሔር የሰውን ዘርና ከብትን ከዚያ ምድር ሲያጠፋ ኤዶም ባድማ ትሆናለች። ይህ ጥፋት ከቴማን ጀምሮ እስከ ድዳን ድረስ ያለውን ሁሉ የሚያካትት ነው። ሌሎች ምንባቦች ይህ ቅጣት የሚፈጸመው በናቡከደነፆር እንደ ሆነ ያመለክታሉ (ኤር 9፥26፤ 25፥21 ይመ፤ 27፥1-11፤ ከሕዝ 32፥29፤ ከሚል 1፥2-5 ጋር ያነጻ)። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ኤዶም በይሁዳ ላይ ለፈጸመችው ቂም በቀል ምላሽ፣ እርሱም የራሱን በቀል በኤዶም ላይ እንደሚያወርድ ተናግሮአል። ይህንንም የሚያደርገው እስራኤልን በመሣሪያነት በመጠቀም ነው። በሕዝቅኤል ዘመን ያለው ዐውድ ታሪካዊ ዐውድ ይህ ሁኔታ በዚያ ጊዜ እንዳይፈጸም ያግደዋል። ይሁን እንጂ ሕዝቅኤልና ሌሎች ነቢያት እስራኤል ኤዶምን በመጨረሻው የፍጻሜ ዘመን እንደምትይዝ ተናግረዋል (ከ35፥1-36፥15፤ ከኢሳ 11፥14፤ ከዳን 11፥41፤ ከአሞ 9፥12፤ ከአብድዩ ቍ. 18 ጋር ያነጻ)።

በኤዶም ላይ የወረደው የእግዚአብሔር ፍርድ ከተለመደው አገላለጽ የተለየ ነው፤ ይኸውም በእርሱ ፍርድ የእግዚአብሔርን በቀል እንዲያውቁ ነው። እግዚአብሔር የእስራኤል ታማኝ አምላክ፣ ሕዝቡን የሚረግሙትን የሚረግም እርሱ እንደ ሆነ ይገነዘባሉ። በምላሹም ኤዶም እርሱ እውነተኛ አምላክ እንደ ሆነ ያውቃል።

4. በናፍስዋኤም ላይ የተነገረ ፍርድ (25፥15-17)

15-17 ሕዝቅኤል በይሁዳ የቅርብ ጐረቤቶች ላይ ፍርድን ሲያውጅ ሳለ መልክአ ምድሩን የቃኘው ቀኙን ይዞ በመጓዝ ነው። በቀኝ በኩል ወዳለችው ምድር ዘወር አለ።

ፍልስጥኤማውያንም ለይሁዳ በበቀል ምላሽ በመስጠታቸው ተከሰዋል፤ ይኸውም በተለይ በይሁዳ ላይ በክፉ ልብና በቋሚ ጠላትነት በመነሣታቸው ነው። ዐላማቸው ይሁዳን ለማጥፋት ነበር። ፍልስጥኤም በእስራኤል ላይ ያላት የቁየ ጠላትነት ከሳምሶን (መሳ 13-16)፣ ከዔሊ (1ሳሙ 4)፣ ከሳኦል (1ሳሙ 13፤31)፣ ከዳዊት (2ሳሙ 5)፣ ከሕዝቅያስ (2ነገ 18፥8)፣ ከኢዮራም (2ዜና 21፥16-17) እና ከአካዝ (2ዜና 28፥18) ጋር በነበራቸው ግንኙነት ተገልጾአል። የእግዚአብሔር የፍርድ ውሳኔ ከሊታውያንንም እቁርጣለሁ በሚል የፍልስጥኤም አንዱ የግዛት ክፍል በሆነው ተገልጾአል (1ሳሙ 30፥14፤ ሶፎ 2፥5)። እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ያለው ታላቅ በቀል፣ በይሁዳ ላይ ስላሳዩት የበቀል አስተሳሰብና ስለ ፈጸሙት የበቀል ድርጊት ተገቢውን ፍርድ በዐይነቱ መክፈል ነው። እግዚአብሔር በፍልስጥኤማውያን ላይ የሚያደርሰው ጥፋት ሙሉ በሙሉ ይፈጽማል፤ በጠረፍ ላይ ባሉት ትሩፋንም ጥፋቱ ይደርሳል። ይሁን እንጂ መዓቱን የሚያወርደው ሥርዐቱን ይማሩ ዘንድ ነው፤ ፍልስጥኤማውያን በዚህ በደረሰባቸው ነገር እግዚአብሔር እርሱ ብቻ እውነተኛ አምላክ እንደ ሆነ ያውቃሉ።

በፍልስጥኤም ላይ የደረሰው የዚህ ቅጣት ጊዜ ባይታወቅም ባቢሎን በአሞን፣ በሞዓብና በኤዶም ላይ ፍርድን በፈጸመችበት ተመሳሳይ ጊዜ እንደ ነበረ ዐውዱ ያመለክታል (ከኤር 25፥20፤ 47፥1-7 ጋር ያነጻ)። የዚህ ፍርድ የመጨረሻው ተፈጸሚነት እውን የሚሆነው በመጨረሻው ዘመን እስራኤል ፍልስጥኤምን በቀጥጥር ሥር ስታደርግ ነው (ከኢሳ 11፥14፤ ከኢዩል 3፥1-4፤ ከአብ ቁ 19፤ ከሶፎ 2፥4-7 ጋር ያነጻ)።

ለ. በጢሮስ ላይ የተነገረ ፍርድ (26፥1-28፥19)

1. በባቢሎን አማካይነት የተፈጸመ ፍርድ (26፥1-21)

ሀ. በጢሮስ ላይ የተነገረ የፍርድ ንግር (26፥1-14)

1-6 ሕዝቅኤል አሁን ወደ ሶሜን ዘወር በማለት በጢሮስ ከተማና በአካባቢዋ ባሉት ላይ ፍርድን ተናገረ። የዚህ ንግር ርዝማኔ ከተማዪቱ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ በሆነው ጉዳይ ላይ ሁሉ የቱን ያህል ዋነኛ እንደ ነበረች ያመለክታል። እግዚአብሔር በጢሮስ ላይ የተናገረው ፍርድ በአራት ተከታታይ መልእክቶች እንደሚከተለው ቀርቦአል፤ ይህም የፍርድ ንግግር ከተጨማሪ መግለጫዎች ጋር (26፥1-21)፤ የከተማዪቱን ውድቀት በተመለከተ የቀረበ የሐዘን እንጉርጉሮ (27፥1-36)፣ በጢሮስ ልዑል ላይ የቀረበ የፍርድ ንግግርን (28፥1-10) እና የጢሮስን ንጉሥ ውድቀት በተመለከተ የቀረበ የሐዘን እንጉርጉሮን (28፥11-19) የሚያካትት ነው።

እነዚህ አራት ንግሮች የተፈጸሙበትን ጊዜ በተመለከተ "በዐሥራ አንደኛው ዓመት፣ ከወሩም በመጀመሪያው ቀን" በሚል ቀርቦአል። ወሩ የትኛው እንደ ሆነ በግልጽ አልተመለከተም። በጢሮስ ላይ የታወጁት እነዚህ ንግሮች "በዐሥራ አንደኛው ዓመት" የኢየሩሳሌም ከበባ በተጀመረበት ወቅት የተነገሩ ይመስላል።

ጢሮስ በመጀመሪያ የተጠቀሰችው እንደ ብርቱ የተመሸገች ከተማ ሲሆን፣ ድንበሯም የአሴር ነገድ ርስት ከሆነው የተወሰነን በመውሰድ የተካለለ እንደ ሆነ ተገልጾአል (ኢሱ 19፥29)። ጢሮስ በዳዊትና በሰሎሞን ዘመን በጣም የታወቀች ከተማ ነበረች። በሰሎሞን ዘመን የነበረው የጢሮስ ንጉሥ ኪራም ከተማዪቱን አስፍቶአትና አስጊጦአት ነበር። ከተማዪቱም በጥንታዊቷ የቅርብ ምሥራቅ አገሮች መካከል የታወቀች የባሕር ንግድ ወደብ ሆነች። አሦር ገናና ኃያል መንግሥት ሆና በተነሣችበት ጊዜ ጢሮስ ለጊዜውም ቢሆን ካላት የተትረፈረፈ ሀብት ግብር በመክፈል ተገዢነቷን አሳውቃ ነበር። ይሁን እንጂ በተቻላት ጊዜ ጢሮስ በአሦር ላይ በማመፅ እጅግ የተጠናከረ ጥበቃ ባለው የደሴት ምሽጓ ውስጥ የምትከፍለውን ግብር አስቀረች፤ ይህም በሰናክሬም ዘመን የታየ ነበር። አሦር ዐቅሟ ቀንሶ መውደቅ ስትጀምር ጢሮስ ሙሉ ነጻነቷን በኀይሏ ጨበጠች። እንግዲህ እነዚህ ንግሮች በታወጁበት ወቅት ጢሮስ በእንዲህ ዐይነቱ ቁይቶ በታየ ሁኔታ ላይ ነበረች።

ከቁ 1ለ - 6 ያለው ጥቅስ በጢሮስ ላይ የታወጀውን መሠረታዊ የፍርድ ንግግር፣ በቁ 2 ላይ ካለው ክስ ጋር የሚያቀርብ ሲሆን፣ ውሳኔው ከቁ 3-6 ባለው ላይ ተሰጥቶአል። ጢሮስ የተከሰሰችው በኢየሩሳሌም የወደፊት ውድቀት እጅግ በመደሰቷ ነበር፤ ኢየሩሳሌም ስትወድቅ የከተማዪቱን ሀብት ለመዝረፍና በውድቀትም የሚገኘውን ማንኛውንም ጥቅም ለማግኘት እጅግ ትጠባበቅ ነበርና። (ለምሳሌ፣ ኢየሩሳሌም በግብፅና በዐረቢያ ያሉትን ከሰሜን ጋር የሚያገናኙትን የንግድ መሥመሮች ትቈጣጠር ነበር)። "እሰይ" የሚለው ቃልዋ ጢሮስ በኢየሩሳሌም ውድቀት ደስ መሰኘትዋን የሚገልጽ ነው። ጢሮስ "የሕዝቦች በር" የሆነችውን የኢየሩሳሌምን መሰባበር ትናፍቅ ነበር። "በሮች" የሚለው ቃል የኢየሩሳሌምን ደጆች የሚያመለክት ሲሆን፣ ወደ አሕዛብ መግቢያ መንገድ የሆነው መሰበሩን ያመለክታል። የኢየሩሳሌም በሮች በባቢሎን ተሰብረው ለጢሮስ ክፍት ይሆናሉ ማለት ነው።

የጢሮስ ዋነኛ ፍላጎት የሚሟላው ከኢየሩሳሌም በምትበዘበዘው ምርኮና በውድቀቷም በሚያጋጥማት ዕድል ነው፤ ኢየሩሳሌም ከፈራረሰች በምዕራብ እስያ ያለው ሁሉ የጢሮስ ይሆናል። ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምን ሲወስዱ፣ ጢሮስ በኢየሩሳሌም ያለውን ሁሉ መዝረፍ እንድትችል ክፍት አድርገውላት ነበር። እንዲህ ዐይነቱን ሀብትና ብልጥግና ለማግኘት ሲባል የታየው የማያቋርጥ ምኞት፣ በዘፍ 12፥3 ላይ የሰጠው ተስፋ ይፈጸም ዘንድ የእግዚአብሔርን ቍጣ በጢሮስ ላይ እንዲገለጥ አደረገ።

በጢሮስ ላይ በግሉ የተነሣው እግዚአብሔር ጢሮስ የተራቈተ ዐለት እስክትሆን ድረስና የመረብ ማስጫ ብቻ ሆና እስክትቀር ድረስ እንደ ባሕር ማዕበል ያጠፉአት ዘንድ በተከታታይ በጢሮስ ላይ አያሌ መንግሥታትን ያስነሣባታል። "በባሕር ውስጥ" የሚለው አገላለጽ የጢሮስን አይበገሬ ሁኔታ የሚገልጽ ነው። የሞዓብ ገደላገደሎች፣ የኤዶም ከፍታዎችና የጢሮስ ደሴት ምሽግ የልዑል እግዚአብሔርን መዓት ፈጽሞ ሊከላከሉ አይችሉም። ጢሮስ ራስዋ ኢየሩሳሌምን ለመዝረፍ እንደ ተመኘች ሁሉ አሕዛብ እንዲዘርፉአት ዐልፋ ትሰጣለች። በጠረፏ ላይ ያሉ ስፍራዎች እንኳ ሳይቀሩ ይደመሰሳሉ። ነገር ግን በዚህ በተራዘመ ፍርድ እንኳ እግዚአብሔር ለጢሮስ ያለው ዐላማ፣ እርሱ እግዚአብሔር ብቻውን እውነተኛ አምላክ መሆኑን እንድታውቅ ነው።

ጢሮስ በናቡከደነፆር የተከበበችበት ዘመን ለዐሥራ ሦስት ዓመት ያህል የዘለቀ ነው (በግምት 586-573 ዓክክ)። ይሁን እንጂ ባቢሎን መውደቅ ስትጀምር ጢሮስ እንደ ገና ነጻነቷን አገኘች። ይህ ዐጭር የነጻነት ጊዜ በ525 ዓክክ በፋርሶች እስከ ተገዛችበት እስከ ሁለተኛው የጥፋት ማዕበል ጊዜ ድረስ የቁየ የቀረው የጢሮስ ታሪክ ቀጣይ የሆነውን የአሸናፊዎቿን "ማዕበል" ገልጦ አሳየ። እግዚአብሔር በጢሮስ ላይ "ብዙ ሕዝብ አስነሣብሻለሁ" በማለት የተናገረውንና ተከታታይ በሆኑ የማሸነፍ ማዕበሎች እንደሚቀጣት የገለጠውን ቃሉን ለመፈጸም ታማኝ ነበር። ጌታ ኢየሱስ ለዚህች አረማዊት ከተማ የስብከትና የፈውስ አገልግሎቱን አምጥቶላታል (ማቴ 15፥21፤ ማር 7፥24-31፤ ሉቃ 6፥17)። የተሰጣት ኀላፊነትና ያለባት ፍርድ የክርስቶስን ቋሚ አገልግሎት ከተቃወሙት ከገሊላ ሰዎች ያነሰ ይሆናል (ማቴ 11፥21-22፤ ሉቃ 10፥13-14)።

7-14 ናቡከደነፆርና ታላቁ ሰራዊቱ በቁ 7 ላይ ተለይተው ቀርበዋል። ጢሮስንም የያዘበት ሂደት ሙሉ በሙሉ ተገልጾአል። የከተማዪቱ መውደም እንዲሁም የነዋሪዎቿ መታረድ በዝርዝር ቀርቦአል፤ ይህንንም ተከትሎ ተዘርፎ ስለ ተወሰደው ሀብትና ስለ ቀረው የጢሮስ ክብር መውደም ተገልጾአል። "እርሱ" ከሚለው ስም በቁ 12 ላይ "እነርሱ" ወደሚለው መለወጡ የእግዚአብሔር የፍርድ መሣሪያ ከሆነችው ከባቢሎን በመቀጠል ሌሎች አያሌ መንግሥታት ወደፊት ጢሮስን በስፋት እንደሚዘርፉ ለመግለጽ የገባ ሳይሆን አይቀርም። ትልቁ እስክንድር የጢሮስን ከተማ ድል ለማድረግ ወደ ደሴቲቱ ምሽግ የሚያስኬደውን አንድ ተኩል ምዕራፍ የሚያህል መንገድ ለማበጀት "የጢሮስስ ከተማ ድንጋዮች፣ ዕንጨትና ፍርስራሽ በባሕሩ ላይ ሞልቶት ነበር"።

የጢሮስ ባድማነት በአጽንዖት የተገለጠው በከተማዪቱ ውስጥ ምንም ዐይነት የዘፈን ድምፅ እንዳይሰማ (ምንም ዐይነት የተለመደ ማኅበራዊ እንቅስቃሴ እንደማይኖር የሚያመለክት ነው) በመደረጉና የከተማዪቱ ራቁትነት ሥዕላዊ የሆነ

መግለጫም የመረብ ማስጫ ቦታ ብቻ እንደምትሆን የተጠቀሰበት ነው።

ለ. በጢሮስ ውድቀት ላይ ተገዢዎቹ የነበሩ አገሮች ምላሽ (26፥15-18)

15-18 እርሷን እንደ ጠባቂያቸው አድርገው በመኖር የሚተማመኑባት ጢሮስ አያሌ ተገዢ አገሮች ነበሩአት። ሕዝቅኤል የጢሮስ መውደቅና ለባቢሎን ዐልፋ የመሰጠቷ ወሬ ለእነዚህ ሕዝብ በሚደርስበት ጊዜ፣ እጅግ እንደሚደነግጡ ትንቢት ተናግሮአል። መሳፍንቶቷ ዙፋኖቻቸውን ይተዋሉ፤ ምናልባትም ባቢሎን እነርሱን ከመያዝዋ በፊት እጅ መስጠታቸውንና መገዛታቸውን የሚያሳይ ነው። ሐዘንተኞች እንደ መሆናቸው መጠን መጮኻቸዉን ሙሾ ማውረድ አይችሉም። እጅግ ደንግጠው በመቆም ጢሮስ በመውደቅዋ ይገረማሉ። እነዚህ ተገዢ መሪዎች ስለ ሞተችው ጢሮስ የሐዘን ሙሾ ያወርዳሉ። ምጸታዊ በሆነ መልኩ ጢሮስ በኢየሩሳሌም ውድቀት ላይ ለመደሰት ደካማ የሆነ ስሜት ነበራት። ይሁን እንጂ እነዚህ ከተሞች የጢሮስ ውድቀት በእነርሱም ላይ ተመሳሳይ የሆነ ነገርን እንደሚያመጣ በሚገባ ተረድተውት ነበር።

ሐ. የእግዚአብሔር የማጠቃለያ ፍርድ (26፥19-21)

19-21 የጢሮስን ዘላለማዊ ሞት በተመለከተ የተነገረው ትንቢት አሕዛብን በተመለከተ ለቀረበው የነዝን እንጉርጉሮ ተገቢ ምላሽ ነው። ሕዝቅኤል ለማስፋፋት የፈለገውን ቀደም ያለውን የመልእክቱን ገጽታ ለማመልከት የቁ 3-6 ምስያን ያመለክታል። ጢሮስ በአሕዛብ ታላላቅ ማዕበሎች (ቁ 3) በምትፈራርስበትና ገላጣ ዐለት ሆና በምትቀርበት ጊዜ (ቁ 4)፣ በዚህ ምድር ላይ እንደ ገና የዋናነት ስፍራዋን እንደማትይዝ አድርጎ እግዚአብሔር በርግጠኝነት ያጠፋታል። ጢሮስ ትሞታለች። የሞቱት "የጥንት ዘመን ሰዎች ወደ ገቡበት ጕድጓድ" ትወርዳለች። በምትፈራርስበት ጊዜ ከምድር በታች በሲያል እንዳደሩት ትሆናለች። በተጨማሪም ጢሮስ ጥንት በታሪክ ውስጥ ዋነኛ ሆና እንደ ኖረች ከእንግዲህ ከቶ አትቀጥልም። አንዳንዶች ቢፈልጓትም ፈጽሞ አትገኝም።

2. ሕዝቅኤል ለጢሮስ ያሰማው የሐዘን እንጉርጉሮ (27፥1-36)

ሀ. የጢሮስ የትዕቢት መርከብ መሠራት (27፥1-11)

1-3 ቀደም ብሎ የነበረው ሙሾ በአቅራቢያ ያሉት ነገሥታት ያወረዱት ነበረ (26፥15-18)። ይህ ዐዲስ መልእክት ሌላ የሐዘን እንጉርጉሮ ነው፤ ይሁን እንጂ ሕዝቅኤል ራሱ ስለ ጢሮስ ሞት ያወረደው ሙሾ ነው። ለዚህች የባሕር ላይ ኃያል መንግሥት ውድቀት ዋና ምክንያት ትዕቢትዋ ነበር። ጢሮስ ሙሉ በሙሉ በራስዋ ከመተማመንዋ በላይ ከሕዝቦች ጋር በምታደርገው ንግድ ባገኘችው ሁሉ ራስዋን ፍጹም እንደ ነበረች ትቈጥር ነበር። እግዚአብሔር ትዕቢትን ይጠላል (ምሳ 8፥13፤ 16፥18)።

4-11 የጢሮስ መሰባበር ሐዘን የምታምር መርከብ ስትሰባበር እንደሚታዘነው ዐይነት ይታዘናል። ምስስሎሹ በቅኔው የተገለጠ ሲሆን፣ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰውም ከመሰባበሩ ላይ ነው። በተለመደው የሙሾ ዘይቤ የሞተችው ከተማ የቀደመ ክብር በመጀመሪያ ላይ ተጠቅሶአል። ሕዝቅኤል የጢሮስን ትምክሕት፣ የእድገት ከፍታ እንዲሁም የባሕር ላይ ግዛት የበላይነት ለማሳየት የመርከብን አሠራርና አጊያጌጥ ምስያን ይጠቀማል።

የጢሮስ የበላይነት በባሕሩ ዋነኛ ስፍራ ላይ ነበር። የባሕር ንግድዋ እንቅስቃሴ ጥንታዊውን የቅርብ ምሥራቅ አገሮችን ሁሉ ያቀፈ ነበር። እጅግ ምርጥ የሆኑ ቍሳቍሶችን ከባሕር ላይ ንግድዋ ታገኝ ነበር። በሌሎች አገሮች ላይ ያላትን የበላይነት ተጠቅማ "መርከብዋን" ማለትም ጢሮስን ትሠራና ታስጌጥ ነበር። ለሳንቃዎችዋ የሚሆነው ዕንጨት (ጥድ ወይም ጥድ የመሰለ እሾሃማ ዛፍ) በሔርሞን ተራራ አውራጃ ሳኒር ከሚባል ስፍራ የሚመጣለት ሲሆን፣ "ምሰሶዋ" ደግሞ ከሊባኖስ በመጡ ምርጥ ዝግባዎች የተሠራ ነበር። የመርከብዋ "መቅዘፊያዎች" ከባሳን በመጣ ወርካ የተሠሩ ናቸው፤ በዝኖን ጥርስ የተሰበጠው ወለልዋ የተሠራውም ከቆጵሮስ ጠረፍ በመጣ ዝግባ ነበር። የመርከቦችዋ "ሸራ" እና "አርማ" የተሠሩት ከግብፅ በመጣ በፍታ ሲሆን፣ መጋረጃዎችዋ ደግሞ የተሠሩት ከኤሊሳ በመጡ ሐምራዊና ሰማያዊ ጨርቆች ነበረ። እነዚህ ጥቅሶች የሚያሳዩት ጢሮስ እጅግ ውብና ታላቅ የባሕር ከተማ አገር ለመሆን የቻለችው እጅግ ምርጥ የሆኑትን ቍሳቍሶች በአካባቢዋ ከሚያመርቱ አገሮች በማግኘትዋ መሆኑን ነው። እነዚህን ቍሳቍሶች ለማግኘት የቻለችው የባሕር ላይ ነጋዴዎችዋ ካላቸው ታዋቂነትና ኃያልነት የተነሣ ነው።

የጢሮስን የንግድ እንቅስቃሴ እድገትና ስፋት ሲመሩ የነበሩት ፊንቃውያን የተባሉት የአካባቢው ነዋሪዎች ነበሩ። ጢሮስ ያሏት እጅግ የሠለጠኑ ዘማች የባሕር ላይ ነጋዴዎች ከፊንቄ ከተሞች ከሆኑት ከሲዶና፣ ከአራድና ከጌባል (ቢብሎስ) የመጡ ከመሆናቸውም በላይ ቀዛፊዎችና የመርከብ ባለሙያዎች ነበሩ። ይሁን እንጂ የጢሮስ ጥበበኞች መርከበኛ ነበሩ። ጢሮስ በባሕር ላይ ንግድ እጅግ ሥልጡን ከመሆንዋ የተነሣ ሁሉም ከእርስዋ ጋር መነገድን ይመርጥ ነበር። ይህም ጉዳይ ከተማዎቿንና መርከቦችዋን መከላከል እንድትችል የጦር ኀይል እንድታደራጅ አደረጋት። ስለሆነም ወዲያውኑ አያሌ ወደገብ ዘማች ወታደሮችን ከሩቅ አገር ከፋርስ፣ ከሉድ፣ ከፉጥ (ከአፍሪካ) ከውስጥ አገርም ከአራድ፣ ከሔሌክና ከገማድ ለመሳብ ችላለች። ጢሮስ እነዚህን ሁሉ ቅጥረኛ ወታደሮች ለመሳብ ያስቻላት ያለጥርጥር ክብርዋ፣ ሀብትዋና ኃያልነትዋ ነበር። በሌላ በኩል የእነዚህ የውጪ ዜጎች በጢሮስ መገኘት የጢሮስን ታዋቂነት አጉልቶ አሳይቶአል። በርግጥ ጢሮስ በጥንቱ የቅርብ ምሥራቅ ካሉ አገሮች ሁሉ የከበረች የባሕር ላይ መንግሥት ከመሆንዋ የተነሣ፣ ሌሎች መጥተው ከእርስዋ ጋር እንዲነግዱና ከተማ እንደመሆንዋ መጠን የእርስዋን ታላቅነት እንዲያዩ የሚያደርግ የመሳብ ኀይል አግኝታለች።

በዚህም ምክንያት ጢሮስ "ፍጹም ውብ ነኝ" ለማለት ችላለች።

ለ. የጢሮስ ሰፊ የንግድ ግንኙነቶች (27፥12-24)

12-24 ጢሮስ ለመነገድ የሚያስችላት የተትረፈረፈ ሸቀጥ ስለ ነበራት፣ ብዙ አገሮች ከእርስዋ ጋር መገበያየትን ይመኙ ነበር። በጊዜው በነበረው የመልክአ ምድራዊ ሁኔታ የነበሩ አገሮች ዝርዝርና እነዚሁም አገሮች እያንዳንዳቸው እንዲገበያዩ የሚያስችላቸው የሸቀጥ ዐይነት የጢሮስ ንግድ ስፋት፣ ብዛትና ዐይነት የቱን ያህል እንደ ነበር የሚያሳይ ነው። ጢሮስ በአካባቢው ከነበሩ ከሁሉም አገሮች ጋር የንግድ ግንኙነት ነበራት። እነዚህም ከተርሴስ (ስፖኝ) በኤጂያን በኩል በምሥራቅ ምዕራብ መገናኛ እስካለችው እስከ ሰሜን ምሥራቅ አናቶሊያ (ቱባል፣ ቤት ቱርጋማ)፣ ከዐረቢያ በሶርያና በፍልስጥኤም በኩል በሰሜን ደቡብ መገናኛ ድረስ ነበሩ።

ሐ. የጢሮስ መርከብ መስመጥ (27፥25-36)

25-27 ይህ የሕዝቅኤል የሐዘን ሙሾ የመጨረሻ ክፍል እግዚአብሔር በጢሮስ ላይ የሰጠውን ፍርድና የሕዝቡን ምላሽ የሚያመለክት ነው። የሚሰምጥ መርከብ ምስያ በመቀጠል ተለዋጭ ዘይቤውን ከማመልከቱም በላይ የጢሮስን መውደም ያመለክታል። በአገሮች ሀብት ሁሉ በመጫንና በቍሳቁስ ብልጥግና በመታበይ "መርከቡ" ለባሕሮች ማዕበል የተጋለጠ ሆነ። ብዙ ሀብት ለማግኘት ካላት ብርቱ ፍላጎት የተነሣ ወደ ታላላቅ ባሕሮች ለከፍተኛ ንግድ ስትወጣ፣ ጢሮስ በፍጥነት ከባቢሎን በሚመጣው ብርቱ "የምሥራቅ ነፋስ" ተሸነፈች። የጢሮስ የሀብት፣ ቍሳቍሳውና የትምክሕት ጭነት ሁሉ እርሷንም ከሚያገለግሏት ጋር በድንገት ወደ ባሕሩ ሰመጠ።

28-36 ከጢሮስ ጋር ሲነግዱ የነበሩ በፍጥነት "መርከባቸውን ጥለው ይሄዳሉ፤" ይኸውም ለጢሮስ የሚሠሩትን ሥራ ይተዋሉ፣ ደንግጠውና ኅሊናቸውን ስተውም ዳርቻው ላይ ይቆማሉ። ማቅ በመልበስ፣ ጠጕራቸውን በመላጨት፣ ትቢያን በላያቸው ላይ በመነስነስና በዐመድ ላይ በመንከባለል ስለ ጢሮስ ሞት አምርረው ያለቅሳሉ። እንደ ጢሮስ ፈጥኖ የወደቀ ማንንም አይተው አያውቁም። በባሕር ላይ በሚደረገው ንግድ ሉዓላዊ መንግሥት ነበረች፤ በሸቀጥዋ ብዛት ብዙዎችን ታረካም ነበር። አሁን ግን የቀረ ምንም ነገር የለም። ሁሉም ነገር ባሕር ውስጥ ሰጠመ። ጢሮስ የምትባል ፈጽሞ ከምድር ጠፋች።

ከጢሮስ ጋር ሲነግዱ የነበሩ ሕዝቦችና ነገሥታት የእርስዋ ዕጣ ፈንታ የእነርሱም እንዳይሆን እጅግ ፈሩ (ከ26፥17-18 ጋር

ያነጻ)። ከፍርሀትና ራስን ከመጠበቅ የተነሣ ጢሮስን እጅግ ከማድነቅ ዘወር በማለት ሙሉ በሙሉ ከዷት። በሚያዋርድ ሁኔታም እርስዋን ማንቋሸሽ ጀመሩ። ትዕቢተኛዋ እንዴት ፈጥና እንደ ወደቀች እዩ! የጢሮስ ዕድል ፈንታ ይህ ሆነ! ፈጽሞ ከምድር ጠፋች!

2. በጢሮስ ገዥ ላይ የተነገረ የፍርድ ትንቢት (28፥1-10)

1-5 ሕዝቅኤል የመጨረሻውን የፍርድ ንግግር በጢሮስ ገዥ ላይ እንዲያደርግ በእግዚአብሔር ታዘዘ። የጢሮስ ገዥ እጅግ ብልኅ ሰው እንደ ነበረ ተገልጸአል። ነገር ግን በራሱ እጅግ ከመኩራራቱ የተነሣ ራሱን እንደ አምላክ መቊጠር ጀመረ። እርሱም "በአምላክ ዙፋን ላይ (ሜልካርት - የጢሮስ አምላክ) በባሕሮችም ልብ ላይ" ተቀምጦአል። ይህ በትምክሕት የተሞላ ትዕቢትና እንደ አምላክም ራስን ከፍ ከፍ የማድረግ መንፈስ እግዚአብሔርን በጢሮስ ገዥ ላይ እንዲቈጣ አድርጎታል። የጢሮስ ገዥ ሰው እንጂ አምላክ አለመሆኑን በማሳየት እግዚአብሔር ከሶታል። የጢሮስ ንጉሥ ምስጢርን ለናቡከደነፆር እንደ ገለጸው እንደ ነቢዩ ዳንኤል ጠቢብ ስለ መሆኑ ጥያቄ ጠየቀ። የጢሮስ ገዥ ምስጢርን ሁሉ ያውቃልን? ፈጽሞ! የጢሮስ ገዥ ሰው ነው።

6-10 ሕዝቅኤል በጢሮስ ገዥ ላይ ፍርድን ዐውጆአል፡ እግዚአብሔር እጅግ አስከፊ ሞትን በማምጣት ይኸውም ያልተገረዙ ሰዎችን አሟሟት በማምጣት በባዕዳን እጅ እንዲሞት በማድረግ ያዋረደዋል። ፊንቃውያን የግዘረትን ሥርዐት ያውቃሉ፤ ስለሆነም እንዳልተገረዘ ወንድ ታርዶ መሞት ጭካኔ የተሞላበት አሟሟት ነው። ከእንግዲህም ክብርና ውበት አይኖረውም። የባዕዳን ሰይፎች ብልጥግናውንና ታላቅነቱን ይቈራርጣሉ። ገዥ አምላክ እንደ ሆነ የገለጠበትን ማንነቱን፣ በእጃቸው የሚገደል ሟች ሰው እንደ ሆነ በማሳየት እግዚአብሔር በገዳዮቹ ፊት ያዋርደዋል።

4. ስለ ጢሮስ ገዥ የተደረገ የሐዘን እንጉርጉሮ (28፥11-19)

ይህ ምንባብ በመላው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንኳ ባይሆን፣ በሕዝቅኤል መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ እጅግ አስቸጋሪ ምንባብ ነው። ይህን ክፍል ለመረዳት እጅግ አሳማኝና የሚጠበቀው አተረጓጎም ሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ ገዥ ያቀረበው የሐዘን እንጉርጉሮ እንደ ሆነ አድርጎ መመልከት ነው። በጢሮስ ላይ የቀረበው የትንቢት ሂደት ከሐዘን እንጉርጉሮ ጋር በተሰዋዋጭነት የፍርድ ንግግር ነው። በ28፥1-10 ያለው በጢሮስ መሪ ላይ የቀረበውን የፍርድ ንግግር የሚያመለክት ሲሆን፣ በ28፥11-19 ላይ ያለውን ደግሞ ለገዢ የተደረገ የሐዘን እንጉርጉሮ ነው ብሎ ማንም ሊያስብ ይችላል። ይሁን እንጂ ብዙዎች የጢሮስ ገዥ ራሱ ሰይጣን እንደ ነበር ያምናሉ። ነገር ግን እንዲህ ዐይነቱ አተረጓጎም በኋላ እንደሚታየው የራሱ ችግር ይኖረዋል። ስለሆነም አሳማኙና ተቀባይነት ያለው አተርጓጎም እነዚህ ጥቅሶች የሚናገሩት በታሪኩ ስለ ተጠቀሰው ሰው ስለ ጢሮስ ገዥ ነው ማለት ነው።

11-12 በዚህ ምንባብ ውስጥ ያለው ዋነኛ ችግር ስለዚህ ንጉሥ የተሰጠውን ገለጻ በማብራራት ላይ ነው። በዚህ ስፍራ ላይ ጥበብ የተሞላና ፍጹም የሆነ ውበትን የተላበሰ መሆኑ ተገልጾአል፤ ይህም ስለ ጢሮስ ገዥና ስለ ከተማዪቱ ቀደም ብሎ የተሰጠ ሐሳብ ነው። ("የፍጹምነት ምሳሌ ማኅተም" በሚል ቃል በቃል ይተረጐማል) የጢሮስ ንጉሥ የከተማዪቱ የባሕር ንግድ እንቅስቃሴ ዋና መሪ እንደ መሆኑ መጠን፣ የእርሱ ዕቅድ ከተማዪቱ በዘመኑ የባሕር ላይ ንግድ ዋና መሪ እንድትሆን ማድረጉን በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

13ሀ ይህ ሰው "በእግዚአብሔር የአትክልት ቦታ በዔድን" እንደ ነበር ተገልጾአል። "እግዚአብሔር" የሚለው መጠሪያ እውነተኛውን አምላክ ወይም አንድን ሌላ አምላክ (ጣዖት) የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። "ዔድን" የሚለው በዘፍ 1-3 ያለውን የአትክልት ቦታ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ምናልባትም ያለውን የመልክአ ምድራዊ ውበትና ግርማ በዘይቤ ለማሳየት የቀረበ ይሆናል፤ ይህም የተለመደ አገላለጽ ነው (ከዘፍ 13፥10፤ ከሕዝ 31፥9 ጋር ያነጻ)። መቼውንም በዘፍጥረት ዘመን የዚህ ጊዜው የጢሮስ ንጉሥ በዔድን የአትክልት ቦታ አልነበረም፤ ስለሆነም ብዙዎች የጢሮስ ንጉሥ በዔድን የአትክልት ቦታ አልነበረም፤ ስለሆነም ብዙዎች የጢሮስ ንጉሥ ሰይጣን ነው ብለው (ዘፍ 3 ይመ) የሚከራከሩት ለዚሁ ነው። ነገር ግን ማንም ይህን ትርጓሜ ለመቀበል ከመረጠ ስለ ሰይጣን አንዳንድ ግምቶች መቅረብ አለባቸው።

የጢሮስ እውናዊ ንጉሥ በእይታ ውስጥ ከሆነ፣ እንግዲያስ የጥንት ቅርብ ምሥራቅ ቤተ መቅደሶችን ማስተዋል የሚያስችለንን መፍትሒ ማግኘት እንችላለን። አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ቤተ መቅደሶች በትልልቅ የአትክልት ቦታዎች የተከበቡ ናቸው። "እግዚአብሔር" የሚለው ቃል "ጣዖት" የሚለውን የሚያመለክት ከሆነ፣ "በእግዚአብሔር የአትክልት ቦታ በዔድን" የሚለው ተለዋጭ ዘይቤ የሜልካርትን ("የከተማዪቱን ንጉሥ") ቤተ መቅደስ ልዩ ውበት የሚያመለክት ይሆናል፤ ይህም ሰው የሆነው የጢሮስ ንጉሥ ራሱን የሚያመሳስልበት ቦታ ነው። በርግጥ "በእግዚአብሔር የአትክልት ቦታ በዔድን ነበርህ" የሚለው ሐረግ ለትርጓሜ ዕንቅፋት የሚፈጥር ነው፤ አሳማኝ የሆኑ መፍትሒዎች ቢኖሩም እንኳ።

13ለ-14ሀ በጥንት ቅርብ ምሥራቅ "ኪሩብ" የሚለው ቃል የሚተረጐመው የእንስሳ አካል (ብዙውን ጊዜ የኮርማ ወይም የአንበሳ አካል) እና ክንፍ እንዲሁም የሰው ራስ ያለው ስፊኒክስ የመሰለ ፍጥረት እንደ ሆነ ነው። እነዚህ ሐውልት ፍጥረታት ብዙውን ጊዜ የጣዖት ቤተ መቅደሶችን መግቢያ በር የሚጠብቁ ዘቦች ናቸው። የእግዚአብሔር ኪሩቤል የቃል ኪዳኑን ታቦትና የዔደንን የአትክልት ቦታ የሚጠብቁ ሲሆኑ፣ የእግዚአብሔር የዙፋኑ ሠረገላም ናቸው። በዚህ ስፍራ የጢሮስ ንጉሥ ራሱን ሜልካርት ከተባለው ከጢሮስ አምላክ ጋር ያመሳስለ ይመስላል፤ ይህም በቀጥታም ሆነ በምሳሌነት የአማልክት ጠባቂ ስፊኒክስ እንደ ሆነ ነው። የፊንቃውያን ወንድ ሶፊኒክስ (ወይም ኪሩብ) ብዙውን ጊዜ በጌጣጌጥ የተሸለመ ሲሆን፣ አንዳንድ ጊዜ የካህን - ንጉሥ ራስ ይኖረዋል። ስፊኒክሱ በጥበብ የተሞላ ነው ተብሎ ይታሰብ ነበር። ንጉሡ ጠባቂ ኪሩብ (ስፊኒክስ) ተብሎ ስለሚጠራና የፊንቃውያንን ስፊኒክስ (ኪሩብ) ያስጌጡት ብዙዎቹ የተዘረዘሩት የከበሩ ድንጋዮች እንዲሁም ያስጌጡት የዕንቊ መሸፈኛ ልብሶች ከተዘረዘረው መግለጫ ጋር የሚስማሙ ናቸው። ምንባቡ የሚያመለክተው የጢሮስ ንጉሥ ሜልካርት ለተባለው አምላክ ጠባቂ ኪሩብ እንደ ሆነና ኪሩብ ስፊኒክስ በከበሩ ነገሮች እንደሚጌጥ አጒጦ ነው። "በተፈጠርህበት" የሚለው ሐረግ ንጉሡን በዙፋን ላይ ከማስቀመጥ ጋር የተያያዘ ነው። እግዚአብሔር ምንጊዜም ቢሆን ፈጣሪ ነው፤ ስለሆነም እውነተኛው አምላክ በሉዓላዊ ክብሩ ይህን ንጉሥ በጢሮስ ዙፋን ላይ እንዳስቀመጠው የሚያመለክት ይሆናል።

በዔድን የአትክልት ቦታ እነዚህ የከበሩ ድንጋዮች የሰይጣን መሸፈኛ ልብስ እንደ ሆኑ ማሰብና ሰይጣንም በዔድን ጠባቂ መልአክ ነበር ብሎ መገመት መላምት ከመሆን አያልፍም። በርግጥ ሚካኤልም ሆነ ገብርኤል (ሊቃነ መላእክት) ኪሩብ እንደ ሆኑ ተገልጸአል፤ ያለ ጥርጥርም ሰይጣን ከመውደቁ በፊት ከእነዚህ መላእክት ጋር እኩል በሆነ ደረጃ ላይ ነበር።

14ለ "ቅዱስ ተራራ" የሚለው ሐረግ በተከታታይ የአምልኮ ማእከላዊ ቦታ የሆነውንና የእግዚአብሔር ማደሪያ ስፍራ የተባለውን ኢየሩሳሌምንና ወይም ጽዮንን የሚያመለክት ነው (መዝ 99፥9፤ ኢሳ 56፥5፡6፡7)። በሺሁ ዘመነ መንግሥትም የእስራኤል ልጆች እንደ ገና ይሰበሰባሉ የተባለው "በቅዱሱ ተራራዬ" ነው (ኢሳ 11፥9፤ 65፥25)። "ቅዱሱ የእግዚአብሔር ተራራ" ኢየሩሳሌምን የሚያመለክት ከሆነ፣ ይህ ማለት የጢሮስ ንጉሥ ባቢሎን ኢየሩሳሌምን ስትደመሰስ በነበረው የተንበለበለ ፍም እሳት መካከል እርሱ በከተማዪቱ ውስጥ ይዝናና ነበረ ማለት ነው፡ ይሁን እንጂ አንድን ጣዖት የማቃጠል ሥርዐት እንደ ነበረ ጢሮስ የነበረውን የሜልካርት ጣዖት ሥርዐተ አምልኮ በሚያሳየው በቊፋሮ በተገኘው የሲዶና ሸክላ ሳሕን ተጽፎ ተገኝቷል። የሜልካርት ትንሣኤ የሚከበረው "ምስሉን በማቃጠል ነው፤" በዚህም በእሳቱ እንደ ገና በመቀምና የሚቃጠለው መሥዋዕትም በመሸተቱ ይነሣል ተብሎ ይታመናል። ስለዚህ የፊንቃውያንን የሃይማኖት ባህል በመጠበቅ ምናልባት በሚንበለበለው የእሳት ፍም መካከል መራመድ የተገለጠበት ምክንያት ሜልካርት የተባለው ጣዖት ራሱን ከፍ

ከፍ የሚያደርግበትን ሁኔታ ለማሳየት ሲሆን፣ በእሳትም ከተቃጠለ በኋላ ትንሣኤውን የሚገልጥ ነው።

"የእግዚአብሔር ቅዱስ ተራራ" የተባለው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንግሥተ ሰማይ እንደ ሆነ ተተርጉሞ አያውቅም፤ እንዲህ ሊሆን የሚችለውም የጢሮስ ንጉሥ ሰይጣን እንደ ሆነ ከተተረጐመ ነው። ልክ እንደዚሁ በሚንበለበለው እሳት ፍም መካከል የሚራመደው ሰይጣን እንደ ሰው የመታሰቡ ነገር በዚህ ስፍራ ምስጢር ነው።

15-19 በመጨረሻም ይህ ንጉሥ ከተፈጠረበት ቀን ጀምሮ ኀጢአትን እስከ ሠራበት ጊዜ ድረስ በመንገዱ ሁሉ ነቀፌታ አልነበረበትም። "ፍጹም" የሚለው ቃል "ንጹሕት አልባ የሆነ ፍጹምነት" ማለት ሳይሆን፣ አንድ ሰው በአንድ በተወሰነ ስፍራ ነቀፌታ የለበትም ወይም የሚያስነውር ሁኔታ የለበትም ለማለት ነው። የጢሮስ ንጉሥ፤ ተቃውሞ እስከ ተነሣበት፣ በዙፋኑም መታበይ እስከ ጀመረና ኀጢአት እስከ ሠራ ድረስ መልካም ሰው ነበር ማለት ነው።

የጢሮስ ንጉሥ የትዕቢት ኀጢአት የተነሣው ሰፊ ከሆነው የንግድ እንቅስቃሴው ካገኘው ታላቅ ክብር ነው። ለቀኑሳቀሱ ጥቅም የነበረው ታላቅ ፍላጎት በንግድ ምክንያት ሊመጣ የሚችለው ማንኛውም ክፋት ሁሉ ወደ ከተማዪቱ እንዲገባ አደረገ። በዐመፅ የተሞላ ሆነ። የነበረውም ጥበብ በንግድና በክብር ብዛት ደብዝዞ ነበር። ቤተ መቅደሱንም አረከሰ፤ ይኸውም በሚልካርት ቤተ መቅደስ የሚሠራውን የጣዖት አምልኮ ሳያመለክት አይቀርም። ይህ መግለጫ ፈጽሞ ከሰይጣን ጋር ተያያዥነት የለውም። እነዚህን ጥቅሶች ማንም ሰው ከሰይጣን ጋር ማያያዝ የሚችለው ሰይጣን ከጢሮስ ንጉሥ በስተ ጀርባ እንዳለና መንፈስም በእርሱ ውስጥ እንደሚሠራ በማየት ብቻ ነው።

ይህ የሐዘን ልቅሶ የሚጠቃለለው ይህ ንጉሥ በእግዚአብሔር ፍርድ እንደ ወደቀ በቀረበው ገለጻ ነው። ይህ ንጉሥ ራሱን ካጸደቀበት "ከእግዚአብሔር ተራራ" እግዚአብሔር በውርደት ወደ ታች ይጥለዋል። እንደ ኪሩብ ከእሳት ድንጋዮች መካከል እግዚአብሔር ያስወጣዋል፤ ይኸውም በእሳት ተቃጥሎ እንደ ገና ይነሣል የሚለው አባባል ተለውጦ በሚሞትበት ጊዜ ፈጽሞ ይደመሰሳል ወይንም ከኢየሩሳሌም ምርኮን ከመሳፈል ይወገዳል። በዓለም ነገሥታት ሁሉ ፊት እግዚአብሔር ከምድር ላይ ይጥለዋል፤ እሳትም ከንጉሡ እንዲያጠፋው ያደርጋል። 'እሳት ከንጉሡ ወጥቶ' የሚለው ሐሳብ ግልጽ አይደለም። አሚሚቱ ድንገተኛና የከፋ ይሆናል፤ ከእንግዲህም በሕይወት አይኖርም። በርግጥ ይህ አገላለጽ ሰውን የሚመለከት ነው፤ ነገር ግን ስለ ሰይጣን ውድቀትና የመጨረሻ መደምሰስ ከምናውቀው ጋር ተያያዥነት የለውም።

ስለዚህ የጢሮስ ንጉሥ በሕዝቅኤል ዘመን የነበረ የዚያች ከተማ ንጉሥ ነበረ ማለት ነው። እያንዳንዱ ባሕርይ ሊገለጽ የሚችለው በጊዜው በነበረው ባህላዊና ሃይማኖታዊ ዐውድ አንጻር ነው። በአንጻሩ ንጉሡን ከሰይጣን ጋር ማመሳሰል ከልክ በላይ የሆነ ግምትን ይጠይቃል። ብዙዎቹ ዝርዝር መግለጫዎች በርግጥ ከሰይጣን ጋር የተያያዙ ናቸው ከተባለ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ በሌላ ስፍራ ተጠቅሰው አናገኝም።

ሐ. በሲዶን ላይ የተነገረ ፍርድ (28፥20-24)

20-24 የጢሮስ እኅት ከተማ የሆነችው ሲዶን በሕዝቅኤል ዘመን በጢሮስ የባሕር ንግድ አመራር ጥላ ሥር የነበረች ናት። እግዚአብሔር በሲዶን ላይ የሚያወርደው ፍርድ በሰይፍ መቅሠፍትንና ሞትን የሚያስከትል ነበር። ደም መፋሰስ እየተዛመተ ይሄዳል፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ፍርድ የምሕረቱ መግለጫ ነው፤ ሲዶናውያን እግዚአብሔር እርሱ በእውነት ጌታና አምላክ መሆኑን ሲያውቁ በዚያ እግዚአብሔር ይከበራልና። የእግዚአብሔር ቅድስና እርሱ ጻድቅ እንዲሁም በኀጢአት ላይ የሚፈርድ መሆኑን የሚጠይቅ ነው። ይህ ቅድስና በኀጢአት በተሞላችው ሲዶና ላይ በፈረደ ጊዜ ተገልጦ ነበር።

ቁ. 24 ቀደም ሲል በመንግሥታት ላይ የወረደውን የፍርድ ንግር የሚያጠቃልል ነው (ምዕራፍ 25-28)። እነዚህ ፍርዶች ሲፈጸሙ፣ እስራኤል ለረኀርም ጊዜ ባለማቋረጥ ሲነጥቋትና ሲያስጨንቋት ከነበሩት መንግሥታት ነጻ ትሆናለች። ከዚያም እስራኤል እግዚአብሔር በእውነት አምላክዋ እንደ ሆነ ታውቃለች፤ ታስተውላለችም።

መ. እስራኤል ከአሕዛብ ነጻ ወጥታ እንደ ገና መሰብሰቧ (28፥25-26)

25-26 በእስራኤል ዙሪያ ባሉት አሕዛብ ላይ በሚወርደው ፍርድ፣ እግዚአብሔር በሌሎች መንግሥታት ላይ እንዲሁም በይሁዳ ላይ በታማኝነት ጽድቁን እንደሚፈጽም በማሳየት ሕዝቅኤል ምርኮኞችን ያበረታታል። እግዚአብሔር ከተበተኑባቸው መንግሥታት መካከል ወጥተው እንደ ገና እንደሚሰበሰባቸው በማሳሰብ ይበልጥ ያበረታታቸዋል። ይህ ሕዳሴ እውን የሚሆነው እግዚአብሔር በእነዚህ መንግሥታት ላይ ሲፈርድ ነው፤ እነዚህም ፍርዶች እስከ መጨረሻው ዘመን ድረስ የሚፈጸሙ ናቸው። እስራኤልን እንደ ገና በመሰብሰብ እግዚአብሔር እርሱ ቅዱስ፣ ልዩና ተወዳዳሪ የሌለው ድንቅ መሆኑን ይገልጻል።

እግዚአብሔር እስራኤልን በክነዓን መልሶ ሲያቋቁም የማይለወጥ ታማኝ ባሕርዩን ያሳያል። ይህን ምድር ለአብርሃም (ዘፍ 12፥7)፣ ለይስሐቅ (ዘፍ 26፥3) እና ለያዕቆብ (ዘፍ 35፥12) እንደሚሰጥ በአብርሃም ኪዳን ቃል ገብቶአል። እግዚአብሔር ሕዝቡ በምድራቱ በሰላምና በብልጽግና እንዲኖር ያደርጋል። በዚያ ጊዜ ያለ ጥርጥር እርሱ እግዚአብሔር ጌታቸውና አምላካቸው እንደ ሆነ ያውቃሉ።

ሠ. በግብፅ ላይ የተነገረ የፍርድ ትንቢት (29፥1-32፥32)

ሕዝቅኤል በመንግሥታት ላይ ትንቢቱን የሚያጠቃልለው በግብፅ ላይ ስድስት የፍርድ መልእክቶችን በማስተላለፍ ነው። ግብፅ በሁዳ መንግሥት የመጨረሻ ዘመን ላይ ወሳኝ የሆነ ነገሮችን አድርጋለች። ከ609 ዓክክ አንሥቶ በባቢሎን ሥር እስከ ወደቀችበት እስከ 605 ዓክክ ድረስ ግብፅ ይሁዳን ትገዛ ነበር። በከርከሚሽ በግብፅ ላይ ባገኘችው ከፍ ያለ ድል ባቢሎን ይሁዳን መግዛት ጀመረች። ይሁን እንጂ ግብፅ የይሁዳን ተገዢነት ለማረጋገጥ ጥረት ማድረጓን ቀጠለች፤ ይኸውም ይሁዳ በተደጋጋሚ በባቢሎን ላይ እንድታምፅ በማበረታታት ነው። የግብፁ ፈርዖን ሖፍራ ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምን እንዳይከቡ ጥረት አድርጎ ነበር፤ ሆኖም አልተሳካለትም።

የሕዝቅኤል ትንቢቶች ይህን ታሪካዊ ሁኔትና የድርጊት ወጊዜ ቅደም ተከተሉን ያካተተ ነበር። የግብፅ ሰራዊት በሖፍራ መሪነት ወደ ፓለስቲና ያደረገው እንቅስቃሴ የንግሩን ሂደት ድንገት እንዲጣደፍ አድርጎታል። የሕዝቅኤል የመጀመሪያ መልእክት በግብፅ ፍጹም ባድማነት ላይ የተነገረ አጠቃላይ ትንቢት ነው፤ ይህም የሆነው በትዕቢቷና ለይሁዳ በሰጠችው አስተማማኝ ባልሆነ ድጋፍዋ ምክንያት ነው (29፥1-16)። በሦስተኛው ትንቢቱ (30፥20-26) ሕዝቅኤል በባቢሎን ሰራዊት ፈርዖን ሖፍራ ድል መሆኑን ይጠቅሳል፤ ይህም እግዚአብሔር በግብፅ ላይ ያወረደው ፍርድ ጅማሬ ብቻ ነው። በግብፅ ትዕቢትና ዕብሪት ምክንያት መላው አገር እንዳለ ይደመሰሳል፤ ይህም አሦር በታላቅ ኀይልዋ በነበረችበት ዘመን ሕዝቅኤል በምሳሌ ይገልጸው የነበረ ዕብሪት ነው። አሦር በእግዚአብሔር እንደ ተዋረደችው ሁሉ ግብፅም እንዲሁ ትወድቃለች (የሕዝቅኤልን አራተኛ መልእክት 31፥1-18 ላይ ይመ)። ነቢዩ የፍርድ መልእክቶቹን በማስከተል በግብፅ መፍረስ ላይ የቀረበውን የሐዘን እንጉርጉሮ ያሳያል (32፥1-16)። በግብፅ ላይ ያቀረበውን የፍርድ ንግሩን ማጠቃለያና የይሁዳ ምርኮኞች ወደ እግዚአብሔር በመመለስ የተሰጣቸውን ዕድል ተጠቅመው በሕይወት መኖር እንደሚችሉ የተሰጣቸውን ማስጠንቀቂያ በማቅረብ ሕዝቅኤል ትንቢቱን ይደመድማል (32፥17-33፥20)።

ሁለተኛው ትንቢት (29፥17-30፥19) ድርጊት ወጊዜ ቅደም ተከተሉን የተከተለ አይደለም፤ ሕዝቅኤል ለዋና ሐሳብ የነበረው ግድ መሰኘት ለድርጊት ወጊዜ ቅደም ተከተል ከነበረው ግድ መሰኘት የላቀ ነበር። በታኅሣሥ/ ጥር 588/587 ዓክክ (29፥1-16) ካቀረበው የመግቢያ ትንቢት በኋላ ይህን ድርጊት ወጊዜ ቅደም ተከተል የያዘ ሐሳብ በማቅረብ፣ ሕዝቅኤል የግብፅን የመጨረሻና ሙሉ በሙሉ መደምሰስ ለማሳየት ፈጣንና ሙሉ ሐሳብ ሰጥቶአል፤ ይኸውም በመጀመሪያ መልእክት እንደ ተነገረው ከ571 ዓክክ በኋላ በባቢሎናውያን የተካሄደው ነው።

ልክ እንደዚሁ የ571 ዓቅክ መልእክት (29፥17-30፥19) የተቀመጠው በግብፅ ላይ ከቀረበው የመግቢያ መልእክት በኋላ ነው፤ ይህም በጢሮስ ላይ ከቀረበው ፍርድ በግብፅ ላይ ወደ ቀረበው ፍርድ የሚያሸጋግር ሐሳብ ነው። ናቡከደነፆር ጢሮስን ለመቅጣት የፍርድ መሣሪያ ነበር፤ ግብፅ ጣልቃ ስለ ገባች ግን በጢሮስ ላይ ከተደረገው ውጊያ ምርኮን መሰብሰብ አልቻለም፤ እግዚአብሔር ግን በፈንታው ግብፅን ምርኮ አድርጎ ለባቢሎን እንደሚሰጥ ተናግሮአል። በመጨረሻም በግብፅ ላይ ሊወርድ የሚገባው ፍርድ መፈጸሙን መረዳት ከታቻለ፤ በስድስቱ መልእክቶች ውስጥ ያለውን የእያንዳንዱን ትንቢት ዝርዝር በተሸለ መልኩ መረዳት ይቻላል።

1. በግብፅ ላይ የተነገረው የመግቢያ የፍርድ ትንቢት (29፥1-16)

1-7 ፈርዖን በአባይ ወንዝ መካከል እንደሚተኛ አዞ (አውራ)፣ እግዚአብሔር እንደሚይዘው፣ ከአባይ ወንዝም ጐትቶ እንደሚያወጣው፣ እንዳሁም እንዲሞት በገላጣ መሬት ላይ እንደሚጣል አውሬ ተመስሎአል። በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ቃል “አውሬ” ወይም “አዞ” ተብሎ ሊተረጐም ቢችልም፣ ከግብፅ ባህልና ሃይማኖት አኳያ ሲታይ ምስያው በእጅጉ ግብፅን የሚመለከት ነው ተብሎ ቢታይ የሚሻል ይመስላል። በአባይ ወንዝ “አዞ” እጅግ የሚፈራ ፍጥረት ነበር። አብዛኛውን ጊዜ በመንጋጋው ላይ መንጠቆ እንዲገባ ተደርጎ ወደ ምድር ይጐተትና ይታረዳል። በአዞ የተመሰለው ጣዖት የግብፅ ጠባቂ አምላክ ነው ተብሎ ይታመን ነበር።

በምስያው አዞ ፈርዖንን፣ የግብፅ ጠባቂና የአባይ የበላይ ተቈጣጣሪ የሆነውን ማለትም የግብፅ ሁሉ የበላይ የሆነውን ሰው የወከለ ነበር። ይህም ሖፍራ ስለ ራሱ የነበረውን አመለካከት ማለትም ዕብሪቱንና ማንነቱን የሚገልጽ ነው። በዘመነ መንግሥቱ በቆጵሮስ ላይ ስራዊቱን አዘመተ፤ ጋዛንና የሲዶንን ከተማ በመክበብ ያዛቸው (ከኤር 47፥1 ጋር ያነጻ)፤ በባሕር ላይ በነበረ ውጊያ በጢሮስ ላይ ድልን አገኘ፤ በፍልስጥኤምና በፊንቄም ላይ ራሱን የበላይ አደረገ። እንዲህ ዐይነቱ ትዕቢት በዚህ መልእክት ላይ ከሰፈረው ውግዘት ጋር የሚስተካከል ነው፤ ፈርዖን አባይም ሆነ ግብፅ የእርሱ እንደ ሆኑና እንዲያውም ለራሱ ክብር የፈጠራቸው እንደ ሆነ ያስብ ነበርና። ይህ ትዕቢት ባቢሎን ኢየሩሳሌምን ለመያዝ በተንቀሳቀሰችበት ጊዜ ባደረገው ጣልቃ ገብነት ታይቶአል፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ይህን ጣልቃ ገብነት ወደ ሌላ አቅጣጫ እንዲዞር አደረገው።

አዞን የመያዝ ምስያ እግዚአብሔር በፈርዖን ላይ የሚያመጣውን ፍርድ ውብ በሆነ መልክ ይገልጻል። ከሥልጣኑና ከትዕቢቱ ተጐትቶ በመውጣት ለምድር አራዊትና ለሰማይ ወፎች ምግብነት ዐልፎ ይሰጣል። በፈርዖኖች ዘመን እጅግ አስፈላጊ የነበረውን የነገሥታትን የቀብር ሥርዐት የማግኘ ት ዕድል አይኖረውም፤ ይህም እጅግ አሳዛኝ የሆነ ዕድል ነው። ክሱን ሰፋ በማድረግ ግብፃውያንን ሁሉ ያጠቃልል ዘንድ (“ዓሣ”) ተብሎ ተጠቅሶአል፤ ግብፃውያን እንደ ሕዝብ የእስራኤልን መንግሥት መደገፍ አልፈለጉም ነበርና። ይልቁን የሽምበቆ በትር ዐይነት በመሆን እስራኤል ስትደገፋቸው በመሰንጠር በእጅጉ ያቈስሏት ነበር (ከኢሳ 36፥6 ጋር ያነጻ)።

8-16 ፈርዖንና መላዩቱ ግብፅ ፈጽሞ ይጠፋሉ፤ ከትዕቢታቸው የተነሣ እግዚአብሔር ሰይፍን ሲያመጣ ምድሪቱ ባድማ ትሆናለች። በምድሪቱ ላይ የሚመጣው ባድማነት መላዩቱን አገር ከሚገዶል እስከ ሰሜን ምሥራቅ ሶቬር ባሕር ዳርቻ ድረስ ጉዳት የሚያደርስ ይሆናል (ከመጀመሪያው ፏፏቴ አጠገብ ከምሥራቁ የባሕር ዳርቻ ከኤሌፋንታይን ደሴት ባሻገር በዛሬው አስዋን ግድብ አጠገብ ያለው ስፍራ ሁሉ ማለት ነው)። እነዚህ ቦታዎች የጥንታዊቷ ግብፅ የሰሜንና የደቡብ ድንበር ምልክቶች ናቸው። ፍርዱ እስከ ኩሽ ምድር ማለትም እስከ ዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ማለትም ከአባይ በሁለተኛውና በሦስተኛው ፏፏቴ መካከል እስካለው ስፍራ ድረስ ይደርሳል ማለት ነው። በአባይ ወንዝ ዳርቻ ያሉ ጀረቶችም ሆኑ ግድቦች ጉዳት ይደርስባቸዋል (ከ30፥12፤ 32፥13-14 ጋር ያነጻ)።

ግብፅ ለአርባ ዓመት ያህል ባድማ ስትሆን ነዋሪዎቿ ሁሉ በባቢሎናውያን አገዛዝ ሥር ባሉ አገሮች በሙሉ ይበተናሉ። የግብፅ ዕጣ ፈንታ የይሁዳ ዕጣ ፈንታ ድግግሞሽ ዐይነት ይሆናል (በ4፥6 ከተጠቀሰው አርባ ዓመት ተመሳሳይነት ጋር ይህን ያነጻጽሩ)። በባቢሎናውያን ዜና መዋዕል እንደ ተገለጸው ግብፅ በባቢሎናውያን ሥር የወደቀችው በ568 ዓቅክ ከሆነ፣ የግብፅ የአርባ ዓመት “ምርኮ” በፋርሶች ይፈጸማል ማለት ነው። ባቢሎናውያን ያፈናቀሉአቸውን ብዙ ሕዝቦች ፋርሶች ወደ የአገራቸው እንዲመለሱ ስላደረጉ፣ ይህ ትክክለኛ አገላለጽ ይሆናል። በጥንት ታሪክ ይህን የሕዝብ መበተን የሚገልጽ ቀጥተኛ አረፍተ ነገር ባለመኖሩ ይህ ሁኔታ ፈጽሞ አልነበረም ማለት አይቻልም። የእግዚአብሔር ቃል ከግምታችን ወይም ካለመረዳታችን ይበልጥ ትኩረት የሚሰጠው ነው።

ከአርባ ዓመት በኋላ ግብፅ መልሳ ስትቋቋም፣ በጳጥሮስ ወይም በላይኛው ግብፅ ላይ ሰዎቿን ታሰፍርበታለች፤ ይህም ምድር በዛሬዪቱ ካይሮና አስዋን መካከል ያለው ነው። ከእንግዲህ በኋላ ግብፅ ፈጽሞ ታላቅ መንግሥት አትሆንም። ምንጊዜም ደካማና ዝቅ ያለች አገር ሆና ትኖራለች። እስራኤልም ግብፅን ከልብ ተማምና መኖርን ታቆማለች። እስራኤል ወደፊት ወደ ግብፅ በተመለከተች ቊጥር ባለፈው ዘመን ርዳታ ለማግኘት ስትል ወደ ግብፅ የተመለከተችበትን ኀጢአት እንድታስታውስ ትደረጋለች።

የእግዚአብሔር የፍርድ መልእክቶች ዐላማ ምንጊዜም ቢሆን አንድ ዐይነት ነው። የተፈረደባቸው ሁሉ እርሱ እግዚአብሔር ጌታ፣ እውነተኛ አምላክና የእስራኤል አምላክ መሆኑን እንዲያውቁለት ይፈልጋል።

2. የእግዚአብሔር ቀን፤ የግብፅ ፍርድ ማጠቃለያ (29፥17-30፥19)


ሀ. ግብፅ በጢሮስ ላይ ባካሄደችው ትርፍ የሌለው ዘመቻ ባቢሎን ያገኘችው ካሣ (29፥17-21)

17-21 በጢሮስ ላይ የተወሰነው የእግዚአብሔር ፍርድ እንዲሟላ፣ ናቡከደነፆርና የባቢሎን ሰራዊት ጢሮስን ለዐሥራ ሦስት ዓመት ከበቡ። የተገኘው አነስተኛ ታሪካዊ መረጃ ግብፅና ጢሮስ በፈርዖን ሖፍራ ሥር የትብብር ስምምነት አድርገው እንደ ነበር ያመለክታል። ረዥም ጊዜ የፈጀው የጢሮስ ከበባ ምናልባት ጢሮስ ከግብፃውያን ከምታገኘው ርዳታ የተነሣ ሳይሆን አይቀርም። በእንዲህ ዐይነቱ ድርጊት ሖፍራ ከእግዚአብሔር ዐላማዎች በተፃራሪ እንደ ተጓዘ መረዳት ይቻላል። ከበባው በግብፅ ድጋፍ የተራዘመ ብቻ ሳይሆን፣ ግብፅ በባሕር ላይ ንግድ ለጢሮስ ታደርገው የነበረው ርዳታ፡- ጢሮስ ያለምንም ሥጋት ያላትን ሀብት እንድታሸሽ አግዞአታል። ጢሮስ በ573 ዓቅክ ተሸንፋ እጅ ስትሰጥ፣ አሸናፊዋ ባቢሎን ከዚህ ረዥም ከበባ ያገኘችው ጥቅም አልነበረም። ስለዚህ በመጨረሻ ላይ ስለ ግብፅ በተጠቀሰው በዚህ የሕዝቅኤል ንግር ናቡከደነፆር በጢሮስ ከበባ ባጣው ብዝበዛ ምትክ ግብፅን እንደ ካሣ እንደሚሰጠው እግዚአብሔር ቃል ገብቶአል። “የሁሉም ራስ ተመልጦአል፤ የሁሉም ትከሻ ተልጧል” የሚለው አባባል በከበባው ጊዜ ከባድ ጭንቆችን በራሳቸውና በትከሻቸው ላይ መሸከማቸውን የሚያሳይ ነው። ናቡከደነፆር የእግዚአብሔር ፍርድ በጢሮስ ላይ እንዲፈጸም በማድረጉ የግብፅን ከፍተኛ ሀብት ሁሉ በማጋዝ የሰራዊቱን ደመወዝ ይከፍላል፤ ለራሱም ታላቅ ዋጋን ይቀበላል።

ለመጀመሪያ ጊዜ በግብፅ ላይ የእግዚአብሔር የፍርድ መሣሪያ ማን እንደ ሆነ ተገለጠ፤ ይኸውም በባቢሎን በናቡከደነፆር አመራር ሥር በባቢሎን የተፈጸመ መሆኑን የሚያሳይ ነው (ከኤር 43፥8-13 ጋር ያነጻ)። ናቡከደነፆር በ562 ዓቅክ ስለ ሞተ በናቡከደነፆር ሰራዊት አማካይነት ግብፅ ባድማ እንደምትሆን የተነገረው ይህ ትንቢት ከዚያ በፊት የተፈጸመ መሆን አለበት። ታሪካዊ ማስታወሻዎች ባቢሎን ግብፅን የወረረችበት ጊዜ 568/567 ዓቅክ እንደ ነበረ ያመለክታሉ።

በምርኮ የነበሩ እስራኤላውያን እንዲበረቱና እንዲጽናኑ ለማድረግ እግዚአብሔር ባቢሎን ግብፅን ያሸነፈችበትን ሁኔታ ተጠቅሞበታል። ምንባቡ በግብፅ ላይ የወረደው ፍርድ እንደሚገባት ያሳየ ሲሆን፣ በናቡከደነፆር ወረራ ጊዜ ለእስራኤል ቤት “ቀንድ” እንደሚበቅል አመልክቶአል። እግዚአብሔር በእነዚህ ትንቢቶችና በአብራሃማዊው ኪዳን መሠረት (ዘፍ 12፥3) በእስራኤል ጠላት በግብፅ ላይ ፍርዱን ሲፈጽም፣ በዚሁም እስራኤል የእርሱን ታማኝነት ስታስተውል እርሷ

መቀበል የነበረባትን ብርታትና (ከ0መት ማብራሪያ ጋር ያነጻ) ማበረታቻ ትእምርቱ ማመልከት አለበት። በዚህ ጊዜ ሕዝቅኤል አፉን ከፍቶ የእግዚአብሔርን ዐላማና አሠራር በበለጠ ነጻነት ለምርኮኞቹ መናገር ይችላል፤ ምርኮኞቹ አሁን ሊሰሙት ዝግጁ ይሆናሉና። በእነዚህ ሁነቶች አማካይነት እስራኤላውያን በታማኝነት እነዚህን ታላላቅ ነገሮች ይፈጽም የነበረው አምላካቸው ጌታ እንደ ሆነ ያውቃሉ።



ለ. ናቡከደነፆር ግብፅን መውረሩ (30፥1-19)

1-19 "የእግዚአብሔር" ቀን የሚለው እግዚአብሔር ልዩ ሥራ የሚሠራበትን አንድን የተወሰነ ጊዜ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። "የእግዚአብሔር ቀን" የሚለውን ለመግለጥ ዐውዱ በተለየ ሁኔታ የሚያሳየው ናቡከደነፆርን የፍርድ መሣሪያ በማድረግ እግዚአብሔር በባቢሎን አማካይነት በግብፅ ላይ የፈረደውን ፍርድ ነው። በተጨማሪም ይህ ሁነት "የግብፅ ቀን" ተብሎ ተጠርቶአል፤ ይህም ፍርዱ በግብፅና በገባሮቿ ላይ የተፈጸመ ብቻ መሆኑን የሚያመለክት ነው። ይህ የሚፈጸመው እስራኤልን በሆነ መልኩ በረገሙ አሕዛብ ላይ ባቢሎን የእግዚአብሔርን ፍርድ በምታፈስበት ለአሕዛብ የጥፋት ቀን ነው በተባለው ነው (ከ25፥32፤ ከኤር 25፤27፤ 45-48 ጋር ያነጻ)።

የግብፅ የእግዚአብሔር ቀን የግብፅ የመጨረሻ የፍርድ ቀን ሲሆን፣ በታሪኳ ውስጥ የሚፈጸም የጨለማ ቀን ነው ("የደመና ቀን")። በናቡከደነፆር ሰይፍ ፊት የግብፅ ዕብሪት የሞላበት ብርታት ሲሟሽሽ፣ ሕዝብዋ እጅግ ይፈራሉ። ብዙዎቹ ይታረዳሉ። ከብዙ ሕዝብ ጋር የግብፅ ብልጽግና ወደ ባቢሎን ተማርኮ ይወሰዳል። ልዑል ወይንም መሪ እንኳ በአገሪቱ አይቀርም። ባቢሎናውያን ፍጹም ድልና ብልጽግና ለማግኘት በሚፈጽሙት ከፍተኛ ተጋድሎ፣ የግብፅ አማልክትና አያሌ የጣዖት ምስሎች ሙሉ በሙሉ ይሰባበራሉ።

በስተ ሰሜን ካለው ከሚግዶል አንሥቶ በደቡብ እስካለው ሲን ድረስ መላዪቱ ምድር ባድማ ትሆናለች። ከላይኛው ግብፅ እስከ ዛሬዪቱ ካይሮና አስዋን መካከል ያለው ጳጥሮስ የተባለው ምድር ምድረ በዳ ሆኖ ይቀራል። የሚከተሉት የግብፅ ዋና ዋና ከተሞች ተገቢውን የባቢሎንን ቅጣት ይቀበላሉ፤ እነርሱም፦ በሰሜን ምሥራቅ ባሕር ደለል ያለችው ጸአን፣ ለረኟርም ጊዜ የቄየችው የደቡባዊ ግብፅ ዋና ከተማ ቱብስ፣ በሰሜን ምሥራቅ ወሰን ላይ ያለችው በሕዝቅኤል ዘመን የነበረው የገዢው የ26ኛው ሥርወ መንግሥት መኖሪያ የነበረችው ፔሉሲየም፣ የሃይማኖት ማእከል የነበረችው ሄልዮፖሊስ ቡባስቲስና ጣኔዎስ (ከኤር 43፤7-9 ጋር ያነጻ) ናቸው። የአባይ ወንዝ ጅረቶችም ይደርቃሉ (ከ32፥13-14 ጋር ያነጻ)።

የሚከተሉት የግብፅ ተባባሪዎችም በባቢሎን ሰይፍ ይወድቃሉ፤ እነርሱም ኩሽ (ወይም ኢትዮጵያ)፣ በምዕራብ አናቶሊያ ያለችው ልድያ ወይም የዛሬዪቱ ቱርክ፣ ዐረቢያና ሊብያ ናቸው። የይሁዳ ሰዎች እንኳ ማለትም ከነዶልያስ ግድያ ለማምለጥ ወደ ግብፅ የሸሹት "የኪዳኑ ሕዝቦች" በባቢሎናውያን ወረራ በእጅጉ ይሠቃያሉ (2ነገ 25፥23-26፤ ኤር 43)። የእግዚአብሔር ዐላማ መፈጸም ቢኖርበትም እንኳ ፍርዱ አጠቃላይና በጣም አሰፈሪ ይሆናል። ይህ ፍርድ የእግዚአብሔር ምሕረት መግለጫ ነው፤ በዚህም አማካይነት በመጨረሻ እርሱ እግዚአብሔር የእስራኤል አምላክ ብቻውን እውነተኛ አምላክ መሆኑን ግብፃውያን እንዲያውቁ ያደርጋልና።

3. የተሰበረው የፈርዖን ክንድ (30፥20-26)

20-26 ሕዝቅኤል እንደ ገና ድርጊት ወጊዜ ቅደም ተከተል ወደ ነበረው የመልእክት ሂደት ተመልሶአል (ቁ. 1)። ፈርዖን ሐፍራ ባቢሎን ኢየሩሳሌምን ለመክበብ የምታደርገውን እንቅስቃሴ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በ588 ዓክክ አካባቢ ለማስተጓጎል ሞክሮ ነበር (ኤር 34፥1፡ 21-22፤ 37፥5፡9)። ከከበባው ነጻ እንሆናለን የሚለው የአይሁድ ተስፋ ከፍ ብሎ ነበርና። ይሁን እንጂ ሐፍራ አልተሳካለትም። ባቢሎናውያን እርሱንና ሰራዊቱን አሸነፉ፤ የግብፅንም ሰራዊት ወደ አገሩ ከመለሱ በኋላ ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን የመክበቡንና የመያዙን እንቅስቃሴ እንደ ገና ዐደሰ። በእነዚህ ጥቅሶች የተገለጠው ትንቢታዊ መልእክት በጥቂት ወራት የተሰናከለውን የሐፍራን ጣልቃ ገብነት የተከተለ ነው (የካቲት/ መጋቢት 587 ዓክክ)። የሐፍራን ክንድ የሰበረ መሆኑን እግዚአብሔር ተናገረ። የሚታጠፍና የሚዘረጋ ክንድ በግብፅ የተለመደ የፈርዖን ብርታት ምልክት ነው። ስለዚህ የሐፍራ መሸነፍ የፈርዖንን ክንድ ሰብሬአለሁ በሚለው ሐረግ በሚገባ ተወክሎ ነበር። የሐፍራ ክንድ እንዳይድን ሆኖ ተሰንጥቆ ነበር በማለት ሕዝቅኤል ምስያውን ይበልጥ ከፍ አድርጎት ነበር።

እግዚአብሔር በባቢሎናውያን አማካይነት በግብፅ ላይ ለሚያመጣው አጠቃላይ ውድመት፣ ይህ የግብፃውያን ፈርዖን የመጀመሪያ መሸነፍ የፍርዱ መግቢያ ነው። በአንጻሩ እግዚአብሔር የናቡከደነፆርን ክንድ በማጠንከር የእግዚአብሔርን ሰይፍ በእጁ አስገብቶ የግብፅን ዐቅም ሙሉ በሙሉ ለማጥፋት እንዲችል ያግደዋል። ሐፍራ ከቶ ሰይፍ እንዳይዝ በማድረግ ናቡከደነፆር የፈርዖንን ሁለት ክንዶች በትእምርት ይሰብራል። ይህ የሆነው በ568 ዓክክ ነበር። እንደ ገና በዚህ በመጨረሻው መፈራረስ ግብፅ በአሕዛብ መካከል እንደምትበተን እግዚአብሔር እንደ ገና ያሳስባል (ከ29፥12፤ 30፥17-18 ጋር ያነጻ)። ውጤቱ እንደ ገና በተጠናከረ መልኩ ተገልጸአል፤ ይኸውም ይህንን ፍርድ ያመጣው እግዚአብሔር መሆኑን ግብፃውያን የሚያስተውሉ መሆናቸው ነው።

4. የግብፅ ውድቀት ከአሦር ውድቀት ጋር መነጻጸሩ (31፥1-18)

1-9 ይህ ውብ የሆነ ቅኔያዊ መልእክት የተላለፈው የግብፅ ብርታት መሰበሩን በተመለከተ የተሰጠው ቀደም ያለው ትንቢት ከተላለፈ ከሁለት ወር በኋላ ነበር (ግንቦት/ሰኔ 587 ዓክክ)። አሁንም ቢሆን ግብፅ በትዕቢት የተያዘች መሆኗን መልእክቱ ይናገራል። ሕዝቅኤል በምስያው ከታወቁት ዛፎች ሁሉ እጅግ

ረኽርም የሆነውን የሊባኖስን ዝግባ ከአሦር ጋር በማመሳሰል፣ እርሷም በቅርቡ የወደቀች መሆኗን ይናገራል (612 ዓቅክ)። ቀጥሎም ግብፅ ከአሦር ጋር ተነጻጽራለች። ታላቋ ዝግባ ማለትም አሦር ውሃ በደንብ ጠግባ ነበር፤ ይህም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የጤግሮስና የኤፍራጥስ ወንዞች ታላላቅ የውሃ ምንጮቿ እንደ ነበሩ የሚያመለክት ነው። ግብፅም እንዲሁ ከአባይ ወንዝ በምታገኘው የማያቋርጥ አቅርቦት ባልተናነሰ ሁኔታ ትመካ ነበር። ዝግባዋ ማለትም አሦር ከሌሎች ዛፎች ሁሉ ማለትም ከአሕዛብ ሁሉ እጅግ ረኽርም፤ ከሌሎቹ ዛፎች እጅግ ውብ እንዲሁም በኤድን የአትክልት ስፍራ በመጀመሪያ ከነበሩት ልዩ ልዩ ተክሎች እንኳ ይበልጥ ውብ ነበረች። ማንኛውም የሰማይ ዖፍ ጎጆውን በእርስዋ ላይ ይሠራ፣ እያንዳንዱም አውሬ ግልገሎቹን ከቅርንጫፎችዋ ሥር በመውለድ በዚያ ጥላ ሥር ይጠለል ነበር። እነዚህ የሰማይ ወፎችና አራዊት የሚወክሉት በአሦር መንግሥት ሥር ያሉትንና በዚሁ መንግሥት የሚደገፋትን መንግሥታት ነው (ከዳን 4፥10-12፡ 19-22፤ ከማቴ 13፥31-32 ጋር ያነጻ)። አሦር ምናልባት በታሪክ ውስጥ በዚህ ደረጃ የምትጠቀስ ታላቅ መንግሥት ሳትሆን አትቀርም።

10-17 አሦር ከታላቅነትዋ ማለትም ከፍ ከማለትዋ የተነሣ ታበየች። በዚህም ምክንያት ዝግባዋ (ማለትም አሦር) ሌሎችን መንግሥታት በጭካኔ እንደ ገዛች እርሷም እንድትገዛ ለአሕዛብ ሁሉ ገዥ ለናከደነየር ዐልፋ ተሰጠች። እጅግ ጨካኝ በሆኑት የውጭ መንግሥታት ተቁርጣ ተጣለች። አሦር ውሃ እንዳታገኝ እግዚአብሔር ከለከላት። ከወደቀችም በኋላ የማትጠቅም ከንቱ ሆነች። አሕዛብ ሁሉ (ማለትም ሌሎች ዛፎች የሰማይ ወፎችና የዱር አራዊት) በዝግባው መደምሰስ አለቀሱ፤ ተንቀጠቀጡም። በዚያ ዘመን የነበረ ማንኛውም መንግሥት አሦር ከደረሰችበት ከፍታ ከቶ መድረስ አይችልም ነበር።

18 ግብፅ በዘመኗ ከነበሩት መንግሥታት የበለጠ ግርማና ታላቅ ክብር እንዳላት ብታስብ፣ እግዚአብሔር እርሷንም እንዲሁ እንደምትወርድ ያሰስባታል። ያልተገረዘ ባዕድ ያለቀብር ሥርዐት በውርደት እንደሚሞት እርስዋም "ትጋደማለች"፤ ይህ ፍርድ በንጉሣዊ የቀብር ሥርዐታቸው ለሚኩራሩና በዚህም ባዕዳንን ለሚንቁ ግብፃውያን አስደንጋጭ ሐሳብ ነው። እግዚአብሔር አሦርን በዚህ መንገድ የሚያዋርድ ከሆነ ወደ አሦር ታላቅነት በምንም መልኩ ልትጠጋ የማትችለው ግብፅ ራሷ ልትወድቅ እንደምትችል ርግጠኛ ልትሆን ትችላለች።

5. ስለ ግብፅ የወጣ ሙሾ (32፥1-16)

1-10 በባቢሎን ያሉ ምርኮኞች ከሰባት ወር በፊት ኢየሩሳሌም መውደቋን ካወቁ አሁን ሁለት ወር ዐልፎአል። እግዚአብሔር እንዳለ፣ እንዲሁም እንደ ተናገረው ኢየሩሳሌምን በማጥፋት ታማኝ መሆኑን መረዳት ሲጀምሩ፣ እንደ ገናም እግዚአብሔር እንደ ተናገረው እነዚህን የአሕዛብ መንግሥታት ይቀጣ አይቀጣ እንደ ሆነ ምናልባት ሳያስቡ አልቀረም። በሌላ በኩል ግብፅ የኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ውድቀት ተመልክታ ነበር፤ ይሁን እንጅ በመትረፍዋና በኀይሏ በመመካት በሌሎቹ ውድቀት ዕሠይ ሳትል አልቀረችም። ያለዚያ ግብፃውያን እግዚአብሔር እኛን ተከታትሎ አይፈርድብንም ይላሉ፤ ምርኮኞቹም እግዚአብሔር ለቃሉ ታማኝ የመሆኑን ዐዲስ ግንዛቤያቸውን ይጠራጠራሉ፤ ሕዝቅኤል ይህን ስለ ግብፅ ያወረደውን ሙሾ በመጋቢት 585 ዓቅክ አስተላለፈ።

በአሕዛብ ላይ በተነገሩት ባለፉት የፍርድ ትንቢቶች ውስጥ ሕዝቅኤል ዘወትር ከፍርድ መልእክቱ በኋላ ሙሾን ያስከትል ነበር። ስለዚህ ሦስት የፍርድ ንግሮችን ካስተላለፈ በኋላ፣ ሕዝቅኤል የሐዘን እንጉርጉሮን ጻፈ። ግብፅ እንደ ሞተች በመቍጠር የሐዘን እንጉርጉሮው የሚሰማው ግብፅ ፈጽሞ መጥፋቷን በሚመለከቱት "የሕዝቦች ሴት ልጆች" ይሆናል።

በግብፅ ላይ የሚወርደው ሙሾ፣ በግብፅ ከንቱ ትዕቢት ላይ አጽንዖት በማድረግና በፍርዱ ዕጣ ፈንታ ላይ ዋይታ በማሰማት በመሠረቱ የፍርድ መልእክቶች ክለሳ ነው። እንደ ገናም ዕጥፍ ምስያ የፈርዖንን ግትር ትዕቢትና ዐቅመ ቢስ ጉልበት አጉልቶ ያሳያል። ሐፍራ በዚህ ስፍራ የተመሰለው በደቦል አንበሳና የአባይን ወንዝ በመምታት እንደሚያደፈርስ አዞ ነው። አዞው በመረብ ተይዞ የሰማይ ወፎችና አራዊት እንዲበሉት በሜዳ ላይ ይዘረጋል። የአዞው መታረድ እጅግ ታላቅ ስለሚሆን ማንኛውንም ሸለቆና ተራራ የሚሞላ ይሆናል። ምድሪቱን ታላቅ ጨለማ እንደ ሸፈናት ዐይነት ይሆናል፤ ይህም የግብፅ ታላላቅ የፀሓይ አማልክት ፈጽሞ ሊረዱ የማይችሉ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው። የሰማይ ከዋክብት ጎይል መዳከም ከምድር መናወጥ ሁነት ጋር የተለመደ ክሥተት ነው። ይህን የልቅሶ ሙሾ ያወረዱ መንግሥታት ግብፅ በመካከላቸው በመውደቋ እጅግ ይደነግጣሉ ይሸበራሉም።

11-16 በግብፅ ላይ የሚደርሰው ጭፍጨፋ ከሰዎች ሁሉ እጅግ ጨካኞች በሆኑት በባቢሎናውያን እጅ የሚፈጸም ነው። ታላቁን አባይን ጨምሮ ማንኛውም ሰው እንዲሁም ማንኛውም ቦታ በዚህ የሚጐዳ ይሆናል። ሕይወት ሁሉ ሲጠፋ የአባይ ወንዝ ብድግ ብደግ ማለቱን ያቆማል፤ ልክ እንደ ዘይትም በጸጥታ ይፈሳል። በዚህ ጊዜ ብቻ ነው የግብፅ ትምክሕት የሚቆመው። እግዚአብሔር ለግብፅ ምሕረቱን የሚያሳየው ይህን ያህል ነው፤ ይኸውም ይህን ከባድ ፍርድ በማምጣት እነርሱም በመጨረሻ እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ መሆኑን ተረድተው ወደ እርሱ እንዲመለሱ ነው።

6. ሕዝቅኤል ስለ ግብፅ ያወጣው ሙሾ ማጠቃለያ (32፥17-32)

17-32 ይህ ሕዝቅኤል ስለ ግብፅ የተናገረው የመጨረሻ ትንቢት ነው፤ በሌሎች መንግሥታትም ላይ የተናገረውን ንግር የሚያጠቃልል ነው (ምዕ 25-32)። ይህ የተሰጠው በመጋቢት 585 ዓቅክ ነበር። ግብፃውያን ከእነርሱ ቀድመው እንደ ነበሩት ታላላቅ መንግሥታት ወደ ሞት ጕድጓድ ስለሚወርዱ ሕዝቅኤል ለእነርሱ ማልቀስ ነበረበት። ግብፅ አስቀድሞ ካንቋሸሸቻቸው ያልተገረዙ መንግሥታት ይልቅ የተለየ እንክብካቤ የሚደረግላት አትሆንም። እርሷም ልክ እንደ ሌሎች አገሮች ወርደት የሞላባትን የአረመኔዎችን ሞት ትሞታለች። እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ሽብሩን ያመጣባቸዋል፤ እንዲሁም በዚህ ዓለም በጭካኔ በሚነግ በማንኛውም መንግሥት ላይ ሽብሩን በማምጣት ይቀጥላል። በፍጥነትም በባቢሎናውያን አማካይነት ሽብሩን በግብፅ ላይ ያመጣው በዚህ ምክንያት ነበር።

ረ. ሕዝቅኤል ለምርኮኞች የሰጠው ማስጠንቀቂያ (33፥1-20)

1-20 ይህ በግብፅ ላይ የቀረበው የኋለኛው ግማሽ የሕዝቅኤል ማጠቃለያ ትንቢት ቀደም ያሉትን ሁለት መልእክቶች የሚያስተጋባ ነው፤ እነርሱም ሕዝቅኤል ጉበኛ እንዲሆን የተሰጠው ተልእኮ (ቍ. 3፤ ምዕ 3) እና ሰው በየግሉ ሊጠየቅበት የሚገባውን ኀላፊነት በተመለከተ የሰጠው ምክር (ቍ. 8፤ ምዕ 3፤ 18) ናቸው። እርሱ ራሱ በታማኝነት የእስራኤል ጉበኛ በመሆን ኀላፊነቱን ተወጥቶአል (ቍ. 9)፤ ይኸውም እግዚአብሔር በአካባቢው ሊያመጣ ስላለው ፍርድ ማስጠንቀቂያን በመናገር ያከናወነው ነው (ምዕ 4-24)። ይህን መልእክት ካቀረበበት ከሦስት አራት ወር በፊት፣ ሕዝቅኤል ሕዝቡን በመጨረሻ እግዚአብሔር ወደ ምድራቸው እንደሚመልሳቸው በሚያሳዩ የተስፋ መልእክቶች አጽናንቶአቸዋል (33፥21-39፥29)። ስለ ፍርድ የተነገረውን ማስጠንቀቂያ አልሰሙም፤ ስለሆነም ኢየሩሳሌምና ይሁዳ ዐመድ እስኪሆኑ ድረስ ራሳቸውን በምርኮ ውስጥ አገኙት። ሕዝቅኤል ኀላፊነቱን የተወጣ የእግዚአብሔር ጉበኛ በመሆኑ፣ በአገሪቱ ስለ ደረሰው ውድመትና ሕዝቡ በምርኮ ስለ መወሰዱ ከተጠያቂነት ነጻ ነው። ማስጠንቀቂያውን ባለመቀበላቸው የይሁዳ ሕዝብ ሊወቅሡ የሚችሉት ራሳቸውን ብቻ ነው። ስለዚህ ሕዝቅኤል አንድ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ለምርኮኞቹ ሰጠ፤ ይኸውም አሁንም ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ! የሚለው ነው። ቢያንስ ቢያንስ ምርኮኞቹ ይህ የእግዚአብሔር ፍርድ የመጣባቸው በአባቶቻቸው ኀጢአት ምክንያት ሳይሆን፣ በራሳቸው ኀጢአት ምክንያት እንደ ሆነ ያውቃሉ (ከምዕ 18 ጋር ያነጻ)።

ሕዝቅኤል ምርኮኞችን ለማበረታታት ፈለገ። ከበደል የተነሣ ሰው በመሞቱ እግዚአብሔር ደስ አይሰኝም። በተቃራኒው እግዚአብሔር ደስ የሚሰኘው ከኀጢአት በሚመለሱ፣ በሙሴ ኪዳን መሠረት መንገዱን በሚከተሉና ሕያዋን በሆኑ ሰዎች ነው። እያንዳንዱ ግለሰብ ስለ ጽድቁም ሆነ ስለ በደሉ በግሉ ተጠያቂ ይሆናል። አንድ ሰው ጻድቅ መሆኑ ቢነገርለት በግሉ እግዚአብሔርን ለመከተል በመወሰኑ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ሰው በደለኛ ነው ቢባል፣ እግዚአብሔርን በመቃወም የግል ፍላጎቱን ለመከተል በመወሰኑ ነው። አንዳንድ አይሁድ የእግዚአብሔር መንገዶች ተገቢ ያልሆኑና ትክክለኛነት የሚጐድላቸው ይመስሏቸው ነበር። ነገር ግን የእግዚአብሔር መንገዶች ምንጊዜም ተገቢና ትክክለኛ ናቸው፤ እርሱ ስለ አንድ ሰው ኀጢአት ሌላውን አይወቅሥምና። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ሥራው መጠን ትክክለኛውን ፍርድ ይሰጠዋል።

፬. ሊዳኑን በታማኝነት የሚጠብቀው አምላክ የወደፊት በረከቶች (33፥21-48፥35)

አብዛኛዎቹ የወንጌል አማኞች ተርጓሚዎች “ቃል በቃል ትርጕም” የሆነውን ሰዋስዋዊ - ታሪካዊ ሥነ ፍታቴን ይጠቀማሉ። ይሁን እንጂ ያ ሥነ ፍታቴ በሌሎች የወንጌል አማኞች ተርጓሚዎች ደግሞ በተለያየ አመለካከት ይታያል። አንዳንዶች “ቃል በቃል” ትርጕም ሲባል “ጥሬ ትርጉም” ነው ብለው ያስባሉ፤ ይኸውም ጽሑፍን በቀመ ማየት ነው። ቀጥተኛ ንባብ በማየት ትርጕምን ይሰጣሉ (ይህ ብዙውን ጊዜ ዘይቤያዊ አነጋገሮችን ከትርጓሜ ውጭ በማድረግ የሚሰጥ ትርጕም ነው) ብለው ያስባሉ። ሌሎች ደግሞ ቃል በቃል ትርጓሜን የሚረዱት ዘይቤያዊ አነጋገሮችን፣ ታሪካዊ እይታን፣ ዐውዳሚ ጥናትን፣ ቀጣይነት ያለው መገለጥን፣ የእምነት ምስስሎሽን ወዘተ ይፈቅዳል ይላሉ። ሌሎች ደግሞ “ቃል በቃልን” የሚረዱት የትንቢተ መልእክትን ትእምርትና ዘይቤያዊ አነጋገርን ለማየት ቀጥተኛ በሆነ መንገድ መጽሐፍ ቅዱስን ቃል በቃል እንደ ማንበብ አድርገው ነው። ብዙዎቹ የወንጌል አማኞች ባለማቋረጥ ቃል በቃል የሆነውን ሥነ ፍታቴ ቢጠቀሙም ሆነ ሌሎቹ ደግሞ ይህን ባይጠቀሙ ይህ መጽሐፍ የተከተለው የፍካሬ ወይም የሐተታ አካሄድ በዐጭሩ ዝርዝሩ ቀርቦአል።

ይህ ትርጓሜ ከምዕ 33-48 ያለውን ጽሑፍ ቀጥታ በማንበብ በታሪክ፣ በዐውድ፣ በዘይቤያዊ አነጋገር፣ በእምነት ምስያ፣ ቀጣይነት ባለው መገለጥ ወዘተ አንጻር ያቀርበዋል። የመጽሐፉ ሐሳብ ፍሰት አጽንዖት የተሰጠው ከመላው የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖናና ዋና ዋና ሐሳቦቹ ጋር በተያያዘ መልኩ ነው። አቡቀለምሲሳዊ ራእዮች የሚታዩት አያሌ ትእምርቶችንና ብዙ እውነታዎችን እንደ ያዙ ተደርገው ነው። በራእዮቹ ውስጥ ያሉ የመለኮታዊ ተርጓሚዎች ትርጕሞች በተከታታይ ቀርበዋል። እነዚህ ተርጓሚዎች ትእምርቶችን ተርጕመዋል (ከምዕ 37 ጋር ያነጻ)፤ ነገር ግን ጽሑፉ በቀጥታ ሲነበብ ሳለ በጽሑፉ ውስጥ ያለው ቀጥተኛ ትርጉም በቁመ እንዲታይ ይፈቅዳሉ (ለምሳሌ፣ በምዕ 40-42 ያለው ቤተ መቅደስ)። መለኮታዊ ተርጓሚዎች እንደ ገለጹትም በምዕራፍ 40-48 ላይ የሚገኘው የወደፊቱ ቤተ መቅደስ ከመሥዋዕቶቹ ጋር መንፈሳዊ ትምህርቶችን ሲያስተላልፍ እንኳ ከእውነታዎቹ መንፈሳዊ ትምህርትን መማር ይቻላል (ምሳሌ የቅድስና አስፈላጊነት)።

ይህ ሐተታ ወደ ፊት እስራኤል ንጹሕ ሆና፣ ዐዲስ ልብ ከተቀበለች በኋላ በምድርዋ ተመልሳ እንደምትቋቋም እንዲሁም በመሲሑ የወደፊት ሺህ መንግሥት አገዛዝ ሥር በሰላምና በብልጽግና እንደምትኖር ያለውን ምልከታ ያቀርባል። የእግዚአብሔርን ቅድስና ለማሳየት ሲባል በዝርዝር ዕቅዶቹ መሠረት የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ይሠራል። ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሚፈጽመው የድነት ሥራ መታሰቢያ በመሆን የመሥዋዕት ሥርዐቶች ይመሠረታሉ። ምድሪቱን ለመፈወስ ከቤተ መቅደሱ በቀጥታ የሚፈስ እውነተኛ ወንዝ ይኖራል። ሙሉ በሙሉ ዐዲስ የሆነ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ይፈጠራል።

ሀ. በተሰፋፊዉ ምድር መልሶ መቋቋም (33፥21-39፥29)

እግዚአብሔር መባረክን ይፈልጋል፤ በርግማን ፈጽሞ ደስ አይሰኝም። ይሁን እንጂ በረከትም ሆነ መርገም ሁለቱም በእግዚአብሔር ኪዳናዊ ዕቅድ ውስጥ ያሉ ክፍሎች ናቸው። መላው የሕዝቅኤል ትንቢት እግዚአብሔር ለእስራኤል ካለው ኪዳን አንጻር የተሰጠ ነው። በሕዝቅኤል መጽሐፍ ውስጥ ያለውን የሐሳብ አንድነትና እድገት ለማስተዋል የእግዚአብሔርን ኪዳኖች መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው (በ1ዜና ምዕራፍ 17 ላይ ያለውን መረጃና መግለጫ ይመ)።

አብርሃማዊው ኪዳን እግዚአብሔር ዓለምን ለመባረክ ያለውን መሠረታዊ ዕቅድ የሚያመለክት ነው (ዘፍ 12፥1-3)። በዚህ ኪዳን እግዚአብሔር አንድን ሰው ያውም አብራምን እንደሚመርጥ ተናገረ፤ ከዚህም አንድ ሰው እስራኤል የተባለውን ሕዝብ ፈጠረ፤ በዚህ አንድ ሕዝብ አማካይነት ዓለምን ይባርክል። አንድ ሕዝብ እንደ ሕዝብ ጸንቶ እንዲኖር የሚከተሉት ሦስት ነገሮች ያስፈልጋሉ፤ እነርሱም ሕዝብ፣ መንግሥትና አገር ናቸው። በግብፅ ከዐሥራ ሁለቱ የያዕቆብ (የእስራኤል) ልጆች የእስራኤል ሕዝብ ተፈጠረ። የሙሴ ኪዳን የሆነው ሰነድ የእስራኤል መንግሥት ሕግ በመሆን በሲና ተራራ ተሰጠ፤ በኢያሱም አማካይነት ከነዓንን በማሸነፍ የእስራኤል አገር ርስት ተወረሰ።

የሙሴ ኪዳን (ዘፀ 20- ዘኍ 9፤ ዘዳግም) የእስራኤል ሕገ መንግሥት ሆነ፤ ይህም በእስራኤል ሕዝብ ያለ ማንኛውም የሕይወት አቅጣጫ የሚገዛበት ነው። እስራኤል የሙሴን ኪዳን ስትጠብቅ፣ የአብርሃም ኪዳን በረከቶችን ትወርሳለች፤ ለምሳሌ፣ በበረከት ምድር መኖርና ለሕዝቦች በረከት መሆን እንደ ማለት ነው። ይሁን እንጂ በታሪክ ውስጥ በማንኛውም ዘመን እስራኤል በሙሴ ኪዳን ላይ ባመፀች ቊጥር የአብርሃማዊ ኪዳን በረከቶች ተጠቃሚ አትሆንም፤ እንዲሁም ለሌሎች ሕዝቦች በረከት አትሆንም። እስራኤል የሙሴን ኪዳን ባለመከተልዋ ለባቢሎን ምርኮ ተዳረገች። እስራኤል አምላክዋ ቃሉን በመጠበቅ የዘዳ 27-28 ፍርዶችን በእርስዋ ላይ ያመጣ መሆኑን ተገነዘበች።

ቡዳዊት ኪዳን (2ሳሙ 7፥12-16) እግዚአብሔር የዳዊት ዘሮች ለዘላለም በእርሱ ዙፋን ላይ እንደሚቀመጡ የተሰፋ ቃል ሰጠ፤ ይህም የዘላለም መንግሥት ዘላለማዊ ዙፋን ነው። መሲሕ የሚለው ሐሳብ የተመሠረተው በዚህ ኪዳን ላይ ነው፤ እያንዳንዱ የእስራኤል ንጉሥ መሲሕ ወይም “የተቀባ” ነውና። ይህ ኪዳን ወደፊት አንድ ቀን የመጨረሻው የዳዊት ልጅ በዳዊት ዙፋን ላይ ተቀምጦ እንደሚገዛ ተስፋ ሰጥቶአል።

ነቢዩ ኤርምያስ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የሚገባውን ዐዲስ ኪዳን ማለትም የሙሴን ኪዳን ሥራዎች የሚተካውን ዐዲሱን ኪዳን ዐወጀ። ይህ ኪዳን የሙሴን ኪዳን በማካተት ሕጎቹ በመሲሑ በሚያምኑ ሰዎች ልቦች ላይ እንዲጻፉ ይደረጋል። በመግቡቶቹ መሠረት ኀጢአት ሁሉ ለአንዱና ለዘላለም ይቅር ይባላል (በመሲሑ)፤ በሚያምኑትም ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ ይፈሳል (ከምዕ 36፤ 2ቆሮ 3 ጋር ያነጻ)።

እነዚህ ሁሉ ኪዳኖች ለሕዝቅኤል መልእክት አጠቃላይ ሁኔታን የሚያቀርቡ ናቸው። ሕዝቅኤል ከእግዚአብሔር ተልእኮውን ከተቀበለ በኋላ (ምዕ 1-3) በሙሴ ኪዳን መሠረት እግዚአብሔር እንደሚፈርድበት (እንደሚረግማት) እስራኤልን አስጠነቀቀ፤ ይኸውም በአሕዛብ መካከል እንደምትበተን፣ እንዲሁም አየሩሳሌምና ይሁዳ ባድማ እንደሚሆኑ የተናገረው ነው (ምዕ. 4-23)። በምዕራፍ 24 በኢየሩሳሌም ከበባ ጊዜ እንኳ እግዚአብሔር በሕዝቡ የተናገረው የፍርድ ትንቢት እንደሚጀምር ሕዝቅኤል ተናገረ። ከዚያም እግዚአብሔር በአብርሃም ኪዳን የተናገረውን ቃል እንደሚፈጽም በማስታወስ፣ እስራኤልን በጨቋኟት አሕዛብ ላይ ሕዝቅኤል የእግዚአብሔርን ፍርድ ተናገረ (25፥1-33፥20)።

የኢየሩሳሌም ውድቀት የሕዝቅኤል ትንቢት አስፈላጊ ሐሳብ በመሆን ያገለግላል። ለእግዚአብሔር ሕዝብ የተሰጡት ማስጠንቀቂያዎች ከዚያ ውድቀት ጋር ትንቢቱን የሚያሟሉ ይሆናሉ። አሁን ግን ምርኮኞቹን ማጽናናት የሚያስፈልግ ይሆናል፤ ይኸውም እግዚአብሔር ርግማንን ለማምጣት የተሰፋ ቃሉን ለመፈጸም ታማኝ እንደ ሆነ ሁሉ በረከቱንም ለማምጣት እንዲሁ ታማኝ ነው። ቀሪው የሕዝቅኤል መጽሐፍ (33፥21-48፥35) የኪዳኑን በረከቶች በአጽንዖት የሚያመለክት ነው። እግዚአብሔር እስራኤልን በምድርዋ መልሶ እንደሚያቋቁማት ቃል ገብቶላታል (የሙሴ ኪዳን በተለይም ዘዳ 30)፤ በውስጥዋም ዐዲስ ልብና ዐዲስ መንፈስን (አዲስ ኪዳን) እንደሚሰጣት ተስፋ ሰጥቶአታል። መሲሑ፣ ጌታዋ በእርስዋ ላይ ሲነግሥ (የዳዊት ኪዳን) በሰላምና በጸጥታ ትኖራለች። የሰላምን ኪዳን ጨምሮ የእግዚአብሔር የበረከት የተሰፋ ቃሎች ሁሉ ከእያንዳንዱ የኪዳን መሟላት ጋር ወደ ፍጻሜ ይደርሳሉ።

መሲሑ ለዘላለም በእስራኤል ላይ ይነግሣል፤ ከዚህም በኋላ ማንም እንደ ገና እስራኤልን ከምድርዋ አያፈናቅላትም።

የኢየሩሳሌም መውደቅ ወሬ በባቢሎን በነበሩት ምርኮኞች ከመሰማቱ በፊት ምድሪቱን የሚመለከተው ፅንሰ ሐሳብ በዚያ በአንድ ሌሊት ለተሰጡት መልእክቶች በተለይ አስፈላጊ ነበር። ኢየሩሳሌም ስለ ወደቀች፣ በዚህ ሁኔታ እስራኤል ምድሪቱን መልሳ ልትወርስ ትችላለችን (33፥21-33)? የእስራኤልን ሕዝብ ከእውነት በማሳት እስራኤል ምድሪቱን እንድታጣ ያደረጉ ሐሰተኛ እረኞች ነበሩ። ነገር ግን እውነተኛው እረኛ የሆነው መሲሑ በመጨረሻ ምድሪቱን ለእስራኤል ያስመልሳል (ምዕ 34)። የእስራኤልን ምድር የያዙና ሕዝብዋን የጨቁኑ እነዚያ ባዕዳን፣ እስራኤልም እንደ ገና የራስዋን ምድር መልሳ ትወርስ ዘንድ ይፈረድባቸዋል፤ ከምድረቱም ይወገዳሉ (35፥1-36፥15)። ከዚያም እግዚአብሔር እስራኤልን ወደ ተስፋዪቱ ምድር መልሶ ያቋቁማታል፤ ይህም ድርጊት በ36፥16-38 ተዘርዝሮና ውብ በሆነ አቀራረብ በ37፥1-14 በተገለጸው አቡቀለምሲሳዊ ራእይ ተቀምጧል። እስራኤል አንድ መንግሥት ሆና መሲሑ ብቻውን ገዢዋ ይሆናል፤ እግዚአብሔርም ለእርስዋ የገባውን የሰላም ኪዳን ያውጃላታል (37፥15-28)። ከዚህም በኋላ ባዕድ ኀይል እስራኤልን በምድርዋ ላይ ፈጽሞ አይገዛትም (ምዕ 38-39)።

1. እስራኤልና የተስፋዪቱ ምድር (33፥21-33)

21-22 ከ33፥21-39፥29 ላሉት ስድስት መልእክቶች ቀንና መቼት በእነዚህ ሁለት ጥቅሶች ውስጥ ተሰጥቶአል። ሕዝቅኤል ምዕራፍ 24ን የዘጋው አንድ ከኢየሩሳሌም ውድመት ያመለጠ ሰው ከተማዪቱ በባቢሎናውያን ምርኮኞች እጅ እንደ ወደቀች እንደሚናገር በመተንበይ ነበር። የዚያ ትንቢት ፍጻሜ በእነዚህ ቁጥሮች ይገኛል። የኢየሩሳሌም ከበባ የጀመረው በታኅሣሥ/ጥር 589/588 ዓቅክ ነው (24፥1፤ 2ነገ 25፥1)። ከሁለት ዓመት ከሰባት ወር በኋላ ኢየሩሳሌም ወደቀች (መስከረም 586 ዓቅክ፣ 2ነገ 25፥8)። ልክ ከተማዪቱ እንደ ወደቀች አንድ የማይታወቅ ሰው አምልጦ ወይም በባቢሎናውያን ተይዞ መጥቶ በባቢሎን በምርኮ ላሉት ወገኖች የኢየሩሳሌምን ውድቀት ተናገረ። ከዐምስት ወር በኋላ (ታኅሣሥ/ ጥር 586/585 ዓቅክ) ሕዝቅኤል እነዚህን ስድስት መልእክቶች ካስተላለፈ በኋላ ባለው ማለዳ ላይ፣ ይህ ሲጠበቅ የነበረው ወሬ መጣ። ሰባት ዓመት ተኩል ያህል ቁይቶ የነበረው የሕዝቅኤል ዲዳነት (3፥24-27) ምርኮኞቹ የኢየሩሳሌምን የመውደቅ አስደንጋጭ ወሬ ከመስማታቸው በፊት እነዚህን ስድስቱን የማበረታቻ መልእክቶች እንዲናገር እግዚአብሔር አፉን ከፈተው (ከ3፥24-27 ጋር ያነጻ)።

23-29 ከሕዝቅኤል ስድስቱ መልእክቶች አንዱ ሁለት ገጽታዎች አሉት፤ ይኸውም የይሁዳ ትሩፋን ምድሪቱን በተመለከተ ያላቸው ጥያቄ (ቊ 23-29) እና በከነዓንና በባቢሎን ውስጥ የነበሩት እስራኤላውያን ለሕዝቅኤል አገልግሎት ምላሽ የሰጡበት ሁኔታ ናቸው (ቊ 30-33)። ኢየሩሳሌም ወድቃለች! እስራኤል ምድሪቱን ታጣ ይሆን? በፈረሰችው ኢየሩሳሌም የነበሩት ትሩፋን ለአብርሃም ርስት እንደምትሆን እግዚአብሔር የተናገረላት ምድር ዕጣ ፈንታ ምን እንደሚሆን ጥያቄ ተፈጥሮባቸው ነበር። የአብርሃም ትውልድ የሆኑት እነርሱ ለአባቶቻቸው ከተሰጠችው ምድር ለምን ተለዩ! የአብርሃም ኪዳን አሁን አይሠራምን? እነርሱ ከጥፋት የዳኑ እንደ መሆናቸው መጠን ለአብርሃም የተሰጠው ተስፋ እነርሱን አይመለከትም?

የተስፋዪቱን ምድር የመጠባበቅ ተስፋ በእስራኤላውያን ልብ ውስጥ ሊጠበቅ የሚችለው ኪዳኑን በትክክል መረዳት የቻሉ እንደ ሆነ ብቻ መሆኑን እግዚአብሔር መለሰላቸው። የሙሴ ኪዳን ሕገጋት ባለመጠበቃቸው ከአብርሃማዊ ኪዳን በረከቶች አንዱ የሆነውን በተስፋዪቱ ምድር ውስጥ የመገኘትን በረከት እስራኤላውያን ሊቀበሉ አልቻሉምና። ሕዝቡ የሙሴሓዊ ኪዳን ሕገጋትን ጥሰዋል፤ ደም በልተዋል (ከዘሌ 17፥10-14፤ 19፥26 ጋር ያነጻ)፣ ጣዖታትን አምልከዋል (18፥6፤ ከዘፀ 20፥4-5 ጋር ያነጻ)፤ አስጸያፊ ነገሮችን ፈጽመዋል፣ በሰይፍ ደም አፍስሰዋል (18፥10 ይመ፤ ከዘፀ 20፥13 ጋር ያነጻ)፤ የእርስ በርሳቸውን ሚስቶች አርክሰዋል (18፥6፤ 22፥11 ይመ፤ ከዘፀ 20፥14 ጋር ያነጻ)። እነዚህን ዐመፆች ፈጽመው ሳለ፣ ምድሪቱን መውረስ እንዳለባቸው በርግጥ ሊያስቡ ይገባልን?

የእግዚአብሔር ፍርድ ውሳኔ ፈጽሞ አይገባም! የሚል ነው። የሙሴያዊ ኪዳን ፍርዶች (ዘዳ 27፥28፤ 29፥25-29) እየተፈጸሙ ነበር፦ በይሁዳ የቀሩት በስይፍና በደዌ ይሞታሉ ወይም ለዱር አራዊት ዐልፈው ይሰጣሉ። የልባቸው ትዕቢት ጸጥ ይላል። ምድሪቱ ባድማና ጠፍ ትሆናለች። እጅግ ዋና የሆነው ነገር ማለትም እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ያለው የፍርድ ዐላማ ይፈጸማል፦ እነዚህ ፍርዶች ሲፈጸሙ እርሱ አምላካቸው መሆኑን ያውቃሉ።

30-33 በምርኮ ያሉት እስራኤላውያንና በፖለስቲና ያሉት ትሩፋን የሕዝቅኤልን አገልግሎት የሚመለከቱት በፌዝ ነበር። እርስ በርሳቸውም የእግዚአብሔርን ቃል ሄደን እንስማ በማለት ይነጋገሩ ነበር። ይሁን እንጂ የእርሱን መልእክቶች ለመስማት ወደ ሕዝቅኤል ሲመጡ፣ በማስጠንቀቂያዎቹ መሠረት ሊጓዙ አልፈለጉም። በከንፈራቸው ብዙ ታማኝነትን ይገልጻሉ፤ ልባቸው ያረፈው ግን ቊሳዊ ጥቅም ላይ ነበር። በእግዚአብሔር ፊት ይቀልዱ ነበር። ለእነርሱ ሕዝቅኤል ጥሩ አዝናኝ ከመሆን ያለፈ ሰው አልነበረም። በትእምርታውያን ድርጊቶቹ በትንቢቶቹ ሊደመጥና ሊመለከቱት የሚያስደንቅ ሰው ነበር። ይሁን እንጂ አዝናኝ ምንም ዐይነት ምላሽ እንደማይፈልግ ሁሉ፣ ለሕዝቅኤል መልእክቶች መልስ መስጠት እንደማያስፈልግ ያስቡ ነበር። የሕዝቅኤል ትንቢቶች እውን ሆነው ሲገኙ ግን፣ ይህም እውንነት በኢየሩሳሌም መውደቅ ጀምሮአል፤ ከዚያም እውነተኛ ነቢይ በመካከላቸው እንደ ነበር እስራኤላውያን ይገነዘባሉ።

2. ሐሰተኛና እውነተኛ እረኞች (34፥1-31)

ሀ. በሐሰተኛ እረኞች ላይ የቀረበው ክስ (34፥1-6)

1-6 ባለፈው መልእክት ላይ በሙሴያዊው ኪዳን ላይ እስራኤል ስላመፀች ፓለስቲናን ዐጥታ እንደ ነበር ሕዝቅኤል ገልጾአል። ስለዚህ አሁን የተስፋዪቱን ምድር በረከት ልታገኝ አትችልም። ስለዚህ በተስፋዪቱ ምድር በመሆን የሚገኘውን በረከት፣ ማለትም የአብርሃማዊውን ኪዳን በረከት አሁን ተመክሮዋ ማድረግ አትችልም፤ ይህ በረከት ሊገኝ የሚችለውም ሕዝቡ በሙሴ ኪዳን ላሉት ድንጋጌዎች ሲታዘዙ ብቻ ነው። አብርሃማዊውን ኪዳን ልታገኝ አትችልም። ምክንያቱም ይህን አብርሃማዊ ኪዳን ልታገኝ የምትችለው ሕዝቡ እንዳለ የሙሴያዊውን ኪዳን ሕገጋት የታዘዘ እንደ ሆነ ብቻ ነው። ነገር ግን "እረኞች" ተብለው በተገለጹት የእስራኤል መሪዎች ላይ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ክስ ቀርቦባቸዋል።

ይህ የፍርድ ንግግር ባለፉት የእስራኤል "እረኞች" ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ ለምን እንደ መጣ ይገልጻል። የእስራኤል መሪዎች የሚያስቡት ስለ ራሳቸው ብቻና ስለ ቁሳዊ ጥቅም ነበር። "ለመንጋው" ደንታ አልነበራቸውም። መንጋውን ከመመገብ ይልቅ ራሳቸውን በመንጋው ይመግቡ ነበር፤ ለሕዝቡ የሚያስፈልገውን ከማቅረብ ይልቅ የሕዝቡን ምግብና ልብስ ለራሳቸው ይወስዱ ነበር። እጅግ ደካማና ድኽች ለሆኑት ችግረኞች የሚያስፈልጋቸውን ሳይሰጡ ቀሩ። የጠፉትን በኃይል አልፈለጉም። ለእነርሱ ለራሳቸው የሚያስፈልጋቸውን እስካገኙ ድረስ፣ በሕዝቡ ላይ ስለሚደርሰው ሁሉ ግድ አልነበራቸውም፤ አገዛዛቸውም ግፍና ጭካኔ የሞላበት ነበር። የራሱን ፍላጎት እስከ መሠዋት ድረስ አንድ መሪ በቅድሚያ ለሚመራው ሕዝብ እንክብካቤ ማድረግ እንደሚኖርበት እግዚአብሔር ግልጽ አድርጎአል።

በትክክል ሊመራቸው የሚችል እረኛ ከማጣታቸው የተነሣ፣ የእስራኤል መንጋ ከመንገድ በመውጣት በአሕዛብ መካከል ተበተነ (ከኤር 23፥9-10 ጋር ያነጻ)። የሚጠብቃቸው እረኛ ስለሌላቸው ለዱር አራዊት መብል ሆኑ። ፈልጎአቸው እንክብካቤ የሚያደርግላቸው እረኛ አልነበረም (ከማቴ 9፥36 ጋር ያነጻ)። የመሪነት ዕጦት ምን ጊዜም ቢሆን በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል መከፋፈልን፣ የግልና የጋራ ልብ ስብራትን እንዲሁም ጉዳትን ያስከትላል።

ለ. የእስራኤልን መሪነት በተመለከተ የእግዚአብሔር የፍርድ ውሳኔ (34፥7-31)

7-10 መደበኛው የፍርድ ሥርዐት ውሳኔው ከመሰማቱ በፊት ወዲያውኑ ክሱ በድጋሚ ይሰማ ዘንድ ይጠይቃል። የእስራኤል

“እረኞች” ራስ ወዳድ ከመሆናቸው የተነሣ፣ ለግል ጥቅማቸው ሲሉ መንጋውን የዘረፉ ስግብግብ መሪዎች በመሆን ሕዝቡ ለሌሎች መንግሥታት መብል እንዲሆን ዐልፎ እንዲሰጥ አደረጉት። በዚህ መሠረት የእስራኤል መንጋ የበግ ለምድ በለበሱ በእነዚህ ተኩላ እረኞች እንዳይበላ እግዚአብሔር መሪዎችን ከሥልጣናቸው እንደሚያነሣ ተስፋ ሰጠ። እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሐሰተኛ እረኛ ስለ እረኝነቱ በኀላፊነት ይጠይቀዋል።

11-16ለ የእስራኤል ሕዝብ ለየግላቸው ድርጊት በኀላፊነት ተጠያቂ ቢሆኑም፣ በጨካኝ መሪዎች ከመንገድ ስተው ወጥተዋል። እግዚአብሔር የእስራኤልን መንጋ እርሱ ራሱ ኀላፊነት ወስዶ “እረኞቸው” ሆኖ እንደሚመራቸው ቃል በመግባት አበረታቶአቸዋል። እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል የተበተነውን መንጋ እንደሚፈልግ፣ እንደሚያድንና እንደሚሰበስብ እንዲሁም እንደ አፍቃሪ እረኛ እንደሚንከባከባቸው ቃል ገብቶአል። እስራኤልን ወደ ምድርዋ ይመልሳታል፤ በተራሮችዋና በሸለቆችዋ ባሉ የግጦሽ መራቶችም ያሰማራታል። የየግል ፍላጎቶች በመጨረሻ ይሟላሉ፤ የጠፉትም ተፈልገው ይገኛሉ። የተጐዱት ይጠገናሉ፤ የደከሙት ይበረታሉ። እግዚአብሔር ለመንጋው የሚያስፈልገውን እንክብካቤ ሁሉ ያደርጋል።

16ሐ-24 እግዚአብሔር ሕዝቡን በፍትሕ ይጠብቃል። በመንጋው ላይ ጥቅም ያገኙ ሁሉ እንደ ሌላው በግ ወይም ፍየል ይታያሉ። የቀደሙት እረኞች ከለመለመ መስክ ስለ ተመገቡና ከንፁሕ ውሃ ስለ ጠጡ፣ በሣ፣ በለሰለሰና በበረታ በግ ተመስለዋል። በመንጋው ውስጥ ላሉት ሌሎች በጎች ባለማሰብ ግዴለሽ በመሆን በትዕቢት መስኩን ረጋገጡ፤ ውሃውንም አደፈረሱ። የተሰጣቸውን ሥልጣን ያለ አግባብ በመጠቀም ሌሎችን በጎች “በቀንዳቸው ወግተው” አባረሩአቸው። በመሪዎች መካከል ለእንዲህ ዐይነቱ ኀላፊነት ለጐደለው ባሕርይ ስፍራ ስለማይኖር፣ እነዚህ እረኞች ይፈረድባቸዋል፤ ይደመሰሳሉ።

እግዚአብሔር ከመጥፎ አመራርም ሆነ ከአጥቂ መንግሥታት ከሚመጣባት ማንኛውም ጭንቀት እስራኤልን ይታደጋታል። ይህንንም የሚያደርገው እውነተኛና ለሕዝቡ ኀላፊነት የሚሰማው አንድ እረኛ በመሾም ነው፤ ይኸውም መሲሑ የሆነው አገልጋዩ ዳዊት ነው። እግዚአብሔር የእስራኤል አምላክ ይሆናል፤ አገልጋዩ ዳዊት፣ መሲሑ እስራኤልን በምድርዋ ላይ መልሶ ካቋቋማት በኋላ በምድር ላይ የእስራኤል ገዥ ይሆናል። የግጻዌ መሰኮት ሁለት አካላት እዚህ ላይ በተለያዩ ተግባራት በግልጽ ይታያሉ። “አገልጋዬ ዳዊት” የሚለው ሐረግ በቋሚነት የሚያመለክተው መሲሑን ነው። ነቢዩ ኤርምያስ መሲሑን “ጻድቅ ቅርንጫፍ”፣ “እግዚአብሔር ጽድቃችን” ብሎ በመጥራት እውነተኛውን እረኛ ከዳዊት ዘር በመጥቀስ ያመሳስለዋል (ኤር 23፥5-6)። ይህን የመሰለ ማንነትም በሌሎች ነቢያት ተጠቅሶአል (ኤር 30፥9፤ ሕዝ 37፥24-25፤ ሆሴ 3፥5)።

25-31 በመጨረሻ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ሌላ ቃል ኪዳን በመመሥረት እስራኤላውያንን ያበረታታቸዋል፤ ይህም ኪዳን “የሰላም ቃል ኪዳን” የሚባለው ነው (ከ37፥26-28፤ 38፥11-13፤ 39፥25-29 ጋር ያነጻ)። ይህ ኪዳን ዐዲስ ኪዳን አይደለም። ይህ የሰላም ቃል ኪዳን የሚመረቀው፣ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የገባቸው ሌሎች ቃል ኪዳኖች ሲፈጸሙ ነው። (1) ይህ ቃል ኪዳን እስራኤል በሰላምና በጸጥታ ትኖር ዘንድ በመጨረሻ የአሕዛብ መንግሥታትን (“የዱር አራዊት”) ከእስራኤል ምድር የማስወጣት ዋስትናን ይሰጣል። (2) እግዚአብሔር እስራኤልንና ምድሪቱን “በበረከት ዝናብ” ያረሰርሳል፤ ውጤቱም ከምድሪቱ በተገኘ የተትረፈረፈ ምርት ሙሉ ርካታ ይሆናል። (3) እስራኤል በፍጹም ጸጥታ ትኖራለች። ከእንግዲህም ለሌሎች ሕዝቦች ንጥቂያ አትሆንም፤ ወይም የአሕዛብ መሣለቂያ አትሆንም፤ ከእንግዲህም ምድሪቱ በራብ አትጠቃም፤ (4) እግዚአብሔር እስራኤልን በባርነት ከገዟት ነጻ ሲያወጣትና በሰላም ወደ ምድርዋ ሲመልሳት እርሱ በእውነት አምላክዋ እንደ ሆነ ትገነዘባለች። (5) በእስራኤልና በጌታ መካከል ያለው የሙሴያዊው ግንኙነት ቀመር እውን ይሆናል። እግዚአብሔርም በእውነት አምላካቸው ይሆናል፤ እነርሱም በማንኛውም አቅጣጫ የእርሱን መንገዶች በመከተል በመጨረሻ ሕዝቡ ይሆናሉ። ኤርምያስ በተነበየው መሠረት እስራኤል የዚያ ቃል ኪዳን መካከለኛ በሆነው በመሲሑ (ከዕብ 8፥6 ጋር ያነጻ) የተመሠረተውን ዐዲሱን ኪዳን (ኤር 31፥31-34) ስትቀበል ይህ ግንኙነት ይጀመራል።

ይህ የሰላም ኪዳን መታወጁ ቀጥሎ ላሉትና በተከታታይም ለቀረቡት ለእነዚህ ስድስት ንግሮች ለተዘረዘሩት ቀጣይ መልእክቶች መሸጋገሪያን ይሰጣል። እያንዳንዱ ንግር የሰላም ኪዳንን ገጽታ ያብራራል። ሕዝቅኤል 35፥1-36፥15 ያለው ክፍል እስራኤል ወደ ገዛ ምድርዋ እንድትመለስ ለሚደረገው ዝግጅት እነዚህ የውጭ ነጣቂ መንግሥታት እንዴት እንደሚወገዱና ምን ዐይነት ፍርድ እንደሚፈረድባቸው ይገልጻል። በ36፥16-37፥14 ያለው መልእክት እግዚአብሔር እስራኤልን ወደ ምድርዋ መልሶ ያቋቋመበትን ሁኔታ ውብ በሆነና ዘርዘር ባለ አገላለጽ የሚያቀርብ ክፍል ነው። በሕዝቅኤል 37፥15-28 ያለው ክፍል ይህ የሰላም ኪዳን ሲመሠረት የሕዝቡ ሙሉ አንድነትና የኪዳኑ ፍጻሜ እንዴት እንደ ሆነ በአጽንዖት የሚያቀርብ ነው። በመጨረሻም በሕዝቅኤል 38-39 ያለው ክፍል እስራኤል በጌታ ያላትን ፍጹም ሰላም የሚያሳይ ነው፤ የእስራኤልን ምድር ለመያዝና የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመዝረፍ የመጨረሻ ሙከራ የሚያደርገውን የውጭ ኀይል (ጎግ) እርሱ እግዚአብሔር ከመንገድ ውጭ ያደርገዋልና።

በቅርቡ የገዟት የጨካኝ መሪዎች አመራር ቢደርስባትም እንኳ፣ አሁን እስራኤል ሐሤት ማድረግ ትችላለች፤ እረኛ ለበጎቹ ተገቢውን ጥበቃ እንደሚያደርግ በመልከመ እረኛ በመሲሑ አማካኝነት ፍጹም የሆነ አመራርን እንደሚሰጣት አሁን በርግጠኛነት ተነግሮአታል። አሁን ፍጹም የሆነ ተስፋ አለ!

3. የምድሪቱ መዘጋጀት (35፥1-36፥15)

ሀ. የጨቋኞች መወገድ (35፥1-15)

1-9 ከእንግዲህ ወዲያ በነጣቂ መሪዎች እንደማይገዙ በመንገር ሕዝቅኤል በባቢሎን ያሉትን ምርኮኞች አበረታታ። ይልቁን እግዚአብሔር መሲሑን “እረኞቸው” አድርጎ ይመሠርተዋል። ይሁን እንጂ የእስራኤልን ምድር ዕጣ ፈንታስ? ባድማ ሆኖ አልቀረምን? አሁንስ ቢሆን ያንን ምድር የሚገዙ የውጭ ጨቋኞች የሉምን? በባዕዳን በወደመ ምድር ውስጥ የሚኖሩትን ሕዝቡን መሲሑ እንዴት መግዛት ይችላል? እነዚህ ጥያቄዎች ምርኮኞቹ ሕዝቅኤልን በሰሙት ቍጥር ወደ አእምሮአቸው ሳይመጡ አልቀሩም። እግዚአብሔርም እነዚህን ጭንቀቶችና ፍላጎቶች በመረዳት፣ ፍርሀታቸውን ለማቅለል እርሱ ራሱ ባዕዳን ጨቋኞችን ከእስራኤል እንደሚያስወግዳቸውና ምድሪቱም ሕዝቧን ትቀበል ዘንድ እንደሚያዘጋጃት ተናገረ።

የእስራኤልን ምድር ለመያዝና በእርስዋም ላይ የአገዛዝ የበላይነትን ለመግለጽ ጥረት ሲያደርጉ ለነበሩት መንግሥታት የተመረጠች ተወካይ ሆና የቀረበችው ኤዶም (ሴይር ተራራ፤ ከቍ 15 ጋር ያነጻ) ናት። ምናልባትም ኤዶም ከሌሎች መንግሥታት ይልቅ እስራኤልን በተደጋጋሚ የተጸየፈችና የጠላች አገር ሳትሆን አትቀርም። ይህ ታሪክ የጀመረው በያዕቆብ (እስራኤል) እና በዔሳው (ኤዶም) ግጭት ነው (ዘፍ 25፥22-34፤ 27፤ 36፥1)። እስራኤል ወደ ተስፋዪቱ ምድር እንዳትገባ በመጀመሪያ ለማገድ ሙከራ ታደርግ የነበረችው ኤዶም ናት (ዘኍ 20፥14-21፤ 24፥15-19)። በሳኦል (1ሳሙ 14፥47)፤ በሰሎሞን (1ነገ 11፥14-22)፣ በኢዮሣፍጥ (2ዜና 20፥1-23)፣ በኢዮራም (2ነገ 8፥21) እና በአካዝ (2ዜና 28፥17) ዘመን ግጭቶች ነበሩ። ነቢያትም እንዲሁ በተደጋጋሚ ኤዶም በእስራኤል ላይ የምታደርገውን ተቃውሞና ልትቀበለውም የሚገባትን ፍርድ ጠቅሰዋል (ኢሳ 11፥11-16፤ ዳን 11፥41፤ አሞ 2፥1)። ሚልክያስ በእነዚህ ሁለት ሕዝቦች መካከል የነበረው ጠላትነት በእርሱም ዘመን እንደ ነበረ ተናግሮአል (ሚል1፥2-5)። ስለዚህ ሕዝቅኤል የእስራኤልን ምድር ለመውረርና የራሳቸው ለማድረግ የሚፈልጉ መንግሥታት ተወካይ አድርጎ ኢዶማውያንን ማቅረቡ ትክክል ነበር።

ተገቢ የሆኑ የፍርድ ውሳኔዎችን (ቍ. 6፡ 9፡ 11-15) ተከትለው በኤዶም ላይ የቀረቡ ሁለት ዐጫጭር ክሶች አሉ (ቍ. 5-10)። በመጀመሪያ በኤዶም ላይ የሚከተሉት ሁለት ክሶች

ቀርበውባታል፡- በታሪክዋ ውስጥ ኤዶም ጥላቻን በእስራኤል ላይ ስታከማች ኖራለች (ከ25፥12 ጋር ያነጻ)፤ የሌሎች መንግሥታት የጥፋት ግብረ አበር ከመሆን ባሻገር በተፈለገ ጊዜ ሁሉ እስራኤልን ለእነርሱ አሳልፋ ስትሰጥ ኖራለች። መዝ 137፥7 እና ሰቈ 4፥21-22 ኤዶም፣ ባቢሎናውያን ይሁዳን በ589-586 ዓ/ክ በወረሩ ጊዜ በደስታ ስትደግፋቸው እንደ ነበር አመልክተዋል። በአብድዩ ቍ. 10-14 ላይ ኤዶም በችግር ጊዜ እስራኤልን ስለ ካደች አብድዩ አውግዞአታል። የሕዝቅኤል ወቀሣ እንድምታም ኤዶም በእስራኤል ላይ እንደ ገና በጠላትነት እንደምትነሣ ማመልከት ነው።

እግዚአብሔር ኤዶምን ይቀጣል። ኤዶም እስራኤልን በጠላች ጊዜ ከደም ማፍሰስ እንዳልተቈጠበች ሁሉ፣ እግዚአብሔርም ያልተቋረጠን የደም መፋሰስ በኤዶም ላይ ያመጣል። የኤዶም ምድር በሰይፍ በታረዱ ኗሪዎች ይሞላል። ኤዶም ባለማቋረጥ የእስራኤል ጠላት እንደ ሆነች ሁሉ፣ እግዚአብሔርም ማብቂያ የሌለውን ባድማነት በሴይር ተራራ ላይ ያመጣል (ከ25፥12-14፤ ከኤር 49፥13፡17፤ ከአብ ቍ. 18 ጋር ያነጻ)። ከተሞች ሰው አልባ ይሆናሉ። ማንም ከኤዶም ጋር ተገቢው ግንኙነት ሊኖረው አይችልም፤ ፈጽሞ ከምድር ትጠፋለችና። ይሁን እንጂ ከዚህ ፍርድ የተነሣ፣ ይህን ቅጣት ያመጣው እርሱ ብቻ እውነተኛ አምላክ የሆነው የእስራኤል አምላክ እንደ ሆነ ኤዶም ታውቃለች።



ከቤርሳቤህና በስተ ምሥራቅና ከሙት ባሕር በስተ ምዕራብ የነበሩት የኤዶም ከተሞች፣ ባቢሎናውያን በ586 ይሁዳን እስካወደመበት ዘመን ድረስ በሰባተኛው ምእት ዓመት ዓ/ክ አሸበረቁ። ይህ ኮረብታ በፓለስቲና እንዳሉት እንደሌሎቹ ኮረብቶች የአንድን ከተማ ፍርስራሽ ይዞአል።

10-15 በኤዶም ላይ ለደረሰው ቅጣት ሁለተኛው ምክንያት እንደሚከተለው በሦስት ገጽታ ቀርቦአል፡- ኤዶም እስራኤልንና ይሁዳን ለመቈጣጠር ትፈልግ ነበር፤ ኤዶም እስራኤልን ለመበጫጨቅ ከላት ፍላጎት የተነሣ እስራኤልን በስድብ አዋረደች፤ በእግዚአብሔርም ላይ በትዕቢት ተናገረች፤ ኤዶም የእስራኤል አምላክ እውነተኛው አምላክ እንደ ሆነም ሳታውቅ ቀረች። እግዚአብሔር ለምታደርገው ነገር ሁሉ ምንም ስሜት የሌለው ወይም የምትለውን የማይሰማ እንደ ሆነ ገመተች።

ኤዶም በእስራኤል ላይ በቍጣ፣ በቅንዓትና በጥላቻ ማንኛውንም ነገር እንዳደረገች ሁሉ እግዚአብሔርም በኤዶም ላይ እንዲሁ ያደርጋል። በኤዶም ላይ እንዲህ ያለ ፍርድ ማምጣቱ በእውነት እግዚአብሔር ስለ እርሷ ጣልቃ የገባ አምላክዋ መሆኑን እስራኤል እንድታውቅ ያደርጋታል። እስራኤል ባድማ በሆነች ጊዜ ኤዶም ደስ እንዳላት ሁሉ፣ ምድር ሁሉ ደስ በተሰኘች ጊዜ እግዚአብሔር ኤዶምን ባድማ ያደርጋታል። ይኸውም እግዚአብሔር በዚህ ምድር ላይ ወደር የሌለውን ደስታ በሚያመጣበት በመጨረሻው ዘመን ኤዶም በምድር ላይ ፈጽሞ አትኖርም ማለት ነው። በዚህ ፍርድ አማካይነት የእስራኤልን አምላክ እንዳለና እርሱም እውነተኛው አምላክ እንደ ሆነ ኤዶም ታውቃለች።

ለ. የማበረታቻ ትንቢት (36፥1-15)

1-12 ይህ የማበረታቻ ትንቢት የፍርድ ንግግርን ቅርጽ የያዘ ነው። የእስራኤል ምድር በባዕዳን መንግሥታት ላይ የሚከተለውን ክስ ማቅረብ ይችላል፡- ጥንታዊ ሃይማኖታዊ ስፍራዎችን ጨምሮ ብዙ መንግሥታት የእስራኤልን ግዛት የራሳቸው አድርገው ቈጥረዋል፤ በእስራኤል ዙሪያ የነበሩ መንግሥታት በወረራ የረገጡትን የፓለስቲና ስፍራ በሙሉ ባድማ አድርገዋል። የእስራኤል ምድር በመንግሥታት መካከል የክፉ ወሬና የሐሜት መፍለቂያ ሆኖአል።

እግዚአብሔር ጽድቁንና ሕዝቡን ደግፎአል። በአብርሃማዊው ኪዳን እስራኤልን የሚባርኩትን እንደሚባርክ፣ ሕዝቡን የሚረግሙትን ግን እንደሚረግም ተናግሮአል (ዘፍ 12፥3)። ስለዚህ እግዚአብሔር እስራኤል ከመንግሥታት የሚበቃትን ያህል ስድብና ውርደት የተቀበለች መሆኗን ገልጾአል። ቅዱስ ቍጣው ለብዝበዛ ሲሉ እስራኤልን በደስታና በማዋረድ ሲያሰጨንቁ በነበሩት ላይ ይነዳል። መንግሥታት በእስራኤል ላይ ወርደትን እንዳመጡ ሁሉ፣ እግዚአብሔርም ውርደትንና ኀፍረትን በእነርሱ ላይ ያመጣል። እግዚአብሔር እጁ የብርታትና የቍጣ ትእምርት ይሆናቸው ዘንድ በመንግሥታት ላይ በጉልሕ መልኩ ያነሣል። ሕዝቡንም በነጻነት ያሰናብታል።

በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ በረከት አብዛኛውን ጊዜ ፍርድን ተከትሎ የሚመጣ ነው። ስለዚህ በተናቁ መንግሥታት ላይ ፍርድን በመናገር፣ ምድሪቷን ለመጨረሻው ጊዜ መልሶ ለማቋቋም ዝግጅት ማድረጉን በመግለጽ እግዚአብሔር እስራኤልን ለማጽናናት ዘወር አለ። ይህ የእርሱ ሥራ ይሆናል።

የእስራኤል ተራሮች ከሴይር ተራራ ጋር ተነጻጽረዋል። ከእስራኤል ውድቀት በኋላ የሴይር ተራራ በእስራኤል ተራሮች ላይ ተብሎ ሊታሰብ ይችላል። የእስራኤል ምድር በሕዝቅኤል ዘመን ባድማ ቢሆንም እግዚአብሔር ምድሪቱን በሞገስ ይመለከታል፤ እርሷንም እንደ ገና ምርታማና ፍሬያማ በማድረግ ለእስራኤል መልሶ መቋቋም ያዘጋጃታል። ምድሪቱም የገዛ ሕዝቧን መልሳ በመቀበል ትበረታታለች። እስራኤላውያን በሙሉ ወደ አገራቸው ይመለሳሉ። ሕዝቡና እንስሳቱ ከበፊት ይልቅ እጅግ ብዙ ይሆናሉ። ከተማዎቿ እንደ ገና የሰዎች መኖሪያ ይሆናሉ፤ የፈራረሰው ሁሉ እንደ ገና ይገነባል። ለአብርሃማዊው ኪዳን እግዚአብሔር ያለውን ታማኝነት ለመግለጥ፣ እግዚአብሔር ተስፋ የገባላትን ምድር ሁሉ በመጨረሻ ትወርሳለች፤ ይህም ከዚህ በፊት ከቶ እውን ሆኖ የማያውቅ ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡን መልሶ ሲያቋቁም፣ የምድሪቱ ሁኔታ ካለፈው የላቀ ይሆናል። ነገር ግን ምድሪቱ እንደ ገና ልጆችዋን (እስራኤላውያንን) ዐጥታ ባዶዋን ትቀር ይሆን? በፍጻሜው ጊዜ ባለው በመጨረሻው የማሰባሰብ ዘመን እግዚአብሔር ሕዝቡን በተስፋዱቱ ምድር እንደ ገና ሲሰበስብ ምድሪቱ እንደ ገና ልጆቿን እንደማታጣ፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል በማረጋገጥ ተናግሮአል። ይህን ታላቅ ነገር ያደረገው እግዚአብሔር እንደ ሆነም ሁሉ ይገነዘባሉ።

13-15 በምድሪቱ ላይ የቀረበው ሁለተኛው ክስ ሰዎችን ቦጫጭቃ እንደ በላችና በመንግሥታትም መካከል "ልጅ አልባ" እንደ ሆነች የሚያሳይ ነው። ይህ ማጠቃለያ የተሰጠው እስራኤል ካሳለፈቻቸው አያሌ አስከፊ ሁኔታዎች የተነሣ ነው። ሕዝቡን በምድሪቱ ላይ መልሶ ስለሚያቋቁም እግዚአብሔር ይህንን ክስ ይሽረዋል። ከዚያም እስራኤል ዳግም የንቀትና የውርደት ሥላቅን ከአሕዛብ አትሰማም። እንዲህ ዐይነቱን ወቀሣ እንደ ገና አትሰማም፤ ሕዝብ መሆኗ ይቀጥላል እንጂ ከእንግዲህ ሕዝብ ከመሆን ከቶ አትቀምም። ገጥቸው ይሆን ዘንድ መሲሑን እንደሚሰጣቸው ለምርኮኞች በመናገር እግዚአብሔር ያበረታታቸዋል፤ ከእስራኤል ምድር ጨቋኝ መንግሥታትን በማስወገድም ለሕዝቡ እንደ ገና መቋቋም መንገድን ያዘጋጃል።

4. የምድሪቱ እንደ ገና መቋቋም (36፥16-37፥14)

ያለፈው የሕዝቅኤል መልእክት ለሕዝቡ መመለስ እግዚአብሔር የከነዓንን ምድር ያዘጋጀ መሆኑን ገለጸ በማቅረብ ይደመድማል (36፥1-15)። ይህም እግዚአብሔር የውጭ ጨቋኞችን ከምድሪቱ ያስወገደበትንና (35፥1-5) ወደዚህ ወደ

ዐዲሱ ርእስ ጕዳይ የተደረገውን ተፈጥሮኣዊ ሽግግር ያቀርባል፤ ይኸውም እስራኤል በገዛ ምድርዋ እንደ ገና መልሳ የተቋቋመችበት ሁኔታ ነው። ይህ ትንቢት በሕዝቡ መመለስ ላይ አጽንዖት ያደርጋል፤ አራት ጕልሕ ክፍሎችንም ይዞኣል። ይኸውም ሕዝቡ እንደ ገና ሲሰበሰብ፣ የእግዚኣብሔር ጸጋና ምሕረት ሙሉ በሙሉ እንዲገኝባት ነው፤ በአሕዛብ መካከል የተበተኑበት ምክንያትም በንጽጽር መልክ በቢጋር ቀርቦኣል (36፥16-21)። እግዚኣብሔር ሕዝቡን እንዴት አድርጎ መልሶ እንደሚያቋቁም በሚገባ ተገልጾኣል (36፥22-32)፤ መልሶ መቋቋማቸው የሚያመጣው ድንቅ ውጤትም በተከታይ ተቀምጦኣል (36፥33-38)። በባቢሎን ምርኮ ላሉት መበረታቻ ይሆን ዘንድ፣ ሕዝቅኤል ይህን ንግር ለኣባቶቻቸው ተስፋ ሆኖ ወደ ተሰጠው ምድር የእግዚኣብሔር ሕዝብ የተመለሰበትን ሁኔታ በመግለጥ ኣቡቀለምሲኖዊ ራእይን በመስጠት ኣጠቃሎታል (37፥1-14)።

ሀ. የእስራኤል ሕዝብ የተበተኑበት ምክንያት (36፥16-21)

16-21 ወደ ኣባቶቻቸው ምድር ተመልሰው እስራኤላውያን በሚመሠረቱበት ኣስፈላጊነት ላይ ትኩረት ለማድረግ፣ ሕዝቅኤል እስራኤል በኣሕዛብ መካከል እንዲበተኑ ምክንያት የሆነውን ያለፈ ታሪክ በዐጭሩ ገለጠ። ለሙሴያዊ ኪዳናዊ ትእዛዞች ባለመታዘዝዋ፣ እስራኤል የተቀደሰ ምድርዋን ኣረከሰች፤ የእስራኤል ሁለት ታላላቅ ጥፋቶች (1) ሕፃናትን በመግደል፣ በሚራ፣ በዐመፅና በራስ ወዳድነት በሕዝብዋ መካከል የመጣው ደም መፋሰስ እና (2) የሕዝቡን ሕይወት በመበከልና ባለማቋረጥ ከእግዚኣብሔር ዘወር እንዲል ያደረገው ጣዖት ኣምልኮ ናቸው። ድርጊታቸው እጅግ ኣስጸያፊ ከመሆኑ የተነሣ፣ እግዚኣብሔር ሁኔታውን ኣንዲት ሴት በወር ኣበባዋ ጊዜ እንደምትረክስበት ዐይነት ቈጥሮታል። እስራኤል በኪዳኑ መሠረት ሕይወትዋን ሳትመራ ባለመታዘዝ ብትጸና፣ በቅጣት በኣሕዛብ መካከል እንደሚበትናት እግዚኣብሔር በእስራኤል ሕገ መንግሥት ማለትም በሙሴ ኪዳን ላይ ደንግጎኣል (ዘዳ 29፥1-30፥10)። እግዚኣብሔር ለተናገረው ቃሉ ታማኝ ስለ ነበር፣ እስራኤልን በዘመኑ በነበሩ ኣገሮች መካከል እንደ ዘር በተናት።

እግዚኣብሔር እስራኤላውያን ከእርሱ ጋር ወደ ነበራቸው ተገቢ ግንኙነት እንዲመለሱ ይፈልግ ስለ ነበር፣ ሕዝቡ መንገዱን የመከተል ኣስፈላጊነትን ይማሩ ዘንድ ከተስፋዪቱ ምድር ኣስወጣቸው። እርሱ የሕይወት ፈጣሪ እንደመሆኑ ሕይወት በሚጠቅም መንገድ እንዴት መመራት እንዳለበት ያውቃል፤ ስለሆነም የእግዚኣብሔር መንገድ ምንጊዜም እጅግ ጠቃሚ ነው። ነገር ግን በዚህ ሁኔታ እስራኤልን በመቅጣቱ፣ እግዚኣብሔር በዓለም ላይ የነበረውን ዝና ኣሥጊ ሁኔታ ውስጥ ከተተ። በጥንት ቅርብ ምሥራቅ ሕዝቡ በተለየ ሁኔታ ከምድሪቱ ጋር የተያያዘ ነበር። ሕዝብ በጦርነት፣ በራብ፣ በደዌ ወይም በሌላ ምክንያት ከምድሪቱ ተገድዶ ከወጣ፣ የዚያ ሕዝብ ኣምላክ ኣገሪቱን ለመጠበቅና ለመንከባከብ ዐቅም እንዳጣ መግለጫ ነበር። ስለዚህ እግዚኣብሔር እስራኤልን በኣሕዛብ መካከል ሲበትን፣ እነርሱ የእስራኤል ኣምላክ ደካማ እንደ ሆነ ገመቱ፤ በዚህም የእግዚኣብሔር ስም በመካከላቸው ተናቀ።

ነገር ግን እግዚኣብሔር ስሙ ለዘላለም እንዲረክስ ኣይፈቅድም። እስራኤል ወደ ምድርዋ የተመለሰችበት ሁኔታ የተመሠረተው፣ እግዚኣብሔር ለተናቀው ለራሱ ለቅዱስ ስሙ ካለው ርኅራኄ የተነሣ ነው (ከማቴ 6፥9፤ ከሉቃ 11፥2 ጋር ያነጻ)። በእስራኤል መልሶ መቋቋም፣ እግዚኣብሔር እርሱ ብቻ እውነተኛ ኣምላክ እንደ ሆነ ለኣሕዛብ ያሳውቃል። መሆን እንደሚገባውም የእርሱ ስም በቅድስና የተለየ ይሆናል። ስለዚህ እርሷ ስላደረገችው ታላቅ ነገር ሳይሆን የእርሱ ስም ገናናነት ይረጋገጥ ዘንድ፣ እግዚኣብሔር እስራኤልን በምድርዋ መልሶ ያቋቁማታል። በእግዚኣብሔር ቅድስናና ምሕረት እንዲሁም በሰው ልጅ ኀጢኣት መካከል ያለ ንጽጽር እንዴት ድንቅ ነው! ለኀጢኣት ምንም ዐይነት ምሕረት ከቶ ኣይገባም፤ ይሁን እንጂ እግዚኣብሔር ምንጊዜም በምሕረትና በይቅርታ እንዲሁም በጽድቅ ይሠራል።

ለ. የመጨረሻው መልሶ መቋቋም ዝርዝር ሁኔታ (36፥22-32)

22-23 በብሉይ ኪዳን ዘመን የኣንድ "ሰው" ስም ሰውየውን ይወክላል። እስራኤል በእግዚኣብሔር ላይ ባደረገችው ዐመፅ፣ ሕዝቡ የእግዚኣብሔርን ማንነት ኣዋረዱ። ስለዚህ እስራኤልን በምድርዋ ላይ መልሶ ባቋቋማት ጊዜ የተገለጠው የኪዳን ታማኝነቱ ብቻ ሳይሆን፣ ዲበ ተፈጥሮኣዊ በሆነ መንገድ እስራኤልን በማሰባሰቡም በኣሕዛብ ሁሉ ፊት ክብርና ቅድስና ለስሙ ያመጣል። ከዚያም ጻድቁና ኣፍቃሪው የእስራኤል ኣምላክ እውነተኛ ኣምላክ እንደ ሆነ ኣሕዛብ ያውቃሉ።

24-32 የእስራኤል በምድርዋ ላይ እንደ ገና መመሥረት ኣስደናቂ በሆነ ሁኔታ በእነዚህ ቊጥሮች በዝርዝር ቀርቦኣል። ሙሴ ሙሴያዊውን ኪዳን በሞዓብ ሜዳ ላይ ለእስራኤላውያን እንደ ገና በተናገረበት ጊዜ፣ እግዚኣብሔር ከምርኮ በኋላ እስራኤልን መልሶ እንደሚያቋቁም ኣስቀድሞ ተናግሮኣል (ዘዳ 29፥1-30፥10)። በዚህ ስፍራ የመልሶ መቋቋም ሂደት ሲገለጽ መመለስን፣ ኮንጒኣት መንጻትን፣ የመንፈስ ቅዱስን የማስቻል ኀይልና ብልጽግናን የተከተለ ነው።

(1) እግዚኣብሔር ሕዝቡን ከተበተኑበት ከኣሕዛብ ምድር ያስወግዳቸዋል። በኣብርሃማዊው ኪዳን ለኣባቶቻቸው ወደ ተነገረው ወደ ከነዓን ምድር መልሶ ይሰበስባቸዋል፤ ያመጣቸዋልም።

(2) እግዚኣብሔር እስራኤልን በምድርዋ ካረከሳት ኀጢኣት ሁሉ ከጣዖት ኣምልኮ ያነጻታል። "በንጹሕ" ውሃ መርጨት" በመለኮታዊ ይቅርታ በደም የማንጻት ምሳሌ ነው (ከዘፀ 12፥22፤ ከዘሌ 14፥4-7፡ 49-53፤ ከመዝ 51፥7፤ ከ1ቆሮ 6፥11 ጋር ያነጻ)። ሥርዐታዊው መንጻት ከልማድ በላይ እንዲሆን ለማድረግ፣ ሕዝቡ እግዚኣብሔር የሚያሳስባቸውን ያለፈውን በደላቸውን ማወቃቸውና ንስሓ መግባታቸው እጅግ ኣስፈላጊ ነው። ሕዝቡ በኀፍረትና በውርደት ያለፈውን መተላለፋቸውን ሲጠሉት፣ መንጻታቸው የቱን ያህል በምሕረት የተገኘ እንደ ሆነ ያስተውላሉ። ልክ እንደዚሁ ሥርዐታዊው መንጻት ትርጉም ያለው መሆን ካለበት፣ እውነተኛ የኀጢኣት መንጻትና ይቅርታ መደረጉ የግል ነው። ይህም የሚሆነው በዐዲስ ኪዳን ኣማካይነት (ኤር 31፥31-34)፤ ሕዝቡ ወደ ምድሪቱ ይመለሱ ዘንድ በሞቱ ኀጢኣት ሁሉ ለእንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይቅር እንዲባል ያደረገውን መሲሑን ኣዳኛቸው ኣድርገው ይቀበላሉ። በደል ከእንግዲህ በኋላ ኣይታሰብም። ኣሮጌውን ዐመፀኛ የድንጋይ ልባቸውን ርኅራኄ ባለው የሥጋ ልብ ይለውጣሉ።

(3) በዐዲሱ ኪዳን ሕዝቡ በእግዚኣብሔር መንገድ መሄድ የሚያስችላቸውን (ከሮሜ 7፥7-8፥4፤ ከዕብ 8፥6-10፥39 ጋር ያነጻ) ዐዲስ መንፈስ፣ ማለት ቅዱሱን የእግዚኣብሔር መንፈስ ይቀበላሉ (ከ11፥19-20፤ 18፥31፤ 37፥14፤ 39፥29፤ ከኢዩል 2፥28-29፤ ከሐሥ 2፥17-18፤ ከ2ቆሮ 3፥6-18 ጋር ያነጻ)። ኣሮጌው ሙሴያዊ ኪዳን በዐዲስ ኪዳን በሚኖሩ ሰዎች ልብ ላይ ይጻፋል (ኤር 31፥33)። ስለዚህ ዐዲሱ ኪዳን ሕዝቡ ሊያሻሽሏቸው የሚያስፈልጉ ነገሮችን በመጨመር ሙሴያዊውን ኪዳን ተክቶኣል፤ ነገር ግን በፈሪሀ እግዚኣብሔር ለመኖር የሚያስችሉትን የተዘረዘሩትን መልካም፣ ጻድቅና ቅዱስ ትእዛዛት የሆኑትን በማስወገድ ኣይደለም። ዐዲሱ ኪዳን ለእንዴና ለመጨረሻ የኀጢኣት ይቅርታንና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነትን ዕድል ይሰጣል።

(4) ንጹሕ የሆነችው እስራኤል በቋሚነት "ማርና ወተት ከምታፈስ ሰው" (ቊ 1-15) ምድር በላይ ወደ ሆነችው ምርታማና ፍሬያማ ወደ ሆነችው ምድር በዘላቂነት ትመለሳለች። ምድሪቱም ከእንግዲህ ወዲያ እስራኤልን በመንግሥታት መካከል በራብ የተዋረደች እንድትሆን ኣትፈቅድላትም። ልክ እንደዚሁ እስራኤልንና እግዚኣብሔርን በተመለከተ የተገለጠው የሙሴያዊ ኪዳን ዐጭር ማጠቃለያ ኣሁን እውን በሆነ ቀመር ተገልጦኣል፤ ይኸውም እስራኤል የእግዚኣብሔር ሕዝብ መሆኗና እርሱም የእርሷ ኣምላክ መሆኑ ነው። ኣሕዛብ ይህን ኣስገራሚ ሽግግር በመመልከት እግዚኣብሔር መሓሪና ኣፍቃሪ ኣምላክ እንደ ሆነና እስራኤልም ይህ መልሶ መቋቋም የሚገባት እንዳልሆነች ይረዳሉ። ከዚህ ላይ የተገለጠው እስራኤል ዳግም በምድሯ ላይ እንደምትቋቋም

የሚያመለክተው ዝርዝር ጉዳይ ሁሉ በ538 ዓ/ክ በተጀመረው መመለስ አልተከሠተም።

ይህ ዐውድ ከታሪካዊው እይታ ጋር ሲታይ በዚህ ምንባብ የተገለጠው ወደ ከነዓን መመለስ በዘሩባቤል፣ በዕዝራና በነህምያ የተደረገውን እንደማያመለክት ግልጽ ነው፤ ነገር ግን የሚያመለክተው በመጨረሻው ዘመን በመሲሑ የሚደረገውን የመጨረሻና ፍጹም መልሶ መቋቋም ነው።

ሐ. የመልሶ መቋቋም ውጤቶች (36፥33-38)

33-38 የእስራኤል መልሶ መቋቋም ውጤት ታላቅ ይሆናል። ምድሪቱ ልክ እንደ ዔድን የአትክልት ስፍራ ፍሬያማ ትሆናለች። እንደ ገና የተገኘች ገነት ዐይነት ትሆናለች (ከኢሳ 51፥3፤ ከሮሜ 8፥19-22፤ ከ2ጴጥ 3፥13፤ ከራእ 21፥1-4፡ 23-27 ጋር ያነጻ)። የፈረሱ ከተሞች ይሠራሉ፤ ለብዙ ነዋሪዎችም እንዲሆኑ ይመሸጋሉ። ለእረኛው ለመሲሑ የሚበቃ ታላቅ መንጋ እንዲሆኑ፣ የእስራኤል ሕዝብ በቍጥር እጅግ ብዙ ይሆናሉ። በእስራኤል የተወሰኑት በዓላት በኢየሩሳሌም በሚከበሩበት ጊዜ ለብዙ መሥዋዕት እንዲሆኑ እንደሚጠበቁት የበግ መንጎች የሕዝቡ ቍጥር የሚበዛ ይሆናል። የእስራኤል መልሶ መቋቋም ዋነኛ ውጤት በዓለም ሁሉ የእግዚአብሔር ዕውቅና ገንኖ መውጣቱ ነው። አሕዛብም ያለ ጥርጥር የእስራኤል አምላክ ይህን ታላቅ መልሶ መቋቋም እንዳደረገ ያውቃሉ። እርሱ ደካማ አምላክ ሳይሆን የተናገረውን የሚፈጽም አምላክ እንደ ሆነ ይገነዘባሉ። እስራኤል ራሷም በትሕትና መልሶ ያቋቋማት አማላክዋ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ታውቃለች።

መ. የመልሶ መቋቋም ራእይ (37፥1-14)

1-2 ምዕራፍ 37 የሚጀምረው የሕዝቅኤል መልእክት ማጠቃለያ የሆነውን አቡቀለምሲሳዊውን ራእይ በመግለጥ ነው። አቡቀለምሲሳዊ ሥነ ጽሑፍ ለብዙ ሰዎች የተለመደ አይደለም። እንዲህ ዐይነቱ ሥነ ጽሑፍ ትእምርታዊ፣ ራእያዊ - ትንቢታዊ ሲሆን፣ ጸሓፊው ባየው ራእይ መሠረት የተጻፈና በመለኮታዊ ትርጓሜ የሚፈታ ብቻ ነው። ነገረ መለኮታዊ ይዘቱ በመሠረቱ ነገረ ፍጻሜያዊ ሲሆን፣ የተጻፈውም በጭቈናው ጊዜ ነው። አቡቀለምሲሳዊ ሥነ ጽሑፍ ሁለት ገጽታዎች አሉት፤ እነርሱም መልእክቱን የተቀበለው ሰውና በመልክአ ምድራዊ ሁኔታ አንጻር ራእዩ ለተቀባዩ የተሰጠበት መቼትና ከመለኮታዊ ፍቺው ጋር መልእክቱ ራሱ ናቸው።

ሕዝቅኤልን እግዚአብሔር ወደ አንድ ሸለቆ (ወይም ሜዳ) እግዚአብሔር አመጣው፤ ምናልባት ሕዝቅኤል በምዕራፍ 1 የእግዚአብሔርን ራእይ ያየበት ሸለቆ ሳይሆን አይቀርም። ሕዝቅኤል በእጅጉ በደረቁና ስፍር ቍጥር በሌላቸው ዐጥንቶች የተሞላን ሸለቆ ያያል። የእግዚአብሔር መንፈስ በሸለቆው ዙሪያ መራው፤ በደረቁ ዐጥንቶች መካከልም ያልፋል።

3-10 ይህ አቡቀለምሲሳዊ ራእይ ሁለት የተለያዩ ክፍሎች አሉት፤ (1) ሕዝቅኤል ያየውንና ያደረገውን እንደ ገና ቈጠረ፤ (2) ራእዩ ተተረጐመ (ቍ. 11-14)። እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እነዚህ ዐጥንቶች በሕይወት ይኖሩ እንደ ሆነ ጠየቀው። ሕዝቅኤልም ይህንን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ እንደ ሆነ መለሰ። ከዚያም ለእነዚህ ደረቅ ዐጥንቶች የሚነገር ትንቢት ለሕዝቅኤል ተሰጠው። እግዚአብሔር በሕይወት እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል። ጅማት፣ ሥጋ፣ ቈዳና እስትንፋስ በእነዚህ ዐጥንቶች ላይ ይመጣል፤ ሕያዋን ሰዎችም ይፈጠራሉ። ከዚያም እነዚህ "ትንሣኤ" ያገኙ ሰዎች እግዚአብሔር አምላክ እንደ ሆነ ያውቃሉ። ስለዚህ ሕዝቅኤል እግዚአብሔር እንዳዘዘው በትክክል ለእነዚህ ለሞቱ የደረቁ ዐጥንቶች ቃሉን ተናገረ። እርሱም እየተናገረ ሳለ፣ ሁሉም ዐጥንቶች በአንድነት በመሰብሰብ ጅማት፣ ሥጋና ቁርበት ለራሳቸው ወሰዱ። ነገር ግን ምንም እስትንፋስ በውስጣቸው አልነበረም።

ሕዝቅኤል እንደ ገና ትንቢት እንዲናገር ታዘዘ፤ በዚህ ጊዜ ነፋስ ከአራቱ ነፋሳት ይነፍስ ነበረ፤ ምናልባትም እነዚህን አካላት ለማደስ ሙሉ ኀይል ያለው እስትንፋስ (ማለትም ከሁሉም አቅጣጫ) እንደሚመጣ የሚያመለክት ነው፤ ይኸውም እነዚህ የተገደሉት በሕይወት ይኖሩ ዘንድ ነው። ይህን በማድረግ ሕዝቅኤል ይህ ሁሉ ሰራዊት ሕያው ሆኖ ያያል። የደረቁ ዐጥንቶች ሥጋ ለብሰው መታየታቸው እስራኤል በብሔራዊ ደረጃ በመጨረሻ እንደ ገና መቋቋሚን የሚያመለክት ነው። "እስትንፋስ" (ደግሞም ነፋስ ወይም መንፈስ፣) በእነዚህ መልሰው በተቋቋሙት ላይ መግባቱ መንፈሳዊ ተሐድሶን የሚያመለክት ነው። ይህ ከምዕራፍ 36 ተከታታይ ሐሳብ የተወሰደ ነው።

11-14 የአቡቀለምሲሳዊ ራእዮች ዝርዝር ጉዳይ ሁሉ አይተረጐምም፤ ግንዛቤ መደረግ ያለበት የራእዩ ዋና ሐሳብ ብቻ ዐጥንቶቹ የእስራኤል ቤት ሁሉ ማለትም በቍ. 9 ላይ የተገደሉት ተብለው የተመለከቱት እንደ ሆኑ ተገልጸአል (ከ36፥10 ጋር ያነጻ)። እነዚህ ዐጥንቶች ስለ ራሳቸው ሦስት ነገሮችን ያውጃሉ፤ (1) የደረቁ ናቸው፤ ይህም ለረዥም ጊዜ የሞቱ ሰዎች ዐጥንቶች የታወቀ ባሕርይ ነው። የዘመኑ ርዝማኔ የሚያመለክተው የዐጥንቶቹን ደረቅነት ቢሆንም፣ አጽንዖት የሚያደርገው ግን በመንፈሳዊ ሙትነት ላይ ነው። (2) ዐጥንቶቹ ተስፋቸው የወደመ መሆኑን ያውጃሉ። የእስራኤል ሕዝብ እንደ ገና ሕዝብ እንሆናለን ወይም የእግዚአብሔርን ኪዳኖች መፈጸም በዐይናችን እናያለን የሚል ተስፋ አልነበራቸውም። (3) ዐጥንቶቹ አንዳቸው ከሌሎች የተለያዩ እንደ ሆኑ ይናገራሉ፤ ይኸውም ሕዝቡ የተለያዩና የተበታተኑ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፤ ያ አሁን ያሉበት ሁኔታ ነው።

አንዱ ዐጥንቶቹ ከታዩ ራእዩ በራሱ ግልጽና ምንም ዐይነት ትርጓሜ የማያስፈልገው ነው። ራእዩ በጉልሕ የሚያሳየው ለተወሰነ ጊዜ ሞቶ የነበረ ሕዝብ እንደ ገና በሕይወት መልሶ መቋቋሙን ነው። ይህም በሁለት ደረጃ የሚከናወን ነው የመጀመሪያ አካላዊ (ወይም ተፈጥሮአዊ) መልሶ መቋቋም ሲሆን፣ ሁለተኛው መንፈሳዊ ተሐድሶ ነው። የሰው ልጅ አፈጣጠርም ተመሳሳይ ሂደትን የተከተለ ነው፤ በመጀመሪያ ሥጋ ተፈጠረ፣ በኋላም እስትንፋሱ ተገኘ (ከዘፍ 2፥7 ጋር ያነጻ)።

ይህ ብሔራዊና መንፈሳዊ መልሶ መቋቋም በሌላ የአነጋገር ዘይቤ ፍቺው በተሰጠበት ክፍል ተብራርቶአል፤ ይኸውም ከመቃብር መነሣት ነው። የደረቁ ዐጥንቶች ሕያው ሕዝብ መሆናቸውና ከመቃብር የመነሣት ምሳሌ ሁለቱም የሚገልጹት ተመሳሳይ እውነትን ነው። በራሳቸው ምድር እንደ ሕዝብ ያልነበሩትና በአሕዛብ መካከል ተበትነው የነበሩት እስራኤል በገዛ ምድራቸው ይቀመጡ ዘንድ በአካል ይመለሳሉ። በራእይ የታዩት ሁኔቶች ታምራዊ እንደ ሆኑ ሁሉ፣ የእስራኤል መልሶ መቋቋምም እንዲሁ ይሆናል። አንድ ጊዜ በምድሪቱ ከተሰበሰቡ፣ እግዚአብሔር በዐዲሱ ኪዳንና በምዕራፍ 36 ላይ በተላለፈው መልእክት መሠረት መንፈሱን በውስጣቸው ሲያስቀምጥ መንፈሳዊ ተሐድሶን ያገኛሉ።

የእነዚህ ሰድስት መልእክቶች አጠቃላይ ዐውድ ወደፊት የሚፈጸም ነው። በመጨረሻው ዘመን እስራኤል በሕዝብነት መቋቋማቸው በእይታ ውስጥ ነው (ከምዕራፍ 36-37 ዙሪያ ያሉትን ምዕራፎች ያነጻጽሩ)። ይህ አካላዊ መመለስ ወይም መንፈሳዊ መመለስ ብቻ አይደለም። በመጨረሻው ዘመን ከአሕዛብ መካከል የእስራኤል ብሔራዊ መሰባሰብ፣ የእስራኤል መንፈሳዊ ለውጥና በተስፋዱቱ ምድር የብሔራዊ መንግሥት መመሥረት ሁሉ በምዕራፍ 36፥16-38 የተጠቀሱና በዚህም አቡቀለምሲሳዊ ራእይ የሚታዩ ናቸው።

ይህ በእውነት የሕዝቡ "ዳግሞ ልደት" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል። በዚህ በወደፊቱ የእስራኤል ዳግም ልደት፣ እግዚአብሔር ሦስቱን ዐይነተኛ ነገሮች ማለትም ሕዝብ፣ መንግሥትና ምድር እንደ ገና ይሰጣቸዋል። የዚያ ጊዜ እስራኤላውያን በ36፥16-37፥28 በተጠቀሰው መልሶ መቋቋም በአንድ ላይ እንዲሰባሰቡ ተደርገዋል። ምድሪቱም በ35፥1-36፥15 በተጠቀሰው ትንቢት ተሰጥታለች። የዐዲሲቷ እስራኤል መንግሥት በምዕ 40-48 በተጠቀሰው መሠረት ይሰጣል። እስራኤል መልሳ ስትቋቋምና እንደ ገናም ሕዝብ ስትሆን፣ ሕዝቡ በግልጽ ይህን ያደረገው እግዚአብሔር እርሱ ብቻ እንጂ ከአምላካቸው ውጭ ሌላ ማንም እንዳይደለ በርግጥ ያውቃሉ።

5. በተፈጸመው ኪዳን መካከል የእስራኤል አንድ ሕዝብ መሆን (37፥15-28)

15-17 ቀደም ብለው ተከፋፍለው የነበሩት ሁለቱ የእስራኤልና የይሁዳ መንግሥታት እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ምድሪቱ

በሚመልስበት ጊዜ አንድ ሕዝብ እንደሚሆኑ ለመግለጽ ሕዝቅኤል ትእምርታዊ የሆኑ ድርጊቶችን ተጠቀመ። ከዚያም እስራኤል የተሰጣት ኪዳን ሁሉ ተፈጽመውላት ሙሉ ትሆናለች። ሕዝቅኤልም ሁለት በትሮችን ወሰደ። በአንድ በትር ላይ የይሁዳንና የተባባሪዎቿን ስም ሲጽፍ፣ በሌላው በትር ላይ ኤፍሬምንና የተባባሪዎቿን ስም ጻፈ። እንግዲህ አንደኛው በትር ያለፈውን የይሁዳን መንግሥት ሲወክል፣ ሌላው ደግሞ የቀደመውን የድሮውን የእስራኤል መንግሥት የሚወክል ነው። ሕዝቅኤል እነዚህን ሁለት በትሮች በእጁ ሲይዛቸው አንድ በትር ሆኑ።

18-28 የሁለቱ በትሮች አንድ መሆን የሚያመለክተው ይሁዳና እስራኤል በአብርሃማዊው ኪዳን መሠረት በተሰጣቸው ምድር እውን የሚሆነውን የአንድ ሕዝብ መንግሥት ነው። ከእንግዲህም ይህ መንግሥት ከቶ አይከፈልም። የዳዊት ታላቁ ልጅ መሲሑ እርሱ ብቻውን ንጉሥና እረኛ እንዲሁም በዳዊታዊ ኪዳን መሠረት አንድ በሆነችው እስራኤል ላይ ከቶ አቻ የሌለው ልዑል ይሆናል። ይህ አንድ የሆነ የእግዚአብሔር ሕዝብ በመሲሑ ሞትና በዐዲሱ ኪዳን መሠረት፣ በተሰጠው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ሙሉ ይቅርታን በማግኘት ካለፈው ጣዖት አምልኮና በደል ይነጻል። ዐዲሱን ኪዳን በመቀበል እስራኤል በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የመሲያዊ ኪዳንን የጽድቅ ትእዛዞች ለመከተልና በእነርሱም መሠረት ለመኖር ትችላለች። ከዚያም እስራኤል በመጨረሻ እግዚአብሔር ለራሱ የፈጠራት ልዩና ምርጥ ሕዝብ ትሆናለች፤ የሙሴን ኪዳን ፍጹም የሆነ ሐሳብ በመጨረሻ በመፈጸምም እርሱ አምላካቸው ይሆናል።

እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ያሏት ሌሎች ኪዳኖች ሲሟሉ፣ ወደ ምድርዋ ተመልሳ በመትቋቋምበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር ከእርሷ ጋር የሰላም ኪዳን ያደርጋል (ከ34፥25-29 ጋር ያነጻ)። በዚህ የሰላም ኪዳን እስራኤል በምድርዋ ላይ መልሳ ትመሠረታለች፤ የሕዝብዋ ቍጥር ይጨምራል (ከዘፍ 22፥17-18 ጋር ያነጻ)፤ እግዚአብሔርም በሕዝቡ መካከል ለዘላለም ማደሪያውን ያስቀምጣል። እርሷም ከአሕዛብ መካከል ተመርጣ የተሰየች የእግዚአብሔር ልዩ ርስት ትሆናለች። ከእስራኤል በቀር የእግዚአብሔር ማደሪያ በተለየ ሁኔታ በመካከሉ ያለ ሌላ ሕዝብ አይኖርም።

የእስራኤል ኪዳኖች በሙሉ ሲፈጸሙ፣ እግዚአብሔር የሰላም ኪዳኑን ከእስራኤል ጋር ያደርጋል። በመሲሑ በንጉሥዋ አገዛዝ ሥር ለዘላለም በሰላም ትኖራለች።

6. የተሰፋዱቱ ምድርና የባዕዳን ወረራ (38፥1-39፥29)

እነዚህ ሁለት ምዕራፎች የኢየሩሳሌምን መውደቅ ለመናገር ከዚያ አምልጦ የመጣው ሰው በምሽት ከተናገራቸው ከእነዚያ መልእክቶች የተለዩ ናቸው ተብሎው ሊታዩ ይችላሉ (ከ33፥21-22 ጋር ያነጻ)። ይሁን እንጂ በምዕራፍ 38-39 ያለው መልእክት መታየት ያለበት የኢየሩሳሌም መውደቅ ወሬ ከመጣበት ምሽት በፊት ሕዝቅኤል ያስተላለፈው ስድስተኛውና የመጨረሻው መልእክት እንደ ሆነ ነው።

ባለፉት ዐምስት ዋና ዋና መልእክቶች ውስጥ ዋናው ሐሳብ የእስራኤል ምድር ነበር፤ እርሱም እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር በገባው ኪዳን ተጠናቋል (የእነዚህን መልእክቶች ዐጭር ማጠቃለያ ለማግኘት በ33፥21-39፥29 ያሉትን መግቢያ ሐተታዎች ይመ)። በምዕራፍ 38-39 ያለው መልእክት በመጀመሪያ በዝርዝር የሚያቀርበው የእስራኤል ሕዝብ በአጠቃላይ በምድራቸው ያለ ሥጋት በሰላም መኖራቸውን ነው። ያለ ቅጥር፣ ያለ መወርወሪያ ወይም ያለ በሮች ይኖሩ ነበር (38፥7)። የቀረው የመልእክቱ ክፍል ባዕዳን ጎይሎች የእስራኤልን ምድር ለመያዝ የሚያደርጉትን ጥረት የሚያመለክት ነው። ጥረታቸው ውድቅ ይሆናል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለሰላም ኪዳኑና ለስሙ ታማኝ ስለ ሆነ ለእስራኤል ይቆማል። በእስራኤል ሽንፈትና መበተን ቅዱስ ስሙ እንዲረክስ አይፈቅድም (36፥20፤ 39፥7)።

የምዕራፍ 38-39 ሁነቶችና ዝርዝር ጕዳዮች በአንጻራዊነት ሲታዩ በቀላሉ ሊስተዋሉ የሚችሉ ናቸው። ዋና ዋና የአተረጓጐም ችግሮች ገጸ ባሕርያትንና ቦታዎችን መለየት እንዲሁም እነዚህ ሁነቶች የተፈጸሙበትን ጊዜ ማወቅ ነው።

ሀ. በጎግ ላይ የተነገረው የመጀመሪያው የፍርድ ትንቢት (38፥1-23)

1-3 ሕዝቅኤል የሞሳሕና የቶቤል ዋና አለቃ በሆነው በማጎግ ምድር በጎግ ላይ ትንቢት ተናገረ። ለእነዚህ ስሞች የተሰጠው ትክክለኛ ፍቺ ግልጽ ባለመሆኑ የዚህን ክፍል ትርጓሜ እጅግ ብዙ እንዲሆን አድርጎታል። የተሰጠው ማንኛውም መፍትሔ ግን "ጎግ" ለሚለው ስም ለተሰጠው ፍቺ ተቀባይነት ያለው በቂ ድጋፍ የለውም። በዚህ ዐውድ በስምም ሆነ በማዕረግ የቀረበው ጎግ ግን የሰው ስም ይመስላል። እንደ አጋጣሚ የጎግ ማንነት በግልጽ መታወቅ የዚህን ምንባብ ፋይዳ በመተርጐም አስፈላጊ አይደለም። በእነዚህ ሁነቶች ጊዜ ላይ ይበልጥ ሐሳብ መስጠት፣ የጎግ ማንነት በጥቅሉ ምን እንደሚመስል የሚረዳ ሐሳብን ይሰጣል። ማጎግ የያፌት ዝርያ ሲሆን (ዘፍ 10፥7)፣ ታሪክ ጸሓፊው ዮሴፈስ እንዳመለከተው የስካይታውያን ምድር ነው፤ ይህም በጥቍር ባሕርና በካስፒያን ባሕር ዙሪያ ያለውን ተራራማ ምድር የሚያመለክት ነው።

የሞሳሕና የቶቤል ዋና አለቃ (ሮሽ) የሚለው ሐረግ በተለያየ መንገድ ተተርጕሞአል። በሐረጉ ውስጥ የሚገኘው "ሮሽ" የሚለው ብዙ ችግሮችን ፈጥሮአል። የተለመደው ትርጕም "ራስ" ወይም "አለቃ" የሚለው ነበር። አንዳንዶች ለመልክአ ምድራዊ አካባቢ በተሰጠው ሮሽ በሚለው የተጻፈውን ስም ይተረጕሙታል፤ ነገር ግን "ሮሽ" የሚባል አገር ስለ መኖሩ የሚያመለክት ማስረጃ የለም። አንዳንዶች ደግሞ ከዛሬዪቱ ሩሲያ ጋር ያያይዙታል፤ ነገር ግን "ሩሲያ" የሚለው ስም በዐሥራ አንደኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ የመጣ ስም ነው።

በዕብራይስጥ ሁለቱም "አለቃ" እና "ዋና" የሚሉት፣ ሞሳሕና ቶቤል ከተባሉት መልክአ ምድራውያን ቃላት ጋር የተያያዙ ናቸው። ሰዋሰዋዊ በሆነ አተርጓጐም የሞሳሕና የቶቤል ዋና አለቃ (ራስ ወይም ገሸር) በሚል ሐረጉን ማየት ይሻላል። ሞሳሕ የያፌት ልጅ ስም እንደ ሆነ በዘፍ 10፥2 እና በ1ዜና 1፥5 ተጠቅሶአል፤ ስሙም ቶቤል ከሚለው ቃል ጋር ተያይዞአል (ከ27፥13፤ 32፥26 ጋር ያነጻ)። እጅግ ጥቂት የሆኑ መረጃዎች ምሳሕና ቶቤል ከዛሬዪቱ ቱርክ በስተ ምሥራቅ ማለትም በደቡብ ምዕራብ ሩሲያና በሰሜን ምዕራብ ኢራን አካባቢ ያሉት አገሮች ወይም መልክአ ምድራዊ አካባቢዎች እንደ ሆኑ ያመለክታሉ። ይሁን እንጂ ይህ የተሰጠው እነዚህን የቦታ ስሞች ከዛሬዎቹ አገሮች ጋር ለማያያዝ የሚያስችል መሠረት የለውም። ምሳሕና ቶቤል የተባሉትን ከዛሬዎቹ ሞስኮና ቶቦልስክ ከተባሉት ከሩሲያ ከተሞች ጋር ለማያያዝ የሚያስችል ድጋፍ ሰጪ መረጃ የለም።

ስለዚህ ማጠቃለል የሚቻለው ጎግ የማጎግ አካባቢ ሰው መሆኑን፣ እንዲሁም እርሱ የሞሳሕና የቶቤል መልክአ ምድራዊ አካባቢ አለቃ ዋና ገሸር መሆኑን በመግለጽ ነው። እነዚህ ምድሮች ወይም አገሮች ከጥቍር ባሕርና ከካስፒያን ባሕር በስተ ደቡብ በዛሬዎቹ ተርክ፣ ሩሲያና ኢራን አካባቢ ያሉ ቦታዎች እንደ ሆኑ በማጠቃለል መግለጽ ይቻላል።

4-16 ይህ ክፍል የሚያመለክተው እስራኤል በምድርዋ ላይ በእግዚአብሔር መልሳ የተቋቋመችበትን ሂደት ተከትሎ በሰላምና ያለሥጋት የኖረችበትን ሁኔታ ነው። እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገባውን ኪዳን ፈጸመ፤ ሕዝቡም ቃሉን በመፈጸም ታማኝ በሆነው አምላካቸው ብርታት በወረሷት ፍሬያማ ምድር በሰላምና ያለሥጋት በደስታ መኖር ጀመሩ። ነገር ግን ሳይታሰብ ሰላማቸው ታላቅ አደጋ ደረሰበት። እንደ ደመና ማዕበል ድንገተኛ ጨለማ፣ ከምድር ከማንኛውም አቅጣጫ አስፈሪ መንግሥታት ወደ ሰሜናዊው አካባቢ ጥፋትን ይዘው ሲመጡ ታየ። የምሳሕና የቶቤል ዋና አለቃ የሆነው ጎግ ዕቅዱን የሚመራ የጦር አዛዣቸው ነበር። ሕዝብ ከማንኛውም አቅጣጫ እየመጣ ተባብሮት ነበር፤ እነርሱም ፋርስ ከምሥራቅ፣ ኩሽ (ኢትዮጵያ ኑብያ) ከደቡብ ምዕራብ፣ ፉጥ (አብዛኛውን ጊዜ ሊብያ የምትባለው) ከምዕራብ ወይም ከደቡብ ምዕራብ፣ ጎሜር (ምናልባት ጥንታውያን ሱሜራውያን) እና ቤት ቴርጋማን (ምናልባት ጥንታዊትዋ ከጥቁር ባሕር በስተ ደቡብ ምሥራቅ ያለችው ቲል ጋርሙ) ከሰሜን ናቸው። እነዚህ ሁሉ እስራኤልን ለመውረር የተዘጋጁ ነበሩ።

ጎግ ክፉ ዕቅድ ዐቅዷል። በአምላክዋ ብቻ የምትታመነውን መከላከያ የሌላትን እስራኤልን ለመውጋት ተነሥቷል። ራስዋን አልጠበቀችም፤ የከተማዋ ቅጥሮች ያለ በርና ያለ ብረት መወረወሪያ ናቸው። ጎግ ምድሪቷን ሊዘርፍና፣ ሀብታቸውን ሁሉ ሰብሰቦ ይዘርፋል። ሌሎች አገሮች እንደ ሸባና እንደ ድዳን ያሉ፣ በተርሴስ ካሉ ነጋዴዎቻቸው ጋር ይደነግጣሉ፤ ጎግ እስራኤልን ለመበዝበዝና ለመዝረፍ ባቀደው ዕቅድ ላይ ጥያቄ ያቀርባሉ።

ይሁን እንጂ ጎግ የራሱ ሐሳብ እንደ ሆነ ቢገምትም፣ እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ ጎግን ወደ እስራኤል እንዳመጣው ግልጽ አድርጎአል። በምሳሌያዊ አነጋገር እንደ ተገለጸው እግዚአብሔር በመንጋጋው ላይ መንጠቆ አስገብቶ ጎግን ወደ እስራኤል ያመጣዋል። ይህ እግዚአብሔር ሕዝቡን መልሶ ከሚያቋቁምበት እንዲሁም በሰላምና በጸጥታ በተስፋዱቱ ምድር ከሚያስቀምጥበት የሰላም ኪዳን ጋር የማይጣጣም ቢመስልም፣ እግዚአብሔር ይህ ወረራ በጎግ እንዲነሣሣ ያደርጋል፤ ከዚያም መላው ዓለም እንደ ገና እግዚአብሔር ታማኝ አምላክ እንደ ሆነ ያውቃል። ጎግ በእስራኤልና በምድሪቱ ላይ ምንም ዐይነት ጉዳት ከማድረሱ በፊት እግዚአብሔር ቃል እንደ ገባው ጎግን ድል ያደርገዋል (ከ34፥22፡28-29፤ 36፥1-15 ጋር ያነጻ)። ሁሉም እግዚአብሔር ቅዱስ፣ ትክክለኛና የማይለወጥ ታማኝ መሆኑን ያውቃሉ፤ ስሙም እንደ ገና እንዲረክስ አይፈቅድም።

የዚህ ወረራ ጊዜ በእነዚህ ጥቅሶች በተገለጡት አረፍተ ነገሮችና በመልእክቱ ዐውድ ተመልክቶአል፤ ይኸውም በመጨረሻው ዘመን የሚፈጸመው የእስራኤል ወርቃማው ዘመን ነው። “ከብዙ ቀን በኋላ” (ቍ. 8) የሚለው ሐረግ ያልተወሰነን ጊዜ የሚያመለክት ነው። ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ እስከ መጨረሻው ዘመን የሚደርስ ነው (ከኤር 32፥14፤ ከዳን 8፥26 ጋር ያነጻ)። “በኋለኛው ዘመንም” የሚለው አገላለጽ በብሉይ ኪዳን የሚገኘው በዚህ ጥቅስ ብቻ ሲሆን፣ መረዳት የሚገባም በዐውዱ መሠረት ነው። “በዚያ ቀን” የሚለው ሐረግ በመጨረሻው ዘመን የሚሆነውን ወረራ የሚያመለክት ሲሆን፣ ይህ ሐረግ በአብዛኛው የሚያመለክተው በመሲሑ መንግሥትና በመሲሑ ዘመነ መንግሥት የሚሆነውን የእስራኤልን የመጨረሻ መልሶ መቋቋም ነው (ከዘፍ 49፥1፤ ከኢሳ 2፥2፤ ከኤር 23፥20፤ 30፥24፤ ከሆሴ 3፥5፤ ከሚክ 4፥1 ጋር ያነጻ)።

ቍጥር 8 እና 12 ይህ ወረራ የታቀደው እስራኤል በአሕዛብ መካከል በመውጣት ዳግም ወደ ምድርዋ ከተመለሰች በኋላ ከሰይፍ ባመለጠችበት ጊዜ መሆኑን ያመለክታሉ። ይህ እንደ ገና የመሰባሰብ ጊዜ እስራኤል በምድርዋ መልሳ ተቋቁማ በሰላምና በጸጥታ መኖር ከጀመረች በኋላ በመቀጠል የሚከተል ነው (36፥22-37፥14)። እጅግ በሰላምና በጸጥታ ከመኖርዋ የተነሣ ራስዋን በምሽግ መከላከል እንኳ አስፈላጊ አልመሰላትም። እስራኤል ከባቢሎን ከተመለሰችበት ከ539 ዓዋክ በኋላ እንዲህ ዐይነት የከበረ ሕይወት አይታ አታውቅም። “በሰላም ይኖራሉ” የሚለው ሐረግ እስራኤል መልሳ ከተቋቋመች በኋላ መሲሓዊ የሆነውን ሰላምንና ጸጥታን እንደምትለማመድ የሚያመለክት ነው። እነዚህ ንግሮች የመጨረሻውን ዘመንና የዳዊታዊ፣ መሲሓዊ መንግሥትን በተመለከተ ከተገለጡት ሌሎች ንግሮች ጋር የተገናኙ ናቸው (28፥26 ይመ፤ ከኤር 23፥6፤ 33፥16፤ ከዘካ 14፥11 ጋር ያነጻ)። በመጨረሻም የእነዚህ ስድስት የሕዝቅኤል መልእክቶች አጠቃላይ ዐውድ የሚናገረው ወደፊት እስራኤል በመሲሑ አማካይነት በምድርዋ መልሳ የምትቋቋምበትን ሁኔታ ነው። ስለዚህ የዚህ ወረራ ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ በተስፋዱቱ ምድር መልሰው ከተቋቋሙ፣ በመሲሑ ጥበቃም በሰላምና በጸጥታ መኖር ከጀመሩ በኋላ የመጨረሻው ዘመን ነው።

17-23 እግዚአብሔር በፍርዱ ጎግን የሚያሳስበው የእግዚአብሔር ባሪያዎች ማለትም ነቢያት በዘመን መጨረሻ ስለሚሆነው ስለዚህ ወረራ መናገራቸውን ነው። በሌሎቹ ነቢያት ትንቢት ውስጥ በግልጽ ስለ ጎግ የተጠቀሰ ነገር ባይኖርም፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች ላይ ስለሚፈጸመው የመጨረሻ ውድቀት አጠቃላይ ማስረጃዎች አሉ (ከዘዳ 30፥7፤ ከኢሳ 26፥20-21፤ ኤር 30፥1-21 ጋር ያነጻ)።

እስራኤል በእግዚአብሔር ላይ ያላት መታመን ከንቱ አልቀረም። ጎግ በእስራኤል ምድር ላይ በሚመጣበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔር የሚቃጠል ቍጣ በጎግ ላይ ይነዳል። እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ በመሆኑ የራሱ የሆነውን በታማኝነት ይጠብቃል። የእግዚአብሔር አስፈሪ እሳት ድንገት በጎግና ባስከተተው ሰራዊት ላይ ይወርዳል። መላዱቱ ምድር በታላቅ የምድር መናወጥ ትነቃነቃለች፤ መናወጡም ተራሮችን፣ ኰረብቶችንና ማንኛውንም ቅጥር ይገለብጣል። በምድር፣ በባሕርና በሰማይ ያለው ማንኛውም ፍጡር፣ ጎግንና ተከታዮቹን ለማጥፋት በተገለጠው በሁሉን ቻይ የእግዚአብሔር ሀልዎት በታላቅ ፍርሀትና ድንጋጤ ይሸበራል። የጎግ ሰራዊትና የተከተሉት አሕዛብ እግዚአብሔር ዲበ ተፈጥሮአዊ በሆነ መዓት በሕመም፣ በደም መፋሰስ፣ በዝናብ ዶፍ፣ በበረዶ ድንጋይና በሚያቃጥል ድኝ ሲያጠፋቸው ሲያዩ፣ በመሸበር እርስ በርስ በሰይፍ ይገዳደላሉ። ጎግን በዚህ ሁኔታ ሲያጠፋው እግዚአብሔር ቅዱስ ስሙን በማስከበር፣ ራሱንም ከፍ ከፍ በማድረግ በአሕዛብ ሁሉ ፊት እርሱ እውነተኛ አምላክ መሆኑን ያሳያል። የእግዚአብሔር ፍርድ ሁሉ ዐላማ በሌላ መንገድ ላይሆን እርሱን ለማወቅ ወደ እርሱ ለሚመጡ ሁሉ በታላቅነቱና በቅድስናው ራሱን ለማሳወቅ ነው።

ለ. እግዚአብሔር በጎግ ላይ የተናገረው ፍርድ መደጋገሙና በስፋት መገለጹ (39፥1-29)

1-2 እነዚህ ጥቅሶች የ38፥1-16 ማጠቃለያን እንደ ገና የሚገልጹ ናቸው። እግዚአብሔር በሉዐላዊነት ጎግ እስራኤልን እንዲወርር ያስገድደዋል፤ ሆኖም ታማኝነቱን ለእስራኤል ለማሳየት ጎግን ያሸንፈዋል።

3-8 ዲበ ተፈጥሮአዊ የሆኑትን ነገሮች ማለትም የመሬት መንቀጥቀጥን፣ በሽታንና የዝናብ ዶፍን ተጠቅሞ ጎግንና ሰራዊቱን ያጠፋ መሆኑን በማሳየት ሕዝቅኤል 38፥17-23 እግዚአብሔርን ገለጸ። ጎግ ሙሉ በሙሉ ትጥቁን ይፈታል። ሰራዊቱ እንዳለ በምድሪቱ ማለትም በተራሮችና በሜዳ ላይ ይወድቃል። የጎግና የሰራዊቱ በሰይፍ ማለቅ ለሰማይ ወፍና ለምድር አራዊት ምግብ ይሆናል (ከቍ. 17-20 ጋር ያነጻ)። ከዚህ በተጨማሪ እግዚአብሔር አስፈሪ ፍርድን በጠረፎቻቸው ወይም በደሴቶቻቸው ተመቻችተው እየኖሩ ባሉት በማጎግና በተባባሪዎቿ ምድር ላይ ያመጣል። እግዚአብሔር የጎግን መሸነፍ እርሱ የእስራኤል ቅዱስ እውነተኛ አምላክ መሆኑን አሕዛብ እንዲያውቁ ይጠቀምበታል። በሰላም ኪዳን ዘላለማዊ ሰላምንና ጸጥታን ለመስጠት ለሕዝቡ የገባውን ኪዳን ሊፈጽም ለኪዳኑ ታማኝ መሆኑን እግዚአብሔር በዚህ ያረጋግጣል። በእስራኤል ድል መሆንና መበተን እንደ ገና ቅዱስ ስሙ እንዲረክስ እግዚአብሔር አይፈቅድም። እስራኤልም በምላሹ በመካከልዋ የእግዚአብሔር ስም እንዲከበር ታደርጋለች፤ የእስራኤል ምድር ሊወረር ባለበት በዚህ የመጨረሻ ሙከራ እርሱ በማይለወጥ ታማኝነቱ ያደረገላትን ጥበቃ አይታለችና። ለአይሁድ ምርኮኞች መጽናናት ይሆን ዘንድ የጎግ መደምሰስ የማይቀር መሆኑን እግዚአብሔር እንደ ገና በአጽንዖት ተናገረ። “የእስራኤል ቅዱስ” የሚለው ሐረግ እግዚአብሔር ክፉት ፈጽሞ የራቀ መሆኑን ያመለክታል። በጎግ ላይ በመፍረድና የገባውን ተስፋ በመፈጸም የራሱንና የምድሩን ቅድስና ጠበቀ።

9-10 እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ የጎግን ሰራዊት ትጥቅ አስፈታ። የተሰበሰበው የጦር መሣሪያ እጅግ ታላቅ ከመሆኑ የተነሣ፣ ሁሉንም ለማቃጠል እስራኤላውያን ሰባት ዓመት ፈጅቶባቸዋል። እነዚህ መሣሪያዎች ለሰባት ዓመት የእስራኤልን የነዳጅ ፍላጎት ያሟላሉ፤ ለሰባት ዓመትም ያላትን የነዳጅ ሀብት ክምችት መጠቀም አያስፈልጋትም። ጎግና ተባባሪዎቹ እስራኤልን ለመበዝበዝ ቢፈልጉም እንኳ፣ አሁን እነርሱን የሚበዘብዙት እስራኤላውያን ይሆናሉ።

11-16 የጎግ ሰራዊት ብዛት እጅግ ብዙ ከመሆኑ የተነሣ፣ የሞቱትን ለመቅበር እጅግ የሚያስቸግር ነበር። የእስራኤልን ምድር ለማንጻት ሁሉም መቀበር ነበረባቸው። አንድ የተወሰነ ሽለቆ “በምሥራቅ በኩል ወደ ባሕሩ በሚጓዙበት ሽለቆ” የተባለው የመቀበሪያ ስፍራ እንዲሆን ተለይቶ ነበር። ወደየትኛው ባሕር እንደሚያመለክት የተለየ አቅጣጫን ባያሳይም ስፍራው ለቀብሩ ተለይቶአል። የተጠቀሰው ባሕር ሙት ባሕር ከሆነ፣ ሽለቆው አንድም ከባሕሩ በስተ ምሥራቅ ያለው ማለትም ከእስራኤል ድንበር ውጭ የሆነው ስፍራ ወይም መንገደኞችን ከሙት ባሕር ወደ ምሥራቅ የሚመራው ሽለቆ ሊሆን ይችላል። በመጠኑም ቢሆን የዚህ ሽለቆ ዝርዝር መግለጫ የሚያሳየው በታችኛው ገሊላ ያለውን የኤስድራሲዮን ሽለቆ ነው። የተጠቀሰው ባሕር ሜድትራኒያን ከሆነ፣ ይህ ሽለቆ

በእስራኤል ምድር በስተ ምሥራቅ ያለ ሸለቆ ይሆናል። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ያለው መረጃ የሳሳ በመሆኑ፣ የዚህን ሸለቆ ትክክለኛ ስፍራ ለማመልከት የሚሞክሩ ንድፈ ሐሳቦች ሁሉ ጥያቄ ሳያነሡ አያልፉም። ክፍሉ በግልጽ የሚያቀርበው የጎግና የአያሌ ሰራዊቱ ቀብር እጅግ ከፍተኛ ስለሚሆን በዚህ ሸለቆ ለሚያልፉ መንገደኞች ዕንቅፋት እንደሚሆን ነው። ከዚህም የተነሣ ሸለቆው "የሐሞን ጎግ ሸለቆ" ("የጎግ መንጋ") ተብሎ ይጠራል።

እጅግ ብዙ የሆነውን ሬሳ ለመቅበርና ምድሪቱን ለማንጻት ከሰባት ወር በላይ ያስፈልጋል (ከዘሌ 5፥2፤ 21፥1፤ ከዘፀ 21፥1-9 ጋር ያነጻ)። በእስራኤል ያለ እያንዳንዱ ሰው በዚህ ሥራ ይሳተፋል። ለሰበት ወር ያህል በቀላሉ የሚታዩትን ሬሳዎች ይቀብራሉ። ከሰባት ወር በኋላ ጎላፊዎች ሥራውን ለማሠሥና "ምድሪቱን ለማጽዳት" በሁለት ቡድን የተከፈሉ ሰዎችን ይቀጥራሉ (ቁ. 14)። አንዱ ቡድን ሳይቀበር የቀረውን ሬሳ የሚያስስ ሲሆን፣ ዐፅም እንኳ ቢያገኝ ምልክት ያደርግበታል። እነዚህ ዐጥንቶች ከተሰበሰቡ በኋላ ለቀብር በሁለተኛው ቡድን ወደ ሐሞን ጎግ ሸለቆ ይወሰዳሉ። ሐሞና ("መንጋ") ተብላ የምትጠራው ከተማ በሐሞን ጎግ ሸለቆ የምትገኝ ስትሆን፣ ምናልባትም የሙታን ከተማ እንደ ሆነች የምትቈጠር ናት። የከተማዪቱ ባሕርይ እንዴት እንደ ሆነ አይታወቅም። የጎግ መቀበር ለእግዚአብሔር የመታሰቢያ ቀን ይሆናል፤ የዚህ ጠላት ሞት ሕዝቡን ለዘላለም ለመጠበቅ እግዚአብሔር ታማኝ እንደ ሆነ ይህም ለስሙ ክብር እንደሚያመጣ ይገልጻልና።

17-20 የሞቱት ጠላቶች ዐፅም አሠሣ የተነሣሣው የበሰበሰ ሥጋ የሚበሉ ወፎችና ሥጋ በል እንስሳት የጎግንና የተከታዮቹን ራስ እስኪጠግቡ ድረስ እንዲበሉ ስለ ተረጉ ሊሆን ይችላል። ይህ ታላቅ ዕርድ "መሥዋዕት" ተብሎ ሲጠራ፣ ይህም እግዚአብሔር በእስራኤል ተራሮች ላይ ለወፎችና ለዱር አራዊቶች ያዘጋጀው ነው (ከኢሳ 34፥6፤ ከኤር 46፥10 ጋር ያነጻ)። የመሰፍንት፣ የተዋጊዎችና የእንስሶቻቸው ሥጋና ሥብ ይበላል፤ ደማቸውም እነዚህ ወፎችና አራዊት እስኪጠግቡና እስኪሰክሩ ድረስ ይጠጣል። የባሳን "አውራ በጎች ጠቦቶች፣ ፍየሎችና ወይፈኖች" ምንጊዜም የሠቡና ብርቱዎች ናቸው። የዚህ አገላለጽ ምስስሎሽ የተሸነፉት መሰፍንት ደካሞች ሳይሆኑ፣ የምድር ብርቱዎችና ኃያላን መሆናቸውን በአጽንዖት ለመግለጽ ነው።

እነዚህ ሁለት ምዕራፎች ከዮሐንስ ራእይ ጋር የሚገናኙባቸው አንዳንድ ምልክታዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል። በዮሐንስ ራእይ 19-21 ላይ ቁ. 17-21 ታላቅ ድግስ ግልጽ በሆነ መልክ ተጠቅሶአል። ራእይ 19፥11-16 የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ስማያዊ ክሥተት ያቀርባል። ጌታ ክርስቶስ ከሰራዊት ጋር ሆኖ በነጭ ፈረስ ላይ ተቀምጦ በጽድቅ ሊፈርድና ሊዋጋ ይመጣል። የታላቅ መዓቱን ወይን መጭመቂያ እየረገጠ ሲሄድ ከአፉ የሚወጣው ሰይፍ አሕዛብን ያጠፋል። ራእይ 19፥17-21 የተለየ ክፍል ነው፤ ይኸውም በጌታ ላይ በተሰበሰቡትና በአፉም ሰይፍ በጠፋት የአሕዛብ ኃያላን መሪዎች ላይ በሚደረገው ድግስ ማለትም በታላቁ የጌታ እራት ላይ መልአኩ ወጥቶ ለወፎች የግብዣ ጥሪ የሚያደርግበት ነው። አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ተያዙ፤ ወደ እሳተ ባሕርም ተጣሉ። ወፎቹም ከሌሎቹ ከተገደሉት በመብላት ራሳቸውን ያጠግባሉ።

በታላቁ "የእግዚአብሔር እራት" ሐዋርያው ዮሐንስ በግልጽ በሕዝ 39፥17-20 የተገለጠውን በጎግ መንጋ ግድያ ላይ የነበረውን ድግስ አያይዞ አቅርቦታል። ሐዋርያው ዮሐንስ በቀጥታ ሕዝ 39ን ከራእ 19 ጋር አገናኝቶ ለምን በአገላላጹ አቀረበው? መልሶ መቋቋምና መሲሓዊ ዐውድ የሆነው የሕዝቅኤል መልእክት የሐዋርያው ዮሐንስም ስለ ሆነ ነው። በራእ 19፥11-16 ላይ የተገለጸው እስራኤል ወደ ገዛ ምድርዋ ከተመለሰች በኋላ (ከራእ 7 ጋር ያነጻ) በዳግም ምጽአት ጊዜ የመሲሑን ስማያዊ ክብር በውልብታ የሚያመለክት ነው። አውሬውና የምድር ነገሥታት ከሰራዊቶቻቸው ጋር (ራእ 19፥19) በሕዝቅኤል መጽሐፍ ከተገለጹት ከጎግ ጋር ከተሰበሰቡት አሕዛብ ጋር በርግጥ ተመሳሳይ ናቸው (ሕዝ 38፥4-7፡9፡15፡22፤ 39፥4፡11፤ ራእ 19፥15፡ 18-19፡21)። በሕዝቅኤል 38-39 ያለው የእግዚአብሔር ፍርድ መሲሑ በራእ 19 ላይ የእግዚአብሔርን የቍጣ የወይን መጭመቂያ ከሚረግጥበት ሁኔታ ጋር ተመሳሳይነት አለው። በሕዝቅኤል መጽሐፍ እግዚአብሔር በጎግ ላይ ሰይፍን ይጠራል፤ በራእይ መጽሐፍ ላይም ከእግዚአብሔር አፍ የሚወጣው ሰይፍ በእርሱ ላይ የሚወጡትን አሕዛብ ይመታል (ከሕዝ 38፥21፤ ከራእ 19፥15፡ 20 ጋር ያነጻ)።

ግልጽ የሆነ የድርጊት ወጊዜ ቅደም ተከተል ሁኔታ በራእይ መጽሐፍ አልቀረበም። ስለዚህ የመሲሑ ዳግም ምጽአት የሚሆንበት ጊዜ እንደ ሆነ ቢታወቅም፣ የራእ 19ን ትክክለኛ ወቅት ማወቅ እጅግ አስቸጋሪ ነው። መሲሑ አሕዛብን ሁሉ ሊያሸንፍና ምናልባትም የአርማጌዶንን ጦርነት ሊያጠናቅቅ የሚመጣ ይመስላል። ይሁን እንጂ የሕዝ 38-39 ዐውድ የሚያመለክተው እስራኤል ከሰይፍ አምልጣ መልሳ በመቋቋም በሰላም ያለ ሥጋት የምትርበትን ሁኔታ ነው። እንዲህ ዐይነቱ ሁኔታ ከአርማጌዶን ጦርነት ጋር የሚስማማ አይሆንም። ይህ ጦርነት በራእ 19 ላይ በግልጽ ስላልተወሣ፣ ምናልባት በራእይ 19 ላይ የሚገኙት ሁኔታዎች በሕዝ 38-39 ላይ እንደ ተተነበየው በተለይ ስለ አውሬው መጥፋት እንጂ ከአርማጌዶን ጋር ግንኙነት ላይኖራቸው ይችላል። ስለ አርማጌዶን ቀደም ሲል በራእ 14 እና 16 ላይ ተገልጾአል። ስለዚህ መሲሑ ከራሱ መመለስ ጋር የአርማጌዶንን ሁነቶች የሚያጠቃልል ቢሆንም፣ በመከራው መደምደሚያና በሺህ ዓመት መጀመሪያ ላይ በመካከል የሚታየው፣ ማለት ሊሆን በሚችለው ሽግግር ውስጥ የሚገኘው ሁኔታ፣ የእስራኤልን ምድር ለመያዝ የመጨረሻ ሙከራ የሚያደርገው የአውሬው መሸነፍ ይሆናል።

ይህ ምንባብ የሕዝቅኤል 38-39 ፍጻሜ ከሆነ፣ ዮሐንስ ለምን በራእይ 19 ላይ ጎግን አልጠቀሰውም? ዮሐንስ ለመጨረሻ ጊዜ አውሬውን የጠቀሰው በራእይ 17 ላይ ነበር። ዮሐንስ የጎግን ስም በራእይ 19 ቢጠቅስ ኖሮ፣ አንባቢዎቹ በራእይ 19 ዐውድ ውስጥ ማን መሆኑን ባላወቁ ነበር። "አውሬ" የሚለውን ስም በመጠቀም፣ በሕዝቅኤል ላይ እንደ ተገለጠውም ወፎች እስኪጠግቡ ድረስ ከመመገባቸው በመነሣትና ጎግ ወረራ አካሂዷል ብሎ በማመልከትም ዮሐንስ ለአንባቢዎቹ አውሬውን ከጎግ ጋር አንድ አድርጎ ለማቅረብ ፈለገ። ስለሆነም አንባቢዎቹ በራእ 19፥17-21 ያሉትን ሁነቶች የጎግ ትንቢት እንደ ተፈጸመ ይመለከታሉ፤ ይህም በሕዝ 38-39 ያለው ሁነት መቼ እንደ ተፈጸመ ትክክለኛውን ወቅት ለማመልከት ይረዳል።

እንደ ዋና ሐሳብም፣ በወፎች ራት ላይ በሚገኘው በራእ 19 እና በሕዝ 39 መካከል ባለው ማጣቀሻ ላይ የሕዝ 28-39 ዝርዝር ጉዳዮች በራእ 19 ዐውድ አልተጣሱም። የራእይ 19 ምንባብ የትንቢቱን ፍጻሜ፣ የጎግ ወረራን ጊዜና በሕዝ 38-39 ውስጥ ያለውን ሽንፈት ቢደግፍም የእነዚህን ጉዳዮች አፈጻጸም ሙሉ እይታ ለማግኘት የሚያስችሉ ሌሎች ጉዳዮችም ተከተዋል። በመጨረሻው ዘመን ትንቢታዊ መርሐ ግብር ውስጥ የእነዚህን ሁኔታዎች ጊዜ መተርጐም እጅግ አስቸጋሪ ጉዳይ ሲሆን፣ ይህም አንዳንድ አመለካከቶችን አስከትሎአል (ሙሉ የሆነውን ሐሳብ ይበልጥ ለመረዳት የእንግሊዝኛውን መጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ማለትም EBC 6:937-40 ይመልከቱ)።

አያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች በሕዝ 38-39 ያሉት ሁኔታዎች በራእ 20፥7-10 በተገለጸው መሠረት ከሺሁ ዓመት ዘመን በኋላ የተፈጸሙ መሆናቸውን ይናገራሉ። ለዚህ አመለካከት ጠንካራ መከራከሪያ ነጥብ ሆኖ የቀረበው በራእ 20፥8 ላይ ስለ ጎግና ስለ ማጎግ የተሰጠው ግልጽ የሆነ አመላካች ሐሳብ ነው። ስለ ሺሁ ዘመን የቀረበው ዐውድ ስለ እስራኤል ከተነገረው የሰላም፣ የብልጥግናና ያለሥጋት የመኖር ሁኔታ ጋር በእጅጉ የሚስማማ ነው። መልሶ የመቋቋም ሁኔታ እውን ሆኖአል። አሕዛብ የጎግን ዐመፅ ለመመልከት በጊዜው ይኖራሉ። የሰዎችን ሬሳ ለመቅበርና የጦር መሣሪያዎችን ለማቃጠል በቂ ጊዜ ይኖራል።

ይሁን እንጂ ይህን አመለካከት በተመለከተ የቀረቡ ተቃውሞዎች አሉ፤ እነርሱም፡-

1. የጎግ ሰራዊት ሰሜናዊ ትብብር ሲሆን፣ በራእይ የተጠቀሰው ሰራዊት ግን ከአራቱም የምድር ማእዘን የመጣ ነው የሚል ሐሳብ ቀርቧል። ነገር ግን ልብ ሊባል የሚገባው ጎግ ያስተባበራቸው መንግሥታት ከምድር ከማንኛውም አቅጣጫ የመጡ መሆናቸው ነው (38፥5-6)።

2. ሕዝቅኤል ስለ ኢየሩሳሌም ምንም ሳይናገር፣ ዮሐንስ ግን አሕዛብ ውዲቷን ከተማ ከበቧት ማለቱ ልብ ሊባል ይገባል። ለዚህ በተሰጠው ምላሽ ዮሐንስ የጠቀሳት ውዲቷ ከተማ ሕዝቅኤል ከተናገረው ቃል ጋር አለመቃረኑ ነው፤ ምክንያቱም ጎግ በእስራኤል ተራሮች ይመጣል መባሉ በርግጥም ኢየሩሳሌምን ያካትታል።

3. የጦር መሣሪያዎቹ መቃጠልና የቡድኖቹ መወገድ በሺሁ ዘመን መጨረሻ ላይ ከሚፈጸሙት ሁነቶች ጋር የሚጋጭ ሐሳብ ነው ተብሎ ይታመናል፤ ይኸውም የታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ ወዲያውኑ ይከተላልና ነው። ይሁን እንጂ የራእይ መጽሐፍ ድርጊት ወጊዜ ቅደም ተከተል በተለይም በራእ 19-20 ያለውን የሁነቶችን ቅደም ተከተል የሚጠይቅ አይደለም። ከዚህ ላይ የሽግግር ወቅት መኖሩ አሳማኝ ጉዳይ ነው።

ስለዚህ ራእይ 20፥7-10ም የሕዝ 38-39 ፍጻሜ እንደ ሆነ ይገመታል። ፍጻሜው ራቅ ባሉ ሁለት ወቅቶች ሊታይ ይችላል፤ አንደኛው በራእ 19፥17-21 ውስጥ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ በራእ 20፥7-10 ውስጥ ነው። በሕዝ 38-39 እና በራእ 19፥17-21 መካከል ያለው ትስስር የሚገኘው የእስራኤልን ምድር እንደ ገና ለመያዝ ታላቅና የመጨረሻ ሙከራ ያደረገውን ክፉውን እግዚአብሔር ያሸነፈ መሆኑን በሚገልጸው ነው። ራእይ 19 ሙከራው ተሰናክሎ አውሬውና ሰራዊቱ (በምድር የሰይጣን ዋና ወኪል) መደምሰሳቸውን ሲገልጽ፣ ራእይ 20 ደግሞ የሰይጣን ውድቀት የዚህ ዋና ሐሳብ ድምድሜ እንደ ሆነ አድርጎ ያቀርባል። ሁለቱም የመጨረሻና ታላቅ የእስራኤል ጠላቶች ናቸው። ዮሐንስ እያንዳንዱን ሁነት በቀላሉ ሲያጠቃልል፣ ሙሉ ዝርዝር ሐሳቡ በሕዝ 38-39 ላይ ተገልጸ ነበር። ዮሐንስ በራእይ 19 ያለውን ታላቅ እራት በመጠኑ ሲያመላክት አንባቢዎቹ ከዚህ ቀደም ያወቁትን ማለትም የሕዝ 38-39 ሁነት ሁሉ ልብ እንዲሉት ለማድረግ ነው። የአውሬው ማንነት እንዳይምታታ ሲባል ጎግ የሚለው ቃል አልገባም። ግን አንባቢዎች የሰይጣንን ዐመፅ ከሕዝ 38-39 ሁነቶች ጋር አንድ አድርገው እንዲመለከቱት በራእ 20 ላይ ሰይጣንና ጎግ አንድ ሆነው ቀርበዋል። ሁለቱም ምንባቦች የሚያብራሩት የእስራኤል ዋነኛ ጠላቶች የሆኑት አውሬውና ሰይጣን የእስራኤልን ምድር ለመያዝና እስራኤል ከእግዚአብሔር የተቀበለችውን የተስፋ ቃል ለማጥፋት ያደርጉትን ሙከራ ነው።

ሐ. የስድስቱ የሌሊት መልእክቶች ማጠቃለያ (39፥21-29)

21-29 የጎግ መውደም የኢየሩሳሌምን መውደቅ ወሬ አምልጦ ከወጣው ሰው ከመስማቱ በፊት ባለው ምሽት ሕዝቅኤል ላቀረባቸው ለስድስቱ የመጽናናት መልእክቶች ትልቅ እመርታ ነው። የጎግ መሸነፍ እግዚአብሔር እስራኤልን በተስፋዱቱ ምድር መልሶ እያቋቋማት ሳለ ለአሕዛብ የገለጠው የመጨረሻ የክብሩ መገለጫ ነው። እግዚአብሔር በጎግ ላይ ባወረደው ቅጣት ሌሎች መንግሥታት ሁሉ በፍርሀት ደንግጠው ይቆማሉ።

እነዚህ ስድስቱ መልእክቶች እግዚአብሔር በተለይም ምድሪቱን በተመለከተ የተጠቀሱት እግዚአብሔር ለእስራኤል በገባው የተስፋ ኪዳን ላይ አጽንዖት አድርገዋል። እስራኤል መልሳ በመቋቋሟ በእግዚአብሔር ድንቅ ታማኝነትና ከጎግ ጥቃትም ያገኘችውን ጥበቃ ስትለማመድ፣ ከዚያች ቀን ጀምሮ ወደፊት ያለምንም ጥያቄ እግዚአብሔር ጌታዋ፣ እውነተኛ አምላኳና ከእርሱም በቀር ሌላ እንደሌለ ታውቃለች። በሌላ በኩል አሕዛብም እግዚአብሔር እስራኤልን ለምርኮ አሳልፎ ሲሰጥ ደካማ አምላክ እንዳልነበር፣ ነገር ግን እርስዋ ባለመታመን ኀጢአትዋ ከፈጸመችው በደል የተነሣ ፊቱን በእስራኤል ላይ እንዳዞረ ያውቃሉ። ልክ እንደዚሁ እግዚአብሔር እስራኤልን ከአሕዛብ መካከል አውጥቶ ወደ ምድርዋ የመለሳት፣ የተስፋዱቱን ምድር የሰጣት፣ ምንም ዐይነት የጭቄና ሥጋት ሳይኖርባት በሰላም እንድትቀመጥ ያደረጋት ከምሕረቱና ከታማኝነቱ የተነሣ እንደ ሆነ ይረዳሉ። በዚህ መንገድ እግዚአብሔር ራሱን በአሕዛብ ዐይን ፊት ቅዱስ አድርጎ ያቀርባል። አሕዛብ እንደሌሎች አማልክት እነዳይቁጥሩት ስሙ እንዳይረክስ እጅግ ቀናተኛ ነው። ከእንግዲህም ወዲያ እግዚአብሔር ፊቱን ከእስራኤል ዘወር አያደርግም፤ ሌላውም እንዲጨቍኑት አይፈቅድም! ከእንግዲህም ማንም በእስራኤል ላይ ሽብር አያመጣም! እግዚአብሔር እስራኤልን ያነጻል፤ ውርደታቸውና ኀጢአታቸውን በማስወገድ በዐዲሱ ኪዳን መሠረት መንፈሱን በላይዋ ላይ ያፈስሳል። ለእስራኤል የተገቡት ኪዳኖች በሙሉ ይፈጸማሉ። በሰላሙ ኪዳን መሠረት በንጉሥዋ በመሲሑ እየተዳደረች እስራኤል ለዘላለም ያለሥጋት ትኖራለች!

መ. የእግዚአብሔር ክብር ይመለሳል (40፥1-48፥35)

በእነዚህ ዘጠኝ ምዕራፎች ስለ ቤተ መቅደሱ የቀረበው ገለጻ፣ ቤተ መቅደሱ በእግዚአብሔር ክብር መሞላቱ፣ በዚያ የቤተ መቅደስ አምልኮ የሚቀርበው የመሥዋዕት ሥርዐት ክህነታውያት አገልግሎቶች፣ እንዲሁም በምድሪቱ የተመደበው የነገደችና የካህናት አሰፋፈር ለአንባቢው እጅግ ግልጽ ሆኖ ቀርቦአል። ነገር ግን የዚህ ሁሉ ትርጉም ምንድን ነው? እነዚህ ምዕራፎች ሊታዩ የሚገባቸው ቃል በቃል ነው ወይስ ዘይቤአዊ በሆነ መልክ? የመጽሐፉ ይህኛው ክፍል ችላ ሊባሉ የማይገባቸውን እንቆቅልሾችና በጣም አስቸጋሪ ሐሳቦች ያዘለ በመሆኑ፣ በተቻለ መጠን ትክክለኛ ግንዛቤ ይገኝ ዘንድ አንዳንድ መሠረታዊ ጉዳዮችን መመርመሩ ጥበብ ነው።

በትንቢተ በሕዝቅኤል 40-48 ያለው ክፍል ታሪካዊ ነው ወይስ ትንቢታዊ? እነዚህ ምዕራፎች የተተረጐሙት የሰሎሞንን ቤተ መቅደስ፣ የዘሩባቤልን ወይም የሄሮድስን እንዲሁም ወደፊት የሚኖረውን የሺሁን ዘመን ቤተ መቅደስ ወይም ዘላለማዊቷን ቤተ መቅደስ እንደሚያመለክቱ ሆነው ነው። አንዳንዶች በምስያ በመተርጐም ስለ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ስለ ምድራዊ በረከቶቿና ክብሯ የተነገረ ነው በማለት የሚያስተምሩ ሲሆን፣ ሌሎቹ ምንባቡን የሚረዱት ዛሬ ክርስቶስ የሚያገለግልበትን የሰማያዊ ቤተ መቅደስ እውንነት በትእምርት እንደሚያመለክት አድርገው ነው።

ታሪካዊው አፈጻጸም በምንባቡ ውስጥ ከምናገኘው ዝርዝር ሐሳቦች ጋር የሚጣጣም አይደለም። የሰሎሞን፣ የዘሩባቤል ወይም የሄሮድስ ቤተ መቅደሶች በምዕራፍ 40-42 ላይ የተገለጸውን ቤተ መቅደስ ንድፍና መጠን የሚጋሩ አይደሉም። በባሕርዩ ሙሴያዊ ቢሆንም በምዕራፍ 43-46 የተገለጠው የአምልኮ ቅደም ተከተል በእነዚህ ምዕራፎች በተገለጠው ዐይነት በታሪክ ውስጥ ተጠብቆ አያውቅም። በ47፥1-12 በተገለጠው ውስጥ ከቤተ መቅደሱ ወጥቶ የሚፈሰው ወንዝ ከላይ በተጠቀሱት በሌሎቹ ሦስት ታሪካውያን አብያተ መቅደሶች ውስጥ አልተጠቀሰም። ከዚህ ወንዝ ጋር በንጽጽር የቀረቡት ወንዞች የሚታዩት በዘፍ 2፥8-14 እና በራእ 22፥1-2 (ከኢሳ 35፥6-7፤ ከኢዩል 3፥18፤ ከዘካ 14፥8 ጋር ያነጻ) ብቻ ነው። የምድሪቱ መልክአ ምድራዊ መጠንና የየነገዶቹ አመዳደብ ዛሬ ከሚታየው ጋር ተመሳሳይ አይደለም፤ ወይም ባለፉት ዘመናት በዚሁ መልክ አልተመለከቱም። ምዕራፍ 45፤ 47-48 ይፈጸሙ ዘንድ መልክአ ምድራዊ ለውጦች የሚያስፈልጉ ይሆናሉ። ስለዚህ አንድ ሰው የወደፊቱን እንጂ የእነዚህን ምዕራፎች ታሪካዊ ፍጻሜ (ያለፈ ወይም ያሁን) ተስፋ ማድረግ የለበትም።

የእነዚህን ምዕራፎች ችግር ለመፍታት ዘይቤያዊ የሆነውን ወይም "መንፈሳዊ" የሆነውን አመለካከት መያዝ የሚጠቅም አይሆንም፤ ይልቁን ዐዳዲስ ችግሮችን ይፈጥራል። አንድ ሰው የቃል በቃል ትርጓሜን ሲተው፣ የምንባቡ የተለያዩ ክፍሎች እንደ ተርጓሚው ፍላጎት የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ። በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የሚገኙት አቡቀለምሲሳውያን ራእዮች እንኳ የተለመደውን ሰዋስዋዊ ታሪካዊ ሥነ ፍታቴ የሚፈልጉ ናቸው። እነዚህን በሌላ መንገድ መተርጐም ለሕዝቅኤል ማስጠንቀቂያ የተሰጠበትን ይህን ራእይ ለመተርጐም ሊጠበቅ የሚገባውን መመሪያ መቃወም ነው፤ ይኸውም ሕዝቅኤል የቤተ መቅደሱን ንድፍ በተመለከተ እያንዳንዱን ጥቃቅን ዝርዝር ነገር መጻፍ እንዳለበት፣ መመመሪያዎቹና ዝርዝር ጉዳዮቹ ሁሉ በጥንቃቄ ሊጠበቁ እንዲሁም እያንዳንዱን ነገር በተባለው መሠረት ሊከተሉት እንደሚገባ ነው (40፥4፤ 43፥10-11፤ 44፥5)። ስለዚህ ዘይቤያዊ የሆነውን የአተረጓጐም ስልት መከተል በሕ 40 - 48 ያሉትን ጉዳዮች ለመፍታት አይጠቅምም።

የእነዚህን ምዕራፎች አጠቃላይ የጊዜ ማለፍ መረዳት የምንችለው ምናልባት በመላው መጽሐፍ ውስጥ ያለውን የሕዝቅኤልን ሐሳብ እድገትና ፍሰት በመመልከት ነው። ሕዝቅኤል በታሪካዊው የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ

የእግዚአብሔር ክብር መገኘት፣ እስራኤልም የሙሴን ኪዳን የማፍረስ ኀጢአት በመፈጸሟ የእግዚአብሔር ክብር ወጥቶ መሄዱን አስይቶአል። የኢየሩሳሌም ውድቀትና ሕዝቡም በምርኮ ወደ ባቢሎን መጋዙ የዚህ ውጤት ነበር (ምዕ 4-24)። አሕዛብ እንዲት እንደሚፈረድባቸው ካወጀ በኋላ (25፥1-33፥20) ሕዝቅኤል የአይሁድን ምርኮኞች በስድስቱ የሴሊት የተስፋ መልእክቶች ሕዝቡን አጽናና (33፥21-39፥29)። በእነዚህም መሲሑ ወደፊት በተስፋዱቱ ምድር መልሶ እንደሚያቋቁማቸው፣ ለእነርሱም እውነተኛ አረኛ እንደሚሆናቸው ነገራቸው። እነርሱም ይነጻሉ፤ ኪዳናቸውም ሁሉ ይፈጸምላቸዋል። በፍጻሜው ዘመን እንኳ ማለትም ምድሪቱ ከበለጠገችና እስራኤልም ያለ ሥጋት በውስጧ መኖር ከጀመረች በኋላ እንኳ አንዳንዶች የተስፋዱቱን ምድር ከእስራኤል ነጥቀው ለመውሰድና የእግዚአብሔርንም ስም ለማርከስ ይሞክራሉ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ይህን ፈጽሞ አይፈቅድም (ምዕራፍ 38-39)። ስለዚህ ከምርኮው ቀጥሎ ወዳለው ቅርብ ዘመን፣ ወይም ወደ ሄሮድስ ቤተ መቅደስ ዘመን፣ ወይም በግልጽ ወዳልተመለከተው ውብ ቤተ መቅደስ ዘመን ከመመለስ ማለት ድንገት ወደ አንድ ታሪካዊ ዘመን ከመመለስ ይልቅ፣ መሲሓዊ መንግሥትንና የእግዚአብሔር ክብር ሕዝቡን ለመግዛት መመለሱን ከመግለጽም ይልቅ (ሕዝ 40-48)፣ ሕዝቅኤል የትንቢቱን ምክንያታዊና ቅደም ተከተላዊ እድገት ጉልሕ በማድረግ መደምደሙ አመክንዮታዊ ነው።

ሕዝቅኤል የጥንቱንና የዘመኑን ቤተ መቅደስ መንጻት እንዲሁም ከወደፊቱ ቤተ መቅደስ ቅድስና፣ ጽድቅና አሠራር ጋር በማነጻጸር መመሪያዎቹን ለማየት የሞከረ ይመስላል፤ ይህም ከምዕራፍ 33-39 ያለውን ክፍል የገለጠበት መንገድ ነው። ትክክለኛው የወደፊቱ መርሕ በሕዝቅኤል ዘመን በነበሩ ሰዎች ላይ ኀፍረትንና መረታትን የሚያመጣ ነው (43፥6-12፤ 44፥5-16፤ 45፥9-12)። ይህ እንደ ገና እነዚህ ምዕራፎች ወደፊት የሚሟሉበትን ሁኔታ ያመለክታል።

የእግዚአብሔር ክብር የሕዝቅኤል ትንቢት ዋና ገጽታ ነው። ክብሩ ወደ ዐዲሱ ቤተ መቅደስ ተመልሶ በ43፥1-12 የገባበት ሁኔታ የመጽሐፉ ከፍተኛ ክፍል ነው። ዐውዱ ይህ ሁኔታ ሊፈጸም የሚችለው እስራኤል በተስፋዱቱ ምድር መልሳ ከተቋቋመችና ከነጻች በኋላ መሆኑን ግልጽ ያደርጋል። አጽንዖቱ በቅድስና ላይ ነው። ቅድስና እንደ ሕዝብ እስካሁን ድረስ የእስራኤል ባሕርይ አልነበረም፤ ትኩረት የተደረገውም እስራኤላውያን ወደ ተስፋዱቱ ምድር እስካልተመለሱና በመሲሑ ዘመን እስካልነጹ ድረስ (ምዕ 36) በእግዚአብሔር መስፈርት መሠረት ቅዱስ ሕዝብ አለመሆናቸው ላይ ነው (ምዕ 36)። የእግዚአብሔር ክብር ሲመለስ በእስራኤል መካከል ለዘላለም ጽንቶ ይኖራል (43፥6-7)። በሕዝቅኤል ትንቢት ውስጥ እያደገ የመጣው ይህ የውሕደት መንሥኢ ምዕራፍ 40-48 ወደፊት የሚፈጸም መሆኑን በሚያሳምን መልኩ ያመለክታል።

በመጨረሻ በታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔርን የመቤዠት የተለየ ዕቅድ በተመለከተ፣ የቅዱሳት መጻሕፍት ሙሉ ዐውድና ክርክር እነዚህን ምዕራፎችና ከላይ የተጠቀሱትን ገጽታዎች በታሪክ ሁሉ ማጠቃለያ ጊዜ ላይ ያደርጋቸዋል። ይህም ይበልጥ የሚታየው ምናልባት ለምድሪቱ ፈውስን ለማምጣት ከቤተ መቅደሱ በሚፈስሰው በሕይወት ወንዝ ነው (47፥1-12)። ይህ ሐሳብ በመጀመሪያ የታየው የእግዚአብሔር ቅድስና ፍጹም ስፍራ በሆነው በዘፍ 2፥8-14 ላይ በኤደን ገነት ነው።። በኀጢአት ምክንያት ይህ የአትክልት ስፍራና ወንዙ ከስፍራቸው ተወገዱ። ነገር ግን እግዚአብሔር የቤዛነት ዕቅዱን ሲያጠቃልልና በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የዘላለም ሕይወትን ለሰው ልጆች ሁሉ በመስጠት ሙሉ ድነትን ሲያመጣ፣ በምድር ላይ ሙሉ ፈውስን ለመግለጥ የዘላለም ሕይወት ወንዝ እንደ ገና መፍሰሱ ተገቢ ነው። ይህ ማጠቃለያ ማለትም ሙሉው የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ እድገት፣ ሁሉም አጥብቀው የሚያሳዩት በሕዝ 40-48 ያሉት ሁነቶች በመጨረሻው ዘመን የሚፈጸሙ መሆናቸውን ነው።

ሕዝቅኤል 40-48 ተያያዥነቱ ከሺሁ ዘመነ መንግሥት ወይስ ከዘላለም መንግሥት ጋር ነው? በመጀመሪያ መረዳት የሚኖርብን የብሉይ ኪዳንን ነቢያት ትንቢታዊ እይታ መሆን አለበት። ወደፊት ስለሚሆነው የተናገሩት መገለጥ በሁለት ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነው፦ እስራኤል ባለማቋረጥ ከፈጸመችው ኀጢአትና የሙሴን ኪዳን ካፈረሰችበት ሁኔታ የተነሣ ሊመጣባት ያለው ፍርድና ቅጣት፣ በተስፋዱቱ ምድር መልሳ ስትቋቋም፣ ከኀጢአቷ ስትነጻና ወደ መሲሓዊ መንግሥት ስትገባ የእስራኤልን ፍርድ ተከትሎ የሚመጣው የመጨረሻው የበረከት ዘመን። በዚያ ጊዜ ለእስራኤል የተገባላት ኪዳን ሁሉ ይፈጸማል፤ እርስዋም በመሲሑ መለኮታዊ አገዛዝ ሥር በፍጹም ሰላምና ጸጥታ ትኖራለች።

የብሉይ ኪዳን ነቢያት በቅጣቱ ዘመንና በፍርዱ ዘመን መካከል ያለውን ልዩነት ለማሳየት አላሰቡም ነበር። ከዚያ ይልቅ በተመሳሳይ ምንባብ ውስጥ የዚህን ዘመን የቅርብና የሩቅ ገጽታዎች አንድ ላይ አቅርበዋል። ቅጣቱ የሚጀምረው በባቢሎናውያን ሞርኮ ሲሆን፣ እስከ መጨረሻው ዘመን የሚቀጥል ነው። አንዳንድ ልዩነቶች ታይተዋል፤ ይሁን እንጂ የጊዜ ወድርጊት ግንኙነቶች ይህን ያህል በሚገባ አልተብራሩም ነበር።

በተመሳሳይ ሁኔታ ነቢያት ስለ መሲሓዊው በረከት ሲገልጹ፣ በሺሁ ዘመነ መንግሥትና በዘላለሙ መንግሥት መካከል ልዩነት አላሳዩም። በብሉይ ኪዳን ነቢያት አንዳንድ ልዩነቶች በእንድምታ የተመለከቱ ቢሆንም (ለምሳሌ፣ ዳን 9-12)፣ ተጨማሪ ልዩነቶች በዐዲስ ኪዳን ላይ በተለይ በዮሐንስ ራእይ አስቀድሞ የተገለጠው የሂደታዊ መገለጥ ውጤት ናቸው። ሕዝቅኤልም ልክ በዘመኑ እንደ ነበሩት ነቢያት እነዚህን የተለያዩ ነገሮች ስለ ፍርድና ስለ ወደፊቱ መንግሥት በተናገራቸው ትንቢቶቹ አደባልቆ አቅርቦአል። ያለምንም ጥርጥር በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የሚገኘውን የሺሁን መንግሥትና የዘላለማዊውን መንግሥት ልዩነት ለማወቅ ባለው ችግር ላይ ይህ አስተዋፅኦ አድርጎአል።

ከአጠቃላይ የእግዚአብሔር ቃል አንጻር የሺሁ ዘመን መንግሥት የዘላለማዊው መንግሥት ቅድመ እይታ ወይም "በኩር" ተደርጎ ሊታይ ይችላል። ስለዚህ ሁለቱ ተመሳሳይ ከመሆናቸው የተነሣ ተመሳሳይ ልዩነቶችን ይጋራሉ። ይሁን እንጂ ሁለቱም የተገለጡ ልዩ የጊዜ ወቅቶች በመሆናቸው አንዳንድ ልዩነቶችን ያንጸባርቃሉ። እንደ ሕዝቅኤል ያሉ አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ልዩነቶችን ሳያዩ በመቅረታቸው፣ ሕዝ 40-48 የሚናገረው ስለ ሺሁ ዘመን መንግሥት ወይም ስለ ዘላለም መንግሥት ብቻ ነው ብሎ ከማሰብ መጠንቀቅ ይገባል። እንዲህ ዐይነቱ ነገር ባጋጠመ ቊጥር የበለጠ ፍንጭ ለማግኘት ዐዲስ ኪዳንን መመልከት ይገባል።

በሕዝቅኤል 38-39 የተጠቀሰው "የአዕዋፍ እራት" ላይ ተገልጾ እንደ ታየው፣ ዮሐንስ አያሌ የብሉይ ኪዳን ትንቢታዊ ሐሳቦችንና ምስያዎችን በራእዩ ተጠቅሞአል። የዮሐንስ ራእይ 21-22 ስለ ዘላለማዊ ሁኔታ የሚናገር ሲሆን፣ በዚህ የራእይ ክፍል ከሚያስገርም ተመሳሳይነት ጋር ሕዝ 40-48ን በጉልሕነት የሚያጣቅሱ አሉ። ሁለቱም ጸሐፊዎች ከፍ ባለ ተራራ ላይ ሆነው ሳሉ አበቀለምሲሳዊ ራእዮችን ተቀብለዋል፤ የተለያዩ ነገሮችንም እንዲለኩ መለኪያ ገመድ የያዘ መልእክተኛ ም ዐብሮአቸው ነበር (ሕዝ 40፥2-5፤ ራእ 21፥ 2: 10፡15)። ሁለቱም ራእዮች ወደ ምሥራቅ የሚፈስን ውሃ ሲያመለክቱ፣ በዳርና በዳርም ለፈውስ የሚሆኑ ቅጠሎች ያሏቸው ዛፎች ተተክለዋል (ሕዝ 47፥1-7፡12፤ ራእ 22፥1-2)። በሁለቱም ራእዮች በከተሞች ዐሥራ ሁለት በሮች ላይ የእስራኤል ዐሥራ ሁለት ነገዶች ስሞች ተጽፈዋል (ሕዝ 48፥31-33፤ ራእ 21፥12)፤ እንዲሁም በከተሞቹ አራት ማእዘኖች ማለትም በምሥራቅ፣ በደቡብ፣ በሰሜንና በምዕራብ ሦስት ሦስት በሮች ተገኝተዋል (ሕዝ 48፥30-34፤ ራእ 21፥13)።

ይሁን እንጂ፣ በተጨማሪ፣ በሁለቱ ምንባቦች መካከል በግልጽ የሚታዩ አለመመሳሰሎችም አሉ። የከተማዎቹ ወርዶችና ስፋቶች የተለያዩ ናቸው (ሕዝ 48፥30-35፤ ራእ 21፥15-17)። ወደ ምሥራቅ የሚፈስሱት ወንዞች መነሻ የተለያየ ነው፤ በሕዝቅኤል ላለው ቤተ መቅደሱ ሲሆን (43፥7፤9፤ 47፥1-5)፣ በራእይ ደግሞ የእግዚአብሔር ዙፋን

ነው (22፥1:3)። ሕዝቅኤል የእግዚአብሔር ዙፋን ቤተ መቅደሱ እደ ሆነ ስለሚናገር እነዚህ መነሻዎች በርግጥ ተመሳሳይ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ነገር ግን ዮሐንስ በራእዩ የእግዚአብሔር ዙፋን በኢየሩሳሌም ውስጥ እንደሚሆን ተናግሮአል። ስለዝቅኤል ቤተ መቅደሱና የኢየሩሳሌም ከተማ እጅግ የተለያዩ ነገሮች ናቸው (45፥2-4፤ 48፥10፡ 15-17)፤ በዮሐንስ ራእይ ላይ ደግሞ ቤተ መቅደስ የለም (21፥22፤ 22፥3)። የሕዝቅኤል 40-48 ዋና ገጽታ ቤተ መቅደሱና ሥርዐቶች በመሆናቸው፣ የሕዝቅኤል መጽሐፍ የሚያንጸባርቀው ከዘላለሙ መንግሥት ይልቅ የሺህ ዘመነ መንግሥቱን ነው ማለት ምናልባት ይቀልል ይሆናል። በሕዝቅኤል መጽሐፍ በተጠቀሰው የነገዶች አሰፋፈር ባሕሩን የምዕራቡ ድንበር አድርጎ ሲጨምር (47፥15-20)፣ በራእይ ላይ ባሕሩ ከእንግዲህ እንደማይኖር ዮሐንስ ግልጽ ያደርጋል (ራእ 21፥1)። ይኸውም ባሕሩ እስከሌለ ድረስ የሕዝቅኤል የነገድ አሰፋፈር ድንበሮች በዘላለሙ መንግሥት የሚገኙ አይሆኑም። እነዚህ አለመመሳሰሎች የሕዝቅኤል ራእይ ከዘላለሙ መንግሥት ይልቅ የሺሁን ዘመነ መንግሥት ሐሳቦች የሚያንጸባርቁ መሆናቸውን ሲያመለክቱ፣ የዮሐንስ ራእይ ትኩረት ግን በዘላለሙ መንግሥት ላይ ነው።

የወንዙ መነሻ ከራእይ መጽሐፍ የተለየ በመሆኑ፣ ከቤተ መቅደሱ ወደ ምሥራቅ የሚፈስሰው ወንዝ የሺሁን ዘመን መንግሥት የሚወክል ሳይሆን አይቀርም። ይሁን እንጂ በዚህ ስፍራ የሁለቱ ምንባቦች ተመሳሳይ ባሕርይ በተሻለ መልኩ የሚታይ ይመስላል። በዚህ ተመሳሳይ ገጽታ ሕዝቅኤል የዘላለሙን መንግሥት በጨረፍታ ለማሳየት ሞክሮአል። በመጠነኛ መሻሻል መልኩ ቢሆንም፣ በሺሁ ዘመን የሚታየው ምናልባት በዘላለሙ መንግሥትም የሚታይ ይሆናል። በዘላለሙ መንግሥት ውስጥ እግዚአብሔር የቤተ መቅደሱን ቦታ ስለሚይዝ፣ በራእይ 22 ላይ ካለው ቤተ መቅደስ ልዩ ሆኖ በሕዝቅኤል 47 ላይ የእግዚአብሔር ዙፋን ከሆነው፣ ከዚሁ ከሺሁ ዓመት ቤተ መቅደስ ወንዙ ሊፈስ ይችላል።

ስለዚህ ሕዝቅኤል 40-48 አስቀድሞ የሚገልጸው የሺሁን ዘመን ቤተ መቅደስ፣ የአምልኮ ሥርዐቶቹንና የነገዶችን አሰፋፈር ነው። የሺሁ ዘመን መንግሥት የዘላለሙ መንግሥት ጅማሬ የተገለጠበትና መሸጋገሪያም ነው። ከዚህም የተነሣ በራእይ 21-22 በተገለጠው የዘላለም መንግሥት ሥዕል ውስጥ የሕዝቅኤል 40-48 ነጸብራቆችን ማስተዋል፣ እንዲህ ሊሆን ይችላል ተብሎ ሊታሰብ እንጂ አንባቢን ለማስገረም የለበትም።

በቤተ መቅደሱ፣ ካህናት፣ የመሥዋዕት ሥርዐት መታየት የብሉይ ኪዳንን የአምልኮ ሥርዐት መልሶ ማምጣት አይደለምን? ሰዋስዋዊው፣ ታሪካዊው ሥነ ፍታቱ እውነተኛን ቤተ መቅደስ፣ እውነተኞን መሥዋዕቶችና በሺሁ ዓመት ዐውድ ውስጥ እውነተኛ ካህናት እየሠሩ ሳለ ያያል። እነዚህ ነገሮች በጥልቀት ሲመረመሩ፣ የተተዉና የተሻሻሉ ነገሮች ቢኖሩም በባሕርያቸው ሙሴያዊ መሆናቸው በግልጽ የሚታይ ነው። ይሁን እንጂ ዐዲስ ኪዳን የሚገልጸው ኢየሱስ ክርስቶስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በመስቀል ላይ ስለ ሁሉም ኀጢአት መሞቱን ነው። ለኀጢአት ተጨማሪ መሥዋዕት አያስፈልግም። በተጨማሪም የጌታ እራት የታቀደው አማኞች ሁሉ የጌታን ሞት እንዲያስቡት ነው። ዐዲስ ኪዳን ከተሰጠ በኋላ ወደ ብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዐት መመለስ ለምን ያስፈልጋል?

የሌዋዊውን አምልኮ ፅንሰ ሐሳብ ከሕዝቅኤልና ከዐዲስ ኪዳን ጋር በማነጻጸር የሕዝቅኤልን ዐላማ መመርመሩ ለእነዚህ አንዳንድ አጣብቂኞች መፍትሒ ለማግኘት ያግዙናል። ሕዝቅኤል ራሱ ካህን ነበር፤ ስለሆነም በተደጋጋሚ በትንቢቶቹ ውስጥ ያሉትን ጉዳዮች የተመለከታቸው ከካህናዊ አመለካከት አኳያ ነው። ዐዲስ የሆኑትን የአምልኮ መርሖች የሚያያቸው ቤተ መቅደሱን፣ መሥዋዕቶችንና በውስጥ ያሉትን ካህናት ከሚያነጹበት አኳያ እንደ ሆነ ይጠበቃል። ልክ እንደዚሁ እግዚአብሔር ብዙውን ራሱን የሚገልጠው መልእክቱን ከሚቀበሉት ሰዎች ባህልና እይታ አንጻር ነው። እንዲህ ዐይነቱም ነገር እዚህ ላይ ሊሆን እንደሚችል ይታሰባል።

የዚህ ራእይ ተቀባዮች "የእስራኤል ቤት" በመባል ተጠርተዋል። ይህ አባባል በሕዝቅኤል የተገለጸችው እስራኤል በህልውና ዘመኗ ያለችበትን፣ ያለፈውን፣ የአሁኑን ወይም የወደፊቱን የተመለከተ ነው። የብሉይ ኪዳን አቡቀለምሲሳዊ ሥነ ጽሑፍ በተስፋ አስቈራጭ ዘመን የተስፋና የመጽናናት ምንጭ ነው። በመስሓዊው መንግሥት ቤተ መቅደሱ እንደ ገና የሚሠራ፣ የእግዚአብሔር ክብርም ወደ እርሱ የሚመለስ መሆኑ እንዲሁም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሕዝቡ ተመልሰው እርሱን የሚያመልኩበት ስፍራ መሆኑ ይህ ራእይ በእውነት የሚያጽናና ነው። በመሲሓዊው መንግሥት ያለው አምልኮ በዝርዝር ሲቀርብ፣ ለእስራኤል ግልጽ መሆን ካለበትም በላይ ለአምላክዋ ማቅረብ የሚገባትን ኪዳናዊ አምልኮ እንድትጠብቅ የሚያደርጋት አይደለምን?

በሕዝቅኤል 37፥15-28 ላይ የተሰጡት ኪዳኖች ሁሉ የሚፈጸሙት እስራኤል በተስፋዱቱ ምድር መልሳ በምትቋቋምበት ጊዜና መሲሓዊው መንግሥት በሚመሠረትበት ጊዜ ነው። ይህ አብርሃማዊውን፣ ዳዊታዊውን፣ ዐዲሱን፣ የሰላምና ሙሴያዊ ኪዳኖችን የሚያካትት ነው። የሙሴያዊው ኪዳን ቀመር የሚከተለው ነው፦ እነርሱ ሕዝቤ ይሆናሉ፤ እኔም አምላካቸው እሆናለሁ። ይህም እውን የሚሆነው እስራኤል በሙሴአዊ ኪዳን ትእዛዛት መሠረት ስትራመድ፣ በዐዲሱ ኪዳን ስትነጻ፣ በዳዊታዊው ኪዳን መሠረትም በንጉሥዋ በመሲሑ ዘላለማዊ መንግሥት ውስጥ መኖር ስትጀምር ነው (37፥23-26 ይመ፤ ከዘፀ 19፥5-6፤ ከዘሌ 26፥12፤ ከዘዳ 26፥18-19፤ ከኤር 30፥18-22፤ 31፥33፤ 32፥36-40 ጋር ያነጻ)። እስራኤል በአብርሃማዊውና በመሴያዊው ኪዳን መሠረት ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ስለ ነበራት፣ ምንጊዜም ቢሆን እግዚአብሔርን በቅድስና ልታመልከው ይገባት ነበር። መላው የአምልኮ ሥርዐትዋም የታለመው እርስዋ ወደ እግዚአብሔር ቅድስና እንድትመለከትና ራስዋም በፊቱ በቅድስና መኖር እንደሚያስፈልጋት ለማመልከት ነው (ከዘሌዋውያን ጋር ያነጻጽሩ)። በሕዝቅኤል 40-48 ያለው ክፍል በመሠረቱ ትኩረት የሚያደርገው በእግዚአብሔር ቅድስና ላይ ነው። የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅድስናና እርሱንም የማምለክ ሁኔታ በንጽጽር የቀረቡት በእስራኤል ያለፈ የምልጃ ታሪክ ውስጥ ስሙና ቤተ መቅደሱ ከመርከሱ ጋር ነው። እስራኤል በትክክለኛ መንገድ እግዚአብሔርን እንድታመልከው የመጨረሻ ዕድል ተሰጥቶአታል፤ ይኸውም በቅድስናና በንጽሕና ነው። እንዲህ ዐይነቱ አምልኮ እስራኤል በእውነት መቤዠታንና መንጻቷን ይገልጻል።

ሕዝቅኤል 40-48 የሚያቀርበው የሺሁን ዘመን መንግሥት አምልኮ ከዕብራዊው እይታ አንጻር ብቻ ነው። ይህ ሌሎች የአምልኮ ዐይነቶች እንዳይኖሩና እንዳይካሄዱ የሚያግድ አይደለም (ከሉቃ 22፥18 ጋር ያነጻ)። የእግዚአብሔር ኪዳኖች መገለጫዎችና አሠራሮች ሁሉ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም፤ ነገር ግን እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ ናቸው። እስራኤላውያን በመጨረሻ የእግዚአብሔር ሕዝብ ይሆናሉ፤ በሙሴያዊ ትእዛዛት በተገለጠው መሠረትም በቅድስና በመኖር እግዚአብሔርን ያመልካሉ። በሕዝቅኤል 40-48 ከመሴያዊው ሥርዐት የተገደፉትና የተሻሻሉት ነጥቦች ያለጥርጥር የኪዳኑን የተለያዩ ገጽታዎች ለማጣጣም እንዲቻል የቀረቡ ናቸው።

ነገር ግን የቤተ መቅደሱ ህልውና ቀጣይነቱን የሚያመለክት አይደለምን? ጥያቄውን ለመመለስ፣ የአምልኮ ስፍራ ሆኖ ቤተ መቅደሱ መኖሩ፣ የብሉይ ኪዳን እይታ የተለመደ አስተሳሰብ ነው። በተጨማሪም ያለ ቤተ መቅደሱ ሕንጻ መሥዋዕቶች በሚገባ ሁኔታ ሊቀርቡ አይችሉም። ስለዚህ ቤተ መቅደስ ለአምልኮ አስፈላጊ ነው (ሕዝ 43-46)።

ሕዝቅኤል ስለ ሺሁ ዘመን መንግሥት ቤተ መቅደስ ሁለት ዋና ዋና ዐላማዎችን አቅርቦአል። በመጀመሪያ ቤተ መቅደሱ በውስጡ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል መኖሩን የሚያመለክት ዙፋን ይኖረዋል (43፥6-7)፤ ይህ የክብሩ መቀመጫ ሲሆን (43፥1-12)፣ በዚህም ላይ ተቀምጦ ሕዝቡን ይገዛል። ሁለተኛ የቤተ መቅደሱ ሕንጻ በግድግዳዎች መከፋፈሉ፣ አያሌ አደባባዮች በውስጡ መኖራቸውና የቤተ መቅደሱ ልዩ ልዩ ክፍሎች መለየታቸው የእግዚአብሔርን ቅድስና ያንጸባርቃል (40፥5፤ 42፥14-20)። የሕንጻው አሠራር ንድፍ በዚያ ጊዜ የነበሩትን ሰዎች ስለ በደላቸው እንዲያፍሩ ያደርጋቸዋል። ስለዚህ የቤተ መቅደሱ አሠራር በሺሁ ዘመነ መንግሥት ሊኖር የሚችለውን ሌላ የአምልኮ ዐይነት የሚከለክል ወይም የሚያስቀር አይሆንም (ለምሳሌ፣ የጌታ እራት)፤ ይህም ሊሆን የሚችለው ለአንድ ለተወሰነ ጊዜ እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚያስችል የሕንጻ አሠራር ይኖራል ብሎ በመገመት የእግዚአብሔርን የሥራ ወቅት መከፋፈል ከተቻለ ብቻ ነው።

በቤተ ክርስቲያን ዘመን ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ያመለኩባቸው የተለያዩ የሕንጻ አሠራሮች ነበሩ። ሁሉን ለሚችለው እግዚአብሔር በተሠራ ቤተ መቅደስ ውስጥ ክርስቲያን እንዳያመልክ የሚከለክል ምንም ዐይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መከራከሪያ ያለ አይመስልም። ስለሆነም ቤተ መቅደስ በውስጥ አሠራሩም ሆነ በራሱ ጊዜው ያለፈበት አይመስልም።

ሁለተኛው ዋነኛ ችግር ሕዝቅኤል ባቀረበው መሥዋዕትን የማቅረብ ሥርዐትና ዐዲስ ኪዳን የክርስቶስ ሞት ለኀጢአት የመጨረሻና ፍጹም ሥራ እንደ ሆነ ባቀረበው ትምህርት መካከል ያለው ግንኙነት ነው። የጉዳዮቹን ዝርዝር ሁኔታ ለመረዳት የሕዝቅኤልን የሺሁን ዘመን መንግሥት የመሥዋዕት አቀራረብ ሥርዐት በግልጽ ማወቅ ይኖርብናል። ይህን ስናደርግ ከሙሴያዊው ሥርዐት ጋር በሚገባ እናወዳድረዋለን። የሕዝቅኤል ሥርዐት ገጽታዎች በሙሉ ከሙሴያዊው ሥርዐት ጋር ተመሳሳይ ናቸው ማለት ይቻላል። በመጀመሪያ ልዩነቶቹን የፈጠሩት ከሕዝቅኤል የአምልኮ ዐላማ አንጻር አንዳንድ ማሻሻያዎች ታክሎባቸው የተፈጸሙት ግድፈቶች ናቸው።

በሕዝ 45፥17 ላይ "ለእስራኤል ቤት በተወሰኑት በዓላት" በሚል የተጠቀሰ አጠቃላይ ሐረግ ቢኖርም፣ ሦስት በዓላት ብቻ በግልጽ በእነዚህ ምዕራፎች ላይ ቀርበዋል። እነዚህም ፋሲካና የቂጣ በዓል፣ እንዲሁም የዳስ በዓል በተዘዋዋሪ የተገለጸው የበኵራት በዓል ናቸው። ፋሲካ (45፥21-24) በመጀመሪያው ወር (ኒሳን) በዐሥራ አራተኛው ቀን ይጀመራል፤ በዚህ ጊዜ ሕዝቡ ያልቦካ ቂጣ ለሰባት ቀን ይበላሉ (ከዘፀ 12፥1-30፤ ከዘኍ 28፥16-35 ጋር ያነጻ)። "መሪው" በየቀኑ ለራሱና ለምድሪቱ ሕዝብ የኀጢአት መሥዋዕት ከእህል ቁርባን ጋር ያቀርባል (ከዘኍ 28፥22-24 ጋር ያነጻ)። እንደዚሁም በየቀኑ መሪው የሚቃጠል መሥዋዕት ከእህል ቁርባኑ ጋር ያቀርባል (ከዘኍ 28፥19-21፡ 23-24 ጋር ያነጻ)። እነዚህ ነገሮች ከሌዋውያን ሥርዐት ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ልክ እንደዚሁ ለፋሲካ የቀረቡት መሥዋዕቶች ለተመሳሳይ ጊዜ ያህል ለዳስ በዓልም እንደሚቀርቡ ሕዝቅኤል ተናግሮአል (ሕዝ 45፥25)። ዘኍልቊ 29፥12-38 ላይ የመጠጥ ቁርባንን በመጨመሩ ከዚህ ይለያል። ይህ በዓል በሰባተኛው ወር በዐሥራ ዐምስተኛው ቀን ሲጀመር፣ በሙሴ ሥርዐት በተገለጠው መሠረት ለሰባት ቀናት የሚፈጸም ነው። በተጨማሪ ሕዝቅኤል 44፥30 "ከፍሬው በኵራት ምርጥ የሆነው ሁሉ . . . ለካህናት ይሆናል" የሚል ይጨምራል። ይህ የበኵራት በዓልን የሚያመለክት ላይሆን ይችላል፤ ነገር ግን በሕዝቅኤል ሥርዐት ውስጥ የበኵራት ሐሳብ መቅረቡን የሚያመለክት ብቻ ነው።

በአምልኮ ውስጥ የሚቀርቡት ቁርባኖችና መሥዋዕቶች እንዲሁም የቤተ መቅደሱ መቀደስ የሕዝቅኤልን ሥርዐት በብዛት የሚገልጡ ናቸው። ከእነዚህ አያሌ በዓላት ቁርባኖች በተጨማሪ እስራኤላውያን በየቀኑ ለእግዚአብሔር ከሚያቀርቡት የሚቃጠል መሥዋዕት ጋር በየማለዳው የእህል ቁርባን ማቅረብ ነበረባቸው (ከዘፀ 29፥38-42፤ ከዘሌ 6፥12፤ ከዘኍ 28፥3-7 ጋር ያነጻ)። ሙሴያዊው አሠራር እነዚህ መሥዋዕቶች በየቀኑ ከመጠጥ ቁርባን ጋር በየማለዳውና በየምሽቱ መቅረብ እንዳለባቸው ያዛል። የሰንበት መሥዋዕቶች፣ የዐዲስ ጨረቃ በዓላት እንዲሁም የተወሰኑ በዓላት በሕዝቅኤል የአምልኮ ሥርዐት የሚቃጠል መሥዋዕትን፣ የእህል ቁርባንንና የመጠጥ ቁርባንን ይጨምራሉ (45፥17 ይመ፤ ከዘሌ 23፥37፤ ከዘኍ 28፥9-15 ጋር ያነጻ)። በዐዲስ ጨረቃ በዓል ላይ ብቻ ነው ሙሴያዊው ሥርዐት የኀጢአት መሥዋዕትን የሚጨምረው። ካህናት በሰንበትና በዐዲስ ጨረቃ በዓል ለመሪው የሚቃጠል መሥዋዕት ማቅረብ እንዳለባቸው ሕዝቅኤል በተጨማሪ አመልክቶአል (46፥2-7፤ ዘኍ 29፥39)። መሪው ምናልባት በፈቃዱ የሚቃጠል መሥዋዕትና የኀብረት መሥዋዕት በሰንበት ዕለት ማቅረብ ይችላል (46፥12)።

የሕዝቅኤል ቤተ መቅደስ በኀጢአት መሥዋዕት በመጀመሪያው ወር (በየዓመቱ?) በመጀመሪያውና በሰባተኛው ቀን ነጽቶአል ("ስርየትን አግኝቶአል") (45፥18-20)። ተመሳሳይ አሠራሮች በሙሴ ሥርዐትም በዝርዝር ቀርበዋል፤ ነገር ግን የሚቃጠል መሥዋዕትንና የኀብረት መሥዋዕትን ይጨምራሉ (ከዘኍ 7፥87-89፤ ከ2ዜና 7፥1-10፤ 29፥20-24 ጋር ያነጻ)። የሚቃጠል መሥዋዕት ማቅረቢያ የሆነው መሠዊያ ሲዘጋጅ፣ ይነጻል፤ ይቀደሳል፤ ለሰባት ቀን ያህልም በሚቃጠሉ መሥዋዕቶችና በኀጢአት መሥዋዕቶች ለእግዚአብሔር ይለያል (43፥18-25፤ ከዘፀ 29፥36-37፤ ከዘሌ 7፥14 ጋር ያነጻ)። ከእነዚህ ሰባት ቀኖች በኋላ መሠዊያው ለሚዘወተሩ መሥዋዕቶች ማቅረቢያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል (43፥27)። ይህ ምንባብ መሠዊያው በተደጋጋሚ ስለ መንጻቱና ስለ መቀደሱ የሚናገረው የለም። በመጨረሻ መሪው ለእስራኤል ቤት ማስተስረያ ዘወትር ለሚያቀርበው መሥዋዕት፣ እስራኤላውያን ልዩ የእህል፣ የዘይትና የእንስሳት መዋጮ ያቀርባሉ (45፥15-17 ይመ፤ ከዘሌ 9፥17-21 ጋር ያነጻ)። የስርየት መሥዋዕቶች የኀጢአት መሥዋዕት፣ የእህል ቁርባን፣ የሚቃጠል መሥዋዕትና የኀብረት መሥዋዕት ናቸው። ምን ያህል በተደጋጋሚ ወይም መቼ እንዲህ ዐይነቱ ስርየት መደረግ እንዳለበት ጊዜው በግልጽ አልተመለከተም።

በትንቢተ ሕዝቅኤል ውስጥ የተገለጠው የክህነት አገልግሎት በጥገና፣ በአስተዳደር እንዲሁም በቤተ መቅደስ አምልኮ ሥራ ውስጥ ረዳት የሆኑትን ሌዋውያን ያቀፈ ነው፤ ነገር ግን የሳዶቅ ዘር የሆኑት ብቻ በእግዚአብሔር ፊት እጅግ በተቀደሱ ነገሮች እንዲያገለግሉ የተፈቀደላቸው ናቸው (44፥5-16)። ሌሎቹ ሌዋውያን በቤተ መቅደሱ ሥራ ውስጥ በቀደመው ዘመን ባሳዩት ያለመታመን ሁኔታ ይህ መብት ተነፍጎአቸዋል። ሊቀ ካህናት የለም። የተጠቀሱት የክህነት ሥራዎች ማረድ፣ ማጠብ፣ ማብሰልና የተለያዩ መሥዋዕቶችን መብላት ብቻ ናቸው (40፥38-42፤ 42፥13፤ 44፥29 ይመ፤ 46፥20፤ ከዘሌ 7፥7፤ ከዘኍ 18፥8-10 ጋር ያነጻ)።

ስለዚህ በሕዝቅኤል አብዛኛው የተጠቀሰው የአምልኮ ሂደት ሙሴያዊውን ሥርዐት የተከተለ ነው። ከቀሩት ዋና ዋና ነገሮች መካከል የስርየት ቀን፣ የኪዳኑ ታቦት፣ የሳምንት በዓል (በዓለ ኀምሳ)፣ ሊቀ ካህናቱ እንዲሁም የሌዋዊ የክህነት አገልግሎት በሙሳት አለመኖር ናቸው። ደም የሚረጭበት የስርየት ቀንና የኪዳኑ ታቦት አለመኖር የቤዛነት ሥራ ከዚህ ቀደም ሙሉ በሙሉ መፈጸሙን ያመለክታል። እነዚህ ነገሮች በሙሴያዊው ሥርዐት እጅግ ዋና ነገሮች ከመሆናቸው የተነሣ በሕዝቅኤል በተጠቀሰው በሺሁ ዘመነ መንግሥትም ሊካተቱ ይገባል ተብሎ ሊታሰብ ይችላል። ይሁን እንጂ በዝምታ ከታለፈ ነገር ተነሥቶ መከራከሪያ ነጥብ ማቅረብ የሚያስቸግር ይሆናል። የሊቀ ካህናቱ አለመኖር በሺሁ ዘመን መንግሥት በሊቀ ካህናትነት የሚገዛውን ኢየሱስ ክርስቶስን ያመለክታል (ዕብ 4፥14-5፥10፤ 7፥11-8፥13)።

በሌላ አነጋገር የሺሁን ዘመን መንግሥት የአምልኮ ሥርዐት ከሙሴያዊው ልዩ የሚያደርገው አንዳንድ የሙሴያዊ ሥርዐት አሠራሮች ስለ ቀሩ ወይም ስለ ተሻሻሉ ሳይሆን በመስቀል ላይ ክርስቶስ የፈጸመው ሥራ ስላለ ብቻ ነው። በሺሁ ዘመን መንግሥት የሚቀርቡት መሥዋዕቶች በሌሎች የብሉይ ኪዳን ነቢያትም በየስፍራው ተወሥተዋል (ኢሳ 56፥6-7፤ 60፥7፡ 13፤ 66፥20-23፤ ኤር 33፥15-22፤ ዘካ 14፥16-21)።

እነዚህ መሥዋዕቶች በቂ መሆናቸው ዋና ጉዳይ ነው። ሙሴያዊው ኪዳን የተሰጠው በአብርሃማዊው ኪዳን መሠረት ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት መፍጠር ለጀመረ ሕዝብ ነው። ሙሴያዊው ኪዳን የተሰጠው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት እንዲፈጥር ሳይሆን፣ በዚህ ግንኙነት ውስጥ ሰው በእግዚአብሔር ፊት እንዴት አድርጎ በቅድስና መኖር እንደሚችል ለመግለጥ ነው። እውነተኛ አምልኮ የሚያድገው ከእግዚአብሔር ጋር ባለ የጠበቀ የግል ግንኙነት ነው።

ስለዚህ ሙሴያዊው የአምልኮ ሥርዐት አገልግሎት ላይ ሊውል ይችል የነበረው ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት በፈጠሩ ሰዎች ብቻ ነበር። መሥዋዕትም ሆነ ቁርባን ማንንም ከቶ ከኀጢአት ነጻ አላወጡም። ለእስራኤላውያንም ሆነ ለማንኛውም ሰው መፍትሔ ማምጣት የሚችሉ አይደሉም። ይልቁንስ ሙሴ ሐ በቤዛነት ሥራ ስርየትን ለማምጣት ለአንዱና ለመጨረሻ የራሱን ደም መሥዋዕት በማድረግ ኀጢአትን ሁሉ እንደሚያስተሰርይ የሚያሳዩ ሥዕላዊ ትእምርቶችና ተምሳሌቶች ነበሩ። የኀጢአትና የበደል መሥዋዕቶች የአንድን ሰው ግላዊ የውርስ ኀጢአት የሚያስታውሱ ሲሆኑ፣ ይህንን በኀጢአት የተሞላ ሕይወት ለማንጻት የንጹሕ ሰው ደም መፍሰስ እንዳለበት የሚያመለክቱ ናቸው። እነዚህ መሥዋዕቶች የሚታሰቡት ክርስቶስ ከፈጸመው ሥራ አንጻር ዛሬ አማኝ ኀጢአቱን ከሚናዘዝበት ሁኔታ አኳያ ነው (1ዮሐ 1፥9)።

የአማኝ ኑዛዜ በራሱ በቂ አይደለም። የኀጢአት ይቅርታን የሚያስገኘው ክርስቶስ የፈጸመው ሥራ ብቻ ነው። ይሁን እንጂ ኑዛዜ አማኝን የሚያስታውሰው፣ እርሱ ወይም እርሷ ኀጢአት ማድረጋቸውን እንዲሁም ያ ኀጢአት በክርስቶስ ደም ይቅር መባሉን ነው። ስለዚህ የኀጢአትና የበደል መሥዋዕቶች እስራኤላውያንን የሚያስታውሱት እነርሱ ኀጢአተኞች መሆናቸውን፣ እነርሱን ከኀጢአታቸው እንዲያነጻቸውና ከእግዚአብሔርም ይቅርታን እንዲያስገኝላቸው የሚያስፈልጋቸው በእንስሳ የተመሰለው የመሲሑ ንጹሕ ደም መሆኑን ነው።

የሚቃጠለው መሥዋዕት የሚያመለክተው አቅራቢዎቹ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ታማኝነት ነው። ታማኝነት ዛሬ እንደ ሆነው ሁሉ በፈቃደኝነት የሚደረግ ነበር። የሚቃጠሉ መሥዋዕቶች በየዕለቱ የሚያስፈልጉ ሲሆኑ፣ በሌሎቹም በዓላት ሲቀርቡ እስራኤላውያን ለእምላካቸው ሙሉ በሙሉ ታማኝ መሆን እንደሚያስፈልጋቸው በተከታታይ የሚያስገነዝቧቸው ናቸው። የኀጢረት መሥዋዕቶች መሥዋዕት አቅራቢዎች ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡትን ምስጋናና በእነርሱና በአምላካቸው በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ሰላም ያንጸባርቃሉ። በርግጥ ዛሬም አማኞች ከአምላካቸው ጋር ካላቸው ግንኙነት የተነሣ ስለ ተቀበሉአቸው የተለያዩ በረከቶች ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

የስርየት ሐሳብ በሕዝቅኤል ከተጠቀሰው የመሥዋዕት ሥርዐት ጋር ለብዙዎች ትልቅ ችግርን ፈጥሮአል። የዕብራይስጡ ግስ "ምትክ በማቅረብ ማስተስረይ ይላል፤ ይህ ደግሞ ዘወትር አገልግሎት ላይ የሚውለው ኀጢአትን ወይም ርኩሰትን በማስወገድ ነው። በሙሴያዊው ሥርዐት ለስርየት የሚሆን መሥዋዕት ሲቀርብ፣ አቅራቢው ያን ለማድረግ ስለ ተነሣሣ ሳይሆን ይቀርብ የነበረው እግዚአብሔር ስለ ፈለገው ነበር (ዘሌ 10)። ይቅርታንና መንጻትን የሚሰጥ እግዚአብሔር ብቻ እንጂ መሥዋዕቱ አልነበረም። በመጨረሻ የይቅርታና የመንጻት መሠረቱ ለሞት ቅጣት ወጀ በመሆን በፈሰሰው በንጹሑ የመሲሑ ደም የተሠራው ሥራ ነበር። መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርበው እንስሳ መፍትሒ የሚያስገኝ ወጀ ሆኖ መቅረብ አይችልም ነበር፤ ይልቁንስ ለስርየት የሚቀርበው መሥዋዕት ክርስቶስ ለፈጸመው ሥራ ሥዕላዊ ትእምርት ብቻ ነበር።

በሕዝቅኤል 40-48 ስለ "ስርየት" የተጠቀሱት ሐሳቦች ሁሉ ከሁለት ማጣቀሻዎች በቀር ቤተ መቅደሱን ወይም መሠዊያውን ከማንጻትና ከመቀደስ ጋር የተያያዙ ናቸው። የሕዝቡ ስርየት በ45፥15-17 ላይ ብቻ ተጠቅሶ ይታያል። በዚያ ያለው ሐሳብ በሙሴያዊው ሥርዐት ላይ ካለው ሐሳብ ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ይኸውም ኀጢአትን ለማስተስረይና ለአንዱና ለመጨረሻ የኀጢአት ይቅርታን ለማስገኘት እርሱ ወጀ በመክፈል ክርስቶስ በመጨረሻ የሚፈጽመውን የስርየት ሥራ የሚያሳይ ሥዕላዊ ትእምርት ነው።

ሙሴያዊው የኀጢአት ስርየት ቀን በብሉይ ኪዳን ዘመን በዓመት አንድ ጊዜ የሚፈጸም ነው (ከዘሌ 16፥21-22፡ 30፡ 31 ጋር ያነጻ)። ነገር ግን በሺሁ ዘመን መንግሥት የሚከበር በዓል አይሆንም። ይሁን እንጂ ኀጢአት በሺሁ ዘመን መንግሥትም በእስራኤል ቤት መካከል ይከሠታል። ስለዚህ በመሪውና በሕዝቡ የሚቀርቡት የስርየት መሥዋዕቶች ኀጢአታቸው ይቅር ይባልላቸው ዘንድ መሲሑ በመስቀል ላይ ለፈጸመው ሥራ አስገራሚ ማስታወሻዎች ናቸው። በተጨማሪም ኀጢአተኞች ከመሆናቸው የተነሣ ቤዛነትን ያገኙ ዘንድ ንጹሕ የሆነው የክርስቶስ ደም እንደሚያስፈልጋቸው ያሳስባቸዋል። ሙሴያዊ መሥዋዕቶች በክርስቶስ የሚፈጸመው ሥዕላውያን ትእምርቶችና ተምሳሌቶች እንደ ሆኑ ሁሉ የሕዝቅኤል መሥዋዕቶች የክርስቶስ ሥራ መታሰቢያዎች ናቸው።

የዕብራውያን ጸሓፊ በምዕ 7-10 ባለው የሚገልጸው በሙሴያዊ መሥዋዕቶችና በክርስቶስ ሥራ መካከል ያለውን ግንኙነት ነው። እነዚህን ምዕራፎች መመርመር ትምህርት ሰጪ ነው፤ ከላይ የተጠቀሰውን ሐሳብ የሚያረጋግጡ ናቸውና። ሕጉ ማንኛውም ነገር ለመንጻት ደም እንደሚያስፈልገው ያመለክታል፤ ደም ሳይፈስ ስርየት የለምና (ዕብ 9፥21-22)። ይህም በሙሴያዊውም ሆነ በሕዝቅኤል የስርየት ሥርዐት የታየ ነው። ነገር ግን የመገናኛው ድንኳን (ቤተ መቅደስ) መሠረታዊ ነገሮችን ማሚያ ዕቃዎቻቸው የሰማያዊውያን ነገሮች ነጸብራቅ ናቸው (9፥23)፤ በመሥዋዕቶች መንጻት ቢያስፈልጋቸውም እውነተኛው መንጻት የሚሆነው በክርስቶስ መሥዋዕት ነው፤ እነዚህ ነገሮች ነጸብራቅ ብቻ ናቸው (9፥24-28)። እነዚህ የሙሴያዊ ኪዳን ገጽታዎች ሊመጣ ላለው ነገር ጥላ (ማለትም ሥዕል) ብቻ ናቸው እንጂ በራሳቸው ቋሚ እውነታ አይደሉም (10፥1)። በዚህ ስፍራ የሙሴ ኪዳን እንደ ጥላ ቢጠቀስም፣ ሙሴያዊው ሥርዐት ከነተደጋጋሚ መሥዋዕቶቹ ኀጢአትን ሊያስወግድ የሚችል ሁኔታን ለአምላኪዎቹ አያስገኝም (10፥2-4፡11)። በምሳሌነት በሥዕልነት ያነጹት ውጪያዊውን ብቻ ነው (9፥11-14)፤ ኢየሱስ ጎሊናችንን ወደ ሞት ከሚያመሩ ኀጢአተኛ ሥራዎች ከውስጥ ንጹሕ ያደርጋል (10፥8-14)። ሙሴያውያን መሥዋዕቶች ሥርዐቱን የሚፈጽሙትን ቢያነጹና ፍጹማን ቢያደርጓቸው ኖሮ እነዚያ መሥዋዕቶች ለአንዱና ለመጨረሻ ጊዜ በቀሙ ነበር፤ ነገር ግን ፍጹም ማድረግ አልቻሉም (10፥2)። ስለዚህ ኀጢአትን በቋሚነት የሚያስታውሱ ናቸው፤ የእንስሳት ደም ኀጢአትን ፈጽሞ ሊያስወግድ አይችልምና። ኢየሱስ አንድ ጊዜ ራሱን ለሰው ልጅ ኀጢአት አሳልፎ ሰጥቶአል። በዐዲስ ኪዳን በተፈጸመው የተስፋ ቃል መሠረት ሥዕሉ እውን ሆነ (7፥27)።

የዕብራውያን ጸሓፊ በመቀጠል ኀጢአት ይቅር በተባለበት፣ ለኀጢአት ይቅርታ ምንም ዐይነት መሥዋዕት እንደማያስፈልግ ተናግሮአል። ከላይ በተጠቀሰው የዕብራውያን ዐውድ መሠረት ልብ የምንለው ሥዕላዊ ትምህርቶችና ማሳሰቢያዎች ከእንግዲህ እንደማያስፈልጉ፣ ከአንዱና ለመጨረሻ ጊዜ መፍትሒ የሚሆነው የክርስቶስ ደም መሥዋዕት መሰጠቱን ነው። ይሁን እንጂ የዕብራውያን ጸሓፊ የክርስቶስ ብቁ መሥዋዕት ከተፈጸመ በኋላ ሥዕላዊ መሥዋዕቶችና በዓሎች፣ ክርስቶስ የሠራው ሥራ አስታዋሽ ሆነው ከእንግዲህ አይከበሩም ብሎ አያውጅም። በርግጥ በብሉይ ኪዳን ሥርዐት መሥዋዕቶችና በዓሎች በራሳቸው ሥዕላውያን ብቻ በመሆናቸው ከመሲሑ መሥዋዕት ጋር ከቶ አይጋጩም፤ ከቶ በቂ አልነበሩም፤ ከቶም በቂ አይሆኑም።

ልክ እንደዚሁ በሕዝቅኤል የተገለጹት በሺሁ ዘመን መንግሥት ያሉት መሥዋዕቶች፣ ለሰው ዘር ኀጢአትና ክርስቶስ ለአንዱና ለመጨረሻ ጊዜ ለፈጸመው ብቸኛ ብቁ መሥዋዕት ሥዕላዊ ትምህርትና ማሳሰቢያዎች እንጂ ሌላ አይደሉም። የሺሁ ዘመን መንግሥት መሥዋዕቶች በሺሁ ዘመን መንግሥት ላሉ አማኞች ማሳሰቢያዎች እንዲሁም በሺሁ ዘመን መንግሥት ለተወለዱትና ላላመኑት ሥዕላውያን ትምህርቶች ናቸው። ዐላማቸው ይኸው ነው። በብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች ሚናና የዕብራውያን ጸሓፊ በተናገረው መሠረት ሥዕላውያን የሆኑት የሙሴያዊው ሥርዐት መሥዋዕቶች ወይም የሺሁ ዘመን አምልኮ መታሰቢያ መሥዋዕቶች አንድ ጊዜ ለሁሉም ኀጢአት በመስቀል ላይ ከተፈጸመው የክርስቶስ መሥዋዕት ጋር የሚጋጩ ሆነው አልቀረቡም።

በተጨማሪም እየተፈጸመ ያለው የጌታ እራት ሥርዐት ይህንኑ መታሰቢያ የሆነውን አመለካከት የሚደግፍ ነው። የጌታ እራት መታሰቢያ የክርስቶስ ሞት ምትክ አይደለም፤ በዚህ እሳቤ መሠረትም ከተፈጸመው የክርስቶስ ሥራ ጋር የሚጋጭ አይደለም። እንደ መታሰቢያ የጌታ እራት በግልጽ የሚከበረው ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ (ማቴ 26፥29፤ ማር 14፥25፤ ሉቃ 22፥18) ክርስቶስ ባለበት በመሲሑ መንግሥት (በሺሁ ዘመን መንግሥት) ነው። የጌታ እራት መታሰቢያ ከሆነና የሕዝቅኤል ሥርዐት መሥዋዕቶችም መታሰቢያ ከሆኑ፣ ሁለቱ በምንም መንገድ እርስ በርሳቸው አይጋጩም፤ ነገር ግን ዐብረው ይኖራሉ። አንድ ዐይነት ሚና ካላቸው ለምን ሁለቱም በአንድ ላይ ይከበራሉ? የሚል ጥያቄ በርግጥ መጠየቅ ይቻላል። ምናልባት የጌታ እራት መታሰቢያ በቤተ ክርስቲያን ዘመን ላሉት መታሰቢያ ሲሆን፣ በሕዝቅኤል ሥርዐት ያሉት መሥዋዕቶች ደግሞ በሺሁ ዘመን መንግሥት ላሉት አይሁድ መታሰቢያዎች ናቸው፤ ስለሆነም የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑትን አይሁድም ሆነ አሕዛብን አንዳቸውንም በየትኛውም መታሰቢያ እንዳያመልኩ የሚያግድ ምንም ነገር የለም።

በማጠቃለያ በሕዝቅኤል አምልኮ ያለው የመሥዋዕት ሥርዐት ቤተ መቅደሱን ለመለየትና ለማንጻት ቅድስና እንደሚስፈልግ የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ ነው። የሰው ልጅ በኀጢአት የተሞላና መቤዠርት እንደሚያስፈልገው የሚያሳዩ ሥዕላውያን ማሳሰቢያዎች ናቸው፤ እንዲሁም ለአንዱና

ለመጨረሻ ለሰው ልጅ ስርየት የሰጠውን የመሲሑን ፍጹምና ያለቀ መሥዋዕት የሚገልጡ ሥዕላውያን መታሰቢያዎች ናቸው። በኅብረት መሥዋዕት ውስጥ ምስጋና በግልጽ ለእግዚአብሔር ይሰጣል። በተጨማሪም በመሥዋዕቶቹ ውስጥ ለሙሴያውያን ካህናት እንደ ተደረገው የሺሁ ዘመን መንግሥት ካህናትም የሚመገቡት ይኖራል (44፥29-31)። በሺሁ ዘመን መንግሥት ባለው አምልኮ ለመሪውና ለሕዝቡ መሥዋዕትን ለማቅረብ ካህናት ያስፈልጋሉ። ካህናት በቤተ መቅደስ ውስጥ ያሉትን አስፈላጊ አገልግሎቶች ይሰጣሉ። ይሁን እንጂ ዋናው ሥራቸው በሺሁ ዘመን መንግሥት በተቀደሰውና በረከሰው መካከል ያለውን ልዩነት ለሕዝቡ መግለጥ ነው (ሕዝ 44)።

የሕዝቅኤል 40-48 የክርክር ሐሳብ ማጠቃለያ፤ ሕዝቅኤል የተሐድሶ ተስፋ የሚሰጡትን ስድስቱን መልእክቶች ሰጥቶ ምርኮኞችን ካጽናና ዐሥራ ሦስት ዓመት ያህል ዐለፈ (33፥21-39፥29)። ከዚያም በአቡቀለምሲሳዊ ራእይ ሕዝቅኤል የመሲሑን መንግሥት ባሕርይ በመግለጽ የመጨረሻውን የማጽናኛ መልእክት ሰጠ። እግዚአብሔር በታሪክ ሁሉ ከእስራኤል ጋር እጅግ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰውን ሥራ የፈጸመ መሆኑን በመግለጥ ይህ ራእይ የመጽሐፉ መደምደሚያ ነው። የሠራውን ታላቅ ሥራ በመግለጥ፣ ይህ ራእይ የሕዝቅኤልን መጽሐፍ ያጠናቅቃል። ቅድስት ሕዝብ በመሆን እርሱን እንድታመልክና የእርሱንም አምላክነት እንድትገልጥ እግዚአብሔር እስራኤልን ይመሠርታታል። እግዚአብሔር እስራኤልን በመጀመሪያ ሲፈጥር፣ ለህልውናዋ የሚያስፈልጉ ሦስት ነገሮች ነበሩ፤ እነርሱም ሕዝብ፣ መንግሥትና አገር ናቸው። እግዚአብሔር እስራኤልን በመሲሑ መንግሥት እንደ ገና ሲመሠርት እነዚህ ሦስት ተመሳሳይ ነገሮች መኖር አለባቸው። በምዕ 34-37 ላይ በተገለጠው ታላቅ መልሶ መቋቋም መሠረት፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደ ገና ይሰበስባል። ለእስራኤል ዐዲስ መንግሥትን ይሰጣታል (የመኖሪያ መመሪያን ይሰጣታል)፤ በተስፋዱቱም ምድር ለዘላለም ይመሠርታታል (ምዕ 40-48)።

የእስራኤል መንግሥት እንደ ገና መመሥረት በምዕ 40-46 ተገልጾአል። የዐዲስ ሕይወትዋ ማእከል በመካከልዋ ተገኝቶ ይገዛት ዘንድ በክብር ዳግም የሚመጣው ጌታ ራሱ ይሆናል (43፥1-9)። በምዕ 40-42 በዝርዝር በተገለጸው መሠረት የሺሁ ዘመን ቤተ መቅደስ ሲሠራ፣ ያ ለእግዚአብሔር ክብር ማደሪያ አስፈላጊነት ፍጻሜ ያገኛል። ቀደም ባለው ዘመን ማደሪያውን በኋላም በቤተ መቅደሱ እንዳደረገው ሁሉ በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱን ዙፋኑ በማድረግ (43፥7) ይገዛል፤ በ43፥13-46፥24 ያሉት መመሪያዎች ካህናት፣ መሪዎችና ሕዝቡ በቅድስና እንዲኖሩባቸው የሚያሳዩ ዝርዝር ጉዳዮችን የሚያመለክቱ ናቸው። ግዴታዎችና ሥራዎች በቢጋር መልክ ቀርበዋል፤ እስራኤላውያንም የእግዚአብሔርን ቅድስና በጉልሕ በማሳየት እነዚህን ደንቦች ያላንዳች ስሕተት ይፈጽሙ ዘንድ ግዴታ ተጥሎባቸዋል (43፥10-11፤ 44፥5-8)።

እስራኤልን በተስፋዱቱ ምድር መልሶ የማቋቋም ጉዳይ በምዕራፍ 36 ላይ በዝርዝር ቀርቦአል። ከዚያም በምዕራፍ 47-48 ላይ እግዚአብሔር ፍጹም በሆነው መንግሥቱ በሕይወት ወንዝ አማካይነት ያለማቋረጥ ሕዝቡን እንዴት እንደሚፈውስ፣ እንደሚባርክና ምድሪቱንም እንደሚያድስ በጉልሕ ያሳያል (47፥1-12 ይመ፤ ከዘፍ 2፥8-10፤ ከራእ 22፥1-3 ጋር ያነጻ)። የየነገዱ ድንበር ይወሰናል፤ ለካህናት፣ ለመሪዎች፣ ለከተማዪቱና ለቤተ መቅደሱ የሚሆነው መሬትም ይለያል። እስራኤል በበረከት ምድር እንደ ገና ስትመሠረት፣ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ሀልዎቱን ለእነርሱ ለማረጋገጥ ከተማዪቱን (ኢየሩሳሌምን) "እግዚአብሔር በዚያ አለ" (48፥35) በሚል ዐዲስ ስም ይጠራታል። እግዚአብሔር በዚያ ለዘላለም ይሆናል!

1. የአቡቀለምሲሳዊው ራእይ መቼት (40፥1-4)

1-4 ለዚህ አቡቀለሞሲሳዊ ራእይ እጅግ ወሳኝ የሆኑ አራት ሥነ ጽሑፋውያን መቼቶች አሉ፤ እነዚህም፦ የተጻፈበት ዘመን፣ ራእዩን የሚቀበሉት ሰዎች ማንነት፣ ራእዩን የሚቀበሉት ሰዎች ያሉበት ስፍራና ራእዩን ለመቀበል የሚያስችል የተመቻቸ ሁኔታ ናቸው።

ይህ አቡቀለምሲሳዊ ራእይ የተጻፈበት ዘመን አራት ገጽታዎች አሉት፦ (1) ሕዝቅኤል ይህን የገለጠው በተለመደው የዘመን አቁጣጠር ሥርዐት ነው፤ ይኸውም ዮአኪን ወደ ባቢሎን የተሰደደበትን ዘመን ማለትም 597 ዓቅክን በመጥቀስ ነው። ይህንን ራእይ የተቀበለው ዮአኪን በተማረከበት በሃያ ዐምስተኛው ዓመት ወይም በ573 ዓቅክ ነው።

(2) ራእዩ የተሰጠው በዚያ ዓመት መጀመሪያ ላይ ነው። እስራኤላውያን ሁለት የተለያዩ የዘመን አቁጣጠሮች አሏቸው። የሕዝቡ የዘመን አቁጣጠር የሚጀምረው በቲሽሪ ወር ማብቂያ ላይ ሲሆን፣ የሃይማኖቱ የዘመን አቁጣጠር የሚጀምረው ደግሞ በኒሳን የፀደይ ወር ነው። የሃይማኖቱ የዘመን አቁጣጠር የሚመረጥ ነው፤ ይኸውም ሕዝቅኤል ካህን ስለ ሆነና የአቡቃለምሲሳዊው ራእይ ሁኔታም ከሃይማኖት ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያለው በመሆኑ ነው። ስለሆነም የተጻፈበት ዘመን መጋቢት/ሚያዝያ 573 ዓቅክ ይሆናል።

(3) ራእዩ የተሰጠው ወሩ በገባ በዐሥረኛው ቀን ነበር። ይህ ወር ኒሳን ወር ከሆነ፣ ዐሥረኛው ቀን ሕዝቡ ለፋሲካ በዓል ዝግጅት ማድረግ ከጀመሩበት ከአራት ቀን በኋላ ነው። በስደት በነበሩበት ጊዜ ፋሲካን በትክክል ያክብሩ ወይም አያክብሩ አይታወቅም፤ ይሁን እንጂ እስራኤላውያን ከግብፅ እስራት ነጻ ወጥተው የነበሩበትንና አገራቸው የተፈጠረችበትን ሁኔታ ያሰላስሉ ነበር። ስለዚህ ይህ ራእይ እግዚአብሔር በመሲሑ መንግሥት ለሕዝቡ የገባውን የተስፋ ቃል እንደሚፈጽም የተሰጠ ማበረታቻ ነው።

(4) ራእዩ የተሰጠው ኢየሩሳሌም በባቢሎናውያን ሥር በወደቀች ማለትም በ586 ዓቅክ በዐሥራ አራተኛው ዓመት ነበር። ይህም 573 ዓቅክን የሚያረጋግጥ ነው።

የአቡቀለምሲሳዊው ራእይ መቼት ሁለተኛው ዋና ክፍል ራእዩን የተቀበለውን ሰው ማንነት የሚመለከት ነው። በእዝህ ጥቅሶች ውስጥ የሕዝቅኤል ስም ባይጠቀስም፣ ከአጠቃላዩ የመጽሐፉ ዐውድ አንጻር የጻሓፊው ማንነት በአንደኛ መደብ ተውላጠ ስም በመገለጹ ራእዩን የተቀበለው ራሱ ሕዝቅኤል ለመሆኑ ግልጽ ማስረጃ ነው።

የዚህ ራእይ መቼት ሦስተኛ ክፍል ራእዩን የተቀበለው ሰው የነበረበት ስፍራ ነው። ሕዝቅኤል ራእዩን የተቀበለው ከተማዪቱን በስተ ደቡብ ሊመለከት ከሚችልበት ከፍ ካለ ከእስራኤል ተራራ ላይ ሆኖ ነው። ተራራውም ሆነ ከተማዪቱ በስም አልተጠቀሱም። ይሁን እንጂ ሕዝቅኤል በራእይ የቤተ መቅደሱን ሕንጻ በዝርዝር ወደሚመለከትበት ወደ ከተማዪቱ ተወስዶአል። በሕዝቅኤል ዘመን በነበረው መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ መሠረት፣ ከተማዪቱ ኢየሩሳሌም ሳትሆን አትቀርም። ይሁን እንጂ ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን ከፍተኛ ተራራ ነበር ማለት አይቻልም።

የዚህ አቡቀለምሲሳዊ ራእይ ሥነ ጽሑፋዊ መቼት የመጨረሻ ክፍል ሕዝቅኤል ራእዩን በተቀበለበት ወቅት ሊጠቀስ የሚገባው ሁኔታ ነው። በዚህ ወቅት መልኩ ናስ የመሰለ መለኮታዊ መልእክተኛ ነበረ። እርሱም በእጁ የሐር ገመድና መለኪያ ዘንግ ይዞአል። ይህ ራእይ የሚሰጠው ያየውን ሁሉ በዝርዝር ለእስራኤል ቤት እንዲናገር ስለ ሆነ፣ መልእክተኛው የሚያሳየውን ሁሉ ሕዝቅኤል በጥንቃቄ እንዲመለከት መከረው።

2. አቡቀለምሲሳዊው ራእይ (40፥5-48፥35)

ሀ. የሺሁ ዘመን ቤተ መቅደስ (40፥5-42፥20)

መለኮታዊው መልእክተኛ ከውጨ በመጀመር፣ ቀስ በቀስ ወደ ውጫዊና ውስጣዊ አደባባዮች፣ ከዚያም ወደ ቤተ መቅደሱ ማደሪያ በመውሰድ ሕዝቅኤልን ወደ ቤተ መቅደሱ ሁሉ መራው። ይህንንም ያደረገው ብዙ ዝርዝር ጉዳዮችን በመስጠት በተለይም ርዝመቱንና ቁመቱን እንዲሁም ስፋቱን በመለካት ነበር። እነዚህ ዕቅዶችና ውስኖ ልኮች ዕቅዶችን በትክክል ለመሣልና ሞዴሎችን ለመሥራት የሚያስችሉ በእጅጉ ትክክለኛ ነበሩ።

(1) የውጨ አደባባይ (40፥5-27)

5 የቤተ መቅደሱ ዝርዝር መስፈርቶች ከምዕራፍ 40-42 ባሉት ክፍሎች በብዛት ተጠቅሰዋል። አንድ የታወቀ ክንድ የሚባለው ከመካከለኛው ጣታችን ጫፍ እስከ ክንዳችን ሥር ያለው ሲሆን፣ ይኸውም በግምት ዐሥራ ስምንት ኢንች ያህል ይሆናል። አንድ ስንዝር ማለት ከአውራ ጣት ጫፍ እስከ መዳፋችን ድረስ ያለው ስፋት ነው፤ ይህም በግምት ሦስት ኢንች ያህል ነው። ሕዝቅኤልን ይመራ የነበረው መለኮታዊው መልእክተኛ በእጁ የያዘው መለኪያ ዘንግ ስድስት ክንድ ያህል ይረዝማል። ረዥሙ ክንድ የተባለው አንድ ክንድና አንድ ስንዝር ማለት ነው፣ ወይም ዐሥራ ስምንት ኢንችና ሦስት ኢንች ሲደመር ማለት ነው። በዚህ የሕዝቅኤል ክፍል የተጠቀሱት መለኪያዎች የተለኩት በመለኪያው ዘንግ በመሆኑ፣ በሕዝቅኤል የተጠቀሰው "ክንድ" የታወቀው "ረዥም ክንድ" ሃያ ኢንች ያህል ይሆናል።

የቤተ መቅደሱን ሕንጻ የመለካት እንቅስቃሴ ከውጭ ቢጀመርም መልእክተኛው ሕንፃውን ሙሉ በሙሉ የከበበውን ቅጥር ለሕዝቅኤል አሳይቶታል። የቅጥሩ ቁመት አንድ ዘንግ እንዲሁም ስፋቱ አንድ ዘንግ ነው፤ ወይም እያንዳንዱ ስድስት ረዥም ክንድ ያህል ይሆናል ማለት ነው፤ ይህም በግምት ዐሥር ከግማሽ ጫማ ያህል ነው።

6-16 ሕዝቅኤል በቤተ መቅደሱ ሕንጻ ወደ ውጨ አደባባይ ወደሚያወጣው የምሥራቅ በር ተወስደ። መለኮታዊው መልእክተኛ የበሩን ንድፍና የአሠራሩን ዝርዝር ዕቅድ ገለጸለት (ሥዕል 1 ይመልከቱ)። የበሩን ዝርዝር ንድፍ ገለጻ ሲጀምር ከውጭ ወደ ውስጥ በማሳየት ነበር። በሩ ሰባት ደረጃዎች ያሉት ሲሆን፣ ይኸውም ከውጭ ወደ መግቢያው የሚመራ ነው። ምናልባት እነዚህ ደረጃዎች በቍጥር 11 ላይ ከተገለጹት "የዘብ ቤቶች" ጋር ተመሳሳይ ሳይሆኑ አይቀሩም። ነገሩ እንደዚያ ከሆነ መግቢያ ደረጃዎቹ ስፋታቸው ዐሥር ክንድ፣ ቁመታቸው ደግሞ ዐሥራ ሦስት ክንድ ነበር። የሰሜንና የደቡብ የውጭ በሮች ከምሥራቁ በር ጋር ተመሳሳይ የሆነ መጠን አላቸው (ከቍ 20-27 ጋር ያነጻ)። የበሩ መግቢያ መድረክ ስፋቱ ዐሥር ክንድ ከፍታው ስድስት ክንድ ነበር። የመግቢያ በሩ አጠቃላይ አሠራር የሥነ ቅርስ ተመራማሪዎች ካገኙት በሰሎሞን ዘመን ከነበረው አያሌ መግቢያ በር ጋር ተመሳሳይ ነው። በውስጠኛው የሰሎሞን በር ግራና ቀኝ ብዙ የዘብ ቤቶች (ከ1ነገ 24፥28፤ ከ2ዜና 12፥11 ጋር ያነጻ) ወይም የዘብ ጠባቂ ቤቶች ነበሩ። በዚህ በር በውስጠኛው በር ግራና ቀኝ እያንዳንዳቸው በትይዩአቸው እኩል በኩል ስድስት ክንድና አንድ ክንድ ከፍታ ያለው የግንብ ዐጥር ያላቸው ሦስት የዘብ ቤቶች (ዘቤ) ነበሩ። ሦስቱን የውስጥ የዘብ ጥበቃ ቤቶችን የሚለዩት ግንቦች (ግ) ልክ ዐምስት ክንድ ነበር። የበሩ መድረክ ወለል (የመወ) እንደ ውጨ መግቢያ በር አንድ ዘንግ (ወይም ስድስት ክንድ) ነበር።

በውስጠኛው መግቢያ በር የሚገኘው "መተላለፊያ በረንዳው" (መበ) ወይም መተላለፊያ መግቢያው ከበሩና ከአደባባዩ ፊት ለፊት ነው። ከቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት ካለው ሁለት ክንድ የበር መዝጊያ ጋር ስፋቱ ስምንት ክንድ ነበር። የመተላለፊያ በረንዳው ሁሉም ጎኖች ማለትም ሁሉም ስፋቶችና ሁሉም ርዝመቶች ከተለኩ ቀኑ 14 ላይ የተጠቀሰው መጠን አጠቃላይ ልኩ እንደ ሆነ መረዳት ይቻላል። በአጠቃላይ ሥልሳ ክንድ ነው፤ ይህም ሰምንት ክንድ ጎን በሃያ ሁለት ክንድ ርዝመት ማለት ነው። በሌላ አነጋገር እነዚህ መተላለፊያ በረንዳዎች የሚያመለክቱት በበር ላይ ያለውን ክፈፍ ወይም ጌጥ ከሆነ፣ ስድስት ክንድ በእያንዳንዱ በር ላይ ያለው ክፈፍ ቁመት ሊሆን ይችላል ማለት ነው። በእያንዳንዱ የበረንዳ መተላለፊያና የዘብ ቤት፣ መስኮቶች (መ) ወይም የበረንዳ ክፍተቶች ነበሩ፤ ይሁን እንጂ የእያንዳንዱ ቍጥርና ያለበት ስፍራ በትክክል አይታወቅም። የተጠቀሰው ጌጥ በእያንዳንዱ ክፍል ግራና ቀኝ ግድግዳ ላይ የተቀረጸው የዘንባባ ዛፍ ምስል ብቻ ነው።

በአጠቃላይ የበሩ ርዝመት ሃያ ዐምስት ክንድ ሲሆን፣ ቁመቱ ዐምሳ ክንድ ነው።


17-19 የውጪው አደባባይ (ሥዕል 2ን ይመልከቱ) የምሥራቁን በር ርዝመት የሚያህል ስፋት ያለው የድንጋይ ንጣፍ (ድን) አለው፤ ይኸውም ዐምሳ ክንድ ያህል ነው። ይህ የድንጋይ ንጣፍ የውጪውን አደባባይ ድንበር ዙሪያውን ሰለሚለይ የታችኛው ንጣፍ ወለል ተብሎ ይጠራል። በውጪው አደባባይ ዙሪያውን ሠላሳ ክፍሎች (ክ) አሉ። የውጪው አደባባይ ስፋት ማለትም ከውጪው ምሥራቃዊ በር እስከ ውስጠኛው ምሥራቃዊ በር ዙሪያውን አንድ መቶ እንደ ሆነ ይገመታል። ተመሳሳይ የሆነ ልክ የሰሜኑንና የደቡቡን የውጭ በር ፊት ለፊታቸው ካሉት የውስጥ በሮች ለይቶአቸዋል (40፥23፡ 27)።

20-27 የውጪው ሰሜናዊና ደቡባዊ በር አሠራር ከውጪው ምሥራቅ በር አሠራር ጋር ሙሉ በሙሉ አንድ ዐይነት ነበር (ከቍ 6-16 ጋር ያነጻ)።

2. የውስጠኛው አደባባይ (40፥28-47)

28-37 ወደ ውስጠኛው አደባባይ ሲገባ፣ መሪው በመጀመሪያ ስለ በሮቹ መናገር ጀመረ፤ ከዚያም መሥዋዕት ስለሚዘጋጅባቸው፣ በመቀጠልም አገልጋይ ካህናት ስለሚጠቀሙባቸው ክፍሎች እንዲሁም በመጨረሻ ስለ ውስጠኛው ክፍል አጠቃላይ ስፋትና ባሕርይ ተናገረ።

ሥዕላዊ ማስረጃ 1
የውጨ አደባባይ በሮች ሁሉ አቋቋም



ቍልፍ

ግዐ - የግንብ ዐጥር (መካታዎች፣ ወሰኖች፣ ቦታ) (40፥12ሀ)

ዘቤ - የዘብ ቤት (ንዳዎች፣ የዘብ ቤቶች) (40፥7ሀ፡10ሀ፡12ለ)

መበ - መተላለፊያ በረንዳ (ሰበሰብ፣ መተላለፊያ መግቢያ) (407ሐ፡ 8-9፡14)

ግ - የዘብ ቤቶችን የሚለዩ ግንቦች (40፥7ለ፤ 10ለ)

በመመ - የበሩ መግቢያ መድረክ (40፥6፡11)

የመወ - የበሩ መድረክ ወለል (40፥7ሐ)


መ - መስኮቶች (40፥16)

ደ - ደረጃዎች (40፥6ለ፡ 22ለ፡ 26ሀ)

መሪው ከቀኝ ወደ ግራ ያለውን አቅጣጫ ይዞ ከደቡብ መግቢያ በር በመጀመር ወደ ውስጠኛው አደባባይ የሚወስዱትን ሦስቱን መግቢያዎች ለሕዝቅኤል አሳየው፡፡ እያንዳንዳቸው እነዚህ መግቢያዎች በልካቸውና በመሠረታዊ ዕቅዳቸው ረገድ ከውጪው አደባባይ መግቢያዎች ጋር አንድ ናቸው፡፡ ከውጪው በር በተለየ በውስጠኛው በር ሁለት የተለወጡ ነገሮች አሉ፡፡ ሁሉም የውስጥ በሮች ወደ ውስጥ ከመሆን ይልቅ ወደ ውጭ ትይዩ የሆኑ በረንዳዎች አሏቸው፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዱ ደረጃ ወደ ውስጠኛው በር የሚያስገባ ሰባት ሳይሆኑ ስምንት መረማመጃዎች አሉት፡፡ ቍጥር 30 የሚያመለክተው የውስጠኛው በሮች በረንዳዎች ሰፋት ዐምስት ክንድ በሣያ ዐምስት ክንድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ልክ በውጪው በሮች ካሉት በረንዳዎች ልክ ጋር አንድ አይደለም፤ የመጽሐፉ ክፍል ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት ልዩነቶች በቀር የውስጠኛውና የውጩ በሮች ስፋት ተመሳሳይ እንደ ሆነ ይገልጻል፡፡ ምናልባት የመጨረሻው መፍትሔ የውስጠኛ በሮች መተላለፊያ በረንዳ ልክ ከውጪው በሮች መተላለፊያ በረንዳ ልክ በመጠኑ የተለየ መሆኑ ነው፡፡

38-43 ሕዝቅኤልና መለኮታዊው መልእክተኛ በሰሜናዊው ውስጠኛ በር አጠገብ እንደ ቆሙ፣ መልእክተኛው መሥዋዕቶቹ የሚዘጋጁባቸውን ክፍሎችና (መሥማክ) ጠረጴዛዎች (ጠ) ገለጸ፡፡ በእያንዳንዱ የውስጥ በር መግቢያ አጠገብ የተለየ ክፍል አለ፡፡ ይህ ማለት እያንዳንዱ ክፍል (መሥማ) ወደ ውስጠኛው በር መተላለፊያ ከሚመሩት ደረጃዎች ጐን በውጪው አደባባይ ነበር ማለት ነው፡፡ በዚህ ስፍራ በሥርዐቱ መሠረት የሚቃጠሉ መሥዋዕቶች መታጠብ ነበረባቸው፡፡ በቍጥር 38 ላይ በእንግሊዝኛው የተጠቀሰው መግቢያ በር የሚለው ቃል በብዙ ቍጥር የተጠቀሰ ቢሆንም በቍጥር 39 ላይ በነጠላ ቍጥር ተጠቅሶአል፡፡ አንድምታውም በውስጠኛው በር በረንዳ ላይ በትይዩ የተቀመጡት ሁለቱ ጠረጴዛዎች ለመሥዋዕት የሚቀርቡት ከብቶች የሚታረዱባቸው ናቸው ማለት ነው፡፡ በእያንዳንዱ መተላለፊያ በረንዳ ባሉት በእነዚህ ጠረጴዛዎች (ጠ) የሚቃጠል መሥዋዕት፣ የኀጢአት መሥዋዕትና የበደል መሥዋዕት ማለትም መቅረብ የሚገባው የእንስሳ ወይም የወፍ መሥዋዕት ይሠዋል ወይም ይታረዳል፡፡ የእነዚህ መሥዋዕቶች አስፈላጊነት የዚህ ክፍል መግቢያ በሆነውና በአምልኮ ሥርዐት ውስጥ እነዚህ መሥዋዕቶች በተወሠኑበት ከዚህ በታች ታትቶአል፡፡

ሥዕላዊ ማስረጃ 2
የቤተ መቅደሱ ሕንጻ



ቍልፍ

መሠ	*መሠዊያ* **(40፥47ለ)**
ሕግ	የሕንጻው ግንብ **(41፥12፡ 13ለ፡ 15)**
መሥመቀ	ካህናት መሥዋዕት የሚቀቅሉበት ቦታ **(46፥19-20)**
ሕመካቀ	የሕዝቡን መሥዋዕት ካህናት የሚቀቅሉበት ቦታ **(46፥21-24)**
መመ	*መመላለሻ* **(40፥17-18)**
ካክ	የካህናት ክፍሎች **(42፥1-14)**
ክ	ክፍሎች በውጪው አደባባይ የዕቃ ቤት ወይም የካህናት ክፍሎች **(40፥17)**
መዘክ	የመዘምራን (ካህናት) ክፍሎች **(40፥44-46)**
ጠ	መሥዋዕት ማረጃ ጠረጴዛዎች (ሁለት በእያንዳንዱ ሰፍራ **(40፥39-43)**
ቤመ	ቤተ መቅደሱ **(40፥48-41፥11፡13ሀ፡ 14:16:23-26)**
መሥማክሠ	*መሥዋዕት* ማጠቢያ ክፍሎች **(40፥38)**
	የውስጡ አደባባይ **(40፥44-47ሀ)**
	የውጪው አደባባይ
	(40፥17-19:23:27:39-43)
	ወርድ ከውጪ መግቢያ በር እስከ ውስጠኛው መግቢያ በር **(40፥19:23:27)**

በስተ ሰሜን ያለው የውስጠኛው በር ለስፍራው ለየት ያሉ የቤት ዕቃዎች ነበሩት። በውጪ አደባባይ በሰሜኑ ውስጠኛ በር ውጭ በደረጃዎቹ ግራና ቀኝ መሥዋዕቶቹ የሚታረዱባቸው ሁለት ተጨማሪ ጠረጴዛዎች (ጠ) ተቀምጠው ነበር። ይህም በሰሜናዊው የውስጥ በር በውጭና በውስጥ በኩል በአጠቃላይ ስምንት ጠረጴዛዎች አሉ ማለት ነው። በድንጋይ የተሰበጡ አራት ትንንሽ ጠረጴዛዎች በተጨማሪ አሉ፤ እነዚህ ጠረጴዛዎችም አንድ ተኩል ክንድ ስፋትና አንድ ክንድ ከፍታ ያላቸው ሲሆኑ፣ መሥዕቶቹን ለማረድ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች የሚቀመጡባቸው፤ በሰሜናዊው የውስጥ በር በኩል የሚገኙ ነበሩ። ሁለት አፍ ያላቸው ሜንጦዎችም በመተላለፊያው በረንዳ ግድግዳ ላይ ተንጠልጥለዋል።

44-46 በሰሜናዊውና በምሥራቃዊው ውስጠኛ በር በስተ ውስጥ በኩል ለካህናቱ ለሳዶቅ ልጆች የተዘጋጁ ክፍሎች (መክ) አሉ። እነዚህ ካህናት ከሌዋውያን ካህናት በቀጥታ እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ የተፈቀደላቸው ናቸው። የሌዊ ሌሎች ዘሮች ከዚህ አገልግሎት መታገዳቸው በምዕራፍ 44 ላይ ተገልጾአል። የዕብራይስጡ ትርጕም ክፍሎቹ በተለይ ለመዘምራን የተለዩ መሆናቸውን ያመለክታል። በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ ለሚኖሩት ካህናት ሌላ ሥራ ቢኖርም፣ በብሉይ ኪዳን የቤተ መቅደስ አምልኮ ውስጥ የካህናት ሥራ መዘመር ነበር (ከ1ዜና 16፥4-6፤ 23፥5፤ ከ2ዜና 29 ጋር ያነጻ)። ከሰሜኑ በር በስተ ውስጥ በኩል ወደ ደቡብ ፊታቸውን ያደረጉ ክፍሎች በቤተ መቅደሱ የሚያገለግሉ ካህናት ቤቶች ናቸው። ከምሥራቁ በር በስተ ውስጥ በኩል ወደ ሰሜን ፊቱን ያዞረው ክፍል በመሥዋዕቱ መሠዊያ ላይ ቀደም ሲል ያገለገሉ ካህናት ቤት ነው።

47 የውስጠኛው ክፍል አደባባይ መቶ ክንድ የሆነ እኩል በእኩል ባለ አራት ማእዘን ነበር። የመሥዋዕቱ መሠዊያ (መሠ፤ ምዕ 43 ይመ) ከቤተ መቅደሱ (ቤመ) ፊት ለፊት ነው።

(3) የእግዚአብሔር ቤት (40፥48-41፥26)

48-49 መለኮታዊው መልእክተኛ በመቀጠል ወደ ቤተመቅደሱ ሕንጻ ራሱ ተንቀሳቀሰ (*ሥዕዊ መግለጫ* 3 ይመ)። ዐሥራ አራት ክንድ ስፋት ያለው የቤተ መቅደሱ መግቢያ የሚደረስበት ብዙ ደረጃዎችን በመውጣት ነው። ከመተላለፊያው በረንዳ ፊት ለፊት በመሆን (መተበ) ሕዝቅኤል ከቤተ መቅደሱ ግድግዳ ግራና ቀኝ ሦስት ሦስት ክንድ ስፋት ካላቸው ወጣ ወጣ ካሉ ግንቦች ጋር የተያያዙ ዐምስት ክንድ ስፋት ያላቸውን መተላለፊያ በረንዳዎች ተመለከተ። ዐሞዶቹ (ዐ) ምናልባት ያቁምና በዔዝ ከተባሉት ከሰሎሞን ቤተ መቅደስና ከሄሮድስ ቤተ መቅደስ ጋር ተመሳሳይ ሳይሆኑ አይቀሩም፤ እነርሱም ከመተላለፊያ በረንዳዎቹ ፊት ለፊት በግራና በቀኝ የቆሙ ናቸው። ሕዝቅኤል በቤተ መቅደሱ በረንዳ (መተበ) ደጃፍ ላይ እንደ ቆመ ሃያ ክንድ በዐሥራ አንድ ክንድ ስፋት ያለው ክፍል ተመለከተ።

41፥1-2 የውጪው ቤተ መቅደስ (መቅ) ወይም ቅድስት የሚባለው ስፍራ ወርዱ ሃያ ክንድ ርዝመቱ አርባ ክንድ የሆነ ክፍል ነበረው። ዐሥር ክንድ ወርድ ያለው መግቢያ በር (ቤመግ) በግራና በቀኝ ስድስት ክንድ ወርድ ባላቸው የበር መዝጊያዎች የተከበበ ሲሆን፣ በውስጥ ካለው ግድግዳ ወጣ ወጣ ባሉ በግራና በቀኝ ዐምስት ክንድ ወርድ ካላቸው ግንቦች (ወጣግ) ጋር ተያይዞ ነበር።

3-4 ከዚያም ሕዝቅኤል ስድስት ክንድ ወርድ ባለው የመግቢያ በር (መቅቅ) በኩል ሁለት ክንድ ወርድ ባለውና ከግድግዳው ጋር በተያያዘው ሰባት ክንድ ወርድ ባለው መዝጊያ (ወጣግ) ወደ ውስጠኛው ቤተ መቅደስ (ቅቅ) ውስጥ ገባ። ሕዝቅኤል ሃያ ክንድ እኩል በኩል የሆነውን አራት ማእዘን ክፍል ሲመለከት፣ ክፍሉ "ቅድስተ ቅዱሳን" እንደ ሆነ ተነገረው። ወደ ቤተ መቅደሱ መተላለፊያ በረንዳ (40፥48) በመግባት ወደ መግቢያው በር እየተጠጋ፣ ወደ ቤተ መቅደሱ ውጫዊ ክፍል (41፥2) እና ከዚያም ወደ ውስጣዊው ቤተ መቅደስ (41፥3) ማለትም በቅደም ተከተል ከዐሥራ አራት ክንድ ወደ ዐሥር ክንድ፣ ወደ ስድስት ክንድ እየጠበበ ሲመጣ የሕንጻ መሐንዲሱ የአምላኪው ዐይኖች ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ወይም የአምልኮው ማእከል ወደ ሆነው ስፍራ እንዲያተኩሩ ያደርጋል።

5-11 መላው ቤተ መቅደስ ስድስት ክንድ ውፍረት ባለው ግንብ (ግ) የተከበበ ነው። ከዚህ ግድግዳ አጠገብ ግን ያልተያያዙ አራት ክንድ ወርድና በሦስት ደርብ የተሠሩ ዘጠና ክፍሎች አሉ (ቤዙክ)። በእያንዳንዱ ደረጃ ያሉ ሠላሳ ክፍሎች አንድ ሰው ከአንድ ደርብ ወደ ላይ ሲወጣ እየሰፉ ይሄዳሉ። ደረጃዎች ሦስቱን ደርቦች ከታች ወደ ላይ ያይዛሉ። እነዚህ ክፍሎች (ቤዙክ) ዐምስት ክንድ ውፍረት ያለው የውጭ ግንብ አላቸው (ግ)፤ እያንዳንዳቸውም ከቤተ መቅደሱ ግራና ቀኝ ስድስት ክንድ በሆነ መሠረት ላይ ያረፉ ናቸው። ይህ መሠረት ከቤተ መቅደሱ ውጭያዊ ግንብ እስከ መሠረቱ ጫፍ ድረስ በተጨማሪ ዐምስት ክንድ ያህል እየሰፋ የሚሄድ ነው። የእነዚህ ክፍሎች መግቢያ በሮች ከቤተ መቅደሱ ሕንጻ ውስጠኛ አደባባይ (*ሥዕላዊ ማስረጃ 2* ይመ) በስተ ሰሜንና በስተ ደቡብ ያሉ ናቸው። ሃያ ክንድ እነዚህን የጐን ክፍሎች ከካህናት ክፍሎች (ክክ) ይለያቸዋል (መዘክ በ*ሥዕላዊ ማስረጃ 2*)።

12-26 ከቤተ መቅደሱ በስተ ምዕራብ፣ ከቤተ መቅደሱ ሕንጻ ምዕራባዊ ግድግዳ አጠገብ ያለ የሚመስል የተለየ ሕንጻ አለ (*ሥዕላዊ ማስረጃ ሕግ 2* ይመ) አገልግሎቱ ምን እንደ ሆነ አይታወቅም። ሕንጻው ሰባ ክንድ ወርድና ዘጠና ክንድ ርዝመት ያለው ሲሆን፣ በዙሪያው ዐምስት ክንድ ውፍረት ያለው ቅጥር አለ። በግራና በቀኝ ካለው ዐምስት ክንድ ግድግዳ በተጨማሪ ዘጠና ክንድ ርዝመት ያለው ሲሆን፣ ሕንጻው በቀጥታ ከሰሜን ወደ ደቡብ በትክክል አንድ መቶ ክንድ ነው፤ ወርዱም፣ ከውስጠኛው አደባባይ እስከ ምሥራቃዊው የሕንጻ አካል ድረስ ተመሳሳይ ነው።

የቤተ መቅደሱ ሕንጻ ጌጦች በበረንዳዎቹ ዙሪያ ያሉ መስኮቶችን፣ ውጫኣዊውን ቤተ መቅደስና ውስጣዊውን ቤተ መቅደስ ያካተቱ ናቸው። የቤተ መቅደሱ ሕንጻ የውስጥ ግድግዳዎች መስኮቶቹን ጨምሮ በዕንጨት ተሰብደዋል። በእነዚህ የዕንጨት የውስጥ ግድግዳዎች በውጪያቸውም ጭምር የተሰባጠሩ የኪሩብና የዘንባባ ዛፎች ምስሎች ተቀርጸውባቸው ነበር። እያንዳንዱ ኪሩብ ሁለት ፊቶች ሲኖሩት፣ እያንዳንዱ ፊት ወደ እያንዳንዱ የዘንባባ ቅርጽ የዞረ ነበር። ፊቶቹ የሰውና የአንበሳ ምስል ነበራቸው። ኪሩቤል የእግዚአብሔር ቅድስና

ጠባቂዎችን የሚወክሉ ትእምርት ቢሆኑም የዘንባባ ዛፎቹ ምሳሌነት ግን አይታወቅም።

በቤተ መቅደሱ ውስጥ ያለው ዕቃ ሦስት ክንድ ቁመት፣ ሁለት ክንድ ወርድና ሁለት ክንድ ርዝመት ያለው የዕንጨት መሠዊያ ብቻ ነበር። መለኮታዊው መልእክተኛ ይህንን "በእግዚአብሔር ፊት ያለ ገበታ" ብሎ ጠርቶታል። ይህ መሠዊያ ከመሥዋዕት መሠዊያው በእጅጉ ያነሰ ነበር (ከ43፥13-17 ጋር ያነጻ)። አንዳንዶች ይህ በሙሴያዊው ሥርዐት ከቅድስተ ቅዱሳን መጋረጃ በፊት የሚቀመጠው የዕጣን መሠዊያ ነው ብለው ይናገራሉ። የዕጣን መሠዊያው በማደሪያው ውስጥ ያለ ቅዱሳን የሚያቀርቡት ጸሎት ምሳሌ ነው።

የውጫዊው ቤተ መቅደስ መግቢያ በርም (በሥዕላዊ ማስረጃ 3 ቤመግ ይመ) ሆነ የውስጠኛው ቤተ መቅደስ መግቢያ በር (መቅቅ) አራት ማእዘን በሮች ነበሩአቸው። እነዚህ በሮች ሁለት ሲሆኑ፣ በመካከላቸው ላይ በመታጠፊያ የተያያዙ መዝጊያዎች አሏቸው። በውጫዊው ቤተ መቅደስ ባሉት በሮች ላይ ኪሩቤልና የዘንባባ ዛፎቹ ተሰባጥረው በውጫዊው ግድግዳ ላይ ካሉት በተመሳሳይ መልኩ ተቀርጸውባቸዋል።

የቤተ መቅደሱ ሕንጻ በአጠቃላይ ታላቅ ውበትና የተመጣጠነ ቅርጽ ነበረው።

(4) የካህናት ሕንጻዎች (42፥1-14)

1-9 አንዱ በሰሜን ሌላው በደቡብ ያሉ ልክ ከውስጠኛው አደባባይ ውጭ በውጪው አደባባይ ሁለት ሕንጻዎች አሉ (ሥዕላዊ ማስረጃ 2 ከክ 2 ይመ)። ሕንጻው ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ አንድ መቶ ክንድ ርዝመት ሲኖረው፣ ወርዱ ደግሞ ከሰሜን ወደ ደቡብ ዐምሳ ክንድ ያህል ነው። የሰሜኑ ሕንጻ ከውጪው አደባባይ በትይዩ ካለው የንጣፍ ድንጋይ ጋር ያለ ሲሆን፣ ከውስጠኛው አደባባይ ሰሜናዊ ግድግዳ ጋር የተያያዘ ነው። ባለ ሦስት ደርብ ሲሆን፣ በእያንዳንዱም ወለል ብዙ ክፍሎችና ሰገነቶች አሉት። ታችኛዎቹ ደርቦች ለሕንጻው ድጋፍ የሚሆኑ ዐምዶች አሏቸው። በሦስተኛው ወለል ላይ ያሉት ክፍሎች ትንንሾች ናቸው፤ ቢሆንም ሦስተኛው ወለል ከመካከለኛውና በምድር ካሉት ወለሎች ይልቅ ትልልቅ ሰገነቶች አሉት። ሁሉም ክፍሎች ፊቱን ወደ ሰሜን ያዞረ በር አላቸው። ታችኛው ወለል ዐሥር ክንድ ወርድና አንድ ክንድ ርዝመት ያለው ከፊት ለፊቱ ደረጃ ያለው መግቢያ በር አለው (ከሞ 11-12 ጋር ያነጻ)። በሕንጻው ታችኛ ወለልም ምሥራቃዊ መግቢያ በር አለው፤ በእያንዳንዱም ፊት ከሕንጻው መጨረሻ ፊት ለፊት በትይዩ ግድግዳ አለ። ምናልባት ይህ ግድግዳ በውጪው አደባባይ ከሚሠራው ሌላ ሥራ ለመለየት የብቻ ምስጢራዊ ክፍልን የሚሰጥ ነው።

10-12 በማንኛውም አደረጃጀቱ የሰሜኑ ሕንጻ ከደቡብ ሕንጻ ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ያለውንም አጠቃላይ ንድፍ ፍጹም ወጥ የሆነ አሠራሩን የሚያመለክት ነው (በዐመት በቁ. 10 ላይ ያለውን ማስታወሻ በተለይም "ወደ ምሥራቅ" ከማለት ይልቅ "ደቡብ" ያለውን ይመ)።


13-14 እነዚህ ሁለት ሕንጻዎች የተቀደሱ ስፍራዎች ሲሆኑ፣ የሳዶቅ ልጆች የሆኑት ካህናት የተቀደሰውን ቍርባን የሚበሉባቸው እንዲሁም ለአገልግሎት የሚለብሱአቸውን የተቀደሱ ልብሶቻቸውን በዕለት ተለት ልብሶቻቸው የሚቀይሩባቸው ናቸው። ካህናቱ ከፊል የእህል ቍርባን፣ ከፊል የኀጢአት መሥዋዕትና ከፊል የበደል መሥዋዕት መብላት ነበረባቸው። ይህ ሕንጻ በተጨማሪ ከፊል መሥዋዕቶችን ለማስቀመጥ ያገለግል ነበር። ካህናቱም የክህነት ልብሶቻቸውን በእነዚሁ ሕንጻዎች ውስጥ ያኖሩአቸዋል። ይህንንም በማድረግ የተቀደሰውን ከረከሰው መካከል በመለየት ያገለግሉ ነበር።

(5) የቤተ መቅደሱ ልክ (42፥15-20)

15-20 መለኮታዊው መልእክተኛ ሕዝቅኤልን በምሥራቁ በኩል ይዞ ከቤተ መቅደሱ ሕንጻ ወደ ውጭ አወጣው። ለማደሪያው የተለየውንም ሰፊ ሰፍራ ሕዝቅኤል እንዲመለከት ተደረገ። ዐምስት መቶ ክንድ እኩል በእኩል ተለካ (ከዐመት ማብራሪያ ጋር ያነጻ)፤ እኩል በእኩል አንድ ማይል ማለት ነው። አንዳንዶቹ "ዘንግ" (16.5 ጫማ) የሚለውን ቃል በመሰረዝ ክንድ ይላሉ፤ ይህም በእነዚህ ጥቅሶች የተጠበቀው መለኪያ ነው። ይሁን እንጂ እንዲህ ዐይነቱ ለውጥ በ45፥2 ከተጠቀሰው ጋር የሚጣረር ነው፤ ምክንያቱም ይህ የቤተ መቅደሱን ዙሪያ "ዐምስት መቶ ክንድ በዐምስት መቶ ክንድ" ስለሚያደርገው ነው። "ዘንግም" ሆነ "ክንድ" በግልጽ አልተመለከቱም። ሕዝቅኤል 45፥2 የሚገልጸው ዙሪያ ዐምሳ ክንድ መሆኑ "500 በ 500" ለሆነው ስፋት ክፍተትን ይሰጣል። ሕዝቅኤል በግልጽ ክንድ የሚለውን ቃል መጠቀሙ፣ በ42፥15-20 ስፋቱ "500 . . . ዘንግ" በሚል የተገለጸውን በግልጽ ያስቀምጣል። አንዳንዶች 500 ዘንግ የሚለው ስፋት (1.5 ማይል^2) ትልቅ ከመሆኑ የተነሣ የመሬት አቀማመጡን አይሞላውም ብለው ይናገራሉ። ነገር ግን ዘካርያስና ሌሎች ነቢያት በአጠቃላይ የፓለስቲና የመሬት አቀማመጥ በሺሁ ዘመን መጀመሪያ ላይ መልክአ ምድራዊ መሻሻል እንደሚታይበት ተናግረዋል። በእነዚህ ጥቅሶች ያለውን "ዘንግ" የሚያሸር በቂ ምክንያት የለም።

ሥዕላዊ ማስረጃ 3

ቤተ መቅደሱ



ቤመግ	ወደ ቤተ መቅደሱ መግቢያ (የውጪው መቅደስ (41፥20፤ ከ41፥23-25 ጋር ያነጻ)
መቅቅ	ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መግቢያ (ቅድስተ ቅዱሳን) (41፥3 ይመ፤ ከ41፥23-25 ጋር ያነጻ)
መቅ	መቅደስ (መቅደስ) (41፥2ለ፤ 21ለ)
ቅቅ	(የውስጠኛው መቅደስ) (41፥4)
መተበ	መተላለፊያ በረንዳ (40፥48-49)
ዐ	ዐምዶች (40፥49)
ወጣግ	(ቅስት፣ ዐምድ) የቅድስተ ቅዱሳኑ መግቢያ (41፥3)
መተባ	(ቅስት፣ ዐምድ) የመተላለፊያው ግንብ (40፥48)
ቤመግ	(ቅስት፣ ዐምድ) የቤተ መቅደሱ ግንብ (41፥1)
ቤዙክ	የቤተ መቅደሱ ዙሪያ ክፍሎች (41፥5ለ-11ሀ)
ቤዙክቦ	በቤተ መቅደሱ ዙሪያ ክፍተት ቦታ (መድረክ) (41፥11ለ)
ግሠ	የቤተ መቅደሱ ግንብ (41፥5ሀ) በግራና በቀኝ የተከበበ ቦታ ያለው ሆኖ የቤተ መቅደሱ አጠቃላይ ልክ (41፥13ሀ፡14) በመተላለፊያው፣ በጐን ክፍሎችና በጌጦች ላይ (41፥16-20) ላይ ያሉ መስኮቶች (41፥16፡26)

ይህ፣ ትልቁ ስፍራ በቅዱሱ (የቤተ መቅደሱ ሕንጻና የአምልኮው ስፍራ) እና ዕለት ተለት በሚኖርበት በተራው መሬት (ወይም በረከሰው) መካከል ያለውን የሚለየውን ስፍራ ያመለክታል። እስራኤል በተደጋጋሚ ባለፈው ታሪክዋ ይህንን ልዩነት ረስታለች።

ለ. የእግዚአብሔር ክብር ወደ ቤተ መቅደሱ መመለስ (43፥1-12)

1-5 ሕዝቅኤል ከዚህ በኋላ ወደ ውጪው አደባባይ ምሥራቃዊ በር ወደ ምሥራቅ ፊት ለፊት ሊመለከት ወደሚችልበት ቦታ መጣ። በዚህም የዚህን አቡቀለምሲሳዊ ራእይ አጠቃላይ ዋነኛ ገጽታ ሊመለከት ይችላል፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ክብር ወደ ቤተ መቅደሱ መመለሱ ነው!

ሕዝቅኤል ያየው የእግዚአብሔር ክብር በኮቦር ወንዝ በመጀመሪያው ራእይ ከተመለከተው ጋር ተመሳሳይ የእግዚአብሔር ክብርና (ምዕ 1፤3) እንዲሁም የኢየሩሳሌምን ውድመት በተናገረበት ጊዜ ከቤተ መቅደሱ ከሄደው ክብር ጋር (ምዕ 8፤10-11) ተመሳሳይ ነበር። ኢየሩሳሌም ከወደቀችበት ጊዜ አንሥቶ የእግዚአብሔር ክብር በኢየሩሳሌምም ሆነ በሕዝቡ መካከል አልነበረም። እስራኤል በቅጣት በባቢሎናውያን ሥር ነበረች፤ እንዲሁም እስከ መጨረሻው ዘመን ድረስ በቅጣት ትኖራለች። ከዚያም በመሲሑ ነጽታ በተሰፋዩቱ ምድር መልሳ ትቋቋማለች። የእግዚአብሔር ክብር የዘሩባቤልን ቤተ መቅደስም ሆነ የሄሮድስን ቤተ መቅደስ አይሞላም (ሐጌ 2፥7 ጋር ያነጻ)።

የሕዝቅኤል መልእክቶችና ራእዮች ተቀባዮች ያለጥርጥር በዚህ ራእይ ይጽናናሉ። ይህ ራእይ ግልጽ የሚያደርግልን የእግዚአብሔር ክብር የሚመለሰው እስራኤል ከነጻች በኋላና በምዕራፍ 40-42 በተጠቀሰው መለኮታዊ ንድፍ መሠረት የሺህ ዘመን ቤተ መቅደስ ከተሠራ በኋላ ነው። የእግዚአብሔር ክብር በሞላችው ጊዜ እንደ ሆነው ማደሪያው በተመረቀና (ዘፀ 40፥34-35) የሰሎሞን ቤተ መቅደስ በተመረቀ ጊዜ (1ነገ 8፥10-11፤ 2ዜና 5:13-14፤ 7፥1-3) እንደ ነበረው ዐይነት ይሆናል። እግዚአብሔር ለእስራኤል ያቀደው ምንኛ የከበረና አስደናቂ ታላቅ ነገር ነው! ሕዝቅኤል ከምሥራቅ በምሥራቅ በር በኩል አስደናቂው የእግዚአብሔር ክብር ሲመጣና ሙሉ በሙሉም ቤተ መቅደሱን ሲሞላው አየ። ምድሪቱንም በአጠቃላይ በእግዚአብሔር ክብር እንድታበራ አደረጋት። የአመጣጡ ድምፅ እንዳ ባሕር ሞገድ ድምፅ ሲሆን፣ ሕዝቅኤል ቀደም ሲል በነበረው ራእይ የእግዚአብሔር ክብር ሲመጣ ከኪሩቤል ክንፍ ድምፅ (ከ1፥24 ጋር ያነጻ) ጋር ተመሳሳይ ነበር። በርግጥ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ለማደር ተመልሶ መጥቷል!

6-12 የዚህ የእግዚአብሔር ክብር ራእይ አስፈላጊነት እጅግ ጠቃሚ በመሆኑ እግዚአብሔር ራሱ ራእዩን ለሕዝቅኤል ተረጐመለት። ቤተ መቅደሱ በእስራኤል መካከል ለዘላለም የእግዚአብሔር ዙፋንና ማደሪያ ይሆናል። በምዕራፍ 33-37 የተጠቀሱት የተስፋ ቃሎች የሚፈጸሙት የእግዚአብሔር ክብር ሲመለስ ነው። የእግዚአብሔር ክብር ቤተ መቅደሱን ይሞላል፤ የእግዚአብሔር ቅድስናም በአጠቃላይ በቤተ መቅደሱ ሕንጻ ይስፋፋል። ይህም በበኩሉ ለሁለቱም ማለትም በሕዝቅኤል ዘመን ለነበሩትና በመሲሓዊው ዘመን ለሚኖሩት ለእስራኤል ቤት ትምህርት ሰጪ ይሆናል። በዚያ ዘመን እስራኤል በቤተ መቅደሱ ቅጽር ግቢ በምትፈጽመው ሃይማኖታዊ ምንዝርናና (ከ2ነገ 23፥7 ጋር ያነጻ) በኰረብታማ ስፍራዎችም የነጋሥታትዋን ሬሳ በምትቀብርበት ሁኔታ እንደ ገና የእግዚአብሔርን ቅዱስ ስም አታረክስም (ከ39፥7 ጋር ያነጻ)። ስለዚህ እግዚአብሔር በሕዝቅኤል ዘመን የነበሩትን እስራኤላውያንን ለማበረታታት እነዚህንም የረከሱ ልምምዶች እንዲያስወግዱ ለመምከር ይህን ራእይ ተጠቀመበት።

በሕዝቅኤል ዘመን የነበሩት ሰዎች ይህን ራእይ ሲሰሙና የእግዚአብሔር ክብር መመለሱን የሚያበሥረው የዐዲሱን ቤተ መቅደስ ንድፍ ሲመለከቱ ስለ ኀጢአታቸው ያፍራሉ። ልክ እንደዚሁ የሺሁ ዘመን እስራኤል የእግዚአብሔርን ክብር ቅድስናና የዐዲሱን ቤተ መቅደስ ንድፍ ፍጹምነት ካለፈው ከእስራኤል አለመታመንና ርኩሰት አንጻር ስታስተውል ስላለፈው ኀጢአቷ በራእዩ ሁሉ ታፍራለች። የራእዩ ትርጓሜ እግዚአብሔር እስራኤልን ያዘዘው የእግዚአብሔር ክብር በሙላት ይመጣ ዘንድ የሺህ ዘመኑን ቤተ መቅደስ ሕንጻ አሠራር ዝርዝር ንድፍ በጥንቃቄ እንድትከታተል ነው።

ለቤተ መቅደሱ አካባቢ የነበረው አንድ መሠረታዊ ሕግ ብቻ ነበር፤ ይኸውም በአጠቃላይ የቤተ መቅደሱ ተራራ አካባቢ ቅዱስ እንዲሆን ነው። አጽንዖት የተደረገበት ጉዳይ የእግዚአብሔር ቅድስና እንዲሁም የአገዛዙ ቦታና መኖሪያ ነው። በሺሁ ዘመን አጽንዖት የሚደረግበት ቅድስና ነው። የአምልኮ መዋቅሮችና መመሪያዎች ሁሉ የሚገልጹት የእግዚአብሔርን ቅድስና ነው። ቀጣይ የሆነ ንጽጽር የሚታየው በተቀደሰውና በረከሰው መካከል ነው። መሲሑ አለመቀደስን በብረት ዘንግ ይቀጣል (ከመዝ 2፥8-9፤ ከራእ 2፥27፤ 12:5፤ 19፥15 ጋር ያነጻ)።

ሐ. የቤተ መቅደሱ ሕጎች (43፥13 - 46፥24)

(1) የመሥዋዕቱ መሠዊያ፡- ዝርዝር ሁኔታውና መቀደሱ (43፥13-27)

13-17 የመሥዋዕቱ መሠዊያ መሠረታዊ ንድፍ ግልጽ ነው (ሥዕላዊ ማስረጃ 4 ይመ)። በውስጠኛው አደባባይ ከማደሪያው ፊት ለፊት እንዲቀመጥ ተደርጓል (በሥዕላዊ ማስረጃ 2 ዘቤ ይመ)። መሠዊያው ከታች ወደ ላይ በዝርዝር ተገልጾአል። የታችኛው የመሠዊያ ክፍል (በሥዕላዊ ማስረጃ 4 ጥ ይመ) ከመሠረቱ አንድ ክንድ ከፍታና አንድ ክንድ ወርድ ያለው በዙሪያው ቦይ ያለው ነው። የቦዩ ዕርከን አንድ ስንዝር ያህል ነው (በግምት ዘጠኝ ኢንች ያህል)። በዚህ መሠረት ጫፍ ላይ የመሠዊያው ሦስት ክፍሎች ነበሩ። ከዚህ መሠረት አጠገብ ሁለት ክንድ ከፍታ ያላቸው ክፍሎች አሉ (ው)፤ ዐሥራ ስድስት ክንድ ባለ አራት ማእዘን በአንድ ክንድ ዕርከን የታቀፉ ናቸው። ይህ ዕርከን አንድ ክንድ ወርድና ግማሽ ክንድ ከፍታ ጠርዝ ያለው ቦይ ነው። መካከለኛው ክፍል (ዕ) አራት ክንድ ቁመትና ዐሥራ አራት ክንድ እኩል በእኩል የሆነ ሲሆን፣ አንድ

ክንድ ወርድ ያለው ጠርዝ ዙሪያውን አለ። ምድጃው (ም) ማለትም አራት ክንድ ቁመትና ዐሥራ ሁለት ክንድ አኩል በአኩል ስፋት ያለው የመሠዊያው ላይኛ ክፍል ነው። በእያንዳንዱ አራት ማእዘን አንድ ቀንድ (ቀ) ወጣ ወጣ ብሎአል። የመወጣጫዎቹ ልክ ባይገለጽም ከምሥራቅ ጉን ወደ ጫፍ የሚያወጡ ደረጃዎች (ደረ) አሉ። እነዚህ ደረጃዎች በሙሴ ሥርዐት ወደ መሠዊያው እንዳይወጣባቸው ከተከለከሉት (ዘፀ 20፥24-26) በተቃራኒ የተገለጹ የመሥዋዕት መሠዊያ ናቸው። ይህ የሺሁ ዘመን መሠዊያ ትልቅ ነው፤ በግምት ከመሠረቱ ሠላሳ አንድ ተኩል ጫማ ስፋትና ዐሥራ ዘጠኝ ከሩብ ጫማ ከፍታ ያለው ነው!

18-27 የመሥዋዕቱ መሠዊያ ከተሠራ በኋላ ማንጻትና መቀደስ አስፈላጊ ይሆናል። ማንጻት ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም በኀጢአት ተካፋይነት ካለው ከማንኛውም የሰው ልጅ ሁኔታ ጋር ከተያያዙ ነገሮች መንጻት ይኖርበታል በተለይ ደግሞ እግዚአብሔርን ለማምለክ የምንጠቀምበት ከሆነ። ተመሳሳይ የሆነ ማንጻትና መቀደስ በማደሪያው በነበረው የመሥዋዕት መሠዊያና (ዘፀ 29፥36-37፤ ዘሌ 8፥14-17) በሰሎሞን ቤተ መቅደስ መሠዊያ (2ዜና 7፥9) ላይ ተደርጎአል።

መሠዊያውን የማንጻትና የማስተስረይ ሥርዐት ሰባት ቀን ወስዶአል። በመጀመሪያው ቀን የሳዶቅ ልጆች በሆኑት ካህናት የወይፈን ልዩ የኀጢአት መሥዋዕት ቀርቦ ነበር። ከመሥዋዕቱ ደም በመውሰድ መሠዊያው ላይ ባሉት አራት ቀንዶች፣ በላይኛው ዕርከን አራት ጕኖች፣ በጠርዙ ዙሪያ ላይ ሁሉ መርጨት ነበረባቸው። ይህ የኀጢአት ወይም የመንጻት ቁርባን መሠዊያውን ከኀጢአት ያነጻዋል፤ ስለዚህም ለመሠዊያው ስርየት ይደረግለታል። በዚህ ስፍራ የስርየት ሐሳብ መጥረግ ወይም ማንጻት ሲሆን፣ ከዚያም መሠዊያው ይቀደሳል (ከዘሌ 8፥14-15 ጋር ያነጻ)። የቀረው የኀጢአት መሥዋዕት ከቤተ መቅደሱ የተወሰነ ርቀት ባለው ስፍራ ላይ ይቃጠላል (ከ42፥20 ጋር ያነጻ)፤ ይህም የሚፈጸመው ከማደሪያው ራቅ ያለ ስፍራ ላይ ይሆናል (ዘሌ 8፥17)።

በሁለተኛውና በቀጣዮቹ ዐምስት ቀናት መሠዊያውን በቀጣይነት ለማንጻት ካህናቱ እንከን የሌለበትን ተባዕት ፍየል ለኀጢአት መሥዋዕት ያቀርባሉ። ከዚህ የማንጻት ሥርዐት የመሠዊያውን መቀደስ ለማሳየት ካህናቱ እንከን የሌለባቸውን ወይፈንና አውራ በግ ይሠዋሉ፤ በእግዚአብሔር ፊት የሚቃጠል መሥዋዕት እንዲሆን ጨው መሥዋዕቱ ላይ ይረጫሉ። ለተጠቀሱት ሰባት ቀናት በየዕለቱ በሚቀርቡት በእነዚህ መሥዋዕቶች መሠዊያው ማስተስረያ ይደረግለታል፤ ይነጻልም (ከዘፀ 29፥36-37 ጋር ያነጻ)።

ከሰባቱ ቀን የማንጻት ሥርዐትና የመሠዊያው መሥዋዕቶች መቀደስ በኋላ፣ ካህናቱ ስለ ሕዝቡ የሚቃጠል መሥዋዕትና የኅብረት መሥዋዕት ማቅረብ ይጀምራሉ። መሠዊያውን በሚገባ ስለ ቀደሱት እግዚአብሔር የሚቀበለው መሥዋዕታቸውን ብቻ ሳይሆን አምላኪዎቹንም ጭምር ነው። እንዴት የሚያስደንቅ እውነት ነው! ከመሲሑ መሥዋዕት የተነሣ፣ የሚያምኑ ሁሉ ተቀባይነት አላቸው!

2. የምሥራቁ በር መመሪያዎች (44፥1-3)

1-2 የውጪው የምሥራቅ በር (ከ40፥6-16 ጋር ያነጻ) በቋሚነት ተዘግቶ ይቁያል። ይህ የሚደረገው በሩ በተለይ የተቀደሰ በመሆኑ ነው፤ ጌታ በሺሁ ዘመን በክብሩ የገባው በዚህ በር ነውና (ከ43፥1-4 ጋር ያነጻ)።

3 "ገዥ" ብቻ በዚህ በር እንዲገባ ተፈቅዶለታል። በውጪው አደባባይ በረንዳ ብቻ መግባትም መውጣትም አለበት። በዚያ በር የሚገባበት ምክንያት በጌታ ፊት እንጀራ ለመብላት ነው፤ ይሁን እንጂ ምን ዐይነት እንጀራ ወይም በምን ምክንያት እንደ ሆነ አልተገለጸም።

የዚህ "ገዥ" ማንነት እንቆቅልሽ ነው። የእንግሊዝኛው ቃል "ገዥ" ለሚለው "ልዑል" ሲሆን፣ የንጉሣውያን ቤተ ሰብ መሆንን ያመለክታል። ነገር ግን የዕብራይስጡ ቃል "መሪ" በሚል ተተርጕሞአል። ይህ ገዥ መሲሑ አይደለም፣ ምክንያቱም የኀጢአት መሥዋዕት ለራሱ በማቅረቡ ነው (ከ45፥22 ጋር ያነጻ)፤ እንዲህ ዐይነቱ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አይሆንም (ከዕብ 4፥15 ጋር ያነጻ)። በተጨማሪም ይህ መሪ የሚወልዳቸው ልጆች ይኖሩታል (46፥16)፤ ይህ ደግሞ መሲሑን በተመለከተ ፈጽሞ የማይሆን ነው። እንግዲያውስ ገዥ ሰው ነው፤ ማንነቱ ግን አልተገለጸም። የእርሱ ሥራ በሺሁ ዘመን አምልኮ ልክ እንደ ሊቀ ካህናት የሕዝቡ መሪ መሆን ነው፤ ሆኖም ተመሳሳይ ኀላፊነትንና ሥራን የሚመለከት አይደለም።

5. ካህናቱና የቤተ መቅደሱ አገልግሎት (44፥4-16)

4-5 የዚህ ራእይ ትኩረት የእግዚአብሔር ክብርና በሺሁ ዘመን አምልኮ ሊኖር በሚባው ቅድስና ላይ ነው። ሕዝቅኤል የመጣው የእግዚአብሔር ክብር ቤተ መቅደሱን ሲሞላው እንዲያየ ሲሆን፣ ልክ እንደተመለከተም የሰጠው ምላሽ አክብሮት፣ ፍርሀትና በግንባሩ ተደፍቶ መስገድ ነበር። እግዚአብሔር ያለጥርጥር ይህን ክሥተት በመጠቀም እንደ ገና ሕዝቅኤልን በማስገረም የቅድስናን አስፈላጊነት አስተማረው፤ የካህናቱን ባሕርይና አገልግሎት ቅድስና ሊወርሰው ይገባል።


ካህናቱ የቀረውን ሕዝብ በቅድስና ያስተምራሉ፤ በሕይወታቸው፣ በክህነት አገልግሎታቸውና በቃላቸው ቅድስናን ያስተምራሉ። ከዚህም የተነሣ ሕዝቅኤል የቤተ መቅደሱን ሥርዐት በተለይም መግቢያውንና መውጪያውን በተመለከተ በጥንቃቄ እንዲያይና እንዲሰማ በጥብቅ ተመከረ። በዚያ ስፍራ ካህናት ከሕዝቡ ተራ ሕይወት ጋር እንዲሁም በቤተ መቅደሱ ውስጠኛ አደባባይና ማደሪያ ካለው ቅድስና ጋር ግንኙነት ይኖራቸዋል። በዚያም ተገኝተው ሕዝቡን ያገለግላሉ።

6-9 የጥንት ቅርብ ምሥራቅ ሃይማኖቶች በተደጋጋሚ የውጭ ምርኮኞችን ካህናትን እንዲያገዙ የቤተ መቅደስ አገልጋዮች ያደርጓቸው ነበር። በእነዚህ ቍጥሮች እግዚአብሔር እስራኤልን የገሠጸበት ምክንያት የጥንቶቹ እስራኤል እነዚህን ልምዶች በመከተላቸው ነበር። ይህ ልማድ በእስራኤል በመጀመሪያ የታየው ኢያሱ ገባያናውያንን የቤተ መቅደሱ አገልጋዮች ባደረጋቸው ጊዜ ነበር (ኢያ 9፥23:27)። እስራኤላውያን በዕዝራም ዘመን ይህንኑ ልማድ የተከተሉ የመስላል (ዕዝ 8፥20)። ይሁን እንጂ መሲያዊው ኪዳን በሥጋና በልብ ያልተገረዙ ባዕዳን ከአሮን ዘር ውጪ ከሆኑት ከሌሎች እስራኤላውያን ጭምር ካህናት ሆነው በቤተ መቅደስ ማገልገላቸውን ገልጾአል (ከዘኍ 3፥10 ጋር ያነጻ)። ምናልባት በመጀመሪያ እነዚህ ባዕዳን በሥጋም በልብም ተገርዘው በሕጉ መሠረት ወደ ቤተ መቅደስ አካባቢ ገብተው መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ተፈቅዶላቸው ሊሆን ይችላል (ከዘኍ 15፥14 ጋር ያነጻ)። በርግጥም ኢሳ 56፥3:6 በመሲሓዊውም መንግሥት ይህ ሊሆን እንደሚችል ያመለክታል (ከዘካ 14፥21 ጋር ያነጻ)። ነገር ግን እስራኤል ሙሴያዊውን ኪዳን ያፈረሱት ባዕዳን የቤተ መቅደስ አገልጋዮች ሆነው ወደ ማደሪያው እንዲገቡ ብቻ ሳይሆን፣ የቤተ መቅደሱን የሥራ ኀላፊነት እንዲቈጣጠሩ በማድረግም አስጸያፊ ሥራ ሠርተዋል። ከተቀደሱ ነገሮች ጋር በተያያዘ የክህነት ሥራዎችን በማከናወን ቤተ መቅደሱን አርክሰዋል። ነገር ግን እነዚህ ባዕዳን የክህነትን ሥራ እንዲሠሩ ፈቃድ ማግኘት አልነበረባቸውም።

ሙሴያዊው ኪዳን ለሁሉም ጥሪ የሚያቀርበው በልባቸው እንዲገረዙና በተጨማሪም የአብራሃማዊው ኪዳን ምልክት የሆነውን በሥጋቸውም እንዲገረዙ ነው (ከዘሌ 26፥41፤ ከዘዳ 10፥16፤ 30፥6፤ ከኤር 4፥4፤ 9፥25 ጋር ያነጻ)። በእርሱ ፊትና በመንገዶቹ በተለወጠ ልብ መመላለስን፣ የልባቸውን ሸለፈት ጥንካሬ በእውነት መገረዝን ይጠይቃቸው ነበር። በሚገባ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ማድረግ ከፈለጉ ይህ ለእስራኤላውያንም ሆነ ለባዕዳን አስፈላጊ ነበር። ስለዚህ ግልጽ የሆነ ትእዛዝ ተሰጥቶአል፦ በእስራኤል መካከል እንኳ ቢኖሩ ልባቸውና ሥጋቸው ካልተገረዘ በቀር ማናቸውም ባዕዳን ቤተ መቅደስ መግባት አይችሉም። ይሁን እንጂ ትርጓሜው እንደ ማንኛውም ሰው የልቡንና የሥጋውን ሸለፈት የተገረዘ ባዕድ ወደ ቤተ መቅደስ ሊገባ መቻሉን ነው፤ ነገር ግን በምንም መንገድ ካህን ሆኖ ሊያገለግል አይችልም።

ሥዕላዊ ማስረጃ 4

የመሥዋዕቱ መሠዊያ



ም የመሠዊያው ምድጃ (43፥15-16)

ዕ ዕርከን (43፥14:17)

ው ውስጥ (43፥14:17)

ጥ ጥልቀት (43፥13)

መሥዋ የመሠዊያው ቀንዶች (43፥20)

ደረ ደረጃዎች (43፥17ለይመ፤ ከ40፥47፤ ጋር ያነጻ)

10-14 ጌታ አሁን ግልጽ የሚያደርገው በሺህ ዘመን ቤተ መቅደስ ማን ማገልገል እንደሚችልና በምን ሁኔታ ማገልገል እንደሚገባ ነው። ሌዋውያን የሚቃጠል መሥዋዕቱንና ለሕዝቡ ሌሎች መሥዋዕቶች የሚያርዱባቸው፣ ሕዝቡንም በአምልኮአቸው የሚያግዙባቸው የቤተ መቅደሱ በሮች ጎላፊዎች ይሆናሉ። በተጨማሪም በቤተ መቅደስ ውስጥ ለሚሠራው ሥራ ሁሉ ጎላፊዎች ናቸው፤ ምናልባትም እነዚህ ተግባራት ቀደም ብሎ በባዕዳን ሲሠሩ የነበሩት ናቸው።

ሌዋውያን በሚያገለግሉት አገልግሎት ገደብ ተደርጎ ነበር። ልክ እንደ ካህናት ለማገልገል አልተፈቀደላቸውም፤ ወይም ወደ እግዚአብሔር የተቀደሰ ነገር በተለይም ወደ ተቀደሱ መሥዋዕቶች መቅረብ አይፈቀድላቸውም። በውስጠኛው አደባባይም ሆነ በመቅደሱ ውስጥ አያገለግሉም። ይህን እንዳያደርጉ ገደብ የተደረገበት ምክንያት ግልጽ ነው። ባለፈው ዘመን በቡድን ከእግዚአብሔር ዘወር ብለዋል፤ ጣዖት አምልኮንም ተከትለዋል። ይህን በማድረግም ሕዝቡን ወደ ኀጢአት መርተዋል (ከምዕ 8 ጋር ያነጻ)። በዘኍ 18፥23 ላይ ማስጠንቀቂያ በተሰጣቸው መሠረትም ስላለፈው መተላለፋቸው ተጠያቂዎች ናቸው። የኀጢአትን ውጤትና ውርደት መሸከም ይኖርባቸዋል።

15-16 ይህ በ1ሳሙ 2፥35 አስቀድሞ ቢነገርም የሳዶቅ ዘሮች በዋነኛው የክህነት ሥራ የተመደቡት በሰሎሞን ዘመን ነበር (1ነገ 2፥26-35)። የቀረው እስራኤል በሙሉ ከእግዚአብሔር ዘወር ሲል እነርሱ ብቻ በታማኝነት በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ ሥራውን ሲሠሩ ኖረዋል። ከዚህ ታማኝነታቸውም የተነሣ፣ እግዚአብሔር በሺሁ ዘመን ማደሪያ ለእነርሱ ብቻ የተለየ በእርሱ ፊት የሆነ አገልግሎት ይሰጣቸዋል። እነርሱ ብቻ መሥዋዕቶችን ለማቅረብ በእግዚአብሔር ፊት ይቆማሉ። እነርሱ ብቻ ወደ ቤተ መቅደሱ ለመግባት እንዲሁም በአምልኮ አገልግሎትን ለመፈጸም ወደ ጌታ ገበታ (ምን ዐይነት "ገበታ" እንደ ሆነ አይታወቅም) ለመቅረብ ይፈቀድላቸዋል። ምዕራፍ 45 እና 46 የሳዶቅ ዘሮች ለሕዝቡና ለገዢው መሥዋዕትን በየዕለቱ፣ በየሰንበታቱ እንዲሁም በተወሰኑት በዓላት መሥዋዕቶችን እንደሚያቀርቡ ያመለክታሉ። ባለፉት ዘመናት ለእግዚአብሔር ሕገጋት ታማኞች ከመሆናቸው የተነሣ እንዴት ያለ ታላቅ ዕድልና በረከት ይሆንላቸዋል!

4. ለሳዶቅ ልጆች የክህነት አገልግሎት የተሰጡ ሕጎች (44፥17-31)

17-19 በቀረው በዚህ ምዕራፍ ክፍል ለካህናቱ ለሳዶቅ ልጆች አያሌ መመሪያዎችና ሥራዎች በጉልሕ ተመልክተዋል። ሲያገለግሉ የሚለብሱት ልብስ የአገልግሎታቸውን ቅድስና ያመለክታል። ሲያገለግሉ ወደ ውስጠኛው አደባባይ ሲገቡ እነዚህ ካህናት ነጭ የሐር ፈትል መልበስ አለባቸው (ከዘፀ 28፥42፤ ከዘሌ 16፥4 ጋር ያነጻ)። ይህ የሐር ፈትል በነጭነቱ ንጽሕናን ብቻ አይገልጥም፤ ነገር ግን ስስ መሆኑ ካህናቱን ከላብና ከእድፍ ይጠብቃቸዋል። ከውጭ ከሚለብሱት ከዚህ ከሐር ልብስ በተጨማሪ ካህናቱ ከሐር የተሠራ የውስጥ ልብስና በራሳቸውም ላይ ጥምጥም ያደርጋሉ።

ካህናቱ ከውስጠኛው አደባባይ ወጥተው ከሕዝቡ ጋር ሲቀላቀሉ፣ የሐር ልብሳቸውን በተወሰነለት የተቀደሰ ክፍል አውልቀው በማስቀመጥ (42፥1-14) ልብሳቸውን መቀየር ይጠበቅባቸዋል (ከዘሌ 6፥11 ጋር ያነጻ)። በዚህ መንገድ በማይገባ ሁኔታ በአገልግሎት ልብሳቸው ሕዝቡን መቀደስ ፈጽሞ አይችሉም። ከተቀደሰ ነገር ጋር መነካካት ይቀድሳል። አንድ ሰው ወይም አንድ ዕቃ የቅድስና ሁኔታ ውስጥ የሚገባው የተቀደሰ ነገርን ሲነካ ነው፤ በመሆኑም ሌሎች የተቀደሱ ሰዎች ወይም ዕቃዎች በሚገቡበት የቅድስና ግዴታ ውስጥ ይገባል (ዘፀ 29፥37፤ 30፥29፤ ዘሌ 6፥27፤ ከ21፥1-8 ጋር ያነጻ)። የሐር ልብሱን በተቀደሱ ክፍሎች የመተው ነገር የሚያመለክተው መመሪያው በተቀደሰውና በረከሰው መካከል ሊኖር የሚገባውን ግልጽ ልዩነት ለመረዳት የሚያግዝ መሆኑን ነው።

20-22 ካህናቱ የሳዶቅ ልጆች የራሳቸውን ጠጉር መላጨት የለባቸውም ወይም ማስረዘም አይፈቀድላቸውም። በሚገባ መከርከም ይኖርበታል። ጠጉርን መላጨት አብዛኛውን ጊዜ ከጣዖት አምልኮ ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ ጠጉር ደግሞ ግንኙነትን ለመመሥረት ለአማልክት ይሠዋል። የረዘመ ጠጉር ሐዘንን ይገልጣል፤ ካህናት ጣዖት አምልኮን ወይም የጣዖት አምልኮ የሐዘን ሥርዐትን መከተል የለባቸውም (ከዘሌ 10፥6፤ 21፥5፤ 10 ጋር ያነጻ)። ይህ የጠጉር ሥርዐት በሙሴያዊው ሥርዐት የቅድስና ምልክት እንደ ሆነ ሁሉ (ዘሌ 21፥6)፣ በሺህ ዘመን ሥርዐትም እንዲሁ ነው።

በእግዚአብሔር ፊት ሲያገለግል ሳለ አንድ ካህን የወይን ጠጅ መጠጣት የለበትም (ከዘሌ 10፥9 ጋር ያነጻ)። የእግዚአብሔርን አገልግሎት ሲፈጽም ራሱን መቈጣጠር መቻሉን ማረጋገጥ አለበት። ይህ ቅድስና ነው።

የሳዶቅ ልጅ የሆነ ካህን እስራኤላዊት ድንግል ወይም የካህን ሚስት የነበረች መበለትን እንዲያገባ ተፈቅዶለታል። ይህም የጋብቻን ቅድስና ይጠብቃል። ሌላ ፈት ሴትን ማግባት አይችልም። ይህ ግዴታ በሙያዊው ሥርዐት ሊቀ ካህናቱን ብቻ የሚመለከት ቢሆንም አሁን ግን ሁሉንም ካህናት የሚመለከት ነው (ከዘሌ 21፥7፡14 ጋር ያነጻ)።

23-24 ከላይ የተጠቀሱት ደንቦች በተቀደሰው ነገር መካከልና ተራ በሆነው መካከል ያለውን ልዩነት ካህናዊ በሆነ ሕይወታቸው በማሳየት ካህናት እስራኤላውያንን እንዲያስተምሩ ያስችሉአቸዋል። በተጨማሪም እነዚህ ካህናት በማንኛውም ክርክር ዳኖች ሆነው በማገልገልና እንደ እግዚአብሔርም ትእዛዝ ውሳኔ በመስጠት ይሠራሉ። ምን ጊዜም ቢሆን የሙሴያዊው ኪዳን ምልክት የሆኑትን ማለትም የተወሰኑትን በዓላትና ሰንበታትን በተመለከተ ያሉትን የእግዚአብሔርን ሕጎችና ማንኛውንም ዐዋጅ መጠበቅ ይኖርባቸዋል።

25-27 ከመከራ ዘመን አምልጠው በተፈጥሮአዊ ሥጋቸው ወደ ሺሁ ዘመን የሚገቡ ግለሰቦች ይኖራሉ። በሺሁ ዘመን የሥጋዊ ሕይወት ዕድሜ ረዥም ቢሆንም እነዚህ በርግጥ በመጨረሻ ሥጋዊ ሞትን ይሞታሉ (ከኢሳ 65፥20 ጋር ያነጻ)። ካህን ወደ ሞተ ሰው ሬሳ ቢጠጋ ራሱን ያረክሳል፤ የሞተው የቅርብ ዘመዱ ካልሆነ በቀር ይህ ፈጽሞ የተከለከለ ነው (ዘሌ 21፥1-3)። ካህኑ የሞተውን የቅርብ ዘመዱን ሬሳ ሲንከባከብ ይረክሳል፤ በመጽሐፍ ቅዱሳዊው መመሪያ መሠረትም ራሱን ማንጻት እጅግ አስፈላጊ ይሆናል (ከዘኍ 19፥11-19 ጋር ያነጻ)፤ ለመንጻትም ሰባት ቀን መቈየት ይኖርበታል። ካህኑ ከረከሰና ከነጻ በኋላ ለማገልግል ወደ ውስጠኛው አደባባይ ሲመለስ፣ ራሱን ለማንጻት የንጒሥት መሥዋዕት ማቅረብ ይኖርበታል።

28-31 ለካህናት የሚያስፈልጋቸው ማንኛውም ነገር የሚመጣው ከእግዚአብሔር ነው። እርሱ ርስታቸውና ንብረታቸው ይሆናል። በእነዚህ ቍጥሮች ከተገለጹት በቀር ምንም ዐይነት ርስት አይሰጣቸውም። ለካህናቱ የሚሆነው ምግብ ሕዝቡ ለመሥዋዕት ከሚያቀርበው በእግዚአብሔር ይሰጣቸዋል። ካህናቱ ከእህል ቁርባን፣ ከንጒሥት መሥዋዕትና ከበደል መሥዋዕት ይበላሉ። በእስራኤል ለእግዚአብሔር ከተሰጠው ሁሉ ከፍሬ በኵራት፣ ምርጥ ከሆነው ሁሉ፣ ከልዩ ስጦታዎች ሁሉ እንዲሁም ከምድር ከሚያገኙት እህል ሁሉ ካህናት ይካፈላሉ (ከዘኍ 18፥10-13 ጋር ያነጻ)። ለእግዚአብሔር "ከተሰጠው ሁሉ" የሚለውን በተመለከተ የዘሌ 27፥1-34፤ እንዲሁም የቍ 28፣ የዘኍ 18፥14 ማብራሪያ ይመ)። ካህናት ሞቶ የተገኘን ወይም በዱር አራዊት የተዘነጠለ ማንኛውንም ነገር እንዲበሉ አልተፈቀደላቸውም (ከዘሌ 17፥5፤ 22፥8፤ ከዘዳ 14፥21 ጋር ያነጻ)። እስራኤላውያን በዚህ መንገድ በታማኝነት ለካህናት በመስጠታቸው እንደሚባረኩ ቃል ተገብቶላቸዋል። ለእግዚአብሔር በመስጠት ምንጊዜም በረከት አለ።

5. የቅድስቲቱ ምድር የተቀደሰው ስፍራ (45፥1-8)

1-8 በሺሁ ዘመን ከእስራኤል ምድር የተወሰነው ለካህናቱና ለማደሪያው ተለይቶ የተቀደሰ ስፍራ ይሆናል። ስፍራው ሙሉ በሙሉ እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር አስተዋፅኦ የሚያደርጉት (የለዩት) ምድር ነው። መሬት የካህናቱ ሳይሆን፣ በርግጥ የእግዚአብሔር ነው። በዚህም አንጻር ቢሆን እግዚአብሔር የካህናቱ ርስት ይሆናል።

እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር የለዩት ይህ የተቀደሰ ምድር ሃያ ዐምስት ሺህ ዘንግ በሃያ ሺህ ዘንግ ነው። ዐመት የተባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒም በቋሚነት መለኪያ አድርጎ የተጠቀመው "ዘንግን" ሳይሆን "ክንድን" ነው (በ42፥15-20 ያለውን ማብራሪያ ይመ)። በርግጥ በዚህ ክፍል ስለ መለኪያ የተነገረ ቃል የለም፤ ይኸውም "ዘንግ" መለኪያ መሆኑ በ42፥15-20 በመሰጠቱ ነው። በዚህ ስፍራ መገመት የምንችለው ሕዝቅኤል መለኪያ አድርጎ የተጠቀመው ዐምሳ ክንድ ወርድ ያለው ሰፊ ቦታ በዐምስት መቶ እኩል በእኩል ዘንግ በሆነው በማደሪያው ዙሪያ ያለውን ስፍራ እንደ ሆነ ነው።

ይህ ሃያ ዐምስት ሺህ ዘንግ በሃያ ሺህ ዘንግ ስፋት ያለው ስፍራ በሁለት እኩል ቦታዎች ተከፍሎአል፤ ይኸውም አንዱ ሃያ ዐምስት ሺህ ዘንግ በዐሥር ሺህ ዘንግ ነው። አንዱ የተቀደሰው ክፍል በቤተ መቅደሱ ውስጥ እግዚአብሔርን ለሚያገለግሉት ለካህናቱ የሳዶቅ ልጆች የተለየ የተቀደሰ ክፍል ነው (ከ44፥15-16፣ 48፥9-12 ጋር ያነጻ)። በዚህ ስፍራ ቤታቸውን ይሠራሉ። በዚህ ስፍራ መካከል ላይ ዐምስት መቶ ዘንግ እኩል በእኩል ስፍራ ለማደሪያው ወይም ለቅድስተ ቅዱሳን የተለየ ነው። ይህ ዐምስት መቶ ዘንግ እኩል በእኩል ስፍራ ዐምሳ ክንድ ስፋት ያለው ዙሪያውን ክፍት የሆነ ድንበር ይኖረዋል፤ ይህም ከሌላው የሚለየው መከላከያ ነው። እርሱም የማደሪያው አካባቢ የቱን ያህል የተቀደሰ እንደ ሆነ ያመለክታል።

ሌላው ሃያ ዐምስት ሺህ ዘንግ በዐሥር ሺህ ዘንግ የሆነው ስፍራ በቤተ መቅደስ ውስጥ ካህናቱን የሳዶቅ ልጆችን ለሚረዱ ለሌዋውያን የተለየ ስፍራ ነው (ከ44፥10-14፤ 48፥13-14 ጋር ያነጻ)። ስፍራውን ከተሞቻቸውን ለመመሥረት ይጠቀሙበታል። ይህ ስፍራ ለካህናቱ ለሳዶቅ ልጆች ከተለየው ጋር ትይዩ ሲሆን፣ ወደ ሰሜን ያቀና ነው (ከ48፥8፡21 ጋር ያነጻ)።

በሌላ አቅጣጫ ለካህናቱ ለሳዶቅ ልጆች ከተሰጠው ደቡቡን ከሚያገናኘው ጋር ያለው ስፍራ ሃያ ዐምስት ሺህ ዘንግ በዐምስት ሺህ ዘንግ የሆነው ለከተማዪቱ የተሰጠ ነው (ከ48፥15-19፡ 30-35 ጋር ያነጻ)። ስም ባይጠቀስም ይህች ከተማ ኢየሩሳሌም ሳትሆን አትቀርም። ከተማዪቱ በአጠቃላይ ለእስራኤል ቤት የተሰጠች ናት።

በመጨረሻም "ለገሯ" የተሰጠ ምድር አለ (የ44፥3 ማብ ይመ)። የእርሱ ርስት ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ያለውን የተቀደሰ ስፍራ የያዘ ሲሆን፣ የሌዋውያንን የካህናቱን የሳዶቅ ልጆችንና የከተማዪቱን ድርሻ የሚያካትት ነው (ከ48፥21-22 ጋር ያነጻ)። ከይሁዳና ከብንያም ነገድ ድንበር በትይዩ የተቀመጠ ነው።

ሕዝቅኤል ይህን ክፍል የሚያጠቃልለው የእስራኤል የሺሁ ዘመን መሪዎች ያለፉት መሪዎች እንዲደረጉት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ፈጽመው እንደማይጨቍኑ በመናገር ነው (ከ11፥1-13፤ 14፥1-11፤ 20፥1-23፥49፤ 34፥1-10 ጋር ያነጻ)። ምንም ዐይነት የውርስ መከራ ሳያደርጉ እንደየነገዱ ለሕዝቡ ርስቱን በማከፋፈል እንዲኖር ይፈቅዱለታል (48፥1-29 ጋር ያነጻ) ።

6. የሺሁ ዘመን ገዥ ኀላፊነት (45፥9-46፥18)

9-12 ያለፈው ክፍል ማጠቃለያ ቍጥር በሕዝቅኤል ዘመንና ባለፈው የእስራኤል ታሪክ የነበሩ መሪዎች የራሳቸው ያልሆነውን ንብረት ይዘው እንደ ነበር ያመለክታል (ከ46፥18 ጋር ያነጻ)። ስለዚህ ሕዝቅኤል በራሱ ዘመን የነበሩትን ገዢዎች (መሪዎች) ትክክለኛ ያልሆነና ተገቢ ያልነበረ ሚዛን በመጠቀም ሕዝቡን መጨቈንና በዐመፅ መምራት እንደሌለባቸው ይመክራል። እንዲህ ዐይነቱ ጽድቅ የሌለበት አስተዳደር በሕዝቅኤል ዘመን መቆም ነበረበት። በመሲሑ መንግሥት ፈጽሞ አይኖርም።

ተገቢ የሆኑ የሚዛን መለኪያዎች ተሰጥተዋል። የጥንት የቅርብ ምሥራቅ የርዝመት መለኪያዎች የዛሬውን መለኪያዎች ያህል ትክክል እንዳልሆኑ ሁሉ፣ የፈሳሽ መለኪያዎንም በተመለከተ እንዲሁ ነው። ሕዝቅኤል በራሱ ዘመን የነበረውን የፈሳሽ መለኪያ በተገቢው መለኪያ ለማስተካከል ሞክሮአል። ኢፍ (በግምት አንድ ቡሼል) የደረቅ ነገር መስፈሪያ ሲሆን፣ የፈሳሽ ነገር መለኪያ ከሆነው ከባዶስ (በግምት ዘጠኝ ጋሎን) ጋር እኩል ነው። ሁለቱም የሆመር (በግምት ዘጠና ጋሎን ወይም ዐሥራ አንድ ቡሽልስ) አንድ ዐሥረኛ ያህል ሲሆኑ፣ ሆመር የፈሳሽ ነገር ቋሚ መለኪያ ነው። ከዚህ መሠረታዊ መለኪያ አንጻር ሕዝቅኤል በዘመኑ የነበሩ ሰዎች ሚዛናቸው ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለባቸው ይመክራቸዋል።

ልክ እንደዚሁ ሕዝቅኤል የክብደት መመዘኛውን ትክክለኛ መለኪያ ይገልጻል። አንድ ሰቅል (በግምት ዐሥራ አንድ ግራም) ሃያ ጌራ (በግምት ዐምስት ግራም) ያህል ነው። ስድስት ሰቅል (በግምት ስድስት መቶ ሰባ ሁለት ግራም) ያህል ነው። የሕዝቡ መሪዎች በሥራ አፈጻጸማቸው ሁሉ ትክክል መሆናቸው አስፈላጊ ነበር።

13-17 ካለፉት ከእስራኤል መሪዎች ቅዱስ ያልሆነ ባሕርይ ጋር፣ የእስራኤል የሺህ ዘመን ገዥ ሲነጻጸር፣ ለእግዚአብሔር የጽድቅ መመሪያዎች ታማኝ መሆኑን እንረዳለን (የ44፥3 ማብራሪያ ይመ)። ከኀላፊነቶቹ አንዱ ለሕዝቡ ስርየት ማድረግ ይሆናል።

"ስርየት" የሚለው ቃል ብዙ ትርጒሞችን ያዘለ ቃል ነው። ብዙዎች ይህን ነገረ መለኮታዊ ቃል የሚያዩት በአንድ ግለሰብ ወይም በሕዝብ ኀጢአት ላይ ያለ ቍጣ መብረድን በተመለከተ ነው። እንዲህ ዐይነቱ በሙሴያዊው ሥርዐት ይደረግ የነበረውን የስርየት ቀን በተመለከተ ልንማርበት የምንችልበት ሥዕላዊ ትምህርት ነው (ከዘሌ 16 ጋር ያነጻ)። በተለይ ለነገሮች ሲደረግ፣ የስርየት ፅንሰ ሐሳብ በመንጻት ላይ እንደሚያተኩር ተስተውሎም ነበር። በየትኛውም መንገድ ይሁን በእነዚህ ምዕራፎች ላይ የተገለጹት የሙሴያዊ አሠራርና የሺሁ ዘመን አሠራር ሥርዐቶች፣ የሰው ዘሮች ሁሉ ሙሉ በሙሉ ከኀጢአት መንጻትና ፍጹም በሆነው የመሲሑ የኢየሱስ

ክርስቶስ የስርየት መሥዋዕት እንደሚያስፈልጋቸው የሚያመለክቱ ሥዕላውያን ትምህርቶች ነበሩ። ሙሉውና ፈጹም የሆነው የኀጢአት ይቅርታ የሚገኘው ለአንዱና ለመጨረሻ ጊዜ በፈሰሰው በክርስቶስ ደም ነው።

እስራኤላውያን ማደሪያውን ለመሥራት ልዩ ልዩ የቍሳቍስ ስጦታዎችን አድርገዋል (ከዘፀ 25፥2-7፤ 35፥5፡21፡24፤ 36፥3፡6 ጋር ያነጻ)። በተመሳሳይ ሁኔታ እስራኤል በመሲሓዊው መንግሥት ለገዢው ልዩ የእህል፣ የዘይትና የበግ ስጦታ ያደርጋሉ፤ እርሱም በምላሹ ለእነርሱ ያስተሰርይላቸዋል (ከዘፀ 30፥13-15፤ ከዘሌ 1፥4 ጋር ያነጻ)። የእያንዳንዱ እስራኤላዊ ስጦታ እንደሚከተለው ነው። ከተሰበሰበው ስንዴ ወይም ገብስ ከእያንዳንዱ ሆመር (በግምት ዐሥራ አንድ ቡሽልስ) አንድ ስድስተኛ ኢፍ (በግምት አንድ ስድስተኛ ቡሽል)፣ እያንዳንዱ ከሚኖረው ከአንድ ኮር (ወይም ፈሳሽ ሆመር በግምት ዘጠና ጋሎኖች) አንድ ዐሥረኛ ባዶስ (አንድ ጋሎን)፣ ውሃ ከጠገበው ከእስራኤል ማሰማርያ ከተገኙት ከእያንዳንዱ ሁለት መቶ መንጋ አንድ በግ።

ከእነዚህ ከተሰበሰቡ ስጦታዎች ገዢው ሕዝቡን ለማስተስረይ የእህል ቍርባን፣ የሚቃጠል መሥዋዕትና የኀብረት መሥዋዕት ያቀርባል (ከዘሌ 9፥7፤ 10፥17 ጋር ያነጻ)። የቍ 15 አጠቃላይ አረፍተ ነገር በቍ 17 ላይ በግልጽ ቀርቦአል። ገዢው በእያንዳንዱ የእስራኤል በዓል፣ በወር መባቻ በዐላቷና በሰንበታቷ ለእስራኤል ስርየት ለማድረግ የሚቃጠል መሥዋዕት፣ የእህል ቍርባን መሥዋዕት፣ የኀብረት መሥዋዕትና፣ የኀጢአት መሥዋዕት የመጠጥ መሥዋዕት ያቀርባል። እነዚህ የስርየት ሥርዐቶች ክርስቶስ ራሱን ለኀጢአት መሥዋዕት በማድረግ ለሠራው ሙሉና ያለቀ የማዳን ሥራ መታሰቢያ ናቸው (በምዕራፍ 40--48 ያሉትን የመግቢያ ማብራሪያዎች ይመ)። ቢሆንም እነዚህ ሥርዐቶች ፍጹም አልነበሩም። እነዚህ መሥዋዕታዊ መታሰቢያዎች በአምልኮ ውስጥ እያሉ ጌታ ለኀጢአት ስርየት ያደረገውን የምሕረት ስጦታ ሲመለከቱ ምን ዐይነት ምስጋናና አምልኮ ይሰጡ ይሆን! (ከራእ 5፥7-14 ጋር ያነጻ)።

እነዚህ የስርየት መታሰቢያ ድርጊቶች በየሳምንቱ በሚደረጉት ሰንበታት፣ በወር መባቻ በዓላት እንዲሁም በእስራኤል በተወሰኑት በዓላት የተገደቡ ነበሩ (ከዘሌ 23፥1-41፤ ከዘኍ 28፥1-29፡ 40 ጋር ያነጻ)። በሺሁ ዘመን መንግሥት የተለየ የስርየት ቀን የሚባል የለም። ያ ልዩ ቀን ሙሉ ተፈጸሚነቱን ያገኘው ክርስቶስ በመስቀል ላይ ኀጢአትን ለማዳን በፈጸመው የስርየት ሥራ ነው። ሕዝቡም በኋላ ለኀጢአት የተለዩ እንስሳትና የሚቃጠል መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ወይፈንን፣ ፍየልና አውራ በግን እንዲያቀርቡ አይጠበቅባቸውም (ከ45፥21-25፤ 46፥2-8፡ 11-12 ጋር ያነጻ)። በቂ መረጃ ባይኖርም ይህን ያህል ትልቅ ስጦታ ሊያደርግ የሚችለው እግዚአብሔር መሆኑን ለማሳየት እነዚህ ለኀጢአት ስርየትና ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚቀርቡት እንስሳት የሚመጡት ከሕዝቡ ሳይሆን ከገዢ ሳይሆን አይቀርም ከቍ 18፡ 22፤ ከ2ዜና 31፥3 ጋር ያነጻ)። በዚህ በሙሴያዊው ሥርዐት መሥዋዕቱን የሚያቀርበው ሰው የራሱን እንስሳ ለኀጢአት መሥዋዕት ሲያቀርብ፣ በኀጢአቱ ምትክ እንስሳው እንደሚሞትለት በማሰብ ነው፤ በስርየት ቀን ግን ሁሉም ሰው ሲያቀርብ የሕዝቡ ኀጢአት እንደሚሰረይ ይታሰባል። በሺሁ ዘመን ገዢው ከራሱ ወይፈኖች፣ አውራ በጎችና ተባዕት ፍየሎች እንደሚያቀርበው እግዚአብሔር ምትክ የሚሆነውን ያዘጋጃል።

18-20 በየዓመቱ የቤተ መቅደሱን ማደሪያ ማንጻት የሺሁ ዘመን ገሸር ሥራ ይሆናል። በመጀመሪያው ወር (ኒሳን) በመጀመሪያው ቀን ገዢው ምንም እንከን የሌለበትን ወይፈን የኀጢአት መሥዋዕት አድርጎ ያቀርባል (ከዘሌ 16፥16፡33፤ 22፥20 ጋር ያነጻ)። ቤተ መቅደሱን ላረከሰው ለሰው ልጅ ኀጢአት ይህን ማድረግ ተገቢ ነው። ካህናቱ የሳዶቅ ልጆች እንኳን ሰዎች ከመሆናቸው የተነሣ ኀጢአትን ሊያደርጉ ይችላሉ። ስለዚህ በየዓመቱ የእግዚአብሔርን የማደሪያውን ቅድስና ለማስታወስ የቤተ መቅደሱ ማደሪያ ስርየት ይደረግለታል፤ ወይም ይነጻል (ከ2ዜና 7፥1-10፤ 29፡ 20-24 ጋር ያነጻ)። በሥርዐቱ መሠረት ካህኑ ከተሠዋው ወይፈን ደም ወስዶ በቤተ መቅደሱ በር መቃኖች (ከ41፥21 ጋር ያነጻ - ካህናቱ የሚገቡበት)፣ በመሠዊያው ላይኛ ዕርከን አራት ማእዘኖች በውስጠኛው አደባባይ በር መቃኖች ላይ ይረጨዋል። ይህ ሥርዐት እንደ ገና በሰባተኛው ወር ላይ ይደገማል። በዚህ ሥርዐት ቤተ መቅደሱ ለሚቀጥለው ዓመት ይነጻል፤ ስለሆነም ሁሉ እግዚአብሔርን በቅድስናና በንጽሕና ሊያመልኩት ይችላሉ ማለት ነው።

21-25 ገዢው የፋሲካን በዓልና የቂጣን በዓል ይመራል። በሕዝቅኤል መጽሐፍ በተጠቀሰው የአምልኮ ሂደት እነዚህ ሁለት በዓላት በተለይ የተጠቀሱ ናቸው።

ፋሲካ (ከዘፀ 12፥1-14፤ ከዘሌ 23፥5-8፤ ከዘኍ 28፥16-25 ጋር ያነጻ) በሙሴያዊው ሥርዐት እንደሚከበረው ይከበራል። የፋሲካ ቀን የሚከበረው በመጀመሪያው ወር (ኒሳን) በዐሥራ አራተኛው ቀን ነው። ገዢው ለራሱና ለሕዝቡ የሚሆንን የኀጢአት መሥዋዕት በማቅረብ የክርስቶስ ሥራ እንዲታሰብ ያደርጋል። እርሾ የሌለበት እንጀራ የሚበላበት በዓል ለሰበት ቀን ይቀጥላል፤ በዚህ ጊዜ ማንም እርሾ ያለበትን እንጀራ መብላት አይችልም። በየዕለቱ ገዢው ለየቀኑ የሚሆኑ ምንም እንከን የሌለባቸውን ሰባት ወይፈኖችና ሰባት አውራ በጎች ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገው ያቀርባሉ። በተጨማሪም ገዢው በየቀኑ ሕዝብን በመወከል አንድ ተባዕት ፍየል የኀጢአት መሥዋዕት አድርጎ ያቀርባል (ከዘኍ 28፥19-24 ጋር ያነጻ)። ለእያንዳንዱም መሥዋዕት አንድ የኢፍ መስፈሪያ የእህል ቍርባንና አንድ የኢን መስፈሪያ ዘይት ዐብሮት ይቀርባል። እነዚህ የመሥዋዕት አቀራረብ ሂደቶች ከሙሴያዊው ሥርዐት ጋር ተመሳሳይ ናቸው።

የዳስ በዓል በሰባተኛው ወር (ቲሽሪ) በዐሥራ ዐምስተኛው ቀን ይጀምራል፤ ለሳባት ቀንም በተከታታይ ይከበራል (ከዘሌ 23፥33-43፤ ከዘኍ 29፥12-38 ጋር ያነጻ)። በፋሲካ በዓል በየዕለቱ የሚቀርቡት መሥዋዕቶች ለዳስ በዓልም እንዲቀርቡ ይደረጋል። ይህ አካባበር በቀጣይነት የሚያሳስበው እግዚአብሔር እስራኤልን በሰላምና በዘላቂነት ወደ ተስፋቱ ምድር እንደሚያስገባትና የገባውን ቃል እንደሚፈጽም ነው። በርግጥ እስራኤላውያን እግዚአብሔር ይህን በማድረጉ ያለማቋረጥ ለእርሱ ውዳሴና ምስጋና ያቀርባሉ።

46፥1-8 የሰንበትና የዐዲስ ወር መባቻ በዓል የሺሁ ዘመን አምልኮ ሥርዐት አንዱ ክፍል ይሆናል። የሙሴያው ኪዳን ምልክት የሆነው ሰንበት (ከዘፀ 31፥13፡ 16-17 ጋር ያነጻ) በዐዲስ ኪዳን በቤተ ክርስቲያን ዘመን ሳይከበር ቀርቶ በሺሁ ዘመን መንግሥት መከበሩ የማይገጣጠም ነገር ይመስላል። ይህ የእግዚአብሔርን ዐላማ ወደ ኋላ መመለስ ይሆንን? የመሲሑ መንግሥት የእግዚአብሔር ኪዳኖች በሙሉ እንደሚፈጸሙና ሥራ ላይ እንደሚውሉ ከተረዳን፣ ይህ ወደ ኋላ መመለስ አይሆንም (ከ37፥15-28 ጋር ያነጻ)። ሙሴያው ኪዳን ተፈጻሚነትን የሚያገኘው በመሲሓዊው መንግሥት ሲሆን፣ በዚህም እስራኤል በመጨረሻ የእግዚአብሔር ሕዝብ እርሱም በሙሴያዊው ኪዳን በተመሠረተው ግንኙነት አምላክዋ ይሆናል። ምሳሌያዊ የሆኑት መሥዋዕቶች በክርስቶስ ሥራ ተግባራዊ መሆናቸው ቅዱስ የሆነውን የሙሴያዊን ኪዳን ግንኙነት ዋጋ አያሳጣውም። ሙሴያዊው ኪዳን እስራኤልን የሚያስተምረው ከእግዚአብሔር ጋር ባላት ግንኙነት እንዴት ባለ ቅድስና መኖር እንዳለባት ሲሆን፣ እንዲህ ዐይነቱ ምሳሌያዊ ሕይወትም አሁንም በዐዲሱ ኪዳን የሚጠበቅ ነው (ከኤር 31፥33-34፤ ከሮሜ 8፥4 ጋር ያነጻ)። ስለዚህ ሙሴያዊው ኪዳንና ዐዲሱ ኪዳን ይሚሉ ዘንድ ጐን ለጐን መሄዳቸው አለመገጣጠም አይደለም። ይሁን እንጂ ሕዝቅኤል ይህን ሁኔታ የተመለከተው ስለ ሙሴያዊው ኪዳን ካለው መረዳት አንጻር ነው።

ስድስት ቀን ሙሉ ሥራ ተሠርቶ በሰንበት እስራኤላውያን እንደሚያርፉ፣ የውስጠኛው አደባባይ ምሥራቃዊ በር ስድስት ቀን ይዘጋል፤ በሰባተኛውም ቀን ለአምልኮ ይከፈታል። በሰንበት ገዢው እንደ ገና ሕዝቡን በአምልኮ ይመራል። በውስጠኛው አደባባይ ምሥራቃዊ በር ይገባል፤ በበሩ መቃን አጠገብ ይቆማል፤ በሕዝቡ ባልተያዘው ስፍራም ሆኖ ደስ ይሰኛል። የቆመበት ስፍራ በትክክል ባይታወቅም፣ መሥዋዕቱ የሚታረድበት ጠረጴዛ በመግቢያ መተላለፊያ በረንዳ ላይ በመሆኑ በበረንዳው መተላለፊያ ላይ ያለው ደፍ ሳይሆን አይቀርም። ገዢው ወደ ውስጠኛው አደባባይ መግባት ስለማይችል ካህናት እንዲሠዉለት ከዚህ ላይ የራሱን

የሚቃጠል መሥዋዕትና የኅብረት መሥዋዕት ይዞ ይቀርባል (ከዘኍ 29፥38 ጋር ያነጻ)። የሚያቀርበው የሚቃጠል መሥዋዕት ስድስት የበግ ጠቦትና አንድ አውራ በግ ሲሆን፣ ሁሉም እንከን የሌላቸው ናቸው። እያንዳንዱም የሚቀርበው ከእህል ቍርባን ጋር ሲሆን፣ ከአውራ በጉ ጋር የሚቀርበው የእህል ቍርባን አንድ የኢፍ መስፈሪያ ነው፤ ከበግ ጠቦቶቹ ጋር የሚቀርበው ግን የሚቻለውን ያህል ነው። አንድ የኢን መስፈሪያ ዘይት ከእያንዳንዱ ኢፍ መስፈሪያ እህል ጋር ይደበለቃል (ከዘኍ 28፥9-10 ጋር ያነጻ)። የኅብረቱ ወይም የምስጋና መሥዋዕቱ ቅንብር እዚህ ላይ ለምን እንደ ሆነ አይታወቅም፤ አቅራቢው ሰው የወደደውን ይዞ ስለሚመጣ አብዛኛውን ጊዜ በነጻ ፈቃድ የሚፈጸም ነው። ገዢው በበሩ ውስጠኛው ደፍ ላይ ሆኖ ያመልካል፤ ልክ እንደ ገባም በዚያው ይመለሳል። ወደ ውስጠኛው አደባባይ ፈጽሞ አይገባም። ሕዝቡ በእግዚአብሔር ፊት በምሥራቁ በር እየሰገዱ ገዢው በበሩ ውስጥ ሆኖ እነዚህን መሥዋዕቶች በማቅረብ ይሰግዳል።

በወር መባቻ ላይ የሚደረገው የአምልኮ ሂደት ልክ በሰንበት ላይ እንደሚደረገው ነው፤ ይሁን እንጂ በሰንበት ላይ ከሚቀርቡ እንስሳት በተጨማሪ ወይፈን የሚቃጠል መሥዋዕት ሆኖ ይቀርባል (ከዘኍ 28፥11-15 ጋር ያነጻ)።

9-12 እስራኤላውያን በተወሰኑት በዓላት ለማምለክ ሲመጡ (ከዘሌ 23፥37 ጋር ያነጻ)፣ ገዢው ከሕዝቡ ጋር ይተባበራል፤ ሲያመልኩ ዐብሮ ያመልካል፤ አብቅተው ሲሄዱም ዐብሮአቸው ይሄዳል። ሕዝቡ ለማምለክ በሰሜን ወይም በደቡብ በር ይገባሉ። በገቡበት በር እንዲወጡ አይፈቀድላቸውም፤ ነገር ግን ከገቡበት በር በተቃራኒ ባለው በር ይወጣሉ። በአንድ በር በመግባትና ተቃራኒ በሆነው በር በመውጣት ለበዓል የሚመጣው ሕዝብ ፍሰት በሚገባ እንዲስተናገድና መጨናነቅ እንዳይኖር ያደርጋል። እነዚህ በሮች የቤተ መቅደሱ ውስጣዊ በር ይሁኑ ወይም ውጫዊ በር ፈጽሞ አይታወቅም፤ ሕዝቡ ወደ ውጫዊው የቤተ መቅደሱ አደባባይ መግባታቸው የተለመደ በመሆኑ ግን የውስጠኛው አደባባይ በሮች ሳይሆኑ የማይቀሩ ይመስላል። ይህ ከሆነ ካህናት ብቻ ወደ ውስጠኛው አደባባይ ከሚገቡበት ሌሎች ሊገቡበት የቻሉበት የመጀመሪያ ክሥተት ነው። ይሁን እንጂ በሐሳብ ያሉት ውጫዊ በሮች ከሆኑ፣ ምናልባትም ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ በአንድ በር የመግባትና ከእርሱም በተቃራኒ በሆነው በር የመውጣት ሥርዐት ለእነዚህ ቀናት ብቻ ተገቢ ሆኖአል።

በእነዚህ በተወሰኑት በዓላትና ፈንጠዝያዎች የሚቀርቡት መሥዋዕቶች እያንዳንዱ በዓል በሚውሠበት ጊዜ በተለይ ሊገለጹ ወይም ላይገለጹ ይችላሉ። እንደ ገና በጥብቅ የተገለጸው እያንዳንዱ ወይፈን ወይም አውራ በግ በሚቀርብበት ጊዜ አንድ የኢፍ መስፈሪያ እህል ዐብሮ እንዲቀርብ፣ እንዲሁም ከበግ ጠቦት ጋር ሰውየው የወደደውን እህል እንዲያቀርብ ነው (ከቍ 7 ጋር ያነጻ)። ገዡ በፈቃዱ ራሱን ለመቀደስ የሚቃጠል መሥዋዕት ማቅረብ ቢፈልግ ወይም የምስጋና የኅብረት መሥዋዕት ማቅረብ ቢፈልግ፣ ለዚህ የተለየ አምልኮ የምሥራቅ በር መከፈት ይኖበታል፤ ሲጨርስም ይዘጋል። ያ በር በዘወትሩ ሰድስት ቀናት ሙሉ መዘጋቱ ይህ ብቸኛ ሁኔታ ነው። ገዢው በሰንበት መሥዋዕቱን በሚያቀርብበት መንገድ በፈቃዱ ለሚያቀርበው መሥዋዕትም እንዲሁ ያደርጋል።

13-15 ስለዚህ መሥዋዕት የሚቀርብባቸው ሦስት ሁኔታዎች አሉ፤ እነርሱም የዋና ዋና በዓላት፣ ካህኑ በፈቃዱ የሚያቀርብባቸውና የየዕለቱ መሥዋዕቶች ናቸው። በየዕለቱ በሚቀርቡት መሥዋዕቶች ላይ ገዢው ሕዝቡን ይመራል። በየማለዳው እንከን የሌለበትን የአንድ ዓመት ጠቦት የሚቃጠል መሥዋዕት ከአንድ ስድስተኛ የኢፍ መስፈሪያ ዱቄትና መለወሻ ከሚሆነው የኢን መስፈሪያ ዘይት ጋር ያቀርበዋል፤ በሙሴያዊው ሥርዐት መሠረት በየዕለቱ የሚቀርበው የሚቃጠል መሥዋዕት የሚደረገው በየማለዳውና በየምሽቱ ይሆናል። ምክንያቱ ባይገለጽም በዚህ ስፍራ የሚቀርበው በየማለዳው ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ለአምላኩ ታማኝነቱን የሚገልጥበት ይህ በየዕለቱ የሚቀርበው የሚቃጠል መሥዋዕት፣ በየዕለቱ መቅረብ ላለበት አምልኮ መታሰቢያ ነው።

16-18 የርስት ነገር ለእስራኤላውያን ትልቅ ጉዳይ ነበር። ማንኛውም እስራኤራዊ የቤተ ሰብን ርስት እንዲወርስ ዋስትና የሚያስገኙለት አያሌ ሕጎች ተመሥረተው ነበር። ይህ አስተሳሰብ ቢያንስ ቢያንስ ገዢውን በተመለከተ በመሲሓዊው መንግሥትም ይቀጥላል። ከልጆቹ ለአንዱ የተሰጠውን ርስት የዚያው ልጅ ዘሮች ይወርሱታል (ገዢው ልጆች እንዳሉት መጠቀሱ መሲሑን በተመለከተ ለሚነሣው ክርክር ማቀትም ይህ ገዥር መሲሑ እዳልሆነ እልባት ይሰጣል)። ለባሪያው የተሰጠ ማንኛውም ንብረት በኢዮቤልዩ ዓመት ለገዢው ይመለሳል ("የነጻነት ዓመት") ከዘሌ 25፥10፤ 27፥24 ጋር ያነጻ)። የቀደሙት የእስራኤል መሪዎች ብዙ ጊዜ እንዳደረጉ ገዢው የሌላውን ሰው ንብረት ወርሶ የራሱ ማድረግ እንደማይገባው ሕዝቅኤል አጥብቆ ይናገራል (ከ34፥3-4፤ ከ1ነገ 21፥19፤ ከሚክ 2፥1-2 ጋር ያነጻ)። ማንም ሰው ከንብረቱ ከቶ መለየት አልበረበትም።

7. የካህናቱ የተቀደሱ ክፍሎች (46፥19-24)

19-24 ሕዝቅኤል ከውስጠኛው አደባባይ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ወዳለው ወደ ውጫዊው አደባባይ እንዲመጣ ተደረገ፤ ከዚያም ወደ ሕንጻው መግቢያና (በሥዕላዊ ማስረጃ 2 ከክ 2 ይመ) ካህናቱ የተቀደሱ መሥዋዕቶችን ወደሚበሉበትና ልብሳቸውን ወደሚቀይሩባቸው ክፍሎች ወዳሰበት ተወሰደ (ከ42፥13-14 ጋር ያነጻ)። በዚህ ሕንጻ ያሉት ክፍሎች ከሰሜን ትይዩ ናቸው። በዚህ መለኮታዊው መልእክተኛ ከእነዚህ ከተቀደሱ ክፍሎች በስተ መጨረሻ ካህናቱ የበደል መሥዋዕትንና የኀጢአት መሥዋዕትን የሚቀቅሉባቸውን ስፍራዎች ለሕዝቅኤል አሳየው። በዚሁ የእህሉን ቍርባን ይጋግራሉ፤ ደግሞም መሥዋዕቶቹን ሁሉ ይበላሉ። በዚህ መንገድ ካህናቱ እነዚህ መሥዋዕቶች ለመቀቀል ወደ ውጫዊው አደባባይ በማምጣት ሕዝቡን የሚቀድሱበት መንገድ አይኖርም (ከ44፥19 ጋር ያነጻ)። እያንዳንዱ በራሱ አደባባይ የሚሆን በውጫዊው አደባባይ አራት ማእዘኖች አራት የተቀደሱ ስፍራዎች አሉ (ሥዕል 2 ይመ)። እነዚህ የተቀደሱ ስፍራዎች የእያንዳንዳቸው ስፋት አርባ በሠላሳ ክንድ ነው። በእያንዳንዱ ክፍል ዙሪያውን የድንጋይ ዕርከን ሲኖር ከሥሩ ምድጃ ተተክሎበታል። እነዚህ ምቹ የሆኑ የማብሰያ ስፍራዎች ካህናት (ምናልባትም ሌዋውያን፣ ከ44፥10-14 ጋር ያነጻ) የሕዝቡን መሥዋዕታዊ መብል የሚያዘጋጁባቸው ናቸው።

መ. የሺሁ ዘመን የመሬት አቀማመጥ ገጽታዎች (47፥1-48፥35)

ይህንን ትንቢታዊ መጽሐፍ ለማጠቃለል፣ በሺሁ ዘመን መንግሥት የእስራኤል ምድር ምን እንደሚመስል ማውሣት ተገቢ ነው። በአብርሃማዊው ኪዳን እግዚአብሔር የከነዓንን ምድር ለአብርሃምና ለዘሩ ርስት አድርጎ እንደሚሰጥ ቃል ገብቶአል (ዘፍ 12፥7)። ያንን ምድር ርስት አድርጎ የመያዝ ጉዳይ በኢያሱ ድል አድራጊነት ተጠናቋል። በመሴያዊው ኪዳን መሠረት እስራኤል የአብርሃማዊውን የኪዳን በረከት መውረስ የምትችለው የሙሴያዊውን ኪዳን ትእዛዞች ስትፈጽም መሆኑን እግዚአብሔር ቃል ገብቶአል (ዘዳ 7፥12፤ 8፥2)። ከእነዚያ በረከቶች አንዱ የከነዓን ምድር ነው። ይሁን እንጂ እስራኤል በታሪክዋ ባለማቋረጥ የሙሴያዊውን ኪዳን ትእዛዝ ስታፈርስ ኖረች፤ ስሆነም ሕዝብዋ ከተስፋዱቱ ምድር እንዲወጣ ተደርጎ በአሕዛብ መካከል በተለይም በባቢሎን ተበተነ። ሕዝቅኤል እግዚአብሔር ወደፊት እስራኤልን በተስፋዱቱ ምድር መልሶ እንደሚያቋቁማትና እንደሚያነጻት እንዲሁም ዐዲስ ልብ እንደሚሰጣትና በምድሪቱም በድነት ታላቅ ደስታን እንደሚያጐናጽፋት ትንቢት ተናገረ (36፥24-40)። ከእንግዲህ እስራኤል ምድርዋን ከቶ አትነጠቅም (ምዕ 39)።

ስለዚህ ትክክለኛው የመጽሐፉ ማጠቃለያ በሺሁ ዘመን መንግሥት የእስራኤል ምድር ባሕርይ ምን እንደሚመስል ምናልባትም የዘላለምን መንግሥት ገጽታ በጨረፍታ የሚያሳየውን ትንቢት ሕዝቅኤል በዝርዝር ሲገልጽ ነው። መለኮታዊው መልእክተኛ ምድሪቱን የሚፈውሰውን ወንዝ ለሕዝቅኤል ያሳየዋል። ከዚያም በሺሁ ዘመን መንግሥት የእስራኤልን ምድር ወሰኖችና የየነገዱን ድርሻ በዝርዝር ይገልጻል።

1. የቤተ መቅደሱ ወንዝ (47፥1-12)

1-12 ሕዝቅኤል በራእዩ ከቤተ መቅደሱ መግቢያ መድረክ ሥር በስተ ደቡብ በኩል ውሃ ወደ ምሥራቅ ሲፈስ ወዳየበት

ወደ ቤተ መቅደሱ መግቢያ እንዲመጣ ተደርጎ ነበር (41፥2)። ውሃው ከመሥዋዕቱ መሠዊያ በደቡብ በኩል በውስጠኛው አደባባይ፣ በውጫዊው አደባባይ በኩል እንዲሁም ከቤተ መቅደሱ ሕንጻ ወጥቶ በምሥራቃዊው ውጫዊ በር ጐን በደቡብ በኩል ያልፍ ነበር። መለኮታዊው መልእክተኛ የውሃው መጠን ምን ያህል እንደ ሆነ ለመግለጽ ሕዝቅኤልን ይመራው ጀመር። መልእክተኛውም የመለኪያ ገመዱን ይዞ አራት ባለ አንድ ሺህ ክንድ የሚለኩ ምልክቶችን (በግምት አንድ ሦስተኛ ማይል) ይዞ ተነሣ። በእያንዳንዱ አንድ ሺህ ክንድ መልእክተኛው ሕዝቅኤልን ይዞ ወደ ወንዙ በመግባት ጥልቀቱን መለካት ጀመረ። እየሄዱ በቀጠሉ ቍጥር ጥልቀቱ ጨመረ፤ ከቁርጭምጭሚት እስከ ጕልበት፤ ከጕልበት እስከ ወገብ በመጨረሻም አራት ሺህ ክንድ ድረስ በመድረስ ሊሻገሩት የማይቻል ሆነ። ይህ ወንዝ ወደ ደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫ ወደ ዓረባ፣ ከዚያም ወደ ባድማው የዮርዳኖስ ሸለቆ እስከ ደቡብ ወደ ቀይ ባሕር (የዛሬው አካባ ባሕረ ሰላጤ) ፈሰሰ። ወንዙም ወደ ሙት ባሕር ፈሰሶ፣ ባሕሩን ሕያው አደረገው።

የዚህ መለኮታዊ ወንዝ ዋና ዐላማ ሕይወትን ማምጣት ነው። በወንዙ ግራና ቀኝ ብዙ ዛፎች ተተክለዋል። የፍሬ ዛፎች ሁሉ ግራና ቀኝ አድገዋል። ቅጠላቸው አይደርቅም፤ ፍሬያቸውም ከዓመት እስከ ዓመት የሚኖር ነው፤ ይህ መለኮታዊ ወንዝ ስለሚፈስስላቸውም በዓመት ውስጥ ባለው በየወሩ ያፈራሉ። ፍሬያቸው ለምግብ፣ ቅጠላቸውም ለመድኃኒት ይሆናል። መላው ሙት ባሕርና ዓረባ በእነዚህ ውሆች ስለሚፈወሱ፣ ሙት ባሕር በብዙ ሕያዋን የባሕር ውስጥ ፍጡራን ይሞላል፤ ዓሣ አጥማጆችም በወንዙ ዳር ቆመው ከዓይንጋዲ እስከ ዓይን ኤግለይም ልዩ ልዩ ታላላቅ ዓሣዎችን ያጠምዳሉ። ዓረባ ለመለመ (ኢሳ 35፥1-2፡ 6-7፤ ኢዩኤል 3፥18 ጋር ያነጻ)። ረግረጉና ዕቂሪው ውሃ ብቻ ሳይፈውሱ ቀሩ፤ እነርሱም የቀሩት ለሕዝቡ ጨው ለመስጠት ነው። በየትኛውም ሁኔታ ወንዙ ሕይወት ሰጪ ኀይሉን አምጥቶአል።

ይህ ወንዝ በዔድን የአትክልት ስፍራና በዘላለም መንግሥት ካሉት ወንዞች ጋር ተመሳሳይ ነው። በዘፍ 2፥8-10 በዚያ ፍጹም በሆነ ስፍራ እግዚአብሔር ለምድሪቱ ሕይወትን የሚሰጥ ወንዝ ሰጠ። ያ ሕይወት ሰጪ ወንዝ በሰው ልጅ ውድቀት ደረቀ። በሕዝቅኤልና በዮሐንስ ራእይ መጻሕፍት የምድሪቱ መቤዠት ሙሉ በሙሉ እውን ይሆናል (ኮሎሜ 8፥19-22 ጋር ያነጻ)። እንደ ገና እነዚህ ሕይወት ሰጪ ውሆች ከእግዚአብሔር መኖሪያ ከቤተ መቅደሱ ይፈሳሉ፤ ምድሪቱንም ይፈውሳሉ።

በራእይ 22፥1-2 (ከዘካ 14፥8 ጋር ያነጻ) የተገለጸው ወንዝ በሕዝቅኤል 47 ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይ ነው። ራእይ 22፥2 የሕይወትን ዛፍ በወንዙ ግራና ቀኝ እንዳለ ቢገልጽም፣ በዚያ ዐውድ ዛፍ የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው አጠቃላይ ዕሳቤን ተከትሎ ይመስላል። ዛፎቹን በተመለከተም በሕዝቅኤል መጽሐፍ የተለየ ነገር አልተቀመጠም፤ ማብራሪያ ብቻ ነው የተሰጠው። የሕይወት ዛፍ በዔድን የአትክልት ስፍራ በወንዙ ዳር እንደ ነበረ ሁሉ፣ በሺህ ዘመን መንግሥት ባይሆንም በዘላለማዊው መንግሥት በሕይወት ሰጪው በዚህ ወንዝ ዳር የሕይወት ዛፍ ትተረፍርፎ ይገኛል። ስለዚህ ወንዝ ሕዝቅኤል በጻፈውና ዮሐንስ በራእይ በጻፈው ያለው ለውጥ በወንዙ መነሻ ላይ ማእከል ያደረገ ነው። የሁለቱም ወንዞች መነሻ ምንጭ እግዚአብሔር ነው፤ ነገር ግን ሕዝቅኤል ወንዙ ከቤተ መቅደሱ ሲፈስ ሲያይ፣ ዮሐንስ ወንዙ ከእግዚአብሔር ዙፋንና ከበጉ (ቤተ መቅደስ አልነበረም፤ ከራእይ 21፥22 ጋር ያነጻ) ሲፈስ አየ። በራእይ 22፥2 ላይ ወንዙ እንደ ሕዝቅኤል ትረካ የሚቻል ሆኖ ሳለ ከዚህ ላይ፣ አስቸጋሪ ቢመስልም በከተማዪቱ መንገድ ላይ ወደ ታች ፈሷል። የሕዝቅኤልና የዮሐንስ ራእዮች የሚናገሩት ስለ አንድ ተመሳሳይ ወንዝ (በሺህ ዘመን መንግሥትና በዘላለም መንግሥት) ወይም ስለ ሁለት የተለያዩ ወንዞች (አንዱ በሺህ ዘመን መንግሥትና ሌላው በዘላለም መንግሥት) ሆነም አልሆነም ሁለቱም በዐላማ ተመሳሳይ ናቸው። የምድሪቱ መቤዠትና ፈውስ ምንጭ የመጣው ከእግዚአብሔርና ከዙፋኑ ነው። እርሱ ምድሪቱን በሺህ ዘመን መንግሥትና በዘላለሙ መንግሥት ይፈውሳል። ከዚህም በላይ የሺህ ዘመን መንግሥት የዘላለም መንግሥት መግቢያ መንገድ ነው።

2. የምድሪቱ አከፋፈል (47፥13-48፥35)

13-14 ሕዝቅኤል በመጀመሪያ ምድሪቱ በእንዴት ዐይነት መንገድ እንደምትከፋፈል አቀረበ። ለዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች እኩል ተደርጋ ትከፋፈላለች። ለዮሴፍ በነገድ አከፋፈል መሠረት ለሁለቱ ልጆቹ ለምናሴና ለኤፍሬም ሁለት ዕጣ ይኖረዋል (ከዘፍ 48፥5-6፡ 22 ጋር ያነጻ)። የዮሴፍ ነገድ ሌዊን ለመተካት በሁለት ነገድ ተከፍሎ ነበር። ስለዚህ እኩል እኩል የተከፋፈሉ ዐሥራ ሁለት የየነገዱ የመሬት ዕጣዎች ነበሩ። የሌዊ ነገድ የካህናት ነገድ ሆነዋል፤ በሺሁ ዘመን መንግሥትም ለመኖሪያ የተለየ መሬት ይሰጣቸዋል (ከ45፥1-8፤ 48፥8-14 ጋር ያነጻ)። የእኩልነት መርሕ ይገለጣል። እኩልነትን በተመለከተ የተፈጸመ ያለፈ በደል ይስተካከላል።

ይህንን የተስፋውን ምድር በየነገዱ እስራኤላውያን ሲከፋፈሉ፣ የተደረገው እርሱ በገባው የተስፋ ቃል መሆኑን እግዚአብሔር እስራኤልን ያሳስባል። ማናቸውም ይህን ዕጣ ለማግኘት የሚገባቸው አልነበሩም። ይህን ምድር ርስት አድርገው ሊወርሱ የቻሉት እግዚአብሔር ለአብርሃም በገባው ኪዳን መሠረት ነው (ከዘፍ 12፥7፤ 15፥7፡ 18-21፤ 17፥8 ጋር ያነጻ)።

15-20 በሺሁ ዘመን መንግሥት ያለው የእስራኤል ብሔራዊ ወሰን ከጥንታዊቷ እስራኤል ወሰን ጋር ተመሳሳይ ነው (ከዘኁ 34፥3-12 ጋር ያነጻ)። የወሰኖቹ ስም የተወሰደው በሕዝቅኤል ዘመን ከታወቁት ሲሆን፣ በዝርዝር ስለ ተሰጡ፣ ያለ ጥያቄ ቃል በቃል ይወሰዳሉ።

የወሰን አከፋፈሉ ከሰሜን ይጀምርና እያንዳንዱም ጐን ቀኙን አቅጣጫ ይዞ ተገልጸአል። የሰሜን አዋሳኝ ካልታወቀ ስፍራ ከታላቁ (ሜድትራኒያን) ባሕር ይጀምራል፤ የቀረው ዝርዝር መግለጫ የሚያመለክተው ግን በዛሬዪቱ ሊታኒ ወንዝ መፍሰሻ አፍ ዙሪያ መሆኑን ያመለክታል። ይህ ወሰን በደቡብ ደማስቆና በሰሜን ሐማት መካከል በሃዘር አናን በኩል ምሥራቃዊ አቅጣጫን ተከትሎአል። የቤሮታን፣ የሲብራይምና የሐድርሃ ቲኮን ቦታዎች አልተመለከቱም። ሐማትና ጽዳድ (ማናልባት የዛሬዪቱ በሆምስ ደቡብ ምሥራቅ ያለችው ሳዳድ) እንዲሁም የሐውራን አካባቢ ለጊዜውም ቢሆን የምንነት መለያ ተቀብለዋል።

የምድሪቱ ምሥራቃዊ ወሰን በሐውራንና በደማስቆ መሬዳዎች መካከል ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሲሆን ከምሥራቁ ባሕር (ሙት ባሕር) ወደ ደቡብ ያለውን መሥመር የተከተለ ነው። የደቡብ ወሰን ከታማር (የሙት ባሕር ደቡብ ምዕራብ) ተነሥቶ በቃዴሶ በርኔ በኩል በግብፅ ወዳለው ደረቅ ወንዝ (የዛሬው ኤል አሪሽ ደረቅ ወንዝ) አድርጎ ወደ ታላቁ (ሜድትራኒያን) ባሕር ይዘልቃል። የምዕራቡ ወሰን ታላቁ ባሕር ነው። በንጽጽር በዘላለም መንግሥት የእግዚአብሔር ሕዝብ መሬት ምንም ባሕር አይኖረውም፤ ባሕር የሚባል ነገር አይኖምና (ራእ 21፥1)። የብሉይ ኪዳን የእስራኤል ወሰን ከዮርዳኖስ ማዶ ለሁለት ተኩል ነገዶች የተሰጠ ነው።

21-23 በእስራኤል መካከል የሚኖሩትን መጻተኞች በተመለከተ እነርሱም ርስት እንዲመደብላቸው ተጨማሪ መመሪያ ተሰጥቶአል። በእስራኤል በአንድ በተወሰነ ነገድ መካከል ይኖሩ የነበሩ ልጆች ያሏቸው (ቋሚነታቸውን ያመለክታል) መጻተኞች፣ መሬት በሚከፋፈልበት ጊዜ በዚያ ባሉበት ነገድ ይቈጠራሉ። እነዚህ መጻተኞች ልክ እንደ እስራኤል ተወላጆች መያዝ ነበረባቸው። ይህን በማድረግ እስራኤል የሙሴን ኪዳን ይታዘዛሉ (ከዘሌ 19፥34 ጋር ያነጻ)።

48፥1-7 በ47፥14 መሠረት የእያንዳንዱ ነገድ ርስት እኩል መሆን ይኖበታል። እያንዳንዱ ከሰሜን ወደ ደቡብ የሚዘልቅ ትይዩ ወሰን ይኖረዋል፤ ይህም የምዕራብ ወሰን ወደ ምሥራቅ ወሰን ተዘርግቶ አንዱ በሌላው አጠገብ ሆኖ እኩል መጠን ይኖረዋል። ድልድሉ ሁሉ ከሰሜን ጀምሮ ወደ ደቡብ እየሰፋ በመሄድ ለነገዶቹ ተዘርዝሮ ነበር። ይህ ሥርዐት በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ከሌላ የሚገናኝበት የለም። ከያዕቆብ ሚስቶች ደንገጡሮች የተወለዱት ነገዶች ዙሪያውን ሲሰፍሩ፣ ከራሔልና ከልያ የተወለዱት ነገዶች ግን በምድሪቱ መካከል ላይ እንዲሰፍሩ ተደርገዋል (ከዘፍ 35፥23-26 ጋር ያነጻ)። የደቡቡ መንግሥት ታማኝ ነገዶች ማለትም ይሁዳና ብንያም የተለየ

ስፍራ ተሰጥቶአቸዋል፤ ይኸውም በምድሪቱ የተለየ የተቀደሰ ስፍራ አጠገብ ነው።

8-14 የምድሪቱ ድርሻ 25,000 ዘንግ ወርድ አለው (የ42፥15-20፤ 45፥1-8 ማብራሪያ ይመልከቱ)፤ ይህም ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከተዘረጋ የነገዶች ድልድል ርዝመት ጋር እኩል ሲሆን፣ ለእግዚአብሔር ከሕዝቡ በተለይ የተሰጠ ነው (ከ45፥1-8 ጋር ያነጻ)። ይህ የተለየ ድርሻ አራት የተለያዩ ክፍሎችን የያዘ ነው፤ እነዚህም ለካህናቱ ለሳዶቅ ልጆች የተሰጠው የተቀደሰ ስፍራ (ቊ. 9-12)፣ የሌዋውያን መሬት (ቊ. 13-14)፣ የከተማዪቱ መሬትና (ቊ. 15-20) የገዢው መሬት ናቸው (ቊ. 21-22)።

ለእግዚአብሔር የተሰጠው የተለየ ድርሻ ማለትም ለካህናቱ ለሳዶቅ ልጆች የተሰጠው የተቀደሰ ስፍራ ከሰሜን እስከ ደቡብ 25,000 ዘንግ ርዝመት ሲኖረው፣ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ጐን 10000 ዘንግ ርዝመት ነበረው። በዚህ መሬት ላይ የእግዚአብሔር ማደሪያ በመካከል ይሆናል (ከ45፥4ሐ ጋር ያነጻ)።

ለካህናቱ ለሳደቅ ልጆች ከተሰጠው ድርሻ በስተ ሰሜን የሌዋውያን ምድር አለ። የዚህ ምድር መጠን ከላይ ከተጠቀሰው ከሳደቅ ልጆች ድርሻ መጠን ጋር ተመሳሳይ ነው። ይህ ምድር የእርሱ ስለ ሆነ ሌዋውያኑ ይህንኑ ምድር እንዳይሸጥ ወይም እንዳይለወጥ ወይም በምንም መንገድ ወደ ሌላ ሰው እጅ እንዳይተላለፍ ርግጠኛ ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔር በብርቱ ያስጠነቅቃቸዋል። ለእርሱ የተቀደሰ ነውና።

15-20 ለከተማዪቱ የተለየው ድርሻ ርዝመት 25,000 ዘንግ በስተ ሰሜን ሲሆን፣ 5,000 ዘንግ በምሥራቅና በምዕራብ ጐን ይሆናል። ይህ መሬት ጥቅም ላይ የሚውለው ለከተማ፣ ለመኖሪያ ቤትና ለክብት ማደሪያ ነው። ከተማዪቱ በዚህ ድርሻ ውስጥ በመካከል ትሆናለች። እርስዋም 4,500 ዘንግ እኩል በእኩል አራት ማእዘን ስትሆን፣ 250 ዘንግ የሚያህል ትንሽ መሬት ዙሪያውን በየጐኑ ይሆናል። ይህ ትንሽ መሬት ለከተማዪቱ ክብት ማደሪያ ይውላል። የከተማዪቱ አጠቃላይ ስፋት ወሰኖቿን ጨምሮ 5,000 ዘንግ ያህል ይሆናል (ከቊ. 15፤ 45፥6 ጋር ያነጻ)። በከተማዪቱ ግራና ቀኝ ያለው የቀረው ምድር በከተማዪቱ ያሉት ሠራተኞች ለምግባቸው የሚያመርቱበት ስፍራ ይሆናል። እነዚህ ሁለት እኩል በእኩል የሆኑ መሬቶች ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ 5,000 ዘንግ ርዝመት ሲኖራቸው፣ ከሰሜን ወደ ደቡብ ደግሞ 10,000 ዘንግ ርዝመት ይኖራቸዋል። በዚህ ከተማ የሚኖሩ ከየትኛውም ነገድ የመጡ ሠራተኞች በዚህ ምድር ያርሳሉ።

ምድሩ በአጠቃላይ የሌዋውያን ምድር፣ የሳዶቃውያንን ምድር፣ እንዲሁም የከተማዪቱን ምድር ጨምሮ በአንድ ላይ 25,000 ዘንግ እኩል በእኩል ይሆናል።

21-22 ከዚህ ከ25,000 ዘንግ እኩል በእኩል የተቀደሰ ምድር ግራና ቀኝ ያለው ስፍራ ለገዢው ይሰጣል (ከ45፥7-46፥18 ጋር ያነጻ)። የእርሱ የምድር ስፋት ከተቀደሰው ድርሻ ምሥራቅና ምዕራብ እስከ ብሔራዊው ወሰን ይዘረጋል፤ ይኸውም የየነገዶች ምድር ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ እንደ ተዘረጋው ነው። የሌዋውያንና የካህናት ርስት፣ ለከተማዪቱ ከተለየው ምድር ጋር በገዢው ምድር መካከል ላይ የተቀመጠ ነው። የተቀደሰው ምድርና የገዢው ምድር ለይሁዳ ነገድ በስተ ሰሜን በተሰጠውና ለብንያም ነገድ በስተ ደቡብ በተሰጠው ምድር መካከል ይገኛል።

23-29 በእስራኤል ምድር ለየነገዱ የተከፋፈሉት ድርሻዎች በተለይም ከምድሪቱ የተለየ ድርሻ በስተ ደቡብ ያሉት በእነዚህ ቊጥሮች ላይ ተገልጸዋል።

30-35 ከካህናቱ የተቀደሰ ስፍራ በስተ ደቡብ ያለችው 10,000 በ5,000 ዘንግ የተለየችው በማእከል የተቀመጠችው ከተማ ስም አልተጠቀሰም፤ ይሁን እንጂ ከተማዪቱ ኢየሩሳሌም ሳትሆን አትቀርም (ከዘካ 14፥8 ጋር ያነጻ)። በቊ. 15-19 የተሰጡትን መለኪያዎች በመጠበቅ ሕዝቅኤል በከተማዪቱ ዙሪያ ያለውን ርቀት የከበቡቹን ማደሪያ ስፍራ በመቀነስ 18,000 ዘንግ እንደ ሆነ ይናገራል። በዚህ ክፍል ውስጥ ዋና ትኩረት የተደረገባቸው በእያንዳንዱ የእስራኤል ነገድ ስም የተጠሩት ዐሥራ ሁለቱ በሮች ናቸው (ከራእ 21፥12-13 ጋር ያነጻ)። በእያንዳንዱ የከተማዪቱ ጐን ሦስት በሮች ነበሩ። የልያ ልጆች በሰሜንና በደቡብ ጐን እንዲሰፍሩ ተደርገዋል። በስተ ሰሜን ሦስቱ በሮች የተሰየሙት በሮቤል (በኩር)፣ በይሁዳና (የዳዊት ነገድ) በሌዊ (የካህናት ነገድ) ስም ነው። በስተ ደቡብ ሦስቱ በሮች የተሰየሙት በስምዖን፣ በይሳኮርና በዛብሎን ስም ነው። በስተ ምሥራቅ ያሉት ሦስት በሮች በራሔል ልጆች በዮሴፍና በብንያም እንዲሁም የራሔል ደንገጡር በሆነችው በባላ ልጅ በዳን ስም ተሰይመዋል። በስተ ምዕራብ ያሉት ሦስት በሮች በሁለቱ የቤት ሠራተኞች በዘለፋና በባላ ልጆች በጋድ፣ በአሴርና በንፍታሌም ስም ተሰይመዋል።

ከተማዪቱ አራት ማእዘን ናት፤ በራእይ ያለችውም ከተማ አራት ማእዘን ናት (በርግጥ ባለ ስድስት ጐን ናት፤ ከራእ 21፥16 ጋር ያነጻ)። እነዚህ ተመሳሳይነቶች በሁለቱም መካከል አንድነት እንዳለ ሌሎች እንዲገምቱ አድርጎአል። ነገር ግን በራእይ መጽሐፍ የምናገኘው ተጨማሪ መረጃ ፈጣን ውሳኔ ከመስጠት መዘግየት እንደሚገባ ያመለክታል። ሁለቱ ተመሳሳይ ካልሆኑ የሺሁ ዘመን መንግሥትና የዘላለም መንግሥት ባሕርይ ተመሳሳይ መሆኑን ይገልጣሉ።

ሕዝቅኤል ይህን ታላቅ ትንቢት የሚያጠቃልለው ለከተማዪቱ ስም በመስጠት ነው፤ ከተማዪቱ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ወደ ፊት የሚኖራት ስም "እግዚአብሔር በዚያ አለ" የሚል ይሆናል። እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ለዘላለም ዐብሮ ይኖራል። ከእንግዲህም በኋላ በቅጣት ከእነርሱ ፈጽሞ አይለይም። ለዘላለም እስራኤል የእግዚአብሔር ሕዝብ በመሆን ትኖራለች፤ እርሱም ለዘላለም የእርሷ አምላክ ይሆናል! በዕብራውያን አስተሳሰብ ማንኛውም ዐዲስ ስም ሲሰጥ ለተቀባዩ ዐዲስ ባሕርይን ስለሚሰጥ፣ ይህ ስም የእግዚአብሔርን ከተማ ባሕርይ ይገልጣል።

ብሉይ በዐዲስ ውስጥ

የብሉይ ኪዳን ክፍል	የዐዲስ ኪዳን ክፍል	ርእሰ ጕዳይ
ሕዝ 1፥4-10	ራእ 4፥8-8	አራቱ ሕያዋን ፍጥረታት
ሕዝ 3፥1-3	ራእ 10፥9-10	ጥቅልሉን መጽሐፍ መብላት
ሕዝ 9፥4	ራእ 7፥3	በግንባር ላይ ያለ ምልክት
ሕዝ 14፥21	ራእ 6፥8	አራት አስፈሪ ፍርዶች
ሕዝ 20፥41	2ቆሮ 6፥17	ከዓለም መለየት
ሕዝ 27፥27-32	ራእ 18፥13-19	የኀጢአተኞዪቱ ከተማ መጥፋት

ሕዝ 36፥22	ሮሜ 2፥24	የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መሰደቡ
ሕዝ 37፥27	2ቆሮ 6፥16	እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መኖሩ
ሕዝ 38፥1-39፥16	ራእ 20፥8-9	እግዚአብሔርና ማጎግ
ሕዝ 39፥17-20	ራእ 19፥17-21	ምግብ ለአዕዋፍ
ሕዝ 40፥1-2	ራእ 21፥10	የዐዲሲቷ ኢየሩሳሌም ራእይ
ሕዝ 40፥3	ራእ 11፥1	ቤተ መቅደሱን መለካት
ሕዝ 43፥2	ራእ 1፥15	የብዙ ውሆች ድበፅ
ሕዝ 47፥1:12	ራእ 22፥1-2	የሚፈወሱ ውሆችና የሚያፈሩ ዛፎች
ሕዝ 48፥30-35	ራእ 21፥12-13	የከተማዪቱ ዐሥራ ሁለት በሮች